# የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ።

## ማ ው ጫ ፤


ገጽ ፡

መ ቅ ድ ም ። .... .... .... .... .... .... ፩
ቍ ፡ ፩ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን .... .... .... .. ፩
ቍ ፡ ፪ ፡ የጊዜ ፡ ወሰን ፡ .... .... .... .... .. 〃
ቍ ፡ ፫ ፡ ስለ ፡ ቃላት ፡ ትርጓሜ ፡ .... .... .... .. ፪

አንደኛ ፡ መጽሐፍ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ .... ..

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ .... .... ፪
ቍ ፡ ፬ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ በሕግ ፡ ካልተገለጸ ፡ ክስን ፡ ተቀብሎ ፡ ለማከራከር ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ስለመሆኑ ፡ ........ ፬
ቍ ፡ ፭ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ስላገኙ ፡ ጉዳዮች ፡ .... .. ፬
ቍ ፡ ፮ ፡ ዳኝነት ፡ እንዲታይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ .. ፭
ቍ ፡ ፯ ፡ ስለ ፡ ቀደምትነት ፡ .... .... .... .... ፮
ቍ ፡ ፰ ፡ በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኙ ፡ ክሶች ፡ .... .... ፮
ቍ ፡ ፱ ፡ ሥረ ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... .... .... ፯
ቍ ፡ ፲ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... ፰
ቍ ፡ ፲፩ ፡ ክሶችን ፡ ስለ ፡ ማጣመር ፡ .... .... .... ፰

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሥረ ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ስላላቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ .... .... ... ፱
ቍ ፡ ፲፪ ፡ መሠረቱ ፡ .... .. . .... .... .... ፱
ቍ ፡ ፲፫ ፡ ስለ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ .... ፲
ቍ ፡ ፲፬ ፡ ስለ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ .... ፲
ቍ ፡ ፲፭ ፡ ስለ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድን ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ .... ፲
ቍ ፡ ፲፮ ፡ በገንዘብ ፡ መጠን ፡ የተወሰነ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ .... .... .... .... ... ፲፩

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፲፯ ፡ ተጣምረው ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ .... .... ፲፪
ቍ ፡ ፲፰ ፡ በገንዘብ ፡ ግምት ፡ ሊወሰን ፡ ስለማይችል ፡ ሃብት ፲፫

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ በግዛት ፡ ክልል ፡ ስለሚወሰን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ .... .... .... .... .... ..

ቍ ፡ ፲፱ ፡ መሠረቱ ፡ .... .... .... .... ... ፲፫
ቍ ፡ ፳ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ በሚኖር ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... .... .... .... ፲፫
ቍ ፡ ፳፩ ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... ፲፬
ቍ ፡ ፳፪ ፡ በሕግ ፡ በተመሠረቱ ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... .... .... .... ... ፲፬
ቍ ፡ ፳፫ ፡ በውርስ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... ፲፭
ቍ ፡ ፳፬ ፡ በውል ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... ፲፭
ቍ ፡ ፳፭ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... .... .... .... .... ፲፭
ቍ ፡ ፳፮ ፡ በተለያየ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... .... .... .... ፲፮
ቍ ፡ ፳፯ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... .... .... .... .... ... ፲፮
ቍ ፡ ፳፰ ፡ በመክሰር ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... ፲፯
ቍ ፡ ፳፱ ፡ ከአንድ ፡ ስለሚበልጡ ፡ የክስ ፡ ምክንያቶች ፡ .. ፲፯
ቍ ፡ ፴ ፡ ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ክስና ፡ ስለተከሣሽ ፡ ከሳሽ ፡ ክስ ፡ ፲፯
ቍ ፡ ፴፩ ፡ ክስን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ስለማዛወር ፡ .... ፲፰

ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ በከሣሽነት ፡ ወይም ፡ በተከሣሽነት ፡ የሙግት ፡ ተካፋይ ፡ ስለመሆን ፡

ቍ ፡ ፴፪ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ፡ .... .... .... .. ፲፱

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ .... .... .... ....

ቍ ፡ ፴፫ ፡ ከሣሽ ፡ የመሆን ፡ ችሎታ ፡ .... .... .... ፲፱

ገጽ ፡

ቊ ፡ ፴፬ ፤ ስለ ፡ ውክልና ፡ ስለ ፡ እንደራሴነት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሞግዚትነት ፡ .... .... .... .... ፳

ቊ ፡ ፴፭ ፤ ከሣሾች ፡ የኅብረት ፡ ክስ ፡ ስለሚያቀርቡበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... .... .. ፳

ቊ ፡ ፴፮ ፤ ተከሣሾችን ፡ በአንድነት ፡ አጣምሮ ፡ ስለመክሰስ ፡ .... .... .... .... .... ... ፳፩

ቊ ፡ ፴፯ ፤ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙዎች ፡ ተከራካሪዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈረድባቸው ፡ ወይም ፡ ስለሚፈረድላቸው ፡ ፍርድ ፡ .... .... .... .... .. ፳፪

ቊ ፡ ፴፰ ፤ በነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ስለ ፡ መሟገት ፡.... .... .... .... .. ፳፪

ቊ ፡ ፴፱ ፤ በአንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ተደምሮ ፡ መከሰስ ፡ የሚገባውን ፡ ስለመተውና ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ የማያገባውን ፡ ሰው ፡ አጣምሮ ፡ ስለመክሰስ ፡ .... .... ፳፪

ቊ ፡ ፵ ፤ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ስለመጨመር ፡ ወይም ፡ ስለ መተካት ፡ .... .... .... .... .... ፳፫

ቊ ፡ ፵፩ ፤ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ .... ፳፬

ቊ ፡ ፵፪ ፤ ስለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ .... .. ፳፬

ቊ ፡ ፵፫ ፤ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ በክስ ፡ ውስጥ ፡ ስለማግባት ፳፭

ቊ ፡ ፵፬ ፤ የንግድ ፡ ሸሪኮችን ፡ በሚነግዱበት ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ስም ፡ ስለ ፡ መክሰስ ፡ .... .... .. ፳፮

ቊ ፡ ፵፭ ፤ የንግድ ፡ ሸሪኮችን ፡ ስም ፡ ስለመግለጽ ፡ .... ፳፮

ቊ ፡ ፵፮ ፤ በራሱ ፡ ስም ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በሚነግድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ .... .. ፳፮

ቊ ፡ ፵፯ ፤ በንግድ ፡ ሸሪኮች ፡ መካከል ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ፳፯

ምዕራፍ ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ መክሰር ፡ .... .... .... .... .... ፳፰

ቊ ፡ ፵፰ ፤ ስለ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ መሞትና ፡ ስለ ፡ ክሱ ፡ ያለማቋረጥ ፡ .... .... .... .... .. ፳፰

| | ገጽ ፡ |
| --- | --- |
| ቍ ፡ ፶፱ ፤ ከከሣሾቹ ፡ ያንዱ ፡ ወይም ፡ ካንዱ ፡ የበለጡት ፡ መሞት ፡ .... .... .... .... .... | ፳፰ |
| ቍ ፡ ፷ ፤ ከተከሣሾቹ ፡ ያንዱ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ የበለጡት ፡ መሞት ፡ .... .... .... .... .... | ፳፱ |
| ቍ ፡ ፷፩ ፤ ከንግድ ፡ ሽሪኮች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚኖር ፡ የክስ ፡ መብት ፡ .... .... .... | ፳፱ |
| ቍ ፡ ፷፪ ፤ ስለጊቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ .... .. | ፴ |
| ቍ ፡ ፷፫ ፤ ክርክሩ ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ የበለጠ ፡ ብዛት ፡ ያላቸው ፡ ስለመሟገታቸው ፡ .... | ፴ |
| ቍ ፡ ፷፬ ፤ እዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ስለማይችል ፡ ከሣሽ ፡ (ስለ ከሠረ ፡ ከሣሽ) .... .... .... ..... .. | ፴፩ |
| ቍ ፡ ፷፭ ፤ የክስ ፡ መቅረት ፡ ወይም ፡ መሠረዝ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ .... .... .... .... | ፴፩ |
| ቍ ፡ ፷፮ ፤ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ በክርክር ፡ ያለውን ፡ የጥቅም ፡ መብት ፡ ስለማስተላለፍ ፡ ... | ፴፪ |
| ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለወኪሎችና ፡ ስለ ፡ ተሟጋቾች ፡ .... .... | |
| ቍ ፡ ፷፯ ፤ መሠረቱ ፡ .... .... ... .... .... | ፴፪ |
| ቍ ፡ ፷፰ ፤ ስለ ፡ ነገረፈጆችና ፡ ስለ ፡ ወኪሎች ፡ በጠቅላላው ፡ | ፴፫ |
| ቍ ፡ ፷፱ ፤ ለመንግሥት ፡ ነገረፈጅ ፡ ሆነው ፡ እንዲከራከሩ ፡ ስለተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ .... .... .... | ፴፫ |
| ቍ ፡ ፸ ፤ በመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... | ፴፫ |
| ቍ ፡ ፸፩ ፤ ለጦር ፡ ኃይል ፡ አባሎች ፡ ስለሚወከሉ ፡ ነገረፈጆች ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎች ፡ .... .... .. | ፴፬ |
| ቍ ፡ ፸፪ ፤ በእስር ፡ ቤት ፡ ለሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ ነገረፈጅ ፡ ሆነው ፡ ስለሚከራከሩ ፡ ወኪሎች ፡ .... .... .... .... .... .. | ፴፭ |
| ቍ ፡ ፸፫ ፤ ተሟጋች ፡ ስለማቆም ፡ .... .... .... | ፴፭ |

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፺፬ ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ነገረ፡ፈጆች ፡ መጥሪያ ፡ ስለ ሚቀበሉበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .. ፴፮

<u>ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ስለ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብና ፡ ሳይቀርብ ፡ መቅረት</u> ፡ .... .... .... .. ፴፮

ቍ ፡ ፺፭ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ መሆኑ ፡ .... .... .... .... ....

ቍ ፡ ፺፮ ፡ ከብዙ ፡ ከሣሾች ፡ ወይም ፡ ተከሣሾች ፡ መካከል ፡ ያንዱን ፡ ብቻ ፡ መቅረብ ፡ .... .... .... ፴፯

ቍ ፡ ፺፯ ፡ ስለ ፡ ሽሪኮች ፡ መቅረብ ፡ .... .... .... ፴፯

ቍ ፡ ፺፰ ፡ አንዳንድ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ራሳቸው ፡ እንዲቀርቡ ፡ ለማዘዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ፡ .... ፴፰

ቍ ፡ ፺፱ ፡ ስለ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መቅረብ ፡ .... ፴፰

ቍ ፡ ፻ ፡ የተከሣሹ ፡ አለመቅረብ ፡ .... .... .... ፴፱

ቍ ፡ ፻፩ ፡ የክሱ ፡ መዝገብ ፡ መዘጋት ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ .... .... .... .... .... ፵

ቍ ፡ ፻፪ ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ስለመቅረብ ፡ ... ፵

ቍ ፡ ፻፫ ፡ የከሣሹ ፡ አለመቅረብ ፡ .... .... .... ፵

ቍ ፡ ፻፬ ፡ የክሱ ፡ መዝገብ ፡ መዘጋት ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ .... .... .... .... .... ፵፩

ቍ ፡ ፻፭ ፡ የብዙ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ያለመቅረብ ፡ .... ፵፩

ቍ ፡ ፻፮ ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያለመቅረብ ፡ .... ... ፵፪

ቍ ፡ ፻፯ ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ የታዘዘው ፡ ሰው ፡ ያለመቅ ረብ ፡ .... .... .... .... .... .. ፵፪

ቍ ፡ ፻፰ ፡ ተከሳሽ ፡ በሌለበት ፡ የተሰጠውን ፡ ውሣኔ ፡ ስለ ማንሳት ፡ .... .... .... .... .... ፵፪

ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ክስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ .... .... ....

ቍ ፡ ፻፱ ፡የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ፡ .... .... .... .. ፵፫

<u>ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ አቤቱታ</u> ፡ .... .... .... ....

ገጽ :

ቊ ፡ ፹ ፤ በአቤቱታ ፡ ማመልከቻ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ስለሚ ገለጹ ፡ ነገሮች ፡ .... .... .... .... ፵፬

ቊ ፡ ፹፩ ፤ በተቀዳሚነት ፡ መፈጸም ፡ ስለሚገባቸው ፡ ግዴ ታዎች ፡ .... .... .... .... .... ፵፭

ቊ ፡ ፹፪ ፤ አዲስ ፡ ነገር ፡ .... .... .... .... ፵፭

ቊ ፡ ፹፫ ፤ ነገርን ፡ በግልጽ ፡ መካድ ፡ ተገቢ ፡ ስለመሆኑ ፡ . ፵፭

ቊ ፡ ፹፬ ፤ ውልን ፡ ስለመካድ ፡ .... .... .... .. ፵፮

ቊ ፡ ፹፭ ፤ በክርክር ፡ ላይ ፡ የሚቀርቡትን ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነ ዶች ፡ ባለዋጋነት ፡ ስለማስረዳት ፡ .... .... ፵፮

ቊ ፡ ፹፮ ፤ ስለ ፡ አእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... ፵፮

ቊ ፡ ፹፯ ፤ ማስታወቂያ ፡ ስለመስጠት ፡ .... .... .. ፵፮

ቊ ፡ ፹፰ ፤ በነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሚታወቁ ፡ ውሎ ችና ፡ ሕጋዊ ፡ ግንኙነቶች ፡ .... .... .. ፵፮

ቊ ፡ ፹፱ ፤ ሕጋዊ ፡ ስለሆኑ ፡ ግምቶች ፡ .... .... .. ፵፮

ቊ ፡ ፺ ፤ ከፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ክርክር ፡ መሥመር ፡ ውጭ ፡ ስለ መውጣት ፡ .... .... .... .... ..

ቊ ፡ ፺፩ ፤ አቤቱታን ፡ ስለማሻሻል ፡ .... .... .... ፵፯

ቊ ፡ ፺፪ ፤ አቤቱታን ፡ ስለማረጋገጥ ፡ .... .... ... ፵፰

ቊ ፡ ፺፫ ፤ አቤቱታን ፡ ስለመፈረም ፡ .... .... ... ፵፰

ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለመጥሪያ ፡ .... .... .... ....

ክፍል ፡ ፩ ፤ መጥሪያ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለመቀበልና ፡ ለተ ጠሪው ፡ ስለመስጠት ፡ .... .... ... ..

ቊ ፡ ፺፬ ፤ መጥሪያ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማስወጣት ፡ .... ፶

ቊ ፡ ፺፭ ፤ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፡ .. ፶፩

ቊ ፡ ፺፮ ፤ መጥሪያን ፡ ለነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ ለጠበቃው ፡ ስለመስጠት ፡ .... .... .... .... ፶፩

ቊ ፡ ፺፯ ፤ መጥሪያ ፡ ለንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ስለመስጠት ። ፶፩

ቊ ፡ ፺፰ ፤ መጥሪያን ፡ ሽሪክ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ስለመስጠት ፶፪

ቊ ፡ ፺፱ ፤ በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ለሚነግድ ፡ ተከሣሽ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ፡ .... .... .... ፶፫

| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ቍ ፡ ፪፻ ፤ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በሚቀርብ ፡ ክስ፡ ለንብረቱ ፡ ወኪል ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ፡ .... | ፶፫ |
| ቍ ፡ ፪፻፩ ፤ መጥሪያን ፡ ለተከሣሽ ፡ ቤተሰቦች ፡ ስለመስጠት ።.... .... .... .... .... | ፶፫ |
| ቍ ፡ ፪፻፪ ፤ መጥሪያ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ደረሰኝ ፡ መፈረም ፡ የሚገባው ፡ ስለመሆኑ ።.... .... ... | ፶፫ |
| ቍ ፡ ፪፻፫ ፤ ተከሣሽ ፡ መጥሪያን ፡ ለመቀበል ፡ እምቢተኛ ፡ ስለመሆኑ ፡ ወይም ፡ ስላለመገኘቱ ። .... ... | ፶፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፬ ፤ መጥሪያው ፡ የተሰጠበትን ፡ ሁኔታና ፡ ጊዜ ፡ ስለ ማረጋገጥ ፡ .... .... .... .... ... | ፶፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፭ ፤ በምትክ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ። .... .... | ፶፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፮ ፤ በፖስታ ፡ ስለሚላክ ፡ መጥሪያ ። .... .... | ፶፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፯ ፤ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖር ፡ ተከሣሽ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ። .... .... .... .... .... | ፶፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፰ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ ለሚኖር ፡ ተከሣሽ፡ ስለሚላክ ፡ መጥሪያ ። .... .... .... . | ፶፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፱ ፤ ለመንግሥት ፡ ወይም ፡ ለኩባንያ ፡ ሠራተኞች ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ። .... .... .... | ፶፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፲ ፤ መጥሪያ ፡ ለተከሣሽ ፡ እንዲሰጥ ፡ የታዘዘ ፡ ሰው ፡ ስላለበት ፡ ግዴታ ። .... .... .... ... | ፶፯ |
| <u>ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለምሥክሮች ፡ አጠራርና ፡ አቀራረብ ።</u> .... ... | |
| ቍ ፡ ፪፻፲፩ ፤ መጥሪያ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለመቀበል ። .... | ፶፰ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፪ ፤ ለምስክሮች ፡ ስለሚከፈል ፡ ውጭ ። .... .. | ፶፰ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፫ ፤ ተቀማጭ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ የማይበቃ ፡ ሲሆን ፡ ስለሚታዘዝ ፡ ተጨማሪ ፡ ሒሣብ ። ... | ፶፰ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፬ ፤ በመጥሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ጉዳዮች ። .... .... .... .... .... | ፶፱ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፭ ፤ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ። .... .... .... .... .. | ፶፱ |

ገጽ ፡

ቊ ፡ ፻፲፮ ፤ ስለመጥሪያ ፡ አሰጣጥ ። .... .... .... ፷
ቊ ፡ ፻፲፯ ፤ መጥሪያ ፡ ለመስጠት ፡ ስለተወሰነ ፡ ጊዜ ። ... ፷
ቊ ፡ ፻፲፰ ፤ የጥሪን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለማያከብሩ ፡ ምስክሮች ። ፷
ቊ ፡ ፻፲፱ ፤ የምስክርነት ፡ ቃልን ፡ መስጠትና ፡ የተጠየቀ
ውን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ስለመሆኑ ። ፷፩
ቊ ፡ ፻፳ ፤ ምስክርን ፡ ስለማሰናበት ። .... .... ... ፷፩
ቊ ፡ ፻፳፩ ፤ የምስክርነት ፡ ቃልን ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡
የጽሑፍ ፡ ማስረጃን ፡ ለማቅረብ ፡ ስላለመቻል ። ፷፩

ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚወከል ፡
ምትክ ፡ ዳኛ ፡ .... .... .... ....

ቊ ፡ ፻፳፪ ፤ መሠረቱ ። .... .... .... .... ፷፪
ቊ ፡ ፻፳፫ ፤ ለምትክ ፡ ዳኞች ፡ የሚከፈለውን ፡ አበል ፡ ለፍ
ርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ። .... ... ፷፪
ቊ ፡ ፻፳፬ ፤ ስለምትክ ፡ ዳኞች ፡ ሥልጣን ። .... .... ፷፫
ቊ ፡ ፻፳፭ ፤ ምስክሮችን ፡ በምትክ ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ አቅርቦ፡
ስለመመርመርና ፡ ቃላቸውን ፡ ስለመቀበል ። . ፷፫
ቊ ፡ ፻፳፮ ፤ ተከራካሪዎች ፡ ወገኖች ፡ በምትክ ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡
ስለሚቀርቡበት ፡ ሁኔታ ። .... .... ... ፷፬

ክፍል ፡ ፪ ፤ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ስለሚጠየቁና ፡ ስለ
ሚመረመሩ ፡ ምስክሮች ። .... .... ....

ቊ ፡ ፻፳፯ ፤ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ስለሚሾምበት ፡ ቦታ ። .... ፷፬
ቊ ፡ ፻፳፰ ፤ ምትክ ፡ ዳኞች ፡ የታዘዙትን ፡ ሥራ ፡ ስለመጨ
ረሳቸው ። .... .... .... .... . . ፷፭
ቊ ፡ ፻፳፱ ፤ የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በጠየቁ ፡
ጊዜ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የምትክ ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ። ፷፯
ቊ ፡ ፻፴ ፤ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚወስደው ፡ እር
ምጃ ። .... .... .... .... .... ፷፯
ቊ ፡ ፻፴፩ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ቊጥሮች ፡ ድን
ጋጌ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚጠየቅ
ጉዳይ ፡ ስላላቸው ፡ ተፈጻሚነት ። .... .... ፷፯

ገጽ ፡

ክፍል ፡ ፫ ፡ ምትክ ፡ ዳኞች ፡ ማስረጃን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚወስዱት ፡ ሌላ ፡ እርምጃ ። .... .... ፹፯
ቍ ፡ ፻፴፪ ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ በመገኘት ፡ ስለሚደረግ ፡ ምርመራ ። .... .... .... .... .. ፹፯
ቍ ፡ ፻፴፫ ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ስለሚያከናውንበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ። .... .... ... ፹፰
ቍ ፡ ፻፴፬ ፡ በምትክ ፡ ዳኞች ፡ ስለሚደረግ ፡ የሒሳብ ፡ ምርመራ ። .... .... .... .... .... ፹፰
ቍ ፡ ፻፴፭ ፡ ስለተጨማሪ ፡ ምርመራ ። .... .... .. ፹፱
ቍ ፡ ፻፴፮ ፡ ልዩ ፡ አዋቂ ፡ (ኢክስፔርት) ስለመሾም ። .... ፹፱

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፬ ። ሰነዶችን ፡ ስለማቅረብ ፡ ታሽገው ፡ እንዲጠበቁ ስለማድረግና ፡ ስለመመለስ ።
ቍ ፡ ፻፴፯ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ጊዜ ። . ፺
ቍ ፡ ፻፴፰ ፡ ለክርክሩ ፡ አግባብ ፡ ያልሆኑትን ፡ ወይም ፡ ከነገሩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሌላቸውን ፡ ማስረጃዎች ፡ ስላለመቀበል ። .... .... .... ፺፩
ቍ ፡ ፻፴፱ ፡ በማስረጃነት ፡ በሚቀርቡ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ስለማድረግ ። .... .... .... ፺፩
ቍ ፡ ፻፵ ፡ በግልባጭ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ምልክት ። .... .... .... .... .. ፺፩
ቍ ፡ ፻፵፩ ፡ ተቀባይነት ፡ በሌላቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ምልክት ። .... .... .... ፺፪
ቍ ፡ ፻፵፪ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተቀበላቸውንና ፡ የነቀፋቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ ስለመመዝገብ ። .... .. ፺፫
ቍ ፡ ፻፵፫ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ተከብሮ ፡ ታሽጐ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ። .... .... ፺፫
ቍ ፡ ፻፵፬ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ስለመመለስ ። .... ፺፫
ቍ ፡ ፻፵፭ ፡ አንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሌሎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ወይም ፡ ከሌላ ፡ ክፍል ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ፺፬

ገጽ ፡

ጽሑፍ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ሰነድ ። . . . . ፻፸፩

ቍ ፡ ፪፻፹፮ ፡ ስለጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በግዙፍ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ተፈጻሚነት ፻፸፩

<u>ም ዕ ራ ፍ ፡ ፰ ። ለጊዜው ፡ ስለሚሰጡ ፡ የማገጃና ፡ ሌሎች ፡ ትእዛዞች ።</u>

<u>ክ ፍ ል ፡ ፩ ። ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ስለሚሰጥ ፡ የእሥራት ፡ ትእዛዝ ።</u>

ቍ ፡ ፪፻፹፯ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቅረብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ዋስትና ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፸፪

ቍ ፡ ፪፻፹፰ ፡ ስለዋስትና ፡ የሚያዝ ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ። . . . .

ቍ ፡ ፪፻፹፱ ፡ ዋስትናን ፡ ለማስወረድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፸፫

ቍ ፡ ፪፻፺ ስለዋስትና ፡ የሚያዝ ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ሌላ ዋስ ፡ ለመስጠት ፡ እምቢተኛ ፡ ስለመሆን ። . . ፻፸፫

<u>ክ ፍ ል ፡ ፪ ። ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ንብረት ፡ እንዲረከብ ፡ ስለማድረግ ።</u>

ቍ ፡ ፪፻፺፩ ፡ ተፈላጊውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ዋስትና ። . . . . . . . . ፻፸፫

ቍ ፡ ፪፻፺፪ ፡ ንብረት ፡ ስለማስከበር ፡ ወይም ፡ ስለማስያዝ ። ፻፸፬

ቍ ፡ ፪፻፺፫ ፡ የንብረት ማስያዝ ፡ ወይም ፡ ማስከበር ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ። . . . . . . . . . . . . ፻፸፬

<u>ክ ፍ ል ፡ ፫ ። ለጊዜው ፡ ስለሚሰጥ ፡ የማገድ ትእዛዝ ።</u>

ቍ ፡ ፪፻፺፬ ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ለጊዜው ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፸፭

ቍ ፡ ፪፻፺፭ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ግዴታ ፡ ተደጋግሞ ፡ እንዳይፈርስ ፡ ወይም ፡ ለማፍረስ ፡ የተወሰደው ፡ እርምጃ ፡ እንዳይቀጥል ፡ ስለሚሰጥ ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፸፮

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፻፶፮ ፡ የማገጃን ፡ ትእዛዝ ፡ ስላለማክበር ። .... ... ፻፬
ቍ ፡ ፻፶፯ ፡ ላንደኛው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማስ ታወቂያ ። .... .... .... .... .. ፻፭
ቍ ፡ ፻፶፰ ፡ የማገጃው ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሻሻል ፡ ሊነሳ ፡ ወይም ፡ ሊሠረዝ ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ። .... ... ፻፭
ቍ ፡ ፻፶፱ ፡ በሕግ ፡ በተቋቋመው ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ የሚሰጥ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ መሪዎች ፡ ላይ ፡ ስላለው አስገዳጅነት ። .... ፻፮

ክ ፍ ል ፡ ፬ ። ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

ቍ ፡ ፻፷ ፡ ክርክሩ ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እን ዲሸጥ ፡ ተቀዳሚ ፡ ትእዛዝ ። .... .... .... ፻፮
ቍ ፡ ፻፷፩ ፡ ክርክር ፡ የተነሣበትን ፡ ሀብት ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ አኑሮ ፡ ስለመጠበቅ ፡ እንዳይበላሽ ፡ ስለሚደረግ ለት ፡ ጥንቃቄና ፡ የመቆጣጠር ፡ ምርመራ ። .... ፻፮
ቍ ፡ ፻፷፪ ፡ ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ለባላጋ ራው ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለመስጠት ። .... .... ፻፯
ቍ ፡ ፻፷፫ ፡ ሽያጭን ፡ ስለማገድ ። .... .... .... ፻፰
ቍ ፡ ፻፷፬ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚቀመጥ ፡ ገንዘብ ። .... ፻፰
ቍ ፡ ፻፷፭ ፡ ስለሌሎች ፡ ትእዛዞች ። .... .... .... ፻፱

ክ ፍ ል ፡ ፭ ። ተቀባይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ስለመሾም ።

ቍ ፡ ፻፷፮ ፡ ተቀባይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ስለሚሾምበት ፡ ሁኔታ ። .... .... .... .... .... ፻፱
ቍ ፡ ፻፷፯ ፡ ለተቀባዩ ፡ ስለሚከፈል ፡ አበል ። .... .... ፻፲
ቍ ፡ ፻፷፰ ፡ ስለተቀባዩ ፡ ግዴታዎች ። .... .... ... ፻፲
ቍ ፡ ፻፷፱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀባዩን ፡ ግዴታ ፡ ስለሚፈጽ ምበት ፡ ሥርዓት ። .... .... .... .... ፻፲

ክ ፍ ል ፡ ፮ ። ስለማሸግና ፡ የሀብት ፡ ዝርዝር ፡ ስለማዘ ጋጀት ።

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፪፻፹ ፡ መሠረቱ ። .... .... .... .... ... ፻፹፯
ቍ ፡ ፪፻፹፩ ፡ እሽግ ፡ እንዲደረግ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ። ፻፹፯
ቍ ፡ ፪፻፹፪ ፡ ስለመዝገብ ። .... .... .... .... ፻፹፰
ቍ ፡ ፪፻፹፫ ፡ ስለማይታሸግባቸው ፡ ነገሮች ። .... .... ፻፹፱
ቍ ፡ ፪፻፹፬ ፡ ስለ ፡ ኑዛዜዎችና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ጽሑፎች ። .. ፻፹፱
ቍ ፡ ፪፻፹፭ ፡ እሽግን ፡ ስለማንሳት ። .... .... .... ፻፺
ቍ ፡ ፪፻፹፮ ፡ የዕቃዎችንና ፡ የንብረቶችን ፡ ዝርዝር ፡ ስለማዘጋጀት ። .... .... .... .... .... ፻፺

ክ ፍ ል ፡ ፫ ። ተገድዶ ፡ የመያዝን ፡ ሕጋዊነት ፡ ለማጣ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡

ቍ ፡ ፪፻፹፯ ፡ ተገድዶ ፡ በመያዝ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ። .... .... .... .... ... ፻፺፩
ቍ ፡ ፪፻፹፰ ፡ እንዲቀርብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ። ፻፺፪
ቍ ፡ ፪፻፹፱ ፡ ጉዳዩን ፡ ስለመስማት ፡ ውሳኔ ፡ ስለመስጠትና ፡ ስለማመልከቻ ፡ አቀራረብ ፡ .... .... .... ፻፺፪

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፲ ፡ ስለ ፡ ፍርድና ፡ ስለ ፡ ትእዛዝ ፡

ክ ፍ ል ፡ ፩ ፡ አጠቃላይ ፡ ድንጋጌዎች ፡

ቍ ፡ ፪፻፺ ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጥበት ፡ ጊዜ ። .... .... .. ፻፺፫
ቍ ፡ ፪፻፺፩ ፡ የፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ሁኔታና ፡ ፎርም ። .... ፻፺፫
ቍ ፡ ፪፻፺፪ ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሐተታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰፍሩ ፡ ነገሮች ። .... .... .... .... .... ፻፺፬
ቍ ፡ ፪፻፺፫ ፡ ስለውሳኔ ፡ አጻጻፍ ፡ ሥርዓትና ፡ በላዩም ፡ ስለ ሚገለጹት ፡ ነገሮች ። .... .... .... ... ፻፺፬
ቍ ፡ ፪፻፺፬ ፡ ስለ ፡ ፍርድና ፡ ስለ ፡ ትእዛዝ ፡ ግልባጭ ። .... ፻፺፭

ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡ በአንዳንድ ፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የተለየ መምሪያ ።

ቍ ፡ ፪፻፺፭ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ለማስረከብ ፡ ስለሚሰጥ ውሳኔ ። .... .... .... .... .... ፻፺፮

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፻፹፮ ፡ በየጊዜው ፡ ለሚከፈል ፡ ዕዳ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ። .... .... .... .... .... ፺፮

ቍ ፡ ፻፹፯ ፡ ይዞታንና ፡ ያላግባብ ፡ የተወሰደ ፡ ጥቅምን ፡ ስለሚመለከት ፡ ውሣኔ ። .... .... .... ... ፺፯

ቍ ፡ ፻፹፰ ፡ ስለማስተሳሰብ ። .... .... .... ... ፺፯

ቍ ፡ ፻፹፱ ፡ በሽርክና ፡ የተቋቋመ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ እንዲፈርስ ፡ በቀረበ ፡ ክስ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ። ... ፺፯

ቍ ፡ ፻፺ ፡ ንብረትን ፡ ለመካፈል ፡ ወይም ፡ ይዞታን ፡ ለመለየት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ። .... .... .... ፺፰

ቍ ፡ ፻፺፩ ፡ በማቻቻል ፡ ውሳኔ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ። ... ፺፰

## ምዕራፍ ፡ ፯ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ጊዜ ፡ አወሳሰንና ፡ ስለቀጠሮ ።

ቍ ፡ ፻፺፪ ፡ ስለ ፡ ጊዜ ፡ አወሳሰንና ፡ አቆጣጠር ።...... ፺፰

ቍ ፡ ፻፺፫ ፡ የጊዜን ፡ ውሣኔ ፡ ስለማክበር ። .... .... ፺፱

ቍ ፡ ፻፺፬ ፡ የጊዜን ፡ ወሰን ፡ ስለማራዘም ፡ .... .... ፺፱

ቍ ፡ ፻፺፭ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ስለማሳለፍ ፡ .... ... ፺፱

ቍ ፡ ፻፺፮ ፡ አዲስ ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ ስለመስጠት ፡ .... . ፺፱

ቍ ፡ ፻፺፯ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጊዜን ፡ በመወሰን ፡ ቀጠሮ ፡ መስጠት ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .. ፻

ቍ ፡ ፻፺፰ ፡ ቀጠሮ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ .... .. ፻፩

ቍ ፡ ፻፺፱ ፡ ለቀጠሮው ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ያለመፈጸም ፡ .... .... ... .... .... ፻፩

### ክፍል ፡ ፪ ፡ ለኪሣራ ፡ ለሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ዋስትና ፡

ቍ ፡ ፪፻ ፡ ከሣሽ ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያስይዝ ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... ፻፪

ቍ ፡ ፪፻፩ ፡ የዋስትና ፡ መስጠት ፡ ግዴታን ፡ ያለመፈጸም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ .... .... ... ፻፪

ቍ ፡ ፪፻፪ ፡ ከይግባኝ ፡ ባይ ፡ ስለሚጠየቅ ፡ የኪሣራ ፡ መያዣ ፻፫

| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ወይም ፡ ዋስትና ። .... .... .... .... | ፻፫ |
| **ክ ፍ ል ፡ ፫ ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ (አፊዳቪት)** | |
| ቍ ፡ ፪፻፫ ፡ የጉዳዩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ስለማድረግ ። .... .... .... ... | ፻፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፬ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ በጽሑፍ ፡ የሰጠው ፡ ወገን ፡ እንዲቀርብ ፡ ስለማድረግ ። .... .... .... | ፻፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፭ ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የሚሰጡ ፡ ነገሮች ፡ ወሰን ። | |
| ቍ ፡ ፪፻፮ ፡ የመሐላን ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ ስለሚችል ፡ ባለሥልጣን ። .... .... .... .... .... | ፻፭ |
| **ክ ፍ ል ፡ ፬ ፡ ትእዛዝን ፡ ያለመፈጸም ፡ ስለ ፡ ሚያስከትለው ፡ ውጤት ።** | |
| ቍ ፡ ፪፻፯ ፡ መሠረቱ ፡ .... .... .... .... .. | ፻፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፰ ፡ ስሕተትን ፡ ስለማረም ። .... .... .... | ፻፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፱ ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ወይም ፡ እንዲዘጋ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ። .... .... .... | ፻፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፲ ፡ አቤቱታን ፡ ስለመፎ.ን ። .... .... ... | ፻፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፩ ፡ ስለ ፡ ይግባኝ ። .... .... .... .... | ፻፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፪ ፡ ክርክሩ ፡ ስለሚጸናበት ፡ ሁኔታ ። .... ... | ፻፰ |
| **አ ራ ተ ኛ ፡ መ ጽ ሐ ፍ ፡ በመ፫መሪያ ፡ ደረጃ ፡ ስለሚታዩ ፡ መደበኛ ፡ ክርክሮች ፡** | |
| **ክ ፍ ል ፡ ፩ ፡ ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡** | |
| ቍ ፡ ፪፻፲፫ ፡ ክስ ፡ የሚጀመረው ፡ የክሱን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጽ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ስለመሆኑ ፡ .... | ፻፰ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፬ ፡ ክስ ፡ ስለሚመዘገብበት ፡ መዝገብ ፡ .... .. | ፻፱ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፭ ፡ ለዳኝነት ፡ ስለሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ .... ... | ፻፱ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፮ ፡ ስለ ፡ ክሱ ፡ አቀራረብና ፡ አገላለጽ ፡ .... .. | ፻፱ |

| | ገጽ ፡ |
| --- | --- |
| ቍ ፡ ፪፻፲፯ ፡ ለክሱ ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አጣምሮ ፡ ስለማቅረብ ፡ .... .... .... .. | ፻፲ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፰ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ለማስመለስ ፡ ተጣምረው ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ........ | ፻፲ |
| ቍ ፡ ፪፻፲፱ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚ ዎችና ፡ ወራሾች ፡ ስለሚያቀርቡትና ፡ ስለሚቀርብ ባቸው ፡ ክስ ፡ .... .... .... .... .. | ፻፲፩ |
| ቍ ፡ ፪፻፳ ፡ ያላገባብ ፡ ተጣምሮ ፡ መክሰስን ፡ ስለመቃወም ፡ | ፻፲፩ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፩ ፡ ክሱ ፡ ተነጣጥሎ ፡ ስለሚታይበት ፡ ሁኔታ ፡ | ፻፲፪ |

ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ ክስና ፡ ስለመከላከያ ፡ ጽሑፍ ፡

| | |
| --- | --- |
| ቍ ፡ ፪፻፳፪ ፡ በክስ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠፍሩ ፡ ነገሮች ፡ | ፻፲፪ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፫ ፡ ከክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ ስለሚ ቀርቡ ፡ ጽሑፎችና ፡ መግለጫዎች ፡ .... .... | ፻፲፫ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፬ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዳኝነት ፡ በዝርዝር ፡ ስለመግ ለጽ ፡ .... .... .... .... .... .. | ፻፲፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፭ ፡ ለክርክሩ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ለይቶ ፡ ስለመግለጽ ፡ .... .... .... ... | ፻፲፬ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፮ ፡ ገንዘብን ፡ ለመጠየቅ ፡ በሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫዎች ፡ ..... .. | ፻፲፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፯ ፡ በየጊዜው ፡ ስለሚከፈል ፡ ሒሣብ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ..... .... .... .... .... .. | ፻፲፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፰ ፡ መብትን ፡ ስለመመሥረት ፡ ስለማስከበር ፡ ወይም ፡ ስለመሠረዝ ፡ .... .... ... ... | ፻፲፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፳፱ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጅስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝ ገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የሚቀርብለትን ፡ አቤቱታ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ ስለሚመልስበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... .... | ፻፲፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፴ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጅስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝ ገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ስለሚቀበል በት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... .. | ፻፲፮ |

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፪፻፴፩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የክስ ፡ አቤቱታው ፡ ተቀባይ ነት ፡ እንዲኖረው ፡ ስለሚወስንበት ፡ ሁኔታ ፡ ... ፻፲፯
ቍ ፡ ፪፻፴፪ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ተቀባይነት ፡ ማጣቱ ፡ ወይም መሠረዙ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ...... ፻፲፯
ቍ ፡ ፪፻፴፫ ፡ የክስን ፡ ማመልከቻ ፡ ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ስለመስጠት ፡ .... .... ..... .. ፻፲፰
ቍ ፡ ፪፻፴፬ ፡ በመከላከያ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ዝር ዝር ፡ ነገሮች ፡ .... .... .... ..... .. ፻፲፰
ቍ ፡ ፪፻፴፭ ፡ ነገሩን ፡ በመሸሸግ ፡ ስለማስተባበል ፡ .... ፻፳
ቍ ፡ ፪፻፴፮ ፡ በማናቸውም ፡ ክስ ፡ ስለማቻቻል ፡ በሚቀርብ ፡ ጥያቄ ፡ ውስጥ ፡ መ ገለጽ ፡ ስለሚገባቸው ፡ ነገሮች ፡ ፻፳
ቍ ፡ ፪፻፴፯ ፡ በተለያዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ የመቻቻል ፡ ጥያቄና ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ .... ፻፳፩
ቍ ፡ ፪፻፴፰ ፡ የመከላከያን ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ መመርመር ፡ ... ፻፳፩
ቍ ፡ ፪፻፴፱ ፡ ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ክርክሮች ፡ .... .... ፻፳፩
ቍ ፡ ፪፻፵ ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነዶችን ፡ ለማሳመን ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ፡ .... .... .... ..... .. ፻፳፪

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፪ ፡ ክስን ፡ ስለመስማት ፡ የመጀመሪያ ፡ ክስ ፡ ሲከፈት ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡

ቍ ፡ ፪፻፵፩ ፡ ተከራካሪዎቹን ፡ ስለመመርመር ፡ ..... .. ፻፳፪
ቍ ፡ ፪፻፵፪ ፡ በዕምነት ፡ መሠረት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ፻፳፫
ቍ ፡ ፪፻፵፫ ፡ ማብራሪያ ፡ .... .... .... .... ፻፳፬
ቍ ፡ ፪፻፵፬ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ስለሚ ቀርቡ ፡ መቃወሚያዎች ፡ .... .... ....
ቍ ፡ ፪፻፵፭ ፡ በቀረቡት ፡ መቃወሚያዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚ ሰጥ ፡ ውሣኔ ፡ .... .... .... ..... .. ፻፳፭
ቍ ፡ ፪፻፵፮ ፡ የነገር ፡ ጭብጥ ፡ ስለመያዝ ፡ ወይም ፡ ስለማስ ያዝ ፡ .... .... .... .... ..... .. ፻፳፮
ቍ ፡ ፪፻፵፯ ፡ የነገር ፡ ጭብጥ ፡ አመሠራረት ፡ .... ... ፻፳፮
ቍ ፡ ፪፻፵፰ ፡ ጭብጥን ፡ ለመመሥረት ፡ ስለሚያገለግሉ ፡ ፻፳፯

ገጽ ፡

ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ .... .... .... .... ..
ቍ ፡ ፪፻፵፱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጭብጥን ፡ ከመያዙ ፡ በፊት ፡ ምስክሮችንና ፡ በጽሑፍ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ለመመ ርመር ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .. ፻፹፯
ቍ ፡ ፪፻፶ ፡ ክስ ፡ በቀረበበት ፡ የሀብት ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚነሳ ፡ ክርክር ፡ .... .. ፻፹፰
ቍ ፡ ፪፻፶፩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተያዙትን ፡ ጭብጦች ፡ ለማሻ ሻል ፡ ወይም ፡ ለመሠረዝ ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ። ፻፹፰
ቍ ፡ ፻፶፱ ፡ በሕግ ፡ በተቋቋመው ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ የሚሰጥ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ላይ ፡ ስላለው ፡ አስገዳጅነት ። ፻፹፰
ቍ ፡ ፪፻፶፫ ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ በተደረገ ፡ ስምምነት ፡ መሠ ረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ .... .... .... .... .... .. ፻፹፱
ቍ ፡ ፪፻፶፬ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሚለያዩበት ፡ ጉዳይ ፡ ያለመኖሩ ፡ ሲታወቅ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሳኔ ፡ ፻፺
ቍ ፡ ፪፻፶፭ ፡ የሚያከራክር ፡ ነገር ፡ ስላላቸው ፡ ከሣሾችና ፡ ተከሣሾች ፡ .... .... .... .... ... ፻፺
ቍ ፡ ፪፻፶፮ ፡ ማስረጃ ፡ ያለማቅረብ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ .... .... .... .... .... ፻፺፩
ቍ ፡ ፪፻፶፯ ፡ ስለ ፡ መጥሪያ ፡ .... .... .... ... ፻፺፩
ቍ ፡ ፪፻፶፰ ፡ ስለክሱ ፡ መከፈትና ፡ ሙግትን ፡ የመጀመር ፡ መብት ፡ .... .... .... .... .... ፻፺፪
ቍ ፡ ፪፻፶፱ ፡ የክስ ፡ ቃል ፡ መስጠትና ፡ ማስረጃ ፡ ስለማቅረብ ፻፺፪
ቍ ፡ ፪፻፷ ፡ በብዙ ፡ ጭብጦች ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማስረጃ ፡ ፻፺፪
ቍ ፡ ፪፻፷፩ ፡ የማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ሥርዓት ፡ .... .. ፻፺፫
ቍ ፡ ፪፻፷፪ ፡ የምስክርን ፡ ቃል ፡ ስለመተርጐም ፡ ... ... ፻፺፫
ቍ ፡ ፪፻፷፫ ፡ ጥያቄ ፡ የማይቀርብበት ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ፎርም ፡ .... .... .... .... .... ፻፺፬
ቍ ፡ ፪፻፷፬ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሌሎችን ፡ ምስክሮች ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ .... ... ፻፺፭

| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ቍ ፡ ፪፻፷፭ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የምስክሮችን ፡ ቃል ፡ ባስቸኳይ ፡ ለመቀበል ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ፡ . . . . . . . | ፻፴፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፷፮ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮችን ፡ አስጠርቶ ፡ እንደገና ፡ ለመመርመር ፡ ስለመቻሉ ፡ . . . . . . . . | ፻፴፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፷፯ ፡ የምስክርነትን ፡ ቃል ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ ስላለመሆን ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፻፴፭ |
| ቍ ፡ ፪፻፷፰ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለምስክሮች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መጥሪያ ፡ በተላከላቸው ፡ ተከራካሪዎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለመሆኑ ፡ . . . . . . . . . . . . | ፻፴፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፷፱ ፡ የምስክርን ፡ ቃል ፡ በመዝገብ ፡ ላይ ፡ ስለማስፈር ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፻፴፮ |
| ቍ ፡ ፪፻፸ ፡ በጥያቄ ፡ አቀራረብ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ መቃወሚያ ፡ ስለመመዝገብ ፡ . . . . . . . . . . | ፻፴፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፩ ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዳኛ ፡ ስለመዘገበው ፡ ማስረጃ ፡ . . . . . . . . . . . | ፻፴፯ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፪ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምርመራ ፡ ለማድረግ ፡ ስለመቻሉ ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፻፴፰ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፫ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፻፴፰ |
| **ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ክርክርን ፡ ስለማቋረጥ ፡** . . . . . . . . . . . . . | |
| **ክፍል ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ መገላገልና ፡ ከክስ ፡ ውጭ ፡ ስለመሆን ፡** . . . . | |
| ቍ ፡ ፪፻፸፬ ፡ መሠረቱ ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . | ፻፴፰ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፭ ፡ ስለ ፡ እርቅ ፡ ወይም ፡ ስለግልግል ፡ . . . . . . | ፻፴፱ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፮ ፡ የእርቅ ፡ ወይም ፡ የግልግል ፡ ስምምነት ፡ ስለማይዛቸው ፡ ጉዳዮች ፡ . . . . . . . . . . . . . . | ፻፵ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፯ ፡ የእርቅንና ፡ የግልግልን ፡ ስምምነት ፡ ስለመመዝገብ ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፻፵ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፰ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ክስን ፡ ስለመተው ፡ ወይም ፡ ከክርክር ፡ ውጭ ፡ ስለመሆን ፡ . . . . . . . | ፻፵ |
| ቍ ፡ ፪፻፸፱ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ክስን ፡ ስለመተው ፡ ከክርክር ፡ ውጭ ፡ ስለመሆን ፡ . . . . . . . | ፻፵፩ |

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፲፻፷ ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ተቋርጦ ፡ ስለመቅረቱ ፡ .... .... .... .... .. ፪፻፺፩

<u>ክፍል ፡ ፪ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚቀመጥ ፡ ገንዘብ</u> ፡ .... ...

ቍ ፡ ፲፻፷፩ ፡ ተከሣሽ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚያሲዝበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .. ፪፻፺፩
ቍ ፡ ፲፻፷፪ ፡ ተከሣሽ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ በከፊል ፡ ስለሚያሲዝበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... ፪፻፺፪
ቍ ፡ ፲፻፷፫ ፡ የተያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ዕዳውን ፡ በሙሉ ፡ የሚያሸንፍ ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ ስለመቀበል ፡ .... ፪፻፺፪

<u>አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት</u> ፡ .... ....

<u>ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ በአጭር ፡ ሁኔታ ፡ በሚወሰኑ ፡ ክርክሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት</u> ፡ .... .... ..

ቍ ፡ ፲፻፷፬ ፡ በክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰፍር ፡ ልዩ ፡ መግለጫ ፡ .... .... .... .... ... ፪፻፺፫
ቍ ፡ ፲፻፷፭ ፡ ተከሣሹ ፡ ባለመቅረቡ ፡ በሌለበት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ .... ... ... .... ... ፪፻፺፬
ቍ ፡ ፲፻፷፮ ፡ ቀርቦ ፡ ለመከላከል ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ .... ... .... . ፪፻፺፬
ቍ ፡ ፲፻፷፯ ፡ ተከሣሹ ፡ ለመከላከል ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ያቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነትን ፡ ሲያጣ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ .... .... .... .... ፪፻፺፭
ቍ ፡ ፲፻፷፰ ፡ ጉዳዩን ፡ በከፊል ፡ ስለመወሰን ፡ .... ... ፪፻፺፭
ቍ ፡ ፲፻፷፱ ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ተከሣሾች ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ .... .... .... ... ፪፻፺፭
ቍ ፡ ፲፻፸ ፡ መከላከል ፡ ስለሚፈቀድበት ፡ ሁኔታ ፡ .... ፪፻፺፮
ቍ ፡ ፲፻፸፩ ፡ ለወደፊት ፡ ክስ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ሁኔታ ፡ ፪፻፺፮
ቍ ፡ ፲፻፸፪ ፡ ፍርድን ፡ ስለማገድ ፡ .... .... .... ፪፻፺፮

<u>ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ አላፊነትን ፡ ለማስወገድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ</u> ፡

ቍ ፡ ፲፻፸፫ ፡ ትርጓሜ .... .... .... .... .. ፪፻፺፮

ገጽ ፡

ቁ ፡ ፪፻ ፶፬ ፡ አላፊነትን ፡ ለማውረድ ፡ ለሚቀርብ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ .... .... .... .... .. ፪፻፵፯
ቁ ፡ ፪፻ ፶፭ ፡ ክስ ፡ የቀረበበትን ፡ ብር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ማስቀመጥ ፡ .... .... .... .... ... ፪፻፵፯
ቁ ፡ ፪፻ ፶፮ ፡ ቶከማሹ ፡ በከማሹ ፡ ላይ ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ .... .... .... .... ... ... ፪፻፵፯
ቁ ፡ ፪፻ ፶፯ ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ስለ ፡ ሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... .... .. ፪፻፵፰
ቁ ፡ ፪፻ ፶፰ ፡ ተከራዮችና ፡ ወኪሎች ፡ አላፊነትን ፡ የማስወረድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የማይችሉ ፡ ስለመሆናቸው ፡ .... .... .... .... .... .. ፪፻፵፰
ቁ ፡ ፪፻ ፶፱ ፡ ለመዝገብ ፡ ቤት ፡ ስለማስረከብ ፡ .... ... ፪፻፵፱

<u>ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የተፋጠነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡</u> .... .... ...
<u>ክፍል ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡</u> .... .... .... ..
ቁ ፡ ፫፻ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ፡ .... .... .... .. ፪፻፶
ቁ ፡ ፫፻፩ ፡ ክስ ፡ የሚቀርብበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... . ፪፻፶
ቁ ፡ ፫፻፪ ፡ ማመልከቻው ፡ ተቀባይነትን ፡ የሚያጣበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... .... ፪፻፶፩
ቁ ፡ ፫፻፫ ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ፡ ፪፻፶፩
ቁ ፡ ፫፻፬ ፡ በዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚሰጡ ፡ ትእዛዞች ፡ .... .... .... .... ..... . ፪፻፶፪
ቁ ፡ ፫፻፭ ፡ የማረጋገጫ ፡ ወረቀት ፡ ስለመስጠት ፡ .... ፪፻፶፪
ቁ ፡ ፫፻፮ ፡ ስለ ፡ ይግባኝ ፡ ..... .... .... .... ፪፻፶፫

<u>ክፍል ፡ ፪ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡</u> .... .... .... ....
ቁ ፡ ፫፻፯ ፡ ስብሰባ ፡ .... .... .... .... .... ፪፻፶፬
ቁ ፡ ፫፻፰ ፡ ስለመሾም ፡ .... .... .... .... ፪፻፶፭
ቁ ፡ ፫፻፱ ፡ ውሣኔዎችን ፡ ስለመሻር ፡ .... .... ...
ቁ ፡ ፫፻፲ ፡ ለማሰናበት ፡ ለማስወገድና ፡ ለመሻር ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ .... .... .... ፪፻፶፭
ቁ ፡ ፫፻፲፩ ፡ ሺርክናን ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅትን ፡ ፪፻፶፮

| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ስለማፍረስ ፤.... .... .... .... | |
| ቍ ፡ ፫፻፲፪ ፤ የበጐ ፡ አድራጐት ፡ ድርጅቶችን ፡ ስለማቀ ላቀል ፤.... .... .... ... | ፻፶፮ |
| ቍ ፡ ፫፻፲፫ ፤ ጋብቻን ፡ ስለመቃወም ፤.... .... ... | ፻፶፯ |
| ቍ ፡ ፫፻፲፬ ፤ ክልከላን ፡ ለማስወገድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤ ቱታ ፤.... .... .... .... | ፻፶፯ |
| ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ስለግልግል ፤.... .... .... .... | |
| ቍ ፡ ፫፻፲፭ ፤ መሠረቱ ፤.... .... .... .... | ፻፶፯ |
| ቍ ፡ ፫፻፲፮ ፤ የግልግል ፡ ዳኞች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚሾ ሙበት ፡ ሁኔታ ፤.... .... .... ... | ፻፶፰ |
| ቍ ፡ ፫፻፲፯ ፤ የግልግል ፡ ዳኝነት ፡ አፈጻጸም ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፤... .... .... .... .... | ፻፶፰ |
| ቍ ፡ ፫፻፲፰ ፤ የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤተዘመድ ፡ ሽምግልና፡ ዳኞች ፡ ስለሚሰጡት ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፤.... .... .... .... ... | ፻፶፱ |
| ቍ ፡ ፫፻፲፱ ፤ ብይኑን ፡ ስለማስፈጸምና ፡ ስለይግባኝ ፤.... | ፻፶፱ |
| ስድስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለይግባኝ ፡ ፍርድን ፡ መቃወምና ፡ ፍርድ ፡ እንዲሻሻል ፡ ወይም ፡ እንዲ ጣራ ፡ ስለማመልከት ፤.... .... | |
| ክፍል ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፤.... .... .... | |
| ቍ ፡ ፫፻፳ ፤ ይግባኝ ፡ ስለሚፈቀድበት ፡ ሁኔታ ፤.... .. | ፻፷ |
| ቍ ፡ ፫፻፳፩ ፡ ይግባኝ ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ስላላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፤.... .... .... ... | ፻፷፩ |
| ቍ ፡ ፫፻፳፪ ፤ ስለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፤.... .... .... .... ... | ፻፷፪ |
| ቍ ፡ ፫፻፳፫ ፤ ይግባኝ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ ስለአቀራ ረቡ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤.... .... .... | ፻፷፪ |
| ቍ ፡ ፫፻፳፬ ፤ ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ እንዲከፈት ፡ስለሚቀርብ ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፤.... .... ... | ፻፷፫ |
| ቍ ፡ ፫፻፳፭ ፤ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ እንዲከፈት ፡ | |

| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ስለሚቀርብ ፡ የፈቃድ ፡ መጠየቂያ ፡ ማመልከቻ ፤.... .... .... .... .... | ፻፳፫ |
| ቍ ፡ ፫፻፹፮ ፤ በቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፤.... .... .... .... ... | ፻፳፬ |
| ቍ ፡ ፫፻፹፯ ፤ በይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፉ ፡ ነገሮች ፤.... .... .... .... ... | ፻፳፬ |
| ቍ ፡ ፫፻፹፰ ፤ ይግባኝ ፡ ስለሚባልባቸው ፡ ምክንያቶች ፤... | ፻፳፭ |
| ቍ ፡ ፫፻፹፱ ፤ ስለአዲስ ፡ ነገሮችና ፡ ስለአዲስ ፡ ክርክሮች ፤.. | ፻፳፭ |
| ቍ ፡ ፫፻፺ ፤ የይግባኝ ፡ ማመልከቻን ፡ ስለመሠረዝ ፡ ወይም ፡ ስለማሻሻል ፤.... .... .... | ፻፳፮ |
| ቍ ፡ ፫፻፺፩ ፤ የከሣሽ ፡ ወይም ፡ የተከሣሽ ፡ ቍጥር ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፤.... .... .... | ፻፳፮ |
| ክፍል ፡ ፯ ፡ ክርክር ፡ እንዳይቀጥልና ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለማገድ ፤.... .... .... .... .... | |
| ቍ ፡ ፫፻፺፪ ፤ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚሰጠው ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፤.... .... .. | ፻፳፯ |
| ቍ ፡ ፫፻፺፫ ፤ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚሰጠው ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፤.... .... .... .... .... | ፻፳፯ |
| ቍ ፡ ፫፻፺፬ ፤ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ፍርዱን ፡ ለማገድ ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ፤.... ....... | ፻፳፯ |
| ቍ ፡ ፫፻፺፭ ፤ ፍርድን ፡ ለማገድ ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ምክንያት ፤.... .... .... | ፻፳፱ |
| ቍ ፡ ፫፻፺፮ ፤ ፍርድን ፡ ለመፈጸም ፡ ስለሚሰጥ ፡ ዋስትና ፤.... .... .... .... .... | ፻፳፱ |
| ክፍል ፡ ፰ ፡ ይግባኝን ፡ ስለመቀበልና ፡ ስለመስማት ፤...... | |
| ቍ ፡ ፫፻፺፯ ፤ መልስ ፡ ሰጪ ፡ ሳይጠራ ፡ ይግባኝን ፡ ለመሠረዝ ፡ ስለሚቻልበት ፡ ሁኔታ ፤.... .... | ፻፴ |
| ቍ ፡ ፫፻፺፰ ፤ ይግባኝ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ስለመወሰን ፤.... .... .... .... .... | ፻፴ |

| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ቍ ፡ ፫፻፵፱ ፤ ክርክሩን ፡ የሚጀምረው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ስለመሆኑ ፤.... .... .... .... | ፪፻፴፩ |
| ቍ ፡ ፫፻፶ ፤ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በይግባኙ ፡ ላይ ፡ ስለሚያስማው ፡ ቅሬታ ፤.... .... .... ... | ፪፻፴፩ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፩ ፤ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለይግባኝ ፡ የቀረበለትን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚመልስበት ፡ ሁኔታ ፤.... ... | ፪፻፴፪ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፪ ፤ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ በሰፈረው ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፤.... .... | ፪፻፴፫ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፫ ፤ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የነገሩን ፡ ጭብጥ ፡ አስተካክሎ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚመልስበት ፡ ሁኔታ ፤. . | ፪፻፴፫ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፬ ፤ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ውሣኔ ፡ ስለመቃወም ፤... | ፪፻፴፬ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፭ ፤ ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፤.... .... .. | ፪፻፴፬ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፮ ፤ የተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ አቀባበል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤.... .... .... .... .. | ፪፻፴፭ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፯ ፤ የፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤..... | ፪፻፴፭ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፰ ፤ ስለ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፤.... .... .... .... .... | ፪፻፴፭ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፱ ፤ የተወሰደን ፡ ነገር ፡ ለማስመለስ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፤.... .... .... ... | ፪፻፴፮ |
| ቍ ፡ ፫፻፷ ፤ ስለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖችና ፡ ስለአፈጻጸሙ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤.... .... .... .... | ፪፻፴፮ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፩ ፤ ይግባኝ ፡ ስለሚባልባቸው ፡ ምክንያቶች ፤... | ፪፻፴፮ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፪ ፤ ይግባኙ ፡ ስለሚቀርብለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤... | ፪፻፴፯ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፫ ፤ ስለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፤.... .... .... .... .... | ፪፻፴፯ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፬ ፤ ብይኑ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ ስለመመለስ ፤.... .... .... .... .... | ፪፻፴፰ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፭ ፤ ብይኑን ፡ ስለመሻር ፤.... .... .... | ፪፻፴፰ |

| | ገጽ ፡ |
|---|---|
| ቍ ፡ ፫፻፶፯ ፤ ለማመልከቻው ፡ አቀራረብ ፡ መሠረት ፡ ስለሚሆኑ ፡ ነገሮች ፤.... .... .... | ፻፹ |
| ቍ ፡ ፫፻፶፰ ፤ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ፤.. | ፻፹ |
| ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ስለመቃወም ፤.... .... .... .... | |
| ቍ ፡ ፫፻፶፱ ፤ መቃወሚያን ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚችሉ ፡ ወገኖች ፤.... .... .... .... .. | ፻፹ |
| ቍ ፡ ፫፻፷ ፤ መቃወሚያን ፡ የሚያቀርቡበት ፡ ፎርም፤..., | ፻፹፩ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፩ ፤ መቃወም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፤.... | ፻፹፩ |
| ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ፍርድን ፡ ስለማጣራት ፤.... .... .... | |
| ቍ ፡ ፫፻፷፪ ፤ ፍርድ ፡ እንዲጣራ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፤.... .... .... .... .... | ፻፹፪ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፫ ፤ ስለኪሳራና ፡ ስለወጭ ፡ የሚሰጥ ፡ ዋስትና ፤.... .... .... .... .... | ፻፹፪ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፬ ፤ አቤቱታን ፡ ስለመቀበል ፤.... .... .. | ፻፹፪ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፭ ፤ ማስታወቂያ ፡ ስለመስጠት ፤.... .... | ፻፹፫ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፮ ፤ ስለዋስትና ፡ ወይም ፡ ስለወጭ ፡ መያዣ ፡ የሚሰጥ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፤.... .... | ፻፹፫ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፯ ፤ በትእዛዙ ፡ መሠረት ፡ ስላለመፈጸም ፤.... | ፻፹፬ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፰ ፤ አቤቱታው ፡ እስኪሰማ ፡ ድረስ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፤.... .... .... .... | ፻፹፬ |
| ቍ ፡ ፫፻፷፱ ፤ ተጨማሪ ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለማድረግ ፤....... | ፻፹፭ |
| ቍ ፡ ፫፻፸ ፤ የችሎት ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፤.... .... .... | ፻፹፮ |
| ቍ ፡ ፫፻፸፩ ፤ ስለ ፡ ማስፈጸም ፤.... .... .... ... | ፻፹፮ |
| ሰባተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፤.... .... ... | |
| ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የተሰጡትን ፡ ፍርዶች ፡ አፈጻጸም ፤.... .... .... .. | |
| ክፍል ፡ ፩ ፤ ፍርድን ፡ ስለሚያስፈጽሙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች፤ | |
| ቍ ፡ ፫፻፸፪ ፤ መሠረቱ ፤.... .... .... .... | ፻፹፮ |

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፫፻፸፪ ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ትእዛዝ ፡ ስለማስተላለፍ ፡.... .... .... .... ... ፻፹፯
ቍ ፡ ፫፻፸፫ ፡ የፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ በሚተላለፍበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡.... .... .... .... .... ፻፹፰
ክፍል ፡ ፫ ፡ ስለአፈጻጸሙ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡.... ....
ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡.... .... ..
ቍ ፡ ፫፻፸፬ ፡ ፍርድን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ፍርድ ቤት ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ፡.... .... ፻፹፱
ቍ ፡ ፫፻፸፭ ፡ ፍርድን ፡ በሚፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚወሰኑ ፡ ነገሮች ፡.... .... .... ፻፹፱
ቍ ፡ ፫፻፸፮ ፡ የፍርዱን ፡ አፈጻጸም ፡ ስለማገድ ፡.... .. ፻፺
ቍ ፡ ፫፻፸፯ ፡ በፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ውሣኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የፍርድ ፡ ማገድ ፡ ትእዛዝ ፡.... .... .... .. ፻፺
ክፍል ፡ ፬ ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻና ፡ ስለአፈጻጸሙ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡.... ....
ቍ ፡ ፫፻፸፰ ፡ ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ስለሚይዛቸው ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡.... ፻፺፩
ቍ ፡ ፫፻፸፱ ፡ ንብረት ፡ እንዲከበር ፡ በሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ነገሮች ፡.... ... ፻፺፪
ቍ ፡ ፫፻፹ ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡.... .... .... .... .... ፻፺፫
ቍ ፡ ፫፻፹፩ ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ጥቅም ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ።.... ፻፺፫
ቍ ፡ ፫፻፹፪ ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ ተያዥ ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ ስለማድረግ ፡.... .... ፻፺፬
ቍ ፡ ፫፻፹፫ ፡ በንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ በወራሾች ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚቀርብ ፡ ፻፺፬

| | |
|---|---|
| | ገጽ ፡ |
| አቤቱታ ፤.... .... .... .... | |
| ቊ ፡ ፫፻፹፩ ፤ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ በይርጋ ፡ ስለሚታገድበት ፡ ሁኔታ ፤.... .... .... .... | ፻፺፩ |
| ቊ ፡ ፫፻፹፪ ፤ ለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ማመልከቻ ፡ የውሳኔ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤.... .... | ፻፺፪ |
| ቊ ፡ ፫፻፹፫ ፤ የፍርድ ፡ ባለዕዳውን ፡ ስለመጠየቅ ፤.... | ፻፺፫ |
| ቊ ፡ ፫፻፹፬ ፤ የማሰር ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ፤.. | ፻፺፫ |
| ቊ ፡ ፫፻፹፭ ፤ በማሠር ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፉ ፡ ነገሮች ፤.... .... .... .... .... | ፻፺፬ |
| ቊ ፡ ፫፻፹፮ ፤ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የማቆየት ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፤.... .... .... | ፻፺፬ |
| ቊ ፡ ፫፻፺ ፤ ከእሥራት ፡ ስለመለቀቅ ፡ .... .... .. | ፻፺፭ |
| ቊ ፡ ፫፻፺፩ ፡ መያዝና ፡ ተይዞ ፡ መለቀቅ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ .... .... .... .... | |
| ቊ ፡ ፫፻፺፪ ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ | ፻፺፭ |
| ቊ ፡ ፫፻፺፫ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ መግለጫ ፡ .... .... ... | ፻፺፮ |

<u>ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዓት ፡</u> .... .... ....

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡</u> .... .... ...

| | |
|---|---|
| ቊ ፡ ፫፻፺፩ ፤ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፤ .... .... .... .... | ፻፺፮ |
| ቊ ፡ ፫፻፺፪ ፤ ገንዘብ ፡ ስለሚከፈልበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .. | ፪፻ |
| ቊ ፡ ፫፻፺፫ ፤ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ለፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ስለመክፈል ፡ .... .... .... .... .. | ፪፻ |
| ቊ ፡ ፫፻፺፬ ፤ ሁለቱም ፡ ወገን ፡ ተከራካሪዎች ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... .... .... | ፪፻፩ |
| ቊ ፡ ፫፻፺፭ ፤ ባንዱ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... ... | ፪፻፪ |

ገጽ ፡


ቍ ፡ ፳፻ ፺፱ ፤ ተለይቶ ፡ በታወቀ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ፡ .... .... .... ፪፻፫

ቍ ፡ ፩፻ ፤ በተለይ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔና ፡ የማገድ ፡ ውሣኔ ፡ .... .... .... .... ፪፻፫

ቍ ፡ ፩፻፩ ፤ የጽሑፍ ፡ ሰነድ ፡ እንዲፈረም ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ወይም ፡ በሚዘዋወሩና ፡ በሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ እንዲፈረም ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ .... .... .... .... ፪፻፫

ቍ ፡ ፩፻፪ ፤ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ፡ .... .... .... .... .... ፪፻፬

ቍ ፡ ፩፻፫ ፤ ሀብትንና ፡ ንብረትን ፡ ስለማከፋፈል ፡ .... ፪፻፬

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ንብረት ፡ ስለማስረከብ ፡</u> .... .... ..

ቍ ፡ ፩፻፬ ፤ ስለማይከበሩና ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ ስለማይወሰዱ ፡ ሀብቶች ፡ .... .... .. ፪፻፭

ቍ ፡ ፩፻፭ ፤ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ተወስኖ ፡ ያልታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ስለሚከበር ፡ የንብረት ፡ መጠን ፡ ....

ቍ ፡ ፩፻፮ ፤ ከእርሻ ፡ ሰብል ፡ በተቀር ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ስለሚያዝበትና ፡ ስለሚከበርበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... ፪፻፮

ቍ ፡ ፩፻፯ ፤ የእርሻ ፡ ሰብል ፡ ስለሚከበርበትና ፡ ስለሚያዝበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... .... .. ፪፻፮

ቍ ፡ ፩፻፰ ፤ በተያዙ ፡ ወይም ፡ በተከበሩ ፡ ሰብሎች ፡ ላይ ፡ ስለሚጸኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ .... .... .... ፪፻፯

ቍ ፡ ፩፻፱ ፤ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ የማይገኝ ፡ ንብረት ፡ ስለሚከበርበት ፡ ወይም ፡ ስለሚያዝበት ፡ ሁኔታ ፡ ፪፻፱

ቍ ፡ ፩፻፲ ፤ በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ድርሻ ፡ ስለማይከበርና ፡ ስለማስያዝ ፡ .... .. ፪፻፲፩

ቍ ፡ ፩፻፲፩ ፤ ደመወዝ ፡ ስለሚያዝበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .. ፪፻፲፩

ቍ ፡ ፩፻፲፪ ፤ የሚዘዋወር ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ ስለሚያዝበትና ፡ ስለሚከበርበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .. ፪፻፲፪

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፩፻፲፫ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ ንብረት ፡ ስለሚያዝበትና ፡ ስለሚከበርበት ፡ ሁኔታ ፡ ... ..... .. ፪፻፲፪
ቍ ፡ ፩፻፲፬ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለሚያዝበትና ፡ ስለሚከበርበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... ፪፻፲፪
ቍ ፡ ፩፻፲፭ ፡ የተያዘ ፡ ወይም ፡ የተከበረ ፡ ንብረት ፡ ስለሚለቀቅበት ፡ ሁኔታ ፡ .... .... .... ... ፪፻፲፫
ቍ ፡ ፩፻፲፮ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የባንክ ፡ ኖት ፡ (የወረቀት) ገንዘብ ፡ እንደከፈለ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ፪፻፲፫
ቍ ፡ ፩፻፲፯ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ በሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሳኔ ፡ .... .... .... ፪፻፲፬

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ መብት ፡ አለን ፡ በማለት ፡ የሚያመለክቱትንና ፡ ይህንኑ ፡ መብት ፡ የሚቃወሙትን ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ አቤቱታ ፡ ስለመመርመር ፡

ቍ ፡ ፩፻፲፰ ፡ በተያዘ ፡ ወይም ፡ በተከበረ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለን ፡ ባዮች ፡ ያቀረቡትን ፡ አቤቱታ ፡ ስለመመርመር ፡ .... .... .... .... ፪፻፲፬
ቍ ፡ ፩፻፲፱ ፡ በአቤቱታው ፡ ወይም ፡ በመቃወሚያው ፡ ክስ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሳኔ ፡ .... .... .... ፪፻፲፭
ቍ ፡ ፩፻፳ ፡ በሚያዘው ፡ ወይም ፡ በሚከበረው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የመያዙ ፡ ወይም ፡ የማስከበሩ ፡ ሥርዓት ፡ ስለሚቀጥልበት ፡ ሁኔታ ፡ .... ... ፪፻፲፭
ቍ ፡ ፩፻፳፩ ፡ በተያዘ ፡ ወይም ፡ በተከበረ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ለማሳወቅ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ፪፻፲፮

ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ንብረትን ፡ የመሸጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ .... .... ....

ቍ ፡ ፩፻፳፪ ፡ የተያዘው ፡ ወይም ፡ የተከበረው ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ ስለማዘዝ ፡ .... .... .... .. ፪፻፲፮
ቍ ፡ ፩፻፳፫ ፡ የሐራጅ ፡ ሺያጭ ፡ መደረጉን ፡ ለሕዝብ ፡ ፪፻፲፮

ገጽ ፡

ስለ ፡ ማስታወቅ ፡ . . . . . . . . . . . . . . . .
ቍ ፡ ፩፻፳፩ ፤ ሺያጭ ፡ እንዲደረግ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፪፻፲፰
ቍ ፡ ፩፻፳፫ ፤ ማስታወቂያው ፡ የሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፡ . . . . ፪፻፲፰
ቍ ፡ ፩፻፳፮ ፤ ሺያጭ ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ . . . . . . ፪፻፲፱
ቍ ፡ ፩፻፳፯ ፤ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ ስለሚቆምበት ፡ ወይም ፡ ስለሚቋረጥበት ፡ ሁኔታ ፤. . . . . . . . . . . ፪፻፲፱
ቍ ፡ ፩፻፳፰ ፤ ፪ኛ ፡ የሐራጅ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለሚወጣበት ፡ ሁኔታ ፤. . . . . . . . . . . . . . . ፪፻፲፱
ቍ ፡ ፩፻፳፱ ፤ በጨረታ ፡ ለገዛው ፡ ንብረት ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከፍል ፡ ወይም ፡ ግዴታውን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ ገዥ ፡ ንብረቱ ፡ በሁለተኛ ፡ ጨረታ፡ ሲሸጥለት ፡ ለጐደለው ፡ ገንዘብ ፡ በአላፊነት ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ሁኔታ ፤. . . . . . . . . . . ፪፻፳
ቍ ፡ ፩፻፴ ፤ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ በሐራጅ ፡ የሚሸጠውን ፡ ሀብት ፡ ያለፈቃድ ፡ ለመግዛት ፡ የማይችል ፡ ስለመሆኑ ፤. . . . . . . . . . . . ፪፻፳፩
ቍ ፡ ፩፻፴፩ ፤ የሐራጅ ፡ ሺያጭ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘ ፡ ማናቸውም ፡ ባለሥልጣን ፡ በጨረታው ፡ መወዳደርና ፡ ንብረተ ፡ ለመግዛት ፡ የተከለለ ፡ ስለመሆኑ ፤. . . . . ፪፻፳፩

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለሚሸጥበት ፡ ሁኔታ ፤</u>. . . . . . . . . . . . . . . .
ቍ ፡ ፩፻፴፪ ፤ የእርሻ ፡ ሰብል ፡ ስለሚሸጥበት ፡ ሁኔታ፤. . . . ፪፻፳፪
ቍ ፡ ፩፻፴፫ ፤ ቡቃያ ፡ ለሆኑ ፡ ሰብሎች ፡ ስለሚጸና ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፤. . . . . . . . . . . . . . . . . . ፪፻፳፫
ቍ ፡ ፫፻፴፬ ፤ ስለ ፡ ተዘዋዋሪ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ ስለ ንግድ ፡ ድርጅት ፡ አክሲዮኖች ፤. . . . . . . ፪፻፳፫
ቍ ፡ ፩፻፴፭ ፤ የሺያጭ ፡ ሥርዓት ፡ በትክክል ፡ ያለመፈጸም ፡ ሽያጩን ፡ ስለሚያፈርስበት ፡ሁኔታ፤. . ፪፻፳፫

ገጽ ፡


ቍ ፡ ፩፻፴፮ ፤ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረትን ፡ ዕዳንና ፡ አክሲዮ ንን ፡ ለገዢው ፡ ስለማስረከብ ፤. . . . . . . . ፪፻፷፬

ቍ ፡ ፩፻፴፯ ፤ የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ አክሲዮ ኖች ፡ የሚዘዋወሩበት ፡ ሁኔታ ፤. . . . . . . . ፪፻፷፬

ቍ ፡ ፩፻፴፰ ፤ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ ስለሚተላለ ፍበት ፡ ሁኔታ ፤. . . . . . . . . . . . . . ፪፻፷፭

<u>ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፮ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለሚሸጥበት ፡ ሁኔታ</u> ፤. . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ቍ ፡ ፩፻፴፱ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የተፈረደበትን ፡ ገንዘብ፡ እስኪያዘጋጅ ፡ ሺያጩን ፡ ስለማቆየት ፤. . . .

ቍ ፡ ፩፻፵ ፤ ገዢ ፡ ስለሚያስቀምጠው ፡ መያዣና ፡ ሙሉ፡ ገንዘብ ፡ ባለመክፈሉ ፡ ስለ ፡ ሚደረግ ፡ ሽያጭ ፤. . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፪፻፷፮

ቍ ፡ ፩፻፵፩ ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ስለሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፤. . . . ፪፻፷፮

ቍ ፡ ፩፻፵፪ ፡ ዋጋው ፡ ሳይከፈል ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈ ጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤. . . . . . . . . . . . . ፪፻፷፮

ቍ ፡ ፩፻፵፫ ፤ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ማናቸው ውም ፡ መብት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ስለሚሰጠው፡ የተቀዳሚነት ፡ መብት ፤. . . . . . . . . . . ፪፻፷፯

ቍ ፡ ፩፻፵፬ ፡ ሺያጭ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ወይም ፡ እንዲቀር ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፤. . . . . . . . . . ፪፻፷፯

ቍ ፡ ፩፻፵፭ ፡ የሺያጩ ፡ ሥርዓት ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ መን ገድ ፡ ወይም ፡ በማጭበርበር ፡ ተፈጽሟል ፡ በማለት ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲታገድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፤. . . . . . . . . . ፪፻፷፰

ቍ ፡ ፩፻፵፮ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በተሸጠው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ሺያጩ ፡ ስለሚፈርስበት ፡ ሁኔታ ፤. . . ፪፻፷፰

ቍ ፡ ፩፻፵፯ ፤ ሽያጩ ፡ ስለሚጸናበትና ፡ ወይም ፡ ስለሚሠ ረዝበት ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፤. . . . . . . . . . . ፪፻፷፰

ገጽ ፡

ቍ ፡ ፬፻፵፰ ፡ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ ስለማስረከብ ፡.... ..... .... ፪፻፷፱
ቍ ፡ ፬፻፵፱ ፡ በተከራይ ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ ስለማስረከብ ፡.... .... .... .... ... ፪፻፷፱
ክፍል ፡ ፮ ፡ ማስረከብን ፡ ስለወም ፡ ወይም ፡ በእምቢተኛነት ፡ ስለመጋፋት ፡.... .... .......
ቍ ፡ ፬፻፶ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ለማስረከብ ፡ እንቢተኛ ፡ ስለመሆንና ፡ መሰናክል ፡ ስለመፍጠር ፡.... .... .... .... ..... ፪፻፸
ቍ ፡ ፬፻፶፩ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ስለሚፈጥረው ፡ መሰናክል ፡ ወይም ፡ የተቃዋሚነት ፡ ተግባር ፡.... ፪፻፸
ቍ ፡ ፬፻፶፪ ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ ባለመብት ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ርክክቡን ፡ ስለሚቃወም ፡ ሰው ፡.... ... ፪፻፸፩
ቍ ፡ ፬፻፶፫ ፡ በፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ኛይም ፡ በገዢው ፡ ስለሚፈጸም ፡ የይዞታ ፡ ማስለቀቅ ፡ ተግባር ፡.... .... .... .... .... ፪፻፸፩
ቍ ፡ ፬፻፶፬ ፡ ነገሩ ፡ በፍርድ ፡ እስኪወሰን ፡ ድረስ ፡ መብቱ፡ በተላለፈለት ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ደንቡ ፡ የማይጸናበት ፡ ስለመሆኑ ፡.... .... ...... ፪፻፸፩
ቍ ፡ ፬፻፶፭ ፡ ስለትእዛዝ ፡ ተፈጻሚነት ፡.... .... .. ፪፻፸፪
ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፡.... ....
ቍ ፡ ፬፻፶፮ ፡ መሠረቱ ፡.... ..... .... .... ፪፻፸፪
ቍ ፡ ፬፻፶፯ ፡ ስለማመልከቻው ፡ ፎርም ፡.... .... .. ፪፻፸፪
ቍ ፡ ፬፻፶፰ ፡ ማመልከቻው ፡ ስለሚፈቀድበት ፡ ሁኔታ.... ፪፻፸፫
ቍ ፡ ፬፻፶፱ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ሥርዓት ፡.... .... .... ፪፻፸፫
ቍ ፡ ፬፻፷ ፡ ስለ ፡ ውሳኔ ፡.... ..... .... .... ፪፻፸፬
ቍ ፡ ፬፻፷፩ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ብይን ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፡.... .... .... ... ፪፻፸፬

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት

# የፍትሐ ፡ ብሔር ፡
# ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ።

## ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም.

ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቍ ፡ ፫ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ም ፡ በተለይ ፡ የወጣ ፡
አዲስ ፡ አበባ ፡

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ በሠላሳ ፡ ስድስተኛው ፡ ዓመታ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ / ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም.

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ የሚመራበትንና ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ በተሻሻለ ፡ ሁኔታ የሚቋቋምበትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘነው ፡

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በ፺፪ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የመከረበትን ፡ ዓይተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ድንጋጌ ፡ አውጀናል ።

፩/ ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ "በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ም ፡ የወጣ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ" ፡ ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።

፪/ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ.ም ልዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሆኖ ፡ በቁጥር ፡ ፫ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

፫/ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ በልምድ ፡ ወይም ፡ ተጽፈው ፡ ይሠራባቸው ፡ የነበሩት ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ስለተተኩ ፡ በሙሉ ፡ ተሽረዋል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ መስከረም ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም.

ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አክሊሉ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡
ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር ።

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት

| ሀያ ፡ አምስተኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫ ።<br>25th Year No. 3 | አዲስ ፡ አበባ ፡ መስከረም ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም.<br>Addis Ababa 8th October 1965. |
|---|---|

# ነጋሪት ጋዜጣ ።

በ ተ ለ ይ የ ወ ጣ

# NEGARIT GAZETA

*Gazette Extraordinary*

| | | |
|---|---|---|
| ዋጋ | በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በጽሕፈት ሚኒስቴር ተጠባባቂነት የቆመ ። | ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይታተማል ።<br>የፖስታ ሣጥን ቍ. 136 |


በድንጋጌ ፡ ቍጥር ፡ ፶፪ / ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. የወጣ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ።

**DECREE No. 52 OF 1965**
**THE CIVIL PROCEDURE CODE DECREE**

BACK

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ።

# የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ።

## መቅድም ።

**ቁጥር ፡ ፩ ። የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ።**

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ከታወጀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ለሚቀርቡ ፡ ክሶችና ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ላሉትም ፡ ክሶች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) ክሱን ፡ ተቀብሎ ፡ መስማት ፡ የጀመረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ያልተጠቀሰ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በነበረው ፡ ሥልጣኑ ፡ የጀመረውን ፡ ነገር ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

**ቁጥር ፡ ፪ ። የጊዜ ፡ ወሰን ።**

(፩) የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋላቸው ፡ በፊት በይርጋ ፡ የታገዱትን ፡ ጉዳዮች ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ባለፈው ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ የታገደውን ፡ ነገር ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ አይቻልም ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚጸናው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ የሚቆጠረው ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ፡ ነው ።

(፫) የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ የሚጸናበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚያራዝሙ ፡ ሲሆን ፤ የዘመኑ ፡ አቆጣጠር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ሕጉ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ያለፈው ፡ ጊዜ ፡ ከዋናው ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ መቀነስ ፡ አለበት ።

(፬) ይህ ፡ ሕግ ፡ የይርጋ ፡ ዘመኑን ወሰን ፡ የሚያሳጥር ፡ ሲሆን ፡ ሕጉ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ተቆጥሮ ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቊ ፤ ፫ ። ስለ ፡ ቃላት ፡ ትርጓሜ ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በልዩ ፡ አኳኋን ፡ እንዲተረጐሙ ፡ በግልጽ ፡ የተመለከተ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ቃላቶችና ፡ አረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተመለከተው ፡ ይተረጐማሉ ።

"አፊዳቪት ፡" ማለት ፡ እውነተኛነቱ ፡ በመሐላ ፡ ተረጋግጦ ፡ በጽሑፍ ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ።

"ፍርድ ፡ ቤት ፡" ማለት ፡ በሕግ ፡ የተቋቋመ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ ነው ።

"ውሳኔ ፡" ማለት ፡ ክርክሩን ፡ በሚሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ያቀረቡትን ፡ ክስና ፡ መልስ ፡ እንዲሁም ፡ ማስረጃዎቹን ፡ መርምሮ ፡ ስለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መብትና ፡ ስለ ፡ ክሱ ፡ አወሳሰን ፡ የሚሰጠው ፡ የመጀመሪያ ፡ ወይም ፡ የመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ውሳኔ ፡ ማለት ፡ ነው ።

"የፍርድ ፡ ባለ ፡ ገንዘብ ፡" ማለት ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱን ፡ በመደገፍ ፡ ፍርዱን ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚያስችል ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠለት ፡ ወይም ፡ የተፈረደለት ፡ ረቺ ፡ ወገን ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ቃል ፡ ከተፈረደለት ፡ ወገን ፡ መብት ፡ የተላለፈለትን ፡ ወይም ፡ በተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ እንዲጠቀም ፡ መብት ፡ ያገኘውንም ፡ ሰው ፡ አጠቃሎ ፡ የሚይዝ ፡ ነው ።

"ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡" ማለት ፡ የማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የሾመው ፡ ባለሥልጣን ፡ ወይም ፡ ያዘዘው ፡ ሠራተኛ ፡ ማለት ነው ።

"የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡" ማለት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ የሚገኝ ፡ በአገሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመ ፡ የማናቸውም አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ ነው ።

"የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡" ማለት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ማለት ፡ ነው ።

"የመንግሥት ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተገለጹትን ፡ አጠቃሎ ፡ ይያዛል ።

(ሀ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ በመንግሥት ፡ ሥም ፡ ሆኖ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚሟገተውን ፡ እንዲሁም ፡

BACK



(ለ) በመንግሥት ፡ ነገረፈጅ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ተወ ክሎ ፡ ስለመንግሥት ፡ ጉዳይ ፡ የሚሟገተውን ።

"ፍርድ ፡" ማለት ፡ የትእዛዝ ፡ ወይም ፡ የውሳኔ ፡ ወይም ፡ የብይን ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ፡ የፍርድ ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ።

"የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡" ማለት ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ በሕግ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠበት ፡ ተረቺ ፡ ወገን ፡ ማለት ፡ ነው ።

"ሕግ ፡" ማለት ፡ አዋጆችን ፡ በአዋጅ ፡ የወጡ ፡ ትእዛዞችን ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያዎችንና ፡ ደንቦችን ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ ቃል ፡ ነው ።

"ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡" ማለት ፡ በሕግ ፡ ችሎታ ፡ የሌለውን ፡ ወይም ፡ የሚችን ፡ ንብረት ፡ የሚያስተዳድር ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው ።

"የማይገባ ፡ ጥቅም ፡" ማለት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ከያዘው ፡ ወይም ፡ ከሚይዘው ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ላይ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ የሥራ ፡ ጥረትና ፡ ድካም ፡ ያገኘው ፡ ወይም ፡ ማግኘት ፡ የሚገባው ፡ ጥቅም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ወለድን ፡ ጨምሮ የሚይዝ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የያዘውን ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ በተሻለ ፡ ዘዴ ፡ አስፋፍቶ ፡ ወይም አልምቶ ፡ ያገኘውን ፡ ጥቅም ፡ አይመለከትም ።

"ትእዛዝ" ማለት ፡ ከውሳኔ ፡ የተለየና ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጥ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ እንደ ፡ ብይን ፡ የሚቆጠር ፡ ተፈጻሚ ፡ ትእዛዝ ፡ ማለት ፡ ነው ።

"ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡" ማለት ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ የተወሰነበት ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው ።

"ተሟጋች ፡" ማለት ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ስለሌላ ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ ተወክሎ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲከራከር ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው ።

"በይርጋ ፡ የታገደ ፡" ማለት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተወሰነው ፡ ዘመን ፡ ያለፈበት ፡ ጉዳይ ፡ ማለት ፡ ነው ።

"ሬጂስትራር ፡" ማለት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ሹሙንና ፡ ረዳቱን ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የመዝገብ ፡ ሠራተኞችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ አጠቃሎ ፡ የሚይዝ ፡ ቃል ፡ ነው ።

BACK



"የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ተካፋይ ፡" ማለት ፡ የአክሲዮን ፡ ባለቤትነትን ፤ የዕዳ ፡ መተማመኛዎችን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የንግድ ፡ በነዶችን ፡ ባለቤትነት ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ ቃል ፡ ነው ።

# አንደኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ።

## ም ዕ ራ ፍ ፩ ፡

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፤ ፩ ። በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ በሕግ ፡ ካልተገለጸ ፤ ክስን ፡ ተቀብሎ ለማከራከር ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ስለመሆኑ ፡**

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ ካልታገዱ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ክስ ፡ ተቀብሎ ፡ ለማከራከር ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

**ቍ ፤ ፪ ። የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ስላገኙ ፡ ጉዳዮች ፡**

(፩) በሕግ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ማንኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክሩን ፡ ተቀብሎ ፡ የመጨረሻ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፤ ቀድሞ ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነው ፡ ክርክር ፡ ሥረ ፡ ነገርና ፡ የተያዘው ፡ ጭብጥ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ከሆነ ፤ በክርክሩ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ ወይም ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ መብት ፡ ያገኙ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በዚያው ፡ ነገር ፡ ሁለተኛ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሌላ ፡ ክርክር ፡ ለማቅረብ ፡ አይችሉም ።

(፪) በቀድሞው ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የማስረጃ ፡ ወይም ፡ የመከላከያ ፡ ወይም ፡ የመቃወሚያ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ ይገባቸው ፡ ነበር ፡ ወይም ፡ ለመሆን ፡ ይችሉ ፡ ነበረ ፡ የሚባሉት ፡ ነገሮችና ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ለሥረ ፡ ነገሩ ፡ መሠረት ፡ በመሆን ፡ ከቀድሞው ፡ ውሳኔ ፡ ጋር ፡ ተቀላቅለው ፡ እንዳለቁ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ናቸው ።

BACK



(፫) በቀድሞው ፡ ክርክርና ፡ ሙግት ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ ዳኝነት ፡ ተጠይቆበት ፡ ጥያቄው ፡ ተቀባይነትን ፡ ሳያገኝ ፡ የታለፈ ፡ እን ደሆነ ፤ በዚህ ፡ ቊጥር ፡ አግባብ ፡ የተጠየቀው ፡ ዳኝነት ፡ እንደ ተከለከለ ፡ ይቆጠራል ።

(፬) ማኅበራዊን ፡ ወይም ፡ ግላዊ ፡ መብትን ፡ መሠረት ፡ በማድ ረግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ክስ ፡ አቅርበው ፡ የተከራ ከሩ ፡ ሲሆኑ ፤ በመብቱ ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆኑ ፡ ቢቀሩም ፡ እንኳ ፤ በዚህ ፡ ቊጥር ፡ አግባብ ፡ በክርክሩ ፡ ከገቡት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ መብት ፡ እንዳገኙ ፡ ይቆጠራሉ ።

ቊ ፡ ፮ ። ዳኝነት ፡ እንዲታይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ይግባኝ ፡ ሊቀርብበት ፡ በሚ ችል ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ ወይም፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ቅሬታውን አቅርቦ ፡ ከማሰማቱ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ፡ ያልተ ፈቀደበት ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ቢሰጥበት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ብቻ ፡ ፍርዱን ፡ ለፈረደው ፡ ወይም ፡ ትእዛዙን ፡ ወይም ፡ ውሳኔውን ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተወሰነውን ፡ ዳኝነት ፡ በመከፈል ፡ አቤቱታ ውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(ሀ) የመጨረሻው ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእ ዛዝ ፡ የተሰጠው ፡ በሐሰት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቀረበውን ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ሐሰተኛ ፡ የምስክርነት ፡ ቃልን ፡ ወይም ፡ መደለያን ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ ጠቀስ ፡ የሆነ ፡ ተግባርን ፡ መሠረት ፡ በማድ ረግ ፡ ሲሆንና ፡ አቤት ፡ ባዩም ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ አስ ፈላጊውን ፡ ትጋት ፡ አድርጎ ፡ ለማወቅ ፡ ያለመቻሉን ፡ ለማስረ ዳት ፡ የቻለ ፡ እንደሆነ ፤

(ለ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ተግባሮች ፡ መፈጸማቸው ፡ ቢገለጽ ፡ ኖሮ ፡ ለፍርዱ ፡ መለወጥ ፡ ወይም ፡ መሻሻል ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆኑ ፡ ይችሉ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለማስረዳት ፡ የቻለ፡ እንደ ሆነ ።

BACK



(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ በደል ፡ ደርሶብኛል ፡ ሲባል ፡ የሚቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ በሚ ቀርብበት ፡ ዓይነት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) በ (ሀ) ፊደል ፡ የተነገሩት ፡ የተንኰል ፡ ተግ ባሮች ፡ መፈጸማቸውን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ትክክለኛ ፡ ማስረጃ ፡ በመ ሐላ ፡ ቃል ፡ ከተደገፈ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ መቅረብ ፡ አ ለበት ። ነገሩ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይለት ፡ የሚጠይቀው ፡ ወገን ፡ ተገኝቷል ፡ የሚለውን ፡ አዲስ ፡ ማስረጃ ፡ ካገኘበት ፡ ወይም ፡ መ ኖሩን ፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ አቤቱ ታውን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) ዳግመኛ ፡ ዳኝነት ፡ እንዲታይ ፡ የቀረበውን ፡ አቤቱታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከመቀበሉ ፡ በፊት ፡ የአቤቱታውን ፡ ግልባጭ ፡ ለባለጋ ራው ፡ በመላክ ፡ አቤቱታው ፡ ሊሰማ ፡ የማይችልበትን ፡ መከራ ከሪያ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ክርክሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ይወስናል ።

(፬) ዳኝነቱ ፡ እንደገና ፡ ሊታይ ፡ ይገባዋል ፡ ወይም ፡ አይገባውም ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅ ረብ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፣ ፺ ። ስለ ፡ ቀደምትነት ።**

(፩) አንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ መታየት ፡ የሚገባው ፡ በአ ንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) አንዱን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ባንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በበ ለጡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዘንድ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ የከሱ ፡ ማመልከቻ ፡ በቀደምትነት ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ ተቆጥሮ ፡ ለክርክሩ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፣ ፺፩ ። በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኙ ፡ ክሶች ።**

(፩) ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይነት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ለውሳኔም ፡ የቀረበው ፡ ጭብጥ ፡ ሥረ ፡ ነገሩ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ እንዲሁም ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡

አንድ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ሲሆኑና ፡ ክሱም ፡ ለባለ ፡ ሥልጣኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ በመሰማት ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ሌላው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቀብሎ ፡ ለማከራከር ፡ አይችልም ። እንዲሁም ፡ ሌሎቹ ፡ ወገኖች ፡ ከዋናዎቹ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለን ፡ በማለት ፡ በዚሁ ፡ ክርክር ፡ በቀረበበት ፡ በአንዱ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችሉም ።

(፪) በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ክስ ፡ ቀርቦ ፡ ጉዳዩ ፡ በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይህንኑ ፡ ነገር ፡ ተቀብለው ፡ ዳኝነት ፡ ከማየት ፡ አይከለከሉም ።

(፫) ለውሳኔ ፡ የቀረቡት ፡ ክርክሮች ፡ በሥረ ፡ ነገርም ፡ ሆነ ፡ በጭብጥ ፡ አንድ ፡ ዓይነትና ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆነው ፡ በተለያዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቀርበው ፡ መታየት ፡ የጀመሩ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ የክርክሮቹ ፡ መነጣጠል ፡ ለዳኝነቱ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ወይም ፡ ለትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ አሰጣጥ ፡ የማይመች ፡ ወይም ፡ የማይገባ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በቍጥር ፡ ፲፩ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፩ እና ፡ ፪፻፴፭ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ እንደነገሩ ፡ አግባብ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥባቸዋል ።

<u>ቍ ፡ ፱ ። ሥረ ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።</u>

(፩) በሥረ ፡ ነገሩ ፡ ለመዳኘት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፩ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻው ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) የቀረበለትን ፡ ክስ ፡ ለመቀበልና ፡ ለመዳኘት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፩ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ መቃወሚያ ፡ ባያቀርብም፡ እንኳ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፭ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ ራሱ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

BACK



ቍ ፡ ፲ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚ ፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

(፩) ክርክሩ ፡ በተነሳበት ፡ ሥፍራ ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያልሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፩ በተመ ለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻው ፡ ተቀባይነት ፡ የለ ውም ፡ ብሎ ፡ መመለስ ፡ አለበት ። ስለሆነም ፡ ከቁጥር ፡ ፲፱ እስከ ፴ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገ ሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ በግዛቱ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ነገሩን ፡ ለመቀበል ፡ የሚችል ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መኖ ሩን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ብቻ ፡ የቀረበለትን ፡ ክስ ፡ አልቀበ ልም ፡ ለማለት ፡ አይችልም ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፵፩ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የግዛት ፡ ክልል ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ ለሚቀር ብለት ፡ መቃወሚያ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ይህም ፡ ውሳኔ ፡ ፍትሕን ፡ የሚያጓድል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይግባኝ ፡ ሊቀርብበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፩ ። ክሶችን ፡ ስለማጣመር ፡

(፩) ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ክሶች ፡ ወይም ፡ ይግ ባኞች ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ በመስማት ፡ ላይ ፡ በሚ ገኙበት ፡ ጊዜና ፡ ተከራካሪዎቹም ፡ ወገኖች ፡ ባንድ ፡ ዘንግ ፡ የተ መደቡ ፡ ሲሆኑ ፡ የቀረበውም ፡ የሕግ ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ የነገር ፡ ጭብጥ ፡ ተመሳሳይና ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሲሆን ፡ ከባለጉዳዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ባመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ነቱን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ ክሶቹ ፡ ተጣምረው ፡ በአንድነት ፡ እን ዲታዩ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ክሶችን ፡ ወይም ፡ ይግባኞችን ፡ ያቀረቡት ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ በአንድ ፡ ዘንግ ፡ የተመደቡ ፡ ሲሆኑና ፡ ለውሳኔም ፡ የቀረበው ፡ የሕግ ፡ ጥያ ቄና ፡ የሥረ ፡ ነገር ፡ ጭብጥ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዘንድ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ተነጣጥለው ፡ የቀረ

ቡት ፡ ክሶች ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢታዩ ፡ ለዳኝነቱ ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑ ፡ የተገመተ ፡ እንደ ሆነ ፡ ክሱን ፡ ከተቀበሉት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንዱ ፡ ማስረጃ ፡ መቀበልና ፡ ማከራከር ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ክሶቹ ፡ ተጠቃለው ፡ በአንድነት ፡ እንዲታዩ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥልኝ ፡ በማለት ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ማንኛውም ፡ ወገን ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

(፫) ተነጣጥለው ፡ የሚሰሙት ፡ ክሶች ፡ የቀረቡት ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ በሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ አቤቱታ ፡ የሚቀርበው ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ክሶቹ ፡ የቀረቡት ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ላስቻሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አቤቱታው ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(፬) ማመልከቻው ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤቱታውን ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ ክሶቹ ፡ ተጠቃለው ፡ የሚታዩበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለይቶ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፭) ተለያይተው ፡ የቀረቡት ፡ ክርክሮች ፡ በይግባኝ ፡ ደረጃ ፡ የቀረቡ ፡ ሆነው ፡ የሕግ ፡ ጥያቄዎቹና ፡ የሥረ ፡ ነገር ፡ ጭብጦቹ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ባንድ ፡ ዘንግ ፡ የተመደቡ ፡ ሲሆኑ ፡ የአፈጻጸማቸው ፡ ሥርዓት ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በ፪ኛው ፡ እና ፡ በ፬ኛው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥሮች ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፪ ፡

## ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሥረ ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ስላላቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡

### ቍ ፡ ፲፱ ። መሠረቱ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለደረጃቸው ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ክርክር ፡ ለመቀበልና ፡ ዳኝነት ፡ ለማየት ፡ ይችላሉ ። ክሱም ፡ የሚቀርበው ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) ይግባኙን ፡ የሚሰሙት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፳፩ ፡ በተ ነገረው ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ።

ቍ ። ፲፫ ፡- ስለወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፲፭/፪/ እና /፫ / እንዲሁም ፡ በቍጥር ፡ ፲፮ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ተመድቧል ።

(ሀ) በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከ፭፻ ፡ የኢት/ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ክስ ፡

(ለ) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከ፩ሺህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የማይ በልጥ ፡ ክስ ።

ቍ ። ፲፬ ፡- ስለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፲፭ /፪/ እና /፫/ እንዲሁም ፡ በቍጥር ፡ ፲፮ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የአውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ተመድቧል ።

(ሀ) በሚንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ከ፭ሺህ ፡ የኢት/ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ክስ ፡

(ለ) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከአሥር ፡ ሺህ ፡ የኢት /ብር ፡ የማ ይበልጥ ፡ ክስ ።

ቍጥር ፡ ፲፭ ፡- ስለ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡

(፩) የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተ መለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ተመድቧል ።

(ሀ) በሚንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ከአምስት ፡ ሺህ ፡ የኢት/ ብር ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ክስ ፡

(ለ) ለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ግምቱ ፡ ከአሥር ፡ ሺህ ፡ የኢት / ብር ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ክስ ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ የግል ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(ሀ) በንግድ ፡ ሕግ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተቋ

BACK



ቋሙ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችና ፡ ድርጅቶች ፡ ስለሚደረጁበት ፡ ወይም ስለሚፈርሱበት ጉዳይ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ለመቀበል ፤

(ለ) ስለሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ ስለ ፡ ኪሣራና ፡ በባሕር፡ ሕግ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ለመቀበል ፤

(ሐ) በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ የሚነሳውን ፡ ክር ክር ፡ ለመቀበል ፤

(መ) በንግድ ፡ ምልክቶች ፡ በፓቴንትና ፡ በድርሰት ፡ ባለ ፡ ሀብ ትነት ፡ ላይ ፡ የሚነሱትን ፡ ክሶች ፡ ለመቀበል ፤

(ሠ) ንብረትን ፡ በማስለቀቅና ፡ ለሕዝባዊ ፡ ጥቅም ፡ በማዋል ፡ ምክንያት ፡ የሚነሱትን ፡ ክርክሮች ፡ ለመቀበል ፤

(ረ) በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፩ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በሥራቸው ፡ ምክንያት ፡ የተሰጣቸውን ፡ አላፊነት ፡ በማጓደል ፡ የሚቀርበውን፡ ክስ ፡ ለመቀበል ፤

(ሰ) ስለ ፡ ዜግነት ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስ ፡ ለመቀበል ፤

(ሸ) ወላጅነትን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ለመቀበል ፤

(ቀ) የግል ፡ ነፃነትን ፡ ወይም ፡ አካልን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ የሚ ቀርበውን ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ ለመቀበል ፤

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ፍርድና ፡ ብይን አፈጻጸም ፡ ጉዳይ ፡ የሚቀርብለትን ፡ አቤቱታ ፡ ለመቀበልና ፡ ተገ ቢውን ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ የግል ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ከፍተ ኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ቍ ፤ ፲፰ ። በገንዘብ ፡ መጠን ፡ የተወሰነ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ።

(፩) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ለ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተመደበው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚበልጥ ፡ ካ ልሆነ ፡ በቀር ፡ ክሱን ፡ ተቀብሎ ፡ ለማከራከር ፡ የሚቻለው ፡ በገን ዘቡ ፡ መጠን ፡ ዳኝነት ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ ነው ።

BACK



(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፴፩ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት፡ የቀረበውን ፡ የገንዘብ ፡ ክስ ፡ ለመቀበል ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚወስነው ፡ ከቁጥር ፡ ፪፻፳፯ እስከ ፡ ፪፻፳፰ የተመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ በመከተልና ፡ በማመል ከቻው ፡ ላይ ፡ የተገለጸውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፫) ክሱ ፡ ቀርቦ ፡ የማስረጃው ፡ መሰማት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የቀረበበትን ፡ ክስ ፡ በከፊል ፡ በማመኑ ፡ ምክ ንያት ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ የተቀነሰ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ በተቀነሰው ፡ መጠን ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያስተላልፈዋል ። ወይም ፡ ራሱ ፡ ማስረጃውን ፡ በመቀበል ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥበት ፡ ይችላል ።

(፬) በመሠረቱ ፡ ክሱ ፡ የቀረበው ፡ ሥልጣኑ ፡ ለሚፈቅድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ የገንዘብ ፡ መጠን ፡ በጊዜው ፡ ኤኮኖሚ ፡ መለዋወጥ ፡ ምክንያት ፡ የቀነሰ ፡ ወይም ፡ የጨመረ ፡ እንደሆነ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ መለዋወጥ ፡ የፍር ርድ ፡ ቤቱን ፡ ሥልጣን ፡ ሊነካው ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፤ ፲፯ ። ተጣምረው ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ክሶች ፤</u>

(፩) አንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ከሳሾች ፡ በአንድነት ፡ ሆነው ፡ ባንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ በሆኑ ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክሶችን ፡ ያቀረቡ ፡ እንደሆነ ፤ ክሱ ፡ ተጣምሮ ፡ እንዲ ታይ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወሰ ነው ፡ በቀረቡት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክሶች ፡ ጠቅላላ ፡ ግምት ፡ መሠረት፡ ነው ።

(፪) በአንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አቤቱታዎች ፡ ቀርበው ፡ ከነ ዚሁ ፡ በከፊል ፡ ዋናውን ፡ ክስ ፡ የሚመለከቱ ፡ በከፊል ፡ ደግሞ ፡ ዋናውን ፡ ክስ ፡ መነሻ ፡ አድርገው ፡ ቅርንጫፍ ፡ ነገሮችን ፡ የሚ መለከቱ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ በተለዋዋጭ ፡ ዳኝነት ፡ ለመጠ የቅ ፡ የቀረቡ ፡ ሲሆኑ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስነው ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ያለውን ፡ አቤቱታ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመ ከተል ፡ ነው ።

BACK



(፫) እንዲሁም ፡ ከሳሹ ፡ ባቀረበው ፡ ክስ ፡ ተከሳሹም ፡ በበኩሉ፡ የተከሳሽ ፡ ከሳሽነት ፡ ክስ ፡ ያቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወሰነው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ያቀረበውን ፡ ከፍተኛ ፡ የሀብት ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ፡፡

ቊ ፤ ፲፰ ፡፡ በገንዘብ ፡ ግምት ፡ ሊወሰን ፡ ስለማይቻል ፡ ሀብት ፤

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፲፭ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፪) እና (፫) የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ በገንዘብ ፡ ግምት ፡ ሊወሰን፡ በማይችል ፡ ሀብት ፡ ምክንያት ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ የሚታየው ፡ ክሱ ፡ በተነሳበት ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ፡፡

## በግዛት ፡ ክልል ፡ ስለሚወሰን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡፡

ቊ ፤ ፲፱ ፡፡ መ ሠ ረ ቱ ፡፡

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቊጥሮች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ክሱን ፡ እንዲቀበሉ ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጣቸው ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ማናቸውም ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ተከሳሹ ፡ በሚኖርበት ፡ ወይም ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ በሚሠራበት ፡ ክፍል ፡ በሚያስችለው ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡

(፪) ቁጥራቸው ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ በሆኑ ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ከተከሳሾቹ ፡ አንዱ ፡ በሚኖርበት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ጥቅሙን ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውንበት ፡ ክፍል ፡ በሚያስችለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡

ቊ ፤ ፳ ፡፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ በሚኖር ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ፡ ክስ ፡፡

(፩) ተከሳሹ ፡ የሚኖረው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ጥቅሙ ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውነው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሹ ፡ በሚመርጠው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ ባንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ፡፡ ስለሆነም ፡ ለክሱ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሲሆንና ፡

BACK



ንብረቱም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ክፍል ፡ በሚያስችለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) ተከሳሹ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖረውና ፡ ሥራውንም ፡ የሚያካሒደው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ ሲሆን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ወይም ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፤ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ክፍል ፡ ባስቻለው ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ቍ ፤ ፳፩ ። በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።

በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ቅርንጫፍ ፡ በሆነ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ በከሳሹ ፡ ምርጫ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከተመለከቱት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላንደኛው ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(ሀ) ከሳሽ ፡ በሚኖርበት ፡ ወይም ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ በሚሠራበት ፡ ክፍል ፡ ላስቻለው ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

(ለ) ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ውል ፡ በተፈረመበት ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ ሊፈጸም ፡ በታቀደበት ፡ ክፍል ፡ ላስቻለው ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡

(ሐ) አላፊነትን ፡ ያስከተለው ፡ ወይም ፡ ለክሱ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ተግባር ፡ በተፈጸመበት ፡ ክፍል ፡ ላስቻለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ቍ ፤ ፳፪ ። በሕግ ፡ በተመሠረቱ ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።

(፩) በአንድ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ የድርጅቱ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ላስቻለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) በማኅበር ፡ ወይም ፡ በኮሚቴ ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ ንብረት ፡ ጥበቃ ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ማኅበሩ ፤ ኮሚቴው ፡ ወይም ፡ ድርጅቱ ፡ በተመሠረተበት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ እንዲመዘገብ ፡ በሕግ ፡ በተወሰነበት ፡ ቦታ ፡ ላስቻለው ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

BACK



(፫) የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ ኩባንያ ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ በፈጸመው ፡ አላፊነት ፡ ምክንያት ፡ የተከሰሰ ፡ እንደሆነ ፡ ክሱ ፡ በዚህ ፡ ቁጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በቁጥር ፡ ፲፬ (፩) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፤ ፲፭ ። በውርስ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።</u>

ሂሣቡ ፡ በመጣራት ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ውርስ ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ የውርሱ ፡ ክፍያ ፡ በተጀመረበት ፡ ቦታ ፡ ለሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፤ ፲፮ ። በውል ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።</u>

(፩) በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ ካል ተገለጸ ፡ በቀር ፤ በውል ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ በከሳሹ ፡ ምርጫ ፡ ውሉን ፡ በተዋዋሉበት ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ በታቀደበት ፡ ክፍል ፡ በሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ማመላለሻን ፡ (ትራንስፖርትን) በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፰ ወይም ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፲፪፶፯ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፫) በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ክሱ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ኩባንያ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ኩባንያው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በተመዘገበበትና ፡ በሚሠራበት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ የተደረገበት ፡ ሀብት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ባስቻለው ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(፬) በመያዣ ፤ በተቀማጭ ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ በተሰጠ ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ በሚነሳ ፡ ክርክር ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ የመያዣው ፡ ወይም ፡ ተቀማጩ ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ የተሰጠው ፡ ሀብት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ላስቻለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፲፯ ። በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።</u>

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፴፩ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተ

BACK



ጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፤

(ሀ) ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ከኪራዩ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ኪራዩ ፤ እንዲሁም ፡ ያላገባብ ፡ ከተወሰደ ፡ አላባ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ያለአላባ ፡ ለማስመለስ ፤

(ለ) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ስለማከፋፈል ፤

(ሐ) በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ መብት ፡ ለማስወሰን ፤

(መ) በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ላስቻለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) በተከሳሹ ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በስሙ ፡ በተያዘው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ደርሷል ፡ በማለት ፡ ክስ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የተጠየቀውን ፡ ዳኝነት ፡ ተከሳሹን ፡ በማዘዝ ፡ ለማስከፈል ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፤ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ላስቻለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፲፱ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

<u>ቍ ፤ ፳፯ ። በተለያየ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።</u>

(፩) የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ አቀማመጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፤ ንብረቱ ፡ በከፊል ፡ በሚገኝበት ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

(፪) ንብረቱ ፡ የሚገኝበት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ አጠራጣሪ ፡ ሲሆን ፤ ክሱ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ የሥልጣኑ ፡ ድርሻ ፡ የሚያሻማ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ ዘርዝሮ ፡ በመዝገብ ፡ ላይ ፡ ካሠፈረ ፡ በኋላ ፡ ክሱን ፡ ተቀብሎ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥበት ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ የሚሰጠው

BACK



ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ እንደተሰጠ ፡ ይቆጠራል ።

(፫) የዚህ ፡ ቁጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክርክሩን ፡ ተቀብሎ ፡ ለመስማት ፡ በንብረቱ ፡ ግምት ፡ መጠን ፡ የመዳኘት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፳፯ ። በሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፤

(፩) በሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ካሣ ፡ የመጠየቅ ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ክሱ ፡ ጉዳቱ ፡ በደረሰበት ፡ ሥፍራ ፡ ለሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በቁጥር ፡ ፲ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) በባሕር ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ የመርከብ ፡ ግጭት ፡ በተነሳ ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ለሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፯ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፳፰ ። በመክሰር ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡

በመክሰር ፡ ምክንያት ፡ ለሚነሳው ፡ ክርክር ፡ ክስ ፡ የሚቀርበው ፡ የከሰረው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት ፡ ላስቻለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፳፱ ። ከአንድ ፡ ስለሚበልጡ ፡ የክስ ፡ ምክንያቶች ፤

በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራዎች ፡ በተፈጠረ ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ እያንዳንዱ ፡ ምክንያት ፡ በተፈጠረበት ፡ ቦታ፡ ለሚያስችለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፴ ። ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ክስና ፡ ስለ ፡ ተከሳሽ ፡ ከሳሽ ፡ ክስ ፡

(፩) ተጨማሪ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ በበኩሉ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ የሚታየው ፡ ዋናውን ፡ ክስ ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ክስ ፡ ለመቀበል ፡ የሚችለው ፡ ዋናውን ፡ ክስ ፡ መሥማት ፡ የጀመረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተጨማሪው ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ በተከሳሹ ፡ ክስ ፡

BACK



ገምት ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፪) የዋናው ፡ ክስ ፡ መነሳት ፡ ወይም ፡ መሠረዝ ፡ ተከሳሹ ፡ በከሳሽነት ፡ የሚያቀርበውን ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተቀብለሎ ፡ እንዳያይ ፡ ሊያገደው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፴፩ ። ክስን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ስለ ፡ ማዛወር ፡

(፩) ፍርድ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ምክንያቶች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤቱታ ፡ ሲያቀርብና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የአቤቱታውን ፡ ተገቢነት ፡ አረጋግጦ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡

(ሀ) ነገሩን ፡ መስማት ፡ የጀመረው ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክሩን ፡ በትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ ሰምቶ ፡ ያላንዳች ፡ አድልዎ ፡ ለመወሰን ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ማስረጃ ፡ ሲያቀርብ ፡ ወይም

(ለ) ዘወትር ፡ የማያጋጥምና ፡ አስቸጋሪ ፡ ክርክር ፡ የሚያስነሳ ፡ የሕግ ፡ ጥያቄ ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ ሲችል ፡ ወይም

(ሐ) በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ቢሰጥ ፡ ለሁለቱም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖችና ፡ ለምስክሮቹም ፡ ምቹ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠቱ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ትክክለኛን ፡ ፍርድ ፡ ለማስገኘት ፡ የሚያስችል ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተነገረውን ፡ ይገባኛ ፡ የማይባልበትን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(ሀ) በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ ለማከራከር ፡ የሚችለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ እንዲቀበል ፡ በማዘዝ ፡ ወይም

(ለ) ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወደርሱ ፡ እንዲተላለፍለት ፡ አዞ ፡ ዳኝነቱን ፡ ለማየት ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያመለከተ ፡

BACK



እንደሆነ ፡ ነገሩን ፡ መስማት ፡ ከጀመረው ፡ ችሎት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ችሎት ፡ እንዲዛወር ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ ትእዛዙን ፡ ለመስጠት ፡ የሚቻለው ፡ አመልካቹ ፡ ነገሩ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ችሎት ፡ እንዲዛወርለት ፡ ያመለከተው ፡ በማስረጃ ፡ የተ ደገፈ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ለማቅረብ ፡ ሲችል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

# ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## በከሳሽነት ፡ ወይም ፡ በተከሳሽነት ፡ የሙግት ፡ ተካፋይ ፡ ስለመሆን ።

ቍ ፡ ፴፪ ። የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ።

(፩) በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የዚህ ፡ ሕግ ፡ አነጋገር ፡ በይግባኝ ፡ የሚቀርቡትንም ፡ ክር ክሮች ፡ እንደነገሩ ፡ አግባብ ፡ አጠቃሎ ፡ የሚመለከት ፡ በመ ሆኑ ፡ ከሳሽ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ይግባኝ ፡ ባይን ፡ ተከሳሽ ፡ የሚ ለው ፡ ቃል ፡ መልስ ፡ ሰጭን ፡ ክስ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ይግባኙን ፡ አጠቃሎ ፡ የሚይዝ ፡ ይሆናል ።

### ምዕራፍ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።

ቍ ፡ ፴፫ ። ከሳሽ ፡ የመሆን ፡ ችሎታ ።

(፩) በሕግ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ክስ ፡ ለማቅ ረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ለክሱ ፡ መነሻ ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ በተመሠረተ በት ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይ ፈቀድለትም ።

(፫) ከሳሽ ፡ ከተከሳሽ ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ መ ብት ፡ በማረጋገጥ ፡ አቤቱታ ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

BACK



ቍ ፡ ፴፬ ። ስለ ፡ ውክልና ፡ ስለ ፡ እንደራሴነት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሞግዚትነት ።

(፩) በሕግ ፡ ችሎታ ፡ የላቸውም ፡ የተባሉ ፡ ሰዎች ፡ በሞግዚታቸው ፡ ወይም ፡ በተሾመላቸው ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ አማካይነት ፡ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ ለመከሰስ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የሕግ ፡ ችሎታ ፡ የለውም ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ሞግዚት ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ ያልተሾመለት ፡ እንደሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ እስኪሾምለት ፡ ድረስ ፡ ክርክሩ ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ ታግዶ ፡ ይቆያል ።

(፫) ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ሊከሱ ፡ ወይም ፡ ሊከሰሱ ፡ ይችላሉ ።

(፬) የባሕርን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ የሚሰጠው ፡ ውክልና ፡ ወይም ፡ እንደራሴነት ፡ የሚፈጸመው ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፭) በንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ በኑዛዜ ፡ አስፈጻሚ ፡ በአደራ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ ሥር ፡ በሚተዳደር ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ በተጠቃሚዎችና ፡ በሌላ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚው ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂው ፡ ስለዋናዎቹ ፡ ባለመብቶች ፡ ሆነው ፡ ለመከራከር ፡ ይችላሉ ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተለይ ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ዋናዎቹ ፡ ባለጥቅሞች ፡ በክርክሩ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፴፭ ። ከሳሾች ፡ የኅብረት ፡ ክስ ፡ ስለሚያቀርቡበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ዓይነታቸው ፡ አንድ ፡ በሆኑ ፡ በብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ የተመሠረተ ፡ ክስ ፡ ሲያቀርቡና ፡ ምክንያቱም ፡ እያንዳንዱን ፡ ከሳሽ ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፡ ከሳሾቹም ፡ ተነጣጥለው ፡ በየራሳቸው ፡ ስም ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችሉ ፡ ሲሆኑ ፡ ለክሱ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡

BACK


መብት ፡ የጋራ ፡ ወይም ፡ የየራሳቸው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በሚቀ ርበው ፡ ክስ ፡ ሊወሰን ፡ የሚችለው ፡ የሕግና ፡ የሥረ ፡ ነገር ፡ ጭብጥ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ከሆነ ፡ ከሳሾቹ ፡ በኅብረት ፡ ሆነው ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ብቻ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፴፮ ። ተከሳሾችን ፡ በአንድነት ፡ አጣምሮ ፡ ስለመክሰስ ።

(፩) አንድ ፡ የክስ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ተከሳሾችን ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆንና ፡ ተከሳሾችንም ፡ በኅብረት ፡ ወይም ፡ በግንባር ፡ ለመከ ሰስ ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ እንዲሁም ፡ በአንድነትም ፡ ሆነ ፡ በተነ ጣላ ፡ ቢከሰሱ ፡ የሚወሰነው ፡ የሕግ ፡ ጥያቄና ፡ የሥረ ፡ ነገር ፡ ጭብጥ ፡ አንድ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሾችን ፡ በአንድነት ፡ አጣምሮ ፡ ለመክሰስ ፡ ይቻላል ።

(፪) በአንድ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በሚተላለፍ ፡ የንግድ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ በተመሠረተ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚ ቻል ፡ ሲሆንና ፡ ከሳሹም ፡ ተከሳሾችን ፡ በኅብረት ፡ ወይም ፡ በም ትክነት ፡ ወይም ፡ በተለዋዋጭ ፡ ወይም ፡ በነፍስ ፡ ወከፋ ፡ ለመ ክሰስ ፡ የሚችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎቹን ፡ ተከሳሾች ፡ በአንድ ነት ፡ አጣምሮ ፡ ሊከሳቸው ፡ ይችላል ።

(፫) ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ጠባ ቂዎች ፡ ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚዎች ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የሚ ጠብቁትን ፡ ንብረት ፡ የሚመለከት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከነዚህ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ በሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ሌሎቹም ፡ ተከሳሽ ፡ መሆን ፡ አለባ ቸው ።

(፬) ከሳሹ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ለማስለቀቅና ፡ ለመረ ከብ ፡ ክስ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በማናቸው ፡ ምክንያትና ፡ ሁኔታ ፡ በን ብረቱ ፡ ላይ ፡ ሠፍረው ፡ የሚገኙትን ፡ ሁሉ ፡ አጣምሮ ፡ መክሰስ ፡ ይገባዋል ።

(፭) ከሳሹ ፡ መብቱን ፡ ማግኘት ፡ የሚገባው ፡ ከየትኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ላይ ፡ እንደሆነ ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ ያጋ ጠመው ፡ ሲሆን ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ በኅብረት ፡ በመክሰስ ፡ አላፊነቱ ፡ የሚመለከተው ፡ የት ኛውን ፡ እንደሆነ ፡ ተለይቶ ፡ እንዲወሰንለት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

(፫) በዚህ ፡ ቁጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ በሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ ከብዙዎቹ ፡ ተከሳሾች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ቁጥራቸው ፡ ከአንድ ፡ የበለጡት ፡ ተከሳሾች ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ የተጠየቀው ፡ ሀብት ፡ በሙሉ ፡ አይመለከተንም ፡ በማለት ፡ ከክሱ ፡ ነፃ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

<u>ቍ ፡ ፴፯ ። ባንድ ፡ ወይም ፡ በብዙዎች ፡ ተከራካሪዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈረድላቸው ፡ ወይም ፡ ስለሚፈረድባቸው ፡ ፍርድ ።</u>

ፍርድ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

ሀ/ ፍርድ ፡ ለሚገባቸው ፡ ላንድ ፡ ወይም ፡ ለብዙዎች ፡ ከሳሾች ፡ የሚገባውን ፡ ፍርድ ፡ በመስጠት ፡

ለ/ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ተከሳሾች ፡ በአላፊነት ፡ ስለሚጠየቁበት ፡ ክስ ፡ እንደየአላፊነታቸው ፡ መጠን ፡ እንዲፈረድባቸው ፡ በማድረግ ።

<u>ቍ ፡ ፴፰ ። በነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ስለመማገት ።</u>

(፩) ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ክስ ፡ የጥቅም ፡ ግንኙነት ፡ ሲኖራቸው ፡ ለየብቻ ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ ሊከሱ ፡ ወይም ፡ ሊከሰሱ ፡ ይችላሉ ። ስለሆነም ፡ ስለጋራ ፡ ጥቅማቸው ፡ ለመከላከል ፡ በወኪልነት ፡ እንዲከሱ ፡ ወይም ፡ በተከሳሽነት ፡ እንዲከላከሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈቅድላቸው ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፩) በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ በነገረፈጅ ፡ ወይም ፡ በወኪል ፡ አማካይነት ፡ የከሰሰ ፡ ወይም ፡ የተከሰሰ ፡ ራሱም ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ለመከራከር ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፴፱ ። ባንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ተጣምሮ ፡ መክሰስ ፡ የሚገባውን ፡ ስለመተውና ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ የማይገባውን ፡ ሰው ፡ አጣምሮ ፡ ስለመክሰስ ።</u>

(፩) ባንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ተጣምሮ ፡ መክሰስ ፡ የሚገባውን ፡ ሰው ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለማግባት ፡ ወይም ፡ ሊከሰስ ፡ የማይገባውን ፡ አጣምሮ ፡ የመክሰስ ፡ ተግባር ፡ ከሳሹ ፡ ወገን ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ አያደርገውም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረቡትን ፡ ተከሳሾች ፡

ጉዳይ ፡ ተመልክቶና ፡ በከሳሽ ፡ የቀረበውን ፡ አቤቱታ ፡ መርምሮ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ፡፡

(፪) በክሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚያገባቸው ፡ ወገኖች ፡ ሳይገቡ ፡ ቀርተዋል ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ የማያገባቸው ፡ ወገኖች ፡ ደግሞ ፡ በክሱ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነዋል ፡ በማለት ፡ የሚቀርበው ፡ መቃወሚያ ፡ ሁሉ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚገባው ፡ ክርክር ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ መሆን ፡ አለበት ፡፡ ክርክሩ ፡ ከተጀመረ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ የሚቀርበው ፡ መቃወሚያ ፡ ተቀባይነትን ፡ አያገኝም ፡፡

<u>ቍ ፡ ፵ ፡፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖችን ፡ ስለመጨመር ፡ ወይም ፡ ስለመተካት ፡፡</u>

(፩) በቅን ፡ ልቦና ፡ በተደረገ ፡ ስህተት ፡ ምክንያት ፡ ከሳሽ ፡ መሆን ፡ በማይገባው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ አጠራጣሪ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ የክሱ ፡ አቀራረብ ፡ በተንኰል ፡ ያልተደረገ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ በተሳሳተው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ፋንታ ፡ የተገቢው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ተተክቶ ፡ እንዲቀርብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲተካ ፡ ለማዘዝና ፡ ይህም ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ጉዳይ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የታየውን ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ፡፡

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ከባለ ፡ ጉዳዮቹ ፡ የሚቀርብለትን ፡ ክርክር ፡ በመመልከት ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ የከሳሽ ፡ ወይም ፡ የተከሳሽ ፡ ስም ፡ በማይገባ ፡ የተጠቀሰ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ ያላግባብ ፡ የተጻፈው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ እንዲሠረዝና ፡ በምትኩም ፡ በጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ እንዲተካ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፡፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ውሳኔው ፡ አሰጣጥ ፡ አስፈላጊና ፡ ምቹ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ ማንኛውም ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እንዲተካ ፡ ወይም ፡ አባሪ ፡ ሆኖ ፡ በነገሩ ፡ እንዲገባ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፡፡ ስለሆነም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኑን ፡ ሳይገልጽ ፡ በከሳሽነት ፡ ተባባሪ ፡ እንዲሆን ፡ አይገደድም ፡፡

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩ ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመራ ፡ካላደረገ ፡ በቀር ፡ ተከሳሽ ፡ በተጨመረ ፡ ወይም ፡ በተተካ ፡ ጊዜ ፡ የክሱ

BACK



ማመልከቻ ፡ በተሻሻለ ፡ ሁኔታ ፡ ተለውጦ ፡ ግልባጩ ፡ ለተጨመረው ፡ ወይም ፡ ለተተካው ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲደርሰው ፡ መደረግ ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ የተሻሻለው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ ለቀድሞው ፡ እንዲደርሰው ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፴፫ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለመክሰስ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ሶስተኛ ፡ ሰው ፡ እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ በከሳሽ ፡ ወይም ፡ በተከሳሽ ፡ እግር ፡ ተተክቶ ፡ ለመከራከር ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ ለመጠቀም ፡ የሚቻለው ፡ የቀድሞው ፡ ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፫) ይግባኝ ፡ በቀረበለት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ የነበረ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በይግባኙ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆን ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ የይግባኙ ፡ ውጤት ፡ የሚመለከተው ፡ መሆኑን ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲረዳው ፡ የይግባኙን ፡ ክርክር ፡ መስሚያ ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ በማስተላለፍ ፡ ተካፋይ ፡ ያልሆነው ፡ ሰው ፡ በመልስ ፡ ሰጭነት ፡ አባሪ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፵፩ ። የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ።

(፩) ባንድ ፡ ክስ ፡ ሌሎች ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ ማናቸውም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በጉዳዩ ፡ ያገባኛል ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፡ ከፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ በፊት ፡ ጣልቃ ፡ ገብ ፡ ሆኖ ፡ ሊመከራከር ፡ ይችላል ።

(፪) የጣልቃ ፡ ገብነቱ ፡ ማመልከቻ ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ያገባኛል ፡ የሚልበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚዘረዝርና ፡ በተለይም ፡ የመብቱን ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) የጣልቃ ፡ ገብነቱ ፡ መብት ፡ ተወስኖ ፡ አመልካቹ ፡ በክርክሩ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ የተፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ የጣልቃ ፡ ገቡ ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ እስኪሰጣቸው ፡ ድረስ ፡ ክርክሩ ፡ ታግዶ ፡ ይቆያል ።

(፬) የጣልቃ ፡ ገብ ፡ ወገን ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ በራሱ ፡ ጉድ ለት ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ሳይደርሳቸው ፡ የቀረ ፡ እንደ ሆነ ፡ ጣልቃ ፡ ገቡ ፡ ነገሩን ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እንደተወው ፡ ተቆጥሮ ፡ መብቱ ፡ ይሠረዝበታል ።

(፭) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻ ፶፫ እስከ ፡ ፪፻ ፶፱ ፡ ለተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቃራኒ ፡ አይሆ ንም ።

<u>ቍ ፡ ፴፪ ። ስለዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ።</u>

ሕግ ፡ የሚፈቅድለት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በነገሩ ፡ ጣልቃ ፡ ገብ ፡ ሆኖ ፡ ለመከራከር ፡ ይችላል ። በተለይም ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ በጣልቃ ፡ ገብነት ፡ መከራከር ፡ አለበት ።

(ሀ) ስለ ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ /የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቁጥር ፡ ፩፻፲፮ — ፩፻፳፪ እና ፡ ፩፻፶፮ /

(ለ) ችሎታ ፡ ስለማጣት ፡ / የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቁጥር ፡ ፪፻፴፩ — ፫፻፶፩ — ፫፻፸፯ /

(ሐ) ስለጋብቻ ፡ / የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቁጥር ፡ ፰፻ ፺፪—፲፻፳—፲፻፱ እና ፡ ፲፻፲፪/

(መ) ስለ ፡ ኪሣራ ፡ /የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፱፻፸፭—፱፻፸፰ ፡ ፱፻፹ ፡ ሺ፩ ፡ እና ፡ ሺ፲፯ / ።

<u>ቍ ፡ ፴፫ ። ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ በክስ ፡ ውስጥ ፡ ስለማግባት ።</u>

(፩) ተከሳሽ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በተከሰሰበት ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ያልሆነ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ድርሻ ፡ ካሣውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ የሌለው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባበትንና ፡ ድርሻው ፡ የሆነ ውን ፡ ካሣ ፡ የሚከፍልበትን ፡ ምክንያት ፡ የድርሻውንም ፡ ልክ ፡ ጨምሮ ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ይግባኝ ፡ ብሎ ፡ በመግለጽ ፡ ማመልከቻውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭና ፡ ለክሱ ፡ የተ

ሰጠው ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ እንዲያደርሰው ፡ ይታዘዛል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡ ከተላከለት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

(፫) በሦስተኛው ፡ ወገንና ፡ በተከሳሹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የመብት ፡ መስተካከል ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመሰለው ፡ ሁኔታ ፡ ሊወስነው ፡ ይችላል ።

(፬) አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ተከሳሽ ፡ ድርሻውን ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ በሚያመለክትበት ፡ ጊዜ ፡ አፈጻጸሙ ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ። ስለሆነም ፡ በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ አመልካቹ ፡ በሌላው ፡ ተከሳሽ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የመከሰስ ፡ መብት ፡ የሚነካበት ፡ አይሆንም ።

<u>ቍ ፡ ፵፬ ።የንግድ ፡ ሸሪኮችን ፡ በሚነግዱበት ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ስም ፡ ስለ ፡ መክሰስ ፤</u>

ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ የሚበልጡ ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ አቋቋመው ፡ በሽርክና ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ በሽርክና ፡ የተቋቋመው ፡ ንግድ ፡ በሚጠራበት ፡ ስም ፡ ሊከሱ ፡ ወይም ፡ ሊከሰሱ ፡ ይችላሉ ። በዚህ ፡ ስም ፡ ሊከሱ ፡ ወይም ፡ ሊከሰሱ ፡ የሚችሉት ፡ ለክሱ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ የተነሳው ፡ ሽርክናው ፡ ጸንቶ ፡ በኖረበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ በጉዳዩ ፡ ያገባኛል ፡ የሚል ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ በተነሳበት ፡ ጊዜ ፡ በሽርክና ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሲጠይቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጠየቀው ፡ ጉዳይ ፡ ተጣርቶና ፡ ተረጋግጦ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሊያዝለት ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፵፭ ። የንግድ ፡ ሸሪኮችን ፡ ስም ፡ ስለመግለጽ ፤</u>

(፩) በሽርክና ፡ በተቋቋመ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ስም ፡ ክስ ፡ የቀረበ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሾቹ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጆቻቸው ፡ ተከሳሾቹ ፡ ወገኖች ፡ የንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ ሸሪኮች ፡ እነ ፡ ማን ፡ እንደሆኑ ፡ እንዲገለጽላቸው ፡ በጽሑፍ ፡ በጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ የሸሪኮቹን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ የሚገልጸውን ፡ ዝርዝር ፡ በተጠየቀው ፡ መሠረት ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ።

BACK



(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ከሳሾች ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጆቻቸው ፡ ተፈላጊውን ፡ ጥያቄ ፡ ባለመመለሳቸው ፡ ክርክሩ ፡ እንዲቆም ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ መስሎ ፡ እስከታየው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ነገሩን ፡ በቀጠሮ ፡ ሊያቆየው ፡ ይችላል ።

(፫) የተጠየቀው ፡ የሽሪኮች ፡ የስም ፡ ዝርዝርና ፡ አድራሻ ፡ በሚገባ ፡ ተገልጾ ፡ ለከሳሾች ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ስማቸው ፡ አስቀድሞ ፡ እንደተመዘገበ ፡ ተቆጥሮ ፡ በመጀመሪያው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ ይቀጥላል ። ስለሆነም ፡ ክሱ ፡ የሚመራውና ፡ ተፈጻሚነትንም ፡ የሚያገኘው ፡ በንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፴፯ ። በራሱ ፡ ስም ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በሚነግድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።

በራሱ ፡ ስም ፡ ሳይሆን ፡ ስለሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የሚሠራው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ በሚጠራበት ፡ ስም ፡ ሊከሰስ ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ሁሉ ፡ እንደተገቢነቱ ፡ መጠን ፡ በራሳቸው ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በሚነግዱ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፴፰ ። በንግድ ፡ ሽሪኮች ፡ መካከል ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ስለሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ የተነገረውና ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ስለሚከሱበትና ፡ ስለሚከሰሱበት ፡ የተደነገገው ፡ በሽሪኮች ፡ መካከል ፡ በሚነሳው ፡ ክርክር ፡ ምክንያት ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ስለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ከሽሪኮቹ ፡ መካከል ፡ ተነጥለው ፡ ሽሪክ ፡ በሆኑበት ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ በሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ መክሰር ።

**ቍ ፡ ፵፰ ። ስለ ፡ ተከራካሪው ፡ ወገን ፡ መሞትና ፡ ስለ ፡ ክሱ ፡ ያለመቋረጥ ።**

(፩) ክርክሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ የሚያስችለው ፡ መብት ፡ የማያቋርጥ ፡ ከሆነ ፡ የከሳሽ ፡ ወይም ፡ የተከሳሽ ፡ መሞት ፡ ክርክሩ ፡ እንዲቆም ፡ አያደርገውም ።

(፪) በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የከሳሾች ፡ ወይም ፡ የተከሳሾች ፡ ቍጥር ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነና ፡ በሕይወት ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ያሉት ፡ ከሳሾች ፡ ክሱን ፡ የመቀጠል ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ከተከሳሾቹ ፡ ያንዱ ፡ መሞት ፡ በቀሩት ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ የመክሰስን ፡ አላፊነት ፡ ያላስቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ያጋጠመውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመመዝገብ ፡ የቀሩት ፡ ከሳሾች ፡ ሲያመለክቱ ፡ ክሱ ፡ በሕይወት ፡ ባሉት ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ እንዲቀጥል ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፵፱ ። ከከሳሾቹ ፡ ያንዱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ የበለጡት ፡ መሞት ።**

(፩) ቍጥራቸው ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ከሆኑ ፡ ከሳሾች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ የበለጡ ፡ ከሳሾች ፡ የሞቱ ፡ እንደሆነና ፡ የነርሱ ፡ መብት ፡ ለቀሪው ፡ ወይም ፡ ለቀሪዎቹ ፡ የሚተላለፍ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሕይወት ፡ የነበረው ፡ አንዱ ፡ ከሳሽ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነና ፡ የክሱ ፡ መብት ፡ ለሌላ የሚተላለፍ ፡ ሲሆን ፡ እንዲሁም ፡ በሕይወት ፡ ያሉት ፡ ከሳሾች ፡ ሲያመለክቱ ፡ የሟቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ተተክቶ ፡ ክሱን ፡ እንዲቀጥል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ ክሱን ፡ ለመቀጠል ፡ መብት ፡ አለን ፡ የሚሉት ፡ ወገኖች ፡ ዋናው ፡ ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ከሳሾች ፡ በሞቱ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ክሱን ፡ ለመቀጠል ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ ሳያመለክቱ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ የተጀመረው ፡ ክርክር ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።

በክሱም ፡ ምክንያት ፡ ወጭ ፡ የተደረገው ፡ ገንዘብና ፡ ማንኛ ውም ፡ ሌላ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ ተከሳሹ ፡ ያመለከተ ፡ እን ደሆነ ፡ ሊከፈል ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ የሚገምተውን ፡ ወጭ ፡ ሁሉ ፡ ከሟቹ ፡ ሀብት ፡ እንዲከፈል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ አይመለከትም ።

ቍ ፡ ፶ ። ከተከሳሾቹ ፡ ያንዱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ የበለጡት ፡ መሞት ።

(፩) ከተከሳሾቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ቍጥራቸው ፡ ካንድ ፡ የበለጠ ፡ ተከሳሾች ፡ ቢሞቱና ፡ የመከሰሱ ፡ አላፊነት ፡ በሕይወት ፡ ባለው ፡ ወይም ፡ ባሉት ፡ ተከሳሾች ፡ የሚተላለፍ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ እርሱም ፡ የሞተ ፡ እንደ ሆነ ፡ የክሱም ፡ አላፊነት ፡ ነዋሪ ፡ ሆኖ ፡ የሚቆይ ፡ ሲሆንና ፡ አግ ባብ ፡ ያለው ፡ ወገን ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብ ፡ የሟቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ተተክቶ ፡ ክርክሩን ፡ እንዲቀጥል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) በሟቹ ፡ እግር ፡ ተተክቶ ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲሆን ፡ የተደረገው ፡ ሰው ፡ ሕጋዊውን ፡ መንገድ ፡ በመከተል ፡ ለቀረበው ፡ ክስ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ መከላከያ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ አይመ ለከትም ።

ቍ ፡ ፶፩ ። ከንግድ ፡ ሸሪኮች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚኖር ፡ የክስ ፡ መብት ።

(፩) ሁለት ፡ ወይም ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ሸሪኮች ፡ በሽርክና ፡ በተቋቋመው ፡ ንግድ ፡ ስም ፡ ሊከሱ ፡ ወይም ፡ ሊከሰሱ ፡ የሚችሉ ፡ ሲሆንና ፡ ከሸሪኮቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑት ፡ ክሱ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ ተጀምሮ ፡ በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ ቢሞቱ ፡ የሟቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ተተክቶ ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፡ አስ ፈላጊ ፡ አይሆንም ።

BACK



(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቊጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ የሟቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ሊሠራባቸው ፡ የሚችልበትን ፡ መብት ፡ አያስቀርበትም ፡ ይኸውም

(ሀ) የክሱ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ ለመከራከር ፡ እንዲፈቀድለት ፡ የማመልከት ፡ መብቱን ፡

(ለ) በሕይወት ፡ ባለው ፡ ወይም ፡ ባሉት ፡ ሸሪኮች ፡ ላይ ፡ ሟቹ ፡ የነበረውን ፡ መብት ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ለማስከበር ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

<u>ቊ ፡ ፶፪ ። ስለ ፡ ሟቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ።</u>

ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ ለነበረው ፡ ሟች ፡ የንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ የቀረበው ፡ እንደራሴ ፡ ስለ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪነቱ ፡ ሥልጣን ፡ በቂ ፡ ያለመሆን ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ክርክር ፡ አስቀድሞ ፡ መወሰን ፡ አለበት ። አስፈላጊ ፡ መስሎም ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ለቀረበው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ስለሟቹ ፡ ሆኖ ፡ የሚከራከር ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ።

<u>ቊ ፡ ፶፫ ። ክርክሩ ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ከተከራካሪ ዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ የበለጠ ፡ ብዛት ፡ ያላቸው ፡ ስለ ፡ መሞታቸው ።</u>

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ያንዱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ የበለጠ ፡ ቊጥር ፡ ያላቸው ፡ መሞት ፡ የመክሰስን ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የመከሰስን ፡ አላፊነት ፡ የሚያስቀረው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ሙግቱ ፡ ተጠናቆ ፡ ለፍርድ ፡ ብቻ ፡ ያደረ ፡ ሲሆን ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ብዙዎቹ ፡ ቢሞቱም ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዳሉ ፡ ያህል ፡ በመቁጠር ፡ የፍርዱን ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ አለበት ። ፍርዱም ፡ እንደማናቸውም ፡ መደበኛ ፡ ፍርድ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፶፩ ። ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ስለማይችል ፡ ከሳሽ ፡ (ስለ ፡ ከሠረ ፡ ከሳሽ ።)

(፩) ከሳሽ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ክርክሩን ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ኪሣራ ፡ የደረሰበት ፡ እንደሆነ ፡ ከኪሣራው ፡ የተረፈውን ፡ ንብረት ፡ ተረክቦ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ እንዲያከፋፍል ፡ የታዘዘው ፡ ሰው ፡ በከሠረው ፡ ከሳሽ ፡ ተተክቶ ፡ ነገሩን ፡ ለመቀጠል ፡ የሚችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የከሳሹ ፡ መክሰር ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ክሱ ፡ እንዲቋረጥ ፡ አያደርገውም ። ስለሆነም ፡ የከሰረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ክርክሩ ፡ ለሚያስከትለው ፡ ኪሣራ ፡ በቂ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ወይም ፡ በነገሩ ፡ ለመግፋት ፡ ካልፈቀዱ ፡ ክሱ ፡ መቆም ፡ አለበት ።

(፪) የከሰረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የኪሣራ ፡ መያዣ ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ታዞ ፡ ትእዛዙን ፡ ሳይፈጽም ፡ ወይም ፡ በቸልተኛነት ፡ ክርክሩን ፡ ሳይከታተል ፡ ቢቀር ፡ ተከሳሹ ፡ ይህንኑ ፡ ገልጾ ፡ በማመልከት ፡ ክሱ ፡ እንዲሠረዝለት ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ የገመተውን ፡ ኪሣራ ፡ በመወሰን ፡ ክሱን ፡ ሠርዞ ፡ የተወሰነው ፡ ኪሣራ ፡ ከከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈል ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ንዑስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ነገሮች ፡ አይመለከቱም ።

ቍ ፡ ፶፪ ። የክስ ፡ መቅረት ፡ ወይም ፡ መሠረዝ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ የቀረ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ እንደሆነ ፡ የቀረው ፡ ወይም ፡ የተሠረዘው ፡ ክስ ፡ ተመሥርቶ ፡ በነበረበት ፡ ምክንያት ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘውን ፡ ክስ ፡ እንደገና ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ አይቻልም ።

(፪) ከሳሹ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ከሳሽ ፡ የነበረው ፡ የሟቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ባለአደራ ፡ ወይም ፡ የከሠረው ፡ ከሳሽ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የዋናው ፡ ከሳሽ ፡ መብት ፡ ተላልፎልኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ክሱ ፡ ቀሪ ፡ በሆነ ፡

ወይም ፡ በተሠረዘ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ እንዲቀጥል ፡ ወይም ፡ ስርዞ ፡ እንዲነሳለት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

(፫) ክሱ ፡ ቀሪ ፡ የሆነው ፡ ወይም ፡ የተሠረዘው ፡ በከሳሹ ፡ ጉድለት ፡ ያለመሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ ስላደረሰው ፡ ኪሣራ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ወስኖ ፡ የቀረው ፡ ወይም ፡ የተሠረዘው ፡ ክስ ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፵፯ ። የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ በክርክር ፡ ያለውን ፡ የጥቅም ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

አንድ ፡ ክርክር ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ መብት ፡ በስጦታ ፡ በውርስ ፡ በግዢ ፡ በዳረጎት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ተላልፎልኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ጥቅሙን ፡ በማመልከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ በክርክሩ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ በከሳሽነት ፡ ወይም ፡ በተከሳሽነት ፡ የክርክሩ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ወኪሎችና ፡ ስለ ፡ ተማጋቾች ።

**ቍ ፡ ፵፰ ። መ ሠ ረ ቱ ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፳፭ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ ወይም ፡ የአቤት ፡ ባዩ ፡ ለክርክር ፡ መቅረብ ፡ በተለይ ፡ ባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲከራከር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካላዘዘ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚያስገድድ ፡ ሕግ ፡ ከሌለ ፡ ራሱ ፡ ለመቅረብ ፡ የማይችል ፡ ወይም ፡ የማይፈቅድ ፡ ሲሆን ፡ ነገሩን ፡ ለማስረዳት ፡ ለመከራከር ፡ ለሚጠየቀው ፡ ሁሉ ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ በዋናው ፡ ባለ ፡ ጉዳይ ፡ ተተክቶ ፡ በነገረ ፡ ፈጅነት ፡ በወኪልነት ፡ በጠበቃነት ፡ እንዲከራከር ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

BACK



**ቊ ፡ ፶፰ ። ስለ ፡ ነገረ ፡ ፈጆችና ፡ ስለ ፡ ወኪሎች ፡ በጠቅላላው ።**

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ በወኪልነት ፡ ወይም ፡ በነገረ ፡ ፈጅነት ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፤ ለመከራከር ፤ ለመሟገትና ፡ ነገሩን ፡ ለመከታተል ፡ የሚችሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

(ሀ) የዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ ባለቤት ፤ ወንድም ፤ እህት ፤ ልጅ ፤ አባት ፤ አያት ፤ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ለውክልናው ፡ ወይም ፡ ለነገረ ፡ ፈጅነት ፡ አበል ፡ ሳይሰጣቸው ፡ ለመከራከር ፡

(ለ)የክሱ ፡ ወይም ፡ የአቤቱታው ፡ ማመልከቻ ፡ በሚቀርብበት ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የግዛት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ በማይገኙ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ የንግድ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ የሚያካሂዱ ፡ ሰዎች ፡ በዋናዎቹ ፡ ባለመብቶች ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ የክስ ፡ ወይም ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻ ፡ በማቅረብ ፡ የነገረ ፡ ፈጅነት ፡ ወይም ፡ የወኪልነት ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖራቸው ፡ ሊከራከሩ ፡ ይችላሉ ። ስለሆነም ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉት ፡ ዋናዎቹ ፡ ባለመብቶች ፡ በራሳቸው ፡ ሥም ፡ ሆኖ ፡ የሚከራከር ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ በተለይ ፡ ያልወከሉ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፶፱ ። ለመንግሥት ፡ ነገረፈጅ ፡ ሆነው ፡ እንዲከራከሩ ፡ ስለተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ።**

የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ ስለመንግሥት ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክር ፡ እንዲያቀርብ ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲከራከር ፤ ነገሩን ፡ እንዲከታተል ፤ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፡ እንደተወከለ ፡ እንደራሴ ፡ ይቆጠራል ።

**ቊ ፡ ፷ ። በመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።**

(፩) መንግሥት ፡ በሾመው ፡ ወይም ፡ በቀጠረው ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ የቀረበበትን ፡ ክስ ፡ ሊከላከልለት ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ ተከ

ሳሹ ፡ ሆኖ ፡ እንዲከላከል ፡ የታዘዘው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ቀርቦ ፡ መልስ እንዲሰጥ ፡ መወከሉን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያስታውቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የውክልናውን ፡ ማስረጃ ፡ ተቀብሎ ፡ እንዲመዘገብ ፡ ያደርጋል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ እንደተነገረው ፡ የመንግሥት ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ስለ ፡ ተከሳሹ ፡ መወከሉን ፡ ከቀነ ፡ ቀጠሮው ፡ በፊት ፡ ያልገለጸ ፡ እንደሆነ ፡ በመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ በግል ፡ ከሳሾች ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ክስ ፡ ተቀጥሮ ፡ ነገሩ ፡ ይቀጥላል ።

ቍ ፡ ፷፩ ። ለጦር ፡ ኃይል ፡ አባሎች ፡ ስለሚወከሉ ፡ ነገረፈጆች ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎች ።

(፩) የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የወታደራዊ ፡ አገልግሎቱ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቅረብ ፡ የማያስችለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ራሱ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ ለመቀጠል ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ለመከላከል ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ በምትኩ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ወክሎ ፡ በነገረ ፡ ፈጂ ፡ አማካይነት ፡ ለመከራከር ፡ ይችላል ።

(፪) የውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጠው ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ መኰንኖች ፡ ፊት ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ።

(ሀ) በአዛዥ ፡ መኰንን ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ ባለጉዳዩ ፡ አዛዥ ፡ መኰንን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በምክትል ፡ አዛዥ ፡ መኰንኑ ፡ ፊት ፡

(ለ) ባለጉዳዩ ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ መምሪያ ፡ ክፍል ፡ በአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግል ፡ ሲሆን ፡ በሥራ ፡ መሪው ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ የጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ፊት ፤

(፫) የባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ፊርማና ፡ የክፍሉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ተጨማሪ ፡ ፊርማ ፡ ለውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ ትክክለኛነት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ የውክልናውን ፡ ሥልጣን ፡ ሰጭ ፡ የሆነው ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ባልደረባ ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ የቀረበበትን ፡ ክስ ፡ ለመከላከል ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ የውክልናው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ነው ።

(፬) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ፡ በተመለከተው ፡ መሠ

BACK



ረት ፡ የወኪልነት ፡ ወይም ፡ የነገረ ፡ ፈጅነት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰ ጠው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፷፪ ። በእርስ ፡ ቤት ፡ ለሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ሆነው ፡ ስለሚከራከሩ ፡ ወኪሎች ።

(፩) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆንና ፡ በመታሠሩ ፡ ምክንያት ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ ለመ ከራከር ፡ የማይችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በከሰሰበትም ፡ ሆነ ፡ በተከሰ ሰበት ፡ ጉዳይ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ የሚከራከርለት ፡ ወኪል ፡ ወይም ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ለመተካት ፡ ይችላል ።

(፪) የሚሰጠውም ፡ ወኪልነት ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅነት ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በእስረኛው ፡ ከተፈረመበት ፡ በኋላ ፡ የወሕኒ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ፈርሞበት ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይመዘገባል ።

(፫) ይህን ፡ ስለመሳሰለው ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፷፩ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፫) እና (፬) የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በተ መሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፷፫ ። ተሟጋች ፡ ስለማቆም ።

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ዋና ፡ ባለጉዳይ ፡ የሆነው ፡ ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴው ፡ ስለራሱ ፡ ሆኖ ፡ እንዲከራከርለት ፡ ለተወሰነ ፡ ነገርና ፡ ለተወሰነ ፡ ሊዜ ፡ የሚሆን ፡ የጽሑፍ ፡ ወኪልነት ፡ ወይም ፡ እንደራሴነት ፡ ካልሰጠው ፡ ወይም ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ለመቅጠርና ፡ ወኪል ፡ ለመሾም ፡ ብቻ ፡ ሥልጣን ፡ ከተቀበለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የጽሑፍ ፡ ውክልና ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ስለሌላ ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ ለመሟገት ፡ አይችልም ።

(፪) ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚሰጠው ፡ የወኪልነት ፡ ወይም ፡ የነገረ ፡ ፈጅነት ፡ ሥልጣን ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ወካዩ ፡ ከፈረመበት ፡ በኋላ ፡ ውክልናው ፡ ወይም ፡ ፈጅነቱ ፡ ከተሰጠበት ፡ የክስ ፡ ወይም ፡ የመልስ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ በተ ከፈተው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተቀማጭ ፡ ይሆ

BACK



ናል ። ጸንቶ ፡ የሚቆየውም ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ የፈጅነቱ ፡ ወይም ፡ የወኪልነቱ ፡ ሥልጣን ፡ የተቋረጠ ፡ መሆኑን ፡ በጽሑፍ ፡ እስኪያስታውቁና ፡ ይህንኑም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቅዶ ፡ እስኪያጸድቀው ፡ ወይም ፡ ከባለጉዳዮቹ ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደ ሆነ ፡ ወይም ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠበት ፡ ነገረ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ለተመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፫፻፺፱ ወይም ፡ ፬፻፰ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ስለሚቀርቡ ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻዎች ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በብይን ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ይግባኞች ፡ ወይም ፡ የሰነዶችንና ፡ የማስረጃዎችን ፡ ግልባጮች ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ የቀረቡትን ፡ ጽሑፎች ፡ ግልባጭ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤትና ፡ በፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ክፍል ፡ የተያዘውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስመለስ ፡ የሚቀርበው ፡ አቤቱታና ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ ከዋናው ፡ የሥረ ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

<u>ቍ ፡ ፷፩ ። ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ነገረፈጆች ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበሉት ፡ ሁኔታ ።</u>

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ለተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ከሚሰጠውም ፡ የወኪልነትና ፡ የነገረ ፡ ፈጅነት ፡ ሥልጣን ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚልከውን ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመቀበል ፡ ብቻ ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ ለመሾም ፡ ይቻላል ።

(፪) የዚህም ፡ ዓይነት ፡ የወኪልነት ፡ ሥልጣን ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ወካዩ ፡ ከፈረመበት ፡ በኋላ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ይቀመጣል ።

## <u>ም ዕ ራ ፍ ፬ ።</u>

### <u>ስለ ፡ ባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብና ፡ ሳይቀርብ ፡ መቅረት ።</u>

<u>ቍ ፡ ፷፪ ። ባለጉዳዩ ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለመሆኑ ።</u>

(፩) ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርበውን ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ አቤቱታና ፡

ማናቸውንም ፡ ማመልከቻ ፡ ለማቅረብ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ራሱ ፡ እንዲ ቀርብ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የወኪልነት ፡ ወይም ፡ የነገረ ፡ ፈጅ ነት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ምትክ ፡ ሆኖ ፡ በመቅረብ ፡ ሊከራከር ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ በማናቸው ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሰጠው ፡ ለክርክሩ ፡ አወሳ ሰን ፡ የዋናውን ፡ ባለጉዳይ ፡ መቅረብ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሚያ ደርግ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) አንዳንድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ ሔዶ ፡ ለማጣራት ፤ ለመመርመር ፤ የምስክሮችን ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ የሚችል ፡ የፍ ርድ ፡ ቤት ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ ልዩ ፡ አዋቂ ፡ (ኤክስ ፐርት) ተተኪ ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ማዘዝ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ ተገኝቶ ፡ ሥራ ውን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ የዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ ወይም ፡ የነገረ ፡ ፈጁ ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ ያለመገኘት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተወከለው ፡ ሰው ፡ የፈጸመውን ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ሊያሳጣው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፷፯ ። ከብዙ ፡ ከሳሾች ፡ ወይም ፡ ተከሳሾች ፡ መካከል ፡ ያንዱ ፡ ብቻ ፡ መቅረብ ።

(፩) ከሳሾች ፡ ወይም ፡ ተከሳሾች ፡ በኅብረት ፡ ለተከሰሱበት ፡ ነገር ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ስለ ፡ ብዙዎቹ ፡ ሆኖ ፡ እንዲከራከርላ ቸው ፡ ለመወከል ፡ ይችላል ።

(፪) የውክልናውም ፡ ሥልጣን ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ወካዮቹ ፡ ከፈረ ሙበት ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ ከሚመለከተው ፡ መዝገብ ፡ ጋር ፡ ተያ ይዞ ፡ ይቀመጣል ።

ቍ ፡ ፷፰ ። ስለ ፡ ሽሪኮች ፡ መቅረብ ።

(፩) ሽሪኮች ፡ የሆኑ ፡ ያንድ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ ተካፋ ዮች ፡ በንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ ሥም ፡ የተከሰሱ ፡ እንደሆነ ፡ ራሳቸው ፡ መቅረብ ፡ ይገባቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ክሱ ፡ የሚቀጥለው ፡ በንግድ ፡

BACK



ድርጅቱ ፡ ስም ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፺፰ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ መጥሪያው ፡ የተላከው ፡ የሽርክናውን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለሚመራው ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ በሽርክና ፡ ተካፋይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መቅረብ ፡ አይገባውም ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ መጥሪያው ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ሽሪክ ፡ ያለመሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ በተቃዋሚነት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ የተቃዋሚው ፡ መቅረብ ፡ ከሳሹ ፡ በንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ ስም ፡ ሌላ ፡ መጥሪያ ፡ ተቀብሎ ፡ ካደረሰ ፡ በኋላ ፡ ሽሪኮቹ ፡ ባለመቅረባቸው ፡ በሌሉበት ፡ በድርጅቱ ፡ ላይ ፡ ከማስፈረድ ፡ ሊያግደው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፷፰ ። አንዳንድ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ራሳቸው ፡ እንዲቀርቡ ፡ ለማዘዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ።

(፩) ማናቸውም ፡ ሙግት ፡ በመቀጠል ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ዲሬክተር ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ ወይም ፡ ነገሩን ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ የሚገምተው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ አባል ፡ ወደ ፡ ችሎቱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ነገሩ ፡ የሚመለከተው ፡ የመንግሥትን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ እንዲከራከር ፡ የተወከለው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ጉዳዩን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚችል ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ ያላቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ጉዳዩን ፡ በሚገባ ፡ ለማብራራት ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ የገመተውን ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ ወደ ፡ ችሎቱ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲያስረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፷፱ ። ስለ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መቅረብ ።

(፩) ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ከሳሽ ፡ ተከሳሾች ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ ወኪሎቻቸው ፡ ተሟልተው ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ። የተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መቅረብ ፡ እንደተረጋገጠም ፡ ክርክሩ ፡ መሰማት ፡ ይጀምራል ።

(፪) የግራ ፡ ቀኙ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡

ሳይቀርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገቡን ፡ ይዘጋዋል ። እንዲሁም ፡ ክርክሩ ፡ የቀረበው ፡ በይግባኝ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የይግባኙን ፡ መዝገብ ፡ ይዘጋዋል ።

(፫) በክርክሩ ፡ ዋናው ፡ ባለ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያላዘዘ ፡ ሲሆንና ፡ በምትኩም ፡ ወኪሉ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጁ ፡ በቀነ ፡ ቀጠሮው ፡ ቀርቦ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፸ ። የተከሳሽ ፡ ያለመቅረብ ።

ክርክሩ ፡ እንዲሰማ ፡ በተወሰነው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ከሳሽ ፡ ቀርቦ ፡ ተከሳሹ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ለጉዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሠጠው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

(ሀ) ለተከሳሹ ፡ የተላከለት ፡ መጥሪያ ፡ የደረሰው ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ በሌለበት ፡ የነገሩ ፡ መሠማት ፡ ይቀጥላል ።

(ለ) መጥሪያው ፡ በትክክል ፡ መድረሱ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁለተኛ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲላክ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(ሐ) መጥሪያው ፡ የደረሰው ፡ መሆኑ ፡ ቢረጋገጥም ፡ እንኳ ፡ ለተከሳሹ ፡ የተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ለክሱ ፡ መልስ ፡ ማዘጋጀት ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በማይገመት ፡ አጭር ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ ሲሆን ፡ የክርክሩን ፡ መስማት ፡ ለሌላ ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ያስተላልፈዋል ።

(መ) አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ ለሆኑ ፡ ተከሳሾች ፡ የተላከው ፡ መጥሪያ ፡ ለተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ከተከሳሾቹ ፡ መካከል ፡ ላንዳንዶቹ ፡ ሳይደርስ ፡ የቀረው ፡ በከሳሹ ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ መጥሪያው ፡ ባልደረሰው ፡ ወይም ፡ ባልደረሳቸው ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ ዘግቶ ፡ ለማሰናበትና ፡ ነገሩም ፡ ይግባኝ ፡ እንደሆነ ፡ የይግባኙን ፡ መዝገብ ፡ ለመዝጋት ፡ ይችላል ። ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ከታየውም ፡ ክሱ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ይለውጣል ። ስለሆነም ፡ መጥሪያ ፡ ያልደረሰው ፡ ተከሳሽ ፡ ወይም ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ ጉዳዩ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ወደ ፡ ችሎቱ ፡

BACK



ቀርቦ ፡ እንዲከራከር ፡ ሊታዘዝ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ መጥሪያ ፡ ባለመስጠቱ ፡ ምክንያት ፡ የሥረ ፡ ነገሩ ፡ ወይም ፡ የይግባኙ ፡ ፋይል ፡ አይዘጋም ።

ቍ ፡ ፸፩ ። የክሱ ፡ መዝገብ ፡ መዝጋት ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፷፱ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፸ ፡ (መ) በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ የተዘጋ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሹ ፡ ተገቢውን ፡ ዳኝነትና ፡ የተወሰነውን ፡ ኪሣራ ፡ ከፍሎ ፡ ፋይሉን ፡ እንደገና ፡ ከማስከፈትና ፡ ነገሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ከማድረግ ፡ አያግደውም ።

(፪) ከሳሹ ፡ በቀነ ፡ ቀጠሮው ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረው ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ይህንኑ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ ዳኝነትና ፡ ኪሣራ ፡ ሳይከፍል ፡ ፋይሉ ፡ እንደገና ፡ ተከፍቶ ፡ ነገሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፸፪ ። በሚቀጥለው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ስለመቅረብ ።

በመጀመሪያው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ባለመቅረቡ ፡ ክርክሩ፡ በሌለበት ፡ እንዲቀጥል ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ቀርቦ ፡ በቀዳሚው ፡ ቀጠሮ ፡ ለመቅረብ ፡ ያልቻለው ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በሚገመት ፡ እክል ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደሆነና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ያቀረበውን ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ አድርጐ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ በቀረበበት ፡ ቀን ፡ መከላከያውን ፡ አቅርቦ ፡ እንዲከራከር ፡ ይፈቀድለታል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ በሌለበት ፡ ተሰምቶ ፡ የነበረው ፡ ክርክር ፡ ራሱ ፡ ባለበት ፡ እንደተሰማ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

ቍ ፡ ፸፫ ። የከሳሽ ፡ ያለመቅረብ ።

ባንድ ፡ ነገር ፡ ክስ ፡ ያቀረበ ፡ ሰው ፡ ክርክሩ ፡ እንዲሰማ ፡ በተወሰነው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነና ፡ ተከሳሹ ፡ ቀርቦ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ያመነ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሹ ፡ በሌለበትም ፡ ቢሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ላመነው ፡ ጉዳይ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። ከሳሹ ፡ የካደ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ መዝገቡን ፡

BACK


በመዝጋት ፡ ያሰናብተዋል ።

ቍ ፡ ፸፬ ። የክሱ ፡ መዝገብ ፡ መዘጋት ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፸፫ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የመጀ መሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክስ ፡ ከተዘጋና ፡ በቍጥር ፡ ፷፱ (፪) ወይም ፡ በቍ ጥር ፡ ፸ (መ) ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፸፫ ፡ ላይ ፡ በተነገረው ፡ ሁኔታ ፡ የይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ከተዘጋ ፡ በኋላ ፡ ከሳሹ ፡ ለመጀመሪያው ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ለይግባኙ ፡ ክርክር ፡ መነሻ ፡ የነበረውን ፡ ነገር ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድን ጋጌ ፡ መዝገቡ ፡ በተዘጋ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንደገና ፡ ተከፍቶ ፡ ነገሩ ፡ እንዲታይለት ፡ ከሳሹ ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚችልበትን ፡ መብት ፡ አያስቀርበትም ። ከሳሹ ፡ በቀዳሚው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረው ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በሚገመት ፡ እክል ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ስለኪሣራውና ፡ ስለማናቸውም ፡ ወጭ ፡ አከፋፈል ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየ ውን ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ የተዘጋው ፡ መዝገብ ፡ እንደገና ፡ ተከፍቶ ፡ ነገሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ይወስናል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሰጠው ፡ ከሳሹ ፡ ያቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፸፭ ። የብዙ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ያለመቅረብ ።

(፩) ከብዙ ፡ ከሳሾች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ የበለ ጡት ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ የቀረቡት ፡ ከሳሾች ፡ ብቻ ፡ ክርክሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ሲያመለክቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ሁሉም ፡ እንደቀረቡ ፡ በመቁጠር ፡ ክርክሩ ፡ እንዲሰማ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ተከሳሾች ፡ መጥሪያ ፡ ደርሷቸው ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ የቀረበው ፡ ወይም ፡ የቀረቡት ፡ ተከሳሾች ፡ ባሉበት ፡ የክርክሩ ፡ መሰማት ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድ

ረግ ፡ ይቻለል ። ፍርድ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ባልቀረበው ፡ ወይም ፡ ባልቀረቡት ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየ ውን ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፸፮ ። የሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያለመቅረብ ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፵፫ ፡ (፪) ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከሳሹ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ ሶስተኛው፡ ወገን ፡ በአላፊነት መጠየቅ ፡ ይገባዋል ፡ ሲል ፡ ተከሳሹ ፡ ባመለ ከተው ፡ መሠረት ይህ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ቀርቦ ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ በመግባት ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዞ ፡ መጥሪያው ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ ቀርቦ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ወይም ፡ አላፊ ፡ የማይሆንበትን ፡ ምክንያት ፡ በማስረዳት ፡ ሳይከራከር ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ዋናው ፡ ተከሳሽ ፡ የተፈረደበትን ፡ ፍርድ ፡ እንደተቀበለ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከሳሹ ፡ ባመለከተው ፡ መጠን ፡ በአላፊ ነት ፡ የሚጠየቅበትን ፡ ድርሻውን ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደዳል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ በነገሩ ፡ የተረታና ፡ የተፈረደበት ፡ እንደሆነ ፡ በፍ ርዱ ፡ ተስማምቶ ፡ ከተቀበለው ፡ በኋላ ፡ ፍርድን ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ መክፈል ፡ ያለበትን ፡ ድርሻ ፡ እንዲከፍል ፡ ይታዘዝልኝ ፡ ብሎ ፡ ተገቢውን ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብ ፡ ይህ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ድርሻውን ፡ ለዋናው ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፸፯ ። ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ የታዘዘው ፡ ሰው ፡ ያለመቅረብ ።

ከሳሹ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካዘዘ ፡ በኋላ ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ስለተከሳሽ ፡ ያለመቅረብ ፡ በዚህ፡ ምዕራፍ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ይፈጸምበታል ።

ቍ ፡ ፸፰ ። ተከሳሽ ፡ በሌለበት ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ስለማንሳት ።

(፩) አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ በክርክሩ ፡ ላይ ፡ ቀርቦ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ወይም ፡ ተገቢውን ፡ መከራከሪያ ፡ ሳያቀርብ ፡ በመቅረቱ ፡ በሌለ በት ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ፡ ሲሆን ፡ ውሳ

BACK



ኔው ፡ ወይም ፡ ትእዛዙ ፡ መስጠቱን ፡ በተረዳው ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ቀርቦ ፡ ትእዛዙ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ እንዲነሳለት ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ይህን ፡ ማመልከቻ ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ የጥሪው፡ ትእዛዝ ፡ በሚገባ ፡ ያልደረሰው ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ክርክሩ ፡ ሊሰማ ፡ በተቀጠረበት ፡ ቀን ፡ ቀርቦ ፡ መከራከሪያውን ፡ ያላሰ ማው ፡ ወይም ፡ መልስ ፡ ያልሰጠው ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳ ፡ እንደሆነ ፡ የተከሳሹ ፡ አቤቱታ ፡ ላንደ ኛው ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ እንዲደርሰው ፡ ካደረገና ፡ ተገቢውን ፡ ኪሣራ ፡ ወይም ፡ መቀጮ ፡ እንዲከፍል ፡ ካዘዘ ፡ በኋላ ፡ ትእዛዙን ፡ ወይም ፡ ብይኑን ፡ በማንሳት ፡ ክርክሩ ፡ እንደገና ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጣል ። ስለሆነም ፡ ነገሩን ፡ ለማመልከት ፡ በቀረ በው ፡ ተከሳሽ ፡ ላይ ፡ ተሰጥቶ ፡ የነበረውን ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ሲያነሳ ፡ ይህ ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲነሳላቸው፡ ቀርበው ፡ ባላመለከቱ ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ የማይጸና ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳው ፡ በአቤት ፡ ባዩ ፡ አመልካችነት ፡ የተነሳው ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ ላላመለከቱት ፡ ተከሳሾች ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ ማዘዝ ፡ አለበት ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የፍ ርዱ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ብይኑና ፡ ትእዛዙ ፡ በንባብ ፡ በተሰማበት ፡ ቀን ፡ አልነበርንም ፡ ለሚሉ ፡ ወገኖች ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

# ሶስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ክስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፤

### ቍ ፡ ፸፱ ። የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ።

(፩) በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚ ሆኑ ፡ ናቸው ።

(፪) ይህ ፡ ድንጋጌ ፡ በይግባኝ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ተፈጻሚ ፡

BACK



በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ከሳሽ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ይግባኝ ፡ ባይን ፤ ተከሳሽ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ መልስ ፡ ሰጭን ፤ ክስ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፡ የይግባኝ ፡ ክስንም ፡ አጠቃሎ ፡ ይይዛል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ፤

## ስ ለ ፡ አ ቤ ቱ ታ ።

**ቍ ፡ ፹ ። በአቤቱታ ማመልከቻ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ነገሮች ።**

23 (ሀ)

(፩) የአቤቱታ ፡ ጽሑፍ ፡ ማለት ፤ ከሳሽ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፤ ተከሳሽ ፡ የሚሰጠው ፡ የመከላከያ ፡ ጽሑፍ ፤ የተከሳሽ ፡ ከሳሽ ፡ የሚያቀርበው ፡ የክስ ፡ ጽሑፍ ፤ የይግባኝ ፡ ማቅረቢያ ፡ ጽሑፍ ፤ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ተጽፎ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርብ ፡ የክስ ፡ መነሻ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ የሚሰጠውን ፡ መልስ ፡ የሚመለከት ፡ ማናቸውም ፡ የጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) ማንኛውም ፡ የአቤቱታ ፡ ጽሑፍ ፡ ሁሉ ፡ በቀለም ፡ የተጻፈ ፡ ወይም ፡ በታተሙ ፡ ፎርሞች ፡ በቀለም ፡ ጽሕፈት ፡ የተሞላ ፡ ወይም ፡ በጽሕፈት ፡ መኪና ፡ የተመታ ፡ መሆን ፡ አለበት ። የሚጻፈው ፡ ለአቤቱታ ፡ ማቅረቢያ ፡ በተዘጋጀ ፡ የፎርም ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የሚገለጽበትም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አመልካቹ ፡ መብቱን ፡ የሚጠብቅበትን ፡ ምክንያት ፡ በአጭሩ ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ስለመከላከያው ፡ የሚሰጠውን ፡ መልስ ፡ በአጭሩ ፡ የሚገልጽ ፡ ሆኖ ፡ ፎርሙም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ አንደኛ ፡ ሰንጠረዥ ፡ በመሆን ፡ በአባሪነት ፡ ከታተመው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) በፎርሙ ፡ ላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ በቀር ፡ በተጨማሪነት ፡ መገለጽ ፡ የሚገባቸው ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ የተጻፉበትን ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በመግለጽ ፡ በአባሪነት ፡ ተጽፈው ፡ ከፎርሙ ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ።

(፬) በሚቀርበው ፡ የማመልከቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ቁጥር ፡ ወይም ፡

BACK



የገንዘብ ፡ ልክ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ቍጥሩ ፡ በአሐዝና ፡ በፊደል ፡ መጻፍ ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ የውጭ ፡ አገርን ፡ ገንዘብ ፡ የሚመለከት ፡ ነገር ፡ ሲያጋጥም ፡ የምንዛሪው ፡ ልክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ መገለጽ ፡ ይገባዋል ።

(፭) እንደ ፡ ኤውሮጳ ፡ አቆጣጠር ፡ የሚጻፍ ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቀን ፡ አቆጣጠር ፡ ተተርጒሞ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፹፩ ። በቅድሚያ ፡ ቀዳሚነት ፡ መፈጸም ፡ ስለሚገባቸው ፡ ግዴታዎች ።**

ለአንድ ፡ ክርክር ፡ መነሻ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፡ የግዴታው ፡ መፈጸምና ፡ ያለመፈጸም ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ከሳሹ ፡ በሚያቀርበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ በሚሰጠው ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ በበኩሉ ፡ ሊፈጽም ፡ ይገባዋል ፡ የሚባለውን ፡ ግዴታ ፡ የፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ አለበት ። ስለሆነም ፡ በከሳሽ ፡ በሚቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ በሚሰጠው ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ከሳሹ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ መብቱን ፡ በመጠበቅ ፡ የሚያቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ ወይም ፡ መልስ ፡ በበኩሉ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ እንደፈጸመ ፡ ያስቆጥረዋል ።

**ቍ ፡ ፹፪ ። አዲስ ፡ ነገር ፡ ስላለማቅረብ ።**

ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ በአቤቱታው ፡ ወይም ፡ በመልሱ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ለክሱ ፡ መሠረት ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የተከሳሽ ፡ ከሳሽ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ተገቢነት ፡ የለውም ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ተቀባይነትን ፡ ለማግኘት ፡ የማይገባው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ አፍራሽ ፡ የሆነ ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ በመጀመሪያ ፡ ያልተያዙትን ፡ ጭብጦች ፡ እንዳይፈርጥ ፡ ሥረ ፡ ነገሩን ፡ ሳይለቅ ፡ የመጀመሪያውን ፡ መሠረታዊ ፡ ሙግት ፡ ተከትሎ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፹፫ ። ነገርን ፡ በግልጽ ፡ መካድ ፡ ተገቢ ፡ ስለመሆኑ ።**

ተከሳሽ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ነገር ፡ መካድ ፡ የሚችለው ፡ በከሳሹ ፡

የቀረቡትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝርና ፡ በግልጽ ፡ ክዶ ፡ በመቃወም ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ከሳሹ ፡ የከሳሽ ፡ ተከሳሽ ፡ ሆኖ ፡ መልስ ሰጭ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ የቀረበበትን ፡ ክስ ፡ በዝርዝርና ፡ በግልጽ ፡ መካድ ፡ አለበት ። ስለ ፡ ካሣ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝርና ፡ በግልጽ ፡ ያለመካድ ፡ ያልተካደውን ፡ ነገር ፡ በከፊል ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ አምኖ ፡ እንደመቀበል ፡ ያስቆጥራል ።

**ቍ ፡ ፹፬ ። ውልን ፡ ስለመካድ ።**

ውል ፡ ጠቀስ ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ውሉን ፡ ቢክድ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ እንደካደ ፡ ይቆጠራል ። ስለሆነም ፡ የውሉን ፡ ሕጋዊነትና ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለውን ፡ ጸኚነት ፡ እንደካደ ፡ አያስቆጥረውም ።

**ቍ ፡ ፹፭ ። በክርክሩ ፡ ላይ ፡ የሚቀርቡትን ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ ባለዋጋነት ፡ ስለማስረዳት ።**

ባንድ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ለክርክሩ ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆን ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነድ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ መግለጥ ፡ ሳያስፈልግ ፡ የክርክሩን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የያዙትን ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ ገልብጦ ፡ ማቅረብ ፡ በቂ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለጉዳዩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ሰነድ ፡ ትርጉሙ ፡ ወይም ፡ መንፈሱ ፡ አከራካሪ ፡ ወይም ፡ የሚያሻማ ፡ ሲሆን ፡ አከራካሪ ፡ የሆነውን ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ጠቅሶ ፡ ማቅረብ ፡ ወይም ፡ የጽሑፉ ፡ መንፈስና ፡ ትርጉም ፡ በሙሉ ፡ አከራካሪ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፹፮ ። ስለ ፡ አእምሮ ፡ ሁኔታዎች ።**

ስላንድ ፡ ክርክር ፡ ጉዳይ ፡ በሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ ወይም ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ ተንኰል ፡ ማታለል ፡ የአዋቂ ፡ አጥፊነት ፡ ወይም ፡ የከፋ ፡ ሐሊና ፡ ዝንባሌ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ጉድለት ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ሁኔታ

ውን ፡ እንጂ ፡ ለዚሁ ፡ መነሻ ፡ የሆነውን ፡ ምክንያትና ፡ አካባቢ ውን ፡ በአቤቱታው ፡ ውስጥ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፹፯ ። ማስታወቂያ ፡ ስለመስጠት ።

ማስታወቂያ ፡ የተሰጠበት ፡ ጕዳይና ፡ ዓይነቱ ፡ በዝርዝር ፡ ተገልጾ ፡ ለተላከለት ፡ ሰው ፡ መድረስ ፡ ያለመድረሱ ፡ የሚያከራ ክር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለተላከለት ፡ ሰው ፡ መድረሱን ፡ ማረጋገጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ አመልካቹ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ያደረሰ ፡ መሆኑን ፡ በ'ነመልከቻው ፡ ላይ ፡ ከገለጸ ፡ በቂ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፹፰ ። በነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሚታወቁ ፡ ውሎችና ፡ ሕጋዊ ፡ ግንኙነቶች ።

(፩) በክሱ ፡ አቤቱታ ፡ ውስጥ ፡ በአካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ብቻ ፡ የተመሠ ረቱ ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ግንኙነቶች ፡ መኖራቸውን ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ የሚባለውን ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ግንኙነት ፡ በጠቅላላው ፡ መጥቀስ ፡ በቂ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ውል ፡ ወይም ፡ ግንኙነት ፡ የተመሠረተበትን ፡ አካባቢና ፡ ምክን ያት ፡ በአቤቱታው ፡ ውስጥ ፡ መዘርዘር ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ በአካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ከሚመሠረቱ ፡ ውሎችና ፡ ግንኙነቶች ፡ ሌላ ፡ ውል ፡ ጠቀስ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ የሚል ፡ አመልካች ፡ እነዚ ሁኑ ፡ በተጨማሪነት ፡ ወይም ፡ በምትክነት ፡ እየጠቀሰ ፡ መከራከ ሪያ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፹፱ ። ሕጋዊ ፡ ስለሆኑ ፡ ግምቶች ።

አስቀድሞ ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ አቤቱታ ፡ ወይም ፡ ሙግት ፡ በግልጽ ፡ የተካደ ፡ ጕዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራ ካሪ ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ ግምት ፡ የሚደገፍበትን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ተገቢ ፡ የሆነበትን ፡ ጕዳይ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በአቤቱታው ፡ ውስጥ ፡ መጥቀስ ፡ አይ ገባውም ።

ቍ ፡ ፺ ። ከፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ክርክር ፡ መስመር ፡ ውጭ ፡ ስለመውጣት ።

አቤቱታን ፡ ለማሻሻል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገ

BACK



ኖች ፡ ቀድሞ ፡ ካቀረቡት ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ ጭብጥ ፡ ውጭ ፡ የሆነና ፡ ከቀድሞው ፡ ክርክር ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሌለው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፺፩ ። አቤቱታን ፡ ስለማሻሻል ።**

(፩) ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፤ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ካገኘው ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ክሳቸውን ፡ እንዲያሻሽሉና ፡ ክርክራቸውን ፡ እንዲለውጡ ፡ ሊፈቅድላቸው ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሚሰጠው ፡ የክሱ ፡ መሻሻል ፡ ወይም ፡ የክርክሩ ፡ መለወጥ ፡ ነገሩን ፡ ይበልጥ ፡ የሚያብራራ ፡ ወይም ፡ ትክክለኛ ፡ ፍትሕን ፡ ለመስጠት ፡ የሚረዳ ፡ ሆኖ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ በሚፈቅድበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ኪሣራ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) ክሱን ፡ እንዲያሻሽል ፡ የተፈቀደለት ፡ ወገን ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህንኑ ፡ ካላቀረበ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጊዜ ፡ ካልቀጠለለት ፡ በቀር ፡ ክሱን ፡ የማሻሻል ፡ ወይም ፡ ሙግቱን ፡ የመለወጥ ፡ መብቱ ፡ ይሰረዝበታል ።

(፫) የማሻሻያው ፡ ማመልከቻ ፡ የክሱን ፡ ወይም ፡ የመከላከያውን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያብራራ ፡ ወይም ፡ የቀረበውን ፡ ክርክር ፡ በተሻሻለ ፡ ዓይነት ፡ ገልጾ ፡ የሚያስረዳ ፡ ወይም ፡ ሁኔታውን ፡ በዝርዝር ፡ አገላለጽ ፡ የሚያመለክት ፡ ሆኖ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ከባለጉዳዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሲያመለክት ፡ ስለኪሣራ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ማሻሻያ ፡ እንዲቀርብ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

(፬) አስፈላጊ ፡ ያልሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ የክርክሩን ፡ አመራር ፡ ሥርዓት ፡ የሚያስነክሉ ፡ ወይም ፡ ሁከትን ፡ የሚፈጥሩ ፡ ወይም ፡ ለትክክለኛው ፡ ፍትሕ ፡ አሰጣጥ ፡ መሰናክል ፡ የሆነው ፡ የሚገመቱት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ወይም ፡ ከአቤቱታው ፡ ውስጥ ፡ ጨርሶ ፡ እንዲወጡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

BACK



(፩) የክሱ ፡ መሻሻል ፡ ነገሩን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ በላይ ፡ ያደረገው ፡ እንደሆነ ፡ የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያስተላልፈዋል ። ጉዳዩ ፡ የቀረበለትም ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የነገሩ ፡ መሰማት ፡ እንዲቀጥል ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፺፪ ፡-አቤቱታን ፡ ስለማረጋገጥ ፡

(፩) ስለማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚያዝ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በአቤቱታ ፡ ማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ ነገር ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ነገሩን ፡ የሚያውቅ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በአቤቱታው ፡ ግርጌ ፡ ይህ ፡ የቀረበው ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፪) አንድ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ በሚከስበት ፡ ወይም ፡ በሚከሰስበት ፡ ጊዜ ፡ በአቤቱታው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የሰፈረው ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጠው ፡ የድርጅቱ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ዲሬክተር ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ ወይም ፡ ጉዳዩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ተገቢነት ፡ ያለው ፡ ማንኛውም ፡ የድርጅቱ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፫) መንግሥት ፡ በሚከስበት ፡ ወይም ፡ በሚከሰስበት ፡ ጊዜ ፡ አቤቱታውን ፡ የሚፈርመው ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ የተወከለው፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ነው ። በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ትክክለኛነት ፡ በማረጋገጥ ፡ የሚፈርመው ፡ ደግሞ ፡ ጉዳዩን ፡ በተለይ ፡ የሚያውቀውና ፡ ስለዚህም ፡ የተለየ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ የክፍል ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፬) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፵፬ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በሽርክና ፡ በተቋቋመ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ስም ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ፡ የአቤቱታውን ፡ ጽሑፍ ፡ ትክክለኛነት ፡ የሚያረጋግጠው ፡ በተለይ ፡ ጉዳዩን ፡ የሚያውቀውና ፡ ስለዚህም ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው፡ ከሸሪኮቹ ፡ አንዱ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፺፫ ፡-አቤቱታን ፡ ስለመፈረም ፡

ማንኛውም ፡ አቤቱታ ፡ በዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ ወይም ፡ በጠበ

ቃው ፡ መፈረም ፡ አለበት ። ዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ አቤቱታውን ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ለመፈረም ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ ዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ሊከስ ፡ ወይም ፡ ሊከሰስ ፡ የሚችል ፡ ወይም ፡ በስሙ ፡ ለመፈረም ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ መፈረም ፡ አለበት ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፪ ፤

## ስ ለ ፡ መ ጥ ሪ ያ ።

### ክፍል ፡ ፩ ፡- መጥሪያን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለመቀበልና ፡ ለተጠሪው ፡ ስለመስጠት ፤

**ቍ ፡ ፺፬ ፡-መጥሪያን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማስወጣት ፤**

(፩) አንድ ፡ ክስ ፡ በሚገባ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ የጉዳዩ ፡ አፈጻጸም ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመራ ፡ የሚያደርግ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፫ ፡ እና ፡ ፪፻፴፬ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ ይላክለታል ። ስለሆነም ፡ የክሱ ፡ አቤቱታ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተከሳሹ ፡ ቀርቦ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ያመነ ፡ እንደሆነ ፡ የተባለውን ፡ መጥሪያ ፡ መላክ ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።

(፪) በቍጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ በሚሰጠው ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ይጠቀመኛል ፡ ሲል ፡ የዘረዘራቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ እንዲቀርብ ፡ በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጠዋል ።

(፫) ማንኛውም ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ተብሎ ፡ በተያያዘው ፡ ፎርም ፡ ዓይነት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ዳኛው ፡ ወይም ፡ ሬጂስትራሩ ፡ ከፈረመበት ፡ በኋላ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ ይታተማል ።

BACK



ቍ ፡ ፺፫ ። የመጥሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ለተከሳሽ ፡ የሚላከውን ፡ መጥሪያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዘዘው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ መጥሪያ ፡ ሰጭ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

(፪) የአሰጣጡ ፡ ሥርዓት ፡ በሌላ ፡ አኳሆን ፡ እንዲፈጸም ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡ ተከሳሾቹ ፡ ብዙ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ መጥሪያው ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ይታዘዛል ።

(፫) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የሚቻል ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ መጥሪያው ፡ የሚሰጠው ፡ ለተከሳሹ ፡ ለራሱ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፺፬ ። መጥሪያን ፡ ለነገረ ፡ ፈጁ ፡ ወይም ፡ ለጠበቃው ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ተከሳሹ ፡ መጥሪያውን ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ወኪል ፡ ያለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ መጥሪያው ፡ ለወኪሉ ፡ ይሰጣል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ለተከሳሹ ፡ እንደደረሰው ፡ ይቆጠራል ። ስለሆነም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፷፩ ፡ እና ፡ ፷፪ ፡ በተገለጹት ፡ ሁኔታዎች ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበል ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ ነገረፈጅ ፡ ያልተወከለ ፡ ወይም ፡ ያልተሾመ ፡ እንደሆነ ፡ መጥሪያው ፡ የሚሰጠው ፡ ተከሳሹ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አባል ፡ ሲሆን ፡ ለክፍሉ ፡ ዋና ፡ አዛዥ ፡ እስረኛ ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ለወሕኒ ፡ ቤቱ ፡ አዛዥ ፡ ነው ።

(፪) መጥሪያውን ፡ ለተከሳሽ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ ጠበቃ በራሱ ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ ቢሮአቸው ፡ በማስቀመጥ ፡ መስጠት ይቻላል ፡ ይህም ፡ ሲሆን ፡ መጥሪያው ፡ ለተከሳሹ ። ለራሱ ፡ እንደደረሰው ፡ ወይም ፡ መድረሱን ፡ እንዳወቀው ፡ ይቆጠራል ።

(፫) ተከሳሹ ፡ መንግሥት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መጥሪያው ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ እንዲከራከር ፡ ለተወከለው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ ለመሥሪያ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ቤቱ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፺፭ ። መጥሪያን ፡ ለንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በንግድ ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ የመጥ

BACK



ሪያው ፡ አሰጣጥ ፡ ሁኔታ ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ ይፈጸማል ።

(ሀ) የተከሰሰው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መጥሪያ ውን ፡ ለዋና ፡ ጸሐፊው ፡ ወይም ፡ ከኩባንያው ፡ ዲሬክተሮች ፡ ላንዱ ፡ ወይም ፡ ከድርጅቱ ፡ ሹማምቶች ፡ ላንዱ ፡ በመስጠት ፡

(ለ) ተከሳሹ ፡ ድርጅት ፡ የተመዘገበ ፡ አድራሻ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ መጥሪያውን ፡ በፖስታ ፡ በመላክ ፡ ወይም ፡ ለመሥሪ ፡ ቤቱ ፡ ወስዶ ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ የታወቀ ፡ አድራሻ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ ድርጅቱ ፡ ለዘወትሩ ፡ የንግድ ፡ ሥራውን ፡ በሚያከናው ንበት ፡ ሥፍራ ፡ በመላክ ፡ ወይም ፡ በመስጠት ።

ቍ ፡ ፺፫ ። መጥሪያን ፡ ሽሪክ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ብዙ ፡ የንግድ ፡ ሽሪኮች ፡ በሽርክና ፡ ባቋቋሙት ፡ የንግድ ፡ ድርጅታቸው ፡ ስም ፡ ሲከሰሱ ፡ መጥሪያው ፡ ከሽሪኮቹ ፡ ላንዱ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ ለሆኑት ፡ እንዲደርስ ፡ ይደረጋል ፡ ወይም ፡ ድርጅቱ ፡ ዋነኛ ፡ ሥራውን ፡ በሚያካሔድበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ይላካል ። መጥሪያው ፡ በሚላክበት ፡ ጊዜ ፡ የንግዱ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ለሆነው ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ ድርጅቱን ፡ በበላይ ፡ ተቆጣጣ ሪነት ፡ ለሚመራው ፡ ሰው ፡ ይሰጣል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የተሰጠ ውም ፡ መጥሪያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ላሉትም ፡ ሆነ ፡ ለሌሉት ፡ ሽሪኮች ፡ እንደደረሳቸው ፡ ይቆጠራል ።

(፪) ክሱ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ የሽርክናው ፡ ድርጅት ፡ የፈረሰ ፡ መሆኑን ፡ ከሳሽ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ መጥሪያው ፡ በኢትዮ ጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙትና ፡ በአላፊነቱ ፡ ለሚጠየቁት ፡ ሽሪኮች ፡ ሁሉ ፡ ይሰጣል ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ላንድ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ አባል ፡ መጥሪያ ፡ ሲሰጥ ፡ መጥሪያው ፡ የተሰጠው ፡ በሽርክናው ፡ በአባልነቱ ፡ በሥራ ፡ አስኪያጅነቱ ፡ ወይም ፡ በበ ላይ ፡ ተቆጣጣሪነቱ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ ለተቀባዩ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲገለጽለት ፡ ያስፈልጋል ።

ይህ ፡ ተለይቶ ፡ ያልተገለጸ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ መጥሪያው ፡ የተሰ ጠው ፡ በሽርክናው ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ ይቆጠራል ።

BACK



**ቍ ፡ ፺፱ ። በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ለሚነገድ ፡ ተከሳሽ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ።**

(፩) የመጥሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ ከሚደርስበት ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚነገድ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ የሚያካሄድ ፡ ሲሆን ፡ ለሚቀርብበት ፡ ክስ ፡ የሚላከው ፡ መጥሪያ ፡ ክሱ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ የመጥሪያውን ፡ ትእዛዝ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የግዛት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ ወኪሉ ፡ ወይም ፡ ለሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ለራሱ ፡ እንደተሰጠው ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ለተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ አፈጻጸም ፡ የመርከብ ፡ አዛዥ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የመርከቡ ፡ ባለቤት ፡ ወይም ፡ የመርከቡ ፡ ተከራይ ፡ ወኪል ፡ እንደሆነ ፡ ይቆጠራል ።

**ቍ ፡ ፻ ። በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ለንብረቱ ፡ ወኪል ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ።**

ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መጥሪያውን ፡ ለመስጠት ፡ ሲሆን ፡ የንብረቱ ፡ ጠባቂ ፡ ለሆነ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለሚገኝ ፡ ሰው ፡ መስጠት ፡ በቂ ፡ ይሆናል ። በዚህ ፡ ዓይነትም ፡ የተሰጠው ፡ መጥሪያ ፡ ለባለንብረቱ ፡ እንደደረሰው ፡ ይቆጠራል ።

**ቍ ፡ ፻፩ ። መጥሪያን ፡ ለተከሳሽ ፡ ቤተሰቦች ፡ ስለመስጠት ።**

ስለማናቸውም ፡ ክስ ፡ የተላከውን ፡ መጥሪያ ፡ ለተከሳሹ ፡ ለራሱ ፡ ለመስጠት ፡ ተከሳሹን ፡ ለማግኘት ፡ ያልተቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ተቀባይ ፡ የሚሆን ፡ ወኪል ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ አብሮት ፡ ከሚኖረው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ከደረሰ ፡ ቤተሰቡ ፡ ላንዱ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፪ ። መጥሪያ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ደረሰኝ ፡ መፈረም ፡ የሚገባው ፡ ስለመሆኑ ።**

መጥሪያ ፡ ሰጭው ፡ ለተከሳሽ ፡ ለነገረ ፡ ፈጁ ፡ ለወኪሉ ፡ ለእ

BACK



ንደራሴው ፡ ወይም ፡ ለመቀበል ፡ አግባብ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ መጥሪያውን ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ተቀባዩ ፡ የደረሰው ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ በዋናው ፡ ግልባጭ ፡ ላይ ፡ መተማመኛ ፡ መፈረም ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፫ ። ተከሳሽ ፡ መጥሪያ ፡ ለመቀበል ፡ እምቢተኛ ፡ ስለመሆኑ ፡ ወይም ስላለመገኘቱ ።**

ተከሣሹ ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ወይም ፡ ስለርሱ ፡ ሆኖ ፡ መጥሪያ ፡ መቀበል ፡ የሚገባው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ መጥሪያ ፡ የደረሰው ፡ ስለመሆኑ ፡ ማረጋገጫ ፡ ደረሰኝ ፡ ለመፈረም ፡ እምቢተኛ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ መጥሪያ ፡ ሰጭው ፡ ተገቢውን ፡ ፍለጋ ፡ አድርጎ ፡ ተቀባዩን ፡ ለማግኘት ፡ ያልቻለ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ተቀባይ ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ መቀበል ፡ የሚገባው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ሲያስታውቁ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የታዘዘው ፡ መጥሪያ ፡ ሰጭ ፡ ወይም ፡ ባለጉዳዩ ፡ መጥሪያውን ፡ ለመስጠት ፡ ያልቻሉበትን ፡ ምክንያት ፡ በመሐላ ፡ ቃላቸው ፡ አረጋግጠው ፡ መጥሪያውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይመልሳሉ ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ሲያጋጥም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፰ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ መጥሪያ ፡ ተልኮለት ፡ ለመቀበል ፡ ፈቃደኛ ፡ ያለመሆኑ ፡ ወይም ፡ ደረሰኝ ፡ ለመስጠት ፡ እምቢተኛነቱ ፡ በመሐላ ፡ በተሰጠ ፡ ቃል ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ እንደደረሰው ፡ ተቆጥሮ ፡ በሌለበት ፡ ክርክሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፻፬ ። መጥሪያው ፡ የተሰጠበትን ፡ ሁኔታና ፡ ጊዜ ፡ ስለማረጋገጥ ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፪ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ስለማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ መጥሪያ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ መጥሪያ ፡ ሰጭው ፡ በዋናው ፡ መጥሪያ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ በሚያያዝ ፡ ሌላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ መጥሪያውን ፡ የሰጠበትን ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ የተቀባዩን ፡ ሥም ፡ ሲቀበል ፡ የነበሩትን ፡ ምስክሮች ፡ ስም ፡ በዝርዝር ፡ ጽፎ ፡ ተቀባዩ ፡ ከፈረመበት ፡ ዋና ፡ ኮፒ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መልሶ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፭ ። በምትክ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ።

(፩) ተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ እንዳይደርሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የተሸሸገ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፡ መጥሪያው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በደንበኛው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዳይደርስ ፡ መሰናክል ፡ ያደረገ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፡ መጥሪያው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ እንዲለጠፍ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ የታወቀ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ይኖርበት ፡ የነበረው ፡ ሥፍራ ፡ ሲታወቅ ፡ ወይም ፡ የሚሠራበት ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውንበት ፡ ሥፍራ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ሥፍራ ፡ በመለጠፍ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፮ እና ፡ ፻፯ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በጋዜጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ አማካይነት ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ ዘዴ ፡ ተከሳሹ ፡ መጠራቱን ፡ እንዲያውቀው ፡ ያደርጋል ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፫ እንደተነገረው ፡ መጥሪያው ፡ ሳይሰጥ ፡ የተመለሰ ፡ እንደሆነ ፡ በከሳሹ ፡ አመልካችነት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዲስ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ መጥሪያው ፡ ሳይሰጥ ፡ በተመለሰ ፡ በ፫ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሳሹ ፡ ሳያመለክት ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፸ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ቸልተኛነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ይሆናል ።

(፫) ለተከሳሹ ፡ ሳይሆን ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ለተከሳሹ ፡ ምትክ ፡ የተሰጠ ፡ መጥሪያ ፡ ለራሱ ፡ እንደተሰጠ ፡ ይቆጠራል ።

(፬) መጥሪያው ፡ በምትክ ፡ እንዲሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ የሚቀርብበትን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ወስኖ ፡ ያስታውቃል ።

ቍ ፡ ፻፮ ። በፖስታ ፡ ስለሚላክ ፡ መጥሪያ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከሚፈጸመው ፡ የመጥሪያ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥርዓት ፡ በቀር ፡

BACK



በተጨማሪም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያው ፡ ተከሳሹ ፡ ወይም ፡ ስለርሱ ፡ ሆኖ ፡ መቀበል ፡ የሚገባው ፡ ወኪሉ ፡ በሚኖርበት ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ለጥቅሙ ፡ በሚሠራበት ፡ ቦታ ፡ በአደራ ፡ ፖስታ ፡ አማካይነት ፡ እንዲላክ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሚላከው ፡ ለዋናው ፡ መጥሪያ ፡ ተጨማሪ ፡ ወይም ፡ መጥሪያው ፡ ራሱ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) መጥሪያው ፡ የደረሰ ፡ መሆኑን ፡ ዋናው ፡ ተከሳሽ ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ በፊርማቸው ፡ ሲያረጋግጡ ፡ ወይም ፡ ለመቀበል ፡ ፈቃደኛ ፡ ያለመሆናቸውን ፡ ፖስታ ፡ ቤቱ ፡ በጽሑፍ ፡ ሲያስታውቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያው ፡ እንደደረሳቸው ፡ ሊቆጥረው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፺፯ ። በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖር ፡ ተከሳሽ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ።**

(፩) ተከሳሹ ፡ የሚኖረው ፡ የመጥሪያውን ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ መጥሪያው ፡ ተከሳሹ ፡ በሚኖርበት ፡ ሥራ ፡ በሚያከናውንበት ፡ ወይም ፡ በሚነግድበት ፡ ቦታ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፖስታ ፡ ወይም ፡ በላኪው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ አማካይነት ፡ ይላካል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ መጥሪያው ፡ የተላከለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመጥሪያውን ፡ ትእዛዝ ፡ ራሱ ፡ እንደሰጠ ፡ አድርጎ ፡ ለተከሳሹ ፡ ማድረሱን ፡ ለላኪው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጽሑፍ ፡ ያረጋግጥለታል ። ስለ ፡ መጥሪያው ፡ አሰጣጥ ፡ የወሰደው ፡ እርምጃ ፡ ወይም ፡ ያዘጋጀው ፡ ቬርባል ፡ ሲኖር ፡ ይህንኑ ፡ በማያያዝ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይልክለታል ።

**ቍ ፡ ፺፰ ። ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ ለሚኖር ፡ ተከሳሽ ፡ ስለሚላክ ፡ መጥሪያ ።**

ተከሳሹ ፡ የሚኖረው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ መጥሪያ ፡ የሚቀበል ፡ ወኪል ፡ የሌለው ፡ እንደሆነና ፡ ያለበት ፡ አድራሻ ፡ ሲታወቅ ፡ መጥሪያው ፡ በተከሳሹ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ ተጽፎ ፡ ለሚገኝበት ፡ አገር ፡ በፖስታ ፡ ይላካል ። መኖሪያውና ፡ አድራ

BACK



ሻው ፡ ያልታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእ ዛዝ ፡ መሠረት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሚታተም ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ የመጥሪያ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሊወጣ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፸፱ ። ለመንግሥት ፡ ወይም ፡ ለኩባንያ ፡ ሠራተኞች ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ።

ተከሣሹ ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የኩባንያ ፡ ሠራተኛ ፡ ሲሆን ፡ መጥሪያውን ፡ ተከሳሹ ፡ ለሚሠራበት ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ድርጅት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መላክ ፡ ለአሰጣጡ ፡ ምቾት ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ ተከ ሳሹ ፡ ለሚሠራበት ፡ ድርጅት ፡ የክፍል ፡ አላፊ ፡ ለሆነው ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲላክ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሚ ላከውም ፡ መጥሪያ ፡ ለተከሳሹ ፡ ሊደርስ ፡ ከሚገባው ፡ ግልባጭ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፹ ። መጥሪያን ፡ ለተከሳሽ ፡ እንዲሰጥ ፡ የታዘዘ ፡ ሰው ፡ ስላሉበት ፡ ግዴዎች ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፸፯ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ወይም ፡ ፸፱ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ መጥሪያ ፡ እንዲ ሰጥ ፡ የታዘዘ ፡ ወይም ፡ የተላከለት ፡ ሰው ፡ ባለ ፡ አድራሻውን ፡ ለማግኘት ፡ የሚችል ፡ በሚሆንበት ፡ መጠን ፡ መጥሪያውን ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ። ይህንንም ፡ ለተጠሪው ፡ ስለማድ ረሱ ፡ ተቀባዩ ፡ የፈረመበትን ፡ ደረሰኝና ፡ ራሱም ፡ ያረጋገጠበ ትን ፡ ለላኪው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲመልስ ፡ መጥሪያው ፡ ለተከሳሹ ፡ እንደደረሰ ፡ ይቆጠራል ።

(፪) በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ መጥሪያውን ፡ ለባለ አድራሻው ፡ ለመስጠት ፡ የማያስችል ፡ መሰናክል ፡ የደረሰበት ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ምክንያትና ፡ ለማድረግ ፡ ያደረገውን ፡ ሙከራና ፡ የወ ሰደውን ፡ እርምጃ ፡ ከሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ዋናውን ፡ መጥሪያ ፡ ለላኪው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይመልሳል ። እነዚህም ፡ ጽሑ ፎች ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲደርሱ ፡ መጥሪያውን ፡ ለተከሳሹ ፡ መስ ጠት ፡ ላለመቻሉ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ።

## ክ ፍ ል ፪ ።

## ስለ ፡ ምስክሮች ፡ አጠራርና ፡ አቀራረብ ።

### ቍ ፡ ፻፲፩ ። መጥሪያን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለመቀበል ።

ቃላቸውን ፡ በምስክርነት ፡ እንዲሰጡ ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ለተቆጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፩፻፵፱ ፡ ፩፻፶፪ ፡ እና ፡ ፪፻፴፬ ፡ በተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ በአቤቱታው ፡ ወይም ፡ በመከላከያው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ አስረጂ ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ስማቸው ፡ የተገለጸውን ፡ ሰዎች ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያ ፡ ሳይጠይቅ ፡ አመልካቹ ፡ ወገን ፡ ሊያቀርባቸው ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፻፲፪ ። ለምስክሮች ፡ ስለሚከፈል ፡ ወጭ ።

(፩) ምስክር ፡ እንዲጠራለት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚያመለክት ፡ ተከራካሪ ፡ ሁሉ ፡ የመጥሪያውን ፡ ትእዛዝ ፡ ከመቀበሉ ፡ በፊት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ልክ ፡ ለምስክሮች ፡ መጓጓዣና ፡ ለሌ ላም ፡ የቀን ፡ ወጭ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ይገደ ዳል ።

(፪) ለምስክርነት ፡ የሚጠራው ፡ ሰው ፡ በልዩ ፡ ሞያ ፡ ረገድ ፡ የሚ ሰጠው ፡ ማስረጃ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ሊከፈለው ፡ ከሚገባው ፡ ወጭም ፡ በቀር ፡ በማስረጃነት ፡ የሚያቀርበውን ፡ ጉዳይ ፡ ከፍተ ኛነት ፡ ሥራው ፡ የሚፈጅበትን ፡ ጊዜ ፡ የልዩ ፡ ሞያው ፡ ምርመራ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚጠይቀውን ፡ የሥራ ፡ ድካም ፡ በማመዛዘን ፡ ተጨ ማሪ ፡ አበል ፡ እንዲከፈለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) ለምስክሮቹ ፡ ወጭ ፡ እንዲሆን ፡ ተቀማጭ ፡ የሚሆነው ፡ ገን ዘብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባዘዘው ፡ ሁኔታና ፡ ጊዜ ፡ ይከፈላል ።

### ቍ ፡ ፻፲፫ ። ተቀማጭ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ የማይበቃ ፡ ሲሆን ፡ ስለሚ ታዘዝ ፡ ተጨማሪ ፡ ሂሳብ ።

(፩) የተቀመጠው ፡ ገንዘብ ፡ ለምስክሮቹ ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ አዋ

BACK



ቂው ፡ አበል ፡ የማይበቃ ፡ ሆኖ ፡ በተገመተ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ የሚገምተውን ፡ የወጭ ፡ ልክ ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፡ ተጨማሪው ፡ ገንዘብ ፡ ለምስክሮቹ ፡ ወይም ፡ ለልዩ ፡ አዋቂው ፡ እንዲከፈል ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ምስክሩ ፡ እንዲቀርብ ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ እንዲቆይ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ለሚቆይበት ፡ ጊዜ ፡ የሚገባውን ፡ ወጭ ፡ ገምቶ ፡ በተጨማሪነት ፡ እንዲከፈለው ፡ ያዝለታል ።

(፫) አስመስካሪው ፡ ወገን ፡ እንዲከፍል ፡ የተወሰነበትን ፡ ወጭ ፡ ለመክፈል ፡ ፈቃደኛ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የእምምቢተኛው ፡ የሚንቀሳቀስና ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ተሸጦ ፡ እንዲከፈል ፡ ወይም ፡ የተጠራው ፡ ምስክር ፡ ቃሉን ፡ ሳይሰጥ ፡ እንዲሰናበት ፡ ወይም ፡ ሁለቱንም ፡ አጣምሮ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፲፬ ። በመጥሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ጉዳዮች ።

(፩) የምስክርነት ፡ ቃል ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡ ይገኛል ፡ የተባለውን ፡ የጽሑፍ ፡ አስረጂ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ለሚጠራ ፡ ሰው ፡ የሚጻፈው ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፤ የተጠራበት ፡ ምክንያት ፤ የሚቀርብበት ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፤ ሥፍራው ፤ የተጠራው ፡ ለምስክርነት ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሁለቱም ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑ ፡ ተለይቶ ፡ ይጻፍበታል ።

(፪) ተጠሪው ፡ የሚያቀርበው ፡ የተለየ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ሲሆን ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ጽሑፍ ፡ ዓይነት ፡ በዝርዝር ፡ ተገልጾ ፡ ይጻፍለታል ።

ቍ ፡ ፻፲፭ ። የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ።

የምስክርነት ፡ ቃል ፡ ለመስጠት ፡ ሳይሆን ፡ የተለየ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ የደረሰው ፡ ሰው ፡ ተፈላጊው ፡ ማስረጃ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲደርስ ፡ ካደረገ ፡ ራሱም ፡ ባይቀርብ ፡ ጥሪውን ፡ አክብሮ ፡ እንደቀረበ ፡ ይቆጠራል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፮ ። ስለ ፡ መጥሪያው ፡ አሰጣጥ ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፷ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ለምስክር ፡ የሚሰጥ ፡ መጥሪያ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ለተከሳሾች ፡ መጥሪያ ፡ ስለ ፡ መስ ጠት ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። ስለሆነም ፡ ከቍጥር ፡ ፪፻ ፡ እስከ ፡ ፪፻፰ ፡ ከተመለከቱት ፡ ድን ጋጌዎች ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ከላይ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። መጥሪያ ፡ ለመስጠት ፡ ስለ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ።

ለምስክር ፡ የሚላክ ፡ ማናቸውም ፡ መጥሪያ ፡ ተጠሪው ፡ እን ዲቀርብ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ለመድረስ ፡ እንዲችል ፡ ለመጓጓዣና ፡ አስፈላጊውን ፡ መሰናዳት ፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በሚገመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲደርሰው ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ይሆ ናል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። የጥሪን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለማያከብሩ ፡ ምስክሮች ።

(፩) የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስ ረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የጥሪ ፡ ትእዛዝ ፡ የተላከለት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ትእዛዙን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስቀድሞ ፡ የተላከለት ፡ ጥሪ ፡ መድረሱን ፡ ያረጋግጣል ።

(፪) እንዲቀርብ ፡ የተፈለገው ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስ ረጃ ፡ ለጉዳዩ ፡ አወሳሰን ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረ ዳው ፡ እንደሆነ ፤

(ሀ) የተላከው ፡ መጥሪያ ፡ ለባለ ፡ አድራሻው ፡ በሚገባ ፡ ያልደረሰው ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያረጋገጠ ፡ ሲሆን ፤ ባለጉ ዳዩ ፡ ተገቢውን ፡ ኪሣራ ፡ ከፍሎ ፡ ሌላ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲወስድ ፡ ያዝለታል ።

(ለ) መጥሪያው ፡ ደርሶት ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረው ፡ በሕግ ፡ በማይደገፍ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ እንዳይደርሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ መሰወሩን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ተጠሪው ፡ ተገዶ ፡ ወይም ፡ ታስሮ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያደርጋል ።

BACK



(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፶፪ ፡ የተመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ የሚነካ ፡ አይደለም ።

**ቍ ፡ ፻፲፱ ። የምስክርነት ፡ ቃልን ፡ መስጠትና ፡ የተጠየቀውን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ስለመሆኑ ፤**

የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ የደረሰው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፤ በጥሪው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮና ፡ ሥፍራ ፡ ቀርቦ ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሲታዘዝ ፡ ራሱ ፡ ማስረጃውን ፡ ይዞ ፡ የመቅረብ ፡ ወይም ፡ ቶፈላጊው ፡ ማስረጃ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፤ እንዲደርስ ፡ የማድረግ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፳ ። ምስክርን ፡ ስለማሰናበት ፤**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ ለምስክርነት ፡ ተጠርቶ ፡ የቀረበ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በጉዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጥ፡ ድረስ ፡ በሚወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ሁሉ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ተገቢውን ፡ የምስክር ፡ ኪሣራና ፡ አበል ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አስይዞ ፡ ለምስክርነት ፡ ወይም፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ የተጠራው ፡ ሰው ፡ ለጉዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡ እንዲቆይለት ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነ ፡ ምስክሩ ፡ በየተወሰነው ፡ ቀጠሮ ፡ እንዲቀርብ ፡ በማስጠንቀቅ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ቢታየው ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ በመቀበል ፡ እንዲቆይ ፡ ሊያዘው ፡ ይችላል ። ዋስትና ፡ ለመስጠት ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ ፈቃደኛ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ያደርገዋል ።

(፫) የተሰጠውን ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ አክብሮ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ (፩) የተነገረውን ፡ ውሳኔ ፡ ባለመጠበቅ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተለይቶ ፡ የሔደ ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፲፰ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ይፈጸምበታል ፡

**ቍ ፡ ፻፳፩ ። የምስክርነት ፡ ቃልን ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃን ፡ ለማቅረብ ፡ ስላለመቻል ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ የጽ

ሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ በመገደድ ፡ ታስሮ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በቀን ቀጠሮው ፡ ሳይቀርቡ ፡ ወይም ፡ ሳይቀርብ ፡ በመቀረቱ ፡ የተፈለገ በትን ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ ማስረጃውን ፡ ለማቅረብ ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወደፊት ፡ ለተወሰ ነው ፡ ቀጠሮ ፡ እንዲቀርብ ፡ ዋስ ፡ አስጠርቶ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መ ያዣ ፡ ሰጥቶ ፡ እንዲሰናበት ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታየው ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ለማዘዝ ፡ እችላል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ፤

## የፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚወከል ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ።

### ቍ ፡ ፪፻፱ ። መሠረቱ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተገለጹት ፡ ምክንያቶች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡ ምስክር ፡ ለመስማት ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ እንደተነገረው ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ሌላ ፡ እር ምጃ ፡ ራሱ ፡ ለመውሰድ ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሆኖ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጉዳይ ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ የሚያከናውን ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ መርጠ ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ። ተፈላጊው ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ምስክር ፡ የሚገኘው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ በሆነ፡ ጊዜ ፡ ለባለ ፡ ሥልጣኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጥያቄ ፡ ደብዳቤ ፡ ይጽ ፋል ። ምትክ ፡ ለሚሆነው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ሲሰጥ ፡ የተመረጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለወካዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ እንደራሴ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ይሠራል ።

### ቍ ፡ ፪፻፲ ። ለምትክ ፡ ዳኞች ፡ የሚከፈለውን ፡ አበል ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማስያዝ ፤

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መ ሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ከመሾሙ ፡ በፊት ፡ ዳኛ ፡ እንዲሾምለት ፡ የሚጠይቀው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ለሥራው ፡ አፈ ጻጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ወጭ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወሰነው ፡

BACK



ጊዜ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ይታዘዛል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ምዕራፍ ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ በወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ባንደኛው ፡ አመልካችነት ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ሲሾም ፡ በቍጥር ፡ ፻፲፪ ፡ የተመለከተው ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፻፳፬ ። ስለምትክ ፡ ዳኞች ፡ ሥልጣን ።

ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ እንደራሴ ፡ ሆነው ፡ በምትክነት ፡ እንዲሠሩ ፡ የታዘዙ ፡ ዳኞች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ፡ የተመለከተውን ፡ ለማከናወን ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

(ሀ) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ የሚያቀርቡዋቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ወይም ፡ ለነገሩ ፡ ተገቢነት ፡ አለው ፡ ብለው ፡ የገመቱትን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ አቅርበው ፡ ቃሉን ፡ መቀበል ፡ መመርመርና ፡ መጠየቅ ፡

(ለ) ከጉዳዩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ወይም ፡ ለነገሩ ፡ ማጣራት ፡ ተገቢ ፡ መስለው ፡ የታዩዋቸው ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነዶችና ፡ ማንኛዎቹም ፡ ማስረጃዎች ፡ እንዲቀርቡላቸው ፡ ለማዘዝና ፡ ለመመርመር ፤

(ሐ) እንዲያጣሩ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ መሬቶች ፡ እየዞሩ ፤ ማየትና ፡ እንዲሁም ፡ በቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ መመርመር ።

ቍ ፡ ፻፳፭ ። ምስክሮችን ፡ በምትክ ፡ ዳኞቹ ፡ ፊት ፡ አቅርቦ ፡ ስለመመርመርና ፡ ቃላቸውን ፡ ስለመቀበል ፤

(፩) ስለ ፡ ምስክሮች ፡ መጠራት ፤ አቅርቦ ፡ ስለመመርመርና ፡ ቃላቸውን ፡ ስለመቀበል ፤ ስለሚከፈላቸው ፡ የቀን ፡ አበል ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፤ ለመቅረብ ፡ ፈቃደኛ ፡ ባልሆኑ ፡ ወይም ፡ ባልቀረቡ ፡ ምስክሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚወሰድ ፡ እርምጃ ፡ ወይም ፡ ስለሚወሰን ፡ ቅጣት ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ምትክ ፡ ዳኞች ፡ ዘንድ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ በታዘዙ ፡ ምስክሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡

ምትክ ፡ ዳኞች ፡ የሠሩት ፡ ተግባር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክፍል ፡ ዳኞች ፡ እንደሠሩት ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

(፪) ምትኩ ፡ ዳኛ ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ እንዲቀርብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳ ፡ ተፈላጊው ፡ ሰው ፡ በሚገኝበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ እንዲቀርብ ፡ እንዲታዘዝለት ፡ ለክፍሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። ይህ ፡ ጥያቄው ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ምትኩ ፡ ዳኛ ፡ የጠየቀውን ፡ መፈጸም ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደ ሆነ ፡ ተፈላጊው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብለት ፡ ያዛል ።

ቊ ፡ ፻፳፯ ። ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በምትክ ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ስለሚቀርቡበት ፡ ሁኔታ ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ በሾመ ፡ ጊዜ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ በጠበቆቻቸው ፡ ወይም ፡ በወኪሎቻቸው ፡ አማካይነት ፡ በተሾመው ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ፤

## ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ስለሚጠየቁና ፡ ስለሚመረመሩ ፡ ምስክሮች ፤

ቊ ፡ ፻፳፰ ። ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ስለሚሾምበት ፡ ቦታ ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ በሚያጋጥሙት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማናቸውም ፡ ክርክር ፡ ስለርሱ ፡ ሆኖ ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ እንዲቀበል ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ይሾማል ።

(ሀ) የምስክርነት ፡ ቃል ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የተፈለገው ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ሆኖ ፡ በሕመም ፡ ወይም ፡ በደዌ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ችሎት ፡ ለመቅረብ ፡ የማይችል ፡ ሲሆን፤

(ለ) ተፈላጊው ፡ ሰው ፡ የሚኖረው ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ሲሆን ፤

(ሐ) ስለምስክር ፡ መስማት ፡ የተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡

ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ለቆ ፡ የሚሔድ ፡ ሲሆንና ፡ የሚያቀርበውን ፡ ማስረጃም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፷፭ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለመቀበል ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተተኪ ፡ ዳኛ ፡ የሚሾመው ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በመሐላ ፡ በተደገፈ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በሚያቀርበው ፡ ተራ ፡ ማመልከቻ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ራሱ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) በተመለከተው ፡ መሠረት ለጉዳዩ ፡ ተገቢነት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ የሚገመተውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መርጦ ፡ በተተኪ ፡ ዳኛነት ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ።

(፬) በዚህ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በፊደል ፡/ለ/ እና ፡ ሐ/ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የተፈለገው ፡ ሰው ፡ በሚገኝበት ፡ ወይም ፡ በሚኖርበት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሾም ፡ ሊታዘዝ ፡ ይችላል ። ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ ይሾማል ።

ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። ምትክ ፡ ዳኞች ፡ የታዘዙትን ፡ ሥራ ፡ ስለመጨረሳቸው ።

(፩) ምትክ ፡ ዳኞች ፡ የታዘዙትን ፡ ሥራ ፡ አከናውነው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ የተሰጣቸውን ፡ የሥልጣን ፡ ማስረጃ ፡ ከተቀበሉት ፡ የምስክርነት ፡ ቃልና ፡ ከሰበሰቡት ፡ ማስረጃ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ ላዘዛቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልሰው ፡ ያስረክባሉ ። ስለሆነም ፡ ሿሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የማስረጃው ፡ አቀራረብና ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠበት ፡ ደብዳቤ ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመለስ ፡ ካዘዘ ፡ በትእዛዙ ፡ ዓይነት ፡ ይፈጽማሉ ።

(፪) ምትክ ፡ ዳኞች ፡ የመለሱት ፡ የሥልጣን ፡ ማስረጃና ፡ በታዘዙትም ፡ መሠረት ፡ ያቀረቡዋቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ነገሩን ፡ ከሚመለከተው ፡ መዝገብ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ ይቀመጣሉ ።

**ቍ ፡ ፲፰፱ ። የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የምትክ ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ።**

(፩) በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክር ክር ፡ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ ተመርምሮ ፡ እንዲላክ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፲፴ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥያቄውን ፡ ተቀብሎ ፡ መፈጸም ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲታየው ፡ አስፈላጊውን ፡ ራሱ ፡ ሊያከናውን ፡ ወ ይም ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ አዞ ፡ በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቁጥር ፡ የተነገረው ፡ ማስረጃ ፡ የሚሰ ጠው ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

(ሀ) በኢትዮጵያ ፡ የሚገኘው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዲፕሎማቲክ፡ መልክተኛ ፡ ጥያቄውን ፡ ፈርሞ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አማካይ ነት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲልክ ፤

(ለ) ማስረጃውን ፡ የሚጠይቀው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚጠይቀውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚያብራራውን ፡ ደብዳቤ ፡ ፈርሞ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አማካይነት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲል ክለት ፤ ወይም ፡

(ሐ) ከውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተላከው ፡ ደብዳቤ ፡ በባለ ፡ ጉዳዩ ፡ እጅ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲቀርብለት ።

**ቍ ፡ ፲፴ ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚወስደው ፡ እርምጃ ።**

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀር ብለት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቍጥር ፡ ፲፰፱ ፡ የተመለከ ተውን ፡ ጉዳይ ፡ ያከናውናል ።

(ሀ) በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክር ፡ ያለው ፡ ባለጉ ዳይ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብለት ፤

(ለ) ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲያስተላልፍለት ።

BACK



**ቍ ፡ ፻፴፩ ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ ድንጋጌ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚጠየቅ ፡ ጉዳይ ፡ ስላላቸው ፡ ተፈጻሚነት ።**

ከቍጥር ፡ ፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ፻፳፯ ፡ እና ፡ በቍጥር ፡ ፻፳፯ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በቍጥር ፡ ፻፳፱ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ስለሚሾሙ ፡ ምትክ ፡ ዳኞች ፡ በተመሳሳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ ምትክ ፡ ዳኞች ፡ የታዘዙትን ፡ ሥራ ፡ አከናውነው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠበትን ፡ ጽሑፍና ፡ በታዘዙት ፡ መሠረት ፡ የሰበሰቡትን ፡ ማስረጃ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባሉ ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የቀረበለትን ፡ ማስረጃ ፡ ከሸኚ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ለጠያቂው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲላክ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያስተላልፋል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፫ ፤

## ምትክ ፡ ዳኞች ፡ ማስረጃን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚወስዱት ፡ ሌላ ፡ እርምጃ ፤

**ቍ ፡ ፻፴፪ ። በሥፍራው ፡ ላይ ፡ በመገኘት ፡ ስለሚደረግ ፡ ምርመራ ።**

ነገሩን ፡ በሚገባ ፡ ለማጣራትና ፡ ለመመርመር ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳውና ፡ እንዲሁም ፡ የዕለት ፡ ገበያ ፡ የዋጋ ፡ ሁኔታ ፡ ለማወቅ ፤ የካሣ ፡ ልክ ፡ ለማረጋገጥ ፤ ካንድ ፡ ሀብት ፡ የተገኘ ፡ የዓመት ፡ ትርፍ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፤ ያላገባብ ፡ ተወስዷል ፡ የተባለውን ፡ የሀብት ፡ ግምት ፡ ለማጣራት ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ተገቢውን ፡ ምርመራ ፡ አድርገው ፡ ውጤቱን ፡ እንዲያቀርቡለት ፡ ምትክ ፡ ዳኞችን ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፴፫ ። ምትክ ፡ ዳኛ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ ስለሚያከናውንበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤**

(፩) ምትኩ ፡ ዳኛ ፡ በተላከበት ፡ ሥፍራ ፡ የተቀበለውን ፡ የምስክር ፡ ቃልና ፡ የሰበሰበውን ፡ ማስረጃ ፡ በጽሑፍ ፡ አድርጐ ፡ ከራሱ ፡

BACK



መግለጫ ፡ ጋር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያቀርባል ።

(፪) ያቀረበው ፡ ማስረጃና ፡ ራፖር ፡ ለጉዳዩ ፡ ተገቢነት ፡ እንዳለው ፡ ማስረጃ ፡ ተቆጥሮ ፡ ለነገሩ ፡ መነሻ ፡ ከሆነው ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ይቀመጣል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ተከራካሪ ዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ እንደኛው ፡ ወገን ፡ ምትክ ፡ ዳኛው ፡ ስላቀረበው ፡ ራፖር ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ በራፖሩ ፡ ላይ ፡ ስለተገለጸው ፡ ጉዳይና ፡ የተመረመሩትን ፡ ነገሮች ፡ በሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቶ ፡ በግልጽ ፡ ችሎት ፡ እንዲጠየቅ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

ቊ ፡ ፪፻፲፩ ። በምትክ ፡ ዳኞች ፡ ስለሚደረግ ፡ የሂሣብ ፡ ምርመራ ።

(፩) በማናቸውም ፡ ክርክር ፡ ሂሣብ ፡ ማጣራት ፡ ወይም ፡ መርምሮ ፡ ማስተካከል ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ የሚገልጽ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ አስፈላጊውን ፡ የሂሣብ ፡ ምርመራ ፡ አጣርቶ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ምትክ ፡ ዳኛው ፡ ሂሣብ ፡ እንዲመረምር ፡ ከመታዘዙ ፡ አስቀድሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሂሣቡን ፡ ለማጣራት ፡ ተገቢነት ፡ አላቸው ፡ ወይም ፡ ከክርክሩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ፡ የሚባሉት ፡ የሂሣብ ፡ ሰነዶችና ፡ መዛግብቶች ፡ ተለይተው ፡ እንዲታወቁ ፡ ያደርጋል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቊጥር ፡ (፪) ፡ እንደተነገረው ፡ ተገቢነት ፡ አላቸው ፡ የተባሉትን ፡ የሂሣብ ፡ ሰነዶችና ፡ መዛግብቶች ፡ ምትክ ፡ ዳኛው ፡ እንዲረከብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ፡ እንዲሁም ፡ ለምርመራው ፡ አፈጻጸም ፡ መምሪያ ፡ እንዲሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከሠፈሩት ፡ ማስረጃዎች ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ተገቢነት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ ግልባጫቸው ፡ ለምትክ ፡ ዳኛው ፡ እንዲሰጡት ፡ ይደረጋል ። በተጨማሪ ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውንበት ፡ ትእዛዝና ፡ መምሪያ ፡ ይሰጠዋል ፡ የሚሰጠውም ፡ ትእዛዝ ፡ ምትክ ፡ ዳኛው ፡ ለፍርድ ፡

BACK



ቤቱ ፡ የሚያቀርበው ፡ በምርመራ ፡ ሥራው ፡ ያገኘውን ፡ ውጤት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ የራሱን ፡ አስተያየት ፡ ከሚገልጽ ፡ ራፖር ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ ያለመሆኑን ፡ ገልጾ ፡ የሚያስረዳ ፡ ይሆናል ።

(፬) ምትክ ፡ ዳኛው ፡ የሒሣብ ፡ ማጣራቱን ፡ ሥራ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሚያከናውን ፡ የሒሣቡን ፡ ትክክለኛነት ፡ የሚያረጋግጠው ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ እንደሆነ ፡ ገልጾ ፡ ሊያስታውቀው ፡ ይችላል ። በተለይም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ተገቢነት ፡ አላቸው ፡ ብሎ ፡ የሚቀበላቸውን ፡ የሒሣብ ፡ ሰነዶችና ፡ መዛግብቶች ፡ ለይቶ ፡ ሊያስታውቀው ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ነገሩ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ተገቢነት ፡ ያለውን ፡ መቃወሚያ ፡ የማቅረብ ፡ መብታቸው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

(፭) በቍጥር ፡ ፻፴፫ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) እና (፫) ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ስለ ፡ ሒሣብ ፡ ማጣራት ፡ ለተሾሙት ፡ ምትክ ፡ ዳኞች ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፻፴፭ ። ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ምርመራ ።

በቍጥር ፡ ፻፴፪ ፡ እና ፡ ፻፴፬ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የተሾመ ፡ ምትክ ፡ ዳኛ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ የፈጸመው ፡ የሥራ ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ሁኔታ ፡ አጥጋቢ ፡ ያለመሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ ተጨማሪ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፴፮ ። ልዩ ፡ አዋቂ ፡ (ኤክስፔርት) ፡ ስለ ፡ መሾም ።

(፩) ጉዳዩን ፡ ይበልጥ ፡ ለማብራራት ፡ ወይም ፡ ለክርክሩ ፡ ውሣኔ ፡ አሰጣጥ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሲያመለክት ፡ ነገሩን ፡ ለመመርመርና ፡ ለማጣራት ፡ ተገቢነት ፡ ያላቸው ፡ ልዩ ፡ አዋቂዎች ፡ (ኤክስፔርቶች) አስፈላጊውን ፡ ምርመራ ፡ አድርገው ፡ የምርመራቸውን ፡ ውጤት ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲያቀርቡለት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ልዩ ፡ አዋቂዎች ፡ (ኤክስፔርቶች) ፡ ሲሾሙ ፡ ሊፈጽሙ ፡ ስለ ሚገባቸው ፡ ምርመራ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሠሩትን ፡ ነገር ፡ በዝርዝር ፡ የሚያሳይና ፡ በግልጽ ፡ ወስኖ ፡ የሚያስታውቅ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ስለዚህም ፡ ጉዳይ ፡ በቍጥር ፡ ፻፴፫ ፡ እና ፡ ፻፴፬ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) ፡ እና ፡ (፫) ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተገቢነቱ ፡ መጠን ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፬ ።

## ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ ታሽገው ፡ እንዲጠበቁ ፡ ስለ ፡ ማድረግና ፡ ስለ ፡ መመለስ ።

ቍ ፡ ፻፴፯ ። የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ የነርሱ ፡ ተሟጋቾች ፡ ጠበቆች ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ በእጃቸው ፡ የሚገኘውን ፡ ወይም ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችሉትን ፡ ወይም ፡ ለክርክራችን ፡ ይጠቅመናል ፡ ብለው ፡ የሚያምኑበትን ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቀርብ ፡ የጠየቀውንና ፡ አስቀድመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያላቀረቡትን ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ሁሉ ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ።

(፪) እነዚህን ፡ ሰነዶች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀበለው ፡ ዝርዝርና ፡ ብዛታቸውን ፡ ከሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ ነው ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፶፯ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ማንኛውም ፡ አቤት ፡ ባይ ፡ ሰነዶችን ፡ ከአቤቱታው ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ ወይም ፡ ከቀነ ፡ ቀጠሮው ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፡ ማስረጃዬ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ጋር ፡ ይያያዝልኝ ፡ ወይም ፡ ለማቅረብ ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፬) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ የተከሣሽን ፡ ምስክሮች ፡ በመስቀልኛ ፡ ለመጠየቅ ፡ ተከሣሹ ፡ በተከሣሽ ፡ ከሣሽነት ፡ የሚያቀርበውን ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ለምስክርነት ፡ የቀረበ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ነገሩን ፡ ለማስታወስ ፡ እንዲችል ፡ የሚቀርቡለትን ፡ ማስረጃዎች ፡

በክርክሩ ፡ ላይ ፡ ለማስማት ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ አያስቀርበትም ።

ቍ ፡ ፻፴፰ ። ለክርክሩ ፡ አግባብ ፡ ያልሆኑትን ፡ ወይም ፡ ከነገሩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሌላቸውን ፡ ማስረጃዎች ፡ ስላለመቀበል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለክርክሩ ፡ አግባብ ፡ ያልሆነውን ፡ ወይም ፡ ከነገሩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሌለውን ፡ ማንኛውንም ፡ ጽሑፍ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንዳይቀርብ ፡ ለማገድ ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ሲወስን ፡ ምክንያቱን ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ በጽሑፍ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፴፱ ። በማስረጃነት ፡ በሚቀርቡ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ስለማድረግ ።

(፩) ከዚህ ፡ በታች ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ በማስረጃነት ፡ በሚቀርቡ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ምልክት ፡ እየተደረገባቸው ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ ይቀመጣሉ ።

(ሀ) የክሱ ፡ መዝገብ ፡ ቍጥርና ፡ አርዕስት ፡

(ለ) የጽሑፍ ፡ አቅራቢው ፡ ስም ፡

(ሐ) ጽሑፉ ፡ የቀረበበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

(፪) እንዲቀርብ ፡ የተፈቀደው ፡ ጽሑፍ ፡ በገቢና ፡ ወጭ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ሌላ ፡ መዝገብ ፡ ሲሆንና ፡ ይኸውም ፡ የቀረበው ፡ በቍጥር ፡ ፻፵ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ በዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ምትክ ፡ ግልባጩ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገሩት ፡ ምልክቶች ፡ በቀረበው ፡ ግልባጭ ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ።

ቍ ፡ ፻፵ ። በግልባጭ ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ምልክት ።

(፩) በክርክሩ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ጽሑፍ ፡ ቀሪ ፡ ደብዳቤዎች ፡ የሚያዝበት ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ የገቢና ፡ የወጭ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ ሂሣብ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ የዕለት ፡ ሂሣብ ፡ የሚያዝበት ፡ ደብተር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለማስረጃነት ፡ ይጠቅመኛል ፡ ብሎ ፡ የሚያቀርበው ፡ ወገን ፡ ትክክል ፡ ግልባጩን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ይፈቀድለታል ።

(፪) ተፈላጊው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ወይም ፡ ከመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተገልብጦ ፡ የሚቀርብ ፡ ወይም ፡ በማስረጃነት ፡ በሚያቀርበው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ ወይም ፡ አቅራቢው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ጽሑፍ ፡ ከሚገኝበት ፡ ክፍል ፡ ተገልብጦ ፡ እንዲቀርብለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

(ሀ) ተፈላጊው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ የሒሳብ ፡ መዝገብ ፡ የሚቀርበው ፡ ለተከራካሪው ፡ ወገን ፡ ሲሆን ፡ በራሱ ፡ እጅ ፡ እንዲቀርብ ፡ ይደረጋል ።

(ለ) ጽሑፉ ፡ የሚቀርበው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝና ፡ ጥያቄ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ይታዘዛል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) እንደተነገረው ፡ ጽሑፎችና ፡ የመዝገብ ፡ ግልባጮች ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲቀርቡለት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴ በተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከዋናው ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ ትክክለኛ ፡ መሆናቸው ፡ ተኖቦና ፡ ተረጋግጦ ፡ ምልክት ፡ ከተደረገባቸው ፡ በኋላ ፡ ዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ መዝገቡ ፡ ለአቅራቢው ፡ ይመለስለታል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፮ ። ተቀባይነት ፡ በሌላቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ምልክት ።</u>

ተከራካሪው ፡ ወገን ፡ ይጠቅመኛል ፡ ሲል ፡ ያቀረበውን ፡ ጽሑፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢነት ፡ የለውም ፡ ወይም ፡ ከክርክሩ ፡ ጋር ፡ አግባብ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፪ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) የተነገሩትን ፡ ምልክቶች ፡ አስፍሮበት ፡ ማስረጃው ፡ የተነቀፈበትን ፡ ምክንያት ፡ በመግለጽ ፡ ዳኛው ፡ ሙሉ ፡ ፊርማ ፡ ወይም ፡ አጭር ፡ ምልክት ፡ ያደርግበታል ።

ቍ ፡ ፻፵፪ ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተቀበላቸውንና ፡ የነቀፋቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ ስለመመዝገብ ።

(፩) በማስረጃነት ፡ የቀረበውን ፡ ማናቸውንም ፡ ጽሑፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፻፵ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ በዋናው ፡ ምትክ ፡ ግልባጩን ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ሆነ ፡ ዋናው ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ ግልባጩ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ እንዲወራረስ ፡ ወይም ፡ እንዲያያዝ ፡ ያደርጋል ።

(፪) ጽሑፉን ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ሳይወራረስ ፡ ለአቅራቢው ፡ ይመለስለታል ።

ቍ ፡ ፻፵፫ ። የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ተከብሮ ፡ (ታሽጎ) እንዲቀመጥ ፡ ስለሚ ሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፵-፻፵፪ እና ፡ ፪፻፴ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማስረጃ ነት ፡ የቀረበለትን ፡ ማንኛውንም ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ መዝገብ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አላፊነት ፡ ተከብሮና ፡ ታሽጎ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አስ ፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእ ዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በሬጂስትራሩ ፡ ዘንድ ፡ ተቀ ማጭ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፵፬ ። የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ስለመመለስ ።

(፩) በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ከክርክሩ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቅርቦት ፡ የነበረው ፡ የጽ ሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲመለስለት ፡ ጥያቄ ፡ ሲያቀርብ ፡ ያቀረበው ፡ ዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ይመ ለስለታል ።

(ሀ) በቍጥር ፡ ፻፵ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ በትክክል ፡ ግልባጩ ፡ የተተካ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ጽሑፉ ፡ የተመለሰለት ፡ ሰው ፡ ዋናው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደገና ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ መልሶ ፡ ለማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ሲገባ ።

(፪) በማስረጃነት ፡ የቀረበው ፡ ጽሑፍ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ውድቅ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ለማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ የማይጠቅም ፡ መሆ ኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወሰነ ፡ እንደሆነ ፡ ለአቅራቢው ፡ አይመለ

ስለትም ።

(፫) ቀርቦ ፡ የነበረው ፡ ጽሑፍ ፡ ለባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ሲመለስለት ፡ መልሶ ፡ ስለመቀበሉ ፡ ደረሰኝ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፸፭ ። አንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሌሎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ክፍል ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ጽሑፍ ፤ መዝገብ ፤ ወይም ፡ ሰነድ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ በተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አመልካችነት ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ መዝገብ ፤ ሰነድ ፤ የጽሑፍ ፡ ማስረጃና ፡ ማንኛውም ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠበትን ፡ መዝገብ ፡ አስቀርቦ ፡ ለመመርመር ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገሩት ፡ ጽሑፎች ፡ ስለሚቀርቡበት ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ እንዲቀርቡለት ፡ የሚያመለክተው ፡ ወገን ፤ የነዚህን ፡ ማስረጃዎች ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ለማምጣት ፡ የማይችልበትን ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ለማስገልበጫ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወጭ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፤ እንዲቀርብ ፡ የተጠየቀው ፡ ጽሑፍ ፡ ለክርክሩ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጠቃሚነት ፡ እንዳለው ፤ ትክክለኛውን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ይህ ፡ ማስረጃ ፡ ባስቸኳይ ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ምክንያት ፡ በጽሑፍ ፡ ገልጾ ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

(፫) በማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ደንብ ፡ ለአስረጂነት ፡ ተገቢ ፡ አይደሉም ፡ የሚባሉትን ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ ማስረጃዎች ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚፈቅድ ፡ አይደለም ።

ቍ ፡ ፻፸፮ ። ስለ ፡ ጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በግዙፍ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ተፈጻሚነት ።

ስለ ፡ ጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ አቀራረብ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በማስረጃነት ፡ በሚቀርቡ ፡ ግዙፍ ፡ ነገሮች ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫

## ለጊዜው ፡ ስለሚሰጡ ፡ የማገጃዎችና ፡ ሌሎች ፡ ትእዛዞች ።

### ክ ፍ ል ፡ ፩

### ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ስለሚሰጥ ፡ የእሥራት ፡ ትእዛዝ ።

**ቍ ፡ ፻፵፯ ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቅረብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ዋስትና ።**

(፩) ከሳሹ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ የተከሳሽ ፡ ከሳሽ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፤ ከሳሽ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ በመሐላ ፡ የተደገፈ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብና ፡ ክርክሩም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የማይመለከት ፡ ሲሆን ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ነገር ፡ ሲረጋገጥለት ፤

(ሀ) ተከሳሹ ፡ የከሳሽ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲጐተት ፡ በማሰብ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የዳኝነቱ ፡ ሥርዓት ፡ በሚገባ ፡ እንዳይከናወን ፡ መሰናከል ፡ በመሆን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በመሸሽ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥበት ፡ የተቃጣው ፡ ሁሉ ፡ እንዳይፈጸምበት ፡ ለማድረግ ፡ አስቦ ፡ ለማሰናከል ፡ በመሞከር ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ለመውጣት ፡ በመሞከር ፡ ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በመሸሽ ፡ ወይም ፡ ሀብቱን ፡ ለማባከን ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ለማዛወር ፡ ወይም ፡ ለማሸሽ ፡ ያቀደ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡

(ለ) ተከሳሹ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ በመውጣቱ ፡ ከሳሹ ፡ ፍርዱን ፡ ለማስፈጸም ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ በመፍጠር ፡ የተሰጡት ፡ ትእዛዞች ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ ወይም ፡ እንዲዘገዩ ፡ ለማድረግ ፡ መሞከሩን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ተከሳሽ ፡ ታስሮ ፡ እንዲቀርብና ፡ ለተከታዩም ፡ ቀጠሮ ፡ ለመቅረብ ፡ ዋስትና ፡ የማይሰጥበትን ፡ ምክንያት ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ዕዳ ፤ አስሮ ፡ እንዲያቀርበው ፡ ለተላከው ፡ ሰው ፡ ሰጥቶ ፡ በመያዣነት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀመጥ ፡ ያደረገ ፡ እንደሆነ ፡ ክርክሩ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ተከሳሹ ፡ ታስሮ ፡ እንዲቆይ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ያግድለታል ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፳ ፡፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ የሚያዝ ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡፡

(፩) ተከሣሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ለሚጠየቀው ፡ ዕዳ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ መያዣ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ወይም ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀርብ ፡ በቂ ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራና ፡ ዋስትናውም ፡ ክሱ ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜና ፡ በተከሰሰበትም ፡ ነገር ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የሚቆይ ፡ እንዲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ ቍ ፡ (፪) ፡ መሠረት ፡ ሊያዝ ፡ ስለሚገባው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ፡፡

(፪) ተከሣሹን ፡ ለማቅረብ ፡ ዋስ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሳያቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ተከሣሹ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ ይገደዳል ፡፡

ቍ ፡ ፪፻፳፩ ፡፡ ዋስትናን ፡ ለማስወረድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡፡

(፩) ተከሣሽን ፡ ለማቅረብ ፡ ዋስ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የዋስትና ፡ ግዴታው ፡ እንዲወርድለት ፡ ለቀጠረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ማመልከቻ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ፡፡

(፪) የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማመልከቻ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲቀርብለት ፡ ተከሣሹ ፡ ተይዞ ፡ እንዲቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ፡፡

(፫) ተከሣሹ ፡ የጥሪውን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብሎ ፡ ወይም ፡ ተገድዶ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞው ፡ ዋስ ፡ አላፊነት ፡ እንዲወርድለትና ፡ ተከሣሹም ፡ ሌላ ፡ ዋስ ፡ እንዲሰጥ ፡ አዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ፡፡

(፬) አዲስ ፡ ዋስ ፡ ለመስጠት ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ሊፈረድበት ፡ ከሚችለው ፡ ገንዘብ ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ግዙፍ ፡ ሀብት ፡ በመያዣ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ይታዘዛል ፡፡

ቍ ፡ ፪፻፳፪ ፡፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ የሚያዝ ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዋስ ፡ ለመስጠት ፡ እምቢተኛ ፡ ስለመሆን ፡፡

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳ ፡ እና ፡ ፪፻፳፩ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡

BACK



(፬) ፡ መሠረት ፡ ተከሣሹ ፡ አዲስ ፡ ዋስትና ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ መያዣ ፡ ለማስቀመጥ ፡ እምቢተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪፈጽም ፡ ወይም ፡ ክርክሩ ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ እስኪያገኝና ፡ በፍርድ ፡ ከተወሰነም ፡ በኋላ ፡ እንደፍርዱ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ ተከሣሽ ፡ በእምቢተኛነቱ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ታስሮ ፡ የሚቆይበት ፡ ጊዜ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ የበለጠ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

## ክ ፍ ል ፡ ፱ ።

## ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ንብረት ፡ እንዲከበር ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

ቍ ፡ ፪፻፩ ። ተፈላጊውን ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ዋስትና ።

(፩) ክርክሩ ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ከሣሹ ፡ ወይም ፡ የተከሣሽ ፡ ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ከሣሽ ፡ ክሱን ፡ ለማሰናከል ፡ ያቀደ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ዘዴ ፡ መፍጠሩን ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ በተደገፈ ፡ አቤቱታ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ያስረዳ ፡ እንደሆነና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲረጋገጡለት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(ሀ) ተከሣሹ ፡ ንብረቱን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለማሸሽ ፡ ወይም ፡ ለማባከን ፡ ማቀዱን ፡ ወይም ፡

(ለ) ንብረቱን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ክሱ ፡ ከቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ለማሸሽ ፡ ማቀዱን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜና ፡ እንዲያዝ ፡ በሚወሰነው ፡ መጠን ፡ ተከሣሹ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ግምቱ ፡ እንዲቀርብ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ እንዲያመጣ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከሚያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሚሆን ፡ መጠን ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ወይም ፡

BACK



ይህን ፡ መያዣ ፡ የማይሰጥበትን ፡ ምክንያት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲያስ ረዳ ፡ ያዛል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈጸም ፡ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ የሚያዘውን ፡ ወይም ፡ የሚከበረውን ፡ ንብረት ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ ከሣሹ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ከሣሹ ፡ ለይቶ ፡ ያመለከታቸው ፡ ንብረቶች ፡ የሚያዙት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንደሆነና ፡ የሚያዝበትንም ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊገልጽ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፪ ። ንብረት ፡ ስለማስከበር ፡ ወይም ፡ ስለማስያዝ ።

(፩) ተከሣሹ ፡ ዋስ ፡ የማይጠራበትን ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ቀርቦ ፡ ያላስረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እንዲያስ ይዝ ፡ የታዘዘውን ፡ ገንዘብ ፡ ሳያስቀምጥ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ በዝ ርዝር ፡ ከታወቀው ፡ ንብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሚወሰንበት ፡ ፍርድ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነው ፡ ሀብቱ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲ ያስይዝ ፡ ወይም ፡ ተከብሮ ፡ እንዲቆይ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) ተከሣሹ ፡ ዋስ ፡ ያልጠራበትን ፡ ምክንያት ፡ በሚገባ ፡ ያስረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የሚፈለግበትን ፡ መያዣ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የተያዘበት ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲለ ቀቅለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያዝለት ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፫ ። የንብረት ፡ ማስያዝ ፡ ወይም ፡ ማስከበር ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈጸም ፡ በግልጽ ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡ ንብረት ፡ የሚከበረው ፡ ወይም ፡ የሚያዘው ፡ ፍርድን ፡ ለማስፈ ጸም ፡ በሚያዝበት ፡ ወይም ፡ በሚከበርበት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

(፪) ንብረቱ ፡ ከመያዙ ፡ ወይም ፡ ከመከበሩ ፡ በፊት ፡ በዚሁ ፡ ንብ ረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ የነበራቸውና ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ የሌሉ ፡ የሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ በተ ከሣሹ ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ የተ

BACK



ያዘው ፡ ወይም ፡ የተከበረው ፡ ንብረት ፡ ተሽጦ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ የመጠየቅ ፡ መብቱን ፡ አያስቀርበትም ።

(፫) ከፍርድ ፡ በፊት ፡ በተያዘ ፡ ወይም ፡ በተከበረ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ የሚለው ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ የሚመረመረው ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ የሶስተኛ ፡ ወገን ፡ መብት ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ በሚመረመርበት ፡ ዓይነትና ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

(፬) ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ንብረቱ ፡ የሚያዝበት ፡ ሰው ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ የተወሰነውን ፡ መያዣ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ባስቀመጠ ፡ ጊዜ እንዲለቀቅለት ፡ ከሚያስይዘውም ፡ ገንዘብ ፡ ጋር ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የተደረገውን ፡ ወጭና ፡ ኪሣራ ፡ ጭምር ፡ እንዲያስይዝ ፡ የገንዘቡን ፡ ልክ ፡ ወስኖ ፡ ያስታውቃል ፡ እንዲሁም ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ውድቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የተያዘው ፡ ንብረት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ገልጾ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፭) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ተከብሮ ፡ ወይም ፡ ተይዞ ፡ በነበረው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለከሣሽ ፡ የተፈረደለት ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ ፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ ሌላ ፡ ማመልከቻ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሳያስፈልግ ፡ በቀድሞው ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ንብረቱ ፡ በመያዝ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፫ ፡

## ለጊዜው ፡ ስለሚሰጥ ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡

**ቍ ፡ ፻፶፬ ። የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ለጊዜው ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፡**

በክርክር ፡ ላይ ፡ ስለሚገኝ ፡ ጉዳይ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ በመሐላ ፡ በተደገፈ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሲረጋገጥ ፡

(ሀ) ለክርክሩ ፡ መነሻና ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ንብረት ፡

የሚጠፋ ፤ የሚበላሽ ፡ ወይም ፡ ተከሣሹ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፤ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዘንድ ፡ በተሰጠ ፡ ውሳኔ ፡ ንብረቱን ፡ ያለገባብ ፡ አዛውሮ ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ያቀደ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) ተከሣሹ ፡ የባለመብቶችን ፡ ጥቅም ፡ ለመጉዳት ፡ ሲል ፡ ንብረቱን ፡ ለማጥፋት ፤ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ ያቀደ ፤ የዛተ ፡ ወይም ፡ ያሰበ ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፤ ነገሩ ፡ በፍርድ ፡ እስኪወሰን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪሰጥ ፡

ድረስ ፡ ንብረቱ ፡ እንዳለ ፡ እንዲቆይ ፤ ከመጥፋት ፡ እንዲድን ፤ እንዳይበላሽ ፤ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ተላልፎ ፡ እንዳይሰጥ ፤ ወደሌላ ፡ ሥፍራ ፡ እንዳይዛወር ፤ እንዳይባክን ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ኃይለ ፡ ቃሎች ፡ የተዘረዘሩት ፡ ነገሮች ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቊ ፡ <u>፻፶፭ ። ውል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ግዴታ ፡ ተደጋግሞ ፡ እንዳይፈርስ ፡ ወይም ፡ ለማፍረስ ፡ የተወሰደው ፡ እርምጃ ፡ እንዳይቀጥል ፡ ስለሚሰጥ ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ።</u>

(፩) ተከሣሽ ፡ የውል ፡ ግዴታውን ፡ እንዳያፈርስ ፡ እንዲታገድ ፡ በሚቀርብ ፡ በማናቸውም ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ከሣሽ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስበትና ፡ ውሉ ፡ እንዲከበር ፡ በሚያቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ እንዲሁም ፡ በአቤቱታው ፡ ላይ ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ የጠየቀ ፡ ወይም ፡ ያልጠየቀም ፡ ቢሆን ፡ ተከሣሹ ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ እንዳያፈርስ ፡ ወይም ፡ ይፈጸማል ፡ የተባለውን ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ ወይም ፡ የውሉ ፡ መፍረስ ፡ የሚያስከትለው ፡ ጉዳት ፡ እንዲወገድ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ምክንያት ፡ በተገኘው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይፈጸም ፡ ከሣሽ ፡ ጊዜአዊ ፡ ማገጃ ፡ እንዲሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለጊዜው ፡ የሚሰጠው ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚጸናበትን ፡ ጊዜ ፡ ሂሣብ ፡ ነክ ፡ የሆነ ፡ ጉዳይ ፡ ሲኖር ፡ የሂሣቡን ፡ አያያዝ ፤ ዋስ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ ዋስትናው ፡ የሚሰጥበትን ፡ ሁኔታና ፡ ሌላም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ በማመዛዘን ፡

BACK



ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ ፱፷፩ ፡ የተመለከተውን ፡ የሚሽር ፡ ወይም ፡ የሚያ ሻሽል ፡ አይደለም ።

ቍ ፡ ፪፻፲ ። የማገጃን ፡ ትእዛዝ ፡ ስላለማክበር ፡

(፩) ተከሣሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ ያላከበረ ፡ ወይም ፡ በትዛዙ ፡ ላይ ፡ የተሰጡትን ፡ ውሣኔዎች ፡ ያል ጠበቀ ፡ እንደሆነ ፤ የእምቢ.ተኛው ፡ ወይም ፡ ትእዛዙን ፡ የተላለ ፈው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ ለማዘዝና፡ ተገቢ ፡ ሆኖም ፡ ሲያገኘው ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ትእዛዝ ፡ በመጋ ፋቱ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፫ በተመለከ ተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣት ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ የንብረት ፡ መያዝ ፡ ወይም ፡ የማስከበር ፡ ትእዛዝ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ መቆየት ፡ አይችልም ። ስለሆነም፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ቢያልፍም ፡ እምቢተኛው ፡ ሰው ፡ ትእዛዝ ፡ መተላለፉን ፡ ያላቋረጠ ፡ እንደሆነ ፡ የተያዘው ፡ ወይም ፡ የተከበረው ፡ ንብረት ፡ ተሽጦ ፡ ከሽያጩ ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገባቸው ፡ ባለመብቶች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በታየው ፡ መጠን ፡ ወስኖ ፡ እንዲከፍላቸው ፡ ትእ ዛዝ ፡ ይሰጣል ። ተራፊ ፡ ገንዘብ ፡ ሲኖር ፡ አግባብ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ እንዲመለስለት ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፪፻፲፪ ። ላንደኛው ፡ ተከራካሪው ፡ ወገን ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ።

የማገጃው ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይሰጥ ፡ መዘገየቱ ፡ ጉዳትን ፡ የሚያስ ከትል ፡ መስሎ ፡ ካልታየው ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዙን ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፤ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ ለአመልካቹ ፡ ባላጋራ ፡ እንዲደርሰው ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፪፻፲፫ ። የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሻሻል ፡ ሊነሳ ፡ ወይም ፡ ሊሠረዝ ፡ ስለሚ ቻልበት ፡ ሁኔታ ።

በተሰጠው ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ ቅሬታ ፡ የተሰማው ፡ ወይም ፡

ያላገባብ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቤቱታውን ፡ ያቀረበ ፡ እንደሆነና ፡ የቀረበውም ፡ አቤቱታ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሰጥቶት ፡ የነበረው ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሻሻል ፤ እንዲነሳ ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፱ ። በሕግ ፡ በተቋቋሙ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ የሚሰጥ ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ አስገዳጅነት ።**

በሕግ ፡ በተቋቋሙ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ ጊዜአዊ ፡ የማገጃ ፡ ውሣኔ ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ ተግባራቸው ፡ እንዳይቀጥል ፤ ለጊዜው ፡ እንዲታገድ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ በሚገመቱት ፡ በማኅበሩ ፡ አባሎችና ፡ በሥራ ፡ መሪዎቹም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ክ ፍ ል ፦ ፬ ፡

## ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

**ቍ ፡ ፪፻፲ ። ክርክሩ ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲሸጥ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ተቀዳሚ ፡ ትእዛዝ ።**

ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ በሚያቀርብለት ፡ ማመልከቻ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከፍርድ ፡ በፊት ፡ የተያዘው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ሀብት ፡ ክርክሩ ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ተይዞ ፡ ቢቆይ ፡ የሚበላሽ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ተይዞ ፡ ከመቆየቱ ፡ ይልቅ ፡ ቢሸጥ ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ ተለይቶ ፡ በሚገለጸው ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ሀብቱ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። ክርክር ፡ የተነሣበትን ፡ ሀብት ፡ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ አኑሮ ፡ ስለ መጠበቅ ፤ እንዳይበላሽ ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥንቃቄና ፡ የመቆጣጠር ፡ ምርመራ ።**

(፩) ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ በሚያቀርብለት ፡ ማመ

BACK



ልከቻ ፡ መሠረትና ፡ የቀረበለት ፡ ጥያቄ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(ሀ) ለክርክሩ ፡ መነሻና ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ ሊነሳበት ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ የተገመተው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ በተወሰነ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀምጦ ፡ እንዲጠበቅ ፤ እንዲያዝ ፤ እንዲፈተሽ ፡ ለማዘዝ ፤

(ለ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ጉዳይ ፡ ለማስፈጸም ፡ የተባለው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ በሚገኝበት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለማለፍ ፤ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሥፍራ ፡ ሄዶ ፡ እንዲመረምር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመረጠውን ፡ ሰው ፡ ለማዘዝ ፡ ወይም ፡ የታዘዘበትን ፡ ጉዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ሥፍራ ፡ ገብቶ ፡ ለምርመራ ፡ የሚያገለግል ፡ ዓይነት ፡ ለመውሰድ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ምርመራ ፡ ለማድረግ ፡ የሚፈተሽ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ለመፈተሽ ፡ ወይም ፡ አፈጻጸሙ ፡ ሊፋጠን ፡ የሚችልበትን ፡ ማገጃ ፡ የሚገኝበትን ፡ መንገድ ፡ ለመከታተል ፡ የሚያስችለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ምሥክሮች ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ አሰጣጥ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ ለተመለከተውም ፡ ጉዳይ ፡ እንደነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቊ ፡ ፻፷፪ ። ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ለባላጋራው ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለመስጠት ።**

(፩) ክሱ ፡ ከተጀመረ ፡ በኋላ ፡ ለተከሣሹ ፡ አስቀድሞ ፡ ማስታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ ከሣሹ ፡ በቍጥር ፡ ፻፷ ወይም ፡ ፻፷፩ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በነዚሁ ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ ትእዛዞች ፡ እንዲሰጡለት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተከሣሹ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በበኩሉ ፡ በሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚህ ፡ በላይ የተነገረው ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰ

BACK



ጥለት ፡ የጠየቀ ፡ እንደሆነ ፡ አስቀድሞ ፡ ለከሣሹ ፡ ማስታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገሩት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተ ውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪፻፫ ። ሽያጭን ፡ ስለማገድ ።

(፩) ክስ ፡ የተነሳበትን ፡ መሬት ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ የተከ ራየ ፡ ሰው ፡ ለመንግሥት ፡ የሚከፈለውን ፡ ግብር ፡ ያልከፈለ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ለባለመሬቱ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ አበል ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ መሬቱ ፡ እንዲሸጥ ፡ በታዘዘ ፡ ጊዜ ፡ በርስቱ ፡ ያገባኛል ፡ ወይም ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ የሚል ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ ሲቀርብ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚከፈለውን ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ ለባለርስቱ ፡ የሚከፈለውን ፡ አበል ፡ ከፍሎ ፡ ሽያጩ ፡ እንዲታገ ድለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ማመልከቻውን ፡ ተቀብሎ ፡ ሽያጩ ፡ ታግዶ ፡ ስለሚቆይበት ፡ ሁኔታ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ውሣኔ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ከታ የው ፡ ወለድ ፡ ጋር ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ የመንግሥት ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ የባለርስቱን ፡ አበል ፡ ሳይከፍል ፡ በመቅረቱ ፡ መሬቱ ፡ ለተሸጠበት ፡ ሰው ፡ እንዲመለስለት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፡ ወይም ፡ ሂሣብ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የተያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከወሰነው ፡ ወለድ ፡ ጋር ፡ በሂሣቡ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ከዕዳው ፡ ጋር ፡ እንዲቻቻል ፡ በሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ ውስጥ ፡ በመግለጽ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፬ ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚቀመጥ ፡ ገንዘብ ።

ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚችል ፡ ዕቃ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ስለሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ የያዘው ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ንብረትነቱ ፡ የሌላው ፡ ወገን ፡ መሆ ኑን ፡ ያመነ ፡ እንደሆነ ፡ ዕቃው ፡ ወይም ፡ ገንዘቡ ፡ ለአደራ ፡ አስ ቀማጩ ፡ ወይም ፡ ለባለ ፡ ሀብቱ ፡ እንዲመለስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ሲመለስለት ፡ ተቀባዩ ፡ ዋስ ፡

BACK



እንዲጠራ ፡ ወይም ፡ ያለዋስ ፡ እንዲረከብ ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፷፭ ። ስለ ፡ ሌሎች ፡ ትእዛዞች ።

ክርክሩ ፡ በመስማት ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ያመለከተ ፡ መሆኑን ፡ ባላጋራው ፡ ለሆነው ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ በሚገባ ፡ ሲያስታውቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በሚገምተው ፡ ሁኔታ ፡ ነገሩን ፡ ለማፋጠን ፡ ወይም  በቶሎ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማድረግ ፡ ምቹ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠትና ፡ በተጨማሪም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ሰው ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ጉዳይና ፡ ክርክሩ ፡ የባልና ፡ ሚስትን ፡ ፍቺ ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፡ የሀብታቸውን ፡ ክፍያ ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ የሚሰጠውን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ገንዘብ ፡ የሚወስን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

## ክ ፍ ል ፳ ።

## ተቀባይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ስለመሾም ።

ቍ ፡ ፻፷፮ ። ተቀባይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ስለሚሾምበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚመችና ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ትእዛዞች ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(ሀ) ውሣኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ማናቸውንም ፡ ንብረትና ፡ ሀብት ፡ ተቀብሎ ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ መሾም ፤

(ለ) የማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ይዞታ ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ አስቀማጭነት ፡ ወይም  ጠባቂነት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የያዘውን ፡ ንብረት ፡ እንዲለቅ ፤

(ሐ) ባለ ፡ ይዞታው ፡ ወይም ፡ ጠባቂው ፡ የለቀቀውን ፡ ነገር ፡ ተቀባዩ ፡ ተረክቦ ፡ እንዲጠብቅና ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ለማዘዝ ፤

(መ) ተቀባዩ ፡ የተረከበውን ፡ ንብረት ፡ ለመጠበቅና ፡ ለማስተዳደር ፡ ለማሻሻል ፡ የሚያስችለው ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖረው ፡

BACK



ስለተቀበለው ፡ ንብረት ፡ የመክሰስ ፡ ወይም ፡ የመከሰስ ፡ መብት ፡ እንዲኖረው ፡ እንዲሁም ፡ ኪራይ ፤ አበል ፡ ወይም ፡ ማንኛውንም ፡ የንብረት ፡ ገቢ ፡ ለመሰብሰብና ፡ የሰበሰበውንም ፡ ገንዘብ ፡ ጠቃሚ ለሚሆን ፡ ጉዳይ ፡ ለማዋል ፡ እንዲችልና ፡ ባለንብረቱ ፡ ራሱ ፡ ለመፈጸም ፡ እንደሚችለው ፡ ሁሉ ፡ ውል ፡ የመጻጻፍንና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ የታየውን ፡ ሌላ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቊጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚቀርበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ሆነ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሰጠው ፤ አመልካቹ ፡ የጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፤ የሚሾመው ፡ ተቀባይ ፡ ሊሰበስብ ፡ ወይም ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለውን ፤ ተቀባዩን ፡ ለመሾም ፡ የሚደረገውን ፡ ወጭ ፡ በማመዛዘንና ፡ በተለይ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግበት ፡ ሌላም ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ አብሮ ፡ እንዲጣራ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

## ቊ ፡ ፪፻፺፯ ። ለተቀባዩ ፡ ስለሚከፈል ፡ አበል ።

ለተቀባዩ ፡ የሚከፈለውን ፡ አበል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚሰጠው ፡ ጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ይወሰናል ።

## ቊ ፡ ፪፻፺፰ ። ስለተቀባዩ ፡ ግዴታዎች ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፪፻፺፮ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የሚሾም ፡ ተቀባይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ መፈጸም ፡ ይኖርበታል ።

(ሀ) ተቀባይ ፡ ሆኖ ፡ እንዲያስተዳድር ፡ የተሾመበትን ፡ ንብረት ፡ በሚገባ ፡ ለመጠበቅ ፡ ለዚሁ ፡ ንብረት ፡ አላፊና ፡ ተጠያቂ ፡ ለመሆን ፡ የሚችል ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ እንዲሰጥ ፡

(ለ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜና ፡ በሚሰጠው ፡ የአቀራረብ ፡ ሥርዓት ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የንብረቱን ፡ ገቢና ፡ ወጭ ፡ የሚሣብ ፡ መግለጫ ፡ እየሠራ ፡ እንዲያቀርብ ፤

(ሐ) የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍልና ፡

(መ) በራሱ ፡ ከባድ ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ባደረገው ፡ ጉድለት ፡ በተረከበው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ እንዲከፍል ።

BACK



**ቍ ፡ ፻፷፱ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀባዩን ፡ ግዴታ ፡ ስለሚያስፈጽምበት ፡ ሥርዓት ።**

ተቀባዩ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ጉድለቶች ፡ ፈጽሞ ፡ ሲገኝ ፥

(ሀ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜና ፡ በሰጠው ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የሚያስተዳድረውን ፡ ንብረት ፡ ሂሣብ ፡ ሳያቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤

(ለ) የሚፈለግበትን ፡ ሂሣብ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወስኖ ፡ ካዘዘው ፡ በኋላ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤

(ሐ) በራሱ ፡ ከፍተኛ ፡ ቸልተኛነት ፡ ወይም ሆነ ፡ ብሎ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ ያደረሰ ፡ እንደሆነ ፤ ንብረቱ ፡ ተሽጦ ፡ ከሽያጩ ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ ሀብት ፡ በቸልተኛነት ፡ ወይም ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ያደረሰው ፡ ጉድለት ፡ እንዲተካ ፡ ወይም ፡ ጉዳቱን ፡ ለመጠገን ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሂሣብ ፡ እንዲከፈል ፡ በማዘዝ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖርም ፡ እንዲመለስለት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፮ ።

## ስለማሽግና ፡ የሀብት ፡ ዝርዝር ፡ ስለማዘጋጀት ።

**ቍ ፻፸ ። መሠረቱ ።**

(፩) ለክርክር ፡ መነሻና ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ ይነሳበታል ፡ ተብሎ ፡ የሚታመን ፡ ንብረት ፡ ሲኖርና ፡ ይህንንም ፡ በሚገባ ፡ አሽጎ ፡ መጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ የተደረገውን ፡ እሽግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲነሳ ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ለመቅደድ ፡ ወይም ፡ ለመክፈት ፡ አይችልም ። ስለሆነም ፡ እሽጉ ፡ ይነሳልኝ ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፸፩ ። እሽግ ፡ እንዲደረግ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።**

(፩) ማንም ፡ ሰው ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ ያስ

BACK



ነሣል ፡ ተብሎ ፡ የሚታመን ፡ ንብረት ፡ እንዲታሸግ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በመሐላ ፡ በተደገፈ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ በተረጋገጠ ፡ ማስረጃ ፡ አስረድቶ ፡ አንድ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንዲታሸግለት ፡ ለፍ ርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከት ፡ ይችላል ።

(፪) ክርክሩ ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ የማሸግ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤት ፡ የማሸግ ፡ ትእዛዝ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ ይሾማል ፤ ስለ ዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የተመረጠውም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከ ቱት ፡ ቍጥሮች ፡ አገላለጽ ፡ አሻጊ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ቍ ፡ ፻፸፱ ። ስለ ፡ መዝገብ ።

(፩) አሻጊው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የእሽጉን ፡ ሥራ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተገለጹትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚያመለክት ፤ የራሱ ፡ ፊርማ ፡ የተፈረመበት ፤ የተሠራበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረተ ፡ ያለበት ፡ መዝገብ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ይይ ዛል ።

በመዝገቡም ፡ ላይ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ዎች ፡ ይሠፍሩበታል ።

(ሀ) የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝና ፡ ትእዛዙ ፡ የተሰጠበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፤

(ለ) የታሸጉትን ፡ ነገሮች ፡ ዝርዝርና ፡ የሚገኙበትን ፡ ሥፍራ ፤

(ሐ)እንዲታሸጉ ፡ ከታዘዙት ፡ ውስጥ ፡ መገኘትና ፡ መታሸግ ፡ የሚገባቸው ፡ ሆነው ፡ ሳይገኙ ፡ የቀሩትን ፡ (የጐደሉትን ) ፡ ነገ ሮች ፡ ዝርዝር ፤

(መ)የታሸጉት ፡ ነገሮች ፡ ያሉበትን ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የሚገኙበ ትን ፡ ቦታ ፤ የሚጠብቀውን ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ቤትና ፡ ሥፍራ ፡ አላፊነት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ስም ።

(፪) የታሸጉት ፡ ነገሮች ፡ የሚገኙበት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ሥፍራ ፡ ቁልፍ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ አሻጊው ፡ መክፈቻዎቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ለፍ

ርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጂስትራር ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፸፫ ። ስለማይታሸግባቸው ፡ ነገሮች ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ እሽግ ፡ እንዲደረግ ፡ አይታዘዝም ፤

(ሀ) በተፈጥሮአቸው ፡ የሚበላሹ ፡ ወይም ፡ ቶሎ ፡ የሚሻግቱና ፡ የሚበሰብሱ ፡ ሲሆኑ ፤

(ለ) በመታሸጋቸው ፡ ምክንያት ፡ የሚበላሹ ፡ ወይም ፡ የሚሻግቱና ፡ የሚበሰብሱ ፡ ሲሆኑ ፤

(ሐ) በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ለሆነው ፡ ወገን ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆናቸውን ፡ ተረድቶ ፡ እንዳይታሸግባቸው ፡ ያዘዘ ፡ ሲሆን ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በሐ) ፡ ፊደል ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ከተከራካሪዎች ፡ ወገኖች ፡ ላንደኛው ፡ አገልግሎት ፡ አስፈላጊ ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ እንዳይታሸግባቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ያልታሸገባቸውን ፡ ነገሮች ፡ ዝርዝር ፡ አሻጊው ፡ አዘጋጅቶ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፸፬ ። ስለ ፡ ኑዛዜዎችና ፡ ስለ ፡ ሌሎች ፡ ጽሑፎች ።

(፩) አሻጊው ፡ በሚያሽገው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የኑዛዜ ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ ቀድሞ ፡ የታሸጉ ፡ ነገሮች ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፤ የነዚሁኑ ፡ ጽሑፎች ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጅቶ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ጠቅልሎ ፡ በእሽጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ያዘጋጀውን ፡ ዝርዝር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያቀርባል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ እነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ ስለሚቀመጡበት ፡ ሁኔታና ፡ ስለ ፡ አያያዛቸው ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ውሣኔ ፡ ይሰጣል ።

እሽግን ፡ ስለ ፡ ማንሳት ።

ን ፡ እንዲነሳ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡

ኑ ፡ አስተያየት ፡ እሽጉን ፡ ማንሳት ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡

ዙን ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያላ

ቸው ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ያዛል ፤ ባለጉዳዮቹም ፡ ቀርበው ፡ ያላቸውን ፡ አሳብ ፡ ለማመልከት ፡ ይችላሉ ።

(፪) እሽጉ ፡ እንዲነሳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ አሻጊው ፡ ሲከፍት ፡ የተገኙትን ፡ ዕቃዎችና ፡ ነገሮች ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጅቶ ፡ ከፈረመባቸው ፡ በኋላ ፡ ቀኑንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ ጽፎ ፡ ያቀርባል ።

## ቍ ፡ ፪፻፺፯ ። የዕቃዎችንና ፡ የንብረቶችን ፡ ዝርዝር ፡ ስለማዘጋጀት ።

(፩) ለክርክሩ ፡ መነሻና ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ወይም ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ ንብረት ፡ ዝርዝር ፡ እንዲዘጋጅና ፡ እንዲታወቅ ፡ ማስፈለጉን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፡ ይህንኑ ፡ ዝርዝር ፡ ለማዘጋጀት ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ የሚገምተውን ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ የዚሁኑ ፡ ንብረት ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጅቶ ፡ እንዲቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጠዋል ። ይህንን ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽም ፡ የሚታዘዝ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ መዝጋቢ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

(፪) መዝጋቢው ፡ ከሁለት ፡ የማያንሱ ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ተለይቶ ፡ የተገለጸውን ፡ የንብረት ፡ ዝርዝር ፡ ያዘጋጃል ። ዝርዝሩም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ ይይዛል ።

(ሀ) የዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝና ፡

(ለ) የተመዘገቡትን ፡ ዕቃዎች ፡ ትክክለኛ ፡ ዝርዝር ፡ ከዋጋቸው ፡ ግምት ፡ ጋር ።

(፫) የዕቃዎቹ ፡ ወይም ፡ የንብረቶቹ ፡ ዋጋ ፡ የሚገመተው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፪፻፴፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፤ በልዩ ፡ አዋቂ ፡ (በኤክስፔርት) አማካይነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ልዩ ፡ አዋቂው ፡ ባደረገው ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ላይ ፡ ቀ
ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ ጽፎና ፡ ፈርሞበት ፡ ከመዝጋቢ
ጋር ፡ ይያያዛል ።

(፬) የመዝጋቢው ፡ ራፖር ፡ የተጻፈበት ፡ ቀ
ረት ፡ ተሞልቶበትና ፡ ተፈርሞበት ፡ ለፍር

ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በተለይ ፡ ይህን ፡ ለመሰለው ፡ ጉዳይ ፡ በተዘጋ ጀው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ሬጂስትራሩ ፡ እንዲመዘግበው ፡ ካደ ረገ ፡ በኋላ ፡ ከክርክሩ ፡ መዝገብ ፡ ጋር ፡ በመያያዝ ፡ አባሪ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ያደርጋል ።

## ክፍል ፡ ፲ ፤

## ተገድዶ ፡ የመያዝን ፡ ሕጋዊነት ፡ ለማጣራት ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤

ቍ ፡ ፻፸፯ ። ተገድዶ ፡ በመያዝ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ።

(፩) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተደነገገ ውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይወስንበት ፡ ወይም ፡ ሳይፈርድበትና ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይሰጥ ፤ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ የተገደደ ፤ እንዳይዘዋወር ፡ የተከለከለ ፤ የተያዘ ፡ ወይም ፡ የታሰረ ፡ ሰው ፡ ሲኖር ፤ ይህ ፡ አድራጐት ፡ እንዲወገድ ለትና ፡ ራሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲያስረዳ ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

(፪) ማመልከቻው ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ሆኖ ፡ የተያዘውን ፡ ወይም ፡ የተገደደውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የአስገዳጁን ፡ ወይም ፡ የያ ዡን ፡ ሰው ፡ ስም ፤ ተገዶ ፡ የተያዘበትን ፡ ሥፍራ ፡ ይህንኑም ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ሰዎች ፡ እንዳሉ ፡ የምስክሮቹን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ ዘርዝሮ ፡ የሚገልጽ ፡ ይሆናል ።

(፫) የተያዘው ፡ ወይም ፡ የተገደደው ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ምክን ያት ፡ አቤቱታውን ፡ ራሱ ፡ ለማቅረብ ፡ ያልቻለ ፡ ወይም ፡ የመ ሐላ ፡ ቃሉን ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ ለመስጠት ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊያቀርብለት ፡ ይችላል ። ይህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አመ ልካቹ ፡ በሚሰጠው ፡ የመሐላ ፡ ቃልና ፡ በማመልከቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ ባለጉዳይ ፡ ለመቅረብ ፡ ወይም ፡ ማመልከቻ ፡ ለመ ጻፍ ፡ ያልቻለ ፡ መሆኑን ፡ ጭምር ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

BACK



**ቊ ፡ ፪፻፷፰ ። እንዲቀርብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፪፻፷፯ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት፤ አስገዳጁ ፡ ወይም ፡ አሳሪው ፡ ተገዳጁን ፡ ወይም ፡ ታሳሪውን ፡ ሰው ፡ ይዞ ፡ እንዲቀርብና ፡ ይህንንም ፡ ሰው ፡ የማይለቅበትን ፡ ምክን ያት ፡ እንዲያስረዳ ፡ በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ የመቅረቢያውን ፡ ቀ ን ፡ ቀጠሮ ፡ ወስኖ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ላዩ ፡ ነገሩን ፡ በምስክርነት ፡ ለማስረዳት ፡ ይችላሉ ፡ ተብለው ፡ የተጠቀ ሱት ፡ ምስክሮች ፡ እንዲቀርቡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥሪ ፡ ሊሰጥ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፪፻፷፱ ። ጉዳዩን ፡ ስለመስማት ፤ ውሣኔ ፡ ስለመስጠትና ፡ ስለ ፡ ማመልከቻ ፡ አቀራረብ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡ ፪፻፷፰ ፡ መሠረት ፡ በሚሰጠው ፡ መጥሪያ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ በቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ የተገለጸውን ፡ አቤቱታ ፡ እውነተኛነት ፡ ፍርድ ቤቱ ፡ ይመረምራል ፤ ስለማስረጃው ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) አመልካቹ ፡ የተያዘው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ መሆኑን፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ትእዛዝ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲኖር ፡ ሳያስፈልግ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፫) በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ የአቤቱታ ፡ ቃል ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያጠራጥር ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ዋስ ፡ ጠርቶ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ያዛል ፤ ዋስትናውም ፡ የገንዘብ ፡ ማስያዝ ፡ ወይም ፡ የሰው ፡ ዋስትና ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በዋስትናውም ፡ የሚገባው ፡ ግዴታ ፤ እንዲለቀቅ ፡ ያደረገው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፈለገው ፡ ጊዜ ፡ እንዲቀርብ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ አክብሮ ፡ እንዲፈጽም ፡ የሚያስገድደው ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ፡

## ስለ ፡ ፍርድና ፡ ስለ ፡ ትእዛዝ ፤

## ክፍል ፡ ፩ ፡

## አጠቃላይ ፡ ድንጋጌዎች ፡

**ቍ ፡ ፻፹ ። ፍርድ ፡ የሚሰጥበት ፡ ጊዜ ።**

የቀረበው ፡ ክርክር ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩ ፡ እንዳለቀ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወይም ፡ በአጭር ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ ችሎት ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፹፩ ። የፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ሁኔታና ፡ ፎርም ።**

(፩) ፍርድ ፡ ተጽፎና ፡ በአስቻሉት ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ ዳኛ ፡ ተፈርሞ ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ይነበብላቸዋል ።

(፪) በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፤ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ብይን ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ። ስለሆነም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሆነው ፡ ባስቻሉ ፡ ዳኞች ፡ በታየ ፡ ጉዳይ ፤ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ከተስማሙት ፡ ዳኞች ፡ በሃሣብ ፡ የተለየው ፡ ዳኛ ፤ በራሱ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ አስተያየት ፤ ሊሰጥ ፡ ይገባቀል ፡ የሚለውን ፡ ፍርድ ፡ በዝርዝር ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፫) ፍርድ ፡ ተጽፎ ፡ በፈረዱት ፡ ዳኞች ፡ የተፈረመበት ፡ ከሆነ ፤ ሌላ ፡ ዳኛም ፡ ቢሆን ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በንባብ ፡ ሊያሰማ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፹፪ ፦ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሐተታ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠፍሩ ፡ ነገሮች ፤**

(፩) በአንድ ፡ የፍርድ ፡ ሐተታ ፡ ላይ ፡ የተያዘው ፡ ጭብጥ ፤ ጭብጡ ፡ እንዴት ፡ እንደተወሰነና ፡ የተወሰነበት ፡ ምክንያት ፡ መገለጽ ፡ አለበት ። ስለሆነም ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆነውን ፡ ዋነኛ ፡ ጉዳይ ፡ ባጭር ፡ የሚገልጽ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። እንዲሁም ፡ የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ያሻሻለው ፡ ወይም ፡ የለወጠው ፡ እንደሆነ ፡ በትችቱ ፡ ላይ ፡ ለይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የሚገባውን ፡ ዳኝነት ፡ ዘርዝሮ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በዝርዝር ፡ ባላቀረቡት ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ ባላመለከቱት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ። የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ መወሰን ፡ ይገባው ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ በሚገምተው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። በተጨማሪም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውንና ፡ ነገሩን ፡ ለማስፈጸም ፡ ተስማሚ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚገምተውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ውሣኔ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) በክርክሩ ፡ ላይ ፡ ከቀረቡት ፡ ብዙ ፡ ጭብጦች ፡ አንዱ ፡ ጭብጥ ፡ ብቻ ፡ ቢወሰን ፡ ሌሎቹንም ፡ ጭብጦች ፡ ያጠቃልላቸዋል ፡ ብሎ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፤ ክርክሩን ፡ ባንድ ፡ ጭብጥ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀረቡትን ፡ ጭብጦች ፡ ሁሉ ፡ በየራሳቸው ፡ መወሰን ፡ የሚያስፈልግ ፡ ከሆነ ፡ ስለ ፡ እያንዳንዱ ፡ ጭብጥ ፡ አወሳሰን ፡ የተሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ በትችት ፡ ላይ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፪፻፫ ፡- ስለ ፡ ውሣኔ ፡ አጻጻፍ ፡ ሥርዓትና ፡ በላዩም ፡ ስለሚገለጹት ፡ ነገሮች ፤

(፩) ፍርድ ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመራው ፡ በትእዛዝ ፡ መልክ ፡ ሆኖ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ነገሮች፡ ይገለጹበታል ፤ ይኸውም ፡

(ሀ) የክሱ ፡ ወይም ፡ የይግባኙ ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፡

(ለ) የተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ስምና ፡ ልዩ ፡ ማብራሪያ ፤

(ሐ) ፍርዱ ፡ የተሰጠው ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ሲሆን ፡ የክሱ፡ ዝርዝር ፤

(መ) እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ከማድረግ ፡ እንዲወገድ ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፤ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ የተገለጸውን ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽም ፡ ወይም ፡ ከመፈጸም ፡ እንዲታገድ ፤ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲያስረክብ ፡ ወይም ፡ እንዲለቅ ፤ ተገቢም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፩ ፡ በተ

ነገረው ፡ መሠረት ፡ የጉዳዩን ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ።

(ሠ) ክሱን ፡ ለማስተካከል ፡ ወይም ፡ ይግባኙን ፡ ለማስፈጸም፡ የተደረገውን ፡ ማናቸውንም ፡ የወጭ ፡ ዝርዝር ፤ ወጭውን ፡ ማን ፡ እንደሚከፍልና ፡ የትኛው ፡ ንብረት ፡ ተሸጦ ፡ መከፈል ፡ እንደሚገባው ፡ መግለጽ ፤ ስለሆነም ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኙን ፡ በሰማበት ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ኪሣራና ፡ ወጭ ፤ ስለከፋዩም ፡ ወገን ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

(ረ) ለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምቹ ፡ መስለው ፡ የታዩትን ፡ ነገሮች ፡ መግለጽ ፤ የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲሆን ፡ ስለ ፡ ፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። ወይም ፡ እንደፍርዱ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ነገሩን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ለሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልሶ ፡ ይልካል ።

(ሰ) የፍርድ ፡ ባለዕዳውን ፡ በቀጥታ ፡ በማዘዝ ፡ ፍርዱን ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ እንደፍርዱ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ጊዜ ፡ ወስኖ ፡ ማስታወቅ ፡ ነው ።

(፪) የትእዛዙ ፡ ውሣኔ ፡ በነገሩ ፡ ተስማምተው ፡ በጻፉት ፡ ወይም ፡ በጻፈው ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ተፈርሞ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ይሞላበታል ። በሃሳቡ ፡ ያልተስማማው ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ ባልተስማሙበት ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ መፈረም ፡ የለባቸውም ። ስለሆነም ፡ ፍርዱን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ በሕመም ፤ በሞት ፡ ወይም ፡ በዝውውር ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ መፈረም ፡ ያልቻለ ፡ ዳኛ ፡ ሲኖር ፤ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ የተዘጋጀው ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርድ ፡ ከሰጡት ፡ ዳኞች ፡ ባንደኛው ፡ ወይም ፡ በሁለቱ ፡ ሊፈረም፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሠረዘ ፡ ወይም ፡ ከሥፍራው ፡ የተነሣ፡ እንደሆነ ፤ ውሣኔ ፡ ከሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከአንድ ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛ ፡ በሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይፈረማል ።

ቍ ፡ ፻፹፩ ። ስለፍርድና ፡ ስለ ፡ ትእዛዝ ፡ ግልባጭ ።

(፩) ትክክለኛነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ የፍርድ ፡ ወይም ፡ የትእዛዝ ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጠው ፡ የሚጠይቅ ፡ በጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ተከራካሪ ፡ ፍርዱን ፡ ወይም ፡ የትእዛዙን ፡ ውሣኔ ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡

ቤት ፡ ሬጂስትራር ፡ ማመልከቻውን ፡ ሲያቀርብ ፤ ግልባጩን ፡ አዘጋጅቶ ፡ የተሰጠበትን ፡ ቀንና ፡ ዓ. ም. ሞልቶ ፡ ለጠያቂው ፡ ይሰጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ሲሆን ፡ ይግባኙን ፡ ተቀብሎ ፡ የወሰነው ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የውሣኔውን፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፤ ነገሩን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ላየው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ይልክለታል ። ግልባጩም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግቦ ፡ የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ፡ ከተደረገበት ፡ መዝገብ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ይቀመጣል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡

### ባንዳንድ ፡ ውሣኔ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የተለየ ፡ መምሪያ ፡

**ቍ ፡ ፪፻፰ ። የሚንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ለማስረከብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ፡**

የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላንደኛው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ እንዲ ተላለፍ ፤ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ እጅ ፡ እንዲዛወር ፣ በሚሰጥ ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፤ በውሣኔው ፡ መሠረት ፡ ንብረቱን ፡ ሳያስረክብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሚሆን ፡ ጥሬ ፡ ገን ዘብ ፡ በምትኩ ፡ እንዲከፍል ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፱ ፡- በየጊዜው ፡ ለሚከፈል ፡ ዕዳ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ፤**

(፩) የሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚያዝ ፡ ሲሆን ፡ የብድሩ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ የአከፋፈሉ ፡ ግዴታ ፡ ስምምነት፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ የተጻፈ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲያጋጥመው ፡ የመክፈያውን ፡ ጊዜ ፡ ለማዘግየት ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲከፍል ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። በተጨማሪም ፡ ገንዘቡ ፡ ከነወለዱ ፡ ወይም ፡ ያለወለድ ፡ እንዲከፈል ፡ ያዛል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሲያመለክት ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፯ ፡ በተነገረው ፡ ሁኔታ ፡ ምርመራ ፡ ሲደረግ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ሲስማማ ፤ ከውሣኔ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፯ ፦ ይዞታንና ፡ ያላገባብ ፡ የተወሰደ ፡ ጥቅምን ፡ ስለሚመለከት ፡ ውሣኔ ፤**

ክሱ ፡ የቀረበው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፤ አላባንና ፡ የተወሰደ ፡ ሌላ ፡ ጥቅምን ፡ ለማስመለስ ፡ ሲሆን ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ ንብረቱ ፡ ወይም ፡ አላባው ፡ ከተወሰደበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ክስ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፤ ክሱም ፡ ቀርቦ ፡ በፍርድ ፡ እስከ ፡ ተወሰነበትና ፡ ይዞታው ፡ ለባለምብቱ ፡ እስከሚመለስበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያላገባብ ፡ የተወሰደው ፡ ንብረትና ፡ አላባ ፤ ሌላ ውም ፡ ጥቅም ፡ ያስገኘውን ፡ ኪራይና ፡ የሰጠውን ፡ ፍሬ ፤ ማንኛ ውንም ፡ ሒሳብ ፡ ጭምር ፡ እንዲከፍል ፡ ለማዘዝ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፰ ፦ ስለ ፡ ማስተሳሰብ ፤**

አንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ማግኘት ፡ የሚገባውን ፡ አጣርቶ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ ፍርድ ቤት ፡ በሾመው ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ እጅ ፡ የሚገኘውን ፡ የንብረት ፡ ገቢና ፡ ወጭ ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ሲያስፈልግ ፤ ወይም ፡ በሿሚውና ፡ በተሿሚው ፡ በወካይና ፡ በተወካዩ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ በሽርክና ፡ የተቋቋመ ፡ ንግድ ፡ የሚፈርስ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በሽሪኮቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ሲያስፈልግ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ውሣኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ሒሳብ ፡ እንዲደረግና ፡ ስለ ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራቱም ፡ አፈጻጸም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ መሪ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፫፻፱ ፦ በሽርክና ፡ የተቋቋመ ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ እንዲፈርስ ፡ በቀረበ ፡ ክስ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፤**

በሽርክና ፡ የተቋቋመ ፡ ንግድ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ ሒሳቡ ፡ እንዲጣራ ፡ በሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሣኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፤ የተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ድርሻ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መሆን ፡ እንደሚገባው ፡ ከለየ ፡ በኋላ ፡ እንዲሁም ፡ የሽርክናው ፡ አቋም ፡ የሚፈርስበትን ፡ ቀን ፡ በመግለጽ ፡ ስለ ፡ ሒሳቡ ፡ መጣራትና ፡ ስለሌላም ፡ ጉዳይ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፶ ፡- ንብረትን ፡ ለማካፈል ፡ ወይም ፡ ይዞታን ፡ ለመለየት ፡ ስለሚ ቀርብ ፡ ክስ ፤

ንብረት ፡ እንዲከፈል ፡ ወይም ፡ ይዞታ ፡ እንዲለይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፤ የክፍያው ፡ ወይም ፡ የይዞታው ፡ ወይም ፡ የመብቱ ፡ መለየት ፡ ጉዳይ ፡ ተጨማሪ ፡ ምርመራ ፡ ሳይ ደረግ ፡ ሊፈጸም ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ የተረዳ ፡ እንደሆነ ፤ የመ ጨረሻ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ የእያንዳንዱን ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ መብት ፡ በመግለጽ ፡ ብቻ ፡ ነገሩን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድ ረስ ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፶፩ ፡- በማቻቻል ፡ ውሣኔ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፤

(፩) የማቻቻል ፡ ውሣኔ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ በሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ለሌላው ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ልክ ፡ ይገልጻል ። እንዲሁም ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ለሌላው የሚመስለውን ፡ ወይም ፡ የሚከፍለውን ፡ ሂሣብ ፡ ይወስናል ።

(፪) ውሳኔው ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ እንደሆነ ፡ ይግባኙ ፡ የሚወሰ ነው ፡ ሌሎቹ ፡ የይግባኝ ፡ ክርክሮች ፡ በሚወሰኑበት ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፯ ፡

## ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፤

### ክፍል ፡ ፩ ፡

### ስለጊዜ ፡ አወሳሰንና ፡ ስለ ፡ ቀጠሮ ፡

ቍ ፡ ፻፶፪ ፡- ስለ ፡ ጊዜ ፡ አወሳሰንና ፡ አቆጣጠር ፤

(፩) በአንድ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ መደረግ ፡ የሚገ ባው ፡ ነገር ፡ ሲኖርና ፡ ይህም ፡ የሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ያል ተወሰነ ፡ ሲሆን ፤ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ ፍርድ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ።

(፪) በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ተገልጾ ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡ በሕግ ፡ የተወሰ ነውን ፡ ጊዜ ፡ ማሳጠር ፡ ወይም ፡ ማስረዘም ፡ አይቻልም ።

(፫) በሕግ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተወሰነው ፡ ወይም ፡ የሚወ ሰነው ፡ ጊዜ ፡ አቆጣጠር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡

ሺ፰፻፺፰ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፻ ፺፫ ፡- የጊዜን ፡ ውሣኔ ፡ ስለማክበር ፤

(፩) አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲፈጸም ፡ በተሰጠው ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ መሠረት ፡ ጉዳዩ ፡ ተፈጽሟል ፡ ወይም ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ተከብሯል ፡ የሚባለው ፤ ጊዜ ፡ የተወሰነለት ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለፉ ፡ ከአንድ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፪) አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲፈጸም ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በመፈጸሙ ፡ ወይም ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደሆነ ፤ ነገሩ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መፈጸሙን ፡ ማስረዳት ፡ የሚገባው ፡ ጊዜውን ፡ አክብሬአለሁ ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ነው ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ /፪/ ፡ በተመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ አወሳሰን ፤ ግልጽ ፡ ወይም ፡ መደበኛ ፡ የሆኑ ፡ የገቢና ፡ የውጭ ፡ ሰነዶች ፤ ደረሰኞች ፡ ወይም ፡ በማኅተም ፡ የተረጋገጡ ፡ ጽሑፎች ፡ የተደለዙ ፡ ወይም ፡ ወደሐሰተኛነት ፡ የተለወጡ ፡ ናቸው ፡ ካልተባሉ ፡ በቀር ፡ አስረጂነታቸው ፡ በቂ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፻ ፺፬ ፡- የጊዜን ፡ ወሰን ፡ ስለማራዘም ፤

(፩) በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሰጠው ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ ጊዜውን ፡ አራዝሞ ፡ መወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) የተለየ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ካላጋጠመ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠውን ፡ የማራዘም ፡ ውሣኔ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ መስጠት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፻ ፺፭ ፡- የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ስለማሳለፍ ፤

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻ ፺፮ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲፈጸም ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ቢፈጸምም ፡ እንዳልተፈጸመ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

ቍ ፡ ፻ ፺፮ ፡- አዲስ ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ ስለመስጠት ፤

(፩) በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባይከናወንም ፡ እንኳ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻ፡ ቀርቦለት ፡ ጊዜው ፡ እንዲራዘም ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ ተራዝሞ ፡ በተሰጠው ፡ አዲስ ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ ውስጥ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማድ

BACK



ረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ካላጋጠሙ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ አዲስ ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ አይሰጥም ።

(ሀ) አመልካቹ ፡ በተሰጠው ፡ የጊዜ ፡ ወሰን ፡ ውስጥ ፡ እንዲፈጽም ፡ የታዘዘውን ፡ ነገር ፡ ለመፈጸም ፡ ያልቻለው ፡ ከአቅሙ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ሲያስረዳ ፤

(ለ) በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ እንዳይፈጽም ፡ ያገደው ፡ መሰናከል ፡ በተወገደ ፡ ከ፲፭ ፡ ቀን ፡ ባልበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነ ፤

(፫) አመልካቹ ፡ ሊፈጽም ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ በመጀመሪያ ፡ በተሰጠው ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ ውስጥ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረው ፡ ከአቅሙ ፡ በላይ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ በሥራ ፡ ብዛት ፤ በዝንጋት ፤ በችልተኛነትና ፡ በራሱ ፡ ጉድለት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደሆነ ፤ አዲስ ፡ የጊዜ ፡ መራዘም ፡ ውሣኔ ፡ አይሰጠውም ።

ቍ ፡ ፻፺፱ ፡- ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጊዜን ፡ በመወሰን ፡ ቀጠሮ ፡ መስጠት ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ክርክሩ ፡ በሚሰማበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲያገኝ ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ላንደኛው ፡ ወገን ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ በመወሰን ፤ ጊዜ ፡ ይሰጣል ። የሚሰጠውም ፡ የጊዜ ፡ ውሣኔ ፡ ለቀጠሮው ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የሚገመተው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በመሰማት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ክርክር ፡ መወሰን ፡ የሚቻለው ፡ በሌላ ፡ ችሎት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ በመሰማት ላይ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ የወንጀል ፡ ወይም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፡ እንደሆነ ፤ ክርክሩ ፡ ውሣኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ በቀጠሮ ፡ እንዲቆይ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ በሚቀጥርበት ፡ ጊዜ ፡ ክርክሩ ፡ እንደገና ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ይወስናል ። የጉዳዩ ፡ መቀጠር ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ኪሣራ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰ

BACK



ጣል ። ስለሆነም ፡ ምስክር ፡ መስማት ፡ የተጀመረበት ፡ ክርክር ፡ ሲሆን ፡ ለምስክርነት ፡ የተጠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ሰምቶ ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ በየዕለቱ ፡ አዳሪ ፡ የሚሆን ፡ ቀጠሮ ፡ እየሰጠ ፡ ሥራውን ፡ ማከናወን ፡ አለበት ።

(፪) የተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ባለ መቅረቡ ፡ ወይም ፡ ለመቅረብ ፡ ባለመቻሉ ፡ ምክንያት ፡ ቀጠሮ ፡ አይሰጥም ።

(፫) ክርክሩ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተቀጠረ ፡ እንደሆነ ፡ እንደገና ፡ ሊሰማ ፡ የተቀጠረበትን ፡ ጊዜ ፡ በመግለጽ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለተከራ ካሪዎቹ ፡ ወገኖችና ፡ ለምስክሮቹ ፡ አዲስ ፡ መጥሪያ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፺፫ ፡- ቀጠሮ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፤

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቀጠሮ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ለቀጠሮው ፡ ምክ ንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ በሚገባ ፡ እንዲከናወን ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) የክርክሩ ፡ መሰማት ፡ ታግዶ ፡ በሚቆይበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ የተሰጠው ፡ የይርጋ ፡ ውሣኔ ፡ ተቋርጦ ፡ ይቆያል ። ስለሆ ሆነም ፡ ከሳሹ ፡ በነገሩ ፡ ሳይገፋበት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የቆየ ፡ እን ደሆነ ፡ ተቋርጦ ፡ የነበረው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ እንዳልተቋረጠ ፡ ሆኖ ፡ ይታሰብበታል ።

ቍ ፡ ፻፺፬ ፡- ለቀጠሮው ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ያለመፈጸም ፤

(፩) ለቀጠሮው ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረው፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በአንደኛው ፡ ጉድለት ፡ የሆነ ፡ እንደ ሆነ ፤ መፈጸም ፡ ይገባው ፡ የነበረው ፡ ጉዳይ ፡ ያልተፈጸመ ፡ ቢሆ ንም ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጉዳዩን ፡ መፈጸም ፡ ሳይጠብቅ ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ የመሰለውን ፡ ውሣኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይች ላል ።

(፪) ለቀጠሮው ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረው፡ በተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ጉድለት ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌላ ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጣል ።

BACK



## ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡

## በኪሣራ ፡ ስለሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጥ ፡ ዋስትና ፤

**ቍ ፡ ፪፻ ፡-ከሣሽ ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያስይዝ ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ሁኔታ ፤**

(፩) ክርክሩ ፡ በሚቀጥልበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ተከሣሽ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብለት ፤ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ለደረሰበት ፡ ወይም ፡ ሊደርስበት ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ ለሚገመተው ፡ ኪሣራ ፡ ከሣሹ ፡ በቂ ፡ መያገ ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ማዘዝ ፡ አለበት ። እንዲሁም የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ትእዛዝ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ምክንያቱን ፡ ገልጾ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ማስፈር ፡ ይኖርበታል ።

(፪) ከሣሽ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሆነው ፡ የሚኖረው ፡ ወይም ፡ በሚኖሩት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ ሲሆንና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ክስ ፡ ከቀረበበት ፡ ንብረት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑ ፡ ሲረጋገጥ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተውን ፡ ትእዛዝ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፫) ማናቸውም ፡ ከሣሽ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ለቆ ፡ የሔደ ፡ እንደሆነና ፡ ተመልሶ ፡ ሲመጣም ፡ የተወሰነበትን ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል፡ መቻሉ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሲሆን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ እንደማይኖር ፡ ሰው ፡ ተቆጥሮ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይፈጸምበታል ።

**ቍ ፡ ፪፻፩ ፡- የዋስትና ፡ መስጠት ፡ ግዴታን ፡ ያለመፈጸም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።**

(፩) ከሣሹ ፡ ወይም ፡ ከሣሾቹ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ የተጠየቁትን ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይሰጡ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነና ፡ በራሳቸውም ፡ ፈቃድ ፡ ከክሱ ፡ ውጭ ፡ ለመውጣት ፡ ያላመለከቱ ፡ እንደሆነ ፡

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ ዘግቶ ፡ ያሰናብታ
ታቸዋል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የተዘጋው ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ እንደገና ፡ ተከፍቶ ፡ እንዲታይለት ፡ ከሣሽ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ማመልከቻ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል። ከሣሽ ፡ የተጠየቀውን ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡ መያዥ ፡ ሊያቀርብ ፡ ያልቻለው ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በሚገመት ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፤ ስለኪሣራው ፡ መያዣና ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ስለሚታየው ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ተዘግቶ ፡ የነበረው ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ እንደገና ፡ ተከፍቶ ፡ ክርክሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጣል ።

(፫) የክሱ ፡ መዝገብ ፡ ተከፍቶ ፡ ነገሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ከሣሽ ፡ ያቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ለተከሣሹ ፡ ካልደረሰው ፡ በቀር ፡ የነገሩ ፡ መሰማት ፡ እንዲቀጥል ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ።

## ቍ ፡ ፪፻፪ ፡- ከይግባኝ ፡ ባይ ፡ ስለሚጠየቅ ፡ የኪሣራ ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፤

(፩) ይግባኝ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ እንዲቀርብ ፡ ከማዘዙ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ቀርቦ ፡ ሲያመለክት ፤ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ያቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ ወይም ፡ የመጀመሪያው ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ ክርክሮች ፡ በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትሉት ፡ ኪሣራና ፡ ስለማንኛውም ፡ ወጭ ፡ በቂ ፡ የሚሆን ፡ የኪሣራ ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ክርክር ፡ ከተነሣበት ፡ ንብረት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሌለው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የሚኖረው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንዲፈጸም ፡ ማዘዝ ፡ አለበት ።

(፫) የተጠየቀው ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ዋስትናው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ የቀረበው ፡ ይግባኝ ፡ እንዲዘጋ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ፤ ይህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፩ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ /፪/ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፫ ፤

## የመሐላ ፡ ቃል ፡ /አፊዳቪት ፤ /

**ቍ ፡ ፪፻፫ ፡- የጉዳዩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ስለማድረግ ፤**

(፩) በክርክሩ ፡ ላይ ፡ የተነሣው ፡ አንዳንድ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ እንዲረጋገጥ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ነገሮች ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ እንዲረጋገጡ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። በመሐላ ፡ የተሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ በግልጽ ፡ ችሎት ፡ በንባብ ፡ እንዲሰማ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ማንኛውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ የምስክሩን ፡ ቃል ፡ በይበልጥ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ምስክሩ ፡ ቀርቦ ፡ መስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ እየተጠየቀ ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነና ፡ ምስክሩም ፡ ተገኝቶ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችል ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ።

**ቍ ፡ ፪፻፬ ፡- የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ በጽሑፍ ፡ የሰጠው ፡ ወገን ፡ እንዲቀርብ ፡ ስለማድረግ ፤**

(፩) ማንኛውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተረጋገጠ ፡ የጽሑፍ ፡ ምስክርነት ፡ እንዲሰጥለት ፡ ሲያመለክት ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይፈቅድለታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ መስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ እንዲጠየቅ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ሲያመለክት ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ሲያዝ ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈውን ፡ ጽሑፍ ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ቃሉን ፡ በመ

ሐላ ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ክርክሩን ፡ በሚሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ ፊት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፭ ፡- በመሐላ ፡ ቃል ፡ የሚሰጡ ፡ ነገሮች ፡ ወሰን ፤**

(፩) በመሐላ ፡ ቃል ፡ የሚረጋገጥ ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ቃሉን ፡ በመሐላ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ የሚያውቀው ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ ስለሆነም ፡ በጣልቃ ፡ ገብነት ፡ የሚቀርቡትን ፡ ወይም ፡ የቀረቡትን ፡ ማመልከቻዎች ፡ ለመደገፍ ፡ የተሰጠ ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ሲሆን ፡ ቃሉን ፡ በመሐላ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ የታየውንና ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ያመነበትን ፡ ነገር ፡ ከነምክንያቱ ፡ በመሐላ ፡ ቃሉ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

(፪) በመሐላ ፡ በተደገፈው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ የሚጠየቀው ፡ የዳኝነት ፡ ጉዳይ ፡ ከመሐላው ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

፫ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሌላ ፡ አኳሆን ፡ እንዲፈጸም ፡ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ለማናቸውም ፡ በመሐላ ፡ ለሚሰጥ ፡ ጽሑፍና ፡ ስለማናቸውም ፡ ሌላ ፡ የሰነድ ፡ ግልባጭ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወጭ ፡ የሚከፍለው ፡ እነዚሁኑ ፡ ሰነዶች ፡ የሚያቀርበው ፡ ወገን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፮ ። የመሐላን ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ ስለሚችል ፡ ባለሥልጣን ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በሚሰጠው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፤ የማስማሉ ፤ ወይም ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ የሚረጋገጥበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፤ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ የያዘው ፡ የሥራ ፡ ሥልጣን ፡ በሚፈቅድለት ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መርጦ ፡ ይህን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ባዘዘው ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ነው ፡

## ክ ፍ ል ፡ ፩ ።

## ትእዛዝን ፡ ያለመፈጸም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

**ቍ ፡ ፪፻፯ ። መሠረቱ ።**

በሕግ ፡ ተለይቶ ፡ ካልተደነገገ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፤ በዚህ ፡

ሕግ ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሣኔዎች ፡ ወይም ፡ በውሣኔዎቹ ፡ መሠረት ፡ የሚወጣውን ፡ ደንብ ፡ ባለመፈጸም ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ፡ ወይም ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ከደንብ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ ሲፈጸም ፤ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ባመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ይህ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ ተሻሽሎ ፡ እንዲቀርብ ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ስለሚደርሰው ፡ ኪሣራና ፡ ስለሌላውም ፡ ወጭ ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

## ቊ ፡ ፻፳፫ ። ስሕተትን ፡ ስለማረም ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሰጠው ፡ መጥሪያ ፤ በወሰነው ፡ ፍርድ ፤ በሰጠው ፡ ውሣኔና ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ የአጻጻፍ ፡ ስሕተት ፤ የቊጥር ፡ አጻጻፍ ፡ ጉድለት ፡ ወይም ፡ ያልታሰበና ፡ ባለማስተዋል ፡ የተዘለለ ፡ ድንገተኛ ፡ የቃል ፡ ስሕተት ፡ መኖሩን ፡ ራሱ ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ከባለ ፡ ጉዳዮቹ ፡ አንዱ ፡ ሲያመለክት ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡ ፻፳፪ ፡ የተነገረውን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለት ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያርመው ፡ ይችላል ።

## ቊ ፡ ፻፳፬ ። በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ወይም ፡ እንዲዘጋ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ክርክሩ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ያልተከተለ ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ለማመልከትና ፡ ይህ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲሠረዝ ፡ ወይም ፡ እንዲዘጋ ፡ በማለት ፡ አቤቱታውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) አቤቱታው ፡ የተመሠረተው ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ በሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ምክንያቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ መገለጽ ፡ አለባቸው ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፻፲፩ ፡ ንዑስ ፡ ቊጥር ፡ (፩) የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ ሁሉ ፡ በመጀመሪያው ፡

BACK



ደረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያስፈልጋል ። ወይም ፡ አመልካቹ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ መኖሩን ፡ እንደተረዳው ፡ ወድያውኑ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፲ ። አቤቱታን ፡ ስለመወሰን ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መኖራቸው ፡ ሲረጋገጥ ፤

(ሀ) በሥረ ፡ ነገሩ ፡ ላይ ፡ የተያዘውን ፡ ጭብጥ ፡ የሚለውጥ ፡ ወይም ፡ የሚነካ ፡ በአመልካቹ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፤

(ለ) አመልካቹ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለት ፡ አለበት ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ መኖሩን ፡ እንደተረዳ ፡ ወዲያውኑ ፡ በነገሩ ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ ያልወሰደ ፡ መሆኑን ፡ እርምጃ ፡ ወስዶ ፡ እንደሆነም ፡ እለ ፡ የተባለውን ፡ ጉድለት ፡ በመቃወም ፡ ያመለከተ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያረጋግጥ ፤ ትእዛዝ ፡ የሰጠበትን ፡ ምክንያት ፡ በዝርዝር ፡ በመግለጽ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፯ ፡ የተነገረውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ አቤቱታውን ፡ ተቀብሎ ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። ስለሆነም ፡ የሥነ ፡ ሥርዓቱን ፡ ጉድለት ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ለማረም ፡ የማይቻል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ የቀረበው ፡ ክስ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ አይዘጋም ። እንዲሁም ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ በከፊል ፡ የሚሠረዝ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ የሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ጉድለት ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ የተወሰደው ፡ እርምጃ ፡ አብሮ ፡ አይሰረዝም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንውስ ፡ ቍጥር ፡ የተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ያልተፈጸመበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚዘረዝር ፡ መግለጫ ፡ በመስጠት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ ውድቅ ፡ ያደርገዋል ። በጉዳዩም ፡ ላይ ፡ ማመልከቻ ፡ እንዳልቀረበበት ፡ በመቁጠር ፡ ክርክሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። ስለ ፡ ይግባኝ ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፪፻፱ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻ፡ ካልቀረበና ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ ምክንያት ፡

BACK



ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ የትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ በተባለበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመውን ፡ ማንኛውንም ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለት ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ሊያርም ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ ያጋጠመው ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለት ፡ ለትክክለኛው ፡ ፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ተቃራኒ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፡ የተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ እንዳልተፈረደ ፡ ሆኖ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፪ ። ከርክሩ ፡ ስለሚጸናበት ፡ ሁኔታ ።

በአንድ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለት ፡ የተፈጸመ ፡ ሲሆን ፤ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ካልተባለበት ፡ የጸና ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ ይግባኝ ፡ ተብሎበት ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያጸደቀው ፡ እንደሆነ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ጉድለት ፡ ምክንያት ፡ ውድቅ ፡ አይሆንም ።

# አራተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ስለሚታዩ ፡ መደበኛ ፡ ክርክሮች ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ።

## የክስ ፡ አቀራረብና ፡ አመሠራረት ።

## ክ ፍ ል ፡ ፩ ።

## ጠ ቅ ላ ላ ፡ ድ ን ጋ ጌ ዎ ች ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፫ ። ክስ ፡ የሚጀመረው ፡ የክሱን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጽ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ስለመሆኑ ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለማመልከቻና ፡ ስለ ፡ አቤቱታ ፡ አቀራረብ ፡ ጉዳይ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ማናቸውም ፡

ክስ ፡ እንደቀረበ ፡ የሚቆጠረው ፡ ዳኝነት ፡ እንዲታይ ፡ የሚጠየቅበት ፡ የክስ ፡ ጽሑፍ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) ማንኛውም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ አጻጻፍ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፹ እስከ ፡ ፺፫ እና ፡ ከቍጥር ፡ ፻፪ እስከ ፡ ፻፴፯ ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተከተለ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ <u>፻፲፩ ። ክስ ፡ ስለሚመዘገብበት ፡ መዝገብ ።</u>

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፳፱ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጂስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የሚቀርብለትን ፡ የክስ ፡ ጽሑፍ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በተዘጋጀው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ መመዝገቢያ ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ የክሱን ፡ ዝርዝር ፡ በመግለጽ ፡ ይመዘግባል ። ክሶቹንም ፡ የሚመዘግበው ፡ እንደ ፡ አቀራረባቸው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ በመስጠትና ፡ ከዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ እስከ ፡ ዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ተከታታይ ፡ ቍጥር ፡ በማስያዝ ፡ በየዓመቱ ፡ የመጀመሪያ ፡ ተራ ፡ ቍጥሩ ፡ ከአንድ ፡ እንዲጀመር ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ቍ ፡ <u>፻፲፪ ። ለዳኝነት ፡ ስለሚከፈል ፡ ገንዘብ ።</u>

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፩፻፳፮ ፡ እስከ ፡ ፩፻፴፱ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በቍጥር ፡ ፻፴ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ዳኝነት ፡ ካልተከፈለባቸው ፡ በቀር ፡ ተቀባይነትን ፡ አያገኙም ።

(፪) የዳኝነቱም ፡ ገንዘብ ፡ በመልስ ፡ ሰጭነት ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ በተከሣሽ ፡ ከሣሽነት ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ በታሪፉ ፡ ልክ ፡ ይከፈላል ።

ቍ ፡ <u>፻፲፫ ። ስለ ፡ ክሱ ፡ አቀራረብና ፡ አገላለጽ ።</u>

(፩) ማናቸውም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ሁሉ ፡ ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጉዳዩን ፡ በሚገባ ፡ መርምሮ ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ በሚያስችለው ፡ በዚያው ፡ ነገር ፡

BACK



ሌላ ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ በማያስከትል ፡ ሁኔታና ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አጻጻፍ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ማናቸውም ፡ ክስ ፡ ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ ምክንያት ፡ የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ አጠቃሎ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ። ስለሆነም ፡ ከሣሹ ፡ ክሱን ፡ የሚያቀርብበት ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣኑ ፡ የሚፈቅድለት ፡ እንዲሆን ፡ ከፈለገ ፡ በክሱ ፡ ከሚጠይቀው ፡ ሀብት ፡ ውስጥ ፡ ቀንሶ ፡ ለመክሰስ ፡ ይችላል ።

(፫) ከሣሹ ፡ ሊከሰበት ፡ ሲችል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ በመቀነስ ፡ ባስቀረው ፡ ሀብት ፡ ምክንያት ፡ እንደገና ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

(፬) ከሣሽ ፡ ያቀረበው ፡ ክስ ፡ ባንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ የሚጠይቀው ፡ ዳኝነት ፡ ግን ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይፈቅድለት ፡ ሊጠይቅ ፡ ይገባው ፡ ከነበረው ፡ ዳኝነት ፡ ውስጥ ፡ በከፊል ፡ ራሱ ፡ ቀንሶ ፡ ያስቀረውን ፡ መብት ፡ እንደገና ፡ ሊከሰበት ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፻፲፮ ። ለክሱ ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አጣምሮ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲቀርብ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ ከሣሽ ፡ ለሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ካለው ፡ ሁሉንም ፡ በአንድነት ፡ አጣምሮ ፡ ባንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ በሆኑ ፡ ተከሣሾች ፡ ላይ ፡ የተጣመረ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ብዙ ፡ ከሣሾች ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ተከሣሾች ፡ ላይ ፡ የሚያቀርቡት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የክስ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖራቸው ፡ ምክንያቶችን ፡ አጣምረው ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

## ቍ ፡ ፻፲፯ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ለማስመለስ ፡ ተጣምረው ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ክሶች ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ የማስመለስ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱ ፡ ክሶችን ፡ አጣምሮ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(ሀ) ከማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ላይ ፡ የሚሰበሰበውን ፡ ውዝፍ ፡ ኪራይ ፡ ወይም ፡ ከንብረቱ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ገቢ ፡ በከፊል ፡ ለመጠየቅ ፡ ሲሆን

(ለ) የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ በሚመለከት ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የተደረገውን ፡ ውል ፡ በመተላለፍ ፡ የሚደርሰውን ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡

(ሐ) የተጠየቀው ፡ ዳኝነት ፡ የተመሠረተው ፡ ባንድ ፡ ዓይነት ፡ ምክንያት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ።

## ቍ ፡ ፻፲፱ ። ንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚዎችና ፡ ወራሾች ፡ ስለሚያቀርቡትና ፡ ስለሚቀርብባቸው ፡ ክስ ።

ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፤ ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚ ፤ ወይም ፡ ወራሽ ፡ በአስተዳዳሪነቱ ፤ በአስፈጻሚነቱ ፡ ወይም ፡ በወራሽነቱ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ክስ ፡ ለግል ፡ ጉዳይ ፡ ከሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ አጣምሮ ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ በተከሰሰበት ፡ ጉዳይ ፡ አጣምሮ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ነገር ፡ ግን ፡ በግሉ ፡ የሚያቀርበው ፡ ወይም ፡ የሚቀርብበት ፡ ክስ ፡ የተመሠረተው ፡ በንብረት ፡ አስተዳዳሪነቱ ፤ በኑዛዜ ፡ አስፈጻሚነቱ ፡ ወይም ፡ በወራሽነቱ ፡ ከሚያስተዳድረው ፡ ንብረት ፡ ጋር ፡ በተያያዘ ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ አጣምሮ ፡ መልስ ፡ ለመስጠትና ፡ እርሱም ፡ በሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ አጣምሮ ፡ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፤ ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚ ፡ ወይም ፡ ወራሽ ፡ አድርጎት ፡ ከነበረው ፡ ሟች ፡ ጋር ፡ በአባሪነት ፡ ሆኖ ፡ በሚከሰስበት ፡ ወይም ፡ በሚከሰስበት ፡ ጉዳይ ፡ አጣምሮ ፡ ሊከስ ፡ ወይም ፡ መልስ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፻፳ ። ያላግባብ ፡ ተጣምሮ ፡ መከሰስን ፡ ስለመቃወም ።

ክሱ ፡ ተጣምሮ ፡ የቀረበው ፡ ያላግባብ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ የሚቀርበው ፡ መቃወሚያ ፡ ሁሉ ፡ ክርክሩ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የነገሩን ፡ ጭብጥ ፡ ይዞ ፡ ክርክሩን ፡ መስማት ፡ ከጀመረ ፡ በኋላ ፡ መቃወሚያ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡

BACK



ተቀባይነትን ፡ አያገኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ መቃወሚያ ፡ የሚቀርብ በት ፡ ነገር ፡ የተፈጠረው ፡ የክርክሩ ፡ መስማት ፡ ከተጀመረ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የቀረበውን ፡ መቃወሚያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊቀበለው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። ክሱ ፡ ተነጣጥሎ ፡ ስለሚታይበት ፡ ሁኔታ ።**

ክሱ ፡ በሚቀጥልበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፤ ባንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ከሣሾች ፤ ባንድ ፡ ክስ ፡ ተጣምረው ፡ የቀረቡት ፡ የክስ ፡ ምክንያቶች ፡ ወይም ፡ ዋናውን ፡ ክስ ፡ የተከሣሽ ፡ ከሣሽ ፡ ካቀረ በው ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ለመወሰን ፡ የሚያስቸግር ፤ ጊዜ ፡ የሚፈጅ ፡ ወይም ፡ የማይመች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ተነጣጥሎ ፡ በተፋጠነ ፡ መንገድ ፡ እንዲታይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ክስና ፡ ስለ ፡ መከላከያ ፡ ጽሑፍ ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፪ ። በክስ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠፍሩ ፡ ነገሮች ።**

(፩) ማናቸውም ፡ የክስ ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ የያዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(ሀ) ክሱ ፡ የሚቀርብለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚያስችልበትን ፡ ቦታና ፡ ሥሙን ፤

(ለ) የክሱን ፡ አርዕስት ፤

(ሐ) የከሳሹንና ፡ የተከሣሹን ፡ ሥም ፤ ልዩ ፡ መግለጫውን ፤ የሚኖርበት ፡ ቦታና ፡ መጥሪያው ፡ የሚሰጥበትን ፡ አድራሻ ፤

(መ) ከሣሽ ፡ ወይም ፡ ተከሣሽ ፡ በሕግ ፡ ችሎታ ፡ የለውም ፡ የተ ባለ ፡ ሲሆን ፡ ይህንኑ ፡ መግለጽ ።

(ሠ) ከሣሹ ፡ ክስ ፡ የሚያቀርበው ፡ በጠበቃነት ፤ በነገረ ፡ ፈጅ ነት ፡ ወይም ፡ በወኪልነት ፡ እንደሆነ ፡ ክሱን ፡ ለማቅረብ ፡ ያለ ውን ፡ ሥልጣን ፡ መግለጽ ።

(ረ) ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮችና ፡ እነዚሁም ፡ የተ ፈጠሩበትን ፡ ጊዜና ፡ ሥፍራ ።

BACK


(ሰ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ስለ መሆኑ ፡ የሚያስረዳውን ፡ ሁኔታ ፤

(ሸ) ተከሣሹ ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ እንዳለው ፡ ወይም ፡ ተጠሪ ፡ የሚሆንበትን ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ለሚቀርበው ፡ ክርክር ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቅበትን ፡ ሁኔታ ፤

(ቀ) አስፈላጊ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ውን ፡ ነገር ፡ ግምት ።

(፪) መንግሥት ፡ በሚከስበት ፡ ወይም ፡ በሚከሰስበት ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተነገረው ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ። ነገር ፡ ግን ፡ የከሣሹን ፡ ወይም ፡ የተከሣሹ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የባለሥልጣኑን ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ መግለጽ ፡ በቂ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፳፫ ። ከክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ጽሑ ፎችና ፡ መግለጫዎች ።**

(፩) ከሣሹ ፡ ከሚያቀርበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ አያይዞ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(ሀ) ክርክሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ ምስክር ፡ ይሆኑኛል ፡ የሚ ላቸውን ፡ ሰዎች ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ ከነ ፡ አድራሻቸው ፤ የሚጠሩ በትን ፡ ምክንያት ፤ እንዲሁም ፡ ማስረጃ ፡ ይሆኑኛል ፡ የሚላቸ ውን ፡ ጽሑፎች ፤ ጽሑፎቹም ፡ በእጁ ፡ የማይገኙ ፡ ሲሆኑ ፡ የሚ ገኙበትን ፡ ሥፍራና ፡ በማን ፡ እጅ ፡ እንደሚገኙ ፡ በመግለጽ ፡ አያይዞ ፡ ካቀረበው ፡ ዝርዝር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አስረጅ ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጦ ፡ በማስታወቅ ፤

(ለ) ለክሱ ፡ መነሻ ፡ ወይም ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ ሰነድ ፡ ዋና ውን ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ ግልባጩን ፤

(ሐ) የሚያቀርበው ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነድ ፡ የሌ ለው ፡ ሲሆን ፡ ይህንኑ ፡ ገልጾ ፡ ማረጋገጥ ።

(፪) በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ለተጠቀሱት ፡ ተከሣሾች ፡ ሁሉ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ግልባጭ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ የቀረቡትን ፡ የጽሑፎችና ፡ ሌሎችም ፡ ማስረጃዎች ፡ የምስክሮች ፡

ስም ፡ ዝርዝር ፡ ማናቸውንም ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የደረሱትን ፡ መግለጫዎች ፡ ትክክል ፡ ግልባጫቸው ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ማድረግ ፤

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ ለክሱ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ ሰነድ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፡ ለተከሣሹ ፡ እንዲደርሰው ፡ ከማድረግ ፡ ይልቅ ፡ ዋናው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ እንዲቀመጥና ፡ ተከሣሹ ፡ መጥቶ ፡ እንዲያየው ፡ ለማዘዝ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፪፻፳፬ ። የሚጠየቀውን ፡ ዳኝነት ፡ በዝርዝር ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ከሣሽ ፡ በሚያቀርበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ ወይም ፡ በምትክ ፡ ወይም ፡ በተለዋዋጭ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ዳኝነት ፡ መግለጽ ፡ አለበት ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሣሹ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ እንዲሰጠው ፡ የሚጠይቀው ፡ ዳኝነት ፡ ጠቅላላ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ የክሱን ፡ ጭብጥና ፡ የማስረጃውን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ትክክለኛ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ።

(፪) ከሣሹ ፡ ክሱን ፡ የመሠረተው ፡ በብዙ ፡ ጉዳዮች ፡ ወይም ፡ በተለያዩ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በተለይ ፡ በየአንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲታይለት ፡ የሚጠይቀውን ፡ ዳኝነት ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፳፭ ። ለክርክሩ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ለይቶ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ለክርክሩ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ጉዳይ ፡ የተወሰነ ፡ ወይም ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ነገሩን ፡ አብራርቶ ፡ በመለየት ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) ክሱ ፡ የሚመለከተው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ንብረቱን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ የሚያስችሉት ፡ ምልክቶች ፡ መገለጽ ፡ ይኖርባቸዋል ። ይኸውም ፡ ንብረት ፡ የሚለየው ፡ በአካባቢው ፡ ወሰን ፡ ወይም ፡ በርስት ፡ መመዝገቢያ ፡ ላይ ፡ በተሰጠው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የወሰኑ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ በመዝገብ ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ ቍጥር ፡ መገለጽ ፡ ይገባዋል ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፳፮ ።ገንዘብን ፡ ለመጠየቅ ፡ በሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ዝርዝ ፡ መግለጫዎች ።

(፩) ክስ ፡ የቀረበው ፡ በገንዘብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ ከሳሹ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ በትክክለኛ ፡ ሁኔታ ፡ ገልጾ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ከሣሹ ፡ የሚጠይቀው ፡ ገንዘብ ፡ ልኩ ፡ ሊታወቅ ፡ የሚችለው ፡ በርሱና ፡ በተከሣሹ ፡ መካከል ፡ የሂሣብ ፡ መጣራት ፡ ተግባር ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ በሚያቀርበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ በግምት ፡ ለመግለጽ ፡ ይችላል ።

(፫) ክሱ ፡ የቀረበው ፡ ተለይቶ ፡ የታወቀ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለማስመለስ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ ለክሱ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ትክክለኛው ፡ ዋጋ ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

(፬) የቀረበው ፡ ክስ ፡ የሚያልቅ ፡ ወይም ፡ የሚበላሽ ፡ ወይም ፡ ዕለታዊ ፡ አገልግሎት ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የዚሁኑ ፡ የዕለት ፡ ዋጋ ፡ መገለጽ ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ ፡ ፪፻፳፯ ። በየጊዜው ፡ ስለሚከፈል ፡ ሂሣብ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ።

(፩) ክሱ ፡ የቀረበው ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲከፈል ፡ ተለይቶ ፡ በታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ ሲሆን ፡ የተጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስገኘው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ካፒታል ፡ ዋጋ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

(፪) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ገንዘብ ፡ በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ ሆኖ ፡ ክፍያው ፡ የሚቀጥልበት ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ተለይቶ ፡ ያልተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ነገሩን ፡ ለመቀበል ፡ የሚችለው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ተለይቶ ፡ የሚታወቀው ፡ የዓመቱ ፡ ክፍያ ፡ ገንዘብ ፡ በ፳ ፡ ተባዝቶ ፡ በሚገኘው ፡ ድምር ፡ ሂሣብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፳፰ ። መብትን ፡ ስለ ፡ መመስረት ፡ ስለ ፡ ማስከበር ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መሠረዝ ።

ከሣሽ ፡ ለመመሥረት ፤ ለማስከበር ፡ ወይም ፡ ለመሠረዝ ፡ የሚ

BACK



ጠይቀውን ፡ መብቱን ፡ ዋጋ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጠየቀውን ፡ መብት ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቢሰጠው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚችል ፡ ገምቶ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፳፱ ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጂስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የሚቀርብለትን ፡ አቤቱታ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ ለመመለስ ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ።**

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጂስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ተሟልተው ፡ የማይቀርቡትን ፡ የክስ ፡ አቤቱታዎች ፡ ተቀባይነት ፡ እንዳይኖራቸው ፡ አድርጎ ፡ ለአቅራቢው ፡ ይመልሳቸዋል ።

(ሀ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተሟልቶ ፡ ያልቀረበ ፡ ሲሆን ።

(ለ) እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱትን ፡ አባሪዎች፣ መግለጫዎችና ፡ ሰነዶች ፡ አጠቃሎ ፡ ያልያዘ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡

(ሐ) በቍጥር ፡ ፺፪ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተገቢው ፡ ማረጋገጫ ፡ ያልተሰጠበት ፡ ሲሆን ።

**ቍ ፡ ፪፻፴ ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጂስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ስለሚቀበልበት ፡ ሁኔታ ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ያልተነቀፉት ፡ የክስ ፡ አቤቱታዎች ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ለሬጂስትራሩ ፡ ሲቀርቡ ።

(ሀ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፲፩ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ተቀብሎ ፡ ይመዘግባል ።

(ለ) ከክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ የቀረቡትን ፡ ሰነዶች ፡ ዋናዎቹንና ፡ ትክክል ፡ ግልባጫቸውን ፡ እያስተያየ ፡ ይመረምራል ።

(ሐ) ግልባጩ ፡ ትክክለኛ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ ትክክለኛነቱን ፡ አረጋግጦ ፡ በመፈረም ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ እንዲቀመጥ ፡

BACK



ያደርጋል ፤ ዋናውንም ፡ ለመለየት ፡ እንዲቻል ፡ ምልክት ፡ ካደረገበት ፡ በኋላ ፡ ለባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ይመልስለታል ።

(መ)የቀረበውንም ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ከአባሪዎቹ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ ለችሎቱ ፡ ያቀርባል ።

**ቍ ፡ ፪፻፴፩ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የክስ ፡ አቤቱታው ፡ ተቀባይነት ፡ እንዳይኖረው ፡ ስለሚወሰንበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ የቀረቡለትን ፡ የክስ ፡ አቤቱታዎች ፡ ተቀባይነት ፡ የላቸውም ፡ ብሎ ፡ በመወሰን ፡ ሊመልሳቸው ፡ ይችላል ።

(ሀ) በክሱ ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ ነገር ፡ የማያስከስስ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፤

(ለ) በክሱ ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ ጉዳይ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ መኖኑን ፡ ሲረዳው ።

(፪) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ሺ፩፻፫ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተጠየቀውን ፡ ማረጋገጫ ፡ ወይም ፡ ፡ መያዣ ፡ ያልሰጠ ፡ ማናቸውም ፡ ከሣሽ ፡ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀውን ፡ መብት ፡ ለማስመለስ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተቀባይነትን ፡ እንዳያገኝ ፡ ወስኖ ፡ ይሠርዘዋል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያልተቀበለው ፡ ክስ ፡ ሲሠረዝ ፡ ወይም ፡ ሲመልስ ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ የመለሰበትን ፡ ምክንያት ፡ በውሣኔው ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፴፪ ።የቀረበው ፡ ክስ ፡ ተቀባይነትን ፡ ማጣቱ ፡ ወይም ፡ መሠረዙ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።**

(፩) ሬጂስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ይፈጽማል ።

(ሀ) በቍጥር ፡ ፪፻፴፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ተያይዞ ፡ ከቀረበለት ፡ ከማናቸውም ፡ ማስረጃና ፡ መግለጫ ፡ ጋር ፡ እንዲ

BACK



ሁም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ወይም ፡ ይሠረዛል ፡ ሲል ፡ ከሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ ግልባጭ ፡ ጋር ፡ ለባለጉዳዩ ፡ ይመለስለታል ። ስለሆነም ፡ ማመልከቻው ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ ሬጂስትራሩ ፡ በሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቤቱታውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(ለ) በቍጥር ፡ ፪፻፴፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ ሲሆን ፡ ከሣሹ ፡ ለዳኝነት ፡ ከፍሎ ፡ ከነበረው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ የሚቀነሰው ፡ ሂሣብ ፡ ከተቀነሰ ፡ በኋላ ፡ ቀሪው ፡ ይመለስለታል ። ሬጂስትራሩም ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ መሆኑን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ መመዝገቢያ ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ ይመዘግባል ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፱ ፡ እና ፡ ፪፻፴፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ መባሉ ፡ ወይም ፡ መሠረዙ ፡ ከሣሽ ፡ ክሱን ፡ አሻሽሎና ፡ የጐደለውን ፡ አሟልቶ ፡ በዚያው ፡ ነገር ፡ እንደገና ፡ ክስ ፡ ከማቅረብ ፡ የሚያግደው ፡ አይሆንም ።

## ቍ ፡ ፪፻፴፫ ። የክስን ፡ ማመልከቻ ፡ ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

የቀረበው ፡ ክስ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የሚነቀፍበት ፡ ወይም ፡ የሚሠረዝበት ፡ ምክንያት ፡ የሌለበት ፡ ሆኖ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ ተቀብሎ ፡ ከማመልከቻው ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ የቀረበለት ፡ ማናቸውም ፡ አስረጂና ፡ የጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡ ከመጥሪያው ፡ ጋር ፡ ለተከሣሹ ፡ እንዲደርሰውና ፡ የመከላከያ ፡ መልሱን ፡ ጽፎ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያዛል ። ተከሣሹ ፡ መከላከያውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳያቀርብ ፡ የቀረ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ መከላከያ ፡ ሳይዝ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ክርክሩ ፡ በሌለበት ፡ የሚሰማ ፡ መሆኑ ፡ በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ ይገለጽለታል ።

## ቍ ፡ ፪፻፴፬ ። በመከላከያ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ከአ

BACK



ባሪዎቹ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ የሚቀርብ ፡ ማናቸውም ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ የያዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(ሀ) የመከላከያው ፡ መልስ ፡ የቀረበበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስምና ፡ የሚያስችልበትን ፡ ቦታ ፤

(ለ) የክሱን ፡ መዝገብ ፡ ቊጥር ፤

(ሐ) ከማሽ ፡ ሕጋዊ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፤ ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክሩን ፡ ለመሥማት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ በይርጋ ፡ ይታገዳል ፡ የሚባል ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ የተባለበትን ፡ ዝርዝር ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ።

(መ) ለቀረበው ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡ የሚሆኑት ፡ ማስረጃዎች ፡ በተለይ ፡ ሲሆኑ ፡ እነዚሁኑ ፡ በአጭር ፡ አገላለጽ ፡ መጻፍ ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ይጠቅማሉ ፡ የተባሉትን ፡ መከላከያዎች ፡ በጠቅላላ ፡ አጻጻፍ ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲሁም ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ በሚጻፍበት ፡ ጊዜ ፡ በመከላከያው ፡ ያልተጠቀሰ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ እንዳይፈጠር ፡ ወይም ፡ ከክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ አዲስ ፡ ነገሮች ፡ እንዳይነሱ ፡ በማድረግ ፡ ተሟልቶ ፡ የተዘጋጀ ፡ መልስ ፤

(ሠ) በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ከተገለጹት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ያልተካዱት ፡ ሁሉ ፡ እንደታመኑ ፡ ስለሚቆጠሩ ፡ የሚካዱትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በግልጽና ፡ በዝርዝር ፡ የሚያስተባብል ፡ መልስ ፡ መስጠት ።

(ረ) የተከማሽ ፡ ከማሽነት ፡ ክስ ፡ እንዳለ ፡ ይህንኑ ፡ አስተካክሎ ፡ መግለጽ ፡ ይህም ፡ አለ ፡ በሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ በቊጥር ፡ ፪፻፴፬ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ (፫) ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተገቢነቱ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪፻፴፩ ፡፡ ነገሩን ፡ በመሸሽ ፡ ስለ ፡ ማስተባበል ፡፡

(፩) በክሱ ፡ ላይ ፡ የቀረበውን ፡ ነገር ፡ ተከሣሹ ፡ በዝርዝርና ፡ በግልጽ ፡ ማስተባበል ፡ አለበት ፡፡ ነገሩን ፡ በመሸሽ ፡ መልክ ፡ የተሰጠ ፡ ማስተባበል ፡ በቂ ፡ አይሆንም ፤ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አይመለከተኝም ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ አከባቢውን ፡ ነገር ፡ በመካድ ፡ የተሰጠ ፡ ማስተባበያ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ እንደመካድ ፡ አይቆጠርም ፡፡

(፪) በማናቸውም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በአነጋገሩ ፡ ሥልት ፡ እንደተካደ ፡ የሚቆጠር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ በተከሣሽ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ነገሩ ፡ የተካደ ፡ መሆኑ ፡ ካልተገለጸ ፡ በሕግ ፡ ችሎታ ፡ የላቸውም ፡ ከተባሉ ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ በሌሎቹ ፡ ተከሣሾች ፡ ሁሉ ፡ እንደታመነ ፡ ይቆጠራል ፡፡ ስለሆነም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ እንደታመኑ ፡ በተቆጠሩት ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሰማባቸው ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፡፡

ቍ ፡ ፪፻፴፪ ፡፡ በማናቸውም ፡ ክስ ፡ ስለማቻቻል ፡ በሚቀርብ ፡ ጥያቄ ፡ ውስጥ ፡ መገለጽ ፡ ስለሚገባቸው ፡ ነገሮች ፡፡

(፩) ተከሣሽ ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ በሚሰጠው ፡ መልስ ፡ በከሣሽ ፡ ላይ ፡ በሕግ ፡ የምፈልገው ፡ ገንዘብ አለኝ ፡ በማለት ፡ እንዲቻቻልለት ፡ የሚጠይቅ ፡ ሲሆን ፤ የሚጠይቀው ፡ ገንዘብ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በበኩሉ ፡ የሚጠይቀውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ገልጾ ፡ ለተከሰሰበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ፡፡

ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ የሚጠይቀው ፡ ገንዘብ ፡ ተከሣሹንና ፡ ከሣሹን ፡ በግል ፡ መብታቸው ፡ ረገድ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡፡

የዚህን ፡ ዓይነት ፡ የመቻቻል ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ የሚገባውም ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ መልስ ፡ በሚሰጥበት ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡፡

(፪) የተከሣሹ ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ የመቻቻልን ፡ መብት ፡ በሚጠቅስበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ከሣሽ ፡ አንደኛው ፡ የተከሣሽ ፡ ከሣሽ ፤ ሆኖ ፡ እንደቀረበ ፡ የክስ ፡

BACK



አቤቱታ ፡ ይቆጠራል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ የሚ ሰጠው ፡ በዋናው ፡ ክስና ፡ በማቻቻል ፡ እንዲታይ ፡ በቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፴፯ ። በተለያዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ የመቻቻል ፡ ጥያቄና ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ።

ተከሣሽ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የተመሠረቱ ፡ መከላከያዎች ፡ የሚያቀርብ ፡ ሲሆንና ፡ በተለያዩ የመቻቻል ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ የሚሰጥ ፡ ሲሆን ፡ እነ ዚህን ፡ ምክንያቶችና ፡ የመቻቻል ፡ ጥያቄዎች ፡ በየመልካቸውና ፡ በየመደባቸው ፡ ለይቶ ፡ በመዘርዘር ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፴፰ ። የመከላከያን ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ መመርመር ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፫ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ የቀረበለትን ፡ መከላከያ ፡ ፍርድ ቤቱ ፡ ይመ ረምራል ። ለዚሁም ፡ ጉዳይ ፡ ስለ መከላከያ ፡ አቀራረብ ፡ በቍ ጥር ፡ ፪፻፳፱ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) ከዚህ በላይ ፡ ባለው ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ መከላ ከያ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ያልተባለ ፡ እንደሆነ ፡ መከላከያው ፡ የተከሣሽ ፡ ከሣሽነት ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ የመቻቻል ፡ ጥያቄ ፡ ያለ በት መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መመርመር ፡ አለበት ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ስለ ፡ ተከሣሽ ፡ ከሣሽነት ክስና ስለመቻቻል ፡ ጥያቄ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፴፩ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተገቢነቱ ፡ በተመ ሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተነገረው ፡ መከላከያው ፡ ተቀባይነትን ፡ ያላገኘ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ክርክሩ ፡ መቀጠል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፴፱ ። ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ክርክሮች ።

(፩) የተከሣሽ ፡ ከሣሽነትን ፡ ወይም ፡ የመቻቻልን ፡ ጉዳይ ፡ የሚ ጠይቅ ፡ ክርክር ፡ ያለበት ፡ የመከላከያ ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ እንደተነገረው ፡ ያልተነቀፈ ፡ እንደሆነና ፡ ከሣ

BACK



ሹም ፡ ስለዚህ ፡ ክርክር ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የሚፈቅድ ፡ እንደ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይጠይቀዋል ። ፈቃደኝነቱንም ፡ የገለጸ ፡ እንደሆነ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መልስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ያዘዋል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከሣሹ ፡ መልሱን ፡ ያላቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ የመከራከሪያ ፡ መልስ ፡ የመቀባበሉ ፡ ሥርዓት ፡ ያቆማል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ከሣሹ ፡ መልስ ፡ ያልሰጠ ፡ ቢሆንም ፡ ወይም ፡ የሰጠው ፡ መልስ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፱ ፡ እና ፡ ፪፻፴፩ ፡ እንደተነገረው ፡ ተቀባይነትን ፡ ባያገኝም ፡ እንኳ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ክርክሩ ፡ መቀጠል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፴ ። የጽሑፍ ፡ ሰነዶችን ፡ ለማሳመን ፡ ስለሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ።

(፩) ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በአባሪነት ፡ በሚገኘው ፡ ፎርም ፡ መሠረት ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ ትክክለኛነት ፡ እንዲያምን ፡ ሌላውን ፡ ወገን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ተጠያቂው ፡ ወገን ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ የተጠቀሰውን ፡ ሰነድ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲችል ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ሰነድ ፡ እንዲያምን ፡ የሚቀርብለት ፡ ጥያቄ ፡ ለክርክሩ ፡ መስማት ፡ ከተወሰነው ፡ ቀጠሮ ፡ ካስር ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ እንዲደርሰው ፡ ያስፈልጋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ክስን ፡ ስለመስማት ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የመጀመሪያ ፡ ክስ ፡ ሲከፈት ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

ቍ ፡ ፪፻፴፩ ። ተከራካሪዎቹን ፡ ስለ ፡ መመርመር ።

(፩) ክሱ ፡ መሰማት ፡ በሚጀምርበት ፡ ቀን ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ራሳቸው ፡ ቀርበው ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እራሳቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ክሱን ፡ ቀርቦም ፡ እንደሆነ ፡ የመከላከያውን ፡ መልስ ፡ ለግራ ፡ ቀኙ ፡ በንባብ ፡ በማሰማት ፡ ዋናውን ፡ ተከሣሽ ፡

BACK



ወይም ፡ ስለርሱ ፡ በፈጅነት ፡ የቀረበውን ፡ ተከራካሪ ፡ የተከሰሰበ ትንና ፡ በመልሱ ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ እንደተካደ ፡ የሚቆጠረውን ፡ ነገር ፡ የሚያምን ፡ ወይም ፡ የሚክድ ፡ መሆኑን ፡ ይጠይቀዋል ።

(፪) ስለ ፡ ተከሣሹ ፡ ሆኖ ፡ የቀረበውን ፡ ወይም ፡ ዋናውን ፡ ተከ ሳሽ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የቀረበውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ የሆኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ነገሮች ፡ አብራርቶ ፡ ለማስረዳት ፡ ጠቃሚና ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በገመተው ፡ ዘዴ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ በማቅረብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊመረምራቸው ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ማንኛውም ፡ ወገን ፡ እንዲብራራለት ፡ የሚፈለገውን ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲጠ ይቅለት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

(፫) ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ላንደኛው ፡ በፈጅነት ፡ ወይም ፡ በጥብቅና ፡ የሚቀርበው ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ ከተሚጋቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ የሚቀር በው ፡ ሰው ፡ ለክርክሩ ፡ ማብራሪያ ፡ የሚሆኑትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ነገሮች ፡ ለማስረዳት ፡ ፈቃደኛ ፡ ሳይሆን ፡ የቀረ ፡ ወይም ፡ ለቀረ በለት ፡ ጥያቄ ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የማይችል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰማ ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ በመወሰን ፡ ባለጉዳዩ ፡ ራሱ ፡ ለቀረበለት ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ለሚቀርብ ብለት ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ሲረ ዳው ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፬) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚደረገው ፡ ምርመ ራና ፡ ማናቸውም ፡ እምነት ፡ ወይም ፡ ክህደት ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተጽፎ ፡ ከክርክሩ ፡ መዝገብ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ይያያዛል ።

ቍ ፡ ፪፻፴፪ ። በእምነት ፡ መሠረት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ።

ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ባለጋራው ፡ በመከላከያ ፡ መልሱ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የሚያምን ፡ መሆኑን ፡ የገለጸ ፡

እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፵፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በሚደረገው ፡ ምርመራ ፡ የእምነት ፡ ቃሉን ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ በእምነቱ ፡ መሠረት ፡ ይገባኛል ፡ የሚለው ፡ ማናቸውም ፡ ዳኝነት፡ እንዲሰጠው ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌላ ፡ የሚወ ስን ፡ ወይም ፡ በምስክር ፡ የሚረጋገጥ ፡ ነገር ፡ መኖሩን ፡ ቢረዳ ው ም ፡ እንኳ ፡ ለታመነውና ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ለተጠየቀው፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፵፫ ። ማብራሪያ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ የእ ምነት ፡ ቃል ፡ ያልተሰጠበትን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ጽሑፍ ፤ እምነት ፡ ክደት ፡ እንዲሰጥበት ፡ ክርክሩ ፡ በሚቀጥል በት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ እየጠየቀና ፡ የተሰጠውን ፡ መልስ ፡ እየመዘገበ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፵፩ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠ ረት ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ከመስጠት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ አያግደውም ።

ቍ ፡ ፪፻፵፬ ። በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርቡ ፡ መቃ ወሚያዎች ።

(፩) ማስረጃ ፡ ተቀብሎ ፡ ከመመርመሩ ፡ ወይም ፡ ምስክሮችን ፡ ከመስማቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ለቀረበለትና ፡ ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ላቀረበው ፡ መቃ ወሚያ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተ ውን ፡ መቃወሚያ ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፵፭ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡

(ሀ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ መቃወሚያ ፡ ሲያቀርብ ፤

(ለ) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ አስቀድሞ ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ መቃወሚያ ፡ ሲቀርብ ፤

(ሐ) ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ መቃወሚያ ፡ ሲቀ ርብ ፤

BACK



(መ) አንደኛው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በነገሩ ፡ የማያገባው ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ በጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መከራከር ፡ አይገባውም ፡ በማለት ፡ መቃወሚያ ፡ ሲቀርብ ፡

(ሠ) ክሱ ፡ በይርጋ ፡ የታገደ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ መቃወሚያ ሲቀርብ ፡

(ረ) ወይም ፡ ክሱ ፡ የተነሳበት ፡ ነገር ፡ በሽምግልና ፡ ታይቶ ፡ በስምምነት ፡ የተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ለእርቅ ፡ የተቀጠረ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ መቃወሚያ ፡ ሲቀርብ ፡ ነው ።

(፫) በዚህ ፡ ቊጥር ፡ እንደተነገረው ፡ የቀረቡት ፡ መቃወሚያዎች ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሲሆኑ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በቶሎ ፡ ተጠቃለው ፡ ሁሉም ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ። መቅረብ ፡ ከሚገባቸው ፡ መቃወሚያዎች ፡ ውስጥ ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩት ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ የማያሰናክሉ ፡ ከሆኑ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ራሱ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ለማቅረብ ፡ ባለመፈለግ ፡ እንደተዋቸው ፡ ይቆጠራሉ ።

(፬) በዚህ ፡ ቊጥር ፡ የተነገረውን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የክሱ ፡ አቀራረብ ፡ ትክክለኛውን ፡ ፎርም ፡ አልተከተለም ፡ በማለት ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

## ቊ ፡ ፪፻፵፭ ። በቀረቡት ፡ መቃወሚያዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሳኔ ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቊጥር ፡ ፪፻፵፬ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የቀረቡትን ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ መቃወሚያዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተቀብሎ ፡ ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ክርክር ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የሚገምተው ማስረጃ ፡ እንዲቀርብለት ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) የቀረበለት ፡ መቃወሚያ ፡ ተገቢና ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ማስረጃ ፡ የተደገፈ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡ በንዑስ ፡ ቊጥር ፡ (፩) (ለ) እና ፡ በ ፡ (ረ) ፊደል ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የቀረቡ ፡ መቃወሚያዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ክሱን ፡ ዘግቶ ፡ ባለ ፡ ጉዳዮቹን ፡ ያሰናብታል ። መቃወሚያዎቹ ፡ የቀረቡት ፡ ከዚህ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ መዝገቡን ፡ ዘግቶ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ክስ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ የመዝገቡ ፡ መዘጋት ፡ ከሳሹ ፡ ክሱን ፡ አሻሽሎ ፡ በዚያው ፡ ነገር ፤ በዚያው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሆነ ፡ ሥልጣኑ ፡ በሚፈቅድለት ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ እንደገና ፡ ከማቅረብ ፡ አያግደውም ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ መዝገቡን ፡ በሚዘጋበት ፡ ጊዜ ፡ ከሳሹ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ ይችላል ።

(፬) መዝገቡ ፡ የተዘጋው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ በመባሉ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሹ ፡ ከከፈለው ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ ከሚቀነሰው ፡ ሂሳብ ፡ የተረፈው ፡ ይመለስለታል ።

(፭) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ ማንኛውም ፡ ውሳኔና ፡ የተሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ ተጽፎ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ይቀመጣል ።

## ቍ ፡ ፪፻፵፯ ፡- የነገርን ፡ ጭብጥ ፡ ስለመያዝ ፡ ወይም ፡ ስለማስያዝ ፤

(፩) የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ መቃወሚያ ፡ /እንዳለ/ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ የሚከራከረው ፤ የተለያዩበት ፡ የሕግ ፡ ወይም ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ አግባብ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ በማረጋገጥ ፡ ለጉዳዩ ፡ ትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስችለውን ፡ ጭብጥ ፡ በመያዝ ፡ ነው ።

(፪) ነገሩ ፡ በመጀመሪያ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን ፡ ተከሳሹ ፡ የመከላከያ ፡ መልሱን ፡ ሳያቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጭብጥ ፡ እንዳይዝ ፡ አያስገድደውም ።

## ቍ ፡ ፪፻፵፰ ፡- የነገር ፡ ጭብጥ ፡ አመሠራረት ፤

(፩) የነገር ፡ ጭብጥ ፡ የሚመሠረተው ፤ አንደኛው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ያመነውን ፡ የሕግ ፡ ወይም ፡ የነገር ፡ አግባብ ፡ ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በማስተባበል ፡ የካደ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፪) ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ማለት ፤ የከሳሽን ፡ መብት ፡ ለመመሥረት ፡ የሚያስችለው ፡ ወይም ፡ ለተከሳሹ ፡ መከላከያ ፡ ለመሆን ፡ የሚችል ፡ ማናቸውም ፡ የሕግ ፡ ወይም ፡ በማስረጃ ፡ የተደገፈ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ማለት ፡ ነው ።

BACK



(፫) ማናቸውም ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፤ በአንዱ ፡ ወገን ፡ የሚታመንበት ፡ ሆኖ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የተካደ ፡ ሲሆን ፡ በተለይ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የነገር ፡ ጭብጥ ፡ ይያዛል ።

(፬) ባንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ የተያዘው ፡ ጭብጥ ፡ ለየራሱ ፡ ፍሬ ፡ ነገርንና ፡ ሕግን ፡ የሚመለከት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሕጉን ፡ ጥያቄ ፡ በመከተል ፡ ክሱን ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ለመወሰን፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፤ በመጀመሪያ ፡ በሕግ ፡ ጉዳይ ፡ ለተያዙት ፡ ጭብጦች ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ አለበት ። ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘውም ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ የተያዙትን ፡ ጭብጦች ፡ እስኪወስን ፡ ድረስ ፡ በፍሬ ፡ ነገር ፡ የተያዘውን ፡ ጭብጥ ፡ በቀጠሮ ፡ ሊያቆየው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፵፯ ፡- ጭብጥን ፡ ለመመሥረት ፡ ስለሚያስፈልጉ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፤

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ አንዱን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመከተል ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ ጭብጥን ፡ ለመመሥረት ፡ ወይም ፡ ለመያዝ ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) በክሱና ፡ በመከላከያው ፡ መልስ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩትን፡ ነገሮች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤

(ለ) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ያቀረበውን ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤

(ሐ) በቍጥር ፡ ፪፻፵፩ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በሚደረገው ፡ ምርመራ ፤ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ጠበቆቻቸው ፡ ወይም ፡ ወኪሎቻቸው ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጆቻቸው ፡ የሚሰጡትን ፡ መልስ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፵፱ ፡፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጭብጥን ፡ ከመያዙ ፡ በፊት ፡ ምስክሮችንና ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ለመመርመር ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፤

ፍርድ ፡ ቤት ፡ የአንድ ፡ ነገርን ፡ ጭብጥ ፡ ከመመሥረት ፡ ወይም ፡ ከመያዝ ፡ አስቀድሞ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎችን ፡ አቅርቦ ፡ ቃላቸውን ፡ በመቀበል ፡ ነገሩን ፡ ማጣራት ፡ ወይም ፡ ማስረጃዎችን ፡ መመርመር ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፤ ነገሩ ፡ የሚሰማበትንና ፡ ጭብጡ ፡ የሚያዝበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ በመወሰን ፤ መቅረብ ፡ የሚገባቸውና ፡ ጽሑፉ ፡ በእጃቸው ፡ ይገኛል ፡ የተባ

ሉት ፡ ሰዎች ፡ በቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ እንዲቀርቡ ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፶ ። ክስ ፡ በቀረበበት ፡ የሃብት ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚነሳ ፡ ክርክር ።

ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፤ ክስ ፡ በቀረበበት ፡ ሃብት ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ምክንያት ፡ ባለመስማማት ፡ ክርክር ፡ ያቀረቡ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጭብጡን ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ወስኖ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ በ፪፴፪ ፡ ወይም ፡ ፪፴፮ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሃብቱን ፡ ግምት ፡ የሚያስታውቁ ፡ ምትክ ፡ ዳኞችን ፡ ይሾማል ።

ቍ ፡ ፪፻፶፩ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተያዙትን ፡ ጭብጦች ፡ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ ለመሠረዝ ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ በፍርድ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፤ በተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የተያዘው ፡ ጭብጥ ፡ እንዲሻሻል ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ጭብጥ ፡ እንዲያዝ ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነና ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ ለጉዳዩ ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ ቀና ፡ መንገድ ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ ሲሆን ፤ የቀረበው ፡ ጭብጥ ፡ እንዲሻሻል ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ጭብጥ ፡ እንዲያዝ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) በስሕተት ፡ ወይም ፡ ተሳስቶ ፡ የተቀበለው ፡ ጭብጥ ፡ ቢኖርም፡ ከፍርድ ፡ በፊት ፡ እንዲሠረዝ ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፪፻፶፪ ። ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በመስማማት ፡ የሕጉን ፡ ወይም ፡ የፍሬ ፡ ነገርን ፡ ጭብጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲይዝላቸው ፡ ለማመልከት ፡ ስለሚችሉት ፡ ሁኔታ ።

ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ያልተግባቡት ፡ ወይም ፡ ያከራከራቸው ፡ የሕግ ፡ ወይም ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ ጭብጥ ፡ የትኛው ፡ እንደሆነ ፡ በመግለጽ ፡ ለክርክራቸው ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኘውን ፡ ጭብጥ ፡ እንዲይዝላቸው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማመልከት ፡ ይችላሉ ። ይህንን ፡ ጭብጥ ፡ አዘጋጅተው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚያቀርቡበትም ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ በፍርድ ፡ ለመወሰን ፡

ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ መንገድ ፡ በመከተል ፤ ጭብጡን ፡ በመያዝ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን፡ ጉዳይ ፡ እንዲወስን ላቸው ፡ የተስማሙበት ፡ መሆናቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ መግለጽ ፡ አለባቸው ።

(ሀ) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ባቀረቡት ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊከፈል ፡ ይገባል ፡ ሲል ፡ የወሰነውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ እንዲከፍል ፡ ወይም ፡ ባቀረቡት ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ተከራካሪ ፡ የጠየቀውን ፡ መብት ፡ እንዲያገኝ ፡ ወይም ፡ በአላፊነት ፡ እንዲጠየቅበት ፤

(ለ) በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ ንብረት ፡ አንደኛው ፡ ተከ ራካሪ ፡ ወገን ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ እንዲመልስ ፡ ወይም ፡ እንዲለቅ ፡ ወይም ፡ አግባብ ፡ ነው ፡ ብለው፡ በተስማሙበት ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፤

(ሐ) ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ቍጥራቸው ፡ የተወሰነ ፡ ሰዎች ፡ ባቀረቡት ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የተወሰነ ፡ ተግባር ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ወይም ፡ ከመፈጸም ፡ እንዲታገዱ ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፺፫ ።በቅን ፡ ልቡና ፡ በተደረገ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፤</u>

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለጉዳዩ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ምርመራ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ ሲረዳ ፤

(ሀ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተነገረውን ፡ ስምምነት፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በሚገባ ፡ የፈጸሙ ፡ መሆናቸውን ፤

(ለ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ መሆኑን ፤

(ሐ) ነገሩን ፡ በዳኝነት ፡ መወሰን ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በስምምነት ፡ ያቀረቡለትን ፡ ጭብጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡ እንደመሠረተው ፡ በመቍጠር ፡ ከመዘገበ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ በተያዘው ፡ ጭብጥ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ለሚያዘው ፡ ጭብጥ ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡

BACK



ወገኖች ፡ ባቀረቡት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ነገሩን ፡ በፍርድ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፬ ። ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሚለያዩበት ፡ ጉዳይ ፡ ያለመኖሩ ፡ ሲታወቅ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሳኔ ፤**

(፩) የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ መቃወሚያ ፡ ከተሰማና ፡ ጉዳዩ ፡ ከተጣራ ፡ በኋላ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በሕጉም ፡ ሆነ ፡ በፍሬ ፡ ነገሩ ፡ የሚያከራክራቸው ፡ ወይም ፡ የሚለያዩበት ፡ ጉዳይ ፡ ያለመኖሩን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተገነዘበው ፡ እንደሆነ ፤ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ነገሩን ፡ በፍርድ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሾቹ ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሆነው ፡ ከነዚህ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ በሕጉም ፡ ሆነ ፡ በፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ከከሳሹ ፡ ጋር ፡ የሚያከራክረው ፡ ወይም ፡ የሚያለያ የው ፡ ነገር ፡ ያለመኖሩ ፡ የታወቀ ፡ እንደሆነ ፡ በነገሩ ፡ የተግባባውን ፡ ተከሳሽ ፡ ከክርክሩ ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ አሰናብቶ ፡ ክርክሩ ፡ ከቀሩት ፡ ተከሳሾች ፡ ጋር ፡ እንዲቀጥል ፡ ያዛል ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፭ ፡ የሚያከራክር ፡ ነገር ፡ ስላላቸው ፡ ከሳሾችና ፡ ተከሳሾች ፤**

(፩) ከሳሾችና ፡ ተከሳሾች ፡ በሚያቀርቡት ፡ ክርክር ፡ የሚያለያያቸው ፡ ወይም ፡ የሚያከራክራቸው ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የነገሩን ፡ ጭብጥ ፡ ከመሠረተ ፡ በኋላ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በመጀመሪያው ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ካቀረቡት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ሙግት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ማስቀረብና ፡ መመርመር ፡ የማያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳውና ፡ በመጀመሪያ ፡ በቀረበው ፡ ክርክርና ፡ ማስረጃ ፡ ብቻ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ቢሰጥ ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍትሐ ፡ የማያጓድል ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ለተመሠረተው ፡ ጭብጥ ፡ የቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔን ፡ ለመስጠት ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ካገኘው ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፶፮ ። ማስረጃ ፡ ያለማቅረብ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፤**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፴፯ ፡ ወይም ፡ ፪፻፵፱ ፡ በተመለከተው ንድጋጌ ፡ መሠረት ፤ መቅረብ ፡ የሚገባቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ባንደኛው ፡ ጉድለት ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ባልሆነ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ። ነገር ፡ ግን ፡ ማስረጃዎች ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩት ፡ ከባድና ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ በሆኑን ፡ የተረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ምክንያት ፡ መዝግቦ ፡ ስለክርክሩ ፡ አወሳሰንና፡ ማስረጃ ፡ ያለማቅረቡ ፡ ስላስከተለው ፡ ኪሣራ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ይወስናል ።

(፪) ክሱ ፡ የተመሠረተው ፡ በሚተላለፍ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሰነዱ ፡ መጥፋቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፤ ጠፍቶብኛል ፡ ብሎ ፡ ያመለከተው ፡ ወገን ፤ ይህን ፡ ሰነድ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አቅርቦ ፡ ባለመብትነቱን ፡ ያስረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ አላፊነት ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚገምተውን ፡ ዋስትና ፡ አመልካቹ ፡ እንዲሰጥ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ሰነዱ ፡ እንዳለ ፡ ተቆጥሮ ፡ ዋጋ ፡ እንዲያገኝ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፲ ፤

## ክርክሩን ፡ ስለመስማትና ፡ ምስክሮችን ፡ ስለመመርመር ፡

**ቍ ፡ ፪፻፶፯ ፡- ስለመጥሪያ ፤**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፵፱ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ከሚቀርበው ፡ ማስረጃ ፡ በቀር ፤ ለክርክሩ ፡ ትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ምስክር ፡ መስማት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፤ በተጨማሪ ፡ መታየት ፡ የሚገባው ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ መስማት ፡ የሚገባቸው ፡ ምስክሮች ፡ እንዲቀርቡለት ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ክርክሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ፪፻፶፰ ።ስለክሱ ፡ መከፈትና ፡ ሙግትን ፡ የመጀመር ፡ መብት ፤

(፩) ክስን ፡ የመክፈትና ፡ ሙግትን ፡ የመጀመር ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ከሳሽ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ከሳሽ ፡ ያቀረበበትን ፡ ክስ ፡ አምኖ ፤ ሕግ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ በከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ያልተመለከተ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ በመጥቀስ ፡ የቀረበብኝ ፡ ክስ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ የሚከራከር ፡ ሲሆን ፡ ሙግቱን ፡ የሚከፍተው ፡ ወይም ፡ የሚጀምረው ፡ ተከሳሹ ፡ ይሆናል ።

(፪) ሦስት ፡ ዳኞች ፡ በሚያስችሉበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ ዳኛ ፡ በችሎቱ ፡ ባይገኝም ፡ እንኳ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ሁለት ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ የቀረቡትን ፡ ምስክሮች ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ ይችላሉ።

ቍ ፡ ፪፻፶፱ ፡- የክስ ፡ ቃልን ፡ ስለመስጠትና ፡ ማስረጃ ፡ ስለማቅረብ ፤

(፩) ሙግቱን ፡ ለመክፈት ፡ ወይም ፡ ለመጀመር ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ወገን ፡ የክሱን፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ የከሳሽነት ፡ ቃሉን ፡ በመስጠት ፡ መመሥረት ፡ የሚገባውን ፡ ጭብጥና ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ የሚደግፍለትን ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባል ።

(፪) ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ለመከላከያ ፡ የሚሆነውን ፡ መክፈቻና ፡ የመከላከያ ፡ ቃል ፡ እንዳለው ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ ስለጠቅላላው ፡ ክስ ፡ ያለውን ፡ አስተያየት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያቀርባል ።

(፫) ቀጥሎም ፡ ክሱን ፡ የከፈተው ፡ ወይም ፡ የጀመረው ፡ ወገን ፡ ስለክርክሩ ፡ ያለውን ፡ ጠቅላላ ፡ አሳብ ፡ ያቀርባል ።

ቍ ፡ ፪፻፷ ።በብዙ ፡ ጭብጦች ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማስረጃ ፤

(፩) የተያዙት ፡ ጭብጦች ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሲሆኑ ፡ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ነገሩን ፡ የማስረዳት ፡ ግዴታ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ክሱን ፡ ያቀረበው ፡ ወገን ፡ በበኩሉ ፡ ማስረዳት ፡ የሚገባውን ፡ ጭብጥ ፡ ያቀርባል ። ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ፈቃደኛ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ማስረጃውን ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፡ በሚሰጠው ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ማስረጃውን ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ነገሩን ፡ በመጀመሪያ ፡ እንዲያስረዳ ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡

BACK



ወገን ፡ የማስረዳት ፡ ቀደምትነትን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ያስቀረ ፡ እንደ ሆነ ፤ ሌላው ፡ ወገን ፡ በበኩሉ ፡ ማቅረብ ፡ የሚገባውን ፡ ማስረጃ ፡ ሁሉ ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፡ አቆይቶት ፡ የነበረውን ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባል ። እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ የማስረዳት ፡ ቀደምትነት ፡ ያለው፡ ወገን ፡ ባሰማው ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በተለይ ፡ ዝርዝር ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። ማስረጃውን ፡ አቆይቶ ፡ የነበረው ፡ ወገን ፡ ግን ፡ በማስረጃው ፡ ላይ ፡ ማጠቃለያ ፡ አሳቡን ፡ ብቻ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፷፩ ፡ የማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ሥርዓት ፤

(፩) በመጀመሪያ ፡ የማስረዳት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ወገን ፤ ምስክሮቹን ፡ ሲያቀርብ ፡ የቀረቡት ፡ ምስክሮች ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ በቍጥር ፡ /፫/ ሰንጠረዥ ፡ በተመለከተው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የሚሰጡት ፡ ቃል ፡ እውነተኛ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ቃላቸውን ፡ ይሳጣሉ ።

(፪) ስለራሱ ፡ ጉዳይ ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ መስጠት ፡ የሚፈልግ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ለመመስከር ፡ ይችላል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ መዝግቦ ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፤ ምስክሮች ፡ የምስክርነታቸውን ፡ ቃል ፡ የሚሰጡት ፡ በጽሑፍ ፡ ሳይሆን ፡ በችሎቱ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ በግልጽና ፡ በቀጥታ ፡ ነው ።

(፬) ስለጉዳዩ ፡ መብራራትና ፡ ስለክርክሩ ፡ አወሰሰን ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ምስክሩን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፪ ፡-የምስክርን ፡ ቃል ፡ ስለመተርጐም ፤

የምስክሩ ፡ ቃል ፡ የተሰጠው ፡ በአማርኛ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ምስክር ፡ የሚሰጠው ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ የሚተረጐመው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተርጓሚ ፡ ነው ። አስተርጓሚውም ፡ የመተርጐም ፡ ሥራውን ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ቃሉን ፡ በትክክለኛ ፡ የሚያስተረጉም ፡ ለመሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ በ፫ኛው ፡ ሰንጠረዥ ፡ የተመለ

BACK



ከተውን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ቃሉን ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፷፫ ፡-ጥያቄ ፡ የሚጠየቅበት ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ፎርም ፡

(፩) ምስክሩ ፡ የመጀመሪያ ፡ ቃሉን ፡ ሲሰጥ ፡ የሚቀርብለት ፡ ጥያቄ፡ ጭብጡን ፡ የሚመለከትና ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ በሚያውቀው ፡ ወይም ፡ ሊያውቀው ፡ በሚችለው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ለሚመሠክረው ፡ ጉዳይ ፡ መሪ ፡ የሚሆን ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፫) በመስቀልኛ ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ምስክሩ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ የተሳሳተበትን ፡ አሰት ፡ ነው ፡ የሚባላበትን ፡ ወይም ፡ አጠራጣሪ ፡ መስሎ ፡ የተገመተበትን ፡ ነጥብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲረዳው ፡ የማድረግ ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ በመስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ምስክሩን ፡ መምራት ፡ ይቻላል ።

(፬) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ የሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ዓላማው ፡ ምስክሩ ፡ በመስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ ለማብራራት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፬ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሌሎችን ፡ ምስክሮች ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡

(፩) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ነገሩን ፡ የሚያውቅ ፡ ወይም ፡ ለክርክሩ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ በእጁ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ቀርቦ ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡ የሚያገኘውን ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲያቀርብ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ካቀረቡዋቸው ፡ ምስክሮችና ፡ ከራሳቸውም ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ ምስክሮች ፡ መስማት ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከገመተው ፡ በሚወስነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ተጠርተው ፡ የምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡

ወይም ፡ በእጃቸው ፡ የሚገኘውን ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ለጉዳዩ ፡ አወሳሰን ፡ መጠራት ፡ የሚገባውን ፡ ምስክር ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ ሳያቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ማቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ወገን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፲፪ ፡ የተመለከተውን ፡ እንዲፈጽምና ፡ ስለምስክሮቹም ፡ ኪሣራና ፡ አበል ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፻፲፰ ።ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የምስክሮችን ፡ ቃል ፡ ባስቸኳይ ፡ ለመቀበል ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ፤

(፩) ክስ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በመነናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የምስክሩን ፡ ቃል ፡ በአስቸኳይ ፡ መቀበል ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳውና ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ምስክሩ ፡ ሲያመለክት ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ የምስክሩን፡ ቃል ፡ ወዲያውኑ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ። እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ የምስክሩ ፡ ቃል ፡ ክሱ ፡ በሚሰማበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ በንባብ ፡ ሊሰማ ፡ ይችላል ።

(፪) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ባሉበት ፡ የምስክሩን ፡ ቃል ፡ ባስቸኳይ ፡ ለመቀበል ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ቃሉን ፡ ለመቀበል ፡ የወሰነበትን ፡ ቀን ፡ የሚገልጽ ፡ መጥሪያ ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ያደርጋል ።

## ቍ ፡ ፻፲፱ ።ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምስክሮችን ፡ አስጠርቶ ፡ እንደገና ፡ ለመመርመር ፡ ስለመቻሉ ፤

የክርክሩ ፡ እርምጃ ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ መስክረው ፡ የነበሩትን ፡ ምስክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደገና ፡ አስጠርቶ ፡ ማናቸውንም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ጥያቄ ሊጠይቃቸው ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፻፳ ፡- የምስክርነት ፡ ቃልን ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኛ ፡ ስላለመሆን ፤

ማንኛውም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ የቀረበ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ከክርክሩ ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ ሰው ፤ የምስክርነት ፡

BACK



ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ ሥር ፡ የሚገኘውን ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያዘው ፣ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ በማይደገፍ ፡ ምክንያት ፡ ትእዛዙን ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቃደኛ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይፈርድበታል ፤ ወይም ፡ ስለክርክሩ ፡ አወሳሰን ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፻፲፫ ።<u>በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለምስክሮች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መጥሪያ</u> ፡ በተላከላቸው ፡ ተከራካሪዎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለመሆኑ ፤

በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ ተከራካሪ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ጽሑፍ እንዲያቀርብ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ የሚቀርብበት ፡ ሁኔታና ፡ የመጥሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ አፈጻጸም ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ለምስክሮች ፡ አጠራርና ፡ አቀራረብ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፻፲፬ ፦ <u>የምስክርን ፡ ቃል ፡ በመዝገብ ፡ ላይ ፡ ስለማስፈር ፤</u>

(፩) የእያንዳንዱ ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ የሚጀመረው ፤ በምስክሩ ፡ ስም ፤ በዕድሜው ፤ በአድራሻው ፤ በሥራው ፤ በሰጠው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ እውነት ፡ መናገሩን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ቃሉን ፡ መስጠቱን ፡ በመጥቀስ ፡ ነው ።

(፪) ቃሉ ፡ የሚመዘገበው ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ራሱ ፡ ለመጻፍ ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ በርሱ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ሌላው ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ የችሎቱ ፡ ጸሐፊ ፡ ሊመዘግበው ፡ ይችላል ።

(፫) የምስክሩ ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ይከፋፈላል ።

መጀመሪያ ፡ ቀጥታ ፡ ጥያቄ ፡ ሲቀርብለት ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፤ ሁለተኛ ፡ የመስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ ሲጠየቅ ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፤ ሶስተኛ ፡ በመጀመሪያ ፡ ቀጥታ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበለት ፡ ወገን ፡ ሁለተኛውን ፡ የማብራሪያ ፡ ጥያቄ ፡ ሲጠይቀው ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የመስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበበትንና ፡ የማብራ

BACK



ሪያ ፡ ጥያቄ ፡ የተጀመረበትን ፡ ነጥብ ፡ ምልክት ፡ ያደርግበታል ።

(፩) የምስክሩ ፡ ቃል ፡ የሚጻፈው ፤ ምስክሩ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እንዳነጋገሩ ፡ በቀጥታ ፡ በመከተል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ስብሳቢው ዳኛ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ሲያገኘው ፡ ጥያቄውንና ፡ ለጥያቄው ፡ የተሰጠውን ፡ መልስ ፡ ለመመዝገብ ፡ ይችላል ።

(፫) የቃሉ ፡ አቀባበል ፡ ሥርዓት ፡ እንደተፈጸመ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይፈርምበታል ።

## ቍ ፡ ፻፲፫ ። በጥያቄ ፡ አቀራረብ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ መቃወሚያ ፡ ስለመመዝገብ ፤

ተከራካሪው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ወይም ፡ ስለርሱ ፡ ሆኖ ፡ የሚነጋገርለት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለምስክሩ ፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ያላግባብ ፡ መሆኑን ፡ እየገለጸ ፡ የተቃወመ ፡ እንደሆነና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መቃወሚያውን ፡ ሳይቀበል ፡ ለጥያቄው ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ያዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ መቃወሚያው ፡ የቀረበበትን ፡ ጥያቄ ፤ የተሰጠውን ፡ መልስ ፡ የተቃወመውን ፡ በው ፡ ስም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ መቃወሚያውን ፡ አልቀበለውም ፡ ሲል ፡ የሰጠ ውን ፡ ውሳኔ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ገልጾ ፡ ማስፈር ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፻፲፫፩ ።ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዳኛ ፡ ስለመዘገበው ፡ ማስረጃ ፤

(፩) ማስረጃውን ፡ የተቀበለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ዳኛ ፡ ለተጀመረው ፡ ክርክር ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሳይሰጥ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ በሥፍራው ፡ ያልተገኘ ፡ እንደሆነ ፤ ተተኪው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ዳኛ ፡ ማስረጃውን ፡ ራሱ ፡ ተቀብሎ ፡ እንደመዘገ በው ፡ በመቍጠር ፡ ነገሩ ፡ ከቆመበት ፡ ላይ ፡ እንዲቀጥል ፡ ያደ ርጋል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንውስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፴፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ከሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ከአንዱ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ችሎት ፡ ተዛው ረው ፡ በሚሰሙ ፡ ክሶችም ፡ ላይ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፪ ፡- ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምርመራ ፡ ለማድረግ ፡ ስለመቻሉ ፤**

ክርክሩ ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ሥፍራው ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ በማየት ፡ ለመመርመር ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የፈጸመውን ፡ ምርመራ ፡ ውጤት ፡ የሚገልጽ ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ አዘጋጅቶ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ እንዲያያዝ ፡ ያደርጋል ። ቬርባሉም ፡ ከሌሎቹ ፡ ማስረጃዎች ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፫ ፡- ስለፍርድ ፤**

የማስረጃው ፡ መስማት ፡ ሥርዓት ፡ ተጣርቶ ፡ ሲፈጸም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፶፱ ፡ የተመለከተው ፡ የፍርድ ፡ መቀበያ ፡ የሚሆነው ፡ ማጠቃለያ ፡ አሳብ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ፤

## ክርክርን ፡ ስለማቋረጥ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፩ ፤

### ስለ ፡ መገላገልና ፡ ከክስ ፡ ውጭ ፡ ስለመሆን ፤

**ቍ ፡ ፪፻፸፬ ።መሠረቱ ፤**

(፩) የክርክሩ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑት ፡ ወገኖች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ክርክራቸውን ፡ በእርቅ ፡ ስምምነት ፡ በመጨረስ ፡ ከክርክሩ ፡ ውጭ ፡ ለመሆን ፡ ወይም ፡ ለክርክሩ ፡ ፍጻሜ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

(፪) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ እርቅ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ግልግል ፡ ውጤት ፤ በእርቅ ፡ ወይም ፡ በግልግሉ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ስለማቅረብ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ስለማፍረስ ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፯ ፡ እስከ ፡ ፫ሺ፫፻፳፬ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፭ ። ስለ ፡ እርቅ ፡ ወይም ፡ ስለግልግል ።**

(፩) ክርክሩ ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በራሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አሳሳቢነት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውጭ ፡ ክርክራቸውን ፡ በእርቅ ፡ ወይም ፡ በግልግል ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላሉ ።

(፪) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ያመለከቱ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕርቃቸው ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመራበትን ፡ አሳብ ፡ ሊገልጽላቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፮ ።የዕርቅ ፡ ወይም ፡ የግልግል ፡ ስምምነት ፡ ስለሚይዛቸው ፡ ጉዳዮች ፤**

(፩) የዕርቅ ፡ ወይም ፡ የግልግል ፡ ስምምነት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ ይይዛል ።

(ሀ) ነገሩ ፡ የቀረበበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስምና ፡ የሚያስችልበትን ፡ ቦታ ፤

(ለ) የክሱን ፡ አርእስትና ፡ የመዝገቡን ፡ ቍጥር ፡

(ሐ) የተከራካሪዎቹን፡ ወገኖች ፡ ስም ፤ ልዩ፡ መግለጫ ፤ የመኖሪያ ፡ ቦታና ፡ መጥሪያ ፡ የሚላክበትን ፡ አድራሻ ፤

(መ) የእርቁ ፡ ወይም ፡ የግልግሉ ፡ ስምምነት ፡ የሚመለከተውን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ መግለጫ ።

(፪) የዕርቁ ፡ ወይም ፡ የግልግሉ ፡ ስምምነት ፡ በተጨማሪ ፡ የካሣንና ፡ የኪሣራን ፡ አከፋፈል ፡ እንዲሁም ፡ ስምምነቱ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚወስን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፯ ። የእርቅንና ፡ የግልግልን ፡ ስምምነት ፡ ስለመመዝገብ ።**

(፩) ክርክሩ ፡ በመስማት ፡ ላይ ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ነገሩን ፡ በዕርቅ ፡ በመጨረስ ፡ የተስማሙ ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ጽፈውና ፡ ፈርመው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያቀርቡ ፡ የዕርቁ ፡ ስምምነት ፡ ሕግንና ፡ ሞራልን ፡ የማይቃወም ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳው ፡ ዕርቁን ፡ ተቀብሎ ፡ በማጽደቅ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ እንዲያያዝ ፡ ያደርጋል ።

BACK



(፪) ይህንንም ፡ ተቀብሎ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ካያያዘው ፡ በኋላ ፡ በተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አመልካችነት ፡ በእርቁ ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ዕርቁ ፡ ወይም ፡ ስምምነቱ ፡ የተፈጸመው ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ታራቂዎቹ ፡ ክርክራቸውን ፡ በዕርቅ ፡ መፈጸማቸውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ። ከሳሹም ፡ ከነገሩ ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲፈቅድለት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፸፰ ።በፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ክስን ፡ ስለመተው ፡ ወይም ፡ ከክርክር ፡ ውጭ ፡ ስለመሆን ።

(፩) ክሱ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከሳሹ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ በማንሳት ፡ ከተከሣሾቹ ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑትን ፡ ከክሱ ፡ ውጭ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለመተው ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ሲያጋጥሙትና ፡ ነገሩም ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ሲገመት ፤

(ሀ) በክሱ አቀራረብ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡

(ለ)ተከሳሹ ፡ ባቀረበው ፡ ነገር ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ሊያስፈቅድለት ፡ የሚችል ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፤ ስለጉዳዩ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ከሳሹ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በተወው ፡ ነገር ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችልበትን ፡ መብቱን ፡ በመጠበቅ ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲተው ፡ (እንዲያነሳ) ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ እንደገና ፡ ለሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክስ ፡ እንዳልቀረበ ፡ ተቆጥሮ ፡ የይርጋው ፡ ዘመን ፡ የሚታሰበው ፡ በአዲሱ ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ ይሆናል ።

BACK



**ቍ ፡ ፪፻፳፱ ። ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ክስን ፡ ስለመተውና ፡ ከክርክር ፡ ውጭ ፡ ስለመሆን ።**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፳፰ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ ባለመጠበቅ ፡ ከሳሹ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ሳይቀበል ፡ ክሱን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የተወ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚወስንበትን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ ያለፈቃድ ፡ በተወው ፡ ወይም ፡ በሠረዘው ፡ ነገር ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

(፪) ከሳሾቹ ፡ ብዙ ፡ ሆነው ፡ ከነዚሁ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ሌሎቹን ፡ ሳያስፈቅድ ፡ ክሱን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የሚተው ፡ በሆነ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ላንዱ ፡ ከሳሽ ፡ ብቻ ፡ ክስን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የማንሳት ፡ ፈቃድ ፡ ይሰጠዋል ፡ የሚል ፡ ትርጉምን ፡ አያስከትልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፴ ። ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ተቋርጦ ፡ ስለመቅረቱ ።**

ክሱ ፡ በሚቀጥልበት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ መቋረጡን ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ መቅረቱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ማስረጃ ፡ የተገነዘበ ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ኪሣራና ፡ ስለ ፡ ካሣ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ክሱን ፡ ይዘጋዋል ። ምክንያቱንም ፡ ዘርዝሮ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ያሰፍራል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

## ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚቀመጥ ፡ ገንዘብ ።

**ቍ ፡ ፪፻፴፩ ። ተከሳሽ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚያስይዝበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ክርክሩ ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ዕዳ ፡ በሙሉ ፡ የሚሸፍን ፡ ገንዘብ ፡ በመያዣ ፡ ሥም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማስቀመጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ ያስያዘ ፡ መሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በኩል ፡ ለከሳሽ ፡ ይገለጽለታል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሌላ ፡

አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ የሚጠየቀው ፡ ዕዳ ፡ በፍ ርድ ፡ ቤቱ ፡ መቀመጡ ፡ የተገለጸለት ፡ ከሳሽ ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲከ ሲያመለክት ፡ እንዲሰጠው ፡ ሊያዝለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። ተከሳሽ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ በከፊል ፡ ስለሚያስይ ዝበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) ተከሳሹ ፡ በከፊል ፡ ያስያዘውን ፡ ገንዘብ ፡ ከሳሽ ፡ የተቀበለ ፡ እንደሆነ ፡ ቀሪ ፡ ለሆነው ፡ ሂሳብ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ያስያዘው ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈለግበ ትን ፡ ዕቃ ፡ ለመሸፈን ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተረ ድቶ ፡ ከሳሹ ፡ ይህንኑ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀበል ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዕዳ ፡ በሙሉ ፡ ካስ ያዘ ፡ በኋላ ፡ የሚነሳው ፡ ክርክር ፡ ያስከተለውን ፡ ወጭና ፡ ኪሣራ ፡ ከሳሹ ፡ ይከፍላል ። እንዲሁም ፡ ተከሳሹ ፡ ገንዘቡን ፡ ከማስቀመጡ በፊት ፡ ከሳሹ ፡ ከሚገባው ፡ በላይ እንዲከፈለው ፡ በመጠየቁ ፡ ምክንያት ፡ የተነሳው ክርክር ፡ ያስከተለውን ፡ ኪሣራና ፡ ወጭ ፡ ሁሉ ፡ ከሳሹ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። የተያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ዕዳውን ፡ በሙሉ ፡ የሚሸፍን ፡ መሆኑን አምኖ ፡ ስለመቀበል ።**

(፩) ተከሳሽ ፡ ያስያዘው ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ዕዳ ፡ በሙሉ ፡ የሚሸፍን ፡ መሆኑን ፡ ከሳሹ ፡ አምኖ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጽሑፍ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያቀርብ ፡ የከሳሹን ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀብሎ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ካያያዘ ፡ በኋላ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለሚወስነው ፡ ኪሣራ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ የሚይዘው ፡ ለተነሳው ፡ ክርክር ፡ ይበልጥ ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ የትኛው ፡ ወገን ፡ እንደሆነ ፡ በማመዛዘን ፡ ነው ።

BACK



# አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## በአጭር ፡ ሁኔታ ፡ በሚወሰኑ ፡ ክርክሮች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፬ ። በክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚሠፍር ፡ ልዩ ፡ መግለጫ ።**

ከሳሽ ፡ ከተከሳሽ ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀው ፡ ሂሳብ ፡ ወይም ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ከነወለዱ ፡ ወይም ፡ ያለወለዱ ፡ ወይም ፡ ልኩ ፡ ተወስኖ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ክሱም ፡ የተመሠረተው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡

(ሀ) በውል ፡ መሠረት ፡ በግልጽ ፡ በተደረገ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በሚመሠረት ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ አለብኝ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ በቸክ ፡ ወይም ፡ ተራ ፡ የሆነ ፡ ባለዕዳነትን ፡ በሚገልጽ ፡ ውል ፡ ወይም ፡

(ለ) በግዴታ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ በሂሳብ ፡ በተጣራ ፡ ሰነድ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ በተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡

(ሐ) ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ ሲሆን ፡ በአላፊነት ፡ ለመክፈል ፡ የዋስትና ፡ ግዴታ ፡ በተጽረመበት ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ የሚጠየቅ ፡ ገንዘብ ፡ ተገቢው ፡ ዳኝነት ፡ ከተከፈለበት ፡ በኋላ ፡ በከሳሹ ፡ ምርጫ ፡ የተፋጠነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻላል ። ክሱ ፡ በከሳሹ ፡ ወይም ፡ ጉዳዩን ፡ በሚያውቀው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ሆኖ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። የመሐላ ፡ ቃሉም ፡ የሚያረጋግጠው ፡ የነገሩን ፡ እውነተኛነት ፡ የተጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ ትክክለኛነት ፡ ተከሳሹም ፡ ለነገሩ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ መከላከያ ፡ እንደሌለው ፡ ከሳሽ ፡ የሚያምንበት ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፹፩ ። ተከሳሹ ፡ ባለመቅረቡ ፡ በሌለበት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ ተደግፎ ፡ ከልዩ ፡ መግለጫ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በተያያዘው ፡ ቍጥር ፡ ፪ ሠንጠረዥ ፡ ወይም ፡ ተስማሚ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በሚገምተው ፡ በሌላ ፡ ፎርም ፡ ለተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲደርሰው ፡ ያደርጋል ። ተከሳሹም ፡ ቀርቦ ፡ ለመከላከል ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ጠይቆ ፡ ካላስፈቀደ ፡ በቀር ፡ መከላከያ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

(፪) በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሽ ፡ ወይም ፡ ከተከሳሾቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ቍጥራቸው ፡ ካንድ ፡ የበለጡ ፡ ተከሳሾች ፡ ቀርበው ፡ መከላከያ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳያመለክቱ ፡ የቀሩ ፡ ወይም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሽ ፡ የጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ ከነወለዱ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ። በፍርዱም ፡ ላይ ፡ ቀርበው ፡ ለመከላከል ፡ ፈቃድ ፡ ያልጠየቁት ፡ ተከሳሾች ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ወጭና ፡ ኪሣራ ፡ ጭምር ፡ እንዲከፍሉ ፡ ይታዘዛሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። ቀርቦ ፡ ለመከላከል ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።

(፩) ተከሳሹ ፡ መከላከል ፡ እንዲፈቀድለት ፡ የሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ መሆን ፡ አለበት ። መከላከያውም ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ ይገባዋል ። ነገሩን ፡ የሚከላከለው ፡ በከፊል ፡ ሲሆን ፡ የሚከራከርበትን ፡ ክፍል ፡ መለየት ፡ ይኖርበታል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ለመቃወም ፡ ፈቃድ ፡ የጠየቀውን ፡ ተከሳሽ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ ተቀብሎ ፡ ሊመረምረው ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተከሳሹ ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰነድ ፡ የርስት ፡ ካርታ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ የጽሑፍ ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ የሰነድ ፡ ቅጂ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሊያዘው ፡ ይችላል ።

(፫) ተከሳሹ ፡ ያቀረበው ፡ የመሐላ ፡ ቃልና ፡ የማመልከቻው ፡ ግልባጭ ፡ ከመጥሪያው ፡ ጋር ፡ ለከሳሽ ፡ እንዲደርሰው ፡ ይደረጋል ፡-

**ቍ ፡ ፪፻፹፯ ። ተከሳሹ ፡ ለመከላከል ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ያቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነትን ፡ ሲያጣ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ።**

ተከሳሹ ፡ ቀርቦ ፡ መከላከል ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ያቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መርምሮ ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፰ ። ጉዳዩን ፡ በከፊል ፡ ስለመወሰን ።**

(፩) የቀረበው ፡ መከላከያ ፡ የሚመለከተው ፡ ክሱን ፡ በከፊል ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ክሱን ፡ በከፊል ፡ ያመነ ፡ እንደሆነ ፡ ከሳሹ ፡ ለመታነበት ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ መከላከያ ፡ ላልቀረበበት ፡ ክስ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ስለ ፡ ኪሣራና ፡ ስለማንኛውም ፡ ወጭ ፡ አከፋፈል ፡ በመያዣ ፡ ስለሚቀመጥ ፡ ገንዘብ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ተከሳሹ ፡ ከቀረበበት ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ ፡ ላልሰጠበት ፡ ጉዳይ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲከላከል ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፹፱ ። በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ።**

ማናቸውም ፡ ተከሳሽ ፡ በቂ ፡ መከላከያ ፡ የሚያቀርብ ፡ መሆኑንና ፡ ቀርቦ ፡ ለመከላከልም ፡ የሚያስፈቅድለት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ የቀሩት ፡ ተከሳሾች ፡ ግን ፡ በቂ ፡ መከላከያ ፡ የሌላቸው ፡ ሆነው ፡ ለመከላከል ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ ያቀረቡትን ፡ ጥያቄ ፡ ያልተቀበላቸው ፡ ሲሆን ፡ እንዲከላከል ፡ የተፈቀደለት ፡ ተከሳሽ ፡ ብቻ ፡ ቀርቦ ፡ ክርክሩን ፡ እንዲቀጥል ፡ በማድረግ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ባላቀረቡትና ፡ መከላከል ፡ ባልተፈቀደላቸው ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ መከ

BACK



ላከል ፡ ከተፈቀደላቸው ፡ ተከሳሾች ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ጉዳይ ፡ አይ መለከትም ።

ቊ ፡ ፪፻ ፺ ። መከላከል ፡ ስለሚፈቀድበት ፡ ሁኔታ ።

ተከሳሹ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲከላከል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ በሚ ሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ፈቃዱን ፡ ያላንዳች ፡ ግዴታና ፡ ገደብ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ። አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ግን ፡ ስለዋስትና ፡ ገን ዘቡ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚያዝበት ፡ ሁኔታ ፡ ክርክሩ ፡ ስለሚሰ ማበት ፡ ሁኔታና ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ መከላከያ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪፻ ፺፩ ። ክሱ ፡ ስለሚመራበት ፡ ሁኔታ ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

የመከላከልን ፡ መብት ፡ ያለ ፡ ግዴታ ፡ ወይም ፡ ከግዴታ ፡ ጋር ፡ ሲፈቅድ ፡ ፍርድ ቤቱ ፡ ለክርክሩ ፡ ወይም ፡ ለተያዘው ፡ ጭብጥ ፡ ወይም ፡ ለቀረበው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ተገቢና ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ በቀጥታ ፡ እንዲሰማ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፪፻ ፺፪ ። ፍርድን ፡ ስለማገድ ።

ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ለተከሳሹ ፡ የተላከው ፡ መጥሪያ ፡ በሚገባ ፡ ያልደረሰው ፡ ወይም ፡ የመጥሪያው ፡ አሰጣጥ ፡ ሥር ዓት ፡ በሚገባ ፡ ያልተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ጉድለት ፡ የተፈጸመበትን ፡ ምክንያት ፡ በመዝ ገቡ ፡ ላይ ፡ አስፍሮ ፡ ፍርዱ ፡ ከመፈጸሙ ፡ እንዲቆይና ፡ የተሰጠ ውም ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳይፈጸም ፡ በማድረግ ፡ ተከሳሹ ፡ ቀርቦ ፡ እን ዲከላከልና ፡ ስለ ፡ ጉዳዩም ፡ አፈጻጸም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየ ውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፱ ።

## አላፊነትን ፡ ለማስወረድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ።

ቊ ፡ ፪፻ ፺፫ ። ትርጓሜ ።

አላፊነትን ፡ ለማስወረድ ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ ማለት ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሌሎች ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ የሆነ ፡ ሀብት ፡

ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ የተባለው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ የኛ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የጠየቁት ፡ እንደሆነ ፡ አላፊነቱ ፡ ላንደኛው ፡ ወይም ፡ ከጠያቂዎቹ ፡ መካከል ፡ ለተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ የተጠየቀውን ፡ ነገር ፡ ለማስረከብ ፡ እንዲችል ፡ ተረካቢዎቹ ፡ ወይም ፡ ባለመብቶቹ ፡ ተለይተው ፡ እንዲታወቁ ፡ ለማስወሰን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ ማለት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻ ፳፬ ። አላፊነትን ፡ ለማውረድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ።**

አላፊነትን ፡ ለማውረድ ፡ ደንበኛው ፡ ዳኝነት ፡ ተከፍሎበት ፡ የሚቀርብ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከሚገለጽበትም ፡ ሌላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ መያዝ ፡ አለበት ።

(ሀ) ከሳሹ ፡ ክስ ፡ ባቀረበበት ፡ በዋናው ፡ ነገር ፡ የሚጠይቀው ፡ ለክሱ ፡ ካወጣው ፡ ወጭና ፡ ኪሣራ ፡ በቀር ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ወለድ ፡ ወይም ፡ ባለቤትነት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፤

(ለ) ተከሳሾቹ ፡ በሚጠይቁት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ መብት ፡ አለን ፡ ሲሉ ፡ የጠየቁት ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፤

(ሐ) በከሳሹና ፡ በማናቸውም ፡ ተከሳሽ ፡ መካከል ፡ ውስጣዊ ፡ የሆነ ፡ የተንኰል ፡ ስምምነት ፡ የሌለ ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ።

**ቍ ፡ ፪፻ ፳፭ ። ክስ ፡ የቀረበበትን ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማስቀመጥ ።**

ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ነገር ፡ ገንዘብ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ ለመቀመጥ ፡ የሚችል ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ አመልካቹ ፡ ይህንኑ ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ይታዘዛል ። ይህንንም ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪፈጸም ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥለትም ።

**ቍ ፡ ፪፻ ፳፮ ። ተከሳሹ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ክስ ።**

አላፊነትን ፡ ለማስወረድ ፡ ክስ ፡ ባቀረበው ፡ ከሳሽ ፡ ላይ ፡ ከተከሳሾቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ክርክር ፡ የተነሳበት ፡ ሀብት ፡

ይገባናል ፡ ሲሉ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ክስ ፡ አቅርበው ፡ እንደሆነ ፡ የአላፊነት ፡ ማስወረድ ፡ ክስ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ እን ዲታገድ ማስታወቂያ ፡ ይሰጣል ። ይህም ፡ ማስታወቂያ ፡ የተላ ከለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ። የኪሣራውና ፡ የሌላው ፡ ወጭ ፡ አከፋፈል ፡ ከሳሾቹ ፡ ክስ ፡ ባቀረ ቡበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ አልተወሰነ ፡ እንደሆነ ፡ አላፊነ ትን ፡ ለማስወረድ ፡ ክሱ ፡ በቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፪፻ ፶፯ ። በመጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

(፩) በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ በቀረበው ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ለመ ስጠት ፡ ይችላል ።

(ሀ) ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ በሚሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ከሳሹ ፡ ከሚፈል ግበት ፡ ግዴታ ፡ ነፃ ፡ እንዲሆን ፡ ኪሣራ ፡ እንዲቆረጥለትና ፡ ከክሱ ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሰናበት ።

(ለ) ትክክለኛና ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ለክርክሩ ፡ ውሳኔ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ እንዲቆዩ ፡ ማድረግ ።

(፪) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሰጡት ፡ የመተማመን ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ ነገሩን ፡ ለመወሰን ፡ የሚያስች ለው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሰጡት ፡ የመተማመን ፡ ቃል ፡ ነገሩን ፡ ለመወሰን ፡ የማያስችል ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እን ደሆነ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ይፈጽማል ።

(ሀ) በተከራካሪዎቹ ፡ መካከል ፡ የተነሳው ፡ ነገር ፡ እንዲጣ ራና ፡ ጭብጡ ፡ ተመሥርቶ ፡ የክርክሩ ፡ መሰማት ፡ እንዲቀጥል ፡ ያዛል ።

(ለ) ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በዋናው ፡ ከሳሽ ፡ ተተክቶ ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ ከሳሽ ፡ ጋር ፡ አባሪ ሆኖ ፡ እንዲከስ ፡ በመወ ሰን ፡ ክሱ ፡ በመደበኛው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲመራ ፡ ያደርጋል ።

BACK



**ቍ ፡ ፪፻ ፺፰ ። ተከራዮች ፡ ተነቃዮች ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ጠባቂዎች ፡ አላፊነትን ፡ የማስወረድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የማይችሉ ፡ ስለመሆናቸው ።**

ተከራዮች ፡ ተነቃዮች ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ጠባቂዎች ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ተከሰናል ፡ በማለት ፡ በዚህ ምዕራፍ ፡ የተነገረውን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት አድርገው በሹዋሚዎቻቸው ፡ ወይም ፡ በባለንብረቶቹ ፡ ላይ የአላፊነትን ፡ ማስወረድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ በሆነው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ከሹሚዎቹ ፡ ወይም ፡ ከባለ ፡ ንብረቶቹ ፡ መብት ፡ አግኝተናል ፡ በሚሉ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ አላፊነትን የማስወረድ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻ ፺፱ ። ለመዝገብ ፡ ቤት ፡ ስለማስረከብ ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ክስ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ባለመብቱ ፡ እንዲረከበው ፡ ማስታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ ከመጠየቅ ፡ አያግደውም ።

(፪) ለማስታወቂያው ፡ መልስ ፡ ያላገኘ ፡ እንደሆነ ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ክሱ ፡ ለቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ በደረሰኝ ፡ ለማስረከብና ፡ ለዚሁም ፡ ያወጣውን ፡ ኪሣራ ፡ ቀንሶ ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሲያስረክብ ፡ የሚያስረክብበትን ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ተቀናሽ ፡ ያደረገውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክና ፡ ምክንያቱን ፡ በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ፡ የተነገረውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ መልስ ፡ ያላገኘ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ በመሐላ ፡ ቃሉ ፡ የተደገፈ ፡ ጽሑፍ ፡ ከሚያስረክበው ፡ ዕቃ ፡ ጋር ፡ አባሪ ፡ አድርጎ ፡ ለመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። ይህንንም ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማናቸውም ፡ መጥሪያ ፡ በሚላክበት ፡ ሁኔታ ፡ ለባለመብቱ ፡ እንዲደርሰው ፡ ይደረጋል ።

(፬) በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የተቀመጠው ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ባለመብት ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ቀርቦ ፡ በጽሑፍ ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የቀረበለት ፡ ማመልከቻ ፡ አጥጋቢ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ለጠያቂው ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ።

## የተፋጠነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

## ክ ፍ ል ፡ ፩ ።

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

### ቍ ፡ ፫፻ ። የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ።

(፩) የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉ ፡ ቍጥሮች ፡ ተገልጾ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ ከተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ ውጭ ፡ የሚቀርቡት ፡ ማመልከቻዎች ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፪ ፩ ሐ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ሊወሰኑ ፡ ይችላሉ ።

### ቍ ፡ ፫፻፩ ። ክስ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ሕግ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ተገቢውን ፡ ዳኝነት ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ላቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ሕግ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ቀንና ፡ ዓመት ፡ ምሕረቱ ፡ ተሞልቶበት ፡ የተፈረመ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። አቤቱታው ፡ የሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ለክሱ ፡ መነሻና ፡ ለአቤቱታው ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ በተፈጠረ ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ አመልካቹ ፡ አቤቱታውን ፡ ለማቅረብ ፡ የቻለበት ፡ ሥልጣን ፡ ለአቤቱታው ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ሕግና ፡ አቤቱታ ፡

BACK



ያቀረበበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጽ ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገሩትን ፡ ሰነዶችና ፡ ሌላም ፡ ለጉዳዩ ፡ አወሳሰን ፡ ይጠቅማሉ ፡ ብሎ ፡ የሚገምታቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ ከማመልከቻው ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፫፻፪ ። ማመልከቻው ፡ ተቀባይነትን ፡ የሚያጣበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነትን ፡ የሚያጣው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ።

(ሀ) አመልካቹ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ሥልጣንና ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሲሆን ፤

(ለ) ማመልከቻው ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፩ ፡ (፩) ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ ተሟልቶ ፡ ያልቀረበ ፡ ሲሆን ፣ ወይም

(ሐ) ማመልከቻ ፡ የቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ መታየት ፡ የማይገባው ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ።

(፪) የማመልከቻው ፡ ተቀባይነትን ፡ ማጣት ፡ ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ እንደተወሰነ ፡ አያስቆጥረውም ። ስለሆነም ፡ በዚያው ፡ ጉዳይ ፡ አዲስ ፡ ማመልከቻ ፡ ከማቅረብ ፡ የሚያግደው ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፫፻፫ ። በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሳኔ ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ። በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ መልክ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) ለማመልከቻው ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚያዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ የሚሰጠው ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

BACK



(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜና ፡ ሁኔታ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብለት ፡ ከማዘዝ ፡ አያግደውም ።

ቍ ፡ ፫፻፬ ። በዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚሰጡ ፡ ትእዛዞች ።

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የተነገረውን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ አከፋፈልና ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ውሳኔ ፡ ለማመልከቻው ፡ መነሻ ፡ በሆነው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠውን ፡ ወይም ፡ መስጠት ፡ የሚገባውን ፡ ወይም ፡ ለጉዳዩ ፡ አፈጻጸም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ አያግደውም ።

ቍ ፡ ፫፻፭ ። የማረጋገጫ ፡ ወረቀት ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመልካቹን ፡ የሚደግፍ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነና ፡ የዚህም ፡ ውሳኔ ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጠው ፡ አመልካቹ ፡ የጠየቀ ፡ እንደሆነ ፡ ቀኑና ፡ ዓመቱ ፡ ምሕረቱ ፡ ተሞልቶበት ፡ ውሳኔውን ፡ በሰጡት ፡ ዳኞች ፡ የተፈረመ ፡ የማረጋገጫ ፡ ወረቀት ፡ ይሰጠዋል ።

25/88 Art. 5(2) Cum 14 - Jurisdiction

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በተለይ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ ስምን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፵፪ ፡ እና ፡ ፵፫ ፡) መዝገብ ፡ እንዳይገባ ፡ ወይም ፡ ጋብቻ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ስለ ፡ መቃወም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፱ ፬፻፸ ፯፻፩ ክስን ፡ ለማቅረብ ፡ ፈቃድ ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፱ ፯፻፸፫ ፯፻፸፱ ፯፻፹፯ ፡) ስለ ፡ ክልከላ ፡ ወረቀት ፡ መነሳት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፸፯ ፡ ጋብቻን ፡ ስለ ፡ መቃወም ፡ ( የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፰፻ ፺፪ ፡ ) ፡ በብቸኝነት ፡ ስለ ፡ መኖር ፡ ቍጥር ፡ ፰፻ ፺፯ ፡ ) አንዳንድ ፡ መዛግብትን ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ሰነዶችን ፡ ለመመልከት ፡

BACK



ስለ ፡ መጠየቅ ፡ ወይም ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፻፳፱ — ፪፻፱ — ፪፻፴፱— ፪፻፹፯— ፭፻፳፫—፭፻፳፰—፭፻፴፭—፮፻፴ ፡ መሠረት ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፫) በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ የሰፈረው ፡ ስሕተት ፡ እንዲታረም ፡ ወይም ፡ እንዲሠረዝ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፻፳፩— ፻፳፯—፩ሺ ፯፻፳፫ ፡ እና ፡ ፩ሺ ፯፻፴ ፡ ወይም ፡ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሠፈረው ፡ እንዲጸድቅ ፡ ወይም ፡ እንዲረጋገጥ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፻፵፩— ፯፻፳፰—፯፻፳፫— ፯፻፵፬— ፯፻፳፫-፯፻፳፯—፯፻፳፯ ፡ እና ፡ ፳፻፬ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፵፩ ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ ነገርን ፡ ትክክለኛነት ፡ ለማስመስከር ፡ ወይም ፡ ሕጋዊነትን ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ ጥያቄ ፡ በሚቀርብለት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ በክስ ፡ መልክ ፡ ሳይሰማ ፡ ተገቢውን ፡ ምርመራ ፡ ካደረገ ፡ ወይም ፡ እንዲደረግ ፡ ካዘዘ ፡ በኋላ ፡ ለጉዳዩ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ፡ ወይም ፡ የቀረበለት ፡ ጉዳይ ፡ ሕጋዊ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጽሑፍ ፡ ይሰጣል ፡ ወይም ፡ እንዲመዘገብና ፡ ሕጋዊነቱ ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ያደርጋል ፡ ወይም ፡ በቀረበለት ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ጉዳዩ ፡ መመዝገቡንና ፡ ሕጋዊነቱን ፡ አረጋግጦ ፡ ቀኑንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ በመሙላት ፡ አስፈላጊውን ፡ ማረጋገጫ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፮ ። ስለ ፡ ይግባኝ ።

(፩) ለማመልከቻው ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ሕግ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚያዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፫፻፱ ፡ እስከ ፡ ፫፻፲፩ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ሌላ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፪) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ሊቀርብበት ፡ የሚገባው ፡ የፍርዱ ፡ ውሳኔ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በአሥር ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ ለይግባኝ ፡ ማቅረቢያ ፡ የተወሰነው ፡ ቀን ፡ ከማለፉ ፡

ወይም ፡ ይግባኙ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ ፍርዱ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

## ል ዩ ፡ ጉ ዳ ዮ ች ።

### ቍ ፡ ፫፻፯ ። ስለ ፡ ስብሰባ ።

በሕግ ፡ የታዘዘ ፡ ስብሰባ ፡ ወይም ፡ የቤተዘመድ ፡ ጉባዔ ፡ ስብሰባ ፡ እንዲደረግ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስብሰባውን ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ ጉዳዩን ፡ ለማስፈጸም ፡ ተገቢነት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ የሚገምተውን ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ ስብሰባውን ፡ እንዲያስፈጽምና ፡ ሌላውንም ፡ በሕግና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የታዘዘውን ፡ ጉዳይ ፡ እንዲያከናውን ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፫፻፰ ። ስለ ፡ መሾም ።

(፩) ተጠባባቂ ፡ ዳሬክተር ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ እንዲሾም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብ ፡ የተጠየቀውን ፡ የመሾም ፡ ጉዳይ ፡ ለማዘዝ ፡ በሕግ ፡ የተነገረ ፡ ድንጋጌ ፡ መኖሩን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ የተጠባባቂ ፡ ዳሬክተርነትን ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂነትን ፡ ወይም ፡ የሒሳብ ፡ አጣሪነትን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ። አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ለተሾመው ፡ ሰው ፡ ተገቢውን ፡ አበል ፡ ይወስንለታል ።

(፪) ሞግዚት ፡ ምትክ ፡ ሞግዚት ፡ ጠባቂ ፡ ወይም ፡ የቤተዘመድ ፡ ጉባዔ ፡ ተጨማሪ ፡ አባል ፡ እንዲሾም ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰው ፡ ልጅ ፡ የቅርብ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ እንዲቀርቡ ፡ ጊዜ ፡ ወስኖ ፡ ቤተዘመዶች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ አሳብ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ የተጠየቀውን ፡ የሹመት ፡ ጉዳይ ፡ ይወስናል ።

(፫) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፲፩ ፩፻፲፱ ፩፻፳ ፩፻፳፱ ፩፻፴፰ ፫፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ ለሚቀርቡት ፡ ጉዳዮችም ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፱ ። ውሳኔዎችን ፡ ስለ ፡ መሻር ።

(፩) ውሳኔ ፡ እንዲሻር ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ በተለይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፵፰ ፡ እና ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፲፮ ፡ በተመለከተው ፡ ዓይነት ፡ ሲሆን ፡ እንዲሻር ፡ የተጠየቀው ፡ ውሳኔ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭና ፡ የድርጅቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ኮፒ ፡ ከማመልከቻው ፡ ጋር ፡ አባሪ ፡ ሆኖ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) በቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተገነዘበው ፡ እንደሆነ ፡ የማመልከቻው ፡ ግልባጭ ፡ ለድርጅቱ ፡ ለዲሬክተሮቹና ፡ ለኦዲተሮቹ ፡ እንዲደርስ ፡ ያደርጋል ። እነዚህም ፡ በበኩላቸው ፡ ውሳኔው ፡ የማይሻርበትን ፡ ምክንያት ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በጽሑፍ ፡ መግለጽ ፡ አለባቸው ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ ምክንያት ፡ ያልተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ ይሽረዋል ።

(፬) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የአንድ ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ ስብሰባ ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከአባልነቱ ፡ እንዲወገድ ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፵፱ ፡ (፩) ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የድርጅቱ ፡ ኮሚቴ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ወይም ፡ ትርፍን ፡ ስለ ፡ መካፈል ፡ ወይም ፡ የሂሳብ ፡ ሚዛንን ፡ ስለ ፡ ማጽደቅ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ባለዕዳ ፡ በሆነ ፡ ነጋዴ ፡ ላይ ፡ ስለሚያቀርቡት ፡ መቃወሚያ ፡ ጉዳይም ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። ስለሆነም ፡ ከዚህ ፡ በተለዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ተገቢነት ፡ ያላቸው ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ሌሎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፲ ። ለማስናበት ፡ ለማስወገድና ፡ ለመሻር ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።

(፩) የአንድ ፡ ድርጅት ፡ ሸሪክ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ከሥራው ፡ እንዲሻር ፡ ወይም ፡ ከሽርክናው ፡ እንዲወገድ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፩ ፡ እና ፡ ፪፻፺፫ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡

ቍጥር ፡ ፰፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ የቀረበለትን ፡ ማመልከቻ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከተው ፡ ሰው ፡ እንዲደርሰው ፡ አድርጎ ፡ ማስታወቂያው ፡ በደረሰው ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የማይሻርበትን ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ የማይለቅበትን ፡ ምክንያት ፡ እንዲያስረዳ ፡ ያዘዋል ፡፡

(፪) በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መልስ ፡ ያልሰጠ ፡ ወይም ፡ የማይሻርበትን ፡ ምክንያት ፡ ያልገለጸ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሥራው ፡ እንዲለቅ ፡ ወይም ፡ ከአባልነቱ ፡ እንዲወገድ ፡ ያዛል ፡፡

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂን ፡ ወይም ፡ ሞግዚትን ፡ ስለ ፡ መሻር ፡ ለሚቀርቡ ፡ ጉዳዮችም ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ፡፡

## ቍ ፡ ፫፻፲፩ ፡፡ ሽርክናን ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅትን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ፡፡

(፩) ሽርክናን ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅትን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ፡ ወይም ፡ በአደራ ፡ ንብረት ፡ ጥበቃ ፡ የተቋቋመ ፡ ድርጅትንና ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅትን ፡ ስለ ፡ መሠረዝ ፡ የሚቀርቡት ፡ ጥያቄዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፱ ፡ (፩) ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ተገቢነቱ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ፡፡

(፪) እንዲሁም ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፱ ፡ (፪) ፡ እና ፡ (፫) ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ለሚቀርቡ ፡ ጉዳዮች ፡ እንደነገሩ ፡ አግባብ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ይኖራቸዋል ፡፡

## ቍ ፡ ፫፻፲፪ ፡፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶችን ፡ ስለ ፡ ማቀላቀል ፡፡

(፩) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፰፻፳ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ብዛታቸው ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶች ፡ በአንድነት ፡ እንዲቀላቀሉ ፡ የሚጠይቅ ፡ ማመልከቻ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይህንኑ ፡ የሚቀበል ፡ ወይም ፡ የሚቃወም ፡ መሆኑን ፡ ጥያቄው ፡ በደረሰው ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እንዲገልጽለት ፡ በማስታወቅ ፡ የቀረበለትን ፡ ማመልከቻ ፡ ይልክለታል ፡፡

(፪) የቀረበለት ፡ ጥያቄ ፡ ለጠቅላላው ፡ ጥቅም ፡ የሚበጅ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ የድርጅቱን ፡ መቀላቀል ፡ ያዛል ፡፡

BACK



ቍ ፡ ፫፻፲፫ ። ጋብቻን ፡ ስለመቃወም ።

ጋብቻ ፡ እንዳይፈጸም ፡ የመቃወም ፡ አቤቱታ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲደርሰው ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ እንዲቀርቡ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ በወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ክርክሩን ፡ ካጣራ ፡ በኋላ ፡ ተገቢ ፡ የመሰለውን ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ ተቃዋሚው ፡ ወገን ፡ የሚቃወምበትን ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ በግልጽ ፡ ሳያስረዳ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ መቃወሚያውን ፡ ባለመቀበል ፡ ነገሩን ፡ ይዘጋዋል ።

ቍ ፡ ፫፻፲፬ ። ክልከላን ፡ ለማስወገድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ።

(፩) በአንድ ፡ ድርጅት ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ ሊመዘገብ ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ እንዳላስመዘግብ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ሥርዓት ፡ እንዳልፈጽም ፡ ተከለከልኩ ፡ የሚል ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ክልከላ ፡ እንዲወገድ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲታዘዝለት ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ ማመልከቻ ፡ አቤቱታው ፡ የቀረበበት ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ሰው ፡ እምቢተኛ ፡ የሆነበትን ፡ ምክንያት ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እንዲገለጽለት ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መልስ ፡ ያልተሰጠ ፡ ወይም ፡ ምክንያቱ ፡ ያልተገለጸ ፡ እንደሆነ ፡ ክልከላው ፡ እንዲወገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፬ ።

## ስ ለ ፡ ግ ል ግ ል ።

ቍ ፡ ፫፻፲፭ ። መ ሠ ረ ቱ ።

(፩) ነገሩ ፡ በግልግል ፡ እንዲወሰን ፡ ሕግ ፡ የሚፈቅድ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሚያከራክራቸው ፡ ነገር ፡ በግልግል ፡ እንዲወሰን ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ በግልግል ፡ እንዲታይ ፡ የተስማሙ ፡ እንደሆነ ፡ ነገሩ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

BACK



(፪) በግልግል ፡ እንዳይወሰን ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫ሺ. ፻፴፭ ፡ እንደተነገረው ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ ለግልግል ፡ ዳኝነት ፡ አይቀርብም ።

(፫) ማንም ፡ ሰው ፡ ጉዳዩን ፡ በግልግል ፡ ለማስወሰን ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ክርክሩን ፡ በግልግል ፡ ዳኝነት ፡ ለማስወሰን ፡ አይችልም ።

(፬) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፫ሺ.፫፻፳፭ ፡ እስከ ፡ ፫ሺ.፫፻፵፮ ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚነኩ ፡ አይደሉም ።

ቍ ፡ ፫፻፲፮ ። የግልግል ፡ ዳኞች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚሾሙበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የግልግል ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ጉባዔ ፡ አባል ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲመረጥ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለጉዳዩ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ ሊሾም ፡ ይችላል ።

(፪) ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ጉዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡ ማናቸውም ፡ ዳኛ ፡ በሌላ ፡ ግልግል ፡ ውስጥ ፡ አባል ፡ ሆኖ ፡ ሊመረጥ ፡ አይችልም ።

(፫) ለማንኛውም ፡ ጉዳይ ፡ የግልግል ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ የተመረጠ ፡ ሰው ፡ የተሾመበትን ፡ ጉዳይ ፡ የሚቀበል ፡ መሆኑን ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ በጽሑፍ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፲፯ ፡- የግልግል ፡ ዳኝነት ፡ አፈጻጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡

(፩) የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባዔ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሁሉ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ ከሚሠራበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይና፡ ተስማሚ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በአስተያየት ፡ ይወስንልን ፡ ብለው ፡ በስምምነት ፡ ካላመለከቱ ፡ በቀር ፡ የግልግሉ ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ጉባዔ ፡ ዳኝነት ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ በተፈቀደው ፡ መሠረት ፡ መወሰን ፡ ይገባዋል ።

(፫) ምስክሮቹ ፡ ቀርበው ፡ ቃላቸውን ፡ በመሐላ ፡ እንዲሰጡ ፡ የግል ግል ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባዔ ፡ ዳኞች ፡ መጥሪያ ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ። ስለሆነም ፡ ጥሪአቸውን ፡ አክብሮ ፡ የማይቀርብ ፡ ምስ ክር ፡ ሲኖር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፻፲፩ ፡ እስከ ፡ ፻፳፩ ፡ በተመ ለከተው ፡ መሠረት ፡ ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ መጥሪያ ውን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀበል ፡ ይችላል ።

(፬) ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ማስረጃውን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ወይም ፡ ክርክሩን ፡ እንዲያሰማ ፡ ተፈቅዶለት ፡ በተሰጠው ፡ መብ ት ፡ ሳይጠቀምበት ፡ ቢቀርም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትክክለኛ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ውሳኔ ፡ በሌለበት ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፰ ። የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ስለሚሰጡት ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ።

(፩) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ብይን ፡ የሚሰጥበትን ፡ ጊዜ ፡ በግል ግሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ እራሳቸው ፡ ለመወሰንና ፡ ይህንንም ፡ የጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ በስምምነት ፡ ለማራዘም ፡ ይችላሉ ።

(፪) የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ብይን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደሚሰጥ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ዓይነት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የካሣንና ፡ የኪሣራንም ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፫) የገላጋዮቹ ፡ ወይም ፡ የሽማግሌዎቹ ፡ ቍጥር ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ የሚሰጡት ፡ ብይን ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

(፬) ብይኑም ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተሞልቶበት ፡ በአባሎቹ፡ ከተፈረመበት ፡ በኋላ ፡ ለተገላጋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዳንድ ፡ ግል ባጭ ፡ ይሰጣቸዋል ።

(፭) ለጋላጋዮቹ ፡ ወይም ፡ ለሽማግሌዎቹ ፡ የሚከፈለው ፡ አበል ፡ አስቀድሞ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደሆነ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታያቸውን፡ አበል ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፱ ፡- ብይኑን ፡ ስለማስፈጸምና ፡ ስለይግባኝ ፤

(፩) በግልግል ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ በሚቀርብበት ፡ ወይም ፡

ብይኑ ፡ እንዲሰረዝ ፡ አቤቱታ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፫፻፶ ፡ እስከ ፡ ፫፻፶፯ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈ ጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ በውሳኔው ፡ ወይም ፡ በብይኑ ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ሲያመለክት ፡ ብይኑ ፡ ወይም ፡ ውሳኔው ፡ የሚፈጸመው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ዓይነትና ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

# ስድስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ይግባኝ ፡ ፍርድን ፡ ስለመቃወምና ፡ ፍርድ ፡ እንዲሻሻል ፡ ወይም ፡ እንዲጣራ ፡ ስለማመልከት ፤

## ክ ፍ ል ፡ ፩ ፤

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፤

### ቍ ፡ ፫፻፸ ፡- ይግባኝ ፡ ስለሚፈቀድበት ፡ ሁኔታ ፤

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ ሕጐች ፡ ውስጥ ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚያዝ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተወሰነ በት ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

(፪) በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት፡ የሚቻል ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ፍርዱን ፡ ለማረም ፤ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ እንደገና ፡ ለማጣራት ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ ይኸው ፡ ሥርዓት ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይፈጸም ፡ ይግባኙን ፡ ማቅረብ ፡ አይፈቀድም ።

(፫) ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክሩን ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ጊዜአዊ ፡ አገልግሎት ፡ ያለው ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፤ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ሲወስን ፤ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ በሚቀርብ ፡ መቃ

ወሚያ ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጥ ፡ ወይም የጠበቃን ፡ እርዳታ ፡ ስለማግኘት ፡ ወይም ፡ ከጠበቃ ፡ ጋር ፡ ስለመ ቅረብ ፤ ወይም ፡ ዳኝነት ፡ ሳይከፈል ፡ በነፃ ፡ ለመክሰስ ፡ እንዲፈ ቀድ ፡ በሚቀርብ ፡ ጥያቄ ፡ በሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛ ዝና ፡ ከሥረ ፡ ነገሩ ፡ ፍርድ ፡ በፊት ፡ በሚሰጠው ፡ በማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ስለሆነም ፡ ለክር ርከሩ ፡ የመጨረሻ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስለተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ያለውን ፡ ቅሬታ ፡ ጨምሮ ፡ ከሥረ ፡ ነገሩ ፡ ጋር ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድን ጋጌ ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዲታሰር ፡ ወይም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ እንዲቆይ ፡ ወይም ፡ ከሥረ ፡ ነገሩ ፡ ፍርድ ፡ በፊት ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ ለሌላው ፡ ወገን ፡ እንዲያዛውር ፡ በተሰጠበት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ የሚያቀርብበትንና ፡ እንዲሁም ፡ ያላግባብ፡ ታስሬአለሁ ፡ ይግባኝ ፡ ይታይልኝ ፡ ሲል ፡ ያቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ተቀባይነት ፡ ባጣ ፡ ጊዜ ፡ ለበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤቱታ ፡ የማቅ ረብ ፡ መብቱን ፡ አያስቀርበትም ።

## ቍ ፡ ፫፻፳፩ ፡- ይግባኝ ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ስላላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፤

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንደየደረጃ ቸው ፡ ይግባኝ ፡ የመስማት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

(ሀ) የወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የፈረደውን ፡ ይግባኝ ፡ ተቀብሎ ፡ የሚያየው ፡ ወረዳው ፡ የሚገኝ በት ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ለ) የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የፈረ ረደውን ፡ ይግባኝ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ሐ) ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የፈረ ደውን ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግ ባኝ ፡ ተቀብሎ ፡ ያያል ።

(፪) የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደውን ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ አይቶ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የተለየ ፡ ፍርድ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፤ እንዲሁም ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረ

ደውን ፡ / ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ አይቶ ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የተለየ ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ይግባኝ ፡ ይግባኝ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ ይሰጣል ።

(ሀ) ከአውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ለ) ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ቍ ፡ ፫፻፳፪ ፡- ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የይግባኝ ፡ ማሰማት ፡ መብቱን ፡ እስከመጨረሻ ፡ ከተጠቀመበት ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፫፻፳፩ ፡ እስከ ፡ ፫፻፰ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነገሩ ፡ እንዲታይለት ወይም ፡ እንዲመረመርለት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱን ፡ አያስቀርበትም ።

ቍ ፡ ፫፻፳፫ ፡- ይግባኝ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ ስለአቀራረቡ ፡ ሥነ ሥርዓት ፤

(፩) ማናቸውም ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፫፻፳፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በይግባኝ ፡ ባዩ ፤ በጠበቃው ፤ በሕግ ፡ አማካሪው ፡ በወኪሉ ፡ ወይም ፡ በነገረ ፡ ፈጁ ፡ ተፈርሞ በት ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ይቀባል ።

(፪) የይግባኙ ፡ አቤቱታ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መረብ ፡ የሚገባው ፡ ይግባኝ ፡ በሚባልበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በተፈረደ በ፷ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

(፫) የይግባኝ ፡ ባዮቹ ፡ ቍጥር ፡ ከአንድ ፡ የሚበልጥ ፡ ሲሆን ፡ የይባኙን ፡ ማመልከቻ ፡ በአንድነት ፡ ጽፈው ፡ ሁሉም ፡ ሊፈርሙበት ፡ ወይም ፡ ጠበቃቸው ፡ ነገረ ፡ ፈጃቸው ፡ ወይም ፡ ወኪላቸው ፡ አንድ ፡ ማመልከቻ ፡ ጽፎ ፡ ስለነርሱ ፡ በመፈረም ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

BACK



(፬) በማናቸውም ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የይግባኝ መዝገብ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በዚሁ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የይግባኙ ነገር ፡ ባጭሩ ፤ የቀረበበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እንደ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራው ፡ ይመዘገባል ።

ቍ ፡ ፫፻፳፬ ። ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ እንዲከፈት ፡ ስለሚቀርብ ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፳፫ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የሚቀርበውን ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ አይቀበለውም ፤ ስለሆነም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻውን ፡ በመለሰው ፡ በ፲ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የተወሰነው ፡ ቀን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ እንዲታይለት ፡ የፈቃድ ፡ መጠየቂያ ፡ ማመልከቻ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ለአመልካቹ ፡ ይገልጽለታል ።

(፪) የይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ ለመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበው ፤ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ከሚጠይቅበት ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ እንደሆነ ፤ የይግባኙን ፡ ማመልከቻ ፡ መልሶ ፡ የፈቃድ ፡ መጠየቂያውን ፡ ማመልከቻ ፡ መቀበል ፡ አለበት ። የፈቃድ ፡ መጠየቂያውና ፡ የይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ የተጻፈው ፡ በአንድ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ሆነ ፡ ጉዳዩን ፡ አለያይቶ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ያዘዋል ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተቀባይነትን ፡ ያላገኙ ፡ ማመልከቻዎች ፡ ለባለጉዳዩ ፡ ቢመለሱም ፤ ቀርበው ፡ ተቀባይነት ፡ ያላገኙ ፡ መሆናቸውን ፡ ይህ ፡ የተወሰነበት ፡ ቀን ፡ በይግባኝ ፡ መመዝገቢያ ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፳፭ ። ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ እንዲከፈት ፡ ስለሚቀርብ ፡ የፈቃድ ፡ ጥያቄ ፡ ማመልከቻ ።

(፩) ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ እንዲከፈት ፡ የሚቀርበው ፡ የፈቃድ ፡ ጥያቄ ፡ ማመልከቻ ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፳፫ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልቀረበበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጽ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ ምክንያቱን ፡ ከሚገልጹ ፡ ማስረጃዎች ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ማስረጃዎቹም ፡ ይግባኙ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልቀረበበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጹና ፡ ውሳኔም ፡ እንዲሰጥበት ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ መገኘት ፡ አለባቸው ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለቀረበለት ፡ የፈቃድ ፡ ጥያቄ ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነትን ፡ የሚያስገኝ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ፈቃድ ፡ ጠያቂውንና ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ወገን ፡ አስቀርቦ ፡ በመጠየቅ ፡ ማስረጃውንም ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፳፮ ፡- በቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሳኔ ፤

(፩) አመልካቹ ፡ የቀረበለትን ፡ የፈቃድ ፡ መጠየቂያ ፡ አቤቱታ ፡ ተቀብሎ ፡ ይግባኙን ፡ በጊዜው ፡ ለማቅረብ ፡ ያልቻለበት ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፤ ይህንኑ ፡ በመዝገብ ፡ ላይ ፡ ካሰፈረ ፡ በኋላ ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻውን ፡ በአሥር ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ይፈቅድለታል ።

(፪) በፈቃድ ፡ መጠየቂያው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ ምክንያት ፡ ይግባኙን ፡ በጊዜው ፡ ለማቅረብ ፡ ያልቻለው ፡ በአመልካቹ ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ወይም ፡ በወኪሉ ፡ ያለመቅረብና ፡ በነዚሁ ፡ ጉድለት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ እንደተነገረው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተቀባይነትን ፡ ለማግኘት ፡ አይችልም ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ የፈቃድ ፡ መጠየቂያ ፡ ማመልከቻ ፡ ቀርቦ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ፡ ተብሎ ፡ በተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ።

(፬) በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የቀረቡ ፡ ማመልከቻዎችና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ በይግባኝ ፡ መመዝገቢያ ፡ ደብተር ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፳፯ ፡- በይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚጻፉ ፡ ነገሮች ፤

(፩) በማናቸውም ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ነገሮች ፡ መገለጽ ፡ አለባቸው ።

BACK



(ሀ) ይግባኝ ፡ የቀረበበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥምና ፡ የሚያስች ልበትን ፡ ቦታ ፤

(ለ) የይግባኝ ፡ ባዩና ፡ የመልስ ፡ ሰጭው ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ሐ) ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስም ፤ ፍርዱ ፤ የተወሰነበትን ፡ ቀንና ፡ የመዝገቡን ፡ ቊጥር ፤

(መ) መጥሪያ ፡ ለመስጠት ፡ እንዲቻል ፡ የመልስ ፡ ሰጭውን ፡ አድራሻ ፤

(ሠ) ለይግባኙ ፡ ምክንያት ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ዝርዝር ፤

(ረ) በይግባኙ ፡ እንዲታረም ፡ የሚፈለገውን ፡ የነገር ፡ ዝርዝ ርና ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዳኝነት ፡ ዓይነት ።

(፪) ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመ ዝገብና ፡ የፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፡ ለመሆኑ ፡ ታት ሞበትና ፡ ተፈርሞበት ፡ ከይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይግባኙን ፡ የሚመሠርተው ፡ ፍርዱ ፡ በተሰጠ በት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ በይግባኝ ፡ ማመ ልከቻው ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ ይኖርበታል ። ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ የሚጠይቅ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ እንዲታ ዩለት ፡ የሚጠይቀውን ፡ የማስረጃ ፡ ዝርዝርና ፡ እንዲሰሙለት ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ስም ፡ የሚገልጽ ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ከይግባኝ ፡ ማመልከቻው ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ያቀርባል ። በተለይም ፡ ይታይልኝ ፡ የሚለው ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ይሰሙልኝ ፡ የሚላ ቸው ፡ ምስክሮች ፡ በመጀመሪያ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ሳይታይለት ፡ ወይም ፡ ሳይሰሙለት ፡ የቀሩበትን ፡ ምክንያትና ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ሊታይልኝ ፡ ይገባል ፡ የሚልበ ትን ፡ ምክንያት ፡ በዝርዝር ፡ የሚያስረዳ ፡ ጽሑፍ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፬) የይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ለመድ ረስ ፡ በሚችል ፡ ግልባጭ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መቅረብ ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፰ ። ይግባኝ ፡ ስለሚባልባቸው ፡ ምክንያቶች ።

(፩) የይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ በአጭሩ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ የሚቃወምበትን ፡ ምክንያት ፡ በመዘርዘር ፡ ለያንዳንዱ ፡ ምክንያት ፡ አርዕስትና ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ በመስጠት ፡ በክርክሩ ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ በሚገባ ፡ ሁኔታ ፡ ተጽፎ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተለይ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ በይግባኝ ማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ዘርዝሮ ፡ ያልገለጸውን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ በማንሳት ፡ ወይም ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ለመከራከር ፡ አይችልም ።

(፫) ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለክርክሩ ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በይግባኝ ፡ ማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የተዘረዘረውን ፡ ወይም ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ አዲስ ፡ ክርክር ፡ እንዲቀርብ ፡ ፈቅዶ ፡ የሰማውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ለመከተል ፡ ሳይገደድ ፡ በማናቸውም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ ምክንያት ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሌሎበለው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ክርክር ፡ እንዲያሰሙ ፡ መብት ፡ በተሰጣቸው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይግባኝ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማመልከቻው ፡ ተዘርዝሮ ፡ ከተገለጸው ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ ከተነሳበት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫፻፷፱ ። ስለ ፡ አዲስ ፡ ነገሮችና ፡ ስለ ፡ አዲስ ፡ ክርክሮች ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፵፰ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያልተነሳውን ፡ ክርክርና ፡ ያልቀረበውን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቀበል ፡ አይችልም ።

(፪) ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭውን ፡ ስለመጥራት ፡ ስለ ፡ ኪሣራው ፡ አከፋፈል ፡ ወይም ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለመስጠትና ፡ ስለ ፡ ሌላውም ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነው ፡ ነገር ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመስ

BACK



ጠት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ክርክሩን ፡ እንዲለውጥ ፡ ወይም ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻውን ፡ እንዲያሻሽል ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፴ ። የይግባኝ ፡ ማመልከቻን ፡ ስለመሠረዝ ፡ ወይም ፡ ስለማሻሻል ።

(፩) የይግባኙ ፡ ማመልከቻ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፳፯ ፡ በተ ነገረው ፡ መሠረት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ለይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይመለስለታል ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ወዲያውኑ ፡ አሻሽሎና ፡ አሟልቶ ፡ እንዲ ያቀርብ ፡ ይነገረዋል ።

(፪) የቀረበውን ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማናቸ ውም ምክንያት ፡ ያልተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ ያልተቀበለበትን ፡ ምክንያት ፡ በመጻፍ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ያደርጋል ።

(፫) ማመልከቻው ፡ ተሻሽሎና ፡ ተሟልቶ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻው ፡ መሻሻሉን ፡ በግርጌው ፡ ጽፎ ፡ የፊ ርማ ፡ ምልክት ፡ ያደርግበታል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፩ ። የከሳሽ ፡ ወይም ፡ የተከሳሽ ፡ ቍጥር ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሲሆን ።

ባንድ ክርክር ፡ ውስጥ የከሳሾች ወይም ፡ የተከሳሾች ፡ ብዛት ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ሲሆንና ፡ ክርክሩም ፡ ከሳሾችን ወይም ፡ ተከሳሾችን ፡ በአንድ ዓይነት ፡ መልክ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሲሆን ፡ ከሳሾቹ ፡ ወይም ከተከሳሾቹ ፡ አንዱ ፡ በጠቅላላው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ይችላል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ይግ ባኙ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ፍርዱን ፡ በማሻሻል ፡ ወይም ፡ በመለወጥ ያሻሻለው ፡ ወይም ፡ የለወጠው ፡ ወይም ፡ ያጸናው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኙን ፡ ባላቀረቡት ፡ ከሳሾች ፡ ወይም ፡ ተከሳሾች ፡ ላይም ፡ ይጸናባቸዋል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

## ክርክር ፡ እንዳይቀጥልና ፡ ፍርድ እንዳይፈጸም ፡ ስለማገድ ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፪ ። ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚሰጠው ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ።**

ይግባኝ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ ባንድ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ መቅረቡ ፡ ብቻ ፡ የተጀመረው ፡ ክርክር ፡ እንዳይቀጥል ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ። እንዲሁም ፡ ባንድ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ብይን ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ሊያግደው ፡ አይችልም ።

ስለሆነም ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ መርምሮ ፡ ለጉዳዩ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡ የክርክሩ ፡ መቀጠል ፡ እንዲቆይ ፡ ወይም ፡ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ለጊዜው ፡ እንዲታገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፫ ። በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚሰጠው ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ።**

በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ይግባኙን ፡ ለበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚያቀርብ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ እስኪሰጥለት ፡ ድረስ ፡ ፍርዱን ፡ አግዶ ፡ እንዲያቆይለት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ክርክሩ ፡ በይግባኝ ፡ ቀርቦ ፡ ከመታየቱ ፡ በፊት ፡ ፍርዱ ፡ ቢፈጸም ፡ ክርክር ፡ በተነሳበት ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የሚደርስ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ፍርድን ፡ ለማገድ ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ።**

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ እና ፡ ፫፻፴፫ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዱ ፡ ወይም ፡ ትእዛዙ ፡ የተሰጠበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ትእዛዙ ፡ ወይም ፡ ፍርዱ ፡ ለ፲፭ ቀን ፡ ብቻ ፤

እንዲታገድ ፡ ከማዘዝ ፡ አያግዱትም ። ስለሆነም ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይግባኙ ፡ ካልተሰማ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቀኑን ፡ የሚያራዝም ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ በፍርዱ ፡ ወይም ፡ በትእዛዙ ፡ መሠረት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፴፭ ። ፍርድን ፡ ለማገድ ፡ ስለሚቻልበት ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡ ምክንያት ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ መኖራቸውንና ፡ በቂ ፡ መሆናቸውን ፡ ካላረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ እስከ ፡ ፫፻፴፬ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ፍርድን ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

(ሀ) ይግባኙ ፡ ከመታየቱ ፡ በፊት ፡ ፍርዱ ፡ ቢፈጸም ፡ ፍርድ ፡ እንዲታገድለት ፡ በሚጠይቀው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የሚደርስበት ፡ መሆኑን ፤

(ለ) እንዲታገድለት ፡ አመልካቹ ፡ ማመልከቻውን ፡ ያቀረበው ፡ ጊዜ ፡ ሳያጠፋ ፡ ፍርዱ ፡ እንደተሰጠ ፡ ወዲያውኑ ፡ መሆኑን ፤

(ሐ) ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ አመልካቹ ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ማስያዙን ፡ ወይም ፡ ለሚጠየቀው ፡ ዕዳ ፡ በቂ ፡ ዋስ ፡ መስጠቱን ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ መያዣ ፡ ማስቀመጡን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደሆነ ።

(፪) የፍርድ ፡ ማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ እንዲታገድ ፡ የቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ባሉበት ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፤ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ባሉበት ፡ ነገሩ ፡ እስኪሰማ ፡ ድረስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፮ ። ፍርድን ፡ ለመፈጸም ፡ ስለሚሰጥ ፡ ዋስትና ።

ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፤ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲያቀርብለት ፤ በፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የተወሰደው ፡ ነገር ፡ እንዲመለስ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ የተወሰደውን ፡ ንብረት ፡ ለመሸፈን ፡ የሚችል ፡ ግምት ፡ ያለው ፡

መያዣ ፡ እንዲያስቀምጥ ፡ ወይም ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሚሰጠው ፡ ለማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ አፈጻጸም ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፫ ፡

## ይግባኝን ፡ ስለመቀበልና ፡ ስለመስማት ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፯ ። መልስ ፡ ሰጪ ፡ ሳይጠራ ፡ ይግባኝን ፡ ለመሠረዝ ፡ ስለሚቻልበት ፡ ሁኔታ ።**

ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ያቀረበው ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ የተመሠረተው ፡ የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲታይለት ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ምሥክሮች ፡ እንዲሰሙለት ፡ የማይጠይቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ወስኖ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ክርክር ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ የመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ የሰጠበትን ፡ የመዝገብ ፡ ግልባጭ ፡ መርምሮ ፡ ፍርዱ ፡ ጉድለት ፡ የሌለበት ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳው ፡ መልስ ፡ ሰጭውን ፡ ሳይጠራ ፡ ይግባኙን ፡ ዘግቶ ፡ አቤት ፡ ባዩን ፡ ሊያሰናብት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፴፰ ። ይግባኝ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ስለመወሰን ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ይግባኙ ፡ ያልተሠረዘ ፡ ሲሆን ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኙ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ወስኖ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያውንና ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻውን ፡ ግልባጭ ፡ ይልክለታል ። በቀን ፡ ቀጠሮው ፡ ሳይቀርብ ፡ ቢቀር ፡ ይግባኙ ፡ በሌለበት ፡ የሚሰማ ፡ መሆኑን ፡ በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ ያስታውቀዋል ።

(፪) ይግባኙን ፡ ለመስማት ፡ የሚሰጠው ፡ የቀን ፡ ቀጠሮ ፡ አወሳሰን ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ የይግባኝ ፡ ሰሚውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሥራ ፡ መጠን ፡ በአጀንዳው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የቀጠሮ ፡ ብዛት ፡

መልስ ፡ ሰጭው ፡ መከራከሪያውን ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችልበት ፡ በቂ ፡ ጊዜ ፡ የሚያገኝ ፡ መሆኑን ፡ የአድራሻውን ፡ ርቀትና ፡ ቅር በት ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በመገመት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፴፱ ።ክርክሩን ፡ የሚጀምረው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ስለመሆኑ ፡

(፩) ይግባኙን ፡ ለመስማት ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ክርክሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ያቀረበውን ፡ ይግባኝ ፡ የሚያ ገኖበትን ፡ ነገር ፡ ለማስረዳት ፡ አስቀድሞ ፡ ክርክሩን ፡ ይጀምራል።

(፪) ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኙን ፡ ወዲያውኑ ፡ ያል ሠረዘው ፡ እንደሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ላሰማው ፡ ክርክር ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ የመከላከያ ፡ መልሱን ፡ ይሰጣል ። ቀጥሎም ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ላቀረበው ፡ መከላከያ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ መልስ ፡ ለመስ ጠት ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በጽሑፍ ፡ ላቀረበው ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ መ ልስ ፡ ሰጭው ፡ የመከላከያ ፡ መልሱን ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ከማዘዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ አያግደውም ።

(፬) የመልስ ፡ ሰጭው ፡ መልስና ፡ ይግባኝ ፡ ባዩም ፡ ለዚሁ ፡ የሚሰ ጠው ፡ የመቃወሚያ ፡ መልስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መቅረብና ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፵ ። መልስ ፡ ሰጭው ፡ በይግባኙ ፡ ላይ ፡ ስለሚያሰማው ፡ ቅሬታ ።

(፩) መልስ ፡ ሰጭው ፡ በቀጥታ ፡ ይግባኝ ፡ ያላቀረበ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ተገቢውን ፡ ዳኝነት ፡ ከፍሎ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ባቀረበው ፡ የይግባኝ ፡ ክርክር ፡ በመልስ ፡ ሰጭነት ፡ ከሚያቀርበው ፡ ክርክር ፡ ጋር ፡ በፍርዱ ፡ ቅር ፡ የተሰኘበትን ፡ ጉዳይ ፡ በማቅረብ ፡ በይግ ባኝ ፡ ባይነትም ፡ ለመከራከር ፡ ይችላል ።

(፪) የመልስ ፡ ሰጭው ፡ የቅሬታ ፡ ማስሚያ ፡ አቤቱታ ፡ በይግባኝ ፡ ማስሚያ ፡ ማመልከቻ ፡ ፎርም ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፰ ፡ (፩) ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ለመልስ ፡ ሰጭው ፡ ወይም ፡ ለጠበቃው ፡ የመጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡

ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) መልስ ፡ ሰጭው ፡ ያቀረበው ፡ የቅሬታ ፡ ማስሚያ ፡ አቤቱታ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከተው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ለጠበቃው ፡ የደረሰው ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የጽሑፍ ፡ መተማመኛ ፡ ከአቤቱታው ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካላቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻው ፡ በአቤት ፡ ባዩ ፡ ኪሣራ ፡ ተገልብጦ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከተው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ለጠበቃው ፡ እንዲደር ሰው ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፬) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የቅሬታ ፡ ማስሚያ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ ወገኖች ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማስ ታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ ዋናው ፡ ይግባኝ ፡ ባለመወሰኑ ፡ ምክንያት ፡ ሳይታገድ ፡ በቅሬታው ፡ አቤቱታ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይች ላል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፩ ። ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ የቀረበለትን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚመልስበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ የወሰነው ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ሳይገባ ፡ በመ ጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የቀረበለትን ፡ መቃወሚያ ፡ ብቻ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሲሆንና ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተለወጠ ፡ እንደሆነ ፡ ክርክሩ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲመለስ ፡ በማድረግ ፡ መታየት ፡ የሚገባቸውን ፡ ነጥቦች ፡ ለይቶ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ ወስኖ ፡ ለመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚመለስበት ፡ ጊዜ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭና ፡ ትእዛዙ ፡ ለመጀ መሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲላክ ፡ ያደርጋል ፡ በትእ

BACK



ዛዙም ፡ ላይ ፡ ነገሩ ፡ በቀድሞው ፡ መዝገብና ፡ ቀድሞ ፡ በተሰ ጠው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ተመዝግቦ ፡ እንዲታይ ፡ ይወሰናል ።

(፫) ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ጉዳይ ፡ ለወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ በመጀመ ሪያ ፡ ደረጃ ፡ የተሰማው ፡ ማስረጃ ፡ ሁሉ ፡ እንደተገቢነቱ ፡ እንደ ገና ፡ እንዲታይ ፡ በተደረገው ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆ ናል ።

## ቍ ፡ ፫፻፵፪ ። በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ በሠፈረው ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ።

ይግባኝ ፡ በተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሠ ፈረው ፡ ማስረጃ ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ የነገሩን ፡ ጭብጥ ፡ በማሻሻል ፡ ወይም ፡ በመ ለወጥ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ። ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዱን ፡ የሰ ጠው ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፤ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ በተረዳው ፡ መሠረት ፡ ጭብጡን ፡ ለውጦ ፡ ከመፍረድ ፡ አይታገድም ።

## ቍ ፡ ፫፻፵፫ ። ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የነገሩን ፡ ጭብጥ ፡ አስተካ ክሎ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚመልስበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ የወሰነው ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለክሱ ፡ ውጤት ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ጭብጥ ፡ ሳይይዝ ፡ መቅረቱን ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የነገሩን ፡ ነጥብ ፡ ወይም ፡ ፍሬ ፡ ጉዳዩን ፡ ሳይመረምርና ፡ ሳይረዳ ፡ ያለፈው ፡ መሆ ኑን ፤ እነዚህም ፡ ነጥቦች ፡ ለፍርዱ ፡ አሰጣጥ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ሊያስገኙ ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፤ የተዘለሉትን ፡ ጭብጦችና ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ለይቶ ፡ በመግለጽ ፡ እንደገና ፡ እንዲመረምርና ፡ እንዲያ ጣራው ፡ ለመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልሶ ፡ ይልክ ለታል ፤ እንዲሁም ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀበል ፡ ያዘዋል ።

(፪) ሊያጠናቅቃቸው ፡ የሚገባው ፡ ጉዳዮች ፡ ተገልጸው ፡ ነገሩን ፡

BACK



እንደገና ፡ እንዲያይ ፡ የተላከለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በትእዛዙ ፡ መሠረት ፡ ዳኝነቱን ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ የተቀበለውን ፡ ማስረጃና ፡ በጉዳዩ ፡ የወሰደውን ፡ እርምጃ ፡ እንዲሁም ፡ ለነገሩ ፡ አወሳሰን ፡ መሠረት ፡ ያደረጋቸውን ፡ ነገሮች ፡ በመግለጽ ፡ ያጣራውን ፡ ነገር ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልሶ ፡ ይልካል ። በተጨማሪ ፡ የታየው ፡ ማስረጃና ፡ የተሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የቀድሞው ፡ መዝገብ ፡ አባሪ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ውሳኔ ፡ ስለ ፡ መቃወም ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በ፪ኛው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተወሰደውን ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ የሚቃወም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የመቃወሚያ ፡ ማመልከቻውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ለመቃወሚያው ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረቢያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፭ ። ስለ ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ በይግባኝ ፡ ተከራካሪ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የማይፈቀድለት፡

(ሀ) ይግባኝ ፡ የቀረበበትን ፡ ክርክር ፡ የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቀበል ፡ ይገባው ፡ የነበረውን ፡ ማስረጃ ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀበለው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤

(ለ) ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ምስክር ፡ እንዲሰማ ፡ ያዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፳፯ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፫) ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲታይ ፡ ወይም ፡ ምስክሮች ፡ እንዲሰሙ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሰነድ ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ማስረጃ ፡

BACK



እንዲቀርብ ፡ ያዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፪) ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረውን ፡ ትእዛዝ ፡ በሚልክበት ፡ ጊዜ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ የተደረገበትን ፡ ምክንያት ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ገልጾ ፡ ማስፈር ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፵፯ ። የተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ አቀባበል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።**

ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያዘዘ ፡ እንደሆነ ፡ የማስረጃው ፡ አቀባበል ፡ ሥርዓት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያደርጋል ።

(ሀ) አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ማስረጃ ፡ ራሱ ፡ በመቀበል ፡ ወይም ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ የወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀበል ፡ በማዘዝ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስረጃውን ፡ ተቀብሎ ፡ እንዲልክለት ፡ ትእዛዝ ፡ በማስተላለፍ ፡

(ለ) የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀበለውን ፡ የማስረጃ ፡ ዓይነትና ፡ ወሰን ፡ በመለየት ፡ ማስረጃ ፡ የሚሰማባቸውን ፡ ነጥቦች ፡ በዝርዝር ፡ ገልጾ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ።-

**ቍ ፡ ፫፻፵፰ ። የፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥርዓት ።**

ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የይግባኝ ፡ ባዩንና ፡ የመልስ ፡ ሰጭውን ፡ ወይም ፡ የጠበቆቻቸውን ፡ ክርክር ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበትን ፡ ፍርድ ፡ የወሰነውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ እንዳስፈላጊነቱ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ የራሱን ፡ መዝገብ ፡ ብቻ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፵፱ ። ስለ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ።**

(፩) ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማናቸውም ፡ ይግባኝ ፡ የቀረበበትን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሳኔ ፡ ለማጽናት ፡ ለማሻሻል ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፪) ይግባኝ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በይግባኝ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ በሚይዘው ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ የተስማሙ ፡ መሆናቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ ያቀረቡለት ፡ እንደሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሣኔውን ፡ ወይም ፡ ትእዛዙን ፡

BACK



የሚሰጠው ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በተስማሙበት ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፱ ።የተወሰደ ፡ ነገር ፡ ለማስመለስ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ።

(፩) ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተለወጠ ፡ ወይም ፡ የተሻሻለ ፡ እንደሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ነገሩን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ላየው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲያመለክት ፡ የተሻሻለው ፡ ወይም ፡ የተለወጠው ፡ ፍርድ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ክርክር ፡ የተነሣበትን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ሁኔታ ፡ ለመመለስ ፡ እንዲችል ፡ በመጀመሪያው ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ የተወሰደው ፡ ንብረት ፡ ወይም ገንዘብ ፡ ለባለመብቱ ፡ እንዲመለስ ፡ ወይም ፡ የተከራካሪዎቹ ወገኖች ፡ መብት ፡ በይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ እንዲስተከል ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት አለበት ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ መሠረት ፡ ለማስፈጸም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ የተወሰደ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስ ፤ ወለድ ፡ እንዲከፈል ፤ ኪሣራ ፡ እንዲወሰን ፤ ካሣና ፡ ያለአገባብ ፡ የተወሰደ ፡ ጥቅም ፡ እንዲከፈል ፡ ወይም ፡ በፍርዱ መሻሻል ፡ ወይም ፡ መለወጥ ፡ ምክንያት ፡ የተከራካሪዎቹን ፡ ወገኖች ፡ መብት ፡ ለማስተካከል ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ ለማስመለስ ፡ የሚቻለውን ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ለማስተካከል ፡ የሚቻለውን ፡ መብት ፡ ለማስፈጸም ፡ ሌላ ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ መክፈት ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በሰጡት ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ስለማቅረብና ፡ ውሣኔውን ፡ ስለማስረዝ ።

ቍ ፡ ፫፻፶ ።ስለ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖችና ፡ ስለ ፡ አፈጻጸሙ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

(፩) በማናቸውም ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ኝነት ፡ ላይ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በዚህ ፡

BACK



ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፶፩ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ወይም ፡ ስለ ግልግሉ ፡ ጉዳይ ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ጉባዔ ፡ አባሎች ፡ በሰጡት ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ይች ላል ።

(፪) ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ የይግባኝ ፡ ማቅረብ ፡ መብ ቱን ፡ አውቆ ፡ ለመተው ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የነገሩን ፡ አካ ባቢ ፡ ሁኔታ ፡ በሙሉ ፡ ባለመረዳትና ፡ ባለማወቅ ፡ ይግባኙን ፡ የተወም ፡ ቢሆን ፡ ጉዳዩን ፡ በተረዳው ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ከማቅ ረብ ፡ አይከለከልም ።

(፫) በፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጡ ፡ ፍርዶች ፡ ወይም ፡ ውሣኔዎች ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተደነገገው ፡ የይግባኝ ፡ አቀራረብ ፡ ደንብ ፡ በግልግል ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ብይን ፡ ይግባኝ ፡ አቀራረብ ፡ ጉዳይም ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆ ናል ።

(፬) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፴፯ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ጉባዔ ፡ በሚሰጠው ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፩ ። ይግባኝ ፡ ስለሚባልባቸው ፡ ምክንያቶች ።

በግልግል ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ማቅረብ ፡ የሚፈቀደው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተነገሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ሲያጋጥሙ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(ሀ) ብይኑ ፡ የተለያየ ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ የማይገናኝ ፡ ወይም ፡ የማይስማማ ፡ ወይም ፡ ግልጽ ፡ ያል ሆነ ፡ ወይም ፡ የሚያጠራጥር ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ በሕግና ፡ በፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ረገድ ፡ የተሳሳተ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ጉባዔ ፡ አባል ፡ እንዲ ወሰን ፡ የቀረበለትን ፡ ጉዳይ ፡ ሳይወስን ፡ ሲቀር ፤

(ሐ) ክርክሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፤ በተለይም ፡

(፩) ጉዳዩ ፡ የሚሰማበት ፡ ቀንና ፡ ሥፍራ ፡ ከተከራካሪዎች ፡ ወገ ኖች ፡ ላንደኛው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ለሁሉም ፡ ሳይገለጽ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እንዲታይላቸው ፡ ተስማምተው ፡ ያቀረቡት ፡ ማስረጃ ፡ ሳይታይ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ።

(፪) በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ተገቢነት ፡ ያለውን ፡ ማስረጃ ፡ ሳይቀበል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በሌሉበት ፡ ወይም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሳይቀርብ ፡ ምስክር ፡ የሰማ ፡ እንደ ሆነ ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ የተቀበለ ፡ እንደሆነ ።

(መ) የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ሊፈጽም ፡ የማይገባ ውን ፡ የአድላዊነትንና ፡ የመጥፎ ፡ ባሕሪይን ፡ ጠባይ ፡ ያሳየ ፡ እንደሆነ ፡ በተለይም ፡

(፩) አንዱ ፡ ወገን ፡ ያቀረበለትን ፡ ሃሣብ ፡ ሰምቶ ፡ ሌላውን ፡ ወገን ፡ ሳይሰማ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤

(፪) መደለያ ፡ በመቀበል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ምክን ያት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ዝንባሌ ፡ ያደረበት ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፤

(፫) ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ በሆነው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ መብት ፡ ያገኘበት ፡ ወይም ፡ የሚ ያገኝበት ፡ መሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ።

ቍ ፡ ፫፻፶፪ ። ይግባኙ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

በግልግል ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጉባዔ ፡ ታይቶ ፡ በተወ ሰነ ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ነገር ፡ የሚቀርበው ፡ ተገቢው ፡ ዳኝነት ፡ ከተከፈለበት ፡ በኋላ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ነገር ፡ በግልግል ፡ ባይታይ ፡ ኖሮ ፡ ክርክሩን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ለመቀበል ፡ የበላይ ፡ ለሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፶፫ ። ስለ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ።

ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብይኑን ፡ ለማጽደቅ ፡ ለመ ለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሰረዝ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ እንደተጠበቀ

ሆኖ ፡ የግልግሉ ፡ ወይም ፡ የሽምግልናው ፡ ጉባዔ ፡ ብይን ፡ እንደ ገና ፡ እንዲታይ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሊመልሰው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፩ ። ብይኑ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ ስለመመለስ ።

(፩) ይግባኙ ፡ የቀረበው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፶፩ ፡ (ሀ) እና ፡ (ለ) በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ጉባዔ ፡ ዳኞች ፡ እንደገና ፡ እንዲያዩት ፡ ተመልሶ ፡ አይላክም ።

(፪) ነገሩ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ የመለሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ነገሩን ፡ እንደገና ፡ እንዲያዩ ፡ ከተመለሰላቸው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በሶስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ውሣኔ ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ።

(፫) ጉዳዩ ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ የተመለሰው ፡ በከፊል ፡ ብቻ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በከፊል ፡ የጸናውን ፡ ውሣኔ ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ የተደረገውን ፡ ጉዳይ ፡ ውሣኔ ፡ ሳይጠብቅ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፫ ። ብይኑን ፡ ስለመሻር ።

(፩) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በሚሰጡት ፡ ውሣኔ ፡ እንስማማለን ፡ ሲሉ ፡ ግዴታ ፡ የገቡ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፶፮ ፡ የተመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረትና ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ብይኑ ፡ እንዲሻርላቸው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ከማመልከት ፡ አይታገዱም ።

(፪) ማመልከቻው ፡ የሚቀርበው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፶፪ ለተመለከተው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ብይኑ ፡ በተሰጠ ፡ በ፴ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ ፡ መቃወሚያን ፡ ስለማቅረብ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ስለተመለከተው ፡ ማመልከቻ ፡ አቀራረብ ፡ ጉዳይም ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፮ ። ለማመልከቻው ፡ አቀራረብ ፡ መሠረት ፡ ስለሚሆኑ ፡ ነገሮች ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፶፭ የተነገረውን ፡ ማመልከቻ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

(ሀ) የግልግል ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የተስማሙበት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የማይጸና ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ግዴታ ፡ በመከተል ፡ ወይም ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ያላቀረቡትንና ፡ ያልተከራከሩበትን ፡ ጉዳይ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ብይን ፡ የሰጡ ፡ እንደሆነ ፡

(ለ) የግልግሉ ፡ ወይም ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ቍጥራቸው ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ነገሩን ፡ የወሰኑት ፡ ለየብቻቸው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡

(ሐ) ከግልግል ፡ ወይም ፡ ከሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ አባሎች ፡ አንዱ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ለነገሩ ፡ እንግዳ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለቀሩት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወይም ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ላንደኛው ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ።

ቍ ፡ ፫፻፶፯ ። በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሚሰጥ ፡ ውሣኔ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፫፻፶፭ ፡ መሠረት ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣ ፡ እንደሆነ ፡ ብይኑ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በመቆጠር ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) ማመልከቻው ፡ ተቀባይነትን ፡ አግኝቶ ፡ ውሣኔ ፡ የተሰጠው ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ጉዳዩ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ተቆጥሮ ፡ ይሠረዛል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ መቃወም ።

ቍ ፡ ፫፻፶፰ ። መቃወሚያን ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚችሉ ፡ ወገኖች ።

ባክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ ወይም ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ የሚችልና ፡ እንዲሁም ፡ ተካፋይ ፡ ባልሆነበት ፡ ክርክር ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ መብቱን ፡ የሚነካበት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ጠበቃው ፡ ወይም ፡

ነገረ ፡ ፈጁ ፡ ተካፋይ ፡ ባልሆነበት ፡ ክርክር ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ መቃወሚያውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፱ ። መቃወሚያው ፡ የሚቀርብበት ፡ ፎርም ።** See Art 376 for [illegible]

(፩) መቃወሚያው ፡ የሚቀርበው ፡ በአቤቱታ ፡ አቀራረብ ፡ መልክ ፡ ሆኖ ፡ ተገቢው ፡ ዳኝነት ፡ ተከፍሎበት ፡ መቃወሚያ ፡ የቀረበበትን ፡ ነገር ፡ ለወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) የመቃወሚያው ፡ ማመልከቻም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ በዝርዝር ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(ሀ) ማመልከቻው ፡ የሚቀርብበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ለ) የአቤት ፡ ባዩን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ሐ) መቃወሚያ ፡ በቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ተከራካሪ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(መ) ለመቃወሚያው ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ ዝርዝር ፡ ምክንያቶች ፤

(ሠ) አቤት ፡ ባዩ ፡ የሚጠይቀውን ፡ የዳኝነት ፡ ዓይነት ፤

(፫) በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ጽሑፍ ፡ ተያይዞ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ፤

(፬) እንዲሁም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከማመልከቻው ፡ ጋር ፡ መቃወሚያ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚጠይቅ ፡ ጽሑፍ ፡ ተያይዞ ፡ በአባሪነት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፷ ። መቃወም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የመቃወም ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ቀጥሮ ፡ ወስኖ ፡ መቃወሚያ ፡ በቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተከራካሪ ፡ ለነበሩት ፡ ወገኖች ፡ የመቃወሚያው ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭና ፡ ጥሪው ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ያዛል ።

(፪) የመቃወሚያው ፡ ክርክር ፡ የሚሰማው ፡ የመጀመሪያው ፡ ክርክር ፡ በተሰማበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ ካጣራ ፡ በኋላ ፡ መቃወሚያ ፡ የቀረበበትን ፡ ፍርድ ፡ ለማጽደቅ ፡ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሠረዝ ፡ ይችላል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፬ ፡

## ፍርድን ፡ ስለማጣራት ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፩ ፡- ፍርድ ፡ እንዲጣራ ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፤**

(፩) ፍርድ ፡ እንዲጣራ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፡ የሚቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ የመጨረሻው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰ ጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ወይም ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ የይግባኝ ፡ መብቱን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቅርቦ ፡ ውሣኔ ፡ ካገኘ በት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤ ከአቤቱ ታው ፡ ጋር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ነገሮች ፡ በአባሪነት ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

(ሀ) አቤት ፡ ባዩ ፡ ቅር ፡ የተሰኘበትን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ የፍር ዶች ፡ ግልባጭ ፤

(ለ) ፍርዱ ፡ እንደገና ፡ ታይቶ ፡ መጣራት ፡ ይገባዋል ፡ የሚባ ልበትን ፡ ምክንያት ፡ በዝርዝር ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፤

(፪) ማመልከቻው ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፡ እንዲታይ ፡ የተፈቀደ ፡ ሲሆን፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ፍርዱ ፡ እንደገና ፡ መጣራት ፡ አይገባውም ፡ የሚልበትን ፡ ምክንያት ፡ እንዲገልጽ ፡ ግልባጩ ፡ ይላክለታል ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበው ፡ ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ ከጊዜ ፡ ውጭ ፡ ስለሚቀርቡ ፡ አቤ ቱታዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከ፫፻፳፬ ፡ እስከ ፡ ፫፻፳፯ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፪ ፡- ስለኪሣራና ፡ ስለወጭ ፡ የሚሰጥ ፡ ዋስትና ፤**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቤቱታውን ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ በ፲ ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(ሀ) በመልስ ፡ ሰጭው ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ በቂ ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ መስጠት ፤

(ለ) ፍርድ ፡ የተሰጠበትን ፡ መዝገብ ፡ ለማስገልበጥ ፡ ወይም ፡ ወይም ፡ ለማስመጣት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወጭ ፡ ሁሉ ፡ በተቀዳሚነት ፡ ማስቀመጥ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ መዝገቡን ፡ ራሱ ፡ አስገልብጦ ወጭውን ፡ ከፍሎ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ቍጥር ፡ በ(ለ) ፊደል ፡ የተመለከተው ፡ ለማስገልበጫ ፡ ያስያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ይመለስለታል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፫ ፡- አቤቱታውን ፡ ስለመቀበል ፤

ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ዋስትና ፡ ከተሰጠና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ለተነገረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወጭ ፡ መያዣ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ እንዲከናወን ፡ ይታዘዛል ።

(ሀ) አቤቱታው ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፤

(ለ) ይህንኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ እንዲያውቀው ፡ ማድረግ ፤

(ሐ) ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ተገቢውን ፡ የማስገልበጫና ፡ የማሳተሚያ ፡ ወጭ ፡ በመክፈል ፡ ከክርክሩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ የማስረጃዎችና ፡ የጽሑፍ ፡ ግልባጮች ፡ እንዲሰጡት ፡ ማድረግ ።

ቍ ፡ ፫፻፷፬ ፡- ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ መስጠት ፤

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፷፩ ፡ /፪/ እና ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፷፫ ፡ የተገለጹትን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የፍርዱን ፡ ውሣኔ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በሚታይ ፡ ሥፍራ ፡ በመለጠፍና ፡ በጋዜጣ ፡ ማስታወቂያ፡ በማውጣት ፡ የማስታወቁን ፡ ሥርዓት ፡ ለመፈጸም ፡ ይቻላል ።

(፪) ለተከራካሪዎቹ ፡ ወይም ፡ ለመልስ ፡ ሰጭዎቹ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለመስጠት ፡ ሥርዓት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ክርክሩ ፡ በመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበበት ፡ ወይም ፡ በሚቀጥልበት ፡ ወይም ፡ የመጨረሻው ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ እስከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ ያልተከራ

BACK



ከረ ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ነገሩ ፡ ለችሎት ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ ማስታወቂያው ፡ ለን ብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ወይም ፡ ለወራሾቹ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ይደ ረጋል ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፭ ።ስለ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ወጭ ፡ መያዣ ፡ የሚሰጥ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ።**

(፩) አቤቱታው ፡ ተቀባይነትን ፡ ከማግኘቱ ፡ በፊት ፡ በማናቸውም፡ ጊዜ ፡ ለችሎቱ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፷፪ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ስለወጭ ፡ መያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመሻር ፡ ወይ ም፡ በመለወጥ ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) አቤቱታው ፡ ተቀባይነትን ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፤ በቍጥር ፡ ፫፻፷፪ ፡ ንዑስ ፡ /፩/ /ሀ/ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ /፩/-/ለ/ መሠረት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ወጭ ፡ ተቀማጭ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ የማይበቃ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፤ ችሎቱ ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ዋስትናውን ፡ ወይም ፡ ወጭውን ፡ በተጨማሪ ፡ እንዲሰጥ ፡ ወይም ፡ ተፈላጊ ውን ፡ ገንዘብ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲያስይዝ ፡ ሊያዘው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፮ ፡- በትእዛዙ ፡ መሠረት ፡ ስላለመፈጸም ፤**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የታዘ ዘውን ፤ አቤት ፡ ባዩ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበ በት ፡ ፍርድ ፡ ከመፈጸሙ ፡ ሳይታገድ ፡ የአቤቱታው ፡ መሰማት ፡ ሥርዓት ፡ ይቋረጣል ።

(፪) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፷፫ ፡ የተነገረውን ፡ ድንጋጌ ፡ አይመለከትም ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፯ ፡- አቤቱታው ፡ እስከሚሰማ ፡ ድረስ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፤**

(፩) አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታገድ ፡ በግልጽና ፡ በቀጥታ ፡ ካልታዘዘ ፡ በቀር ፡ አቤቱታው ፡ በችሎት ፡ እንዲታይ ፡ ተቀባይነትን ፡ ማግኘቱ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ የፍርዱን ፡ መፈጸም ፡ አያግደውም ።

(፪) ችሎቱ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ በራሱ ፡ አስተያ የት ፡ ወይም ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለ

BACK



ከተውን ፡ ይፈጽማል ።

(ሀ) ክርክር ፡ የተነሣበት ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲከበር ፡ ያዛል ፤

(ለ) ችሎቱ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ አፈጻጸም ፡ የተረጋገጠ ፡ ውጤት ፡ እንዲያገኝ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ሰጥቶ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲፈጽምለት ፡ ያዛል ፤ ወይም ፤

(ሐ) አቤት ፡ ባዩ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲታገድለት ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነ ችሎቱ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ አፈጻጸም ፡ የተረጋገጠ ፡ ውጤት ፡ እንዲያገኝ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ሰጥቶ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ከመፈጸሙ ፡ እንዲታገድለት ፡ ያዛል ፤ ወይም ፡

(መ) አቤት ፡ ባዩ ፡ የችሎቱ ፡ እርዳታ ፡ እንዲደረግለት ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነ ፡ ክርክር ፡ የተነሣበትን ፡ ንብረት ፤ በአደራ ፡ ጠባቂነት ፡ ወይም ፡ በአስተዳዳሪነት ፡ ራሱ ፡ ተረክቦ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እን ዲሾሙለት ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጥለታል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፯ ። ተጨማሪ ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለማድረግ ፤

(፩) አቤቱታው ፡ በሚሰማበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፤ ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ የሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ በቂ ፡ ያለመሆኑ ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነ ፡ ተጨማሪ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ይታዘዛል ።

(፪) የታዘዘው ፡ ተጨማሪ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ ይፈጸማል ።

(ሀ) የመጀመሪያውን ፡ ዋስትና ፡ የሰጠው ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ሲሆንና ፡ መልስ ፡ ሰጭውም ፡ ስለ ፡ ተጨማሪው ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ያለመፈጸሙን ፡ ያመለከተ ፡ እንደሆነ ፡ የመጀመሪያው ፡ ዋስትና ፡ እንዳልተሰጠ ፡ ተቆጥሮ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ይታዘዛል ።

(ለ) የመጀመሪያው ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠው ፡ በመልስ ፡ ሰጭው

BACK



የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲቋረጥ ፡ አድርጐ ፡ ሁለቱም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ የመጀመሪያው ፡ ዋስትና ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመለሱ ፡ በማዘዝ ፡ ክርክር ፡ ስለተነሳበትም ፡ ጉዳይ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፱ ።የችሎቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፡

ችሎቱ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ በችሎት ፡ የሚሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ነገሩ ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ለሞተ ፡ ለማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ለመልስ ፡ ሰጭ ፡ ለንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ ለወራሾቹ ፡ ማስታወቂያ ፡ ባለመስጠቱ ፡ ምክንያት ፡ ተፈጻሚነትን ፡ አያጣም። ስለሆነም ፡ ማስታወቂያ ፡ ያልተሰጠው ፡ ወገን ፡ ቀርቦ ፡ እንደተሟገተ ፡ ተቆጥሮ ፡ በችሎት ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ የሚጸናበት ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ ክርክሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ ፍርድ ፡ ከተሰሰጠ ፡ በኋላ ፡ በፍርዱ ፡ ውሣኔ ፡ ምክንያት ፡ በተወሰደው ፡ እርምጃ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ ያልተከራከረ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ቍ ፡፫፻፵ ፡-ስለ ፡ ማስፈጸም ፡

(፩) በችሎት ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚፈልግ ፡ ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ ወይም፡ እንደትእዛዙ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ከሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ በማሕተም ፡ የተረጋገጠ ፡ የፍርድ ፡ ወይም ፡ የትእዛዝ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፡ አያይዞ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበትን ፡ ፍርድ ፡ በመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ለወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የቀረበለትን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ፈረደው ፡ ወይም ፡ እንዳዘዘው ፡ አድርጐ ፡ ማስፈጸም ፡ አለበት ።

(፫) ፍርዱን ፡ የሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ችሎት ፡ በፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ጉዳይ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ በፍ

BACK



ርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ሌሎቹ ፡ ትእዛዞች ፡ ይግባኝ ፡ እንደሚባልባቸው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ አፈጻጸሙ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ የማለት ፡ መብት ፡ እንደተጠበቀ ፡ ነው ።

# ሰባተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፤

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ፤

## በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የተሰጡትን ፡ ፍርዶች ፡ ስለማስፈጸም ፤

### ክ ፍ ል ፡ ፩ ፡

### ፍርድን ፡ ስለሚያስፈጽሙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፤

**ቍ ፡ ፫፻፸፩ ፡- መሠረቱ ፤**

(፩) በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ፍርድን ፡ የሚያስፈጽመው ፤ ፍርዱን ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌ ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ መርከብን ፡ ስለመያዝ ፤ ስለ ፡ ማሰርና ፡ ስለመሸጥ ፡ የተነገረውን ፡ ድንጋጌ ፡ አይመለከትም ።

**ቍ ፡ ፫፻፸፪ ፡- ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ ስለማስተላለፍ ፤**

(፩) የፍርዱን ፡ ውሣኔ ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ የተፈረደለት ፡ ወገን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፸፰ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብ ፤ ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽሙ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ለተመለከቱት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ትእዛዝ ፡ ያስተላልፋል ።

(ሀ) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሥራውን ፡ በሚያካሒድበት ፤

ንግድ ፡ በሚነግድበት ፤ ለጥቅሙ ፡ በሚሠራበት ፡ ወይም ፡ በሚኖርበት ፡ ቦታ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ለ) የፍርዱን ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ የፍርድ ፡ ባለ ፡ ዕዳው ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነበትን ፡ ዕዳ ፡ ለመሸፈን ፡ የሚችል ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

(ሐ) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለማስረከብ ፡ ወይም ፡ በሐራጅ ፡ ስለ ፡ መሸጥ ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ሲሆን ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ሥልጣን ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ወይም ፡

(መ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ በታየውና ፡ በሚመዘግበው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ለመረጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ የፍርዱን ፡ ውሣኔ ፡ የሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሥልጣኑ ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፤ ወይም ፡ በሐራጅ ፡ ተሸጦ ፡ ለፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ እንዲከፈል ፡ ራሱ ፡ ከማዘዝ ፡ አያግደውም ።

## ፫፻፹፫ ። የፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ በሚተላለፍበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤

(፩) እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ የሚያስተላልፈው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ጋር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ አያይዞ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

(ሀ) የፍርዱን ፡ ወይም ፡ የውሣኔውን ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፤

(ለ) የፍርዱ ፡ ውሣኔ ፡ በተሰጠበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ፍርዱ ፡ ያልተፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የምስክርነት ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ፍርዱ ፡ በከፊል ፡ ተፈጽሞ ፡ እንደሆነ ፡ የተፈጸመው ፡ ክፍል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነና ፡ ያልተፈጸመው ፡ ቀሪ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ለይቶ ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፤

(ሐ) ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ የተሰጠ ፡ ልዩ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳለ ፡ የዚሁኑ ፡ መግለጫ ፤ እንደሌለ ፡ ደግሞ ፡ ያለመኖሩን ፡ የሚገልጽ ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃ ፤

(፪) እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተላኩለትን ፡ ጽሑፎች ፡ በአንድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ ፍርዱ ፡ ትክክለኛነት ፡ ወይም ፡ በግልባጮች ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሠፈረው ፡ ነገር ፡ ሌላ ፡ መግለጫና ፡ ማብራሪያ ፡ ሳይ ጠይቅ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ማስፈጸም ፡ አለበት ። ስለሆነም ፡ የፍርዱን ፡ ወይም ፡ የትእዛዙን ፡ ወይም ፡ የግልባጩን ፡ ትክክለኛነት ፡ የሚያጠራጥር ፡ ልዩና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያጋጠ ጠመው ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ መዝግቦ ፡ ማረጋገጫ ፡ የሚሆን ፡ ማስረጃ ፡ እንዲላክለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

__ቍ ፡ ፫፻፸፩ ። ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላ ለው ፡ ሥልጣን ።__

(፩) ፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚሰጠው ፡ ትእዛዝና ፡ በትእዛዙም ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ስለሚባል በት ፡ ሁኔታ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ዋናውን ፡ ፍርድ ፡ ከወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

(፪) የማስፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ በትእ ዛዙ ፡ መሠረት ፡ ፈጽሞ ፡ እንደሆነ ፡ ማስፈጸሙን ፤ ፍርዱን ፡ ለማ ስፈጸም ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ደግሞ ፡ ያላስፈጸመበትን ፡ ምክ ንያትና ፡ መሰናክል ፡ ሊሆኑ ፡ የቻሉልን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎች ፡ በዝርዝር ፡ በመግለጽ ፡ ለአዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

__ቍ ፡ ፫፻፸፪ ። ፍርዱን ፡ በሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚወሰኑ ፡ ነገሮች ።__

(፩) ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚነሳውን ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ በፍ ርድ ፡ የተወሰነው ፡ ዕዳ ፡ በሚገባ ፡ ተከፍሏል ፤ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ባለዕዳነት ፡ ነፃ ፡ ሆኛለሁ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳነቱን ፡ ግዴታ ፡ ፈጽሜአለሁ ፡ በማለት ፡ በባለ ፡ ጉዳዮች ፡ መካከል ፡ ለሚ ነሳው ፡ ክርክር ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ መክፈት ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸሙ ፡ መዝ ገብ ፡ ላይ ፡ ሊወሰነው ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፤ ከተከ

ራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ያንደኛው ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ነው ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ የሚነሳውን ፡ ክርክር ፡ የሚ ወሰነው ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፸፯ ። የፍርድን ፡ አፈጻጸም ፡ ስለ ፡ ማገድ ።

(፩) ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ባቀረበው ፡ ምክንያት ፡ ላይ ፤ አቤቱታውን ፤ ለፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመስማት ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ለሚገመት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ፍርዱን ፡ ሊያግድለት ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ፍርዱ ፡ እንዲታገድለት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ውሳኔው ፡ አፈጻጸም ፡ ጉዳይ ፡ ለፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲያመለክት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱን ፡ እንደሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ነገሩን ፡ ይመለከት ለታል ።

(፪) በፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ታሥሮ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ ተይዞበት ፡ እንደሆነ ፡ ለቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡ የታሠረው ፡ እንዲፈታ ፡ ወይም ፡ የተያዘው ፡ ንብረት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥለት ፡ ይችላል ፤ ስለሆነም ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እንደ ገና ፡ እንዲታሠር ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲያዝ ፡ ማድ ረግን ፡ አያግድም ። ወይም ፡ ንብረቱ ፡ እንዲለቀቅለት ፡ ከማድ ረጉ ፡ በፊት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ ዕዳውን ፡ ለመሸፈን ፡ የሚችል ፡ መያዣ ፡ እንዲ ሰጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) ፍርዱን ፡ የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ የሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ በፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘን ድም ፡ የሚጸና ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፫፻፸፰ ። በፍርድ ፡ ባለ ፡ ገንዘቡ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ውሣኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ስለሚሰጥ ፡ የፍርድ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ።

ፍርድ ፡ በተፈረደለት ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡

BACK



የተፈረደበት ፡ ወገን ፡ ክስ ፡ ያቀረበበት ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የገመተውን ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ ወይም ፡ መያዣ ፡ እንዲሰጥ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ለክርክሩ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪ ፡ ሰጠው ፡ ድረስ ፡ ፍርዱ ፡ ከመፈጸሙ ፡ ታግዶ ፡ እንዲቆይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

## ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻና ፡ ስለ ፡ አፈጻጸሙ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

### ቍ ፡ ፫፻፸፰ ። ፍርድን ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ስለሚይዛቸው ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ።

(፩) ፍርድ ፡ የተፈረደለት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ፍርዱን ፡ ለፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ማመልከቻው ፡ ፍርዱ ፡ እንደ ፡ ተፈረደ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የተፈረደበት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቃደኛ ፡ ሆኖ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘ ፡ ሲሆን ፡ ማመልከቻው ፡ የሚቀርበው ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ በተሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

(፫) ማመልከቻው ፡ እንደማናቸውም ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ተፈርሞበትና ፡ ትክክለኛነቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ ይቀርባል ፤ በተጨማሪም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ መያዝ ፡ አለበት ።

(ሀ) የክሱን ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፤

(ለ) የተከራካሪዎቹን ፡ ወገኖች ፡ ሥም ፤

(ሐ) ውሣኔው ፡ ወይም ፡ ፍርዱ ፡ የተሰጠበትን ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፤

(መ) በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ተብሎበት ፡ እንደሆነ ፡ የዚህኑ ፡ መግለጫ ፤

(ሠ) ፍርዱ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ በተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ በፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የተፈጸመ ፡ ክፍያ ፡ ወይም

የተደረገ ፡ መቻቻል ፡ እንዳለ ፡ ይህንኑ ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፤

(ረ) ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሌላ ፡ ማመልከቻ ፡ ቀርቦ ፡ እንደሆነ ፡ የቀረበበትን ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ያስገኘውን ፡ ውጤት ፡ ወይም ፡ የተሰጠውን ፡ ውሣኔ ፤

(ሰ) በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ የሚጠየቀውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከነ ፡ ወለዱ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዳኝነት ፤ እንዲሁም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ላይ ፡ ባስፈረደው ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ ስለተደረገ ፡ መቻቻልና ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ስለተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ።

(ቀ) ኪሣራ ፡ ተወስኖ ፡ እንደሆነ ፡ ልኩን ፤

(በ) ፍርዱን ፡ እንዲፈጽም ፡ ተጠያቂ ፡ የሚሆነውን ፡ ወገን ፤

(ተ) የፍርድ ቤቱ እርዳታ ፡ የሚጠየቅበትን ፡ ሁኔታ ፡ በተለይም ፤

(፩) በፍርድ ፡ የታዘዘውን ፡ ንብረት ፡ እንዲረከብ ፡ ወይም ፡ ይዞታው ፡ እንዲለቀቅለት ፡ መሆኑን ፤

(፪) ማናቸውም ፡ ንብረት ፡ ተከብሮ ፡ ወይም ፡ ሳይከበር ፡ እንዲሸጥ ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡

(፫) የንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ ተረካቢ ፡ እንዲሾም ፡ የሚጠይቅ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፤ ወይም ፡

(፬) ፍርዱን ፡ ለማስፈጸም ፡ ምቹና ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ዘዴ ፡ መግለጽ ።

## ቍ ፡ ፫፻፸፱ ። ንብረት ፡ እንዲከበር ፡ በሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ነገሮች ።

(፩) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ እንዲከበር ፡ ከሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ የሚከበረውን ፡ ዕቃ ፡ ዝርዝርና ፡ ዓይነትነቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ተያይዞ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ የፍር ድ ፡ ባለዕዳው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ በሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ነገሮች ፡ መገለጽ ፡ አለባቸው ።

(ሀ) በቍጥር ፡ ፪፻፳፭ ፡ /፪/ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፤ ይህም ፡ ሲሆን ፡

ንብረቱ ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተመ ዝግቦ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመዝገቡ ፡ ግልባጭ ፡ እንዲላክ ለት ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(ለ) በአመልካቹ ፡ ትጋት ፡ ተፈልጎ ፡ በተገኘው ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጥቅምና ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፫፻፹ ። ከአንድ ፡ በላይ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለማስ ፈጸም ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፤

(፩) በፍርዱ ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ ተለይቶ፡ ካልታዘዘ ፡ በቀር ፤ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ለራሱና ፡ ለሌሎችም ፡ እንዲፈጸም ፡ ከፍርድ ፡ ባለገንዘቦቹ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብ ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ባለገንዘቦቹ ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ ለንብረት ፡ አስተዳዳሪው ፡ ወይም ፡ ለወራሾቹ ፡ ጥቅም ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ። ከዚህ ፡ በ ላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ተካፋይ ፡ ያልሆኑት ፡ ወገኖች ፤ ጥቅም ፡ እንዲጠበቅ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት አለበት ።

## ቍ ፡ ፫፻፹፩ ። በፍርድ ፡ የተወሰነው ፡ ጥቅም ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ስለሚ ያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፤

(፩) አንድ ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ቍጥራ ቸው ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፤ የፍ ርድ፡ ባለመብት ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ በፍርድ ፡ ያገኘውን ፡ መብቱን፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አስተላልፎ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ የተላለፈለት ፡ እንደሆነ ፤ መብቱ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ፍርዱን ፡ ለፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ንዑስ ፡ ቍጥሮች ፡ የተነገረው ፡ ድን ጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ መብቱ ፡ የተላለፈለት ፡ የሌላው ፡ሰው ፡ ፍርድ ፡ የሚፈጸመው ፡ በቀጥታ ፡ ለተፈረደለት ፡ ወገን ፡ በሚፈጸ ምበት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

BACK



(፫) ዋናው ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ በፍርድ ፡ ያገኘውን ፡ መብቱን ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደሆነ ፤ መብቱ ፡ የተላለፈለት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቱን ፡ ለዋናው ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብና ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በመግለጽ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ባለጉዳዮች ፡ የሚያቀርቡት ፡ መቃወሚያ ፡ እንዳለ ፡ አሳባቸውን ፡ ከመቀበሉ ፡ በፊት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ።

ቁ ፡ ፫፻፹፪ ። ዋስ ፡ ወይም ፡ ተያዥ ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ ስለማድረግ ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ግዴታዎች ፡ ለመፈጸም ፡ የዋስትና ፡ ወይም ፡ የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ እንደሆነ ፤

(ሀ) ፍርዱ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲፈጸም ፡

(ለ) በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የተወሰደው ፡ ዕቃ ፡ ለባለንብረቱ ፡ እንዲመለስ ፡ ወይም ፡

(ሐ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ስለውሣኔው ፡ አፈጻጸም ፡ በተወሰደው ፡ በማናቸውም ፡ እርምጃ ፡ ምክንያት ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጸም ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ በገባበት ፡ አላፊነት ፡ መጠን ፤ በቁጥር ፡ ፫፻፸፮ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የክሱ ፡ ተካፋይ ፡ እንደሆነ ፡ ተቆጥሮ ፡ ፍርዱ ፡ ይፈጸምበታል ። ስለሆነም ፡ እንደነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የገመተውን ፡ ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ቁ ፡ ፫፻፹፫ ። በንብረት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ወይም ፡ በወራሾች ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡

የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ፍርዱን ፡ በሙሉ ፡ ሳይፈጽም ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፤ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በሟቹ ፡ ንብረት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ በወራሾቹ ፡ ላይ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ።

ቁ ፡ ፫፻፹፬ ። የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ በይርጋ ፡ ስለሚታገድበት ፡ ሁኔታ ።

አንድ ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ እንዳይፈጸም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚሰጠው ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ማመል

BACK



ከቻ ፡ ቀርቦ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ከቆየና ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ማመልከቻ ፡ በማቅረብ ፡ ነገሩን ፡ ለማንቀሳቀስና ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለመጠየቅ ፡ አይቻልም ። የጊዜውም ፡ መነሻ ፡ የሚታሰበው ፤

(ሀ) እንዲፈጸም ፡ የሚጠየቀው ፡ ነገር ፡ በፍርድ ፡ ከተወሰነበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጀምሮ ፤

(ለ) በፍርዱ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ተከታታይ ፡ ትእዛዝ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ ወይም ፡ ዕቃ ፡ እንዲመለስ ፡ የሚያዝ ሲሆንና ፡ ገንዘቡ ፡ የሚከፈልበት ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ የሚመለስበት ፡ ጊዜ ፡ ተለይቶ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፤ ተለይተው ፡ በተመደቡ፡ ጊዜያቶች ፡ ውስጥ ፡ በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የሚመለስ ፡ ዕቃ ፡ ሲሆን ፤ በአፈጻጸሙ ፡ ትእዛዝን ፡ እንደተወሰነው ፡ የገንዘቡ ፡ መከፈል ፡ ወይም ፡ የዕቃው ፡ መመለስ ፡ ካቋረጠበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጀምሮ ።

ቊ ፡ ፫፻፹፭ ። ለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ማመልከቻ ፤ የውሣኔ ፡ አሰጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

(፩) ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚህ ፡ በላይ፡ ባሉት ፡ ቊጥሮች ፡ የተነገሩትን ግዴታዎችና ፡ ሥርዓቶች ፡ አሟልቶ ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ። በደንቡ ፡ መሠረት ፡ ያልተሟላ ፡ ወይም ፡ ጉድለት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ተቀባይነት ፡ እንደሌለው ፡ አስረድቶ ፡ ለባለጉዳዩ ፡ ይመልስለታል ፤ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው፡ ሁኔታና ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተሟልቶ ፡ እንዲቀርብ ፡ያዛል።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንውስ ፡ ቊጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ተሻሽሎና ፡ ተሟልቶ ፡ እንደገና ፡ የቀረበ ፡ ማመልከቻ ፡ መጀመሪያ ፡ ቀርቦ ፡ በነበረበት ፡ ቀን ፡ ሕጋዊ ፡ ተቀባይነትን ፡ እንዳገኘ ፡ ይቆጠራል ።

(፫) በንውስ ፡ ቊጥር ፡ /፩/ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ተሻሽሎና ፡ ተሟልቶ ፡ የቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ በሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ተፈርሞና ፡ ምልክት ፡ ተደርጎበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ይሞላበታል ።

BACK

ቍ ፡ ፫፻፹፯ ። የፍርድ ፡ ባለዕዳውን ፡ ስለመጠየቅ ።

(፩) ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚቀርበው ፡ የማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ ከመጥሪያ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ይላክለታል ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በመጥሪያው ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ቀርቦ ፡ ፍርዱ ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚቃወምበትን ፡ ምክን ንያት ፡ እንዲያስረዳ ፡ ይታዘዛል ።

(፪) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በቀረበበት ፡ ቀን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱና ፡ የፍ ርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ለሚያቀርቡለት ፡ ጥያቄ ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ አለበት ፤ ፍርዱ ፡ የማይፈጸምበ ትን ፡ ምክንያት ፡ ያስረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበውን ፡ ምክንያት ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእ ዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ያልቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ቀርቦ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያልሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ወዲያውኑ ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፬) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ /፫/ የተነገረው ፡ ድንጋ ጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ማመልከቻው ፡ የቀረበው ፡ ገንዘብ እንዲከፈል ፡ የተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሲሆን ፤ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በመጥሪያው ፡ መሠረት ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ፡ ታስሮ ፡ እንዲቀርብና ፡ ለሚደረግለት ፡ ጥያቄ ፡ ወይም ፡ ምርመራ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፭) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረውን ፡ የምርመራ ፡ ወይም ፡ የጥያቄ ፡ ሥርዓት ፡ ለማከናወን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማናቸውም ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፹፰ ፡- የማስር ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፤

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፬ ፡ /፬/ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፯ ፡ /፩/ የተነገረውን ፡ ድን ጋጌ ፡ ለማስፈጸም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ፍርዱ ፡ እንዳይፈጸም ፡ መሰናክል ፡ በመፍጠር ፡ ወይም ፡ የፍርዱን አፈጻጸም ፡ ለማዘግ የት ፡ ንብረቱን ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ለማሸሽ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡

ውስጥ ፡ ለመውጣት ፡ ለመሸሽና ፡ ለመሠወር ፡ ያቀደ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ በመሐላ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በቀጥታ ፡ እንዲታሠር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የቀረበለትን ፡ ማመልከቻ ፡ መርምሮ ፡ ውሣኔ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ የተነገረውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

ቁ ፡ ፫፻፹፫ ፦ በማሰር ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ስለሚጸፉ ፡ ነገሮች ፡

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፹፩ ፡ /፩/ ወይም ፡ ፫፻፹፪ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ የማሰር ፡ ትእዛዝ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እንዲታሠር ፡ ከመታዘዙ ፡ በፊት ፡ የሚፈለግበትን ፡ ነገር ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ በፈቃዱ ፡ አልፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲያስር ፡ የታዘዘው ፡ ባለሥልጣን ፡ አስሮ ፡ እንዲያቀርበው ፡ የሚገለጽ ፡ ይሆናል ።

(፪) የማሰር ፡ ትእዛዝ ፡ ቢሰጥም ፡ እንኳ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ፍርዱን ፡ በፈቃደኛነት ፡ ፈጽሞ ፡ ከተገኘ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቁ ፡ ፫፻፹፬ ። በማረፊያ ፡ ቤት ፡ የማቆየት ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) በቁጥር ፡ ፫፻፹፮ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተገቢውን ፡ ምርመራ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡

(ሀ) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ፍርዱን ፡ የማይፈጽም ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡

(ለ) በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ ለመፈጸም ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ፈቃደኛ ፡ ባለመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሳፈጸም ፡ መቅረቱን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ታስሮ ፡ የሚገኝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ታስሮ ፡ እንዲቆይ ፡ ሊወሰንበት ፡ ይችላል ።

(፪) በቁጥር ፡ ፫፻፹፮ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ /፪/ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ /፩/ በተነገረው ፡ መሠረት፡ በሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፫፻፺ ፡- ከእሥራት ፡ ስለመለቀቅ ፤**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ከእሥራት ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚያዘው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲፈጸሙ ፡ ነው ።

(ሀ) በፍርዱ ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ የተገለጸው ፡ ገንዘብ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተቀመጠ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ለወሕኒ ፡ ቤቱ ፡ አዛዥ ፡ በመያዣ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ ፍርዱ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፤

(ለ) የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ የጠየቀ ፡ እንደሆነ ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ሁኔታ ፡ ከእሥራት ፡ የተለቀቀ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ ታስሮበት ፡ የነበረው ፡ ፍርድ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ሁለተኛ ፡ አይታሰርም ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፩ ፡- መያዝና ፡ ተይዞ ፡ መለቀቅ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፤**

ማንኛውም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፱ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ መያዙ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፺፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተይዞ ፡ መለቀቁ ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ከሚጠየቀው ፡ አላፊነት ፡ ወይም ፡ መክፈል ፡ ከሚገባው ፡ ዕዳ ፡ ነፃ ፡ አያደርገውም ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፪ ፡- ፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፤**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳውን ፡ ጠርቶ ፡ ከመረመረው ፡ በኋላ ፡ እንደፍርዱ ፡ የማይፈጸምበት ፡ ምክንያት ፡ ያለመሆኑን ፡ ሲያረጋግጥ ፡ ለአፈጻጸሙ ፡ ተስማሚ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ፍርዱን ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተረዳው ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ፡/ ስለሆነም ፡ ለመፈጸም ፡ ችሎታ ፡ በሚያገኝበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንዲፈጽም ፡ ትእዛዝ ፡ ከመስጠት ፡ አይታገድም ።

(፫) ማናቸውም ፡ የፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ትእዛዝ ፤ ለአስፈጻሚው ፡ የሚተላለፈው ፡ የተጻፈበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሀረት ፡ ተሞል

BACK



ቶበት ፡ የዳኛው ፡ ፊርማና ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ ተደርጐበት ፡ ነው ።

(፬) እንዲሁም ፡ ፍርዱ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ቀን ፡ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፺፫ ፡- የአፈጻጸሙ ፡ መግለጫ ፤

(፩) ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ወይም ፡ ያስፈጸመው ፡ ክፍል ፡ ፍርዱ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀንና ፡ የአፈጻጸሙን ፡ ሁኔታ ፤ ፍርዱ ፡ የተፈጸመው ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ አልፎ ፡ እንደሆነ ፡ የቆየበትን ፤ አልተፈጸመም ፡ እንደሆነ ፡ ያልተፈጸመበትን ፡ ምክንያት ፡ በማስፈጸሚያው ፡ ማዘዣ ፡ ላይ ፡ ሞልቶ ፡ እንዲያስፈጽም፡ ላዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይልካል ።

(፪) በማስፈጸሚያው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ተሞልቶ ፡ የተመለሰው ፡ መግለጫ ፡ የፍርዱን ፡ ያለመፈጸም ፡ የሚያስታውቅ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምክንያቱን ፡ በመመርመር ፡ አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲያገኘው ፡ ምስክሮችን ፡ ጠርቶ ፡ በመስማት ፡ ያገኘውን ፡ የምርመራ ፡ ውጤት ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ለማስፈር ፡ ይችላል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፫ ፤

## ስለአፈጻጸሙ ፡ ሥርዓት ፤

### ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፤

ቍ ፡ ፫፻፺፬ ። ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በተለዋዋጭ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ የተሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳውን ፡ ንብረት ፡ በማስከበርና ፡ በመሸጥ ፡ ለማስፈጸም ፡ ይቻላል ።

(፪) የሚከበረው ፡ ወይም ፡ የሚሸጠው ፡ ንብረት ፡ ግምት ፡ በተቻለ፡ መጠን ፡ በፍርዱ ፡ ወይም ፡ በውሣኔው ፡ ላይ ፡ ከተገለጸው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ጋር ፡ ተመዛዛኝ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻ ፺፩ ፡- ገንዘብ ፡ ስለሚከፈልበት ፡ ሁኔታ ፤

(፩) በፍርድ ፡ ወይም ፡ በውሣኔ ፡ መሠረት ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ መከፈል ፡ አለበት ፤

(ሀ) ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ለታዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማስያዝ ፤

(ለ) ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ የሚከፈል ፡ ሲሆን ፤ ለፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በመከፈል ፡ ወይም ፤

(ሐ) ፍርዱን ፡ የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ለመፈጸም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ከፍያው ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርዱ ፡ መፈጸሙን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ያስታውቀዋል ።

ቍ ፡ ፫፻ ፺፪ ፡- ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ለፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ስለመከፈል ፤

(፩) በማናቸውም ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ መሠረት ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውጭ ፡ የተከፈለ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ስምምነት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ መቻቻል ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ ፤ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በስምምነት ፡ መቻቻል ፡ ማድረጉን ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ መቀበሉንና ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብም ፡ ቢኖረው ፡ የቀሪውን ፡ ልክ ፤ ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ለታዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ይህንኑ ፡ ጽፎ ፡ ከመዝገቡ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ ያስቀምጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በስምምነት ፡ መቻቻል ፡ ማድረጉን ፡ ወይም ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ መከፈሉን ፡ ፍርዱን ፡ ለሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማስታወቅ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ቀርቦ ፡ ከፍያ ፡ ወይም ፡ ስምምነት ፡ መደረጉን ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ እንዳይመዘግብ ፡ የሚቃወም ፡ እንደሆነ ፡ እንዲጠየቅለት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ለፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ማስታወቂያ ፡ ደርሶት ፡ ስምምነቱ ፡ ወይም ፡ መቻ

BACK



ቻሉ ፡ ወይም ፡ ክፍያው ፡ መፈጸም ፡ ያለመፈጸሙን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያላስረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ይኸንኑ ፡ በመገንዘቡ ፡ ላይ ፡ ይጽፈዋል ።

(፫) በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ያልተመዘገበ ፡ ክፍያ ፡ ወይም ፡ የስምምነት ፡ መቻቻል ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፫፻ ፺፯ ። ሁለቱም ፡ ወገን ፡ ተከራካሪዎች ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

(፩) ሁለት ፡ ወገን ፡ ተከራካሪዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክስ ፡ ተከራክረው ፡ ባገኙት ፡ የፍርድ ፡ መብት ፡ አንዱ ፡ ላንደኛው ፡ ከፋይ ፡ እንዲሁም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ሆኖ ፡ ፍርዱም ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ለመፈጸም ፡ የሚችል ፡ ሲሆንና ፡ ሁለቱም ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርቡ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ሥርዓት ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

(ሀ) የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ የሆኑት ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ላንደኛው ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እንደተቻቻሉ ፡ ተቆጥሮ ፡ ይመዘገባል ።

(ለ) ከፍርድ ፡ ባለገንዘቦቹ ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ የሚጠይቀው ፡ ገንዘብ ፡ የሚበልጥ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ የሚፈጸመው ፡ ብልጫ ፡ ላለው ፡ ወገን ፡ ሆኖ አፈጻጸሙም ፡ በብልጫው ፡ ሂሣብ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ፡ ይኸውም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ፍርድ ፡ እንደተፈጸመ ፡ ተቆጥሮ ፡ ይመዘገባል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ የጠየቀው ፡ ወገን ፡ የፍርድ ፡ መብት ፡ የተላለፈለትም፡ ቢሆን ፡ እንዲሁም ፡ የፍርድ ፡ ግዴታው፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የተላለፈው ፡ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ መብት ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ የመቀበል ፡ መብቱን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በሚያስተላልፍበትም ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ የን ፡ ቍጥር ፡ /፩/ ድንጋጌ ፡ ቀጥሎ ፡ የተ

BACK



መለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ካላጋጠመ ፡ በቀር ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(ሀ) ውሣኔ ፡ በተሰጠበት ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ የሆነው ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በሌላ ፡ ክስ ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ ሲሆን ፤ እንዲሁም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ በሌላ ፡ ክስ ፡ በተሰጠ ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ሲሆን ፤

(ለ) በፍርዱ ፡ ውሣኔ ፡ እንዲከፈል ፡ የታዘዘው ፡ ገንዘብ ፡ ልኩ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ።

(፩) ቍጥራቸው ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ በአንድነት ፡ ወይም ፡ በተነጣጠለ ፡ አላፊነት ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከፍርድ ፡ ባለዕዳዎቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑት ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ በሆነው ፡ ላይ ፡ አስፈርደው ፡ እንደሆነ ፡ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፺፫ ። ባንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

ሁለት ፡ ተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ ባንድ ፡ ውሣኔ ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ሆነው ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ ማመልከቻ ፡ ያቀረቡ ፡ እንደሆነ ፡ አፈጻጸሙ ፡ የሚመራው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

(ሀ) ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ባንድ ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ የተፈረደላቸው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እንደተቻቻሉ ፡ ተቆጥሮ ፡ የፍርዱ ፡ መፈጸም ፡ ይመዘገባል ።

(ለ) ከፍርድ ፡ ባለገንዘቦቹ ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ የሚጠይቀው ፡ የሚበልጥ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ የሚፈጸመው ፡ ብልጫ ፡ ላለው ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ አፈጻጸሙ ፡ በብልጫው ፡ ሂሣብ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ።

ይህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ፍርድ ፡ እንደተፈጸመ ፡ ተቆጥሮ ፡ ይመዘገባል ።

**ቍ ፡ ፫፻፶፱ ። ተለይቶ ፡ በታወቀ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ፡ ውሣኔ ።**

አንድ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ እንዲመለስ ፡ ወይም ፡ እንዲዛወር ፡ የተሰጠ ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ የሚፈጸመው ፤ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ ለፍርድ ፡ ባለመብቱ ፡ ወይም ፡ ለወኪሉ ፡ በማስረከብ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻ ። በተለይ ፡ እንዲፈጸም ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔና ፡ የማገድ ፡ ውሣኔ ።**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፱-፬፻፲፭-፬፻፳፯ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ውል ፡ እንዲ ፈጸም ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ተገልጾ ፡ የተወሰነ ፡ ነገር ፡ ከመፈጸም እንዲታገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ውሣኔ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፤ በት እዛዙ ፡ መሠረት ፡ ሊፈጽም ፡ ሲችል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እንዳይፈጸም ፡ የተከለከለውን ፡ ነገር ፡ የፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የእምቢተኛው ፡ ንብረት ፡ እን ዲያዝና ፡ እንዲሸጥ ፡ አድርጐ ፡ የተወሰነበት ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈ ጸም ፡ ለማዘዝና ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ሲታየውም ፡ ከንብረቱ ፡ ሽያጭ ፡ ገንዘብ ፡ ለፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ እ ንዲከፈለው ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፤ ፍርዱን ፡ የሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ የታ ዘዘው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ የፍርድ ፡ ባለመብቱ ፡ ራሱ ፡ እንደፍርዱ ፡ ለማስፈጸም ፡ ከማድረግ ፡ አያግደውም ። ስለ ፍርዱም ፡ ማስፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆነውን ፡ ወጭ ፡ የሚከፍ ለው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ መሠ ረት ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ የሚከፈለው ፡ በመጀመሪያ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ከተወሰነው ፡ ሂሣብ ፡ ጋር ፡ በመጠቃለል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፩ ።የጽሑፍ ፡ ሰነድ ፡ እንዲፈረም ፤ እንዲረጋገጥ ፡ ወይም ፡ በሚዘ ዘዋወሩና ፡ በሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ እንዲፈረም፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፤**

BACK



(፩) የጽሑፍ ፡ ሰነዶችን ፡ እንዲፈርም ፤ እንዲያረጋግጥ ፡ ወይም ፡ እንዲያስተካክል ፤ ወይም ፡ በሚዘዋወሩና ፡ በሚተላለፉ ፡ የገንዘብ፡ ሰነዶች ፡ ወይም፡ በቼክ ፡ ላይ፡ እንዲፈርም ፡ የተፈረደበት ፡ ወይም፡ የታዘዘ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በፍርዱ ፡ ወይም ፡ በውሣኔው ፡ መሠረት ፡ ለመፈጸም ፡ እምቢተኛ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ ትእዛዙን ፡ ያላከበረ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለመብቱ ፡ እነዚህን ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነዶች ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማቅረብ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቀረበለትን ፡ ጽሑፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተቀብሎ ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እንዲደርሰው ፡ በማድረግ ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ቀርቦ ፡ ፍርዱን ፡ ወይም ፡ ትእዛዙን ፡ የማይፈጽምበትን ፡ ምክንያት ፡ እንዲያስረዳ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፫) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ቀርቦ ፡ ሰነዶችን ፡ የማይፈርምበትን ፡ ምክንያት ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ አድርጎ ፡ የተቀበለው ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ወይም ፡ ተስተካክለው ፡ እንዲታረሙ ፡ ያደርጋል ፤ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያልቀረበለት ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ሰነዶቹን ፡ የሚያጸድቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፬) በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የተሻሻለው ፡ ሰነድ ፡ እንዳለ ፡ ጸድቆ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያጸደቀበትን ፡ ትእዛዝ ፡ የፍርድ ፡ ባለመብቱ፡ ተቀብሎ ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ለታዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ለታዘዘው ፡ ሰው ፡ ሲያቀርብለት ፤ አስፈጻሚው ፡ ባለሥልጣን ፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በአባሪነት ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ በ፫ኛው ፡ ሠንጠረዥ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረትና ፡ ሁኔታ ፡ ማስፈጸም ፡ አለበት ።

* (፭) ሰነዶቹ ፡ እንዲመዘገቡ ፡ በሕግ ፡ የታዘዘ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ሰው፡ እንዲመዘገቡ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ስለ ፡ አመዘጋገቡና ፡ ለዚሁም ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ወጭ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል።

BACK



ቍ ፡ ፬፻፪ ። በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ።

(፩) ፍርዱ ፡ ወይም ፡ ውሳኔው ፡ የሚመለከተው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የማስረከብን ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ የሚፈጸመው ፡ በውሣኔው ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረት ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ የወከለው ፡ ሰው ፡ እንዲረከብ ፡ በማድረግ ፡ ነው ፡ አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ከሥፍራው ፡ አስለቅቆ ፡ ተረካቢው ፡ እንዲተካ ፡ በማድረግ፡ የርክክቡን ፡ ሥርዓት ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርዱ ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የጋራ ፡ ባለሀብትነት ፡ መኖሩን ፡ የሚወስን ፡ ሲሆን ፡ የሚፈጸመው ፡ የፍርዱን ፡ ውሣኔ ፡ ግልባጭ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በሚታይ ፡ ሥፍራ ፡ በመለጠፍ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ሊገለጽ ፡ በሚችልበት ፡ ዘዴ ፡ ፍርዱን ፡ በአደባባይ ፡ በንበባና ፡ በአዋጅ ፡ ቃል ፡ በማሰማት ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ልማዳዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ እንዲታወቅ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፫) ፍርዱ ፡ ወይም ፡ ውሣኔው ፡ የሚመለከተው ፡ ማናቸውንም ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ተከልሎ ፡ የታጠረ ፡ ቦታ ፡ የማስረከብን፡ ጉዳይ ፡ ሲሆንና ፡ እንዲያስረክብ ፡ የተፈረደበት ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ተከለለው ፡ ቦታ ፡ ለማስገባት ፡ እምቢተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተከላከለ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘው ፡ ሰው ፡ የተዘጋውን ፡ ቤት ፡ ለመክፈት ፡ ወይም ፡ ቁልፉን ፡ ለመስበር ፡ ወይም ፡ በተከለለው ፡ ሥፍራ ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ፡ ገብቶ ፡ የፍርድ ፡ ባለመብቱ ፡ እንዲረከብ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፫ ። ሀብትንና ፡ ንብረትን ፡ ስለማከፋፈል ።

በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ተከብሮ ፡ የተያዘ ፡ ወይም ፡ በፍርድ ቤቱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀማጭ ፡ የሆነ ፡ ሀብት ፡ ከመያዙ ፡ ወይም ፡ ከመቀመጡ ፡ በፊት ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈላቸው ፡ በባለሃብቱ ፡ ላይ ፡ አስፈርደው ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ የሚጠይቁ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ሲቀርቡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ ያለመፈጸሙን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ተገቢውን ፡ ኪሣራና ፡ ሌላውንም ፡ ወጭ ፡ ቀንሶ ፡ የተያዘውን ፡ ወይም ፡ ተቀማጭ ፡ የሆነውን ፡ ሀብት ፡ በውሣኔው ፡ መሠረት ፡ እንዲከፋፈሉ ፡ ያደርጋል ።

BACK



## ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡

## ንብረትን ፡ ስለ ፡ ማስከበር ፡

**ቍ ፡ ፬፻፬ ። ስለማይከበሩና ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ ስለማይወሰዱ ፡ ሀብቶች ።**

የክርክሩ ፡ መቀጠል ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ የደረሰ ፡ ቢሆንም፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ዓይነታቸውና ፡ ልካቸው ፡ የተዘረዘረው ፡ ንብረቶች ፡ በመከበር ፡ የማይያዙና ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የማይወሰዱ ፡ ናቸው ።

(ሀ) ለፍርድ ፡ ባለዕዳውና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ የዕለት ፡ አገልግሎት፡ የሚጠቅሙ ፡ ልብሶች ፡ የምግብ ፡ ማብሰያ ፡ የሆኑ ፡ የቤት ፡ ቁሳቁስ ፡ የመኝታ ፡ አልጋ ፡ የአልጋ ፡ ልብሶችና ፡ የብርድ ፡ ልብሶች ፡

(ለ) ለዕለት ፡ ሞያ ፡ ሥራዎቹ ፡ አገልግሎት ፡ ለንግድ ፡ ሥራው ፡ ማከናወኛ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ ዕቃዎች ፡

(ሐ) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ገበሬ ፡ ወይም ፡ በእርሻ ፡ ሥራ ፡ የሚተዳደር ፡ ሲሆን ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ ለዚሁ ፡ ሥራው ፡ አገልግሎት ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ የሚገመቱ ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ የዘር፡ እሕልና ፡ ሌላም ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡

(መ) ለራሱና ፡ ለቤተሰቡ ፡ ለሶስት ፡ ወር ፡ መተዳደሪያ ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብና ፡ ለዕለት ፡ ምግብ ፡ ጠቃሚ ፡ የሚሆን ፡ ሥንቅ ፡

(ሠ) ለጡረታው ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብና ፡ ባል ፡ ሚስቱን ፡ ከፈታ ፡ በኋላ ፡ ለወር ፡ ቀለቡዋ ፡ የሚከፍላት ፡ ገንዘብ ፡

(ረ) በባሕር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፳፩ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የወር ፡ ደመወዝ ፡ ሁለት ፡ ሶስተኛው ፡ እጅ ፡ ስለሆነም ፡ ደመወዙ ፡ በቀን ፡ ከሁለት ፡ ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ሆኖ ፡ ሌላ ፡ ገቢ ፡ የሌለው ፡ እንደሆነ ፡ ለዕዳ ፡ መክፈያ ፡ አይያዝበትም ።

(ሰ) እንዳይከበር ፡ እንዳይሸጥና ፡ ለዕዳ ፡ መክፈያ ፡ እንዳይሆን ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡

ቍ ፡ ፬፻፳ ። የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ተወስኖ ፡ ያልታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ስለሚ ከበር ፡ የንብረት ፡ መጠን ።

ፍርዱ ፡ ወይም ፡ ውሳኔው ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ የተወሰደ ፡ የገንዘብ፡ ልክ ፡ እንዲጣራ ፡ ወይም ፡ እንዲታወቅ ፡ ማድረግን ፡ የሚመለከት፡ ሲሆን ፡ የማጣራቱ ፡ ሥርዓት ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕ ዳውን ፡ ንብረት ፡ ለማስከበር ፡ ይቻላል ። የንብረት ፡ ማስከበሩም፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ ልኩ ፡ የታወቀ ፡ ማናቸውም ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ የንብረት ፡ መያዝ ፡ ወይም ፡ ማከበር ፡ ሥርዓት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፳፩ ። ከእርሻ ፡ ሰብል ፡ በተቀር ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ስለሚያዝበትና ፡ ስለሚከበርበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የሚያዘው ፡ ወይም ፡ የሚከበረው ፡ ሀብት ፡ ከእርሻ ፡ ሰብል ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፍርዱ ፡ የሚ ፈጸመው ፡ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ ለፍ ርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ በማስረከብ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ አስ ፈጻሚው ፡ የተረከበውን ፡ ንብረት ፡ በሚገባ ፡ ለመጠበቅና ፡ አጠ ባበቁም ፡ ለሚጠይቀው ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፪) የተያዘው ፡ ወይም ፡ የተከበረው ፡ ዕቃ ፡ በቶሎ ፡ የሚበላሽ ፡ ወይም ፡ በስብሶ ፡ ዋጋ ፡ የሚያጣ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ለጥበቃው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ወጭ ፡ ከዕቃው ፡ ዋጋ ፡ የሚበልጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊሸጠው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፳፪ ። የእርሻ ፡ ሰብል ፡ ስለሚከበርበትና ፡ ስለሚያዝበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የሚያዘው ፡ ወይም ፡ የሚከበረው ፡ ሀብት ፡ የእርሻ ፡ ሰብል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አፈጻጸሙ ፡ የሚመራው ፡ ከዚሁ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለ ከተው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

(ሀ) ሰብሉ ፡ ከበቀለበት ፡ መሬት ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተያያዘ ፡ የሚገ ኝ ፡ አዝርዕት ፡ ሲሆን ፡ የመያዝ ፡ ወይም ፡ የመከበር ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠበትን ፡ ማዘዣ ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ በመለጠፍ ፡ ወይም ፡

(ለ) ሰብሉ ፡ ታጭዶ ፡ የተከመረ ፡ ወይም ፡ በመወቃት ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ የድርቆሽ ፡ ክምር ፡ ሲሆን ፡ በክምሩ ፡

BACK



ወይም ፡ በውድማው ፡ አቅራቢያ ፡ ትእዛዙን ፡ በመለጠፍ ።

(፪) በተጨማሪም ፡ ከትእዛዙ ፡ ግልባጮች ፡ አንዱ ፡ የፍርድ ፡ ባለ ዕዳው ፡ በሚኖርበት ፡ ቤት ፡ መዝጊያ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ በሚታይ ፡ ሌላ ፡ ሥፍራ ፡ መለጠፍ ፡ አለበት ። ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚፈቅድ ፡ ሲሆን ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በሚነግድበት ፡ ወይም ፡ ተቀጥሮ ፡ በሚሠራበት ፡ ወይም ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ይኖር ፡ በነበረበት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ይነግድ ፡ በነበረበት ፡ ሥፍራ ፡ ወይም ፡ ይሠራ ፡ ከነበረበት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በራፍ ፡ ላይ ፡ ወ ይም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በሚታይ ፡ ሥፍራ ፡ ሊለጠፍ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገሩት ፡ ማዘዣዎች ፡ ከተለጠፉበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሰብሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እጅ ፡ እንደተያዘ ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠ ራል ።

## ቍ ፡ ፬፻፳ ። በተያዙ ፡ ወይም ፡ በተከበሩ ፡ ሰብሎች ፡ ላይ ፡ ስለሚጸኑ ፡ ድንጋጌዎች ።

(፩) ማናቸውም ፡ የእርሻ ፡ ሰብል ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ አጠባበቁ ፡ ሁኔታ ፡ ተስ ማሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። ይህ ንንም ፡ ተስማሚ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ እንዲያስችለው ፡ ሰብሉ ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ በሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ የሚታጨድበትን ፡ ወይም ፡ የሚወቃበትን ፡ ወይም ፡ የሚከ በርበትን ፡ ጊዜ ፡ ገልጾ ፡ ማስታወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) ስለተያዘው ፡ ወይም ፡ ስለተከበረው ፡ ሰብል ፡ አጠባበቅ ፡ ፍ ርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሰብሉን ፡ በጊዜው ፡ ለማጨድ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ወይም ፡ ተገቢውን ፡ የአጠባበቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረውን ፡ ተግባር ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብሎ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ በወከለው ፡ ወይም ፡ በቀጠረው ፡ ሰው ፡ እንዲከናወን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ለማከናወን ፡ ወጭ ፡ የተደረገው ፡ ገንዘብ ፡ ከዋናው ፡

BACK



ዕዳ ፡ ጋር ፡ ተደምሮ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እንዲከፍል ፡ ይታ ዘዛል ።

(፩) በተዘሩበት ፡ ወይም ፡ በተተከሉበት ፡ እርሻ ፡ ላይ ፡ በሚገኙ በት ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ የተከበሩ ፡ ወይም ፡ የተያዙ ፡ ሰብሎች ፡ በመ ታጨዳቸው ፡ ወይም ፡ በመቆረጣቸው ፡ ምክንያት ፡ የመያዙን ፡ ወይም ፡ የማስከበሩን ፡ ትእዛዝ ፡ ሊያስቀረው ፡ አይችልም ።

(፪) ትእዛዙ ፡ የተሰጠው ፡ ሰብሉ ፡ ገና ፡ በቡቃያነት ፡ ላይ ፡ ባለበት፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መስሎ ፡ ለታየው ፡ ጊዜ ፡ የፍርዱ ፡ መፈጸም ፡ እንዲቆይ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲሁም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ፍርዱ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ሰብሉ ፡ እንዳይ ነካ ፡ ተጨማሪ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) የሚያዘው ፡ ወይም ፡ የሚከበረው ፡ ሰብል ፡ የተፈጥሮ ፡ ሁኔ ታው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተከማችቶ ፡ ለመጠበቅ ፡ የማያስችል ፡ የ ሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ ሰብሉ ፡ ለመታጨድ ፡ ወይም ፡ ለመወቃት ፡ ከሃያ ፡ ቀን ፡ ያላነሰ ፡ ጊዜ ፡ ሲቀረው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፱ ። በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ የማይገኝ ፡ ንብረት ፡ ስለሚከበር በት ፡ ወይም ፡ ስለሚያዝበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ በፍርድ ፡ የታዘዘው ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ መብት ፡ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ያልገባ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀው ፡ በሚተላለፍ ፡ ሰነድ ፤ ያልተደገፈ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ከሶ ፡ በማስፈረድ ፡ መብት ፡ ያገኘበት ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ሀብት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመያዙ ፡ ወይም ፡ የማስከበሩ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ለፍርድ ፡ ባለ ዕዳው ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ የሚከፈለ ለውን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የሚያስተላልፈውን ፡ መብት ፡ ለማ ንም ፡ ሰው ፡ ሳይሰጥ ፡ በእጁ ፡ እንዲያቆይ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፪) የሚያዘው ፡ ወይም ፡ የሚከበረው ፡ ሀብት ፡ በንግድ ፡ ማኅበር ፡ የተመዘገበ ፡ የአክሲዮን ፡ ሰነድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመያዙ ፡ ወይም ፡ የማስከበሩ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ይህን፡

BACK



ሰነድ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ እንዳይሰጥ ፡ ወይም ፡ እንዳይሸጥ ፡ ወይም ፡ ከንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ የሚያገኘውን ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ እንዳይቀበል ፡ በማድረግና ፡ እንዲሁም ፡ በአክሲዮን ፡ የተቋቋመው ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አክሲዮኑን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በመዛወር ፡ ተቀብሎ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ እንዳያገባ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

(፫) ማኀቸውም ፡ ሌላ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም፡ እንዲከበር ፡ የሚታዘዘው ፤ ይህ ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ አሳልፎ ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚያግድ ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ ነው ።

(፬) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገሩት ፡ በንውስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ እና ፡ ፫ የተመለከተው ፡ ትእዛዝ ፡ ግልባጭ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በሚታየ ፡ ሥፍራ ፡ ይለጠፋል ፤ እንዲሁም፡ ፍርዱ ፡ የሚመለከተው ፡ የገንዘብ ፡ ዕዳ ፡ የመክፈልን ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ አንዱ ፡ ግልባጭ ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ይሰጣል ፤ የአክሲዮን ፡ ሰነድ ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ የትእዛዙ ፡ ግልባጭ ፡ ለንግዱ ፡ ድርጅት ፡ ባለሥልጣን ፡ ይላካል ፤ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ሲሆን ፡ የዕቃው ፡ ባለይዞታ ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ይሰጣል ።

(፭) በንውስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ እንዳይከፍል ፡ የተከለከለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቅርቦ ፡ ለማስረከብ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ለባለመብቱ ፡ እንደከፈለ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከዕዳው ፡ ነፃ ፡ ይሆናል ።

(፮) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ ማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ከማስታወቂያው ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ገንዘቡ ፡ ወይም ፡ የሚንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ ለሚገኘው ፡ ሰው ፡ ይላክለታል ። በማስታወቂያውም ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀርቦ ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ የማያስረክብበት ፡ ምክንያት ፡ እንዳለ ፡ እንዲያስረዳ ፡ ይገለጽለታል ።

(፯) በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ተጠርቶ ፡ የቀረበው ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍ ፡ ፬፻፲፰ እስከ ፡ ፬፻፳፩ ፡ የተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ በተመሳሳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፲ ። በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ድርሻ ፡ ስለማስ ከበርና ፡ ስለማስያዝ ።**

የሚያዘው ፡ ወይም ፡ የሚከበረው ፡ ንብረት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕ ዳው ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በተካፋይነት ፡ ወይም ፡ በኅብረት ፡ የሚጠቀምበት ፡ ወይም ፡ የከፈል ፡ ድርሻው ፡ የሆነ ፡ ሀብት ፡ ሲሆን ፤ የመያዙ ፡ ወይም ፡ የማስከበሩ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ ድርሻውን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ እንዳይሰጥ ፤ እንዳይሸጥ ፤ በዕዳ ፡ እንዳያስይዝ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ እንዳያ ስተላልፍ ፡ የማገድ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፲፩ ። ደመወዝ ፡ ስለ ፡ ሚያዝበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) የሚያዘው ፡ ሀብት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የሚያገኘው ፡ ደመ ወዝ ፡ ሲሆን ፡ በየወሩ ፡ እየተቀነሰ ፡ ወይም ፡ ድርሻው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚያዘው ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያዝ ፡ ለማድ ረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠ ረት ፡ የሚያዘው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከትእዛዙ ፡ ግልባጭ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ አሠሪ ፡ ይላክለታል ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ደየረሰው ፡ አሠሪም ፡ በትእዛዙ ፡ ላይ ፡ የተወሰነውን ፡ ገንዘብ ፡ እየቀነሰ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

(፫) እንዲያዝ ፡ የታዘዘው ፡ የደመወዝ ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተሰጠ ፡ ትእዛዝ ፡ ምክንያት ፡ አስቀድሞ ፡ የተ ያዘ ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ትእዛዝ ፡ የደረሰው ፡ ቀጣሪ ፡ ይህንኑ ፡ በመግለጽ ፡ የደረሰውን ፡ የትእዛዝ ፡ ግልባጭ ፡ ከሙሉ ፡ መግ ለጫ ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መልሶ ፡ ይልካል ።

**ቍ ፡ ፬፻፲፪ ። የሚዘዋወር ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ ስለሚያዝበትና ፡ ስለሚከበ ርበት ፡ ሁኔታ ።**

እንዲያዝ ፡ የታዘዘው ፡ ሀብት ፡ የሚዘዋወር ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ ሆኖ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡

ያልተያዘ ፡ ሲሆን ፡ የማስከበሩ ፡ ወይም ፡ የማስያዙ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ ይህ ፡ ተዘዋዋሪ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ ተይዞ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቀማጭ ፡ እንዲሆን ፡ በማድረግ ፡ እንዲሁም ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ እንዳይለቀቅ ፡ የሚያግድ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩፻፲፫ ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ ሚያዝበትና ፡ ስለሚከበር በት ፡ ሁኔታ ።**

እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ የታዘዘው ፡ ንብረት ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ተይዞ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ የመያዙ ፡ ወይም ፡ የማስከበሩ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ ሀብቱ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ የሚያስገኘው ፡ ማናቸውም ፡ ጥቅም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በየጊዜው ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲቆይ ፡ በማዘዝ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ ሀብቱ ፡ የተያዘው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በፍርድ ፡ ባለ ፡ ገንዘቡና ፡ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ መካከል ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎች ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በዚህ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ተላልፎልናል ፡ ወይም ፡ አስቀድመን ፡ አስይዘናል ፡ በማለት ፡ የባለ ፡ ንብረትነት ፡ ወይም ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ አለን ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ያነሱ ፡ እንደሆነ ፡ ክርክሩ ፡ የሚወሰነው ፡ ንብረቱን ፡ ይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩፻፲፬ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ ሚያዝበትና ፡ ስለሚከበር በት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) እንዲያዝ ፡ ወይም እንዲከበር ፡ የተወሰነው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመያዙ ፡ ወይም ፡ የማስከበሩ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳይሰጥ ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለወጥ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ መብቱን ፡ ለማንም ፡ እንዳያዛወር ፡ በማገድና ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ እንዳይኖራቸው ፡ የሚገድ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ ግልባጭ ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ አቅራቢያ ፡ ወይም ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ሊታወቅና ፡ ሊሰማ በሚቻል በት ፡ ዘዴና ፡ በማናቸውም ፡ ልማዳዊ ፡ ዓይነት ፡ በአደባባይ ፡ ይነ ገራል ። እንዲሁም አንደኛው ፡ ግልባጭ ፡ በንብረቱ ፡ አቅራቢያ ፡ ወይም ፡ በማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ በሚታይ ፡ ቦታ ፡ ይለጠ ፋል ።

## ቍ ፡ ፬፻፲፭ ። የተያዘ ፡ ወይም ፡ የተከበረ ፡ ንብረት ፡ ስለሚለቀቅበት ፡ ሁኔታ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ አንዱ ፡ ሲፈጸም ፤

(ሀ) ለንብረቱ ፡ መያዝ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ፍርድ ፡ ሲፈጸ ምና ፡ የማስያዙን ፡ ወይም ፡ የማስከበሩን ፡ ሥርዓት ፡ ለማስፈ ጸም ፡ የተደረገው ፡ ወጭ ፡ በሙሉ ፡ ሲከፈል ፤

(ለ) ይህ ፡ ፍርድ ፤ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አማካይነት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ መፈጸሙን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ሆነ ፡ ወይም ፡

(ሐ) ፍርዱ ፡ የተሻረ ፡ ወይም ፡ የተሠረዘ ፡ እንደሆነ ፤ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደተሻረ ፡ ይቆ ጠራል ። በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ የተለቀቀው ፡ ሀብት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሲሆንና ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሲያመለክት ፡ አስፈላ ጊውን ፡ ወጭ ፡ ከፍሎ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፲፬ ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሊሰጥለት ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፬፻፲፮ ። ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የባንክ ፡ ኖት ፡ (የወረቀት) ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ።

የተያዘው ፡ ሀብት ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የባንክ ፡ ኖት ፡ ወረ ቀት ፡ ገንዘብ ፡ ሆኖ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆን ፡ ተይዞ ፡ እንዲቆይ ፡ በተወሰነበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ፍርዱን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለማስፈጸም ፡ በሚያስችለው ፡ መጠን ፡ በፍ ርዱ ፡ መሠረት ፡ የተያዘው ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ልክ ፡ መብት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ እንዲከፈል ፡ ለማዘዝ ፡ ይቻላል ።

BACK



ቍ ፡ ፬፻፲፯ ። ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ በሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለ ማሰጥ ፡ ውሣኔ ።

(፩) በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውም ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ተይዞ ፡ ወይም ፡ ተከብሮ ፡ በሚቀይበት ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ጉድለት ፡ የማስፈጸሙን ፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ ያል ተቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ የቀረበለ ትን ፡ ማመልከቻ ፡ ለመሠረዝ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ሲታ የው ፡ ፍርዱ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ጊዜ ፡ በማቆየት ፡ ቀጠሮውን ፡ አስተላልፎ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) ማመልከቻው ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የተሠረዘ ፡ እንደሆነ ፡ ንብ ረቱ ፡ እንዲከበር ፡ ወይም ፡ እንዲያዝ ፡ የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ይሻራል ።

ን ዑ ስ ፡ ክ ፍ ል ፡ ፫ ።

መብት ፡ አለን ፡ በማለት ፡ የሚያመለክቱትንና ፡ ይህንኑ ፡ መብት ፡ የሚቃወሙትን ፡ የተከራካሪ ፡ ወገኖች ፡ አቤቱታ ፡ ስለመመርመር ።

ቍ ፡ ፬፻፲፰ ። በተያዘ ፡ ወይም ፡ በተከበረ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ አለን ፡ ባዮች ፡ ያቀረቡትን ፡ አቤቱታ ፡ ስለመመርመር ።

(፩) በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ ንብረት ፡ እንዳይያዝ ፡ ወይም ፡ እንዳይከበር ፡ የመቃወም ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ተቀዳሚ ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ የሚል ፡ ተቃ ዋሚ ፡ አቤቱታ ፡ ያቀረበ ፡ እንደሆነ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መቃወሚያ ፡ ያቀረቡት ፡ ወይም ፡ እንዲያዝ ፡ በታዘዘው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ተቀ ዳሚ ፡ መብት ፡ አለን ፡ የሚሉት ፡ ወገኖች ፡ በመጀመሪያው ፡ ክር ክር ፡ ላይ ፡ ተካፋይ ፡ ባይሆኑም ፡ በሚያዘው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መ ብት ፡ እንዳላቸው ፡ በመቁጠር ፡ የሚ ያቀርቡትን ፡ መቃወሚያና፡ አቤቱታ ፡ ተቀብሎ ፡ መመርመር ፡ አለበት ። ስለሆነም ፡ መቃወ ሚያውን ፡ ወይም ፡ የባለ መብትነት ፡ አቤቱታውን ፡ ያቀረበው ፡ አቤት ፡ ባይ ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ያዘገየው ፡ መሆኑን ፡ ፍ

ርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲረዳው ፡ የቀረበውን ፡ መቃወሚያ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ አይመረምርለትም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ መቃወሚያ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ የሚቀርበው ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ፍርዱን ፡ ለሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፫) ተቃዋሚው ፡ ወይም ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ባዩ ፡ ከሚያቀርበው ፡ የመቃወሚያ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የተቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ባለይዞታነቱን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ አያይዞ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፬) መቃወሚያ ፡ ወይም ፡ የባለመብትነት ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ የሐራጅ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወጥቶ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቤቱታውን ፡ መርምሮ ፡ ውሣኔ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ንብረቱ ፡ ከመሸጥ ፡ ታግዶ ፡ እንዲቆይ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፲፱ ። በአቤቱታው ፡ ወይም ፡ በመቃወሚያው ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ውሣኔ ።</u>

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ አቤቱታና ፡ ማስረጃውን ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ የሚያደርግ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለመኖሩን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ የተያዘው ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚሰጠው ፡ ውሣኔ ፡ መሠረት ፡ እንዲለቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ንብረቱ ፡ በፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ መሠረት ፡ መያዝ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የመቃወሚያውን ፡ ወይም ፡ የመብት ፡ አቤቱታውን ፡ ማመልከቻ ፡ ይሠርዘዋል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፳ ። በሚያዘው ፡ ወይም ፡ በሚከበረው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የመያዙ ፡ ወይም ፡ የማስከበሩ ፡ ሥርዓት ፡ ስለሚቀጥልበት ፡ ሁኔታ ።</u>

እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ የተደረገው ፡ ንብረት ፡ ይዞታ ፡ የሌለው ፡ የሌላ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ የመያዣ ፡ ወይም ፡ ሌሳ ፡ ማገ

ኛውም ፡ መብት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ የሶስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ንብረቱ ፡ እንዲያዝ ፡ ወይም ፡ እንዲከበር ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ፡፡

**ቍ ፡ ፬፻፵፩ ፡፡ በተያዘ ፡ ወይም ፡ በተከበረ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ለማሳወቅ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ፡፡**

የቀደምትነት ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ወይም ፡ የንብረቱን ፡ መያዝ ፡ ወይም ፡ መከበር ፡ እቃወማለሁ ፡ በማለት ፡ አቤቱታ ፡ ባቀረበ ፡ በማናቸውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቤቱታውን ፡ ወይም ፡ ባለመብትነቱን ፡ ባለመቀበል ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፤ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠበት ፡ ወገን ፡ ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ በሆነው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ፡፡ ስለሆነም ፡ የቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ውጤት ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ውሳኔ ፡ እንደጸና ፡ ሆኖ ፡ ይቆያል ፡፡

## ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡፡

## ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ንብረትን ፡ የመሸጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡፡

**ቍ ፡ ፬፻፵፪ ፡፡ የተያዘው ፡ ወይም ፡ የተረከበው ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ ስለማዘዝ ፡፡**

(፩) ፍርድ ፡ የሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ የተያዘው ፡ ወይም ፡ የተከበረው ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፤ በፍርዱ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ንብረቱ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዕዳ ፡ ለመሸፈን ፡ የሚያስችለው ፡ ክፍል ፡ እንዲሸጥ ፡ አድርጎ ፡ ከሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ከተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ተገቢ ፡ ድርሻውን ፡ ለፍርድ ፡ ባለ ፡ ገንዘቡ ፡ ያስረክባል ፡፡

(፪) በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ ካልታዘዘ ፡ በቀር ፡ ማናቸው ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ የሚሸጠው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሥርዓት ፡ ነው ፡፡

(ሀ) የሽያጩን ፡ ሥርዓት ፡ እንዲያፈጽም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተለይ ፡ ባዘዘው ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሠራ

ተኛ ፡ አግካይነት ። (ፍርድን ፡ ለማስፈጸም ፡ ማናቸውንም ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ የታዘዘ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ አነጋገር ፡ ሐራጅ ፡ ባይ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።)

(ለ) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተነገረው ፡ ድን ጋጌ ፡ መሠረት ፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ በማድረግ ፤

(፫) በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ የተወ ሰነውን ፡ ንብረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በግል ፡ ወይም ፡ በስምምነት ፡ እንዲሸጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመስጠት ፡ አያግደውም ። ስለሆነም ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ትእዛዝ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ውን ፡ ፈቃደኛነትና ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡም ፡ በዚሁ ፡ እንዲፈ ጸም ፡ መስማማቱን ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፬፻፵፫ ። የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ መደረጉን ፡ ለሕዝብ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ጉዳይ ፡ ማናቸውም ፡ ንብረት ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሐራጁን ፡ ሥር ዓት ፡ አፈጻጸም ፡ ለሕዝብ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ለሕዝብ ፡ የሚገለጸው ፡ አዋጅ ፡ የሚነገረው ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕ ዳውና ፡ ለፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተሰጣቸው ፡ በኋላ ፡ ነው ። የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ ማስታወቂያውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተ ዘረዘሩትን ፡ ነገሮች ፡ በትክክለኛ ፡ ሁኔታ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(ሀ) የሚሸጠውን ፡ ንብረት ፡ ዓይነትና ፡ የግምቱን ፡ ልክ ፤

(ለ) ከንብረቱ ፡ ላይ ፡ የሚጠየቅ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መብት ፡ እንዳለ ፡ ልኩን ፤

(ሐ) ለንብረቱ ፡ መሸጥ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ በፍርድ ፡ የተ ወሰነውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፤

(መ) ንብረቱ ፡ የሚሸጥበትን ፡ ሁኔታና ፡ ገደቡን ፤ የሽያጩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈልበትን ፡ ጊዜ ፤

(ሠ) ገዢው ፡ ከመግዛቱ ፡ በፊት ፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚገምተውን ፡ ማናቸውንም ፡ ዝርዝር ፡ መግ ለጫ ።

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፡ የሐራጁ ፡ ሽያጭ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ አዋጅ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፬፻ ፡ እስከ ፡ ፬፻፵፪ ፡ የተነገሩትን ፡ ሁሉ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፳፬ ። ሽያጭ ፡ እንዲደረግ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።</u>

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፪ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ሽያጭ ፡ እንዲደረግ ፡ የሚቀርቡ ፡ ማንኛዎችና ፡ የክስ ፡ ማመልከቻዎች ፡ አቤቱታዎች ፡ ሁሉ ፡ ሌሎቹ ፡ አቤቱታዎችና ፡ ማመልከቻዎች ፡ ተረጋግጠውና ፡ ተፈርመው ፡ በሚቀርቡበት ፡ ሁኔታና ፡ ሥርዓት ፡ ይቀርባሉ ። በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ መረጋገጥ ፡ የሚገባው ፡ በተለይ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፫ ፡ (፪) ፡ በተመለከተው ፡ ላይ ፡ አመልካቹ ፡ የሚያውቀውንና ፡ ማወቅ ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሕዝብ ፡ በሚገልጸው ፡ ማስታወቂያ ፡ ላይ ፡ የሚዘረዘሩትን ፡ ነገሮች ፡ ለማጣራት ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ የሚገመተውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ለመጥራት ፡ ወይም ፡ በማስታወቂያው ፡ ላይ ፡ የሚሠፍሩትን ፡ መግለጫዎች ፡ ትክክለኛነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ወይም ፡ ጉዳዩን ፡ የሚመለከት ፡ ማናቸውንም ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ የሚሸጠውን ፡ ነገር ፡ ለመገመት ፡ ልዩ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ኤክስፔርት ፡ የግምቱን ፡ ውጤት ፡ እንዲያቀርብ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፳፭ ። ማስታወቂያው ፡ የሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ።</u>

(፩) ማናቸውም ፡ የሽያጭ ፡ ማስታወቂያ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፲፬ ፡ (፪) ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ለሕዝብ ፡ ይገለጸል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የሚሸጠው ፡ ንብረት ፡ በሚገኝበት ፡ ክፍል ፡ በሚታተም ፡ ወይም ፡ በሚሸጥ ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ እንዲወጣ ፡ ይደረጋል ። ለጋዜጣውም ፡ ማሳተሚያ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ወጭ ፡ ለሽያጩ ፡ ሥርዓት ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ከሚደረገው ፡ ወጭ ፡ ጋር ፡ በመደመር ፡ ከዕዳው ፡ ጋር ፡ ይታሰባል ።

(፫) ንብረቱ ፡ የሚሸጠው ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ተመድቦ ፡ በመከፋፈል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ለየአንዳንዱ ፡ መደብ ፡ ልዩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ። ነገር ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ለሚሸጠው ፡ መደብ ፡ ለየራሱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማው

BACK


ጣት ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ልዩ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲደረግ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፳፯ ። ሽያጭ ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፯ ፡ (፪) ፡ ከተመለከተው ፡ ንብረት ፡ በቀር ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲሸጥ ፡ የሚስማማ ፡ መሆኑን ፡ ለፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካላስታወቀ ፡ በቀር፤ ማናቸውም ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሳይቆይ ፡ በሐራጅ ፡ ሊሸጥ ፡ አይችልም ። ጊዜውም ፡ መቆጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ በሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ከተለጠፈበት ፡ ቀን ፡ ጋዜጣው ፡ ታትሞ ፡ ለሕዝብ ፡ ከታደለበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መጽሔት ፡ ላይ ፡ ከታወጀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፳፰ ። የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ ስለሚቆምበት ፡ ወይም ፡ ስለሚቋረጥበት ፡ ሁኔታ ።

የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ የሚቆመው ፡ የሐራጁ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የተፈረደበትን ፡ ገንዘብ ፡ ኪሣራውንና ፡ ወጭውን ፡ በሙሉ ፡ ለሐራጅ ፡ ሻጩ ፡ ያስረከበ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ እንዲሸጥ ፡ ላዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስረከቡን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የማያጠራጥር ፡ ማስረጃ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፳፱ ። ሁለተኛ ፡ የሐራጅ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለሚወጣበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፫ ፡ (፪) ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በሚሰጠው ፡ ማስታወቂያ ፡ የተገለጸውን ፡ የዋጋ ፡ ግምት ፡ የሚከፍል ፡ ገዢ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደሆነ ፤ ድጋሚ ፡ ማስታወቂያ ፡ በማውጣት ፡ ሁለተኛ ፡ ጨረታ ፡ ይደረጋል ። የሽያጩ ፡ ሥርዓትና ፡ የጊዜው ፡ አወሳሰን ፡ ጉዳይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ። ንብረቱም ፡ የሚሸጠው ፡ በሁለተኛው ፡ ጨረታ ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ለሚያቀርብ ፡ ተጫራች ፡ ነው ።

(፪) በሁለተኛው ፡ የጨረታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ተጫራች ፡ ያልቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ማናቸው ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ቢሆርም ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡም ፡ ተረክቦ ፡ እንዲይዝ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ፤ ይህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንደነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ፍርዱ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንደተፈጸመ ፡ ይቆጠራል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፳፱ ። በጨረታ ፡ ለገዛው ፡ ንብረት ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከፍል ፡ ወይም ፡ ግዴታውን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረ ፡ ገዢ ፡ ንብረቱ ፡ በሁለተኛ ፡ ጨረታ ፡ ሲሸጥ ፡ ለጐደለው ፡ ገንዘብ ፡ በአላፊነት ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ሁኔታ ።</u>

(፩) ገዢው ፡ በጨረታ ፡ ለገዛው ፡ ንብረት ፡ ዋጋውን ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ወይም ፡ በሽያጩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ዋጋውን ፡ ያላስቀመጠ እንደሆነ ፤ ሽያጩ ፡ እንደተሠረዘ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌላ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲወጣና ፡ ሁለተኛ ፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ እንዲደረግ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ንብረቱ ፡ እንደገና ፡ በሚሸጥበት ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ የቀነሰ ፡ እንደ ሆነ ፡ ሐራጅ ፡ ሻጩ ፡ የተቀነሰውን ፡ ሂሳብና ፡ ለሁለተኛው ፡ ሐራጅና ፡ ለማስታወቂያው ፡ የተደረገውን ፡ ወጭ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያስታውቅ ፤ በመጀመሪያ ፡ ጨረታ ፡ ንብረቱን ፡ የገዛውና ፡ ዋጋውን ፡ ያልከፈለው ፡ ተጫራች ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ዕዳ ፡ በሚከፈልበት ፡ ዓይነትና ፡ ሁኔታ ፡ ልዩነቱንና ፡ ኪሣራውን ፡ እንዲከፍል ፡ ይገደዳል ። ይህንንም ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፍለው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርቡ ፡ ነው ።

(፫) የሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ሲከፈል ፡ ሐራጅ ፡ ሻጩ ፡ ለከፋዩ ፡ የጽሑፍ ፡ ደረሰኝ ፡ በመስጠት ፡ ገንዘቡን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ሽያጩ ፡ የመጨረሻ ፡ ይሆናል ።

(፬) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚደረገው ፡ ሽያጭ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያ ፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፵ ። የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ በሐራጅ ፡ የሚሸጠውን ፡ ሀብት ፡ ያለፈቃድ ፡ ለመግዛት ፡ የማይችል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የፍርድ ፡ ባለ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ባለ ፡ መብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጥ ፡ የተወሰነውን ፡ ሀብት ፡ እንዲገዛ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ አስፈቅዶ ፡ የፈቃዱን ፡ ማስረጃ ፡ ለሐራጅ ፡ ሻጩ ፡ ካላቀረበ ፡ በቀር ፤ ራሱ ፡ ባስፈረደው ፡ ዕዳ ፡ ምክንያት ፡ በሚሸጠው ፡ ሃብት ፡ የጨረታ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ሆኖ ፡ ለመግዛት ፡ አይችልም ።

(፪) የፍርድ ፡ ባለ ፡ ገንዘቡ ፡ የጨረታው ፡ ተወዳዳሪ ፡ ሆኖ ፡ በሐራጅ ፡ የሚሸጠውን ፡ ንብረት ፡ እንዲገዛ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጥቶት ፡ የሐራጁን ፡ ሀብት ፡ የገዛ ፡ እንደሆነና ፡ የንብረቱም ፡ ዋጋ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዕዳ ፡ ከነ ፡ ኪሣራው ፡ በሙሉ ፡ የሚሸፍን ፡ ሲሆን ፤ ፍርዱን ፡ የሚያስፈጽመው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚከፍለው ፡ ዋጋና ፡ በሚጠይቀው ፡ ዕዳ ፡ መቻቻል ፡ አድርጎ ፡ ፍርዱ ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ መፈጸሙን ፡ ይመዘግባል ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ የንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ዕዳውንና ፡ ኪሣራውን ፡ የሸፈነው ፡ በከፊል ፡ ሲሆን ፡ ፍርዱም ፡ በከፊል ፡ እንደተፈጸመ ፡ ተቆጥሮ ፡ ሊመዘገብ ፡ ይችላል ።

(፫) የፍርድ ፡ ባለ ፡ ገንዘቡ ፡ ፈቃድ ፡ ሳያገኝ ፡ ራሱ ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ንብረቱን ፡ ገዝቶ ፡ ባለ ፡ ይዞታ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ወይም ፡ በሽያጩ ፡ ምክንያት ፡ መብቱ ፡ የተነካ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሲያመለክት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሽያጩ ፡ እንዲፈርስ ፡ አድርጎ ፡ ሌላ ፡ የጨረታ ፡ ሽያጭ ፡ እንዲደረግ ፡ ያዛል ፡ ይህም ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ የቍጥር ፡ ፬፻፷፱ ፡ ድንጋጌ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፩ ። የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘ ፡ ማናቸውም ፡ ባለ ፡ ሥልጣን ፡ በጨረታ ፡ መወዳደርና ፡ ንብረቱን ፡ ለመግዛት ፡ የተከለከለ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) የሐራጁን ፡ ሽያጭ ፡ ጨረታ ፡ ለማስፈጸም ፡ ወይም ፡ የፍርዱን ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዓት ፡ ለማከናወን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የታዘዘ ፡ ማና

ቸውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘ ፡ ማና ቸውም ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊ ፡ በቀ. ታ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ባላቸው ፡ በሌ ሎች ፡ ሰዎች ፡ አማካይነት ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ በጨረታ ፡ የሚሸጠ ውን ፡ ንብረት ፡ ለመግዛት ፡ የጨረታው ፡ ውድድር ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆንና ፡ በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ሙከራ ፡ ለማድረግ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረውን ፡ ድን ጋጌ ፡ በመተላለፍ ፡ ገዝቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ሽያጩ ፡ ፍርስ ፡ ሆኖ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፴ ፡ (፫) ፡ መሠረት ፡ ሌላ ፡ ሐራጅ ፡ ወጥቶ ፡ ሃብቱ ፡ በጨረታ ፡ እንዲሸጥ ፡ ይደረጋል ።

## ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

## የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለ ፡ ሚሸጥበት ፡ ሁኔታ ።

### ቍ ፡ ፬፻፴፪ ። የእርሻ ፡ ሰብል ፡ ስለሚሸጥበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የሚሸጠው ፡ ንብረት ፡ የእርሻ ፡ ሰብል ፡ ሲሆን ፡ የሐራጅ ፡ ሽያጭ ፡ የሚፈጸመው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

(ሀ) የሚሸጠው ፡ ሰብል ፡ ገና ፡ በቡቃያነት ፡ ሆኖ ፡ ከተተከለ በት ፡ ወይም ፡ ከተዘራበት ፡ እርሻ ፡ ላይ ፡ ያልታጨደ ፡ ወይም ፡ ያልተቆረጠ ፡ ሲሆን ፡ ሐራጁ ፡ የሚደረገው ፡ እርሻው ፡ በሚገኝ በት ፡ ሥፍራ ፤

(ለ) የሚሸጠው ፡ ሰብል ፡ ከእርሻው ፡ ላይ ፡ ታጭዶ ፡ የተከ መረ ፡ ወይም ፡ የድርቆሽ ፡ ክምር ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ለመወ ቃት ፡ ወይም ፡ ለምርት ፡ የተዘጋጀ ፡ ሲሆን ፡ ክምሩ ፡ ወይም ፡ የማ ምረቻው ፡ ውድማ ፡ በሚገኝበት ፡ ሥፍራ ፤ ስለሆነም ፡ ሰብሉ ፡ የተሻለ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ ገበያ ፡ ወጥቶ ፡ ወይም ፡ ምቹ ፡ በሆነ ፡ ሥፍራ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

BACK



**ቊ ፡ ፬፻፴፫ ። ቡቃያ ፡ ለሆኑ ፡ ሰብሎች ፡ ስለሚጸና ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ።**

(፩) የሚሸጠው ፡ ሰብል ፡ ቡቃያ ፡ ሲሆንና ፡ በወቅቱም ፡ ተሰብስቦ፡ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ ለማከማቸት ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፤ ሽያጩ ፡ የሚ ፈጸምበት ፡ ቀን ፡ የሚወሰነው ፡ ሰብሉ ፡ ከተሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ ባለው ተከታይ ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ ሰብሉ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተከማችቶ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ ሽያጩ ፡ አይፈጸምም ።

(፪) የሰብሉ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሁኔታ ፡ ተሰብስቦ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ለመከ ማቸት ፡ የሚያስችለ ፡ ሲሆን ፡ ከመታጨዱ ፡ ወይም ፡ ተቆርጦ ፡ ወይም ፡ ተነቅሎ ፡ ከመሰብሰቡ ፡ በፊት ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይቻላል ። ገዢውም ፡ ሰብሉ ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ገብቶ ፡ እንዲ ሰበስብ ፤ እንዲለቅም ፤ እንዲቆርጥ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊውን ፡ የጥ በቃ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲያደርግ ፡ ይፈቀድለታል ።

**ቊ ፡ ፬፻፴፬ ። ስለ ፡ ተዘዋዋሪ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ድርጅት፡ አክሲዮኖች ።**

በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት፡ የሚሸጠው፡ ሀብት ፡ ተዘዋዋሪ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ አክሲዮን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደሆነ ፡ በሐራጅ ፡ በመሸጥ ፡ ፋንታ ፡ በደላላ ፡ አማካይነት ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፬፻፴፭ ። የሽያጩ ፡ ሥርዓት ፡ በትክክል ፡ ያለመፈጸም ፡ ሽያጩን ፡ ስለሚያፈርስበት ፡ ሁኔታ ።**

የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ በሚወጣው ፡ ማስታወ ቂያ ፡ ላይ ፡ ጉድለት ፡ በመገኘቱ ፡ ወይም ፡ የሽያጩ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ በትክክል ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ማናቸውም ፡ የሚንቀ ሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሽያጭ ፡ አይፈርስም ፤ ስለሆነም ፡ በሥርዓቱ ፡ መጓደል ፡ ምክንያት ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለ ጉዳቱ ፡ አላፊ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ተገቢ ፡ ካሣ ውን ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፡ ለጉድለቱ ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ገዢው ፡ ራሱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የገዛውን ፡ ዕቃ ፡ እንዲመልስ ፡ ወይም ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍል ፡ ይወሰንበታል ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፯ ። ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረትን ፤ ዕዳንና ፡ አክሲዮንን ፡ ለገዢው ፡ ስለማስረከብ ።**

(፩) የተሸጠው ፡ ሀብት ፡ ከፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የተያዘና ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሲሆን ፤ ገዢው ፡ ራሱ ፡ ንብረቱን ፡ እንዲረከብ ፡ ይደረጋል ።

(፪) የተሸጠው ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የማስረከቡ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸመው ፡ የንብረቱ ፡ ባለይዞታ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ለገዢው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳያስረክብ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

(፫) የተሸጠው ፡ ንብረት ፡ በንግድ ፡ ድርጅት ፡ የተመዘገበ ፡ አክሲዮን ፡ ሲሆን ፤ አክሲዮኑን ፡ በስሙ ፡ ያስመዘገበው ፡ ሰው ፡ ለገዢው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ እንዳይሸጥ ፡ ወይም ፡ የሚገኘውን ፡ ማናቸውንም ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ ለሌላ ፡ ተላልፎ ፡ እንዳይሸጥ ፡ በመከልከል ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅቱ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ ወይም ፡ የድርጅቱ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ የአክሲዮኑን ፡ ባለቤትነት ፡ ወይም፡ የሚገኘውን ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ ለገዢው ፡ ካልሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳያስተላልፉ ፡ ትእዛዝ ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፰ ። የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ አክሲዮኖች ፡ የሚዛወሩበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችን ፡ ወይም ፡ አክሲዮኖችን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ለማዛወር ፤ ሰነዶቹን ፡ ወይም ፡ አክሲዮኖቹን፡ በሌላ ፡ ያስመዘገበው ፡ ሰው ፡ ፊርማ ፡ ወይም ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፩ /፪/ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ፤ ይህም ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ የመፈረሙና ፡ የማስተላለፉ ፡ ሥርዓት ፡ በባለ ፡ ሀብቱ ፡ እንደተፈጸመ ይቆጠራል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገሩት ፡ ሰነዶች ፡ ወይም ፡ አክሲዮኖች ፡ በገዢው ፡ ስም ፡ እስኪዛወሩ ፡ ድረስ ፡ ከነዚህ ፡ የሚገኘውን ፡

ጥቅም ፡ ወይም ፡ ሰነድ ፡ እየፈረመ ፡ የሚቀበል ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊሾም ፡ ይችላል ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተወከለው ፡ ሰው ፡ ስለተቀበለው ፡ ገንዘብ ፡ የፈረመው ፡ ደረሰኝ ፡ በነገርው ፡ ወይም ፡ በባለመብቱ ፡ እንደተፈረመ ፡ ይቆጠራል ።

ቍ ፡ ፬፻፴፰ ፡- ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ ስለሚተላለፍበት ፡ ሁኔታ ፤

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያልተጠቀሰ ፡ ማናቸውም ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንደተላለፈ ፡ የሚቆጠረው ፤ ለነገርው ፡ ወይም ፡ ለወኪሉ ፡ ወይም ፡ እንዲረከብ ፡ ላደረገው ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካዘዘበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

## ን ዑ ስ ፡ ክ ፍ ል ፡ ፮.

## የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ስለሚሸጥበት ፡ ሁኔታ ፤

ቍ ፡ ፬፻፴፱ ። የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የተፈረደበትን ፡ ገንዘብ ፡ እስኪያዘጋጅ ፡ ሽያጩን ፡ ስለማቆየት ።

(፩) የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ ከታዘዘ ፡ በኋላ ፡ የፍርድ፡ ባለዕዳው ፡ ይህንኑ ፡ ንብ ረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በማከራየት ፤ በዋስትና ፡ በመስጠትና ፡ በማስያዝ ፤ ወይም ፡ በግል ፡ በመሸጥ ፤ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በመሸጥ ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊቀበለው ፡ በሚችል ፡ ሁኔታ ፡ ሲያመለክት ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፮ /፫/ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ይህን ፡ ለማከናወን ፡ በቂ ፡ መስሎ ፡ የሚገምተውን ፡ ጊዜ ፡ ለመስጠትና ፡ እንዲሸጥ ፡ የታዘዘውም ፡ ንብረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው ፡ ሁኔታ ፡ ከመሸጡ ፡ እንዲቆይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፮ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረውን ፡ ትእዛዝ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፤ የተወሰነውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ራሱ ፡ እንዲሸጠው ፤ እንዲያከራየው ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ እንዲያስይዘው ፡ በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ፈቃድ ፡ ይሰጠዋል ። ስለሆነም ፡ በዚሁ ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡

BACK



ንብረቱ ፡ የተሸጠበት ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ የተከራየበት ፡ ገቢ ፡ ወይም፡ በዋስትና ፡ የተያዘበት ፡ ገንዘብ ፡ በቀጥታ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዘንድ፡ ተቀማጭ ፡ እንዲሆን ፡ ይደረጋል ፤ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡም ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፴ / ፪ / በተነገረው ፡ መሠረት ፡ እንደነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ የሂሣብ ፡ መቻቻል ፡ ከማድረግ ፡ አይታገድም ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚደረገው ፡ የንብረት መሸጥ ፤ ማከራየት ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ማስያዝ ፡ ውል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካላጸደቀው ፡ በቀር ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

በዋስትና ፡ ወይም ፡ በዕዳ ፡ የተያዙ ፡ ንብረቶች ፤ የተያዙበትን ፡ ግዴታ ፡ ለማስፈጸም ፡ በሚሸጡበት ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

## ቍ ፡ ፬፻፵ ። ገዢ ፡ ስለሚያስቀምጠው ፡ መያዣና ፡ ሙሉ ፡ ገንዘብ ፡ ባለመከፈሉ ፡ ስለሚደረግ ፡ ሺያጭ ።

(፩) ማናቸውም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በሚሸጥበት ፡ ጊዜ ፡ ገዢው ፡ የንብረቱ ፡ ገዢነት ፡ መብት ፡ እንደታወቀለት ፡ ወዲያውኑ ፡ ከንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ውስጥ ፡፳፭/ ሃያ ፡ አምስ ፡ በመቶውን ፡ ሂሣብ ፡ ለሃራጅ ፡ ሻጭ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

(፪) ገዢው ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፴ /፪/ የተነገረው ፡ መቻቻል ፡ ስለሚደረግ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ አድሆንም ።

## ቍ ፡ ፬፻፵፩ ፡-ዋጋው ፡ በሙሉ ፡ ስለሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፤

በሐራጅ ፡ የተሸጠው ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ የሚከፈለው ፡ ገዢው ፡ ንብረቱን ፡ መግዛቱ ፡ ከተረጋገጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ስለሆነም ፡ ጠቅላላው ፡ ዋጋ ፡ በሚተሳሰብበት ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፴ /፪/ መሠረት ፡ ስለመቻቻል ፡ የተነገረው ፡ መብት ፡ ሲኖር ፡ እንደተጠበቀ ፡ ይሆናል።

## ቍ ፡ ፬፻፵፪ ። ዋጋው ፡ ሳይከፈል ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡

BACK



የንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ሳይከፈል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ ገዢው ፡ አስይዞት፡ ከነበረው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ለሽያጩ ፡ ሥርዓትና ፡ ለማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ ወጭ ፡ የተደረገው ፡ ገንዘብ ፡ ተቀንሶ ፡ የቀረው ፡ ገንዘብ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ እንዲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ንብረቱም ፡ እንደገና ፡ እንዲሸጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግዴታውን ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀረው ፡ ገዢ ፡ በ ሽያጩ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በተሸጠው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ መብት ፡ ያጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፵፫ ። በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ መብት ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ስለሚሰጠው ፡ የተቀዳሚነት ፡ መብት ።

በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ ተይዞ ፡ የሚሸጠው ፡ የማይን ቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በሕብረት ፡ የያዙትና ፡ ያልተከፋፈሉት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከተካፋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ንብረቱን ፡ ለመግዛት ፡ በጨረታ ፡ ተወዳዳሪ፡ ሆኖ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እንደቀረበ ፡ ተቆ ጥሮ ፡ የተቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ።

ቍ ፡ ፬፻፵፬ ። ሽያጭ ፡ እንዲከበር ፡ ወይም ፡ እንዲቀር ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማ መልከቻ ።

(፩) በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲሸጥ ፡ የተወሰነው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከመሸጡ ፡ በፊት ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ያገኘ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሽያጩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲታ ገድ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከት ፡ ይችላል ።

(፪) ቢሆንም ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፰ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ሽያጩ ፡ እንዲታገድ ፡ ወይም ፡ እንዲፈርስ ፡ የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ካላነሳ /ካልሠረዘ/ በቀር ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

(፫) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ መክፈል ፡ የሚገባውን ፡ ወጭና ፡ ኪሣራ ፡ በማስታወቂያው ፡ ላይ ፡ ያልተገለጸ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ሁሉ ፡ ከመክፈል ፡ ነፃ ፡ አያ ደርገውም ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፮ ። የሽያጩ ፡ ሥርዓት ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ በማጭበርበር ፡ ተፈጽሟል ፡ በማለት ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲታገድ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ።**

በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የተሸጠ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ወይም ፡ ከሽያጩ ፡ ገንዘብ ፡ ድርሻ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የንብረቱ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ በንብረቱ ፡ መሸጥ ፡ ምክንያት ፡ መብቱ ፡ የሚነካ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በአሻሻጡ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ ጉድለት ፡ ወይም ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነ ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ የማታለልና ፡ የማጭበርበር ፡ ተግባር ፡ ተፈጽሟል ፡ በማለት ፡ ሽያጩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲታገድ ፡ ማመልከቻ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ የተጠቀሰው ፡ ተግባር ፡ በአመልካቹ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ቀጥታ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ መሆኑ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ሽያጩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲታገድ ፡ ለማዘዝ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፯ ። የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በተሸጠው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ሽያጩ ፡ ስለሚፈርስበት ፡ ሁኔታ ።**

በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የተሸጠውን ፡ ንብረት ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ ሽያጩ ፡ እንዲፈርስለት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፵፰ ፦ ሽያጩ ፡ ስለሚጸናበት ፡ ወይም ፡ ስለሚሠረዝበት ፡ ሁኔታ ፤**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፬፻፵፬ እስከ ፡ ፬፻፵፯ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሽያጩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲሠረዝ ፡ ማመልከቻ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ግዢው ፡ ሊፈርስ ፡ አይችልም ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ ማመልከቻ ፡ ቀርቦ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያጣ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግዢው ፡ የማይፈርስ ፡ መሆኑን ፡ ይወስናል ።

(፫) በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ግዢው ፡ የጸደቀ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የንብረቱን ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታ ፡ የሚጠቅስና ፡ በሽያጩም ፡

ላይ ፡ ገዢ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የሚገልጽ ፡ ሽያጩም ፡ የማ ይሻር ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ለገዢው ፡ ይሰጣል ።

(፪) ማመልከቻው ፡ ተቀባይነትን፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ሽያጩ ፡ እንዲ ፈርስ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። ስለሆነም ፡ በጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ላላቸው፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ አይሰጥም ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት፡ ሽያጩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ የንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ከነወለዱ ፡ ወይም ፡ እንደነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ያለወ ለድ ፡ ገንዘብ ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፡ ለገዢ ፡ እንዲመልስለት ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፵፰ ። በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ ስለማስረ ከብ ።</u>

የማሸጠው ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በተሰጠው ፡ መብት ፡ መሠረት ፡ ባለይዞታ ፡ በሆነ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ በፍርድ ፡ ከተያዘ ፡ በኋላ ፡ መብት ፡ አግኝቻለሁ ፡ በማለት ፡ ባለይዞታ ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ ሲሆንና ፡ ስለዚሁም ፡ ጉዳይ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፯ ፡

(፪) በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ማረጋገጫ ፡ የተሰጠ ፡ ሲሆን ፡ ይህ ንን ፡ ሁኔታ ፡ ገገርው ፡ ባመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ የወከለው ፡ እንዲረከብና ፡ በንብረቱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ንብረቱን ፡ አላስረክብም ፡ በማለት ፡ እምቢተኛ ፡ ሆኖ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ እንዲወጣ ፡ ያዛል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፵፱ ። በተከራይ ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ ስለማስረከብ ።</u>

የተሸጠው ፡ ንብረት ፡ በኪራይ ፡ ስም ፡ በያዘ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በተጨማሪም ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፯ (፪) መሠረት ፡ ይህንኑ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተሰጠ ፡ ሲሆን ፡ በገዢው ፡ አመልካችነት ፡ ይህ ፡ ንብረት ፡ የተሸጠለት ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ንብረቱ ፡ በሚገኝበት ፡ በግልጽ ፡

BACK



ቦታ ፡ ላይ ፡ እንዲለጠፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ። እንዲሁም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ መብትና ፡ ይዞታ ፡ ለገዢው ፡ የተላለፈለት ፡ መሆኑን ፡ ሕዝብ ፡ ሊያውቀው ፡ በሚችል ፡ በማናቸውም ፡ ልማዳዊ ፡ ዘዴ ፡ በአደባባይ ፡ እንዲነገር ፡ ያደርጋል ።

## ክ ፍ ል ፡ ፬ ፡

## ማስረከብን ፡ ስለመቃወም ፡ ወይም ፡ በእምቢተኛነት ፡ ስለመጋፋት ።

### ቍ ፡ ፬፻፺ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ለማስረከብ ፡ እምቢተኛ ፡ ስለመሆንና ፡ መሰናከል ፡ ስለመፍጠር ።

(፩) በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ የተሸጠ ፡ ንብረት ፡ እንዲረከብ ፡ በፍርድ፡ የታዘዘለት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ እንዳይረከብ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ የመቃወም ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ የማሰናከል ፡ ተግባር ፡ የደረሰበት ፡ እንደሆነ ፡ ያጋጠመውን ፡ ችግር ፡ የሚገልጽ ፡ ማመልከቻውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀን ፡ ወስኖ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበባቸው ፡ ወገኖች ፡ ቀርበው ፡ መልስ ፡ እንዲሰጡና ፡ ነገሩ ፡ እንዲመረመር ፡ ያደርጋል ።

### ቍ ፡ ፬፻፺፩ ። የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ስለሚፈጥረው ፡ መሰናከል ፡ ወይም ፡ የተቃዋሚነት ፡ ተግባር ።

የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ አነሳሺነት ፡ በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ የተሸጠውን ፡ ንብረት ፡ ገዢው ፡ እንዳይረከብ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ በማይገመት ፡ ምክንያት ፡ የተቃወመ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ መሠናከል ፡ የፈጠረ ፡ እንደሆነ ፤ ለፍርድ ፡ ቤቱ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ አመልካቹ ፡ ንብረቱን ፡ በቀጥታ ፡ እንዲረከብ ፡ ያዛል ። ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ በተረካቢው ፡ ላይ ፡ የመቃወምና ፡ የማሰናከል ፡ ተግባር ፡ የቀጠለ ፡ እንደሆነ ፡ ተረካቢው ፡ ይህንኑ ፡ ሲያመለክት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ አነሳሽነት ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ የፈጸመው ፡ ሰው ፡ ከሰላሳ ፡ ቀን ፡ ለማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ታሥሮ ፡ እንዲቆይ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፪ ። በቅን ፡ ልቦና ፡ ባለመብት ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ርክክቡን ፡ ስለሚ ቃወም ፡ ሰው ።**

የተሸጠውን ፡ ንብረት ፡ ርክክብ ፡ የተቃወመው ፡ ወይም ፡ ያሰና ከለው ፡ የንብረቱ ፡ የቅን ፡ ልቦና ፡ ባለይዞታ ፡ ሲሆንና ፡ ይዞታው ንም ፡ ያገኘው ፡ ከፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሳይሆን ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ በተ ላለፈለት ፡ መብት ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በተቃዋሚነቱ፡ ወይም ፡ መሰናከል ፡ በመፍጠሩ ፡ ምክንያት ፡ የቀረበበትን ፡ አቤ ቱታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተቀብሎ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ማመልከቻ ውን ፡ ሊሠርዘው ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፫ ። በፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ወይም ፡ በገዢው ፡ ስለሚፈጸም ፡ የይ ዞታ ፡ ማስለቀቅ ፡ ተግባር ።**

(፩) የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ የገዛው ፡ ሰው ፡ በተ ሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ባገኘው ፡ የንብረት ፡ መረከብ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ያገኘውን ፡ ወይም ፡ የገዛውን ፡ ንብረት ፡ ያስለቀቀው ፡ ከፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ሳይሆን ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ በሌላ ፡ ሁኔታ ፡ ባለ ፡ ይዞታ ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ፡ ንብረቱን ፡ እንዲለቅ ፡ የተገደደ ፡ ወገን ፡ ይህንኑ ፡ በመቃወም ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ሲቀርብለት ፡ ነገሩ ፡ የሚሰማበትን ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፡ ወስኖ ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበባቸው ፡ ወገኖች ፡ ተጠርተው ፡ መልስ እንዲሰጡ ፡ ያዛል ።

(፫) አመልካቹ ፡ የንብረቱ ፡ ባለ ፡ ይዞታ ፡ የሆነው ፡ በራሱ ፡ ባለመ ብትነት ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ በተላለፈለት ፡ መብት ፡ መሠረት፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ይዞታው ፡ እንዲ መለስ ፡ ሊያዝለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፶፬ ። ነገሩ ፡ በፍርድ ፡ እስኪወሰን ፡ ድረስ ፡ መብት ፡ በተላለፈለት ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ደንቡ ፡ የማይጸናበት ፡ ስለመሆኑ ።**

በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ቀርቦ ፡ ክርክር ፡ ከተጀ መረ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ በፍርድ ፡ ከመወሰኑ ፡ በፊት ፡ የንብረቱ ፡ መብት ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ የሚደረገውን ፡ ርክክብ ፡ ተቃውሞ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡

BACK



በቍጥር ፡ ፩፻፶፪ እና ፩፻፶፫ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ ሊጠቀም ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፩፻፶፭ ፡- ስለ ፡ ትእዛዙ ፡ ተፈጻሚነት ፤**

የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ ያልሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፶፩—፩፻፶፪ ወይም ፡ ፩፻፶፫ /፫/ የተመለከተው ፡ ውሳኔ የተሰጠበት ፡ እንደሆነ ፡ በንብረቱ ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የተለየ ፡ ክስ ፡ ከማቅረብ ፡ አይታገድም ። ስለሆነም ፡ ለቀረበው ፡ ክስ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንቶ ፡ ይቆያል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፤

## በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ፤

**ቍ ፡ ፩፻፶፮ ፡- መሠረቱ ፤**

(፩) በኢንቴርናሲዮናል ፡ ስምምነት ፡ በተለየ ፡ እንዲፈጸም ፡ የሚደረግ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውጭ ፡ የተሰጠ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ የሚፈጸመው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) እንዲፈጸም ፡ ማመልከቻ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ የተነገረው ፡ ማመልከቻ ፡ የሚቀርበው ፡ ፍርዱ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ላስቻለው ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩፻፶፯ ። ስለማመልከቻው ፡ ፎርም ።**

በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ብይን ፤ እንዲፈጸም፡ የሚቀርበው ፡ የጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ በአባሪነት ፡ መያዝ ፡ አለበት ።

(ሀ) የሚፈጸመው ፡ ፍርድ ፡ የተወሰነበት ፡ ትክክለኛነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ የፍርድ ፡ ግልባጭ ፤

BACK



(ለ) ፍርዱ ፡ የመጨረሻ ፡ መሆኑና ፡ መፈጸም ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ በፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ወይም ፡ በሬጅስትራሩ ፡ የተፈረመ ፡ የምስክርነት ፡ ጽሑፍ ።

ቍ ፡ ፬፻፶፰ ። ማመልከቻው ፡ ስለሚፈቅድበት ፡ ሁኔታ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ካልተረጋገጡ ፡ በቀር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ።

(ሀ) እንዲፈጸም ፡ የተጠየቀውን ፡ ፍርድ ፡ የወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገኝበት ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድም ፡ የሚፈጸም ፡ መሆኑ ፡ ሲረጋገጥ ፤

(ለ) ፍርዱ ፡ የተሰጠው ፡ በሕግ ፡ በተቋቋመ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፤

(ሐ) የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ቀርቦ ፡ መቃወሚያውን ፡ ለማሰማት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑ ፡ ሲረጋገጥ ፤

(መ) ፍርዱ ፡ የመጨረሻና ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፤

(ሠ) የፍርዱ ፡ መፈጸም ፡ ለሕዝብ ፡ ሞራልና ፡ ጸጥታ ፡ ተቃራኒ ፡ ያለመሆኑ ፡ ሲታወቅ ፤

ቍ ፡ ፬፻፶፱ ። የአፈጻጸሙ ፡ ሥርዓት ።

(፩) ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ማመልከቻ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ቀርቦ ፡ አስተያየቱን ፡ እንዲገልጽ ፡ መብት ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) ይህም ፡ ሲሆን ፤ ለቀረበው ፡ መቃወሚያ ፡ ክርክር ፡ ወይም ፡ ሙግት ፡ የሚሰማ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይወስናል ።

(፫) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ ያጋጠመ ፡ እንደሆነ ፡ ጥርጣሬ ፡ ያስከተሉት ፡ ነጥቦች ፡ እስኪጣሩ ፡ ድረስ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ውሳኔ ፡ ታግዶ ፡ ይቆያል ።

**ቍ ፡ ፬፻፰ ። ስለውሳኔ ።**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበለትን ፡ ጉዳይ ፡ ለማጣራት ፡ ተከራካሪ ዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ቀርበው ፡ ክርክራቸውን ፡ መስማት ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆንበትን ፡ ምክንያት ፡ መዝግቦ ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ካልወሰነ ፡ በቀር ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ በቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ስለኪሣራና ፡ ስለማናቸውም ፡ ወጭ ፡ አከፋፈል ፡ ጉዳይ ፡ ወዲያውኑ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ ተቀብሎ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈ ጸም ፡ የወሰነ ፡ እንደሆነ ፤ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዓት ፡ የሚመ ራው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተሰጠ ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ በሚፈጸም በት ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፰፩ ። በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ብይን ፡ ስለሚፈጸምበት ፡ ሁኔታ ።**

(፩) በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ብይን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ።

(ሀ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፰ ፡ (ሀ) በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ብይኑ ፡ በተሰጠበት ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተሰጠውም ፡ ብይን ፡ የሚፈጸም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ።

(ለ) ብይኑ ፡ የተሰጠው ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ለግልግል ፡ ወይም ፡ ለሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ጉባዔ ፡ ባቀረቡት ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ የተሰጠበት ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅ ደው ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ።

(ሐ) ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የግልግል ፡ ወይም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞችን ፡ ለመምረጥ ፡ የእኩልነት ፡ መብት ፡ ተሰጥቷቸው ፡ እንደ ሆነ ፡ ወይም ፡ በክርክሩ ፡ ላይ ፡ ማስረጃቸውን ፡ ለማቅረብና ፡ ክር ክራቸውንም ፡ ቀርበ ፡ ለማስማት ፡ የእኩልነት ፡ መብት ፡ አግኝ ተው ፡ እንደሆነ ፤

(መ) የግልግሉ ፡ ወይም ፡ የሽምግልናው ፡ ዳኝነት ፡ ጉባዔ ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ተቋቁሞ ፡ እንደሆነ ፤

(ሠ) ብይኑ ፡ የተሰጠበት ፡ ጉዳይ ፡ በኢትዮጵያም ፡ ሕግ ፡ በግልግል ፡ ወይም ፡ በሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ሊታይ ፡ የሚችል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነና ፡ የፍርዱም ፡ አፈጻጸም ፡ የሕዝብን ፡ ሞራልና ፡ ጸጥታ ፡ የማይቃወም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤

(ረ) የተሰጠው ፡ ብይን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በሚያዘውና ፡ በሚፈቅደው ፡ ሁኔታ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ።

(፪) በውጭ ፡ አገር ፡ ስለተሰጡ ፡ ፍርዶች ፡ አፈጻጸም ፡ የተመለከተው ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተነገሩት ፡ ብይኖች ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

# ስምንተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለወጭና ፡ ስለኪሣራ ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ፤

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፪ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ።

በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ በግልጽ ፡ ካልተደነገገ ፡ በቀር ፡ በክስ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚከፈለው ፡ ስለማናቸውም ፡ ወጭና ፡ ኪሣራ ፤ የሚከፍለውን ፡ ወገን ፡ የወጭንና ፡ የኪሣራውን ፡ ልክ ፡ የሚከፈልበትን ፡ የሃብት ፡ ምንጭ ፡ የአከፋፈሉን ፡ ሁኔታ ፡ ሌላውንም ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትክክል ፡ መስሎ ፡ በሚገምተው ፡ ሁኔታ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፬፻፷፫ ። ስለወጭና ፡ ስለኪሣራ ፡ ዝርዝር ።

(፩) ተረቺው ፡ ለረቺው ፡ ኪሣራና ፡ ማናቸውንም ፡ ወጭ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያዝ ፤ ወጭ ፡ ያደረገው ፡ ወገን ፡ የወጭውን ፡ ልክ ፡ የሚያሳይ ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጅቶ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ዝርዝሩ ፡ የሚቀርበው ፡ ፍርዱን ፡ ለፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲሆን ፡ አንዱ ፡ ግልባጭ ፡ ለነፋዩ ፡ ወገን ፡ ይሰጣል ፡

ቍ ፡ ፬፻፷፬ ። የወጭው ፡ ሂሳብ ፡ ስለሚመረመርበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) የወጭው ፡ ሂሳብ ፡ ዝርዝር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ትክክለኛነቱ ፡ የሚመረመርበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ወስኖ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ያዛል ።

(፪) ሂሳቡን ፡ መርምሮና ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ሃሳብ ፡ ተቀብሎ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ይፈጽማል ።

(ሀ) በቀረበው ፡ የሂሳብ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚታየውን ፡ ገንዘብ ፡ ይቀንሳል ። ወይም

(ለ) በዝርዝሩ ፡ ውስጥ ፡ የክሱን ፡ ጉዳይ ፡ ለማስፈጸም ፡ ወይም ፡ አስፈላጊውን ፡ ዳኝነት ፡ ለመከታተል ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ወጭ ፡ ተመልክቶበት ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊቀንሰው ፡ ወይም ፡ ሊያስቀረው ፡ ይችላል ።

(፫) ወጭው ፡ ወይም ፡ ኪሣራው ፡ ሊከፈለው ፡ የሚገባው ፡ ወገን ፡ የሚጠይቀውን ፡ የወጭ ፡ ዝርዝር ፡ ያላቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህንኑ ፡ መዝግቦ ፡ ሌሎቹ ፡ ወገኖች ፡ ያደረጉትን ፡ ወጭ ፡ መርምሮ ፡ ያረጋግጥላቸዋል ። ወይም ፡ የሂሳቡን ፡ ዝርዝር ፡ አንዱ ወገን ፡ ባለማቅረቡ ፡ ምክንያት ፡ ሌሎቹ ፡ ወገኖች ፡ እንዳይጐዱ ፡ ላላቀረበው ፡ ወገን ፡ ተገቢ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ ኪሣራ ፡ ይወሰንለታል ።

(፬) ማናቸውም ፡ የወጭ ፡ ወይም ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ዋናው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ወለድ ፡ ይታሰብበታል ።

(፭) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በኪሣራና ፡ በወጭ ፡ አከፋፈል ፡ ምክንያት ፡ ለተነሳው ፡ ክርክር ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሬጂስትራር ፡ ወይም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የቀረበውን ፡ ዝርዝር ፡ መርምሮና ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ አሳብ ፡ ተቀብሎ ፡ የተጣራውን ፡ ሂሳብ ፡ እንዲያቀርብለት ፡ ከማዘዝ ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ አያግደውም ።

ቍ ፡ ፪፻፳፩ ። ካሣ ፡ ስለሚከፈልበት ፡ ምክንያት ።

(፩) በማናቸውም ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ በክስ ፡ ወይም ፡ በመከላከያ ፡ መልክ ፡ ከሳሹ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ያቀረበው ፡ የመከራከሪያ ፡ ወይም ፡ የመከላከያ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ ወይም ፡ ክርክሩ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ማስረጃው ፡ አሰተኛ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ መከራከሪያውንና ፡ ማስረጃውን ፡ ያቀረበው ፡ ወገን ፡ በሐሰት ፡ የተከራከረውና ፡ አሰተኛ ፡ ማስረጃ ፡ ያቀረበው ፡ ክርክሩን ፡ ለማሰናከል ፤ ጊዜ ፡ ለመፍጀት ፡ ወይም ፡ አንደኛውን ፡ ወገን ፡ ለመበደል ፡ ጐይም ፡ ለማጉላላት ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ያደረገው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ የክርክሩንና ፡ የማስረጃውን ፡ አሰተኛነት ፡ እያወቀ ፡ ወይም ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ማቅረቡን ፡ ሲያመለክትና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ተቃዋሚው ፡ ወገን ፡ ያቀረበውን ፡ ነገር ፡ እርግጠኛነት ፡ ሲረዳው ፡ ይህንኑ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ አስፍሮ ፡ ሃሰተኛ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ መከላከያ ፡ ያቀረበው ፡ ወገን ፡ ላቀረበው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሃሰተኛ ፡ ማስረጃ ፡ አንዱን ፡ ወገን ፡ ለመበደል ፤ ለማጉላላት ፡ ወይም ፡ ጊዜ ፡ ለመፍጀት ፡ ላቀረበው ፡ አሰተኛ ፡ ክርክር ፡ ከማናቸውም ፡ ኪሣራና ፡ ከሌላው ፡ ወጭ ፡ በቀር ፡ ከ፭፻ ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ካሣ ፡ ለተበዳዩ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠበት ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፮ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ሃሰተኛ ፡ ማስረጃና ፡ ክርክር ፡ በማቅረቡ ፡ ከመከሰስና ፡ ከመቀጣት ፡ ነፃ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ካሣ ፡ የተወሰነለት ፡ ወገን ፡ በሃሰት ፡ በመከሰሱ ፡ ወይም ፡ ሃሰተኛ ፡ መከላከያ ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ የቀረበበት ፡ በመሆኑ ፡ ካሣና ፡ ኪሣራ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ ሌላ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ የተወሰነለት ፡ እንደሆነ ፡ በመጀመሪያው ፡ ክስ ፡ የተወሰነለት ፡ ካሣ ፡ በሌላው ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ከሚወሰንለት ፡ ኪሣራና ፡ ካሣ ፡ ላይ ፡ ይቀነስስበታል ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፯ ። ስለ ፡ ይግባኝ ።**

ማናቸውም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በሥረ ፡ ነገሩ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ባያቀርብም ፤ በተወሰነበት ፡ የወጭ ፡ ወይም ፡ የኪሣራ ፡ አከፋፈል ፡ ብይን ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ ነገር ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የመጨረሻ ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፤

## ዳኝነት ፡ ሳይከፈልበት ፡ በነፃ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፰ ። በነፃ ፡ ስለሚከፈቱ ፡ ክሶች ።**

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ገንዘብ ፡ የሌለውና ፡ ለማግኘት ፡ የማይችል ፡ ማናቸውም ፡ ድኃ ፡ ሰው ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፍል ፡ ነፃ ፡ ፋይል ፡ ከፍቶ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) ደሀ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀለት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለመክፈል ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የነፃ ፡ ፋይል ፡ ከፍቶ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ለማመልከት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፱ ። በሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ስለሚገለጹ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ።**

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) በተነገረው ፡ መሠረት ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ከዚሁ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ሰስተኛ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ሆኖ ፡ በተያያዘው ፡ ፎርም ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በዚሁ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ በተመለከተው ፡ ዓይነት ፡ በመሐላ ፡ ቃል ፡ ተደግፎ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) ማመልከቻው ፡ የሚቀርበው ፡ በአመልካቹ ፡ ወይም ፡ በወኪሉ ፡ ሆኖ ፡ ከክሱ ፡ አቤቱታ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። አመልካቹ ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ማመልከቻው ፣ በሚገባ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲቀርብ ለት ፤ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ስለተገለጸው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ስለአመ ልካቹ ፡ የሀብት ፡ ሁኔታ ፤ ስለማመልከቻው ፡ ተገቢነት ፡ አስፈ ላጊ ፡ የሆነውን ፡ መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ አመልካቹን ፡ ወይም ፡ ወኪ ሉን ፡ ጠርቶ ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ።

(፪) ማመልከቻው ፡ የቀረበው ፡ በወኪሉ ፡ አማካይነት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመልካቹ ፡ ራሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ወይም ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ በተተኪ ፡ ዳኛ ፡ እንዲመረምር ያዛል ።

(፫) ማመልከቻው ፡ በሚገባ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ያልቀረበ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ወዲያውኑ ፡ ተሻሽሎ ፡ እንዲቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፸ ። ማመልከቻው ፡ ተቀባይነትን ፡ ስለማያገኝበት ፡ ሁኔታ ።

ማመልከቻው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፷፱ ፡ እና ፡ በ፪፻፸፩ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ በተደረገው ፡ ምርመራ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱትን ፡ ነገሮች ፡ ያስረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ተቀባይነትን ፡ አያገኝም ።

(ሀ) አመልካቹ ፡ ድኃ ፡ ያለመሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፤

(ለ) በነፃ ፡ ለመክሰስ ፡ ያቀረበው ፡ ነገር ፡ የማያስከስስ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤

(ሐ) ክስ ፡ ከማቅረቡ ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ንብ ረት ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ አስተላልፎ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በማጭበር በር ፡ መንገድ ፡ ንብረቱን ፡ አዛውሮ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ዳኝነት ፡ ከመክፈል ፡ ለመዳን ፡ ዘዴ ፡ ፈጥሮ ፡ እንደሆነ ፤

(መ) ክርክር ፡ በሚያቀርብበት ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ መብት ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ እንዲጠቀም ፡ ወይም ፡ ማናቸው ንም ፡ መብት ፡ እንዲያገኝ ፡ ተዋውሎ ፡ ወይም ፡ ተስማምቶ ፡ የተ ገኘ ፡ እንደሆነ

<u>ቍ ፡ ፪፻፸፩ ። የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፈል ፡ በነፃ ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ ለመ ክፈት ፡ የሚቀርበውን ፡ ጥያቄ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለሚመረምርበት ፡ ሁኔታ ።</u>

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ባደረገው ፡ ምርመራ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ የሚነቅፍበት ፡ ምክንያት ፡ ያላገኘ ፡ እንደሆነ ፡ አመልካቹ ፡ ድኃ ፡ ስለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ እንዲሁም ፡ ሃብት ፡ አለው ፡ የሚሉ ፡ ሌሎች ፡ ወገኖች ፡ እንዳሉ ፡ ቀርበው ፡ እንዲያስረዱ ፡ ነገሩ ፡ የሚመረመርበትን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ የሚሰጠው ፡ ቀጠሮ ፡ ከመድረሱ ፡ ካስር ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ለባላጋራው ፡ ወይም ፡ ለተከሣሹ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲደርሰው ፡ ይደረጋል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፸፪ ። የማስረጃው ፡ አቀባበል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።</u>

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ያቀረቡለትን ፡ ምስክሮች ፡ ይሰማል ። እንዲሁም ፡ አመልካቹን ፡ ወይም ፡ ወኪሉን ፡ ሊመረምር ፡ ይችላል ። ምስክሮችንና ፡ የባለ ፡ ጉዳዮችንም ፡ ቃል ፡ ይመዘግባል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ መቃወሚያ ፡ ያቀረበው ፡ ወገን ፤ አመልካቹ ፡ ያቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፷ ፡ (ሀ) (ለ) (ሐ) መሠረት ፡ ተቀባይነትን ፡ ማግኘት ፡ የማይገባው ፡ መሆኑንና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተቀበለው ፡ ማስረጃና ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ተከራካሪዎቹም ፡ ወገኖች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ክርክር ፡ ይሰማል ።

(፫) ይህን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ አመልካቹ ፡ ዳኝነት ፡ ሳይከፍል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ጥያቄው ፡ ተቀባይነትን ፡ ያለማግኘቱን ፡ ይወስናል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፸፫ ። በነፃ ፡ የቀረበ ፡ ክስ ፡ ተቀባይነትን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።</u>

አመልካቹ ፡ ዳኝነት ፡ ሳይከፍል ፡ በነፃ ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ እንዲከፍት ፡ የተፈቀደለት ፡ እንደሆነ ፤ ማመልከቻው ፡ ተመዝግቦ ፡

ተራ ፡ ቊጥር ፡ ከተሰጠው ፡ በኋላ ፤ በነፃ ፡ እንዲከራከር ፡ የተፈቀደለት ፡ ስለመሆኑ ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ ይሰጠዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ያቀረበው ፡ ክስ ፡ ዳኝነት ፡ እንደተከፈለበት ፡ እንደማናቸውም ፡ ክስ ፡ ተቆጥሮ ፡ በመደበኛው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይመራል ። በነፃ ፡ በተከፈተና ፡ ዳኝነት ፡ በተከፈለበት ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፤ ዳኝነት ፡ ሳይከፈል ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፤ እንዲከፈት ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ደኃ ፡ በመሆኑ ፤ ተገቢውን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ማንኛውንም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ መክፈል ፡ የሚገባውን ፡ ወጭ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለመክፈል ፡ ያለመቻሉ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፬፻፹፬ ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃ ፡ ስለሚጸናበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ቊጥር ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃ ፤ በነፃ ፡ እንዲታይ ፡ የተፈቀደው ፡ ክርክር ፡ የመጨረሻ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪያገኝ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ ተብሎ ፡ እስኪዘጋ ፡ ድረስ ፡ የሚጸና ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል ።

(፪) ይህ ፡ ማስረጃ ፡ የሚያገለግለው ፡ በነፃ ፡ እንዲታይ ፡ ፈቃድ ፡ ለተሰጠበት ፡ ክርክር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ በይግባኝ ፡ ደረጃ ፡ የሚጸናው ፡ በነፃ ፡ እንዲከራከር ፡ የተፈቀደለት ፡ ወገን ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ሆኖ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በተሰጠበት ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በነፃ ፡ ይግባኝ ፡ በሚልበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሊገለገልበት ፡ አይችልም ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ንውስ ፡ ቊጥር ፡ ድንጋጌ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ነፃ ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ እንዲከፍት ፡ የተፈቀደለት ፡ ድኃ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ነፃ ፡ የይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ እንዲከፍት ፡ ማመልከቻ ፡ ከማቅረብ ፡ አያግደውም ።

ቊ ፡ ፬፻፹፭ ። ዳኝነት ፡ ሳይከፍል ፡ እንዲከራከር ፡ የተፈቀደለት ፡ ድኃ ፡ በነፃ ፡ የመከራከር ፡ መብቱን ፡ ስለሚያጣበት ፡ ሁኔታ ።

(፩) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ሲያጋጥሙት ፡

ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ወገን ፡ ሲያመለክት ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለከሳሹ ፡ ማስታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ በነፃ ፡ የመከራከር ፡ መብቱ ፡ እንዲሰረዝና ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፷፫ ፡ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሠረዝ ፡ ያዛል ።

(ሀ) ክርክሩ ፡ እንዲሰማ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የማወክ ፡ የማስቸገርና ፡ የተንኰለኛነት ፡ ጠባይ ፡ ያሳየ ፡ እንደሆነ ፤

(ለ) ክርክሩ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ ሀብት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ የተገለጸበት ፡ እንደሆነና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በነፃ ፡ ዳኝነት ፡ መጠቀም ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ መቀጠል ፡ የማይገባው ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፤

(ሐ) ለክርክሩ ፡ መነሻ ፡ በሆነው ፡ ሀብት ፡ ላይ፡ ሌላ ፡ ሶስተኛ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ እንዲያገኝ ፡ ስምምነት ፡ አድርጐ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ።

(፪) የከሳሹ ፡ በነፃ ፡ የመከራከር ፡ መብት ፡ የተሠረዘው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ በ /ለ/ እና ፡ በ /ሐ/ ፊደል ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ሲሆን ፡ ከሳሹ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ የተፈቀደለት ፡ ወይም ፡ የታዘዘው ፡ ወገን ፡ ይህ ፡ መብት ፡ እንዳልተሰጠው ፡ ተቆጥሮ ፡ ተገቢውን ፡ ዳኝነትና ፡ ማናቸውንም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ይታዘዛል ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፯ ። በነፃ ፡ እንዲከራከር ፡ የተፈቀደለት ፡ ድኃ ፡ በክርክሩ ፡ በረታ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።**

ዳኝነት ፡ ሳይከፍል ፡ የክስ ፡ መዝገብ ፡ ከፍቶ ፡ በተከራከረበት ፡ ጉዳይ ፡ ተፈርዶለት ፡ ክርክር ፡ የተነሳበትን ፡ ሀብት ፡ በሚረከብበት ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ንብረቱን ፡ ለረቺው ፡ ከማስረከቡ ፡ በፊት ፡ ለመንግሥት ፡ የሚገባውን ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብና ፡ ማናቸውንም ፡ ወጭ ፡ ከሀብቱ ፡ ላይ ፡ ቀንሶ ፡ ገቢ ፡ ከደረገ፡ በኋላ ፡ ቀሪውን ፡ ሀብት ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲረከብ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፯ ። ዳኝነት ፡ ሳይከፍል ፡ በነፃ ፡ ለመሟገት ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቀባይነትን ፡ የማያገኝ ፡ ስለመሆኑ ።**

በነፃ ፡ ፋይል ፡ ከፍቶ ፡ ለመከራከር ፡ እንዲፈቀድለት ፡ መጀመሪያ ፡ ያቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነትን ፡ እንዲያጣ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ ጉዳይ ፡ በነፃ ፡ ልከራከር ፡ ብሎ ፡ የሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ተቀባይነትን ፡ እንዳያገኝ ፡ ያግደዋል ። ስለሆነም ፡ አመልካቹ ፡ ደንበኛውን ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ በዚያው ፡ ጉዳይ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ የነፃ ፡ ዳኝነት ፡ እንዲፈቀድለት ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ባለጋራው ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ ያወጣውን ፡ ኪሣራና ፡ ወጭ ፡ የከፈለ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፰ ። በነፃ ፡ ዳኝነት ፡ እንዲከራከር ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፸፫ በተነገረው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት፡ ድኃ ፡ መሆኑ ፡ ታውቆለት ፡ ዳኝነት ፡ ሳይከፍል ፡ በነፃ ፡ እንዲከራከር ፡ ተፈቅዶለት ፡ የነበረ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ በተሰጠው ፡ በአሥር ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ክርክሩ ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ ማናቸውንም ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፤ ድኃ ፡ ስለመሆኑ ፡ የምስክርነት ፡ ማስረጃ ፡ ለሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማስታወቅ ፡ በነፃ ፡ እንዲከራከር ፡ ለተፈቀደለት ፡ ጉዳይ ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ዳኝነትና ፡ የፍርድ ፡ ቤት ወጭ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። ይህን ፡ ሳያስታውቅ ፡ ወይም ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፶፮ ፡ የተመለከተውን ፡ ድንጋጌ ፡ እንደተላለፈ ፡ ተቆጥሮ ፡ ቅጣት ፡ ይወሰንበታል ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፱ ፡- ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወጭዎች ፤**

በነፃ ፡ ለመሟገት ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻና ፡ ይህንንም ፡ ጉዳይ ፡ ለመመርመር ፡ የሚያስፈልገው ፡ ማናቸውም ፡ ወጭ ፡ ሁሉ ለዳኝነት ፡ መክፈል ፡ ከሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ጋር ፡ ተጠቃሎ ፡ ይታሰባል ።

# ዘጠነኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ ፡ ድ ን ጋ ጌ ዎ ች ፡

ቍ ፡ ፬፻፹ ። ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ለማስከበር ፡ ስለተሰጠ ፡ ሥልጣን ።
የማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፤ ፍርድ ፡

ቤቱንና ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለማስከበር ፡ ማናቸውንም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ እርምጃ ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ለማስፈጸም፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ችሎት ፡ ክብር ፡ ወይም ፡ ለዳኝነቱ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ መልካም ፡ አመራር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡የሚያሳየ ውን ፡ ማናቸውንም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ በችሎቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ተቃራኒ ፡ ተግባር ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ በያዘው ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፹፩ ። በቀጥታ ፡ ሊወሰን ፡ ስለሚቻልባቸው ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮች ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፪-፬፻፵፯ ፡ ወይም ፡ ፬፻፵፯ ፡ የተመለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመተላለፍ ፡ የወንጀል ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ጥፋቱ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በያዘው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ወዲያ ውኑ ፡ ቀጥታ ፡ ቅጣት ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ፤ ስለሆነም ፡ ይህ ፡ ቅ ጣት ፡ የሚወሰነው ፤

(ሀ) በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲሆን ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ የማይ በልጥ ፡ እሥራት ፤

(ለ) በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲሆን ፡ ከሶስት ፡ ዓመት ፡ የማ ይበልጥ ፡ እሥራት ።

ቍ ፡ ፬፻፹፪ ፡-ስለ ፡ ደንቦች ፤

ይህን ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤ በተለይ ፡ የሚወጡትን ፡ ወይም ፡ እንዲወጡ ፡ የሚታዘዙትን ፡ ደንቦች ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስ ቴር ፡ ለማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፬፻፹፫ ፡-ሚኒስትሩ ፡ ደንቦችን ፡ ለማውጣት ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ፡

(፩) የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በየጊዜው ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ የሚገኙትን ፡ ደንቦች ፡ ለማውጣትና ፡ "በዚሁ ፡ ድንጋጌ ፡ " የወጡትንም፡ ለማሻሻልና ፡ ለማረም ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

ስለሆነም ፡ በሚኒስትሩ ፡ ሥልጣን ፡ የሚወጡት ፡ ደንቦች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃና ፡ የይግባኝ ፡ ደረጃ ፡ ሥልጣን ፡ የተነገሩትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቀራኒ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

(ቍጥር ፡ ፲፪—፲፰) ፡ (ቍጥር ፡ ፫፻፳፩ ፡ እና ፡ ፫፻፳፪) ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያወጣቸው ፡ ደንቦችና ፡ ማሻሻያዎች ፡ የሚጸኑት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታውጀው ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

## በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት በወጡት ሰንጠረዦች ውስጥ የሚገኙ ፎርሞች ፤

| | |
|---|---|
| አንደኛ ሰንጠረዥ | የክስ ፡ ወይም ፡ የክርክር ፡ ማቅረቢያ ፡ ፎርሞች ፤ |
| ሁለተኛ ሰንጠረዥ | የሥርዓት ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ፎርሞች ፤ |
| ሦስተኛ ሰንጠረዥ | ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ፎርሞች ፤ |
| አራተኛ ሰንጠረዥ | የትእዛዝና ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ፎርሞች ፤ |
| አምስተኛ ሰንጠረዥ | የተጨማሪ ፡ እርምጃዎች ፡ ማከናወኛ ፡ ፎርሞች ፤ |
| ስድስተኛ ሰንጠረዥ | የይግባኝ ፡ ፎርሞች ፤ |

## ለፎርሞቹ ፡ መሠረት ፡ የሆኑት ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ማውጫ ።

| የሕጉ አንቀጽ | የሰንጠረዡና የፎርሙ ቁጥር | ጉ ዳ ዩ ፡ |
|---|---|---|
| ፵ (፪) | ሁለተኛ (፲፫) | ተባባሪ ፡ ከሣሽ ፡ ለሚሆን ፡ ሰው ፡ የሚተላለፍ ማስታወቂያ ፡ |
| ፵ (፩) | ስድስተኛ (፳፯) | በመልስ ፡ ሰጭነት ፡ ተባባሪ ፡ ለሆነ ፡ ወገን ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፶ | ሁለተኛ (፫) | ለሟቹ ፡ ተከሣሽ ፡ ወኪል ፡ የሚላክ ፡ መጥሪያ ፡ |
| ፷ | ሁለተኛ (፵፩) | ለተከሣሽ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፸ | አንደኛ ከ(ሀ (መ) | የክስ ፡ ወይም ፡ የክርክር ፡ ማቅረቢያ ፡ ፎርም ፡ |
| ፺፪ | አንደኛ (ሠ) | ለቀረበ ፡ ክስ ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ ማረጋገጫ ፡ ቃል ፡ |
| ፺፬ | ሁለተኛ (፬) | ተከሣሽ ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡ |
| ፺፮ (፩) | ሁለተኛ (፭) | ለእሥረኛ ፡ ወይም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባልደረባ ፡ እንዲደርስ፡ ስለሚላክ፡ መጥሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፻፬ | ሁለተኛ (፮) | መጥሪያ ፡ ሲመለስ ፡ አብሮ ፡ የሚላክ ፡ የመጥሪያ ፡ አድራሽ ፡ መኰንን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ |
| ፻፯ (፩) | ሁለተኛ (፯) | ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚዳኘው ፡ ቦታ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፻፱ | ሁለተኛ (፰) | ለሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ እንዲደርስ ፡ ስለሚላክ ፡ መጥሪያ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፻፲፩ እና ፻፲፬ | ሁለተኛ (፱) | ለምስክር ፡ የሚላክ ፡ መጥሪያ ፡ |
| ፻፲፰ (፪) | ሁለተኛ (፲) | ምስክር ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፻፳ (፫) | ሁለተኛ (፲፩) | በመሀኒ ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፻፳፩ | ሁለተኛ (፲፪) | በመሀኒ ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |

## ለፎርሞቹ ፡ መሠረት ፡ የሆኑት ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ማውጫ ።

| የሕጉ አንቀጽ | የሰንጠረዡና የፎርሙ ቁጥር | ጉዳዩ |
|---|---|---|
| ፪፳፪ | ሶስተኛ (፬) | የጥያቄ ፡ ደብዳቤ ፡ |
| ፪፳፮ | ሶስተኛ (፭) | የምስክር ፡ ቃል፡ ለመቀበል፡ የሚሰጥ፡ ሥልጣን፡ |
| ፪፴፪ እና ፪፴፬ | ሶስተኛ (፲) | ጉዳዩ ፡ በቦታው ፡ ላይ ፡ እንዲመረመርና ፡ የሂሳብ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ የሚሰጥ ፡ ሥልጣን ፡ |
| ፪፵፮ | አምስተኛ (፩) | ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ስለሚያዝ ፡ ሰው ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፪፵፰ | አምስተኛ (፪) | ከፍርድ ፡ በፊት ፡ የተያዘ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ተያዥ ፡ |
| ፪፵፱ | አምስተኛ (፫) | ዋስ ፡ ዋስትናው ፡ እንዲወርድለት ፡ በሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ፡ |
| ፪፶ | አምስተኛ ፬) | በእሥር ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፪፶፩ እና ፪፶፪ | አምስተኛ (፭) | ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ስለሚያዝ ፡ ንብረት ፡ |
| ፪፶፩ | አምስተኛ (፮) | ንብረት ፡ ለማስረከብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ተያዥ ፡ |
| ፪፶፮ | አምስተኛ (፯) | ለጊዜው ፡ የሚሰጡ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዞች ፡ |
| ፪፷፮ | አምስተኛ (፰) | ተረካቢ ፡ ስለመሾም ፡ |
| ፪፷፰ | አምስተኛ (፱) | ንብረት ፡ ተረካቢው ፡ የሚሰጠው ፡ የዕዳ ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነድ ፡ |
| ፫፻፪ | ስድስተኛ (፩) | ለይግባኝ ፡ ወጭ ፡ የሚሰጥ ፡ መያዣ ፡ |
| ፫፻፳፫ | አንደኛ (ሀ) (ረ) | የአባሪዎች ፡ ዝርዝር ፡ |
| ፫፻፱ | ሶስተኛ (፩) | ስለ ፡ ሰነዶች ፡ መተማመኛ ፡ ቃል ፡ እንዲሰጥ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፫፻፶፪ | ሶስተኛ (፪) | በፍርድ ፡ ስለሚታዩት ፡ ጭብጦች ፡ ባለጉዳዮቹ፡ የሚያደርጉት ፡ ስምምነት ፡ |
| ፫፻፳፩ ፫፻፳፪ | ተጨማሪ ፎርም | የመሐላ ፡ መፈጸሚያ ፡ ፎርም ፡ |
| ፫፻፳፭ | ሶስተኛ (፫) | የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ለቆ ፡ ለመሔድ ፡ የተቃረበ ፡ ምስክር ፡ እንዲጠየቅ ፡ ለባለ ጉዳዮቹ ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፫፻፴፩ | ሶስተኛ (፬) | ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፫፻፴፫ | ሁለተኛ (፪) | ስለ ፡ ተዘዋዋሪ ፡ ሰነድ ፡ በቀረበ ፡ ክስ ፡ መሠረት የሚተላለፍ ፡ መጥሪያ ፡ |
| ፫፻፵፫ | ስድስተኛ (፪) | የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲተላለፍ ፡ የሚሰጥ ፡ ተያዥ ፡ |
| ፫፻፵፮ | ስድስተኛ (፫) | ጉዳዩ ፡ በይግባኝ ፡ ሳለ ፡ የሚሰጥ ፡ ተያዥ ፡ |
| ፫፻፵፰ | ስድስተኛ (፬) | ይግባኝ ፡ እንዲሰማ ፡ ስለተወሰነው ፡ ቀን ፡ ለመልስ ፡ ሰጭ ፡ ማስታወቂያ ፡ |

# ለፍርሞቹ ፡ መሠረት ፡ የሆኑት ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ማውጫ ።

| የሕጉ አንቀጽ | የሰንጠረዡና የፎርሙ ቁጥር | ጉ ዳ ይ ፡ |
|---|---|---|
| ፫፻፹፪ | አራተኛ (፫) | የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ለሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፫፻፹፫ | አራተኛ (፬) | ፍርድ ፡ ላለመፈጸሙ ፡ የሚሰጥ ፡ ማረጋገጫ ፡ |
| ፫፻፺፩ (፫) | አራተኛ (፩) | ፍርድ ፡ የማይፈጸምበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲገለጽ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፫፻፺፪ | ሶስተኛ (፲፫) | በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ዕዳ ፡ ለተያዥ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፫፻፺፰ | አራተኛ (፱) | የፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ያልፈጸመ ፡ ሰው ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፫፻፺፱ | አራተኛ (፲) | የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፫፻ ፺ | አራተኛ (፲፩) | በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የታሰረ ፡ ሰው ፡ እንዲለቀቅ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፩ (፪) | አራተኛ (፯) | ስለሰነድ ፡ ረቂቅ ፡ መቃወሚያ ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲገለጽ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፬፻፩ (፩) | አራተኛ (፬) | ፍርድ ፡ ላለመፈጸሙ ፡ የተሰጠ ፡ ማረጋገጫ ፡ |
| ፬፻፪ | አራተኛ (፰) | የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ ለፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፱ | አራተኛ (፲፪) | በፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ እጅ ፡ ያልሆነ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፲፩ | አራተኛ (፲፫) | ደመወዝ ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፲፪ | አራተኛ (፲፬) | ተዘዋዋሪ ፡ ሰነድ ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፲፫ | አራተኛ (፲፭) | በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፲፱ | አራተኛ (፲፮) | የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፲፯ | አራተኛ (፲፯) | በሶስተኛ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፲፰ | አራተኛ (፲፰) | ንብረት ፡ ላስያዘ ፡ ባለገንዘብ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፬፻፳፪ | አራተኛ (፲፱) | የተያዘ ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፬፻፳፫ | አራተኛ (፳፩) | የሺያጭ ፡ ሁኔታ ፡ መግለጫ ፡ |
| ፬፻፳፭ | አራተኛ (፳፪) | የሽያጭ ፡ ሁኔታ ፡ እንዲገለጽ ፡ ትእዛዝ ፡ |

## ለፎርሞቹ ፡ መሠረት ፡ የሆኑት ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ማውጫ ።

| የሕጉ አንቀጽ | የሰንጠረዡና የፎርሙ ቁጥር | ጉ ዳ ዩ ፡ |
|---|---|---|
| ፩፻፷፱ | አራተኛ (፵፫) | ንብረቱ ፡ እንደገና ፡ ሲሸጥ ፡ ስለደረሰው ፡ የዋጋ፡ ጉድለት ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ |
| ፩፻፸፮ | አራተኛ (፵፬) | ለፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የተሸጠ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ በይዞታው ፡ ለሚገኝ ፡ ሰው ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፩፻፸፱ | አራተኛ (፵፮) | ንብረት ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ እንዲያዝ ፡ እንዲከራይ ፡ ወይም ፡ እንዲሸጥ ፡ ሲፈቀድ ፡ የሚሰጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ |
| ፩፻፹፮ | አራተኛ (፵፯) | ሺያጭ ፡ እንዳይታገድ ፡ መቃወሚያ ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲገለጽ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡ |
| ፩፻፹፰ | አራተኛ (፶) | የተሸጠ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለገዢው ፡ እንዲሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፩፻፺ | አራተኛ (፶፩) | የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ በማሰናከል ፡ የተከሰሰ ፡ሰው ቀርቦ ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚላክ ፡ መጥሪያ ፡ |
| ፩፻፺፩ | አራተኛ (፶፪) | በእሥር ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ ትእዛዝ ፡ |
| ፩፻፺፰ | ተጨማሪ ፎርም | በድኃ ፡ ደንብ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ |
| ፩፻፸፩ | ሶስተኛ (፲፪) | በድኃ ፡ ደንብ ፡ ስለቀረበ ፡ ክስ ፡ ማስረጃ ፡ ለመስማት ፡ የተወሰነውን ፡ ቀን ፡ ማስታወቅ ፡ |

## ተጨማሪ ፡ ፎርሞች ።

| ተራቍጥር ፡ | ገ ዳ ዩ ፡ |
|---|---|
| ፩ኛ | ኑዛዜ ፡ እንዲረጋገጥና ፡ ንብረት ፡ እንዲከፋፈል ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ |
| ፪ኛ | ሕጋዊ ፡ ወራሾች ፡ መሆናቸው ፡ እንዲረጋገጥላቸውና ፡ የንብረት ፡ ማከፋፈያው ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ወራሾቹ ፡ የሚያቀርቡት ፡ አቤቱታ ፡ |
| ፫ኛ | ስለኑዛዜ ፡ ውርስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሂሣብ ፡ አጣሪ ፡ እንዲሾም ፡ የሚቀርብ ፡ ማመልከቻ ፡ |
| ፬ኛ | ኑዛዜ ፡ ስላልተገኘለት ፡ ውርስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሂሣብ ፡ አጣሪ ፡ እንዲሾም ፡ የሚቀርብ ፡ አቤቱታ ፡ |
| ፭ኛ | መቃወሚያ ፡ ቢኖር ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ |

ጠቅላላ ፡ ፎርም ፡

## ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡ ፩.

## የክስ ፡ ማቅረቢያ ፡ ፎርም ፡

### ሀ) የክሱ ፡ አርእስተ ፡ ነገሮች ፡

በ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፍርድ ፡ ቤት ፡

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም) . . . . (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መጨ መር ፡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ..ከሣሽ ።

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም) . . . . (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መ ጨመር ፡). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ተከሣሽ ።

### ለ/ ተለይተው ፡ በታወቁ ፡ ጉዳዮች ፡ ተከራካሪ ፡ የሆኑት ፡ ወገኖች ፡ መለያ ፡ ዝርዝር ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ . . . . . . . . . . . . .
ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ . . . . . . . . . . . . . .
የተመዘገበ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ በ . . . . . . . . . የሆነ ፡ የ . . . . . . አክሲዮን ማኅበር ፡

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . የ . . . . ኩባንያ ፡ ባልደረባ ፡

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . በራሱና ፡ በሌሎቹ ፡ በ . . . . . ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠላ ቸው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መጨመር ፡)

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . በራሱና ፡ በሌሎቹ ፡ ግዴታው ፡ የተወሰነ ፡ የ . . . . . . ኩባንያ ፡ ላላቸው ፡ ድርሻ ፡ የምሥክር ፡ ወረቀት ፡ በሰጣቸው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መጨመር ፡)

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . በዕድሜ ፡ ለኃላፊነት ፡ ስላልደረሰ ፡ ሰው ፡ ሞግዚቱ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . . . . . (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መ ጨመር ፡)

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መ ጨመር ፡)

በደንብ ፡ የታወቀው ፡ ነገረ ፡ ፈጁ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . . (አስፈላጊውን ፡ ዝር ዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መጨመር ፡)

. . . . . በ . . . . . በሽርክና ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡-

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . የሟቹ ፡ የ . . . . ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መጨመር ፡)

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . የሟቹ ፡ የ . . . . ወራሽ ፡ (አስፈላጊውን ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ አድራሻ ፡ መጨመር ፡)

## ሐ/ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡

## ቍጥር ፡ ፩.

## በብድር ፡ የተሰጠ ፡ ገንዘብ ፡

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . ዓ.ም. ሊከፍል ፡ በ . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . ዓ.ም. ለተከ
ሣሹ ፡ . . . . . ብር ፡ አበድሮት ፡ ነበር ፡

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ በ . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . ዓ.ም. ከከፈለው ፡ . . . . ብር ፡ በቀር ፡ ብድሩን ፡
አልከፈለም ፡
(ከሣሹ ፡ ከማናቸውም ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ ነፃ ፡ ነኝ ፡ ይል ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ይግለፅ ፡)

፫ኛ. ከሣሹ ፡ ከ . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . ዓ.ም. እስከ ፡ . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . ዓ.ም. ድረስ
ዕድሜው ፡ ለኃላፊነት ፡ ያልደረሰ ፡ (ወይም ፡ አዕምሮው ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡) ነበር ፡

፬ኛ. (ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነበትን ፡ ጊዜና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ለማየት ፡ ሥል
ጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ የሚገልፁ ፡ ማስረጃዎች ፡)

፭ኛ. ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ጉዳይ ፡ ሂሣብ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ተብሎ ፡ ሲታሰብ ፡ . . . .
ብር ፡ ለዳኝነት ፡ ዋጋ ፡ ተብሎ ፡ ሲታሰብ ፡ ደግሞ ፡ . . . . . ብር ፡ ነው ።

፮ኛ. ከሣሹ ፡ ከ . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . ዓ.ም. ጀምሮ ፡ . . . . . በመቶ ፡ ሂሣብ ፡ ወለድ ፡ ጭ
ምር ፡ . . . . . ብር ፡ እንዲከፈለው ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፪.

## በትርፍ ፡ የተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . . ዓ.ም. በቶላ ፡ . . . . የኢት/ብር ፡ ሂሣብ ፡ የነጠረ ፡ ብር ፡ ድ
ብሎች ፡ ከሣሹ ፡ ሊገዛ ፡ ተከሣሹም ፡ ሊሸጥ ፡ ተስማሙ ።

፪ኛ. የማስመዘኛውን ፡ ዋጋ ፡ ተከሣሹ ፡ ከፍሎ ፡ ድብሎቹን ፡ አቶ ፡(ወይም ፡ በማስረግ ፡ ስም ፡)
. . . . . በመዘናቸው ፡ እያንዳንዱ ፡ ድብል ፡ ፩ሺ.፭፻. ቶላ ፡ የነጠረ ፡ ብር ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ስላስታ
ወቀ ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ . . . . . ብር ፡ ከፈለ ።

፫ኛ. እያንዳንዱ ፡ ድብል ፡ ያለው ፡ የነጠረ ፡ ብር ፡ ፩ሺ.፪፻. ቶላ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ። ይህም ፡ ገንዘቡን፡
በከፈለ ፡ ጊዜ ፡ ከሣሹ ፡ ያላወቀው ፡ ነገር ፡ ነው ።

፬ኛ. በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በትርፍ ፡ የተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ተከሣሹ ፡ አልመለሰም ፡ (በፎርም ፡
፩. በ፩ና ፭ኛ. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄውን ፡ ማመልከት፡)

## ቍጥር ፡ ፫.

## በተቆረጠ ፡ ዋጋ ፡ የተሸጡና ፡ ገዢው ፡ የተረከባቸው ፡ ዕቃዎች ፡

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. . . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . ዓ.ም. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . ለተከሣሹ ፡ (አንድ
መቶ ፡ በርሚል ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ስንጠረዥ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ዕቃዎች፡
ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ዕቃዎችን ፡) ሸጠ ፡ አስረከበም ፡-

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ ዕቃዎቹን ፡ እንደተረከበ ፡ (ወይም ፡ ክሱ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡፡ በ . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . ዓ.ም.) የዕቃዎቹን ፡ ዋጋ ፡ . . . . ብር ፡ ሊከፍል ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ ነበር ።

፫ኛ. ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ።

፬ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . በ . . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . ዓ.ም. ሞተ ። በመጨረሻ ፡ ኑዛዜው ፡ ያሁኑን ፡ ከሣሽ ፡ ወንድሙን ፡ ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ አደረገው ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፬ና ፡ በ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡)

፭ኛ. የአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ በመሆኑ ፡ ከሣሽ ፡ ጥያቄ ውን ፡ ያቀርባል ፡ (ጥያቄውን ፡ መግለፅ ፡)

## ቍጥር ፡ ፬ ፡

## ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ዋጋ ፡ የተሸጡና ፡ ገዢው ፡ የተረከባቸው ፡ ዕቃዎች ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . . .ዓ.ም. ከሣሽ ፡ ለተከሣሹ ፡ (ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤት ፡ ዕቃዎችን) ሸጦ ፡ አስረከበም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ የተደረገ ፡ ግልጽ ፡ ስምምነት ፡ አልነበረም ።

፪ኛ. ዕቃዎቹ ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ዋጋ ፡ . . . . . .ብር ፡ ያወጡ ፡ ነበር ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ፡

(በፎርም ፡ ፩. በ፬ ና ፭. ተራ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ፡)

## ቍጥር ፡ ፭.

## በተከሣሹ ፡ ጥያቄ ፡ የተሠሩና ፡ አሠሪው ፡ ያልተቀበላቸው ፡ ዕቃዎች ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . . . .ዓ.ም. ከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . . . (ስድስት ፡ ጠረጴዛዎችና ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ወንበሮች) ሊሠራለትና ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . .ዕቃዎቹን ፡ ሲረከቡ ፡ ዋጋቸውን ፡ . . . . .ብር ፡ ሊከፍል ፡ ተስማሙ ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ሠርቶ ፡ ከ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓም ፡ ጀምሮ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ሲጠባበቅ ፡ ቆየ ።

፫ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . . .ዕቃዎቹን ፡ አልተቀበለም ፡ (ዋጋቸውንም ፡ አልከፈለም ፡ ) (በፎርም ፡ ፩. በ፪ና. ፭. ተራ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽና ፡ ጥያቄንም ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ፡)

## ቍጥር ፡ ፮.

## ዕቃ ፡ እንደገና ፡ በመሸጥ ፡ የደረሰ ፡ የሂሣብ ፡ ጉድለት ፡ (በሐራጅ ፡ የተሸጡ ፡ ዕቃዎች ፡)

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . . ዓ.ም ከሣሹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ዕቃዎች ፡ በሐራጅ ፡ ለመሸጥ ፡ አቀረበ ። ይኸውም ፡ ሲሆን ፡ ማናቸውም ፡ ዕቃ ፡ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ በአሥር ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ዋጋው ፡ ተከፍሎ ፡ ሳይወሰድ ፡ ቢቀር ፡ በገዛው ፡ ሰው ፡ ሂሣብ ፡ ሐራጅ ፡ ወጥቶ ፡ ይሸጣል ፡ የሚለውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተከሣሹም ፡ እንዲያውቀው ፡ ሆኖ ፡ ነበር ።

፪ኛ. በጨረታው ፡ ተከሣሹ (አንድ ፡ የዕቃ ፡ መያዣ ፡ ቅርጫት ) በ. . . . .ብር ፡ ገዛ ።
፫ኛ. ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ ዕቃዎቹን ፡ የሺያጩ ፡ ዕለትና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ድረስ
ለማስረከብ ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነበር ።
፬ኛ. ተከሣሹ ፡ ከሺያጩ ፡ በኋላ ፡ በአሥር ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ የገዛ
ቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ አልወሰደም ፡ ዋጋውንም ፡ አልከፈለም ።
፭ኛ. በ. . . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም. ከሣሹ ፡ የዕቃ ፡ መያዣ ፡ ቅርጫቱን ፡ በተከሣሹ ፡
ሒሣብ ፡ ጨረታ ፡ አውጥቶ ፡ በ. . . . . .ብር ፡ ሸጠው ።
፮ኛ. ዕቃውን ፡ እንደገና ፡ በመሸጥ ፡ የደረሰው ፡ ወጪ ፡ . . . . .ብር ፡ ሆ ነ ።
፯ኛ. በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የደረሰውን ፡ የሒሣብ ፡ ጉድለት ፡ . . . . . .ብር ፡ ተከሣሹ ፡ አልከፈለም ።
በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር
ዝሮ ፡ ማመልከት ፦

## ቍጥር ፡ ፯ .

## ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ሒሣብ ፡ የተፈጸሙ ፡ አገልግሎቶች ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፦
፩ኛ. በተከሣሹ ፡ ጥያቄ ፡ በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም. እና ፡ በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም.
ከሣሹ ፡ (ልሙዋ ፡ ሥዕሎችን ፡ የሥዕል ፡ ንድፎችንና ፡ ዲያግራሞቹን ፡ ) ለተከሣሹ ፡ ሠርቶ ፡ አዘ
ጋጀ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለነዚሀ ፡ አገልግሎቶች ፡ ዋጋ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የተደረገ ፡ ግልጽ ፡
ስምምነት ፡ አልነበረም ፦
፪ኛ. አገልግሎቶቹ ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ግምት ፡. . . .ብር ፡ ያወጡ ፡ ነበር ፦
፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ፦
በፎርም ፡ ፩. መ. ፬. እና ፡፭. ተራ ፡ ቍጥሮቹ ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽና ፡ ጥያቄን ፡
ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ፡

## ቍጥር ፡ ፰.

## ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ወጪ ፡ የተፈጸሙ ፡ አገልግሎቶችና ፡ የተሸጡ ፡ ዕቃዎች ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።
፩ኛ. በተከሣሹ ፡ ጥያቄ ፡ ከሣሹ ፡ በ. . . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም. በ. . . . .(ቍጥር ፡. . . .
በመባል ፡ የታወቀ ፡ ) ቤት ፡ በ. . . . . .ሠራ ። ለመሥሪያው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ አቀ
ረበ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለዚሀ ፡ ሥራና ፡ ለዕቃዎች ፡ ዋጋ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የተደረገ ፡ ግልጽ፡
ስምምነት ፡ አልነበረም ።
፪ኛ. የተሠራው ፡ ሥራና ፡ የተሰጡት ፡ ዕቃዎች ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ግምት ፡ . . . . .ብር ፡ ያወጡ፡
ነበር ።
፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ፡ -
በፎርም ፡ ፩. በ ፬. እና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄንም ፡
ማመልከት ፦

## ቁጥር ፡ ፱.

## መገልገልና ፡ ይዞታ ፡

የሚቱ ፡ የአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . . ኑዛዜ ፡ አስፈጻሚ ፡ የሆነው ፡ እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. (በ. . . . . . መንገድ ፡ የሚገኘውን ፡ ቁጥር ፡ . . . . . ቤት ፡) ተከሣሹ ፡ በአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) ፈቃድ ፡ ከ. . . . . . ቀን ፡ ፲፱ ፡ . . . . . . ዓ.ም. እስከ ፡ . . . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . . . ዓ.ም. ድረስ ፡ ተቀመጡበት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በንብረቱ ፡ ለተገለገሉበት ፡ ፡ዋጋ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የተደረገ ፡ ግልፅ ፡ ስምምነት ፡ አልነበረም ።

፪ኛ. ለዚሁ ፡ ለተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ በንብረቱ ፡ የተገለገሉበት ፡ ሂሣብ ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ግምት፡ . . . . . . ብር ፡ ያወጣል ፡-

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ፡-

በፎርም ፡ ፩. በ ፬. ና ፰. ተራ ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡-

፮ኛ. ከሣሹ ፡ የአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . . . . ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ በመሆኑ ፡ የሚገባው ፡ እንዲደረግለት ፡ ይጠይቃል ፡ (ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ፡ )

## ቁጥር ፡ ፲.

## በውሣኔ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ ክርክር ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ለአሥር ፡ የዘይት ፡ በርሚሎች ፡ ከሣሹ ፡ የጠየቀውን ፡ ዋጋ ፡ ተከሣሹ ፡ አልከፍልም ፡ በማለቱ ፡ ምክንያት ፡ ከሣሹና ፡ ተከሣሹ ፡ ሳይስማሙ ፡ ስለቀሩ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . . . . ይገላግሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ክርክሩን ፡ ሊያቀርቡላቸው ፡ ከሣሹና ፡ ተከሣሹ ፡ በ. . . . ቀን ፡ ፲፱ . . . . . ዓ.ም. የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ አደረጉ ፡ ሰነዱም ፡ ዋናው ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ።

፪ኛ. በ. . . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ . . . . . ብር ፡ እንዲከፍለው ፡ ገላጋዩቹ፡ ወሰኑ ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ፡-

በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፰. ተራ ፡ ቁጥርሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ።

## ቁጥር ፡ ፲፩.

## በውጭ ፡ አገር ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለ ክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . . ፍርድ ፡ ቤት ፡ በከሣሽና ፡ በተከሣሽ ፡ መካከል ፡ ቀርቦ ፡ የቆየውን ፡ ክስ ፡ በመመልከት ፡ ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ . . . . ብር ፡ ከ. . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓም ፡ ጀምሮ ፡ ወለድ ፡ ጭምር ፡ እንዲከፍል ፡ በ. . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. ፡ በ. . . . ተፈረደ ።

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ፡-

በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፰. ተራ ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ፡

## ቍጥር ፡ ፲፪.

## ለቤት ፡ ኪራይ ፡ አከፋፈል ፡ ሞስ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ከከሣ ሹ ፡ ላይ ፡ (በ. . . .መንገድ ፡ የሚገኘውን ፡ ቍጥር ፡ . . . .የሆነ ፡ ቤት ፡) በየወሩ ፡ በሚከፈል ፡ በዓመት ፡. . . . ብር ፡ በሆነ ፡ ኪራይ ፡ ለ. . . .ዓመታት ፡ ተከራየ ።

፪ኛ. ይህ ፡ ቤት ፡ ለአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .በመከራየቱ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ተከሣሹ ፡ ኪራይ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲከፈል ፡ ሞስ ፡ ሆነ ።

፫ኛ. የ. . . .ወር ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ኪራይ ፡ . .ብር ፡ አልተከፈለም ።

(በውሉ ፡ መሠረት ፡ ለሞሱ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ መስጠት ፡ ያስፈልግ ፡ እንደሆነ ፡ ይገለፅ ፡)

፬ኛ. ኪራዩ ፡ ስላልተከፈለ ፡ ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ በ. . . . ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም ማስታወቂያ ፡ በመስጠት ፡ እንዲከፍለው ፡ ጠየቀ ።

፭ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፪. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር ዝር ፡ ማመልከት ።)

## ቍጥር ፡ ፲፫.

## መሬት ፡ ለመግዛት ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ለማፍረስ ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. ከሣሽና ፡ ተከሣሹ ፡ ውል ፡ ተፈራረሙ ። ሰነዱም ፡ ዋናው ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ።

(ወይም ፡ በ. . . .መንደር ፡ የሚገኘውን ፡ አርባ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ በ. . . .ብር ፡ ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ ሊሸጥ ፡ ተከሣሹም ፡ ከከሣሹ ፡ ሊገዛ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ከሣሹና ፡ ተከሣሹ ፡ ተስማሙ ።)

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የንብረቱ ፡ ፍጹም ፡ ባለቤት ፡ ስለነበረና ፡ ንብረቱም ፡ ለተከሣሹ ፡ በቀረበለት ፡ አኳኋን ፡ ከማናቸውም ፡ ግዴታ ፡ ነፃ ፡ ስለነበረ ፡ (ንብረቱን ፡ ለማዘዋወር ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ለተከሣሹ ፡ አቀረበለት ፡ ) (ወይም ፡ ንብረቱን ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ለተከሣሹ ፡ ለማዛወር ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነበረ ። አሁንም ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ገልፆለት ፡ ነበር፡)

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ገንዘቡን ፡ አልከፈለም ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፪. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄንም ፡ ዘር ዝር ፡ ማመልከት ፡)

## ቍጥር ፡ ፲፬.

## የተሸጡ ፡ ዕቃዎች ፡ ለገዥው ፡ ሳይደርሱት ፡ ስለቀሩ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ለከሣሹ ፡ (አንድ ፡ መቶ ፡ በርሜል ፡ ዱቄት ፡) ሊያስረክብና ፡ ከሣሹም ፡ . . . .ብር ፡ ሊከፍል ፡ ከሣሹና ፡ ተከሣሹ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ተዋዋሉ ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ዕቃዎቹን ፡ እንደተረከበ ፡ ገንዘቡን ፡ ለተከሣሹ ፡ ለመክፈል ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነበር ፡ ይህንኑም ፡ ለተከሣሹ ፡ ገልፆለት ፡ ነበር ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ዕቃዎቹን ፡ አላስረከበም ፡ ከሣሹም ፡ ዕቃዎቹ ፡ ደርሰውት ፡ ቢሆን ፡ ያገኘው ፡ የነበረው ፡ ትርፍ ፡ ቀረበት ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፩. ና በ፩. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር ዝር ፡ ማመልከት ፡ )

## ቍጥር ፡ ፲፩.

## ያላገባብ ፡ ሰውን ፡ ከሥራ ፡ ስለ ፡ ማሰናበት ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ (የሂሣብ ፡ ሠራተኛ ፡ ) ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ ተከሣሹም ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ሊያሠራውና ፡ (በወር ፡ )....ብር ፡ ሊከፍለው ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ከሣሹና ፡ ተከሣሹ ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ተዋዋሉ ።

፪ኛ. በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ አገልግሎቱን ፡ ጀመረ ፡ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላው ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ አገልግሎት ፡ ለመቀጠል ፡ መቸውንም ፡ ቢሆን ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነበረ ።አሁንም ፡ ነው ፡ ይህንኑም ፡ ተከሣሹ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲያውቀው ፡ ሆኖ እል ።

፫ኛ. በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ከሣሹን ፡ ያላገባብ ፡ ከሥራ ፡ አሰናበተው ።

እላይ ፡ እንደተገለፀው ፡ እንዲያገለግል ፡ መፍቀድ ፡ ወይም ፡ ያገልግሎቱ ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ እምቢ ፡ አለ ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፩. ና ፩. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄንም ፡ ዘር ዝሮ ፡ ማመልከት ፡)

## ቍጥር ፡ ፲፪.

## ለማገልገል ፡ የገቡትን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከሣሹ ፡ ተከሣሹን ፡ (ባመት ) በ....ብር ፡ ደመወዝ ፡ ሊያሠራው ፡ ተከሣሹም ፡ ከሣሹን፡ (አርቲስት) ሆኖ ፡ ሊያገለግል ፡ በ....ቀን ፡፲፱....ዓ.ም. ከሣሹና ፡ ተከሳሹ ፡ (ለአንድ ፡ ዓመት) ተዋዋሉ ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በበኩሉ ፡ ውሉን ፡ ለመፈጸም ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነበር ፡ (ይህንኑም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱ ....ዓ.ም. ገልፆአል ፡ )

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ አገልግሎቱን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በተገለፀው ፡ ቀን ፡ (ጀመረ ። ) ግን ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. እላይ ፡ እንደተገለፀው ፡ ከሣሹን ፡ ለማገልገል ፡ እምቢ ፡ አለ ፡

(በፎርም ፡ ፩. በ፩. ና ፩. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር ዝሮ ፡ ማመልከት ፡ )

## ቍጥር ፡ ፲፯.

### ጉድለት ፡ ስለ ፡ ተገኘበት ፡ ሥራ ፡ በገንቢ ፡ ላይ ፡ የቀረበ ፡ ክስ ፡

አላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. ከሣሽና ፡ ተከሣሹ ፡ ውል ፡ ተዋዋሉ ። ሰነዱም ፡ ዋናው ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ፡ (ወይም ፡ የውሉን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ መግለፅ ፡ ነው ፡ )

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በበኩሉ ፡ የውሉን ፡ ግዴታዎች ፡ በሙሉና ፡ በትክክል ፡ ፈጸመ ፡

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ (በውሉ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ቤት ፡ በመጥፎና ፡ ባላዋቂ ፡ አሠራር ፡ ሠራው ፡ )
(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር ዝሮ ፡ ማመልከት ፡)

## ቍጥር ፡ ፲፰.

### ለጸሐፊ ፡ ታማኝነት ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ተያዥ ፡

አላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡

፩ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .ን ፡ በጸሐፊነት ፡ ቀጠረው ።

፪ኛ. ይህም ፡ ሲሆን ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ለከሣሹ ፡ የጸሐፊነት ፡ ተግባሮቹን ፡ በታማኝነት ፡ ባያከናውን ፡ ወይም ፡ ለከሣሹ ፡ ጥቅም ፡ ለተቀበለው ፡ ማናቸውም ፡ ገንዘብ ፡ ዕዳ ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፡ የግዴታ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ በከሣሹ ፡ ዘንድ ፡ ኃላፊነቱን ፡ ሳይፈጽም ፡ ቢቀር ፡ ከሣሹ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ከ. . . .ብር ፡ ያልበለጠ ፡ ኪሣራ ፡ ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ ሊከፍል ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ከከሣሹ ፡ ጋራ ፡ ተዋዋሉ ።

ወይም ፡ ፪ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .ለከሣሹ ፡ የጸሐፊነትና ፡ የገንዘብ ፡ ያዢነት ፡ ተግባሮቹን ፡ በታማኝነት ፡ ያከናወነና ፡ ለከሣሹ ፡ ባላአደራ ፡ ሆኖ ፡ ለያዘው ፡ ማናቸውም ፡ ገንዘብ ፡ የባለዕዳዎች ፡ ግዴታ ፡ ማስረጃ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ንብረት ፡ ኃላፊነቱን ፡ በከሣሹ ፡ ዘንድ ፡ በትክክል ፡ የፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ የተከሣሹ ፡ ተያዥነት ፡ ሊወርድ ፡ ተደርጐ ፡ ያጠፋ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ተከሣሹ ፡. . . .ብር ፡ ሊከፍል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቀን ፡ በፈረመው ፡ ተያዥነት ፡ ሠራተኛው ፡ ሲቀጠር ፡ ግዴታ ፡ ገብቷል ።

ወይም ፡ ፪ኛ. ሠራተኛው ፡ ሲቀጠር ፡ ተያዥ ፡ በመሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቀን ፡ ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ የፈረመለት ፡ ሰነድ ፡ ዋናው ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ ቀርቧል ፡

፫ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. እና. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. መካከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ አቶ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡). . . .ለከሣሹ ፡ ተቀብሎ ፡ በከሣሹ ፡ ዘንድ ፡ ኃላፊነቱን ፡ ያልፈጸመበት ፡ ገንዘብና ፡ ሌላም ፡ ንብረት ፡ ልክ ፡ . . . .ብር ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ገና ፡ የሚጠየቅበትና ፡ ያልተከፈለ ፡ ነው ።
(በፎርም ፡ ፩. በ፬.ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር ዝሮ ፡ ማመልከት ፡ )

## ቍጥር ፡ ፲፱.

### ተከራይ ፡ ልዩ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ በአከራይ ፡ ላይ ፡ ያቀረበው ፡ ክስ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. (በ. . . .መንገድ ፡ የሚገኘውን ፡ ቍጥር ፡ . . . .ቤት ፡ (ተከ ሳሹ ፡ ለከሣሹ ፡ በተመዘገበ ፡ ጽሑፍ ፡ ለ. . . .ዓመት ፡ ሲያከራየው ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሣሹና፡ ሕጋዊ ፡ ወኪሎቹ ፡ በጥሞና ፡ እንዲኖሩበት ፡ ለከሣሹ ፡ ውል ፡ ገብቶለት ፡ ነበር ።

፪ኛ. ውለታዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጽመው ፡ ነበር ፡ ከሣሹም ፡ ይህን ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የሚያስ ገድዱ ፡ ነገሮች ፡ ደረሱ ።

፫ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የቤቱ ፡ ሕጋዊ ፡ ባለ መብት ፡ የሆነው ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡). . . .ከሣሹን ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ በሚገባ ፡ አስወ ጥቶ ፡ ቤቱን ፡ በእጁ ፡ አግብቶታል ።

፬ኛ. ከሣሹ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ (በዚያ ፡ ቦታ ፡ የነበረውን ፡ የልብስ ፡ ስፌት ፡ ሥራ ፡ እንዳይ ቀጥል ፡ ተከለከለ ፡ በመዛወሩ ፡ . . . .ብር ፡ ወጪ ፡ ለማድረግ ፡ ተገደደ ፡ ከዚያም ፡ በመነሣቱ ፡ የአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡). . . .ንና ፡ የ. . . .ን ፡ ደንበኛነት ፡ አጣ ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄንም ፡ ዘር ዝሮ ፡ ማመልከት ፡)

## ቍጥር ፡ ፳.

### ከተጠያቂነት ፡ መድን ፡ ለመሆን ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ስምምነት ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. . . . .እና. . . .በተባለ ፡ ስያሜ ፡ ሽሪኮች ፡ ሆነው ፡ ሲነግዱ ፡ የቆዩት ፡ ከሣሽና ፡ ተከሣሽ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ሺርክናውን ፡ አፍርሰው ፡ ተከሣሹ ፡ የሺርክናውን ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ እንዲወስድና ፡ እንዲይዝ ፡ የንግዱን ፡ ማኅበር ፡ ዕዳ ፡ በሙሉ ፡ እንዲከፍልና ፡ ከንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ሊጠየቅ ፡ ከሚችል ፡ ከማንኛቸውም ፡ ዕዳ ፡ ከሣሹን ፡ መድን ፡ እንዲኖረው ፡ (ነፃ) ሊያደርግ ፡ ተዋዋሉ ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በበኩሉ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ የሚፈለግበትን ፡ በሙሉ ፡ ፈጸመ ።

፫ኛ. በ. . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. ከንግድ ፡ ማኅበር ፡ ለአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) ስለ ፡ ሚከፍል፡ ዕዳ ፡ በ. . . .ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በከሣሹና ፡ በተከሣሹ ፡ ላይ ፡ የተፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ በማክበር ፡ ከሣሹ ፡ . . . .ብር ፡ ከፈለ ።

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ ለከሣሹ ፡ አልከፈለም ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር ዝሮ ፡ ማመልከት ፡ )

## ቍጥር ፡ ፳፩.

### በማጭበርበር ፡ ስለ ፡ ተወሰደ ፡ ዕቃ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ አንዳንድ ፡ ዕቃዎች ፡ እንዲሸጥለት ፡ ከሣሹን ፡ ለማግባባት ፡ ሲል ፡ (በቂ ፡ ሐብት ፡ አለኝ ፡ ሐብቴም ፡ ዕዳዬን ፡ በሙሉ ፡ ከፍሎ ፡ . . . .ብር ፡ ያወጣል ፡ ) ብሎ ፡ በ. . . ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ ነገረው ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ ተግባብቶ ፡ ለተከሣሹ ፡ ዋጋቸው ፡ . . . .ብር ፡ የሆነ ፡ (ሽቀጣ ሽቀጥ ፡ )ዕቃዎች ፡ ሸጠለት ፡ (አስረከበውም ፡ )

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ የተናገረው ፡ ሐሰት ፡ (ወይም ፡ ሐሰት ፡ የሆነው ፡ በተለይ ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ በመግለፅ ፡ ) ነበር ። ተከሣሹ ፡ ነገሩ ፡ ውሸት ፡ መሆኑን ፡ ያውቅ ፡ ነበር ።

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ የዕቃዎቹን ፡ ዋጋ ፡ አልከፈለም ። (ወይም ፡ ዕቃዎቹን ፡ አልተረከበ ፡ እንደ ሆነ ፡ ደግሞ ፡ ከሣሹ ፡ ዕቃዎቹን ፡ በማሰናዳትና ፡ በማስፈር ፡ ቀጥሎም ፡ መልሶ ፡ በእጁ ፡ ለማግባት ፡ . . . .ብር ፡ ወጪ ፡ አደረገ ።

(በፎርም ፡ ፭. በ፬.ና ባ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘር ዝሮ ፡ ማመልከት ፡ )

## ቍጥር ፡ ፳፪ ፤

## በማጭበርበር ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ተወሰደ ፡ ዱቤ ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ አቶ ፡(ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም) ... በቂ ፡ ሐብትና ፡ ደህና ፡ ገቢ ፡ አለው ፡ ሐብቱም ፡ ዕዳውን ፡ በሙሉ ፡ ከፍሎ ፡ . . . .ብር ፡ ያወጣል ፡ (ወይም ፡ አቶ ፡ (በማዕረግ ፡ ስም ፡). . . .በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የኃላፊነት ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ በደህና ፡ ሁኔታ ፡ የሚገኝ ፡ በመሆኑ ፡ ዕቃ ፡ በዱቤ ፡ ቢሰጠው ፡ ሊታመን ፡ የሚችል ፡ ነው/ ብሎ ፡ በ..... ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ ነገረው ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ ተግባብቶ ፤ በ.... ወሮች ፡ በሚከፈል ፡ ዱቤ ፡ .... የስንዴን ፡ ዱቄት ፡ በ... ብር ፡ ሸጠለት ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ የተናገረው ፡ ሐሰት ፡ ነበረ ፡ ሐሰት ፡ መሆኑም ፡ በተከሣሹ ፡ በራሱ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ሆኖ ፡ ከሣሹን ፡ ለማታለልና ፡ ለማጭበርበር ፡ /ወይም ፡ ከሣሹን ፡ ለማታለልና ፡ ለመ ጉዳት ፡/ ታስቦ ፡ የተደረገ ፡ ነበር ።

፬ኛ ፡ ... የዕቃዎችን ፡ ዋጋ ፡ ሳይከፍል ፡ የተወሰነው ፡ የዱቤ ፡ ጊዜ ፡ አለቀ ፤ ወይም ፡ የስንዴ ውን ፡ ዱቄት ፡ ዋጋ ፡ አልከፈለም ፤ ከሣሹም ፡ ገንዘቡ ፡ በሙሉ ፡ ቀረበት ።

(በፎርም ፡ ፭ ፡ በ፬ና ፡ በ፭ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ።)

## ቍጥር ፡ ፳፫ ፤

## በከሣሹ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ውሀ ፡ ማበላሸት ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ ፡ ከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ከተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ በፊትና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ... ለተባለ ውና ፡ በ... ለሚገኘው ፡ መሬት ፡ ለውሀ ፡ ጉድጓድና ፡ በጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ውሀ ፡ ይዞታ ፡ ነበረው ። በጉድጓዱና ፡ በውስጡ ፡ ባለው ፡ ውሀም ፡ ሊገለገልና ፡ ሊጠቀምበት ፡ እንዲሁም ፡ በጉድ ጓዱ ፡ ውስጥ ፡ እየተሞሉ ፡ የሚተላለፉትና ፡ የሚያገለግሉት ፡ ምንጮችና ፡ ወራጅ ፡ ውሀዎች ፡ ሳይ ቆሽሹ ፡ ወይም ፡ ሳይበላሹ ፡ እንዲወርዱ ፡ ወይም ፡ እንዲተላለፉ ፡ ለማድረግ ፡ ባለመብት ፡ ነበረ ።

፪ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ጉድጓዱንና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ውሀ ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ጉድ ጓዱ ፡ የሚገቡትን ፡ ምንጮችና ፡ ወራጅ ፡ ውሀዎች ፡ ተከሣሹ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ አቆሸሾ ፡ አበላሸ አቸው ።

፫ኛ ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ በጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ውሀ ፡ ቆሽሾ ፡ ለቤትና ፡ ለሌላም ፡ አስ ፈላጊ ፡ ጉዳይ ፡ የማይስማማ ፡ ሆነ ።

ከሣሹና ፡ ቤተ ፡ ሰቡም ፡ ያገኙት ፡ የነበረውን ፡ አገልግሎትና ፡ ጥቅም ፤ እንዲሁም ፡ ጉድጓዱንና ፡ ውሀውን ፡ አጡ ። (በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፩ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ።)

## ቍጥር ፡ ፳፬ ፤

## በፋብሪካ ፡ አማካይነት ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ጉዳት ።

እላይ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ ከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ... ለተባለው ፡ በ... ለሚገኘው ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ ነበራቸው ።

፪ኛ ፡ ተከሣሹ ፡ ያላግባብ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የሚያስቀይምና ፡ የማይስማማ ፡ ጢስና ፡ ሌላም ፡ ላቦትና ፡ የሚጐዳ ፡ ነገር ፡ ራሱ ፡ ከሚያካሂደው ፡ የብረት ፡ ማቅለጫ ፡ ፋብሪካ ፡ በብዛት ፡ እየወጣ ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በመሰራጨት ፡ ዓየሩን ፡ እንዲያበላሽና ፡ በዚያ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እየረጋ ፡ እንዲቀር ፡ አደረገ ።

፫ኛ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ የከሣሹ ፡ ዛፎች ፡ የእርሻ ፡ ትልሞች ፤ የግጦሽ ፡ ሣሮችና ፡ ሰብሎች ፡ ተጐድተው ፡ ዋጋቸው ፡ መና ፡ ሆነ ፤ ከብቶችም ፡ ጤና ፡ የሌላቸው ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ ብዙዎቹ ፡ ተመርዘው ፡ ሞቱ ።

፬ኛ ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ከሣሹ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ከብቶቹንና ፡ በጐቹን ፡ ለማጋጥ ፡ ስላል ቻለ ፡ ከብቶቹን ፡ በጐቹንና ፡ የእርሻ ፡ ከብቶቹን ፡ ከዚያ ፡ ለማዛወር ፡ ተገደደ ። ከመሬቱ ፡ ያገኘው ፡ የነበረው ፡ አገልግሎትና ፡ ይዞታ ፡ ቀረበት ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፭ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ።)

## ቍጥር ፡ ፳፭ ፤

## መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ መዝጋት ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ ከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ (... በተባለው ፡ መንደር ፡ ለሚገኘው ፡ ቤት ፡) ይዞታ ፡ ነበረው ፡ አሁንም ፡ አለው ።

፪ኛ ፡ ከሣሹ ፡ ከዓመቱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ (በመኪና ፡ ወይም ፡ በእግር ፡) ራሳቸ ውና ፡ ሠራተኞቻቸው ፡ ከ... (ቤቱ) አውራ ፡ ጐዳናው ፡ እንዲሁም ፡ ከአውራ ፡ ጐዳናው ፡ እስከ ፡ ቤቱ ፡ ድረስ ፡ የሚመላለስበት ፡ መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ ነበረው ።

፫ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ያላግባብ ፡ መተላለፊያውን ፡ መንገድ ፡ ስለዘጋበት ፡ ከሣሹ ፡ (በመኪና ፡ ወይም ፡ በእግር ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡) በዚያ ፡ መንገድ ፡ ለመተላለፍ ፡ ካለመቻሉም ፡ በላይ ፡ (አሁንም ፡ ድረስ ፡ መንገዱ ፡ ያላግባብ ፡ እንደተ ዘጋ ፡ ነው) ።

፬ኛ ፡ (የመንገዱ ፡ አዘጋግ ፡ የተለየ ፡ ሁኔታ ፡ አለው ፡ እንደሆነ ፡ ይግለፅ) ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፩ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት) ።

## ቍጥር ፡ ፳፮ ፤

### አውራ ፡ ጐዳና ፡ ስለ ፡ መዝጋት ።

፩ኛ ፡ ተከሣሹ ፡ ከ... ወደ... ለመዝጋት ፡ ሲል ፡ ያላግባብ ፡ ጉድጓድ ፡ ቆፍሮ ፡ አፈርና ፡ ድንጋይ ፡ በአውራ ፡ ጐዳናው ፡ ላይ ፡ ከመረበት ።

ከሣሹ ፡ በዚሁ ፡ አውራ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ በሚገባ ፡ ሲተላለፍ ፡ ሳለ ፡ በአፈሩና ፡ በድንጋዩ ፡ ላይ ፡ (ወይም ፡ በጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡) ወደቀ ፤ እጁ ፡ ተሰበረ ፤ እጅግ ፡ ተሠቃየ ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ለመሥራት ፡ ሳይችል ፡ ቆየ ፡ እንዲሁም ፡ ለሕክምና ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ደረሰበት ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፪ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት) ።

## ቍጥር ፡ ፳፯ ፤

### የውሀ ፡ አወራረድ ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ ከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ....በተባለው ፡ በ... መንደር ፡ በ... አውራጃ ፡ በሚገኘው ፡ (ወራጅ ፡ ውሀ ፡) ላይ ፡ ለቆመው ፡ ወፍጮ ፡ ይዞታ ፡ ነበረው ፡ አሁንም ፡ አለው ።

፪ኛ ፡ በዚሁ ፡ ይዞታ ፡ ምክንያት ፡ ወፍጮውን ፡ ለማሠራት ፡ ከሣሹ ፡ ለውሀው ፡ አወራረድ ፡ ባለመብት ፡ ነበረ ።

፫ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ የወንዙን ፡ ዳር ፡ በመናድ ፡ ያላግባብ ፡ የውሀውን ፡ አውራረድ ፡ ስለ ፡ ለወጠው ፡ ወደ ፡ ከሣሹ ፡ ወፍጮ ፡ የሚሄደው ፡ ውሀ ፡ ተቀነሰ ።

፬ኛ ፡ የውሀው ፡ አወራረድ ፡ ከመለወጡ ፡ በፊት ፡ በቀን ፡ ... ጆንያ ፡ ይፈጭ ፡ የነበረው ፡ ከሣሹ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በቀን ፡ ከ... ጆንያ ፡ በላይ ፡ ለመፍጨት ፡ አልቻለም ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፪ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት) ።

## ቍጥር ፡ ፳፰ ፤

### ለመስኖ ፡ ማጠጫ ፡ ውሀው ፡ እንዲያገለግል ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ማሰናከል ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ ከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ... በተባለው ፡ ቦታ ፡ ለሚገኘው ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ እንዲሁም ፡ በዚያው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ መስኖ ፡ ለማጠጣት ፡ ወራጅ ፡ ውሀ ፡ በከፊል ፡ እንዲያገለግለው ፡ መብት ፡ ነበረው ፡ አሁንም ፡ አለው ።

፪ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ያላግባብ ፡ የውሀውን ፡ አወራረድ ፡ በማሰናከልና ፡ በመለወጥ ፡ ከሣሹን ፡ እላይ ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ ውሀውን ፡ በከፊል ፡ እንዳይወስድና ፡ እንዳይገለገልበት ፡ ከለከለው ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፪ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት) ።

## ቍጥር ፡ ፳፱ ፡

## በባቡር ፡ ሐዲድ ፡ ላይ ፡ በቸልታ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰ ፡ ጉዳት ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ. . . .በ... ና በ.... መካከል ፡ መንገደኞችን ፡ አጓጓዦዎች ፡ ሆነው ፡ ነበር ።

፪ኛ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከሣሹ ፡ በዚያው ፡ ባቡር ፡ ከነበሩት ፡ ሠረገላዎች ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ መንገደኛ ፡ ሆኖ ፡ ይጓዝ ፡ ነበር ።

፫ኛ ፡ እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ መንገደኛ ፡ ሆኖ ፡ ... ላይ ፡ ወይም ፡ ... ቦታ ፡ ባለው ፡ ጣቢያ ፡ አጠገብ ፡ ወይም ፡ በ... ና በ... ጣቢያዎች ፡ መካከል ፡ ሲደርስ ፡ (በተከሣሾቹ ፡ ሠራተኞች ፡ ቸልታና ፡ አላዋቂነት ፡ በባቡሩ ፡ ላይ ፡ በደረሰው ፡ ግጭት ፡ ምክንያት ፡ ከሣሹ ፡) እግሩን ፡ በመስበር ፡ ራሱን ፡ በመፈነካከትና ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ሁኔታ ፡ (ከዚህም ፡ የተለየ ፡ ጉዳት ፡ ደርሶ ፡ እንደ ሆነ ፡ በመግለጽ ፡) ብዙ ፡ ተጐዳ ፡ ለሕክምና ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አወጣ ፡ (አሻሻጭ ፡ ሆኖ) ይሠራ ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ እንዳይቀጥል ፡ ለዘለዓለም ፡ ስንኩል ፡ ሆነ ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፪ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት) ።

(ወይም ፡ ደግሞ ፡ ፪ኛ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ተከሣሾቹ ፡ በሠራተኞቻቸው ፡ አማካይነት ፡ ሞተርና ፡ ከዚያ ፡ ጋር ፡ የተጋጠመ ፡ የሠረገላዎች ፡ ባቡር ፡ በቸልታና ፡ ባላዋቂነት ፡ ከሣሹ ፡ በሕጋዊ ፡ አኳኋን ፡ በመሻገር ፡ ላይ ፡ በነበረው ፡ በተከሣሾቹ ፡ ሐዲድ ፡ ላይ ፡ ስለነዱ ፡ ሞተሩና ፡ ባቡሩ ፡ ከሣሹን ፡ ገጩት ፡ ... በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በ፫ተኛ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የተባለውን ፡ መዘርዘር) ።

## ቍጥር ፡ ፴ ፡

## በቸልታ ፡ እነዳድ ፡ የደረሰ ፡ ጉዳት ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ ከሣሹ ፡ በ... ሥራ ፡ የሚያከናውን ፡ ጫማ ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ ተከሣሹ ፡ የ... ነጋዴ ፡ ነው ።

፪ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ከሣሹ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ከባቡሩ ፡ ሐዲድ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ከቀትር ፡ በላይ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ በእግሩ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ባቡሩ ፡ ጣቢያ ፡ የሚያደርሰውን ፡ ... መንገድ ፡ ለማቋረጥ ፡ ተገደደ ። ይህን ፡ መንገድ ፡ ሲያቋርጥ ፡ ሳለና ፡ ከማዶው ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀረው ፡ የተከሣሹ ፡ ሠረገላ ፡ በሁለት ፡ ፈረሶች ፡ እየተሳበና ፡ በተከሣሹ ፡ ሠራተኞች ፡ እየተነዳ ፡ በቸልታ ፡ በድንገትና ፡ ያላንዳች ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በፈጣንና ፡ በአደገኛ ፡ አረማመድ ፡ ከ... መንገድ ፡ ወደ ፡ ባቡሩ ፡ ጣቢያ ፡ ገባ ። የሠረገላው ፡ እንጨት ፡ ከሣሹን ፡ በመግጨት ፡ መትቶ ፡ ጣለው ። ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ፈረሶቹም ፡ ብዙ ፡ ረጋገጡት ።

፫ኛ ፡ በግጭቱ ፡ በመውደቁና ፡ በመረጋገጡ ፡ የከሣሹ ፡ የግራ ፡ ክንድ ፡ ተሰበረ ፡ ጐኑና ፡ ጀርባው ፡ ቆሰለ ፡ ተጐዳ ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ውስጣዊ ፡ አካሉም ፡ ተጐዳ ፡ በዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከሣሹ ፡ አራት ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ ታመመ ፡ ተሠቃየ ፡ ሥራውን ፡ ለመሥራት ፡ አልቻለም ፡ ለሕክምናና ፡ ለሌላም ፡ ከባድ ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ደረሰበት ፡ ሥራውና ፡ የሥራ ፡ ትርፉም ፡ ስላቋረጠ ፡ ትልቅ ፡ ኪሣራ ፡ ደረሰበት ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፩ና ፡ ፪ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ።)

## ቍጥር ፡ ፴፩ ፤

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ከሣሹን ፡ በሐሰት ፡ በመወንጀል ፡ ለዳኛ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ከሣሹ ፡ እንዲያዝ ፡ ትእዛዝ ፡ አስወጣ ። ከሣሹም ፡ ተይዞ ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ታሠረ ። (ለመለቀቅም ፡ ልኩ ፡ ... ብር ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ አስያዘ) ።

፪ኛ ፡ ተከሣሹ ፡ ይህን ፡ ያደረገው ፡ በተንኰል ፡ እንጂ ፡ ይገባዋልና ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ በሚያሰኝ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ።

፫ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ዳኛው ፡ የተከሣሹን ፡ አቤቱታ ፡ ውድቅ ፡ አድርጐ ፡ ከሣሹን ፡ ለቀቀው ።

፬ኛ ፡ በከሣሹ ፡ ዘንድ ፡ ስማቸው ፡ ያልታወቀ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከሣሹ ፡ መያዙን ፡ ሰምተው ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ ስለ ፡ ቆጠሩት ፡ ከእሱ ፡ ዘንድ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ አቋርጠዋል ። ወይም ፡ በመያዙ ፡ ምክንያት ፡ ከሣሹ ፡ በአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) ... ዘንድ ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ አጣ ። ወይም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ከሣሹ ፡ በአካልና ፡ በአዕምሮ ፡ ተሠቃየ ፤ ሥራውን ፡ ከማከናወን ፡ ተቋረጠ ፤ በገቢው ፡ ተጐዳ ፤ ከእሥራት ፡ ለመለቀቅና ፡ የቀረበበትን ፡ ክስ ፡ ለመከላከል ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ደረሰበት ።

(በፎርም ፡ ፩ ፡ በ፬ና ፡ ፭ ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽና ፡ ጥያቄን ፡ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት) ።

## ቍጥር ፡ ፴፪ ፤

### ያላግባብ ፡ ስለ ፡ ተያዙ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎች ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለጸው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ።

፩ኛ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ እባሪ ፡ በሆነው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ ለተመለከቱት ፡ ዋጋቸው ፡ ... ብር ፡ መሆኑ ፡ ለተገመተው ፡ ዕቃዎች ፡ (ወይም ፡ ዕቃዎቹን ፡ በመዘርዘር ፡) ባለቤት ፡ ነበር ። (ወይም ፡ ባለይዞታ ፡ እንደሆነም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ማስረጃ ፡ መዘርዘር) ።

፪ኛ. ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ እስከተጀመረበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ተከሣሹ ፡ እነዚህን ፡ ዕቃዎች ፡ ከከሣሹ ፡ ላይ ፡ ይዟቸዋል ።

፫ኛ. ክሱ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ማለት ፡ -በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ከሣሹ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ከተከሣሹ ፡ ጠይቆ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አላስረክብ ፡ ብሎ ፡ ከለከለው ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ። )

፮ኛ. ስለዚህ ፡ ፩ -

፩ኛ. ዕቃዎቹን ፡ እንዲያስረክበው ፡ አለዚያም ፡ ዕቃዎቹን ፡ ማስረከብ ፡ ባይችል ፡ . . . .ብር ፡ እንዲከፍለው ።

፪ኛ. ዕቃዎቹ ፡ ስለ ፡ ተያዙ ፡ ካሣ ፡ . . . .ብር ፡ እንዲከፍለው ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፴፫.

### በማጭበርበር ፡ ዕቃ ፡ የገዛና ፡ ነገሩንም ፡ እያወቀ ፡ ዕቃው ፡ የተላላፈለት ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. አንዳንድ ፡ ዕቃዎች ፡ እንዲሸጥለት ፡ ከሣሹን ፡ ለማግባባት ፡ ሲል ፡ ተከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በግዕረግ ፡ ስም ፡ )....(በቂ ፡ ሐብት ፡ አለኝ ፡ ሐብቴም ፡ ዕዳዬን ፡ በሙሉ ፡ ከፍሎ ፡ ....ብር ያወጣል ፡ ) ብሎ ፡ ለከሣሹ ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ፡ ነገረው ።

፪ኛ. በዚሁ ፡ ተግባብቶ ፡ ግምቱ ፡ ....የሆነ ፡ (አንድ ፡ መቶ ፡ ሳጥን ፡ ቡና ፡ ) ሸጠለት ፡ አስረከበውም ።

፫ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በግዕረግ ፡ ስም ፡ )....የተናገረው ፡ ሐሰት ፡ ነበረ ፤ ሐሰት ፡ መሆኑንም ፡ ራሱ ፡ ያውቅ ፡ ነበረ ።

፬ኛ. ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በግዕረግ ፡ ስም ፡ )....ዕቃዎቹን ፡ ያለዋጋ ፡ (ወይም ፡ በሐሰት ፡ የተገኙ ፡ መሆናቸውን ፡ ላወቀው ፡ )ለተከሣሹ ፡ ለ....አሳልፎ ፡ ሰጠው ።
(በፎርም ፡ ፩. በ፮. ና ፳. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፭ኛ. ስለዚህ ፡-

፩ኛ. ዕቃዎቹ ፡ እንዲሰጡት ፡ ወይም ፡ ዕቃዎቹ ፡ ሊሰጡ ፡ ባይቻል ፡ ....ብር ፡ እንዲከፈለው ።

፪ኛ. ዕቃዎቹ ፡ ስለ ፡ ተያዙበት ፡ ካሣ ፡ ....ብር ፡ እንዲከፈለው ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፴፬

### ስሕተት ፡ ስለ ፡ ተገኘበት ፡ የተሻረ ፡ ውል ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ....የሚገኝ ፡ የራሴ ፡ መሬት ፡ (ሶስት ፡ ጋሻ ፡ ) ነው ፡ ብሎ ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱.... ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ ነገረው ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ መስሎት ፡ በነገሩ ፡ ተግባብቶ ፡ መሬቱን ፡ በ....ብር ፡ ገዛው ። ለዚህ ፡ የፈረመው ፡ ውል ፡ ዋናው ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ መሬቱ ፡ በስሙ ፡ አልተዛወረለትም ።

፫ኛ. በ....ቀን ፡ ፲፱ ..ዓ.ም. ከገዛው ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ ....ብር ፡ ከፈለው ።

፬ኛ. የመሬቱ ፡ ትክክለኛ ፡ ልክ ፡ (አንድ ፡ ጋሻ ፡) ብቻ ፡ ሆነ ።
(በፎርም ፡ ፩.በ፮. ና ፳. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፭ኛ. ስለዚህ ፡ -

፩ኛ. ....ብር ፡ ከ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ጀምሮ ፡ ከወለድ ፡ ጋር ፡ እንዲከፈለው ።

፪ኛ. እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ውል ፡ እንዲቀርብና ፡ እንዲሠረዝ ፡ ከሣሽ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፴፭.

### ንብረት ፡ እንዳይባክን ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከሣሹ ፡ የ....(የንብረቱን ፡ ዓይነት ፡ በመግለፅ ፡ ) ፍጹም ፡ ባለቤት ፡ ነው ።

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ ከከሣሹ ፡ ጋር ፡ ባለው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ለዚሁ ፡ ንብረት ፡ ባለይዞታ ፡ ነው ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ያለ ፡ ከሣሹ ፡ ፈቃድ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ ለመሸጥ ፡ ቆርጧል ፡ እንደገናም ፡ በተጨማሪ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ ለመቍረጥ ፡ ይዝታል ።
(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ እንዳያባክን ፡ ወይም ፡ እንዲባክን ፡ እንዳያደርግ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲደርሰው ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።
(የገንዘብ ፡ ካሣም ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ። )

## ቍጥር ፡ ፴፮.

## አዋኪን ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚ ከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ከሣሽ ፡ በ. . . .መንገድ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኘው፡ የቍጥር ፡ . . . .ቤት ፡ ፍጹም ፡ ባለቤት ፡ ነበረ ፡ አሁንም ፡ ነው ።

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ (በዚያው ፡ በ. . . .መንገድ ፡ የሚገኝ ፡ መሬት ፡ ) ፍጹም ፡ ባለቤት ፡ ነበረ ፡ አሁንም ፡ ነው ።

፫ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ በዚሁ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የከብት ፡ ማረጃ ፡ ቁራ ፡ አቋቋመ ። ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ ወደዚያ ፡ እየመጡ ፡ እንዲ ታረዱ ፡ ከማድረግ ፡ አላቋረጠም ፡ (ደምና ፡ ፈርስም ፡ ከከሣሹ ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ መንገድ ላይ ፡ እንዲጣል ፡ አድርጓል ። )

፬ኛ. በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ከሣሹ ፡ ያን ፡ ቤት ፡ ትቶ ፡ ለመውጣት ፡ ተገደደ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሊያከ ራየውም ፡ አልቻለም ።
(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፭ኛ. ተከሣሹ ፡ ካሁን ፡ በኋላ ፡ የማወክ ፡ ተግባር ፡ ከመፈጸም ፡ ወይም ፡ ከማስፈጸም ፡ የሚያ ግድ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲደርሰው ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፴፯.

## ሕዝብን ፡ ማወክ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ተከሣሹ ፡ የሕዝቡን ፡ መተላለፊያ ፡ ለመዝጋት ፡ ቀበና ፡ . . . .በተባለው ፡ የሕዝብ ፡ መን ገድ ፡ ላይ ፡ ካግባብ ፡ የወጣ ፡ አድራጐትን ፡ ለመቀጠልና ፡ ለመደጋገም ፡ ዝቷል ፡ አስቧልም ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ ይህን ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ከጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የጽሑፍ ፡ ፈቃድ ፡ አግኝ ቷል ።
(በፎርም ፡ ፩. በ፬ ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለጽ ፡ )

፫ኛ. ስለዚህ ፡ -

፩ኛ. ተከሣሹ ፡ በተባለው ፡ የሕዝብ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የሚመላለሰውን ፡ ሕዝብ ፡ መተላለፊያ፡ ለመዝጋት ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ በይፋ ፡ እንዲገለጽ ።

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ በተባለው ፡ የሕዝብ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የሚመላለሰውን ፡ ሕዝብ ፡ መተላለፊያ ፡ እንዳይዘጋ ፡ እንዲታገድና ፡ እንደተገለፀው ፡ ያለአገባብ ፡ የከመረውን ፡ አፈርና ፡ ድንጋይ ፡ እንዲ ያነሣ ፡ እንዲታዘዝ ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፴፰.

### የውሀ ፡ አወራረድ ፡ እንዳይለወጥ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-
(በፎርም ፡ ቍጥር ፡ ፳፮. እንደተባለው ፡ )

እላይ ፡ እንደተገለፀው ፡ ተከሣሹ ፡ የውሀውን ፡ አወራረድ ፡ ከመለወጥ ፡ የሚያግድ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲደርሰው ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፴፱.

### ጥፋት ፡ የተዛተበት ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ እንዲመለስና ፡ ዛቻውም ፡ እንዳይፈጸም ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከሣሹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ (በታወቀ ፡ ሠአሊ ፡ የተሳለውና ፡ ቅጂ ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ በገንዘብ ፡ የማይተካ ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ ይገለፅ ፡). . . .(የአያቱ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ) ባለቤት ፡ ነበር ፡ አሁንም ፡ ነው ።

፪ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. በተከሣሹ ፡ ዘንድ ፡ በአደራ ፡ አስቀመጠው ።

፫ኛ. በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ይህንኑ ፡ ዕቃ ፡ እንዲሰጠው ፡ ተከሣሹን ፡ ጠየቀው ፤ ዕቃ ው ፡ እዚያ ፡ በመቆየቱም ፡ የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ የሚከፍል ፡ መሆኑን ፡ ገለፀ ።

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ ዕቃውን ፡ ለሠሣሹ ፡ ለመመለስ ፡ አልፈቅድም ፡ ከማለቱም ፡ በላይ ፡ አስረክብ ፡ የተባለ ፡ እንደሆነ ፡ ያንኑ ፡ ለመደበቅ ፤ ለመሸጥ ፡ ለመለወጥ ፤ ለመቆራረጥ ፡ ወይም ፡ ለመጉዳት ፡ ዝቷል ።

፭ኛ. ከሣሹ ፡ (ሥእሉን ፡ ) ያጣ ፡ እንደሆነ ፡ በቂ ፡ ካሣ ፡ የሚሆነው ፡ የገንዘብ ፡ ካሣ ፡ አይገኝም ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፮ኛ. ስለዚህ ፡ -

፩ኛ. ተከሣሹ ፡ (ሥእሉን ፡ ) ከመሸጥ ፡ ከመለወጥ ፡ ከመጉዳት ፡ ወይም ፡ ከመደበቅ ፡ ይታገድ ፡ ዘንድ ፡ እንዲታዘዝ ።

፪ኛ. ለከሣሹ ፡ ያስረከበው ፡ ዘንድ ፡ እንዲገደድ ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፵.

### የእርስ ፡ በእርስ ፡ ክርክር ፡

በዚህ ፡ በላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጠቀሰው ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .በከሣሹ ፡ ዘንድ ፡ (የንብረቱን ፡ ዓይነት ፡ በመግለፅ ፡ ) (በአደራ ፡ ) አስቀመጠ ።

፪ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .ዳርጉኛል ፡ በማለት ፡ ተከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ይኸው ፡ ዕቃ ፡ እንዲሰጠው ፡ ጠይቋል ።

፫ኛ. እንደዚሁም ፡ ተከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ለሱ ፡ እንዲሰጥ ፡ ባዘዘለት ፡ መሠረት ፡ ይኸው ፡ ዕቃ ፡ እንዲሰጠው ፡ ጠይቋል ።

፬ኛ. ተከሣሾቹ ፡ በየበኩላቸው ፡ አለን ፡ የሚሉትን ፡ መብት ፡ ከሣሹ ፡ አያውቀውም ።

፭ኛ. ከሣሹ ፡ ንብረቱን ፡ እንዲቀምጡ ፡ በማቆየቱ ፡ ከሚጠይቀው ፡ ዋጋና ፡ ወጪ ፡ በቀር ፡ በንብ

ረቱ ፡ ላይ ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ የሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ የለውም ። ዕቃውንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ላዘዘ ላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለማስረከብ ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው ።

፭ኛ. ክሱ ፡ የቀረበው ፡ ከተከሣሾቹ ፡ ከአንዳቸው ፡ ጋራ ፡ በመመሳጠር ፡ አይደለም ።
(በፎርም ፡ ፩. በ፬. ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፮ኛ. ስለዚህ ፡-

፩ኛ. ከሣሾቹ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በከሣሹ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ከማቅረብ ፡ ይታገዱ ፡ ዘንድ ፡ እንዲታ ዘዙ ።

፪ኛ. በዚህ ፡ ንብረት ፡ ምክንያት ፡ በየበኩላቸው ፡ ስላቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ ተገጣጥመው ፡ እን ዲነጣጠሩ ።

፫ኛ. ክርክሩ ፡ እስከ ፡ አበቃ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ የሚረከብ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲታዘዝ።

፬ኛ. ከሣሹ ፡ ንብረቱን ፡ ለታዘዘው ፡ ሰው ፡ በማስረከብ ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ረገድ ፡ ከተከሣ ሾቹ ፡ ለማንኛቸውም ፡ ቢሆን ፡ ተጠያቂ ፡ ከመሆን ፡ ነፃ ፡ እንዲሆን ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፺፩.

## ዕዳ ፡ ያልተከፈለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ስለ ፡ ራሱና ፡ ስለ ፡ ሌሎችም ፡ ባለገንዘቦች ፡ ሆኖ ፡ የሚያስተዳድረው ፡ ንብረት ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ሚቹ ፡ . . . .በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የከሣሹ ፡ ልኩ ፡ . . . የሆነ ፡ ዕዳ ፡ ነበረበት ፤ ንብረቱም ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ይኸው ፡ ዕዳው ፡ አለበት ። (የብድሩ ፡ ዓይነትና ፡ መያዣም ፡ እንዳለው ፡ ይገለፅ ፡ )

፪ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .በ ፡ . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. ወይም ፡ ወደ ዚያው ፡ ገደማ ፡ ሞተ ። በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. ባደረገው ፡ የመጨረሻ ፡ ኑዛዜ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማ ዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ አድርጐ ፡ ሾመው ፡ (ወይም ፡ ንብረቱን ፡ በአደራ ፡ ሰጥቶ ፡ ወይም ፡ ሳይናዘዝ ፡ ሞቶ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሁኔታ ፡ እንዳለ ፡ የሆነው ፡ ይገለፅ ፡ )

፫ኛ. ኑዛዜውን ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .አስመስክሮአል ፡ (ወይም ፡ ለንብ ረቱ ፡ አስተዳዳር ፡ ደብዳቤዎች ፡ ተሰጥተዋል ፡ )

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ የአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .ን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ (ወይም ፡ የማይን ቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ከማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ሺያጭ ፡ ላይ ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ) በእጁ ፡ አድርጐታል ። ለከሣሹ ፡ ዕዳውን ፡ አልከፈለውም ።
በፎርም ፡ ፩. በ፬. ና ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፭ኛ. ከሣሹ ፡ ለሚቹ ፡ ለአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ተንቀሳቃሽ ፡ (እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ) ንብረት ፡ ሂሣብ ፡ እንዲያዝና ፡ ንብረቱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ እንዲተዳደር ፡ ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፺፪.

## በተረጋገጠ ፡ ኑዛዜ ፡ መሠረት ፡ የሚተዳደር ፡ ሀብት ፡

(ፎርም ፡ ፺፩ን ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ መለወጥ ፡ (፩ኛውን ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ አስቀርቶ ፡ በ፪ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ በመጀመር ፡ ) አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ሚቹ ፡ የ. . . .በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም . ወይም ፡ ወደዚያው ፡ ገደማ ፡ ሞተ ። በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. ባደረገው ፡ የመጨረሻ ፡

ኑዛዜ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . . .ን ፡ ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ አድርጉ ፡ ሾመው ፡ ለከማ ሹም ፡ (ምን ፡ እንደተናዘዘለት ፡ ተገልጾ ፡ )ተናዘዘለት ።

በ፩ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ምትክ ፡ -

ተከማሹ ፡ የአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ . . . .ን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ከብዙም ፡ በጥ ቂቱ ፡ (በኑዛዜው ፡ የታዘዘው ፡ ንብረት ፡ ተገልጾ ፡ ) . . . .ን ፡ በእጁ ፡ አግብቶታል ።

ከ፪ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ምትክ ፡ -

ከማሹ ፡ እላይ ፡ የተገለፀውን ፡ (በኑዛዜ ፡ የታዘዘውን ፡ ንብረት ፡ ገልፆ ፡ ) ተከማሹ ፡ እንዲያስረ ክበው ፡ እንዲታዘዝና ፡ . . . .ይጠይቃል ።

## ቍጥር ፡ ፶፫.

## የኑዛዜ ፡ ውርስ ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ የሚያስተዳድረው ፡ ሀብት ፡

(ፎርም ፡ ፶፩ን ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ መለወጥ ፡ ) (፩ኛውን ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ አስቀርቶ ፡ በ፪ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ በመጀመር ፡ ) አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ሚ፷ ፡ የ. . . .በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. ባደረገው ፡ የመጨረሻ ፡ ኑዛዜ ፡ አቶ ፡ . . . .ን ፡ ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ አድርጉ ፡ ሾመው ፡ ለከማሹም ፡ . . . .ብር ፡ ውርስ ፡ ተናዘዘለት ።

በ፩ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ “ዕዳ”የሚለውን ፡ “ውርስ”በሚለው ፡ መተካት ፡ ነው ።

## ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ፎርም ።

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡ -

፩ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ) . . .የ. . . .በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. ሞተ ። በ. . . . ቀን. . . .ዓ.ም. ፡ ባደረገው ፡ የመጨረሻ ፡ ኑዛዜ ፡ ተከማሹንና ፡ (ተናዛዡው ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ የሞ ተውን ፡ ) አቶ. . . .ን ፡ ጉዳይ ፡ አስፈጻሚዎች ፡ አድርጉ ፡ ሾማቸው ። እንዲሁም ፡ የሚንቀሳቀስም ፡ ሆን ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቱን ፡ ጉዳይ ፡ አስፈጻሚዎቹ ፡ ባለአደራዎች ፡ ሆነው ፡ ኪራ ዩንና ፡ ከንብረቱ ፡ የሚገኘውን ፡ ገቢ ፡ ለከማሹ ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልኩ ፡ ድረስ ፡ እንዲከፍሉት ፡ ተና ዘዘለት ። ከማሹም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዕድሜው ፡ ሀያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የሞላው ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ እዚሁ ፡ ዕድሜ ፡ የደረሰች ፡ ወይም ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ የሌለው ፡ እንደሆነ ፡ የማይንቀ ሳቀሰውን ፡ ንብረቱን ፡ በሕግ ፡ የተናዛዡ ፡ ወራሾች ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ እንዲሁም ፡ የማይንቀሳ ቀሰውን ፡ ንብረቱን ፡ ከሣሹ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ባለንብረቱ ፡ የተወው ፡ ኑዛዜ ፡ ባይገኝና ፡ እላይ ፡ እንደ ተመለከተው ፡ ከማሹ ፡ ልጅ ፡ ባይኖረው ፡ ተናዛዡው ፡ ከሁሉም ፡ የቀረቡ ፡ ዘመዶቹ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ተናዘዘ ።

፪ኛ. ኑዛዜውን ፡ በ. . . ቀን. . . . .ዓ.ም. ተከማሹ ፡ አረጋግጧል ። ከማሹ ፡ አላገባም ።

፫ኛ. ተናዛዡው ፡ ሲሞት ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ እንደዚያውም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ነበረው ። ተከማሹ ፡ የማይንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ ኪራይ ፡ ተቀባይ ፡ ሆን ። የሚንቀሳቀሰውን ፡ ንብረት ፡ አን ዳንዱን ፡ ሸጦታል ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፬ና. ፭. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፬ኛ. ስለዚህ ፡-

፩ኛ. የሚንቀሳቀሰውና ፡ የማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዲ ተዳደርና ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ማናቸውም ፡ ተገቢ ፡ መመሪያ ፡ እንዲሰጥና ፡ ሂሣብም ፡ እንዲያዝ ።

፪ኛ. ከዚህ ፡ በላይ ፡ ወይም ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ለጉዳዩ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ዓይነት ፡ ውሣኔ ፡ እንዲሰጥ ፡ ከማሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቅጥር ፡ ፺፬.

## የባለ ፡ አደራነት ፡ አፈጻጸም ፡፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. አቶ. . . .እና ፡ ወይዘሮ. . . .የተከሣሹ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ ሲጋቡ ፡ በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. ወይም ፡ ወደዚያው ፡ ገደማ ፡ በተፈራረሙት ፡ ውል ፡ (የአቶ . . . .ንብረትና ፡ የግል ፡ ዕቃ ፡ ለተከሣሹ ፡ ለአቶ . . . .እና ፡ ለሌሎቹም ፡ በአቶ . . . .ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ለነበራቸው ፡ ጥቅም ፡ እንዲሆን ፡ ባለቤትነቱ ፡ በተዛወረበት ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ ከሣሹ ፡ ከባለ ፡ አደራዎች ፡ አንዱ ፡ ነው ፡፡

፪ኛ. አቶ. . . .እላይ ፡ የተመለከተውን ፡ የባለ ፡ አደራነት ፡ ግዴታ ፡ በመቀበል ፡ በሰነዱ ፡ መሠረት ፡ የተዛወረውን ፡ የሚንቀሳቀስና ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ (ወይም ፡ ከሱ ፡ ገቢ ፡ ሺያጭ ፡ ላይ ፡ የተገኘውን ፡) እጁ ፡ አግብቷል ፡፡

፫ኛ. አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . .በሰነዱ ፡ መሠረት ፡ የጥቅም ፡ ወለድ ፡ ይገባኛል፡ ሲል ፡ ጠይቋል ፡፡

(በፎርም ፩.በ፩ና. ፩. ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፬ኛ. ከሣሹ ፡ ባለአደራ ፡ በመሆኑ ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ የማናቸውንም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይና ፡ ጥቅም ፡ እንዲሁም ፡ ከዚያው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ከንብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ከግማሹ፡ ሺያጭ ፡ ወይም ፡ የተንቀሳቃሹን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ከተንቀሳቃሹ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ከገሚሱ ፡ ሺያጭ ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ የተገኘውን ፡ ሂሣብ ፡ ለማቅረብ ፡ ስለሚሻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዚህን ፡ የአደራ ፡ ንብረት ፡ ሂሣብ ፡ እንዲተሳሰብና ፡ የአደራው ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ለተከሣሹ ፡ ለ' . . .እና ፡ ለሌሎቹም ፡ አግባብ ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ በሚውልበት ፡ አኳኋን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ይተዳደር ፡ ዘንድ ፡ አቶ ፡ . . . .እና ፡ ሌሎቹም ፡ ባለ ፡ አግባብ ፡ መሆናቸውን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያወቀላቸው ፡ ሰዎች ፡ ባሉበት ፡ እንዲወሰን ፡ አለዚያ ፡ ግን ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡) . . . . ለዚሁ ፡ ተቃራኒ ፡ ምክንያት ፡ እንዳለው ፡ እንዲያስረዳ ፡ ከሣሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ይለምናል ፡፡

## ቍጥር ፡ ፺፭.

## ሺ ያ ጭ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከሣሹ ፡ የተከሣሹን ፡ መሬት ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ይዟል ፡፡

፪ኛ. የወለድ ፡ አግዱ ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡ -

ሀ. ቀንና ፡ ዓ. ም.

ለ. የወለድ ፡ አግድ ፡ አስያዢውና ፡ ያዢው ፡ ስም ፡

ሐ. የተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡

መ. የወለዱ ፡ ሂሣብ ፡

ሠ. በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘው ፡ ንብረት ፡

ረ. አሁን ፡ የሚፈለገው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡

ሰ. የከሳሹ ፡ ባለወለድ ፡ አግድነት ፡ ከሌላ ፡ የተላለፈ ፡ እንደሆነ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ተላለፈለት ፡ ይገለፅ ፡፡

ከሣሹ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘውን ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ አግብቶት ፡ እንደሆን ፡ ይገለፅ ፡

፫ኛ. ከሣሹ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘውን ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ ያገባው ፡ በ. . . .ቀን ፡ . . .

ዓ.ም. ነው ። ንብረቱ ፡ በእጁ ፡ የሚገኝ ፡ ባለወለድ ፡ አግድ ፡ በመሆኑም ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሂሣቡን ፡ ለመተሳሰብ ፡ ዝግጁ ፡ ነው ።

(በፎርም ፡ ፩.በ፩፻.፩. ተራ ፡ ቊጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፪ኛ. ስለዚህ ፡-

፩ኛ. ገንዘቡ ፡ እንዲከፈለው ፡ አለዚያ ፡ ግን ፡ ንብረቱ ፡ እንዲሸጥ ፡

፪ኛ. ከንብረቱ ፡ ሽያጭ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ለከሣሹ ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ያልበቃ ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ ቀሪው ፡ ከሣሹ ፡ ለማመልከት ፡ የሚፈቅድለት ፡ መሆኑ ፡ እንዲረጋገጥለት ፡ ከሣሺ ፡ ይጠይቃል ።

## ቊጥር ፡ ፶፮.

## የተያዘ ፡ ንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ መሬት ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ አስይዟል ።

፪ኛ. የወለድ ፡ አግድ ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡-

ሀ. ቀንና ፡ ዓ. ም.

ለ. የወለድ ፡ አግድ ፡ ያዢውና ፡ አስያዢው ፡ ስም ፡

ሐ. የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡

መ. የወለዱ ፡ ሂሣብ ፡

ሠ. በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘው ፡ ንብረት ፡

ረ. የከሣሹ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ አስያዢነት ፡ ከሌላ ፡ የተላለፈ ፡ እንደሆነ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደተላለፈለት ፡ ባጭሩ ፡ ይገለፅ ። ተከሣሽ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘውን ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ አግብቶት ፡ እንደሆነ ፡ ይገለፅ ፤

፫ኛ. ተከሣሽ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘውን ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ አግብቶታል ፡ ወይም ፡ ኪራዩን ፡ ተቀብሏል ።

(በፎርም ፡ ፩.በ፩፻ .፩. ተራ ፡ ቊጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፬ኛ. ይህ ፡ ንብረት ፡ እንዲለቀቅለትና ፡ እንደገና ፡ በስሙ ፡ እንዲዛወር ፡ (በእጁም ፡ እንዲያገባው ፡ ) ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቊጥር ፡ ፶፯.

## የተጣራ ፡ ግዴታ ፡ ቊጥር ፡ ፩.

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡-

፩ኛ. በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. በተጻፈና ፡ ተከሳሹ ፡ በፈረመው ፡ ውል ፡ እዚያው ፡ ላይ ፡ የተዘረዘረ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከከሣሹ ፡ በ. . . . ብር ፡ ሊገዛ ፡ (ወይም ፡ ለከሣሹ ፡ ሊሸጥ ፡ ) ውል ፡ ገባ ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ ተከሣሹን ፡ በበኩሉ ፡ ውለታውን ፡ እንዲፈጽም ፡ ጠይቆት ፡ ነበር ። ተከሣሹ ፡ ግን ፡ አልፈጸመም ።

፫ኛ. ከሣሹ ፡ በበኩሉ ፡ ውለታውን ፡ በትክክል ፡ ለመፈጸም ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ለተከሣሹ ፡ ተገልፆለታል ።

(በፎርም ፡ ፩.በ፩፻. ፩. ተራ ፡ ቊጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡)

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ ውለታውን ፡ በትክክል ፡ እንዲፈጽምና ፡ ለንብረቱ ፡ ከሣሹ ፡ ሙሉ ፡ ይዞታ ፡ ይኖረው ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ እንዲያደርግ ፡ (ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ተረክቦ ፡ እንዲይዝ ) እንዲሁም ፡ የክሱን ፡ ወጪ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያዘው ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቅጥር ፡ ፺፰.

## የተጣራ ፡ ግዴታ ፡ ቅጥር ፡ ፪.

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡ -

፩ኛ. በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. ከሣሽና ፡ ተከሣሹ ፡ በጽሑፍ ፡ ውል ፡ ተዋዋሉ ፡ ዋናው ፡ ሰነድም፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ይገኛል ።

ተከሣሹ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ፍጹም ፡ ባለቤት ፡ ነበር ።

፪ኛ. በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. ከሣሹ ፡ ለተከሣሹ ፡ . . . .ብር ፡ እንዲከፍለውና ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ንብረቱን ፡ በስሙ ፡ እንዲያዛውርለት ፡ ጠየቀው ።

፫ኛ. በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. ከሣሹ ፡ ንብረቱ ፡ በስሙ ፡ እንዲዛወርለት ፡ እንደገና ፡ ጠየቀ ። (ወይም ፡ ተከሣሹ ፡ ንብረቱን ፡ ለከሣሹ ፡ እንዲዛወር ፡ ሳይፈቅድ ፡ ቀረ ። )

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ ያቀረበው ፡ የንብረት ፡ ማዛወሪያ ፡ ሰነድ ፡ ምንም ፡ የለም ።

፭ኛ. ከሣሹ ፡ የገገርውን ፡ ገንዘብ ፡ ለተከሣሹ ፡ ለመክፈል ፡ አሁንም ፡ ዝግጁና ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው ።

(በፎርም ፡ ፩. በ፬.ና ፭. ተራ ፡ ቊጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ፡ )

፮ኛ. ስለዚህ ፡ -

፩ኛ. ንብረቱን ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ የሰነድ ፡ ማስረጃ ፡ ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ (በውሉ ፡ መሠረት ፡) በስሙ ፡ እንዲያዛውርለት ።

፪ኛ. ንብረቱን ፡ ይዞ ፡ ስለቆየበት ፡ ካሣ ፡ . . . .ብር ፡ እንዲከፈለው ፡ ከሣሹ ፡ ይጠይቃል ።

## ቅጥር ፡ ፺፱.

## ሺ ር ክ ና ፡

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተገለፀው ፡ ከሣሽ ፡ የሚከተለውን ፡ ያመለክታል ፡ -

፩ኛ. እሱና ፡ አቶ ፡ . . . . .ተከሣሹ ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ (ወይም ፡ ወራት ፡ ) በጽሑፍ ፡ በተስ ማሙበት ፡ የማኅበር ፡ ደንብ ፡ (ወይም ፡ በተፈራረሙበት ፡ ውል ፡ ወይም ፡ በቃል ፡ ስምምነት ፡) መ ሠረት ፡ በአንድነት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ ቆይተው ፡ ነበር ።

፪ኛ. በከሣሹና ፡ በተከሣሹ ፡ መካከል ፡ ዓያሌ ፡ ጊዜያት ፡ ጥልና ፡ አለመስማማት ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ በሺርከና ፡ ለጋራ ፡ ጥቅማቸው ፡ አብረው ፡ በመሥራት ፡ የሺርከና ፡ ሥራቸውን ፡ ለመቀጠል ፡ የማ ይቻል ፡ ሆነ ። (ወይም ፡ ተከሣሹ ፡ ከሺርከናው ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ግዴታ ዎች ፡ አፍርሷል ። )

፩ኛ.

፪ኛ.

፫ኛ.

(በፎርም ፡ ፩. በ፬ና. ፭. ተራ ፡ ቊጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መግለፅ ።)

፭ኛ. ስለዚህ ፡-

፮ኛ. ሺርክናው ፡ እንዲፈርስ ፡

፯ኛ. ሂሣቡ ፡ ተመርምሮ ፡ እንዲታወቅ ፡

፰ኛ. ገንዘብ ፡ ተቀባይ ፡ እንዲሾም ፡

(ማስታወሻ ፡) ሺርክናው ፡ እንዲያበቃ ፡ በሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ሺርክናው ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ አስቀርቶ ፡ ስለፈረሰው ፡ ሺርክና ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ማስረጃዎች ፡ መዘርዘር ፡ ነው ።

መ/ የመከላከያ ፡ ክርክር ፡

## ጠቅላላ ፡ መከላከያዎች ፡

መ ካ ድ ፡ ተከሣሹ ፡ (ነገሩን ፡ በመዘርዘር ፡) ክዷል ፡
ተከሣሹ ፡ (ነገሩን ፡ በመዘርዘር ፡) አያምንም ፡
ተከሣሹ ፡ . . . .ያምናል ፡ ግን. . . .ይገልፃል ፡

መ ቃ ወ ም ፡ ተከሣሹ ፡ በፈረሰው ፡ የ. . . .የንግድ ፡ ማኀበር ፡ ሽሪክ ፡ መሆኑን ፡ ይክዳል ፡
ተከሣሹ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ውል ፡ ከከሣሹ ፡ ጋር ፡ መዋዋሉን ፡ ይክዳል ።
ተከሣሹ ፡ እላይ ፡ እንደተመለከተውም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ከከሣሹ ፡ ጋራ ፡ መዋዋሉን ፡ ይክዳል ።
ተከሣሹ ፡ በማኀበሩ ፡ ውስጥ ፡ አለው ፡ የተባለው ፡ ሀብት ፡ መኖሩን ፡ ያምናል ፡ ግን ፡ ከሣሹ ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ አያምንም ።
ከሣሹ ፡ በአቤቱታው ፡ ላይ ፡ ለተከሣሹ ፡ ሸጥኩአቸው ፡ ያላቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም፡ ከእነሱ ፡ ውስጥ ፡ ማንኛቸውንም ፡ ቢሆን ፡ ተከሣሹ ፡ መግዛቱን ፡ ይክዳል ።

ገደብ ፡- ክሱ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፳. ታግዷል ።

ሥ ል ጣ ን ፡- በ. . . .ምክንያት ፡ (ምክንያቱን ፡ በመግለፅ ፡) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ።
የተባለውን ፡ ክስ ፡ ለማስቀረት ፡ በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ የእልማዝ ፡ ቀለበት ፡ ሰጥቶት ፡ ከሣሹም ፡ ተቀብሏል ።

መ ደ ህ የ ት ፡- ተከሣሹ ፡ የደኸየ ፡ መሆኑ ፡ በፍርድ ፡ ተረጋግጧል ።
ክሱ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ከሣሹ ፡ መደህየቱ ፡ ተረጋግጦ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብም ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ተቀባዩ ፡ መሆኑ ፡ ተወስኗል ።

የዕድሜ ፡ ማነስ ፡- የተጠቀሰውን ፡ ውል ፡ በተዋዋሉ ፡ ጊዜ ፡ ተከሣሹ ፡ በእድሜ ፡ አነስተኛ ፡ ነበረ ።

ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የተከፈለ ፡

ተከሣሹ ፡ የተጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ (ወይም ፡ ከተጠየቀው ፡ ውስጥ ፡ . . . .ብር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለከፈለ ፡ ከሣሹ ፡ ይገባኛል ፡ ለሚለው ፡ ወይም ፡ ከጠየቀው ፡ ውስጥ ፡ ለገሚሱ ፡) የተከፈለው ፡ በቂ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ።

ግዴታው ፡ ሳይፈጸም ፡ እንዲቀር ፡ ስለተደረገ ፡-
በ. . . . ቀን . . . . ዓ.ም. ፡ ግዴታው ፡ መፈጸሙ ፡ እንዲቀር ፡ ተደርጓል ።

ውሉ ፡ እንዲሻር ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡- ከሣሹና ፡ ተከሣሹ ፡ ተስማምተው ፡ ውሉ ፡ እንዲሻር ፡ ተደርጓል ።

ከሁን ፡ በፊት ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠበት ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፤

....የከሣሹ ፡ ጥያቄ ፡ በ....ክስ ፡ ተጠቅሶ ፡ በ....ላይ ፡ በተደረገው ፡ ውሣኔ ፡ ታግዷል ፤

ክሱ ፡ ከቀረበ ፡ ወዲህ ፡ የደረሱ ፡ የመከላከያ ፡ ሁኔታዎች ፡-

ክሱ ፡ ከቀረበ ፡ ከ....ዓ.ም. ወዲህ ፡ የሆነውን ፡ መዘርዘር....

## ቍጥር ፡ ፩.

## በተሸጡና ፡ ገዢው ፡ በተረከባቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ምክንያት ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡-

፩ኛ. ተከሣሹ ፡ ዕቃዎቹን ፡ አላዘዘም ፤
፪ኛ. ዕቃዎቹን ፡ ተከሣሹ ፡ አልተረከባቸውም ፤
፫ኛ. ዋጋው ፡ ....ብር ፡ አልነበረም ፤

ወይም ፡ -

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ ከ....ብር ፡ በላይ ፡ ዕቃ ፡ አላዘዘም ፤
፭ኛ. ተከሣሹ ፡ ከ....ብር ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ዕቃዎች ፡ አልተረከበም ።
፮ኛ.
፯ኛ. ተከሣሹ ፡ (ወይም ፡ አቶ ፡ ....የተከሣሹ ፡ ወኪል ፡) ከክሱ ፡ አስቀድሞ ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ለከሣሹ ፡ ወይም ፡ ለከሣሹ ፡ ወኪል ፡ የሚገባውን ፡ በመክፈል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ፈጽሟል ።
፰ኛ. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ ክስ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የሚገባውን ፡ በመክፈል ፡ አስፈላጊውን ፡ ፈጽሟል ።

## ቍጥር ፡ ፪.

## ስለ ፡ መያዣ ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፤

፩ኛ. መያዣው ፡ የተከሣሹ ፡ መያዣ ፡ አይደለም ፤
፪ኛ. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ በመያዣው ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ ገንዘቡን ፡ በቀኑ ፡ ከፍሎታል ፤
፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ቀን ፡ በኋላና ፡ ከክሱ ፡ በፊት ፡ በመያዣው ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዋና ፡ ገንዘብና ፡ ወለድ ፡ ከፍሎታል ።

## ቍጥር ፡ ፫.

## በዋስ ፡ ላይ ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፤

፩ኛ. ዋናው ፡ ባለዕዳው ፡ ከክሱ ፡ በፊት ፡ የሚገባውን ፡ ፈጽሟል ።
፪ኛ. አስገዳጅነት ፡ ባለው ፡ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ለዋናው ፡ ባለ ፡ ዕዳ ፡ ጊዜ ፡ በመስጠት ፡ ከሣሹ ፡ የተከሣሹን ፡ ዋስትና ፡ አውርዶለታል ።

## ቁጥር ፡ ፩.

**በዕዳ ፡ ምክንያት ፡ ለቀረበ ፡ ለማናቸውም ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡**

፩ኛ. የተጠየቀውን ፡ ፰፻. ብር ተከሣሹ ፡ ለከሣሹ ፡ በሸጣቸውና ፡ ባስረከበው ፡ ዕቃዎች ፡ እስቦ፡ ለማስቀረት ፡ ተከሣሹ ፡ መብት ፡ አለው ።

ዝርዝሮቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡

ጥር ፡ ፳፭. ቀን ፡ ፲፱፻፷፰. ዓ.ም. ፭፻. ብር ፡

የካቲት ፡ ፲፫. ቀን ፡ ፲፱፻፷፱. ዓ.ም. ፡ ፫፻. ብር ፡

፰፻. ብር ፡

፪ኛ. ተከሣሹ ፡ ክስ ፡ ከማቅረቡ ፡ በፊት ፡ የተጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ (ወይም ፡ ከተጠየቀው ፡ ውስጥ ፡ . . . .ብር ፡ ) ልከፈል ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ይህንኑ ፡ ገንዘብ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከፍሏል ።

## ቁጥር ፡ ፪.

**በቸልታ ፡ አንዳድ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡**

፩ኛ. በአቤቱታው ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ሰረገላ ፡ ተከሣሹ ፡ የሱ ፡ ሠረገላ ፡ መሆኑንና ፡ በተከሣሹ ፡ ሠራተኞች ፡ ኃላፊነት ፡ ወይም ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ሥር ፡ የነበረ ፡ መሆኑን ፡ ተከሣሹ ፡ ክዷል ፡ ሠረገላው ፡ መኖሪያው ፡ በ. . . . አዲስ ፡ አበባ ፡ የሆነው ፡ ሠረገላዎችንና ፡ ፈረሶችን ፡ እንዲያቀር ብለት ፡ የተከሣሹ ፡ ቅጥር ፡ የሆነውና ፡ የጋማ ፡ ከብቶች ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቤት ፡ ባለቤት ፡ የሆነው ፡ የ . . . . ሠረገላ ፡ ነው ፡ ለዚሁ ፡ ሠረገላም ፡ ኃላፊና ፡ ተቆጣጣሪ ፡ የዚያው ፡ ሰው ፡ ሠራተኛ ፡ ነበረ ።

፪ኛ. የተጠቀሰው ፡ ሠረገላ ፡ . . . . የተባለውን ፡ መንገድ ፡ ለቅቆ ፡ የወጣው ፡ በቸልታ ፡ በድንገት ፡ ወይም ፡ ያለማስጠንቀቂያ ፡ ወይም ፡ በፈጣን ፡ ወይም ፡ በአደገኛ ፡ እርምጃ ፡ መሆኑን ፡ ተከሣሹ ፡ አያምንም ።

፫ኛ. ከሣሹ ፡ ተገቢ ፡ ጥንቃቄና ፡ ንቃት ፡ አድርጐ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ሠረገላው ፡ ሲመጣበት ፡ ለማየትና ፡ ማናቸውም ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ ለማድረግ ፡ ይችል ፡ የነበረ ፡ መሆኑን ፡ ተከሣሹ ፡ ይገልፃል ።

፬ኛ. ከአቤቱታው ፡ በሶስተኛው ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተባለውን ፡ ነገር ፡ ተከሣሹ ፡ አይቀበለውም ።

## ቁጥር ፡ ፫.

**ጥፋት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ለቀረበ ፡ ለማናቸውም ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡**

፩ኛ. ክስ ፡ የቀረበበትን ፡ ጉዳይ ፡ በሙሉ ፡ መካድ ፡

## ቁጥር ፡ ፬.

**ስለተያዙ ፡ ዕቃዎች ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡-**

፩ኛ. ዕቃዎቹ ፡ የከሣሹ ፡ ንብረቶች ፡ አልነበሩም ።

፪ኛ. ዕቃዎቹ ፡ የተያዙት ፡ ለተከሣሹ ፡ የሚገባው ፡ ሒሣብ ፡ ስላልተከፈለው ፡ ነው ። የሒሣቡ ፡ ዝርዝር ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ግንቦት ፡ ፫. ቀን ፡ ፲፱፻፷. ዓ.ም. እነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ድሬ ፡ ዳዋ ፡ የተጓዙበት ፡ ዋጋ ፡ . . . .፰. ኪሎ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ኪሎ ፡ በ ፡ ፩. ብር ፡ ሒሣብ ፡ . . . .፫፻. ብር ፡

## ቍጥር ፡ ፰.

## የሐጸፊነት ፡ መብት ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡

፩ኛ. ደራሲው ፡ ከሣሹ ፡ አይደለም ፡ (ወይም ፡ የደራሲው ፡ ባለአደራ ፡ አይደለም ፡ )
፪ኛ. መጽሐፉ ፡ የተመዘገበ ፡ አይደለም ።
፫ኛ. ተከሣሹ ፡ መብት ፡ አልተላለፈም ።

## ቍጥር ፡ ፱.

## የንግድ ፡ ምልክት ፡ መብት ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡

፩ኛ. የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ የከሣሹ ፡ አይደለም ፡
፪ኛ. የንግድ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ አይደለም ።
፫ኛ. ተከሣሹ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ መብት ፡ አልተላለፈም ።

## ቍጥር ፡ ፲.

## አዋኪ ፡ ነገር ፡ ተደርጓል ፡ ተብሎ ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡

፩ኛ. የከሣሹ ፡ መብራቶች ፡ ያረጁ ፡ አይደሉም ፡ (ወይም ፡ አሉኝ ፡ የሚላቸውን ፡ ሌሎቹን ፡ መብቶች ፡ መካድ ። )

፪ኛ. የተከሣሹ ፡ ሕንፃዎች ፡ የከሣሹን ፡ መብራቶች ፡ ጉልህ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ አያደናቅፏቸውም ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ ራሱም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሠራተኞቹ ፡ ውሀውን ፡ አበላሹተዋል ፡ የተባለውን ፡ (ወይም ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበበትን ፡ ነገር ፡ )ክዷል ። (ተከሣሹ ፡ ክስ ፡ የቀረበበትን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ መብት ፡ አለኝ ፡ ይል ፡ እንደሆነ ፡ በሕግ ፡ የታወቀለት ፡ ወይም ፡ የተፈቀደለት ፡ ወይም ፡. . . . .መሆኑን ፡ ለይቶ ፡ ይገልፅ ። )

፬ኛ. ከሣሹ ፡ የሚገባውን ፡ ሳይፈጽም ፡ በመቅረት ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑን ፡ የሚከተሉት ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎች ፡ ያስረዳሉ ፡ -

በ፲፱፻፶. ዓ.ም. የከሣሹ ፡ ወፍጮ ፡ ሥራ ፡ ጀመረ ፡

በ፲፱፻፶፪. ዓ.ም.ከሣሹ ፡ በእጁ ፡ አገባው ፡

በ፲፱፻፷. የመጀመሪያውን ፡ አቤቱታ ፡ አቀረበ ፡

፭ኛ. ከሣሹ ፡ ስለጠየቀው ፡ ኪሣራ ፡ ተከሣሹ ፡ እላይ ፡ የዘረዘራቸውን ፡ መከላከያዎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ አቤቱታ ፡ የቀረበባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ በከሣሹ ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ያላደረሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልፃል ።

(ሌላም ፡ ለመከላከያ ፡ መሠረት ፡ የሆኑ ፡ ሆኔታዎች ፡ . . . .ለምሳሌ ፡ ላለፈ ፡ ጉዳት ፡ የጊዜ ፡ ገደብ ፡ እንዳለ ፡ . . . .መግለፅ ፡ ያሻል ፡ )

ቍጥር ፡ ፲፭.

በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘ ፡ ንብረት ፡ ልቅ ፡ እንዲሆን ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡

፩ኛ. ተከሣሹ ፡ የወለድ ፡ አግድን ፡ ውል ፡ አልፈረመም ።

፪ኛ. ወለድ ፡ አግድ ፡ ለከሣሹ ፡ አልተላለፈም ። (ካንድ ፡ የበለጠ ፡ ዝውውር ፡ ተደርጓል ፡ ተብሎ ፡ እንደሆን ፡ የተካደውን ፡ መግለፅ ፡ ነው ። )

፫ኛ. ክሱ ፡ በ፲፱. . . .ዓ.ም. ከወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ . . . .ታግዷል ።

፬ኛ. ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘረው ፡ ሂሣብ ፡ ተከፍሏል ።

በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. ኢ.ት. $፫ሺ.

በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. ኢ.ት. $፩ሺ-

፭ኛ. ከሣሹ ፡ ንብረቱን ፡ በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. በእጁ ፡ ካገባው ፡ ጀምሮ ፡ ያለውን ፡ ኪራይ ፡ ተቀብሏል ።

፮ኛ. ከሣሹ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ዕዳ ፡ በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. አውርዷል ።

፯ኛ. ተከሣሹ ፡ ጥቅሙን ፡ በሙሉ ፡ ለእቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .በ. . . .ቀን. . . ዓ.ም. በተጻፈው ፡ ሰነድ ፡ አስተላልፏል ።

ቍጥር ፡ ፲፮.

ንብረት ፡ ለማስለቀቅ ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡

፩ኛ. ከሣሹ ፡ ንብረቱን ፡ ለማስለቀቅ ፡ አለኝ ፡ የሚለው ፡ መብት ፡ በ፲፱. . . .ዓ.ም. ከወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ . . . .ታግዷል ።

፪ኛ. ከሣሹ ፡ በንብረቱ ፡ ያለውን ፡ ጥቅም ፡ በሙሉ ፡ ለእቶ ፡ . . . .አስተላልፏል ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፡ በ. . . .ቀን. . . .ዓ.ም. በተጻፈ ፡ ሰነድ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ዕዳና ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጥቅም ፡ በሙሉ ፡ ለእቶ ፡ . . . .አስተላልፏል ።

፬ኛ. ተከሣሹ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ የተያዘውን ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ አግብቶት ፡ ወይም ፡ ኪራዩን ፡ ተቀብሎ ፡ አያውቅም ።

(ተከሣሹ ፡ ንብረቱን ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ በእጁ ፡ ማግባቱን ፡ ያምን ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ገልፆ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ በእጁ ፡ አለመግባቱን ፡ ያረጋግጥ ። )

ቍጥር ፡ ፲፫.

የተረጋገጠ ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለቀረበ ፡ ክስ ፡ መከላከያ ፡

፩ኛ. ተከሣሹ ፡ ውሉን ፡ አልተዋዋለም ።

፪ኛ. አቶ ፣ (ወይም ፣ በማዕረግ ፣ ስም ፣ ). . . .የተከሣሹ ፣ ወኪል ፣ አልነበረም ፣ (ከሣሹ ፣ ነበረ፣ ብሎ ፣ እንደሆነ ፣ )

፫ኛ. ከሣሹ ፣ የሚከተሉትን ፣ ውለታዎች ፣ አልፈጸመም ፣ -

(ው ለ ታ ዎ ቹ ፣ )

፬ኛ. ተከሣሹ ፣ ከግዲታው ፣ ውስጥ ፣ የተጠየቀባቸውን ፣ ነገሮች ፣ በመዘርዘር ፣ . . . .

፭ኛ. እንዲሸጥ ፣ ስምምነት ፣ ለተደረገበት ፣ ንብረት ፣ የከሣሹ ፣ ባለቤትነት ፣ ተከሣሹ ፣ ሊቀ

በለው ፣ የሚገደድበት ፣ ዓይነት ፣ አይደለም ፣ (ምክንያቱን ፣ መግለፅ፣ )

፮ኛ. በሚከተሉት ፣ ምክንያቶች ፣ ስምምነቱ ፣ ያልተረጋገጠ ፣ ነው ፣ (ምክንያቱን ፣ መዘር

ዘር ፣ )

፯ኛ. (ወይም ፣ ከሣሹ ፣ ጉዳዩን ፣ በማዘግየቱ ፣ ጥፋተኛ ፣ ነው ።

፰ኛ. (ወይም ፣ ከሣሹ ፣ አጭበርብሯል ፣ (ወይም ፣ ያልሆነውን ፣ ሆነ ፣ ብሎ ፣ ተናግሯል ። )

፱ኛ. ስምምነቱ ፣ የሚገባ ፣ አይደለም ፣

፲ኛ. (ወይም ፣ ) ስምምነቱ ፣ የተደረገው ፣ በስሕተት ፣ ነው ።

፲፩ኛ. በቍጥር ፣ ፯. ፣ ፰. ፣ ፱. ፣ ፲. ፣ (ወይም ፣ ከዚያ ፣ ውስጥ ፣ የተፈለገው ፣ ክፍል ፣ )

ዝርዝር ፣ ሁኔታዎቹ ፣ የሚከተሉት ፣ ናቸው ።

፲፪ኛ. ከሺያጩ ፣ ውል ፣ በ፲፩ኛው ፣ ቍጥር ፣ መሠረት ፣ (ወይም ፣ ሁለቱ ፣ ወገኖች ፣ ተስማም ተው ፣ ) ስምምነቱ ፣ እንዲቀር ፣ ሆኗል ። ( ኪሣራ ፣ ተጠይቆ ፣ ተከሣሹ ፣ የኪሣራው ፣ ባለዕዳ ፣ አይደ ለሁም ፣ ብሎ ፣ እንደሆነ ፣ ) ውሉን ፣ ወይም ፣ ውል ፣ አፍርሷል ፣ የተባለውን ፣ መካድ ፣ ወይም ፣ ለመከላከያው ፣ መሠረት ፣ ያደረገውን ፣ ማናቸውንም ፣ ክርክር ፣ ማቅረብ ፣ ለምሳሌ ፣ በ፲፱. . . .ዓ.ም በወጣው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ እንደተመለከተው ፣ ከሣሺ ፣ የተስማማበት ፣ የተደሰተበት ፣ የተ ከሣሹን ፣ ተጠያቂነት ፣ ያወረደበት ፣ አጭብርብሯል ፣ የሚባልበትና ፣ ይህንም ፣ የመሳሰለ ፣ ሁኔታ ፣ እንዳለ ፣ መግለፅ ፣ አለበት ። )

ቍጥር ፣ ፲፬.

## የኑዛዜ ፣ ገንዘብ ፣ ወራሽ ፣ የሆነ ፣ ሰው ፣ ስለ ፣ ኑዛዜው ፣ ሀብት ፣ አስተዳደር ፣ ላቀረበው ፣ ክስ ፣ መከላከያ ።

፩ኛ. የአቶ ፣ (ወይም ፣ በማዕረግ ፣ ስም ፣ ). . . .ኑዛዜ ፣ ሰጪ ፣ መኖሩን ፣ ጋልጿል ፣ በሞተ ፣ ጊዜ፣ በቂ ፣ ሀብት ፣ አልነበረውም ። በሞተ ፣ ጊዜ ፣ የነበረውን ፣ የማይንቀሳቀስ ፣ ንብረት ፣ ተከሣሹ ፣ ሸጦ፣ ያገኘበት ፣ የተጣራ ፣ ገንዘብ ፣ . . . .ብር ፣ ነበር ። እንዲሁም ፣ የተናዛዡው ፣ ሀብት ፣ የነበረውን ፣ ተን ቀሳቃሽ ፣ ንብረት ፣ ተከሣሹ ፣ በእጁ ፣ አግብቶ ፣ ያገኘበት ፣ የተጣራ ፣ ገንዘብ ፣ . . . .ብር ፣ ነበር ።

፪ኛ. ተከሣሹ ፣ የተባለውን ፣ ገንዘብ ፣ በሙሉና ፣ ከማይንቀሳቀሰው ፣ ንብረት ፣ ላይ ፣ ተከሣሹ በኪራይ ፣ የተቀበለውን ፣ . . . .ብር ፣ ለቀብሩና ፣ ለኑዛዜ ፣ ማስፈጸሚያ ፣ እንዲሁም ፣ የተናዛዡን ፣ ዕዳ ፣ ገሚሱን ፣ በመክፈል ፣ ወጪ ፣ አደረገው ።

፫ኛ. ተከሣሹ ፣ ሂሣቡን ፣ ሠርቶ ፣ ግልባጩን ፣ ለከሣሹ ፣ በ. . . .ቀን. . . .፲፱. . . .ዓ.ም. በመ ላክ ፣ ቫውቸሮቹን ፣ ራሱ ፣ መርምሮ ፣ ሂሣቡን ፣ ለማረጋገጥ ፣ የሚችል ፣ መሆኑን ፣ ገልፆለት ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ የተከሳሹን ፣ ጥያቄ ፣ ሳይቀበለው ፣ ቀረ ።

፬ኛ. ስለዚህ ፣ የዚህን ፣ ክስ ፣ ወጪ ፣ ከሣሹ ፣ መክፈል ፣ የሚገባው ፣ መሆኑን ፣ ተከሣሹ ፣ ይገልጻል ።

## ቅጥር ፣ ፲፩.

## (አርእስት ፣ )

## በተሚላ ፣ ሥርዓት ፣ የሚፈጸም ፣ ኑዛዜ ፣

፩ኛ. የተጠቀሱት ፣ የሟቹ ፣ ኑዛዜና ፣ ማሻሻያው ፣ በ፲፱. . . . ዓ.ም. በወጣው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ የተከናወኑ ፣ አይደሉም ።

፪ኛ. ኑዛዜውና ፣ ማሻሻያው ፣ ተከናወኑ ፣ በተባለበት ፣ ጊዜ ፣ የሟቹ ፣ አዕምሮ ፣ ለማሰብ ፣ ለማስታወስና ፣ ለማስተዋል ፣ ብቁ ፣ አልነበረም ።

፫ኛ. ኑዛዜውና ፣ የኑዛዜ ፣ ማሻሻያው ፣ የተከናወኑት ፣ ያላገባብ ፣ በከሣሹና ፣ በሌሎቹም ፣ ለጊዜው ፣ ስማቸው ፣ በተከሣሹ ፣ ዘንድ ፣ ባልታወቀው ፣ የከሣሽ ፣ ተባባሪ ፣ በሆኑት ፣ አግባቢነት ፣ ነበር ።

፬ኛ. ኑዛዜውና ፣ ማሻሻያው ፣ የተከናወነው ፣ በከሣሹ ፣ አጭበርባሪነት ፣ ሲሆን ፣ የአጭበረበረበትም ፣ አኳኋን ፣ ከሣሹ ፣ ለጊዜው ፣ እንደተረዳው ፣ (አኳኋኑን ፣ በመግለፅ ፣ ) . . . . ነው ።

፭ኛ. የተጠቀሰው ፣ ኑዛዜና ፣ ማሻሻያው ፣ በተከናወነበት ፣ ጊዜ ፣ ሟቹ ፣ የተጻፈውን ፣ አውቆ፣ አልተስማማበትም ፣ (ወይም ፣ ሳይሻሻል ፣ በቀረው ፣ አንቀጽ ፣ የተጻፈውን ፣ አውቆ ፣ አልተስማማበትም ፣ )

፮ኛ. ሟቹ ፣ የመጨረሻውን ፣ እውነተኛ ፣ ኑዛዜ ፣ በ. . . . ቀን ፣ ፲፱. . . .ዓ.ም. አድርጐ ፣ በዚያው ፣ መሠረት ፣ ተከሣሹን ፣ ብቻ ፣ የኑዛዜ ፣ አስፈጻሚ ፣ አድርጐ ፣ ሾሞታል ።

ስለዚህ ፦

፩ኛ. ከሣሹ ፣ ያቀረበውን ፣ ኑዛዜ ፣ እንደዚያውም ፣ ማሻሻያውን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ወድቅ ፣ እንዲያደርገው ።

፪ኛ. ሟቹ ፣ . . . .ቀን ፣ ፲፱. . . .ዓ.ም. ፣ ያደረገውን ፣ ኑዛዜ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ በተሟላ ፣ ሕጋዊ፣ አቅድ ፣ የሚያረጋግጥ ፣ ድንጋጌ ፣ እንዲያወጣ ፣ ተከሣሹ ፣ ይጠይቃል ።

## ቅጥር ፣ ፲፪.

## ዝርዝር ፣ ሁኔታዎች ፣ (አንቀጽ ፣ ፪፲፯. )

የሚከተሉት ፣ የ. . . .(ዝርዝር ፣ ሁኔታዎች ፣ እንዲቀርቡ ፣ የታዘዘበትን ፣ ጉዳይ ፣ በመግለፅ ፣ ) ዝርዝር ፣ ሁኔታዎች ፣ ናቸው ።

በ. . . .ቀን ፣ ፲፱. . . .ዓ.ም. በተሰጠው ፣ ትእዛዝ ፣ መሠረት ፣ . . . .(እዚህ ፣ ላይ ፣ እንዲቀርቡ ፣ የታዘዙትን ፣ ዝርዝር ፣ ሁኔታዎች ፣ በያስፈልግም ፣ ልዩ ፣ አግባብ ፣ ያላቸውን ፣ አንቀጾች ፣ በመጥቀስ ፣ መግለፅ ፣ ነው ። )

## ሠ/ ለቀረበ ፣ ክስ ፣ ወይም ፣ ክርክር ፣ ማረጋገጫ ፣ ቃል ፣

እኔ. . . . . . . . . .በዚህ ፣ ክስ ፣ (ወይም ፣ ክርክር ፣ ) ውስጥ ፣ የተመለከተው ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ እኔ ፣ የማውቀውንና ፣ የማምነውን ፣ ያህል ፣ እውነት ፣ መሆኑን ፣ አረጋግጣለሁ ።

(ቀን ፦. . . . . . . . . . . . . . . . . . . .)

(የማረጋገጫውን ፣ ቃል ፣ የሰጠው ፣ ሰው ፣ ፊርማና ፣ መለያ ፣ ዝርዝር ፣ )

## ረ/ አባሪዎች ፤

ለ................/........ፍርድ ፡ ቤት ፡

ከሣሽ ፡ ..........................

ተከሣሽ ፡ ..........................

ከሣሽ ፡ (ወይም ፡ ተከሣሽ ፡ )መልስ ፡ እሰጥባቸዋለሁ ፡ የሚላቸው ፡ ሰነዶች ፡ ዝርዝር ፡

እላይ ፡ ለተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ (ወይም ፡ ክርክር ፡ ) በማስረጃነት ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ሰነዶች ፡ የማቀርብ ፡ መሆኔን ፡ አረጋግጣለሁ ። (ወይም ፡ የማቀርብው ፡ ሰነድ ፡ የለኝም ። )

ሀ/ በእጇ ፡ የሚገኙ ፡ ወይም ፡ ላገኛቸው ፡ የምችል ፡ ሰነዶች ፤

፩ኛ. ከሣሽ ፡ (ወይም ፡ ተከሣሽ ፡ ) የፈረመው ፤ በ...........ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፤

፪ኛ. በ...........ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተጻፈ ፡ ከሣሽና ፡ ተከሣሽ ፡ የተፈራረሙበት ፡ ውል ፤

፫ኛ. በ............ቀን ፡ ፲፱.....ዓ ም. ለከሣሽ ፡ (ወይም ፡ ለተከሣሽ ፡ ) የጻፍኩትና የፈረምኩት ፡ ደብዳቤ ፡ ግልባጭ ።

ለ/ በከሣሽ ፡ (ወይም ፡ በተከሣሽ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ) እጅ ፡ የሚገኙ ፡ ሰነዶች ፤

፩ኛ. ከዚህ ፡ በላይ ፡ በ(ሀ) ፊደል ፡ በ፫ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከተው ፡ ደብዳቤ ፡ ዋናው፤

፪ኛ. የ............አዲተሮች ፡ ያቀረቡት ፡ የሒሣብ ፡ መግለጫ ፤

፫ኛ. የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የሰጠውና ፡ በዚያው ፡ ሚኒስቴር ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ፡ ትእዛዝ ፤

፬ኛ. እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ (ወይም ፡ እንደማምነው ፡ ) በተከሣሽ ፡ (ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ) እጅ ፡ የሚገኝ ፡ -

በ...............ቀን ፡ ፲፱.....ዓ.ም. የተጻፈ ፡ ኑዛዜ ፤

እላይ ፡ ለተጠቀሰው ፡ ጉዳይ ፡ ምስክሮች ፡ የማቀርብ ፡ (ወይም ፡ ምንም ፡ ምስክሮች ፡ ለማቅረብ ፡ የማልችል ፡ ) መሆኔን ፡ አረጋግጣለሁ ።

የምስክር ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ ..............................

የምስክር ፡ ቃል ፡ የሚሰጥበት ፡ ጉዳይ ፡..........................

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የሰጠሁት ፡ ዝርዝር ፡ ሙሉ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጣለሁ ።

ቀን ፡ ....................

ፊርማ ፡

## ሰንጠረዥ ፡ ፪ ።

## ሥርዓት ፡

### ቅጥር ፡ ፩ ።

### ተከሣሽ ፡ እንዲቀርብ ፡ መጥሪያ ።  (አንቀጽ ፡ ፺፱ ።)

ለ..............

.......................... በማለት ፡ ክስ ። ስለ ፡ አቀረረበብዎ ፤ .... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ከ... በ... ሰዓት ፡ ለክሱ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ በ... ፍርድ ፡ ቤት ፡ ራስዎ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ መምሪያ ፡ የተሰጠውና ፡ ስለ ፡ ክሱ ፡ ዋና ፡ ጥያቄዎችን ፡ ሁሉ ፡ ለመመለስ ፡ የሚችል ፡ ወይም ፤ እነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ ለመመለስ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ አብሮት ፡ የሚገኝ ፡ ነገረ ፡ ፈጅዎ ፡ እንዲቀርብ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ይህ ፡ መጥሪያ ፡ ተልኮልዎታል ።

በዚያም ፡ ቀን ፡ ለመከላከያዎ ፡ መሠረት ፡ እንዲሆኑዎ ፡ የሚሹዋቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ሁሉ ፡ ለማቅረብ ፡ መዘጋጀት ፡ አለብዎ ።

እላይ ፡ በተመለከተው ፡ ቀን ፡ ሳይቀርቡ ፡ ቢቀሩ ፤ ክሱ ፡ በሌሉበት ፡ ተሰምቶ ፡ የሚወሰን ፡ መሆኑን ፡ ይወቁት ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተሳለፈ ።

.... ዳኛ ፡

### ቅጥር ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ ተዘዋዋሪ ፡ ሰነድ ፡ ባጭሩ ፡ በቀረበ ፡ ክስ ፡ መሠረት ፡ የሚተላለፍ ፡ መጥሪያ ። (አንቀጽ ፡ ፪፻፹፭ ፤ )

ለ....................................

(ስም ፤ መለያ ፡ ዝርዝርና ፤ የመኖሪያ ፡ ሥፍራ ፡)....... በ... ረገድ ፡ ከሚገባቸው ፡ ከዋናውና ፡ ከወለዱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ቀረብዎ ፡ ... ብር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፹፮ ፡ መሠረት ፡ ግልባጩ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ የተላከልዎትን ፡ ክስ ፡ ስላቀረቡበዎ ፤ ይህ ፡ መጥሪያ ፡ ከደረሰዎ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በአሥር ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ቀርበው ፡ ክሱን ፡ ለመከላከል ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲቀበሉና ፡ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊውን ፡ እንዲያስወስኑ ፡ ይህ ፡ መጥሪያ ፡ ተልኮልዎታል ።

ይህን ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ቢቀሩ ፡ ግን ፡ ከሣሹ ፡ አሥሩ ፡ ቀናት ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ከ... ብር ፡ በላይ ፡ ላልሆነ ፡ ገንዘብና ፡ ለኪሣራም ፡ ለ... ብር ፡ (ወለድም ፡ ቢኖር ፡ ክሱ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሚያዝዘው ፡ ወለድ ፡ ጭምር ፡) ውሳኔ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ለመቅረብ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ፈቃድ ። ስለ ፡ ክሱ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ መከላከያ ፡ ያለዎት ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ቀርበው ፡ ሊከራከሩ ፡ የሚገባዎ ፡ መሆኑን ፡ በሚገልፅ ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የመግለጫ ፡ ቃል ፡ የተደገፈ ፡ ማመልከቻ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማቅረብ ፡ ሊያገኙ ፡ ይችላሉ ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

..... ዳኛ ።

ቍጥር ፡ ፫ ፤

ተከሣሽ ፡ ለሆነው ፡ ሟች ፡ ሕጋዊ ፡ ወኪል ፡ የሚተላለፍ ፡ መጥሪያ ፡፡
(አንቀጽ ፡ ፶)

ለ...........................................................

ከሣሹ ፤ ... ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሞቱት ፡ በ... ላይ ፡ ክስ ፡ ስላቀረቡና ፡ እኒሁ ፡ ከሣሽ ፡ ስማቸው ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ሟች ፡ እርስዎ ፡ ሕጋዊ ፡ ወኪል ፡ መሆንዎንና ፡ በርሳቸው ፡ ምትክ ፡ እርስዎ ፡ ተከሣሽ ፡ እንዲሆኑ ፡ የሚሹ ፡ መሆናቸውን ፡ በመግለጽ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረቡ ፡፡

ክሱን ፡ ለመከላከል ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ከጧቱ ፡ በ... ሰዓት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ይህ ፡ መጥሪያ ፡ ተልኮልዎታል ፡፡ በዚሁ ፡ በተባለው ፡ ቀን ፡ ባይቀርቡ ፡ ግን ፡ ክሱ ፡ በሌሉበት ፡ ተሰምቶ ፡ ይወሰናል ፡፡

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተሰለፈ ፡፡

...... ዳኛ ፡፡

ቍጥር ፡ ፬ ፤

ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሚዳኘው ፡ በታ ፡ ተላልፎ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መጥሪያ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡-
(አንቀጽ ፡ ፷፯ ፡ /፩)

... የተባለው ፡ ተከሣሽ ፡ (ወይም ፡ ምስክር ፡) አሁን ፡ የሚኖረው ፡ በ... መሆኑ ፡ እላይ ፡ በተመለከተው ፡ ክስ ፡ ተገልጾ ፡ መጥሪያ ፡ ከክሱ ፡ ቅጅ ፡ ጋራ ፡ ለተከሣሹ ፡ (ወይም ፡ ለምስክሩ ፡) ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ በ... ለሚገኘው ፡ ለ... ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲተላለፍ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ተልኳል ፡፡

ለመጥሪያው ፡ የሚጠየቀው ፡ የ... የዳኝነት ፡ ወጪ ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቴምብር ፡ ተከፍሏል ፡፡ ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም.

.... ዳኛ ፡፡

ቍጥር ፡ ፭ ፤

ለእሥረኛ ፡ ወይም ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቶች ፡ ባልደረባ ፡ እንዲደርስ ፡ ስለሚላክ ፡
መጥሪያ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡፡
(አንቀጽ ፡ ፺፮ ፡፡ )

ለ...........................................................

የ... ወህኒ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡፡

የ... አዛዥ ፡ መኰንን ፡፡

በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፮ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ የወህኒ ፡ ቤቱ ፡ እሥረኛ ፡ ለሆነው ፡ (ወይም ፡ በርስዎ ፡ ሥር ፡ ለሚያገለግለው ፡) ... ለተባለው ፡ ተከሣሽ ፡ እንዲደርስ ፡ የሚያስፈልገው ፡ መጥሪያ ፡ በሁለት ፡ ቅጅ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተልኮልዎታል ፡፡

የዚሁ ፡ መጥሪያ ፡ ግልባጭ ፡ ለተከሣሹ ፡ እንዲደርስ ፡ አድርገው ፡ ዋናውን ፡ ተከሣሹ ፡ ከፈረመበት ፡ በኋላ ፡ ለመድረሱ ፡ የርስዎ ፡ ማረጋገጫ ፡ ተጽፎበት ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲመልሱት ፡ ይጠየቃሉ ፡፡

....... ዳኛ ፡፡

## ቍጥር ፡ ፮ ፡

## ለሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ ወይም ፡ ለወታደር ፡ እንዲደርስ ፡ ስለ ፡ ተላከ ፡ መጥሪያ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ።

(አንቀጽ ፡ ፻፱ ።)

ለ.........................................................................

በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፱ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ በርስዎ ፡ ሥር ፡ ያገለግላል ፡ ለተባለው ፡ ተከሣሽ ፡ ለ... እንዲደርስ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መጥሪያ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ በሁለት ፡ ቅጅ ፡ ተልኮልዎታል ። የመጥሪያው ፡ ግልባጭ ፡ ለተከሣሹ ፡ እንዲደርስ ፡ አድርገው ፡ ዋናውን ፡ ተከሣሹ ፡ ከፈረመበት ፡ በኋላ ፡ ለመድረሱ ፡ የርስዎ ፡ ማረጋገጫ ፡ ተጽፎበት ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲመልሱት ፡ ይጠየቃሉ ።

.... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፯ ፡

## ከሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚተላለፍ ፡ መጥሪያ ፡ ሲመለስ ፡ አብሮ ፡ የሚላክ ።

(አንቀጽ ፡ ፻፲ ፡ ፩ ፡)

በቍጥር ፡ ... በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በ... ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ለ... እንዲደርስ ፡ ከ... የተላከውን ፡ የክስ ፡ ቃል ፡ ይመልከቱት ። ... በመሐላ ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ ማስረጃውን ፡ የተቀበሉ ፡ መሆናቸውንና ፡ ... ከቃሉ ፡ ግልባጭ ፡ ጋር ፡ ለ... ተመልሶ ፡ እንዲላክ ፡ መታዘዙን ፡ በመግለጽ ፡ መጥሪያ ፡ አድራሺው ፡ መኰንን ፡ የጻፉበትን ፡ ማረጋገጫ ፡ ቃል ፡ ይመልከቱት ።

..... ዳኛ ።

ማ ስ ታ ወ ሻ ፡ ይህ ፡ አጻጻፍ ፡ የሚያገለግለው ፡ ለመጥሪያ ፡ በሚያስፈልገው ፡ አኳኋን ፡ ለሚደርስ ፡ ግን ፡ መጥሪያ ፡ ላልሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

## ቍጥር ፡ ፰ ፡

## ተመልሶ ፡ ከሚላክ ፡ መጥሪያ ፡ ወይም ፡ ማስታወቂያ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የሚላክ ፡ የመጥሪያ ፡ አድራሽ ፡ መኰንን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ።

(አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ።)

የ.................... የ............................................................ ልጅ ፡ የመሐላ ፡ ቃል ።

እኔ ፡ ... የመሐላ ፡ ቃሌን ፡ ወይም ፡ የማረጋገጫ ፡ ቃሌን ፡ በመስጠት ፡ የሚከተለውን ፡ እገልጻለሁ ።

፩ኛ ፡ የዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መጥሪያ ፡ አድራሽ ፡ ነኝ ።

፪ኛ ፡ በቍጥር ፡ ... በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. መጥሪያ ፡ (ማስታወቂያ) ተቀብያለሁ ።

፫ኛ ፡ ...ን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አውቀው ፡ (አውቃት ፡) ነበረ ። መጥሪያውንም ፡ (ማስታወቂያውንም ፡) በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ከ... ወይ... ገደማ ፡ ግልባጩን ፡ ለሱ ፡ (ለሷ) በመስጠትና ፡ በዋናው ፡ መጥሪያ ፡ (ማስታወቂያ ፡) እሱን ፡ (እሷን) በማስፈረም ፡ መጥሪያውን ፡ (ማስታወቂያውን ፡) ለሱ ፡ (ለሷ) አድርሻለሁ ።

ሀ.

ለ.

ሀ. የተላከለት ፡ ሰው ፡ ጽሑፉን ፡ መፈረሙ ፡ ወይም ፡ እምቢ ፡ ብሎ ፡ ሳይፈርም ፡ መቅረቱ ፡ ይህም ፡ ሲሆን ፡ ማን ፡ እንደነበረ ፡ ይገለጽ ።

ለ. የመጥሪያ ፡ አድራሺው ፡ መኰንን ፡ ፊርማ ፡

ወይም ፡-

፫ኛ ፡ ...ን. እኔ ፡ ስለማላውቀው ፡ ... አብሮኝ ፡ ሄዶ ፡ ይህ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አመለከተኝ ፤ መጥሪያውንም ፡ (ማስታወቂያውን ፡) በ... ቀን ፲፱... ዓ.ም. ከ... በ... ሰዓት ፡ ግል ባጩን ፡ ለሱ ፡ (ለሷ) ሰጥቼ ፡ በዋናው ፡ መጥሪያ ፡ (ማስታወቂያ ፡) ላይ ፡ እሱን ፡ (እሷን) በማስፈረም ፡ ለሱ ፡ (ለሷ) አድርሻለሁ ።

ሀ.

ለ.

ሀ. ጽሑፉን ፡ የተላከለት ፡ ሰው ፡ ፈርሞት ፡ እንደሆን ፡ ወይም ፡ አልፈረመም ፡ ብሎ ፡ እንደሆን ፡ ይህን ፡ ሲሆን ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ነበሯ ፡ ይገለፅ ፡

ለ. የመጥሪያ ፡ አድራሺው ፡ መኰንን ፡ ፊርማ ።

ወይም ፡-

፫ኛ ፡ ... የተባለው ፡ ሰው ፡ አብሮኝ ፡ ሄዶ ፡ ለዘወትሩ ፡ ... የሚኖርበት ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ አሳየኝ ። ...ን ፡ እዚያ ፡ አላገኘሁትም ።

ሀ.

ለ.

ሀ. በተለይ ፡ በአንቀጽ ፡ ፶፩ ፡ እና ፡ ፶፫ ፡ የተደነገገውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ጽሑፉ ፡ የተሰጠበትን ፡ አኳኋን ፡ በሙሉና ፡ በትክክል ፡ ዘርዝረህ ፡ ግለፅ ።

ለ. የመጥሪያ ፡ አድራሺው ፡ መኰንን ፡ ፊርማ ።

ወይም ፡

ካሁን ፡ በፊት ፡ በተገለጸው ፡ አኳኋን ፡ ሳይሆን ፡ በዚያ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ የመጥሪያ ፡ አሰጣጥ ፡ ታዞ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ እንዲሆን ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለይተህ ፡ በመጥቀስ ፡ መጥሪያው ፡ የተሰጠበትን ፡ አኳኋን ፡ በሙሉና ፡ በትክክል ፡ ዘርዝረህ ፡ ገለፅ ።

በኔ ፡ ፊት ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የሰጠው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ (የማረጋገጫ ፡ ቃል ።)

## ቍጥር ፡ ፱ ፤

## ለምስክር ፡ የተላለፈ ፡ መጥሪያ ።

## (አንቀጽ ፡ ፻፲፭ ፡ እና ፡ ፻፲፬ ።)

ለ.............................................................................................

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ስለ... ይ... ዘንድ ፡ እንዲገኙ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፤ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በ... ሰዓት ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ (ራስዎ ፡) እንዲቀርቡ ፡ ደግሞም ፡ ...ን ፡ ይዘው ፡ እንዲመጡ ፡ (ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ለ... ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲልኩ ፡) አስታውቃለሁ ።

ለመንገድ ፡ ኪሣራዎና ፡ ለሌላው ፡ ወጪዎ ፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ የሚሆነው ፡ ... ብር ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ተልኮልዎታል ። ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖርዎ ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ቢቀሩ ፡ በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፬፻፵፯ ፡ እንደተደነገገው ፡ ባለ መገኘትዎ ፡ አስፈላጊው ፡ ይፈጸምብዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

..... ዳኛ ።

ማ ስ ገ ን ዘ ቢ ያ ።

፩ኛ ፡ መጥሪያ ፡ የተላከልህ ፡ ለመመስከር ፡ ሳይሆን ፡ ሰነድ ፡ ለማቅረብ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ በተጠየቀው ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ ሰነድ ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ ካደረግህ ፤ የመጥሪያውን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደፈጸምህ ፡ ይቆጠራል ።

፪ኛ ፡ ከተባለው ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ እዚሁ ፡ የቆየህ ፡ እንደሆን ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ለምትቆይበት ፡ ለያንዳንዱ ፡ ቀን ፡ ... ብር ፡ ይከፈልሀል ።

## ቍጥር ፡ ፲ ፤

### ምሥክር ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ።

ለ.................................................................

የ...... ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የፖሊስ ፡ አዛዥና ፡ ሌሎችም ፡ የፖሊስ ፡ መኰንኖች ፡ ... መጥሪያ ፡ ... ደርሶት ፡ ሳይቀርብ ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ (መጥሪያውን ፡ ላለመቀበል ፡ ስለ ፡ ሚደበቅና ፡ ስለ ፡ ሚሸሽ ፡) ...ን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያመጡት ፡ ታዘዋል ።

እንዲሁም ፡ ትእዛዙ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀንና ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ ያልተፈጸመበትን ፡ ምክንያት ፡ በመግለጽ ፡ ፈርመው ፡ ይህንኑ ፡ ትእዛዝ ፡ በ... ቀን ፡ ወይም ፡ ከ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በፊት ፡ መልሰው ፡ እንዲልኩ ፡ ታዘዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

..... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፩ ፤

### በወህኒ ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ።

... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ቀርቦ ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ (ወይም ፡ ሰነድ ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡) መያዣ ፡ እንዲያሲዝ ፡ በማለት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ ክስ ፡ ከሣሽ ፡ (ወይም ፡ ተከሣሽ ፡) የሆነው ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላመለከተ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ መያዣ ፡ እንዲያስይዝ ፡ ...ን ፡ ጠይቆት ፡ እምቢ ፡ ስላለ ፡ ይህንኑ ፡ ...ን ፡ ተቀብለው ፡ በሲቢሉ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ እንዲጠበቅ ፡ እንዲያደርጉና ፡ ብዚሁ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ በ... ሰዓትና ፡ እንዲሁም ፡ ወደፊት ፡ በሚታዘዘው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወደዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያቀርቡት ፡ ታዘዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

...... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፪ ፤

### በወህኒ ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ።

### (አንቀጽ ፡ ፻፳፩ ።)

ለ..........................................................................................

የ.............................. ወህኒ ፡ ቤት ፡ አስተዳዳሪ ።

.................... ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ (ወይም ፡ ሰነድ ፡ እንዲያቀርብ ፡) ለማድረግ ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ እየተጠበቀ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ከሣሹ ፡ (ወይም ፡ ተከሣሹ ፡) ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የምሥክርነት ፡ ቃሉን ፡ ለመስጠት ፡ (ሰነዱን ፡ ለማቅረብ ፡) ባለመቻሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በ... ሰዓት ፡ ይቀ

ርብ ፡ ዘንድ ፡ መያዣ ፡ እንዲያሲዝ ፡ ጠይቆት ፡ አላሲዝም ፡ ስላለ ፡ ...ን ፡ ተቀብለው ፡ በሲቢሉ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ እየተጠበቀ ፡ እንዲቆይ ፡ እንዲያደርጉና ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ... ሰዓት ፡ ወደዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያቀርቡት ፡ ይሁን ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

.... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፫ ።

## ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አባሪ ፡ ከሣሽ ፡ ሆኖ ፡ ሊጨመር ፡ ያስፈልጋል ፡ ለሚለው ፡ ሰው ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ። (አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ፪ ።)

ለ.......................................................................

(ስም ፡ መለያ ፡ ዝርዝርና ፡ የመኖሪያ ፡ ሥፍራ ፡ መግለጽ ።)

........................... እላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ክስ ፡ በ... ረገድ ፡ በ... ላይ ፡ ስላቀረበና ፡ የሚያከራከረውን ፡ ነገር ፡ በሙሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መርምሮ ፡ በትክክልና ፡ በተሟላ ፡ አኳኋን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠትና ፡ ለመወሰን ፡ ይቻለው ፡ ዘንድ ፡ እርስዎም ፡ በከሣሽነት ፡ እንዲጨመሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ታየው ፡ ለመጨመር ፡ ይፈቅዱ ፡ እንደሆነ ፡ በ... ቀን ፡ ወይም ፡ ከ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በፊት ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያስታውቁ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውቃለን ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

## ሰንጠረዥ ፣ ፫ ፣

## ብዙ ፣ ዓይነት ፣ ፎርሞች ።

### ቍጥር ፣ ፩ ፣

### ስለ ፣ ሰነዶች ፣ መተማመኛ ፣ ቃል ፣ እንዲሰጥ ፣ የተላከ ፣ ማስታወቂያ ።
### (አንቀጽ ፣ ፪፻፱ ።)

በዚህ ፣ ክስ ፣ ከሣሹ ፣ (ወይም ፣ ተከሣሹ ፣) ከዚህ ፣ ግርጌ ፣ የተዘረዘሩትን ፣ እያሌ ፣ ሰነዶች ፣ በማስረጃነት ፣ የሚጠቅሳቸው ፣ መሆኑን ፣ ስለ ፣ ገለጸና ፣ እነሱም ፣ በ... ላይ ፣ በ... ቀን ፣ በ... እና ፣ ... ሰዓቶች ፣ መካከል ፣ ባለው ፣ ጊዜ ፣ ውስጥ ፣ በተከሣሹ ፣ (በከሣሹ ፣) በነገረ ፣ ፈጁ ፣ ወይም ፣ በወኪሉ ፣ ሊፈተሹ ፣ ስለ ፣ ሚችሉና ፣ ዋና ፣ የተባሉት ፣ ሰነዶች ፣ እንደተባለው ፣ የተጻፉ ፣ የተፈረሙና ፣ አስፈላጊው ፣ የተፈጸመባቸው ፤ እንዲሁም ፣ ግልባጮች ፣ የተባሉትም ፣ ትክክል ፣ ግልባጮች ፣ መሆናቸውን ፣ እንዲሁም ፣ ለተላከለት ፣ ደርሰዋል ፣ የተባሉትም ፣ መላካቸውንና ፣ መድረሳቸውን ፣ ከነሱ ፣ ውስጥ ፣ ለማስረጃነት ፣ ሊቀርቡ ፣ የማይችሉትን ፣ ለይቶ ፣ በመዘርዘር ፣ እላይ ፣ ከተጠቀሰው ፣ ጊዜ ፣ ከመጨረሻው ፣ ሰዓት ፣ አንስቶ ፣ ባአርባ ፣ ስምንት ፣ ሰዓት ፣ ውስጥ ፣ ተከሣሹ ፣ (ወይም ፣ ከሣሹ ፣) የመተማመኛ ፣ ቃሉን ፣ እንዲሰጥ ፣ መታዘዙን ፣ እናስታውቃለን ።

አቶ ፣ (ወይም ፣ በማዕረግ ፣ ስም ፣)... የከሣሽ ፣ (ወይም ፣ የተከሣሽ ፣) ነገረ ፣ ፈጅ ፣ (ወይም ፣ ወኪል ፣)

ለአቶ ፣ (ወይም ፣ በማዕረግ ፣ ስም ፣)... የተከሣሽ ፣ (ወይም ፣ የከሣሽ ፣) ነገረ ፣ ፈጅ ፣ (ወኪል ፣)

(ሰነዶቹን ፣ ዘርዝር ፣ እያንዳንዱም ፣ ሰነድ ፣ ዋና ፣ ወይም ፣ ግልባጭ ፣ መሆኑን ፣ ለይተህ ፣ ግለፅ ።)

### ቍጥር ፣ ፪ ፣

### በፍርድ ፣ ስለሚታዩት ፣ ጭብጦች ፣ ባለጉዳዮቹ ፣ የሚያደርጉት ፣ ስምምነት ።
### (አንቀጽ ፣ ፪፻፸፯ ።)

እኛ ፤ እላይ ፣ የተጠቀሰው ፣ ክስ ፣ ባለጉዳዮች ፣ በተካሰስንበት ፣ ጉዳይ ፣ ውስጥ ፣ በፍርድ ፣ ሊታይ ፣ የሚገባውን ፣ ማስረጃ ፣ (ወይም ፣ የሕግ ፣) ክርክር ፣ በስምምነት ፣ ወስነናል ፤ የክርክራችን ፣ ጭብጥም ፣ በ... ቀን ፣ ፲፱... ዓ.ም. የተፈረመውና ፣ ኤግዚቢት ፣ ... ተብሎ ፣ ፋይል ፣ የተከፈተለት ፣ የባለዕዳነት ፣ ማረጋገጫ ፣ ሰነድ ፣ ከይርጋው ፣ ሕግ ፣ ውሣኔ ፣ ውጭ ፣ መሆንና ፣ አለመሆኑን ፣ መለየት ፣ ነው ። (ወይም ፣ ጭብጡ ፣ ሌላ ፣ እንደሆነ ፣ ይገለጽ ።)

ስለዚህ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ያንኑ ፣ ጭብጥ ፣ አይደለም ፣ (ወይም ፣ ነው ፣) በማለት ፣ በሚያደርገው ፣ ውሣኔ ፣ መሠረት ፣ እኛ ፣ በበኩላችን ፣ ... ብር ፣ (ወይም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የሚወስነውን ፣ ገንዘብ ፣) ልንከፍል ፣ እያንዳንዳችን ፣ ግዴታ ፣ ገብተናል ። እኔም ፣ ... ይህንኑ ፣ ... ብር ፣ (ወይም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የሚወስነውን ፣ ገንዘብ ፣) እላይ ፣ በተጠቀሰው ፣ ሰነድ ፣ ለተመለከተው ፣ ሂሣብ ፣ ሙሉ ፣ ክፍያ ፣ አድርጌ ፣ እቀበላለሁ ። (ወይም ፣ በውሣኔው ፣ መሠረት ፣ እኔ ፣ ... ፤ ... አደርጋለሁ ፣ ወይም ፣ አላደርግም ፣ ...) ።

ከሣሽ ፣
ተከሣሽ ፣

ምስክሮች ፡ ፩ኛ ፡
፪ኛ ፡

በ.... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም.

## ቍጥር ፡ ፫.

### ክሱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተዛውሮ ፡ እንዲታይ ፡ ስለ ፡ ቀረበ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ።

ለ..................................

በቍጥር ፡ .....፲፱....ዓ.ም ፡ ለ....ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበውና ፡ ....ከሣሽ ፡ ... .ም. ተከሣሽ ፡ የሆኑበት ፡ ክስ ፡ በ....ወደ ሚገኘው ፡ ወደ ፡ ....ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተዛውሮ ፡ እንዲታይ ፡ ....የሆነው ፤ ....ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበ ።

ማመልከቻው ፡ ለ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ሊሰማ ፡ ስለተቀጠረ ፡ መቃወሚያ ፡ ቢኖርዎ ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ሊያቀርቡ ፡ መቻልዎን ፡ እናስታውቃለን ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ፡

..........ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፬.

### ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡
### (አንቀጽ ፡ ፪፻፲፭.)

ተከሣሹ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ....ብር ፡ መክፈሉንና ፡ ይህም ፡ ገንዘብ ፡ ከሣሹ ፡ ለጠየቀው ፡ ሒሳብ ፡ሙሉ ፡ ክፍያ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የገለፀ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውቃለን ።

.................የተከሣሹ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡

ለ.........የከሣሹ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡

## ቍጥር ፡ ፭.

### መቃወሚያ ፡ ቢኖር ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡
### (ጠቅላላ ፡ ፎርም ፡ )

ለ......................

እላይ ፡ ስሙ ፡ የተጠቀሰው ፡ ....ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ....ሲል ፡ ስላመለከተ ፡ ለማመልከቻው ፡ መቃወሚያ ፡ ቢኖርዎ ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ከቀትር ፡ በፊት ፡ በ....ሰዓት ፡ እዚህ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ራስዎ ፡ ቀርበው ፡ ወይም ፡ አስፈላጊው ፡ ትእዛዝ ፡ በተሰጠው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ አማካይነት ፡ እንዲያስረዱ ፡ ይህን ፡ ባያደርጉ ፡ ግን ፡ ማመልከቻው ፡ ተሰምቶ ፡ አመልካቹ ፡ በሚሰጠው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ የሚወሰን ፡ መሆኑን ፡ እንዲያውቁ ት ፡ እናስጠነቅቃለን ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ።

..........ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፯.

### ከሣሽ ፡ (ወይም ፡ ተከሣሽ ፡ )ያቀረባቸው ፡ ሰነዶች ፡ ዝርዝር ፡
### (አንቀጽ ፡ ፪፻፲. )

| ቍጥር ፡ | የሰነዶቹ ፡ ዓይነት ፡ | በሰነዶቹ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ ቀን ፡ እንዳለ ፡ | የባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ወይም ፡ የነገረ ፡ ፈጁ ፡ ፊርማ ፡ |
| --- | --- | --- | --- |
| ፩. | ፪. | ፫. | ፬. |

## ቍጥር ፡ ፰.

### የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ለቅቆ ፡ ለመሄድ ፡ የተቃረበ ፡ ምስክር ፡ እንዲጠየቅ፡ ስለ ፡ ተወሰነው ፡ ቀን ፡ ለባለጉዳዩቹ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡
### (አንቀጽ ፡ ፪፻፳፬. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

. . . .የተባለው ፡ . . .የቆጠረው. . . .የተባለው ፡ ምስክር ፡ በፍጥነት ፡ እንዲጠየቅ ፡ . . . . . ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበና ፡ ይኸው ፡ ምስክርም ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ለቅቆ ፡ ለመሄድ ፡ የተቃረበ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በትክክል ፡ እንዲረዳው ፡ ስለ አደረገ ፡ (ወይም ፡ ሌላ ፡ ጠቃሚና ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ በመግለፅ ፡ ). . . .የተባለውን ፡ ምስክር ፡ በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የ. . . .ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቃሉን ፡ የሚቀበለው ፡ መሆኑን ፡ እና ስታውቃለን ።

በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም.

. . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፱.

### የሌለውን ፡ ምስክር ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚሰጥ ፡ ሥልጣን ፡
### (አንቀጽ ፡ ፪፻፳፫.

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

. . . .የምስክርነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ . . . .ስለ ፡ ጠያቂና ፡ ስለ ፡ . . . .፤ የዚህኑ ፡ . . . .የተባለውን ፡ ምስክር ፡ ቃል ፡ በምርመራ ፡ (ወይም ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ) እንዲቀበሉ ፡ ይጠየቃሉ ፡ ለዚሁም ፡ ሥራ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሆነው ፡ ተሾመዋል ። ባለጉዳዮቹ ፡ ወይም፡ ወኪሎቻቸው ፡ የቀረቡ ፡ እንደሆነ ፤ ቃሉን ፡ እነሱ ፡ ባሉበት ፡ እንዲቀበሉ ፡ ሆኖ ፡ ተለይተው ፡ በተገለፁ ፡ ጭብጦች ፡ ላይ ፡ እነሱ ፡ ምስክሩን ፡ ሊጠይቁት ፡ ይችላሉ ። ቃሉን ፡ ተቀብለው ፡ እንዳበቁ ፡ ውጤቱን ፡ እንዲያስታውቁ ፡ ይጠየቃሉ ።

እርስዎ ፡ በሚያቀርቡት ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ተከሣሹ ፡ ተገድዶ ፡ እንዲቀርብ ፡ ማናቸውም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ሊያስተላልፍ ፡ ይችላል ።

እላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ሥራዎ ፡ ዋጋ ፡ እንዲሆን ፡ . . . .ብር ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተልኳል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተላለፈ ።

. . . . . . . .ዳኛ

## ቅጥር ፡ ፱.

## የጥያቄ ፡ ደብዳቤ ፡

## (አንቀጽ ፡ ፲፱፻፮.

(የጽሕፈት ፡ አርእስት ፡ ለ. . . . . . .ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ )

አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . .ከሣሽ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ተከ ሣሽ ፡ . . . . ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ቀረቡና ፡ በዚሁ ፡ ክስም ፡ ከሣሹ ፤ . . . .ሲል ፡ ስላመለከተ ፡

(ያመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ )

የዳኝነቱ ፡ ሥራ ፡ በትክክል ፡ እንዲከናወንና ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ የሚከራከሩበት ፡ ነገር ፡ በሚገባ ፡ እንዲወሰን ፡ ለማድረግ ፡ ስማቸው ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘረው ፡ ሰዎች ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ በመሐላ ፡ እንዲሰጡ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ተገለ ጠለት ፡

### የምስክሮቹ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡

አቶ ፡ (ወይም ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . . . . . . . . .

አቶ ፡ (ወይም ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . .

እንዲሁም ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . . . . . .

አቶ ፡ (ወይም ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . . . . . .

እነዚህ ፡ ምስክሮች ፡ የሚኖሩት ፡ በተከበረው ፡ ፍርድ ፡ ቤትዎ ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ ለተባለ ፡

ስለዚህ ፡ እላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ በመመልከትና ፡ ይህንኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማገዝ ፡ ቢሉ ፡ እነዚሁ ፡ ምስክሮች ፡ እርስዎ ፡ በሚወስኑት ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፤ ባንዳችሁ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ ሆናችሁ ፡ በምትገኙበት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤትዎ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ የምሥክሮ ቹን ፡ ቃል ፡ ጠይቆ ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ እንዲቀርቡ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲልኩ ላቸውና ፡ እነዚህ ፡ ምስክሮች ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ በተላኩት ፡ ጥያቄዎች ፡ መሠ ረት ፡ (ወይም ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የከሣሹና ፡ የተከሣሹ ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ በሚደርሰው ፡ ማስ ታወቂያ ፡ መሠረት ፡ በሚገኙት ፡ በማናቸውም ፡ ፊት ፡ ቃላቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ እንዲያደርጉ ፡ የ. . . . ፍርድ ፡ ቤት ፡ . . . . በመሆኔ ፡ እኔ ፡ . . . . በማክበር ፡ አሳስባለሁ ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የእነዚሁ ፡ ምስክሮች ፡ ቃል ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲዘጋጅና ፡ በዚሁ ፡ ጥያቄ ፡ ጊዜ ፡ ቀርበው ፡ የነበሩት ፡ መጻሕፍት ፤ ደብዳቤዎች ፡ ወረቀቶችና ፡ ሰሆነዶች ፡ እንዲለዩ ፡ ሆነው ፡ ምል ክት ፡ እንዲደረግባቸው ፡ እንዲሁም ፡ ምርመራውንም ፡ በፍርድ ፡ ቤትዎ ፡ ማኅተም ፡ ወይም ፡ በር ስዎ ፡ በኩል ፡ በተለመደው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ዓይነት ፡ አረጋግጠው ፡ በተጨማሪ ፡ የሚጠየቁ ፡ ሌሎች ፡ ምስክሮች ፡ ቢኖሩ ፡ ይኸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲጠይቃቸው ፡ ከሚያሳስብ ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ መልሰው ፡ እንዲልኩ ፡ በማክበር ፡ አሳስባለሁ ።

ማ ስ ታ ወ ሻ ፡ ጥያቄው ፡ የሚላከው ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ኪዚሀ ፡ ፎርም ፡ በመጨረሻው ፡ መስመር ፡ ላይ ፡ "መልሰው ፡ "ከሚለው ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ን. ነ. መንግሥት ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ "የሚሉትን ፡ ቃላት ፡ ማግባት ፡ ያስፈል ጋል ።

## ቍጥር ፡ ፲.

## ጉዳዩ ፡ በቦታው ፡ ላይ ፡ እንዲመረመር ፡ ወይም ፡ የሒሣብ ፡ ምርመራ ፡ እንዲያደርግ ፡ ስለ ፡ ሚሰጥ ፡ ሥልጣን ፡

(አንቀጽ ፡ ፪፻፹፯. እና ፡ ፪፻፹፰. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ለ. . . .መርማሪዎች ፡ መሾም ፡ ለዚህ ፡ ክስ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየ ፡
ለ. . . .መርማሪ ፡ ሆነው ፡ መሾምዎን ፡ እናስታውቃለን ።

ቃሉን ፡ ለመቀበል ፡ የሚሹትን ፡ ማንኛውንም ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ ለመመርመር ፡ የሚሹአቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰነዶች ፡ እርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚያስገድዱ ፡ መጥሪያዎች ፡ በእርስዎ ፡ አመልካችነት ፡ ማናቸውም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያወጣ ፡ ይችላል ።

እላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ሥራዎ ፡ ዋጋ ፡ የሆነው ፡ . . . .ብር ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተላለፈ ፡

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፲፩.

## ንብረት ፡ ለማከፋፈል ፡ የሚሰጥ ፡ ሥልጣን ፡

(አንቀጽ ፡ ፪፻፹፱. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ መብት ፡ መሠረት ፡ የሚያከፋፍል ፡ ኮሚሲዮን ፡ መሾም ፡ ለዚሁ ፡ ክስ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየ ፤ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ የኮሚስዮኑ ፡ ኃላፊ ፡ ሆነው ፡ መሾምዎን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ምርመራ ፡ ለማድረግ ፤ በፍርዱ ፡ ላይ ፡ ስለተዘረዘሩት ፡ ድርሻዎች ፡ ባለ ዎት ፡ ዕውቀትና ፡ አስተያየት ፡ መሠረት ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ ለማከፋፈልና ፡ ለያንዳንዱም ፡ ድርሻውን ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠዎ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውቃለን ።

የያንዳንዱ ፡ ድርሻ ፡ እኩል ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ለሌላው ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶዎታል ።

ቃሉን ፡ ለመቀበል ፡ የሚሹትን ፡ ማናቸውንም ፡ ምስክር ፡ ወይም ፡ ለመመርመር ፡ የሚሹአቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰነዶች ፡ እርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚያስገድዱ ፡ መጥሪያዎች ፡ በእርስዎ፡ አመልካችነት ፡ ማናቸውም ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያወጣ ፡ ይችላል ።

እላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ሥራዎ ፡ ዋጋ ፤ . . . .ብር ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተላለፈ ።

. . . . . . . . . . .ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፮.

### ዕድሜው ፡ ለኃላፊነት ፡ ላልደረሰ ፡ ተከሣሽና ፡ ለሞግዚት ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡

### (አንቀጽ ፡ ፺፮. )

ለ.......................

በ፲፱....ዓ.ም. በወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፺፮. መሠረት፡ ....በ.....ላይ ፡ በድኃ ፡ ደንብ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲፈቀድለት ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላ መለከተና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ማመልከቻውን ፡ አልቀበልም ፡ የሚልበት ፡ ምክንያት ፡ ስለሌለውና ፡ አመልካቹ ፡ ድህነቱን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚያቀርበውን ፡ ማስረጃ ፡ ለመቀበልና ፡ ለዚሁ ፡ መቃወሚያ ፡ የሚቀርብ ፡ ማስረጃ ፡ ቢኖር ፡ ለመስማት ፡ የተወሰነው ፡ ....ቀን ፡ ፲፱....ስለሆነ ፡

አመልካቹ ፡ ድኃ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፮. መሠረት ፡ የሚያቀርቡት ፡ ማስረጃ ፡ ቢኖርዎ ፡ ይዘው ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርቡ ፡ መቻልዎን ፡ እናስ ታውቃለን ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ.....ቀን ፡ ፲፱.....ዓ.ም. የተላለፈ ፡

..........ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፲፯.

### በፍርድ ፡ መሠረት ፡ ስለሚጠየቅበት ፡ ዕዳ ፡ ለተያዥ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡

አላይ ፡ በተመለከተው ፡ ክስ ፡ በተከሣሹ ፡ በ.....ላይ ፡ የሚሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ለመፈጸም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. እርስዎ ፡ ግዴታ ፡ ስለገቡና ፡ ተከሣሹ ፡.....ብ.....ብር ፡ እንዲከ ፍል ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ይኸውም ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸምብዎ ፡ ማመል ከቻ ፡ ስለቀረበ ፡

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ አይፈጸምብኝም ፡ የሚሉበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱..ዓ.ም ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ማስረጃዎን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዘንድ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ባይቀርብ ፡ ግን ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ በተጠየቀው ፡ አኳኋን ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ወዲያውኑ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውቃለን ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ.....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ፡

...........ዳኛ ፡

## ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡ ፯ ፤

## የትእዛዝ ፡ አፈጻጸም ፡

### ቍጥር ፡ ፩ ፤

**የተከፈለ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የተስተካከለ ፡ ሒሣብ ፡ መከፈሉ ፡ ወይም ፡ መስተካከሉ ፡ ተረጋግጦ ፡ የማይመዘገብበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፤ እንዲገለፅ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡**

**(አንቀጽ ፡ ፫፻ ፺፮.፪.)**

ለ............................

እላይ ፡ ስለተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ . . . የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲታዘዘው ፡ ስለ ፡ ተከፈለ ፡ (ሒሣቡ ፡ ስለ ፡ ተስተካከለ ፡) መከፈሉ ፡ (ሒሣቡ ፡ መስተካከሉ ፡) ተረጋግጦ ፡ የማይመዘገብበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ ለማስረዳት ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ እናስታውቃለን ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . .ቀን ፡ ፲፱. . . ዓ.ም. የተላለፈ ፡

. . . . . ዳኛ ።

### ቍጥር ፡ ፪.

**ማሳሰቢያ ፡ (አንቀጽ ፡ . . . . . . . . . . . . . .)**

ትእዛዝ ፡ የተሰጠለት ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ በአባሪው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝና ፡ ትእዛዙ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠለት ፡ ሰው ፡ የሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ ቢኖር ፡ እስኪያቀርብ ፡ ድረስ ፡ ተይዞ ፡ እንዲቆይ ፡ ከሚል ፡ መምሪያ ፡ ጋር ፤ ይህ ፡ ማሳሰቢያ ፡ በ፲፱. . . . .ዓ.ም. በወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በ. . . . .ለሚገኘው ፡ ለ. . . .ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲላክ ፡ ታዟል ።

ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡

በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ፡ የተጻፈ ፡

. . . . . . . . .ዳኛ ፡

### ቍጥር ፡ ፫.

**የተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲላክ ፡**

**የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡**

**(አንቀጽ ፡ ፫፻፹፫.)**

የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በ. . . . .ፍርድ ፡ ቤት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ኗሪ ፡ ስለ ሆነ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ስላለው ፡ ፍርዱን ፡ ያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያስፈጽመው ፡ ዘንድ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርድ ፡ ማረጋገጫ ፡ ይላክልኝ ፡ ሲል ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠለት ፡ (የተፈረደለት ፡) ሰው ፡ ስላመለከተና ፡ በ፲፱....ዓ.ም. በወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፫፻፹፫. መሠረት ፡ ለዚያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍርድ ፡ ማረጋገጫ ፡ መላክ ፡ አስፈላጊና ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየ ፡

የዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ግልባጭ ፡ ከፍርዱና ፡ ይህንኑ ፡ ለማስፈጸም ፡ ከተሰጠ ፡ ከማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ግልባጭ ፡ ጋር ፡ እንዲሁም ፡ ፍርዱ ፡ ገና ፡ ላለመፈጸሙም ፡ ማረጋገጫ ፡ ተጨምሮ ፡ ለ. . . . . እንዲላክ ፡ ታዟል ።

. . . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም.

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፬.

## ፍርድ ፡ ላለመፈጸሙ ፡ የተሰጠ ፡ ማረጋገጫ ፡
## (አንቀጽ ፡ ፫፻፸፫. )

በቍጥር ፡ . . . . .በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም. ለቀረበው ፡ ክስ ፡ ግልባጩ ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የተላከው ፡ ፍርድ ፡ ያልተፈጸመ ፡ (፩) መሆኑን ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ተረጋግጧል ።

በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም.

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

(፩) ሳይፈጸም ፡ የቀረው ፡ በሙሉ ፡ ሳይሆን ፡ በከፊል ፡ እንደሆነ ፡ይገለፅ ።

## ቍጥር ፡ ፭.

## ፍርድ ፡ የማይፈጸምበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲገለፅ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡ (አንቀጽ ፡ ፫፻፺፩. ፫. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

በቍጥር ፡ በ. . . . . . . . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. ስለቀረበው ፡ ክስ ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የቀወከለ ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ ይኸው ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ . . . . .ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበ ፡ በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ፍርዱ፡ የማይፈጸምበት ፡ ምክንያት፡ ቢኖር ፡ እንዲያስረዱ ፡ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም ፡ የተላለፈ ።

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፮.

## ፍርድ ፡ የተሰጠበት ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡
## (አንቀጽ ፡ ፫፻፺፱. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡

. . . . .በዚህ ፡ አባሪ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ (ወይም ፡ ከተንቀሳቃሹ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ . . . .(ለከሣ ሹ ፡ እንዲያስረክብ ፡ በቍጥር ፡ . . . .በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ለቀረበው ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ . . . .ታዞ፡ ስለ ፡ ነበረና ፡ ንብረቱ ፡ (ወይም ፡ ከዚያው ፡ ውስጥ ፡ . . . .(ለተፈረደለት ፡ ስላልተሰጠ ፡ ያንኑ ፡

ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ (ወይም ፡ ከዚያው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ እንዲይዙና ፡ ለከሣሽ ፡ ወይም ፡ እሱ ፡ ምትክ ፡ አድርጎ ፡ ለሾመው ፡ ሰው ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ተልኮ ልዎታል

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተላለፈ ፡

ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡

. . . . . . . . . . .ዳኛ ፡

ቍጥር ፡ ፺.

ስለ ፡ ሰነድ ፡ ረቂቅ ፡ መቃወሚያ ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲገለፅ ፡
የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡ (አንቀጽ ፡ ፻፶፩. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ከዚህ ፡ በታች ፡ ስለተመለከተው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ረቂቁ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ውን ፡ የ. . . .ውል ፡ ስለ ፡ እርስዎ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈጽምልዎ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ በመግ ለፅ ፡ እሳይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ የተፈረደለት ፡ . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ያቀረበ ፡ መሆኑንና ፡ ማመልከቻው ፡ ለ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. እንዲሰማ ፡ ስለ ፡ ተቀ ጠረ ፡ በዚያን ፡ ቀን ፡ ቀርበው ፡ ረቂቁን ፡ የሚቃወሙበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖርዎ ፡ በጽሑፍ ፡ ሊገልፁ፡ የሚችሉ ፡ መሆንዎን ፡ እናስታውቃለን ።

የንብረቱ ፡ ዓይነት ፡ መግለጫ ፡

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተላለፈ ፡

. . . . . . . . . . .ዳኛ ፡

ቍጥር ፡ ፺፩.

መሬት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ንብረት ፡ እንዲያስረክብ ፡ ለፍርድ ፡ አስፈጻሚ
የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡ (አንቀጽ ፡ ፻፶፪. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡

ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከተው ፡ በ. . . . .እጅ ፡ የሚገኘው ፡ ንብረት ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከሣሽ ፡ ለሆነው ፡ ለ. . . . .ስለ ፡ ተፈረደ ፡ ለ. . . . . .እንዲያስረክቡት ፡ ታዞዋል ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ የሚፈጸ ምበት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ አልለቅም ፡ ቢል ፡ እንዲያስነሱት ፡ ተፈቅዶልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡

በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተላለፈ ፡

ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡

. . . . . . . . . . .ዳኛ ፡

ቍጥር ፡ ፱.

የፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ያልፈጸመ ፡ ሰው ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡
(አንቀጽ ፡ ፫፻፹፩. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡

በቍጥር ፡ . . . . .፲፱. . . . .ዓ.ም. ለቀረበው ፡ ክስ ፡ በ. . . .ዓ.ም. በ. . . . .ላይ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ . . . . .ብር ፡ ለ. . . .እንዲከፍል ፡ ስለ ፡ ተፈረደበትና ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ የታዘዘው ፡ . . . .ብር ፡ ለተፈረደለት ፡ ሰው ፡ ስላልተከፈለ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የሆነውን ፡ . . . .ን ፡ እንዲይዙትና ፡ እንዲሁም ፡ ያንኑ ፡ . . . .ብር ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ወጪ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ከ. . . .ብር ፡ ጋር ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ለእርስዎ ፡ካልከፈለዎ ፡ በቀር ፡ ተከሣሹን ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ተልኮልዎታል ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ መቼ ፡ እንደተፈጸመና ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደተፈጸመ ፡ በማረጋገጥ ፡ ወይም ፡ አልተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ያልተፈጸመበትን ፡ ምክንያት ፡ በመግለፅ ፡ ፈርመው ፡ በ. . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ መልሰው ፡ እንዲልኩት ፡ ታዞዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱ . . . .ዓ.ም. የተላለፈ ፡

. . . . . . . . . . .ዳኛ ፡

ቍጥር ፡ ፲ ፡

የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ።
(አንቀጽ ፡ ፫፻፹፱ ።)

ለ..............................................................

የ... የወህኒ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ።

... በፍርድ ፡ ማስፈጸሚያው ፡ ትእዛዝ ፡'መሠረት ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የወሰነውንና ፡ ያሰማውን ፡ ድንጋጌ ፡ ያላከበረ ፡ ወይም ፡ እጁ ፡ ተይዞ ፡ ከመጠበቅ ፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያላስረዳ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፡ ...ን ፡ ወስደው ፡ በሲቪል ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ እንዲያገቡትና ፡ ከ... ለማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ፍርዱ ፡ በሙሉ ፡ እስከ ፡ ተፈጸመ ፡ ወይም ፡ በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፫፻ ፺ ፡ መሠረት ፡ ሊለቀቅ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑ ፡ እስኪገለጽ ፡ ድረስ ፡ እዚያው ፡ በእሥራት ፡ እንዲያቆዩት ፡ ታዞዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

.... ዳኛ ።

ቍጥር ፡ ፲፩ ፡

በፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክንያት ፡ የታሠረ ፡ ሰው ፡ እንዲለቀቅ ፡ የሚተላለፍ ፡
ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፫፻ ፺ ።)

ለ..............................................................

የ..... ወህኒ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ።

ዛሬ ፡ በተላለፈው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ በእርስዎ ፡ እጅ ፡ የሚገኘውን ፡ ... የተባለውን ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ እንዲለቁት ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ተልኮልዎታል ።

.... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፪ ፡

## ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚያዝ ፡ ንብረት ፡

## ንብረትነቱ ፡ የተከሣሹ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ለጊዜው ፡ በመያዣ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ሊሆን ፡ ስለሚገባው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ የሚተላለፍ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ።

(አንቀጽ ፡ ፬፻፱ ።)

ለ.....................................................

በቍጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. በቀረበው ፡ ክስ ፡ ... ለ... ፤ ... ብር ፡ እንዲከፍል ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተፈረደበትን ፡ ፍርድ ፡ ሳይፈጽም ፡ ስለቀረ ፡ ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪደርስ ፡ ... የተባለው ፡ ተከሣሽ ፡ እርስዎ ፡ ላይ ፡ አለው ፡ የተባለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይቀበል ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግዷል ። እርስዎም ፡ ... ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪደርስ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ እንዳይከፍሉ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግደዋል ። (ወይም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ በ... እጅ ፡ የሚገኘውን ፡ ንብረት ፡ ማለት ፡ ንብረትነቱ ፡ የተከሣሹ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ... የሚከራከርበትን ፡ ... ተከሣሹ ፡ ለ... እንዳይረከብ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግዷል ፤ ...ም ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪደርስ ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንዳያስረክብ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግዷል ።) (ወይም ፤ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ አክሲዮን ፡ ምንም ፡ እንዳያዘዋውሩ ፤ ወይም ፡ ከአክሲዮኑ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ድርሻ ፡ እንዳይቀበሉ ፡ እርስዎም ፡ ... የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ ማናቸውንም ፡ የአክሲዮን ፡ ዝውውር ፡ ወይም ፡ የድርሻ ፡ ክፍያ ፡ እንዳይፈቅዱ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግደዋል ።) (የማያስፈልገውን ፡ ማስቀረት ፡ ነው ።)

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

.... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፫ ፡

## ደመወዝ ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፲፩ ።)

ለ.....................................................

... የተባለው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ በ... ክፍል ፡ እየሠራ ፡ ደመወዙን ፡ (አበሉን ፡) ከርስዎ ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ሚቀበል ፡ እንዲሁም ፡ ... የተባለው ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ ከደመወዙ ፡ (ከአበሉ ፡) ላይ ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ የሚገባው ፡ ... እንዲያዝለት ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላ ቀረበ ፤ ... ታዘዋል ።

## ቍጥር ፡ ፲፬ ፡

## ተዘዋዋሪ ፡ ሰነድ ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፲፪ ።)

ለ.....................................................

ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ።

... እንዲያዝ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ትእዛዝ ፡ ስላስተላለፈ ፡ ያንኑ ፡ ... ይዘው ፡ ወደዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያመጡ ፡ ታዘዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

.... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፭ ፡

### በፍርድ ፡ ቤት ፡ (ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡) እጅ ፡ ስለሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መያዣ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፲፫ ።)

ለክቡር ፡ ...

አሁን ፡ በእርስዎ ፡ እጅ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ (ገንዘቡ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እዚያ ፡ ሊገኝ ፡ እንደቻለ ፡ በመግለጽ ፡) እንዲያዝለት ፡ ከሣሹ ፡ በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፬፻፲፫ ፡ መሠረት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበ ፡ ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪደርስ ፡ ይህንኑ ፡ ገንዘብ ፡ እንደያዙት ፡ እንዲቆዩ ፡ በማክበር ፡ አስታውቃለሁ ።

ታዛዥዎ ፡ .... ዳኛ ።

ሌ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

## ቍጥር ፡ ፲፮ ፡

### ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ ስለሚያዝ ፡ ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሚተላለፍ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፲፬ ።)

ለ.........................................................................................

ተከሣሽ ፡

በቍጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. በቀረበው ፡ ክስ ፡ ለ... ፤ ... ብር ፡ እንዲከፍሉ ፡ ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተፈረደብዎን ፡ ፍርድ ፡ ግይፈጽሙ ፡ ስለቀሩ ፡ ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ እስኪ ፡ ደርስ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በተላከው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረት ፡ በመሸጥ ፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዳያዘዋውሩት ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግደዋል ፤ እንዲሁም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በግዥ ፤ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ይህን ፡ ንብረት ፡ እንዳይቀበል ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግዷል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡

.... ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፲፯ ፡

### በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ ለከሣሹ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፲፯ ።)

ለ.........................................................................................

በቍጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. ለቀረበው ፡ ክስ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ... ብር ፡ ለ... እንዲከፈል ፡ የተፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ንብረት ፡ እንዲያዝ ፡ ስለተወሰነ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የተያዘውን ፡ በገንዘብ ፡ ... ብር ፡ እንዲሁም ፡ በኖት ፡ ገንዘብ ፡ ...ብር ፡ የሆነውን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ለፍርዱ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የሚበቃውን ፡ ገንዘብ ፡ ለ... እንዲከፍሉት ፡ ታዞዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

.... ዳኛ ።

## ቍ ፡ ፲፰ ፤

### ንብረት ፡ ላስያዘ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡፡
### (አንቀጽ ፡ ፬፻፲፰ ፡፡)

ለ..........................................................................

በቍጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. በቀረበው ፡ ክስ ፡ ለተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ በርስዎ ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ... እንዲያዝ ፡ ተሰጥቶ ፡ የነበረው ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲነሳለት ፡ ... ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበ ፡ ራስዎ ፡ ወይም ፡ ጥያቄዎን ፡ ለመደገፍ ፡ አስፈላጊው ፡ ትእዛዝ ፡ በተሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ተነጋጋሪ ፡ አማካይነት ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ወደዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተልኮልዎታል ፡፡

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ፡፡

...... ዳኛ ፡፡

## ቍጥር ፡ ፲፱ ፤

### ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ለተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ንብረት ፡ ተይዞ ፡ እንዲሸጥ ፡ የተላለፈ ፡ ትእዛዝ ፡፡ (አንቀጽ ፡ ፬፻፳፪ ፡፡)

ለ..........................................................................

ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡፡

በቍጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. ስለቀረበው ፡ ክስ ፡ ለተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የተያዘውን ፡ (ተንቀሳቃሽ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ) ንብረት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ የተወሰነውን ፡ ... ብርና ፡ እስካሁን ፡ ያልተከፈለውን ፡ ወጪ ፡ ለመክፈል ፡ የሚበቃውን ፡ ያህል ፡ ማስታወቂያውን ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመለጠፍ ፡ ከ... ቀን ፡ አስቀድመው ፡ ማስታወቂያ ፡ ካወጡና ፡ በሚገባ ፡ እንዲታወቅ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ በሐራጅ ፡ እንዲሸጡት ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ተልኮልዎታል ፡፡

እንዲሁም ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደተፈጸመ ፡ ወይም ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ሳይፈጸም ፡ እንደቀረ ፡ በማረጋገጥ ፡ ፈርመው ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ መልሰው ፡ እንዲልኩት ፡ ታዞዋል ፡፡

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ፡፡

...... ዳኛ ፡፡

## ቍጥር ፡ ፳ ፤

### የሺያጩን ፡ ሁኔታ ፡ ለመግለጽ ፡ ስለ ፡ ተወሰነው ፡ ቀን ፡ የሚተላለፍ ፡ ማስታወቂያ ፡፡

ለ..........................................................................

የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፤

እላይ ፡ በተመለከተው ፡ ክስ ፡ የተፈረደለት ፡ ... እንዲሸጥ ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበ ፡ የሺያጩ ፡ ሁኔታ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. እንዲወሰን ፡ መቀጠሩን ፡ እስታውቃለሁ ፡፡

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ፡፡

...... ዳኛ ፡፡

## ቅጥር ፡ ፳፩ ፡

### የሺያጩ ፡ ሁኔታ ፡ መግለጫ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፳፫ ፡)

በቅጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. በቀረበውና ፡ ... ከሣሽ ፡ እንዲሁም ፡ ... ተከሣሽ ፡ ሆነው ፡ ከተበግ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ሺያጩ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከኪሣራውና ፡ ከወለዱ ፡ ጋር ፡ ... ብር ፡ እንዲከፈል ፡ ተብሎ ፡ ውሣኔ ፡ ባገኘው ፡ ክስ ፡ የፍርዱ ፡ ባለገንዘብ ፡ ለተፈረደላቸው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ተይዞ ፡ የነበረው ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ በተያያዘው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ ያስተላለፈ ፡ መሆኑን ፡ አስታውቃለሁ ።

ሺያጩ ፡ በጨረታ ፡ ይፈጸማል ። ንብረቱም ፡ ለሺያጭ ፡ የሚቀርበው ፡ በሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ አከፋፈል ፡ መሠረት ፡ ነው ።

የሚሸጠው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚገኘው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ እላይ ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሰው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ንብረት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የተጠያቂው ፡ ዕዳና ፡ የጠያቂው ፡ ድርሻ ፡ ሁኔታቸው ፡ ተጣርቶ ፡ የታወቀውን ፡ ያህል ፡ በሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ በያንዳንዱ ፡ ክፍያ ፡ አንፃር ፡ የተመለከቱት ፡ ዕዳና ፡ ድርሻ ፡ ናቸው ።

ሺያጩ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ካልታዘዘ ፡ በቀር ፡ በ... ቀን ፡ ... ዓ.ም. በ... ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ በ... በየወሩ ፡ ይቀጥላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከንብረቱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ከመሸጡ ፡ አስቀድሞ ፡ እላይ ፡ የተገለጸው ፡ ዕዳና ፡ የሺያጩ ፡ ወጪ ፡ እንዲከፈል ፡ የተጠየቀ ፡ ወይም ፡ የተከፈለ ፡ እንደሆነ ፡ ሺያጩ ፡ ያቆማል ።

ሕዝቡ ፡ በጠቅላላው ፡ ራሱ ፡ እየቀረበም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እስፈላጊው ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ወኪል ፡ አማካይነት ፡ በሺያጩ ፡ እንዲጫረት ፡ ተጋብዟል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቦች ፡ ራሳቸውም ፡ ሆኑ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ጨረታ ፡ መቀበል ፡ አይቻልም ፡ እንዲሁም ፡ በቅድሚያ ፡ በግልጽ ፡ የተሰጠ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለነሱ ፡ የተደረገ ፡ ማናቸውም ፡ ሺያጭ ፡ አይረጋም ።

### ስለ ፡ ሺያጩ ፡ ማሳሰቢያዎች ።

፩ኛ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ባለው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባገኘው ፡ ሙሉ ፡ መረጃ ፡ መሠረት ፡ የተገለጹ ፡ ናቸው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚሁ ፡ መግለጫ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ ለማናቸውም ፡ ስሕተት ፡ የተሳሳተ ፡ መረጃ ፡ ወይም ፡ ሳይገለፅ ፡ ለቀረ ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተጠያቂ ፡ አይሆንም ።

፪ኛ ፡ በጨረታው ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ የሚደረጉት ፡ ጭማሪዎች ፡ የሚወሰኑት ፡ ሺያጩን ፡ በሚያከናውነው ፡ ሹም ፡ ነው ። በጨረታው ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ በተጫራቹ ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ ቢነሳ ፡ ያከራከረው ፡ የንብረት ፡ ክፍያ ፡ እንደገና ፡ ለጨረታ ፡ ይቀርባል ።

፫ኛ ፡ በጨረታው ፡ ከሌሎቹ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያቀረበው ፡ ተጫራች ፡ ለተጫረተበት ፡ ድርሻ ፡ ገዢ ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ የሚሆነው ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ለመጫረት ፡ ብቁ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ሺያጩን ፡ ያከናውነው ፡ ሹም ፡ ለመወሰን ፡ ባላቸው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነውን ፡ የጨረታ ፡ ዋጋም ፡ ቢሆን ፡ የማይበቃ ፡ ዋጋ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሺያጩ ፡ አይጠቅምም ፡ በማለት ፡ የማይቀበሉት ፡ ሆነው ፡ ያልተገኙ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

፬ኛ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭፻፰ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሣኔዎች ፡ ሳይጓደሉ ፡ በትክክል ፡ በተገለፁ ፡ ምክንያቶች ፡ የሺያጩን ፡ ጊዜ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ሺያጩን ፡ የሚያከናውነው ፡ ሹም ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

፭ኛ ፡ ንብረቱ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ሲሆን ፡ የያንዳንዱ ፡ ዋጋ ፡ በተሸጠበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ ሺያጩን ፡ የሚያከናውነው ፡ ሹም ፡ ባዘዘው ፡ ጊዜ ፡ መከፈል ፡ አለበት ። ሳይከፈል ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ንብረቱ ፡ እንደገና ፡ ቀርቦ ፡ መሸጥ ፡ አለበት ።

፮ኛ ፡ ንብረቱ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሲሆን ፡ ገዢ ፡ መሆኑ ፡ የተገለፀለት ፡ ሰው ፡ ከግዢው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በመቶ ፡ ሀያ ፡ መያዣ ፡ወዲያውኑ ፡ ሺያጩን ፡ ለሚያከናውነው ፡ ሹም ፡ መከፈል ፡ አለበት ፡ ይህ ፡ መያዣ ፡ ሳይከፈል ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ንብረቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደገና ፡ ቀርቦ ፡ መሸጥ ፡ አለበት ።

፯ኛ ፡ የሺያጩ ፡ ሙሉ ፡ ዋጋ ፡ የሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ንብረቱ ፡ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከመዝጋቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወይም ፡ አሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ እሁድ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ በመጀመሪያው ፡ የቢሮ ፡ ቀን ፡ ገዢው ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

፰ኛ ፡ ከሺያጩ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ቀሪ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይከፈል ፡ ቢቀር ፡ አዲስ ፡ የሺያጭ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ንብረቱ ፡ እንደገና ፡ መሸጥ ፡ አለበት ። መያዣው ፡ ገንዘብ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፡ የሺያጩ ፡ ወጪ ፡ ከተቀነሰለት ፡ በኋላ ፡ ለመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ዋጋውን ፡ በጊዜው ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረው ፡ ገዢ ፡ ለንብረቱም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ንብረቱ ፡ ከሚሸጥበት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ አለኝ ፡ የሚለውን ፡ ማናቸውንም ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

...... ዳኛ ።

የ ን ብ ረ ት ስ ን ጠ ረ ዥ ፡

| የክፍያ ቍጥር | የሚሸጠው ንብረት ዓይነት መግለጫ ዝርዝር፤ ካንድ በላይ የፍርድ ባለ ዕዳዎች ቢኖሩ የያንዳንዱ ባለቤት ስም ጭምር ። | የሚሸጠው ንብረት ለመንግሥት ግብር በሚከፈልበት መሬት ወይም የመሬት አጋማሽ ውስጥ የሚገኝ የሆነ እንደሆነ በመሬቱ ወይም ከመሬቱ በአጋማሹ ላይ የተገመተው ግብር ፤ | ንብረቱ ባለዕዳ የሆነባቸው ግዴታ ዎች ዝርዝር | ስለ ንብረቱ የቀረበ ማናቸውም ጥያቄ ቢኖር ሌላም በዓይነቱም ሆነ ወይም በዋጋው ረገድ አገባብ ያላቸው የታወቁ ዝርዝር ሁኔታዎች ። |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

## ቍጥር ፡ ፳፱ ፡

### የሺያጩ ፡ አዋጅ ፡ እንዲታወቅ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፸፰ ።)

ለ..................................................................

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ።

ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ ንብረት ፡ እንዲሸጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለተሰጠና ፡ የዚሁ ፡ ንብረት ፡ መሸጫም ፡ . . . .ቀን ፡ ፲፱. . . ዓ.ም. እንዲሆን ፡ ስለተወሰነ ፡ የሽያጩ ፡ አዋጅ ፡ ግልባጮች ፡ ከዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ ጋር ፡ ተልከውልዎታልና ፡ በሰንጠረዡ ፡ ላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ንብረቶች ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ውስጥ ፡ አዋጁ ፡ በነጋሪት ፡ እንዲሰማ ፡ እንዲያደርጉ ፤ ከነዚሁ ፡ ንብረቶች ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ውስጥ ፡ ጉልህ ፡ በሆነ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ቀጥሎም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ላይ ፡ የአዋጁን ፡ ግልባጭ ፡ እንዲለጥፉ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አዋጁ ፡ የተነገለጸበትን ፡ ቀንና ፡ አኳኋን ፡ በመግለጽ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሪፖርት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ታዘዋል ።

ቀን ፡ ... ፲፱... ዓ.ም.

ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡

......ዳኛ ።

## ቍጥር ፡ ፳፲ ፡

### ገዢው ፡ ዋጋውን ፡ በጊዜው ፡ ሳይከፍል ፡ በመቅረቱ ፡ ንብረቱ ፡ እንደገና ፡ ተሸጦ ፡ ስለ ፡ ደረሰው ፡ የዋጋ ፡ ጉድለት ፡ ሺያጩን ፡ ያከናወነው ፡ ሹም ፡ የሚሰጠው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ። (አንቀጽ ፡ ፭፻፳፩ ።)

ገዢው ፡ ... ዋጋውን ፡ በጊዜው ፡ ሳይከፍል ፡ በመቅረቱ ፡ እላይ ፡ ለተመለከተው ፡ ክስ ፡ የተፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ ንብረቱ ፡ እንደገና ፡ ሲሸጥ ፡ የንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ...ብር ፡ የጐደለ ፡ መሆኑንና ፡ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ንብረቱን ፡ እንደገና ፡ ለመሸጥ ፡ የተደረገው ፡ ወጪ ፡ ...ብር ፡ በድምሩ ፡ ዋጋውን ፡ በጊዜው ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረው ፡ ገዢ ፡ የሚከፍለው ፡ ... ብር ፡ መሆኑን ፡ እመሠክራለሁ ።

ቀን ፡ ፲፱. . .ዓ.ም.

ሺያጩን ፡ ያከናወነው ፡ ሹም ።

## ቍጥር ፡ ፳፩ ፡

### ለፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የተሸጠ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ በይዞታው ፡ ለሚገኝ ፡ ሰው ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፵፮ ።)

ለ..................................................................

እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ በይፋ ፡ በተደረገው ፡ ሺያጭ ፡ አሁን ፡ በርስዎ ፡ ይዞታ ፡ የሚገኘውን ፡ ... ስለ ፡ ገዙት ፡ ለእኝሁ ፡ ለ... ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ... ለማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እንዳያስረክቡ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግደዋል ። (እርስዎ ፡ ለ... ያለብዎትን ፡ ዕዳ ፡ ለእኝሁ ፡ ለ... ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ እንዳይከፍሉ ፡ ወይም ፡ ... ላይ ፡ ያለዎትን ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይቀበሉ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግደዋል ።)

## ቁጥር ፡ ፳፭ ፡

### ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ የተሸጡ ፡ አክሲዮኖች ፡ ለገዢው ፡ እንዳይዛወሩ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ። (አንቀጽ ፡ ፫፻፹፱ ።)

ለ..........................................................................

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክርክር ፡ ለተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ በይፉ ፡ በተደረገው ፡ ሽያጭ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ በርስዎ ፡ ስም ፡ ያሉትን ፡ አንዳንድ ፡ አክሲዮኖች ፡ ... ስለገዙ ፡ ... ስለ ዚሁ ፡ ለእኚሁ ፡ እላይ ፡ ለተጠቀሱት ፡ ገዢ ፡ ለ... ካልሆነ ፡ በቀር ፤ እነዚህን ፡ አክሲዮኖች ፡ በማንም ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ቢሆን ፡ እንዳያዛውሩ ፡ ወይም ፡ በነዚሁ ፡ አክሲዮኖች ፡ መሠረት ፡ ድርሻ ፡ ሒሣብዎን ፡ እንዳይቀበሉ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ታግደዋል ። እንዲሁም ፡ እርስዎ ፤ ... የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፤ እላይ ፡ ለተመለከቱት ፡ አክሲዮኖች ፡ እላይ ፡ ለተጠቀሱት ፡ ገዥ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማንም ፡ ቢሆን ፡ ዝውርውር ፡ እንዳይፈቅዱ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይከፍሉ ፡ ታዘዋል ።

(ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ የሌለውን ፡ ክፍል ፡ ማስቀረት ፡ ነው ።)

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. .

... ዳኛ ።

## ቁጥር ፡ ፳፮.

### የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ንብረቱን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ እንዲያስይዝ ፤ እንዲያከራይ ፤ ወይም ፡ እንዲሸጥ ፡ በመፍቀድ ፡ የሚሰጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ። (አንቀጽ ፡ ፬፻፴፱. ) 439

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክርክር ፡ ለተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከተው ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ ንብረቱ ፡ እንዲሸጥ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ትእዛዝ ፡ ስለተሰጠና ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ይህንኑ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ገሚሱን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ በማስያዝ በማከራየት ፡ ወይም ፡ በመሸጥ ፡ ፍርዱን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ባቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሺያጩን ፡ ስላስተላለፈው ።

ስለዚህ ፡ ከወለድ ፡ አግዱ ፡ ኪራይ ፡ ወይም ፡ ከሺያጩ ፡ የሚገኘው ፡ ማናቸውም ፡ ገንዘብ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መከፈል ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ ይህን ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ ማስያዝ ፤ ማከራየት ፡ ወይም ፡ መሸጥ ፡ ይህ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ በ. . . .ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እን ዲፈጸም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ የፈቀደለት ፡ ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተሰጥቶአል ።

የንብረቱ ፡ ዓይነት ፡ መግለጫ ፡ ዝርዝር ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም. ፡ የተላለፈ ።

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፷፯.

### ሺያጭ ፡ የማይታገድበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲገለፅ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡
### (አንቀጽ ፡ ፬፻፺፯.)

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

እላይ ፡ በተመለከተው ፡ ክርክር ፡ ለተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከተው ፡ ንብረት ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ተሸጦ ፡ ስለ ፡ ነበረና ፡

ስለ ፡ ሺያጩ ፡ ማስታወቂያ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ (ወይም ፡ ሺያጩ ፡ በተከናወነ ፡ ጊዜ ፡ ). . . .በማድረግ ፡ ጉልህ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ (ወይም ፡ በማጭበርበር ፡ ) ከአግባብ ፡ ውጭ ፡ ተሠርቷል ፡ በማለት፡ የንብረቱ ፡ ሺያጭ ፡ እንዲታገድ ፡ . . . .የተባለው ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘብ ፡ (ወይም ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ) ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስላመለከተ ።

ይህን ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊቀበለው ፡ አያሻም ፡ የሚሉበት ፡ አንዳች ፡ ምክንያት ፡ እንዳለዎ ፡ ማመልከቻው ፡ ተሰምቶ ፡ በሚወሰንበት ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. እዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከነማስረጃዎ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተላለፈ ።

የንብረቱ ፡ ዓይነት ፡ መግለጫ ፡ ዝርዝር ፡

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፷፰.

### ሺያጭ ፡ የማይታገድበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲገለፅ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ፡
### (አንቀጽ ፡ ፭፻፰. እና ፭፻፺፩.)

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክርክር ፡ ለተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለሠተውን ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . . .ዓ.ም. የተሸጠውን ፡ ንብረት ፡ የገዛው ፡ . . . .የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ በዚህ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለሺያጩ ፡ የሚበቃ ፡ ጥቅም ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ የዚሁ ፡ ንብረት ፡ ሺያጭ ፡ እንዲታገድ ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበ ፡ ይህን ፡ ማመልከቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊቀበለው ፡ አያሻም ፡ የሚሉበት ፡ አንዳች ፡ ምክንያት ፡ እንዳለዎ ፡ ማመልከቻው ፡ ተሰምቶ ፡ በሚወሰንበት ፡ በ. . . . ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. እዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከነማስረጃዎ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም የተላለፈ ።

የንብረተ፡ ዓይነት ፡ መግለጫ ፡ ዝርዝር ።

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፷፱.

### የመሬት ፡ ሺያጭ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡
### (አንቀጽ ፡ ፬፻፺፯.)

በዚህ ፡ ክርክር ፡ ለተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. በተደረገው ፡

የሠራጅ ፡ ሺያጭ ፡ .....ን ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ )....የገዛውና ፡ ሺያጩ ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተረጋገጠ ፡ ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተሰጥቷል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. ተሳለፈ ።

..........ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፴.

## ለፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የተሸጠ ፡ መሬት ፡ ለገዢው ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡

## (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፰. )

ለ......................

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡

በቍጥር ፡ ......፤........ዓ.ም. በቀረበው ፡ ክስ ፡ ለተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የተሸጠውን ፡ ....፤......የተመሠከረላቸው ፡ ገዢ ፡ ስለሆኑ ፤

እነሀኑ ፡ .....ን ፡ ለተባለው ፡ ....ባለይዞታ ፡ እንዲያደርጓቸው ፡ ታዘዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ።

..........ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፴፩.

## የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ በማሰናከል ፡ የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ መልስ ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚላክ ፡ መጥሪያ ፡

## (አንቀጽ ፡ ፩፻፶. )

ለ......................

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክርክር ፡ የተፈረደለት ፡ ....፤ ባለይዞታ ፡ እንዲሆን ፡ የተሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ የታዘዘውን ፡ ሹም ፡ እርስዎ ፡ ተቋቍመዋል ፡ (ወይም ፡ አሰናክለዋል ፡ ) በማለት ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቤቱታ ፡ ስለቀረበ ።

ለዚሁ ፡ አቤቱታ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም ፡ እዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ይህ ፡ መጥሪያ ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ።

...........ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፴፪.

## በእሥር ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡

## (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፩. )

ለ......................

የ.....ወህኒ ፡ ቤት ፡ አዣዥ ፡

ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከተው ፡ ንብረት ፡ ከሣሽ ፡ ለሆነው ፡ ለ....ተፈርዶለት ፡ ስለ ፡ ነበረና፡ ምንም ፡ ተገቢ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖረው ፡ በይዞታው ፡ እንዳያገባው ፡ ስለተቋቋመው ፡ (ወይም ፡ ስላሰናከለው ፡ ) አሁንም ፡ መቋቋሙን ፡ (ወይም ፡ ማሰናከሉን ፡ ) ስለቀጠለና ፤ ....በሲቪል ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ በማለት ፡ ... ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረበ ፡ ...ን ወስደው ፡ በሲቪል ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ እንዲያገቡትና ፡ እስከ ፡ ...ቀን ፡ ድረስ ፡ እዚያው ፡ እንዲያቆዩት ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ።

............ዳኛ ፡

## ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡ ፩.

## ተጨማሪ ፡ እርምጃዎች ፡

### ቍጥር ፡ ፩.

### ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ሰው ፡ እንዲያዝ ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡
### (አንቀጽ ፡ ፪፻ ፶፰.)

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ከሣሽ ፡ የሆነው ፡ . . . . ልኩ ፡ . . . . ብር ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ይገባ ኛል ፡ ስለሚልና ፡ ተከሣሹ ፡ . . . . ፡. . . . ለ. . . . ተቃርቧል ፡ የሚያሰኝ ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚገባ ፡ ስላስረዳ ፡ የከሣሹ ፡ ጥያቄ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ከዚሁ ፡ ከ. . . . ላይ ፡ . . . . ብር ፡ ጠይቀው ፡ እንዲቀበሉና ፡ የተባለው ፡ . . . . ብር ፡ ከ. . . . ወይም ፡ ስለ. . . . በፍጥነት ፡ ካልተ ሰጠዎ ፡ በቀር ፡ ይህንኑ ፡ . . . . ን ፡ እጁ ፡ እንዲያዝ ፡ አድርገው ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ ሙሉና ፡ የመጨረሻ ፡ ውሣኔ ፡ እስከ ፡ ተሰጠውና ፡ የሚፈረድበትም ፡ ፍርድ ፡ ቢኖር ፡ ፍርድ ፡ እስከ ፡ ተፈጸመ ፡ ድረስ ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርብ ፡ ዘንድ ፡ የ. . . . ብር ፡ መያዣ ፡ የማያስይዝበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲያስረዳ ፡ ወደዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያቀርቡት ፡ ታዘዋል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም. የተላለፈ ።

. . . . . . . . . . . ዳኛ ፡

### ቍጥር ፡ ፪.

### ከፍርድ ፡ በፊት ፡ የተያዘ ፡ ሰው ፡ እንዲቀርብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መያዣ ፡
### (አንቀጽ ፡ ፪፻ ፶፱. )

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክርክር ፡ ከሣሽ ፡ በሆነው ፡ በ. . . . ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ተከሣሹ ፡ . . . . ተይዞ ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለቀረበ ፤

ወደዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርብ ፡ ዘንድ ፡ መያዣ ፡ የማያስይዝበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እንዲ ያስረዳ ፡ ተጠይቆ ፡ ተከሣሹ ፡ ሳያስረዳ ፡ በመቅረቱ ፡ መያዣውን ፡ እንዲያስይዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስላዘዘው ፤

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ . . . . በፈቃዴ ፡ ዋስ ፡ በመሆን ፤ ክሱ ፡ በውዝፍ ፡ እስካለና ፡ ምናልባትም ፡ በተከ ሣሹ ፡ ላይ ፡ ቢፈረድ ፡ ፍርዱ ፡ እስከ ፡ ተፈጸመ ፡ ድረስ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ሲጠራ ፡ እን ዲቀርብ ፡ ለማድረግ ፡ ራሴን ፡ ወራሾቼንና ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚዎቼን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግዴታ ፡ እገባ ቻለሁ ። ተከሣሹ ፡ ተጠርቶ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነም ፡ በዚሁ ፡ ክስ ፡ ተከሣሹ ፡ እንዲከፍል ፡ የሚፈረድበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልከፍል ፡ ራሴን ፡ ወራሾቼንና ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚዎቼን ፡ ግዴታ ፡ አግብቻለሁ ።

በ. . . . . ቀን ፡ ፲፱. . . . ዓ.ም.

(ፊርማ ፡ )

ምስክሮች ፡ ፩ኛ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

፪ኛ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

## ቍጥር ፡ ፫.

## ዋሱ ፡ ዋስትናው ፡ እንዲወርድለት ፡ በሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ተከሣሹ ፡ እንዲቀርብ ፡ የሚላክ ፡ መጥሪያ ፡

## (አንቀጽ ፡ ፫፻. )

ለ.......................

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ እንዲቀርቡ ፡ በ...ቀን ፡ ፲፱...ዓ.ም. ዋስ ፡ የሆኑዎ ፡ ....ግዴታቸው ፡ እንዲወርድላቸው ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረቡ ።

ይኸው ፡ ማመልከቻ ፡ ተሰምቶ ፡ በሚወሰንበት ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ራስዎ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ይህ ፡ መጥሪያ ፡ ተልኮልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ።

.......... .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፬.

## በእሥር ፡ ቤት ፡ ስለሚቆይ ፡ ሰው ፡ የሚተላለፍ ፡ ትእዛዝ ፡

## (አንቀጽ ፡ ፫፻. )

ለ........................

ተከሣሹ ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ቢፈረድባቸውና ፡ እኒሁ ፡ .....የተባሉት ፡ ተከሣሽ ፡ የሚያስረዱት ፡ ቢኖር ፡ እንዲቀርቡ ፡ ለማድረግ ፡ መያዣ ፡ ያስይዙ ፡ በማለት ፡ ....የተባሉት ፡ ከሣሽ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረቡና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ተከሣሹን ፡ መያዣ ፡ እንዲያስ ይዙ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያስይዙ ፡ ጠይቋቸው ፡ ይህንኑ ፡ ሳያደርጉ ፡ ስለቀሩ ፡ ክሱ ፡ ውሣኔ፡ እስካገኘ ፡ ወይም ፡ የተፈረደባቸውም ፡ እንደሆነ ፡ ፍርዱ ፡ እስከ ፡ ተፈጸመ ፡ ድረስ ፡ እኒሁ ፡ ..... የተባሉት ፡ ተከሣሽ ፡ በሲቪል ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ እንዲቆዩ ፡ ታዟል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ.....ቀን ፡ ፲፱....ዓ.ም. የተላለፈ ።

...........ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፭.

## ለፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የሚሆን ፡ መያዣ ፡ እንዲሰጥ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ትእዛዝ ፡ ጋር ፡ ከፍርድ ፡ በፊት ፡ ስለሚያዝ ፡ ንብረት ፡

## (አንቀጽ ፡ ፫፻፮. )

ለ......................

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ተከሣሹ ፡ ....መሆናቸውን ፡ ....ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በትክክል ፡ ስላስረዱ ፡ እኒሁ ፡ ተከሣሽ ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ አቅርበው ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚያስረክቡት ፡ ለ....ብር ፡ መያዣ ፡ ወይም ፡ የዚያኑ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ የተፈረደባቸው ፡ እንደሆነ ፡ ዋጋው ፡ በፍርድ

ለተወሰነባቸው ፡ ሂሣብ ፡ የሚበቃ ፡ ድርሻ ፡ እንዲያስይዙ ፡ ወይም ፡ የማያስይዙበት ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ ቀርበው ፡ እንዲያስረዱ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ እንዲያስታውቋቸው ፡ ታዘዋል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ይህንኑ ፡ . . .እንዲያዙና ፡ ወደፊት ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ የሚያስተማምን ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ እየተጠበቀ ፡ እንዲቆይ ፡ እንዲያደርጉት ፡ ታዘዋል ። እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀንና ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ ሳይፈጸም፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ምክንያቱን ፡ በመግለፅ ፡ ፈርመው ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ መልሰው ፡ እንዲልኩት ፡ ታዘዋል ።

በኔ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . ዓ.ም. የተላለፈ ።

. . . . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፯.

### ንብረት ፡ ለማስረከብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መያዣ ፡

### (አንቀጽ ፡ ፫፻፪. )

ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ሰንጠረዥ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረት ፡ ለማቅረብና ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማስረከብ ፡ ተከሣሹ ፡ ለ. . .ብር ፡ መያዣ ፡ እንዲያስይዙ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ከሣሽ ፡ የሆኑት ፡ . .. ባቀረቡት ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሣሹን ፡ ስላዘዛቸው ።

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ . . . .በፈቃዴ ፡ ዋስ ፡ በመሆን ፡ እኒሁ ፡ ተከሣሽ ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ሰንጠረዥ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ግምቱን ፡ ወይም ፡ ከግምቱ ፡ ላይ ፡ ለተፈረደባቸው ፡ ሂሣብ ፡ የሚበቃውን ፡ ያህል ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ አቅርበው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ለማድረግ ፡ ራሴን ፡ ወራሾቼንና ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚዎቼን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ግዴታ ፡ አግብቻለሁ ። ይህንም ፡ ሳያደርጉ ፡ ቢቀሩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ . . . . .ብር ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚወስነውን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከተመለከተው ፡ በላይ ፡ ያልሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ ገንዘብ ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልከፍል ፡ ራሴን ፡ ወራሾቼንና ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚዎቼን ፡ ግዴታ ፡ አግብቻለሁ ።

ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡

በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ፊርማ ፡. . . .

ምስክሮች ፡ ፩ኛ. . . . . . . . . . . . . . . . .

፪ኛ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

## ቍጥር ፡ ፰.

### መያዣ ፡ ሳይሰጥ ፡ መቅረቱ ፡ በተረጋገጠ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያዝ ፡ ንብረት ፡

### (አንቀጽ ፡ ፫፻፪. )

ለ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚ ፡

በዚህ ፡ ክስ ፡ የተፈረደባቸው ፡ እንደሆነ ፡ ለፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ሂሣብ ፡ የሚበቃ ፡ መያዣ ፡ . . . .የተባሉት ፡ ተከሣሽ ፡ እንዲያስይዙ ፡ ይጠየቁ ፡ በማለት ፡ . . . .የተባሉት ፡ ከሣሽ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻ ፡ ስላቀረቡና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ይህንኑ ፡ መያዣ ፡ እንዲያስይዙ ፡ ተከሣሹን ፡ ጠይቋቸው ፡ ሳያስይዙ ፡ ስለቀሩ ፡ የተባሉት ፡ የ. . . .ንብረት ፡ የሆነውን ፡ . . . .ን ፡ እንዲይዙና ፡ ወደፊት ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ የሚያስተማምን ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ እየተጠ

በቀ ፡ እንዲቆይ ፡ እንዲያደርጉት ፡ ታዝዋል ። እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ የተፈጸመበትን ፡ ቀንና ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ምክንያቱን ፡ በመግለፅ ፡ ፈርመው ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ወይም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ መልሰው ፡ እንዲልኩት ፡ ታዞአል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. የተሳለፈ ።

. . . . . . . . . .ዳኛ ፡

## ቍጥር ፡ ፰.

## ጊዜያዊ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡

(አንቀጽ ፡ ፻፶፬. )

የከሣሹ ፡ የአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .ጠበቃ ፡ (ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ )ባሳሰበው ፡ መሠረት ፡ እንዲሁም ፡ ይኸው ፡ ከሣሽ ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ፋይል ፡ ከፍቶ ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ያቀረበውን ፡ አቤቱታ ፡ (ወይም ፡ በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም. ስለዚህ ፡ ክርክር ፡ ፋይል ፡ የተከፈተበትን ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ወይም ፡ በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. ፋይል ፡ የተከፈተበትን ፡ የከሣሹን ፡ ጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ) በመመልከትና ፡ ይህንኑ ፡ በመደገፍ ፡ . . . .እና ፡ . . . .የሰጡትን ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ በመስማት ፡ (ማስታወቂያ ፡ ተልኮለት ፡ ተከሣሹ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀርቶ ፡ እንደሆነና ፡ በዚሁ ፡ ማስታወቂያ ፡ መሠረት ፡ ማስታወቂያ ፡ ለተከሣሹ ፡ ለአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ፡ ስም ፡ ) . . . .ተሰጥቷል ፡ በማለት ፡ . . . .የሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ እንዳለ ፡ በመግለፅ ፡ )

ተከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ ). . . .፣ ሠራተኞቹ ፡ ወኪሎቹ ፡ ሙያተኞቹ ፡ በከሣሹ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ (ወይም ፡ በከሣሹ ፡ ጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ወይም ፡ አቤቱታና ፡ ስለዚህ ፡ ማሳሰቢያ ፡ በተሰማው ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ ) የተመለከተውን ፡ በ. . .ወረዳ ፡ በቍጥር ፡ . . .መንገድ ፡ የሚገኘውን ፡ ቤት ፡ እንዳያፈርስ ፡ ወይም ፡ እንዲፈርስ ፡ አድርጐ ፡ እንዳይጐዳው ፡ ቤቱ ፡ ተገጣጥሞ ፡ ከተሠራበት ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ እንዳይሸጥ ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ እስኪሰማ ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ ማገጃ ፡ እንዲደርሰው ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዟል ።

በ. . . .ቀን ፡ ፲፱. . . .ዓ.ም.

. . . . . . . . . . . .ዳኛ ፡

(በገንዘብ ፡ ክፍያ ፡ ወይም ፡ ሒሣብ ፡ ረገድ ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ስለተያዘ ፡ ንግግር ፡ የሚተላለፍ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሆን ፡ የትእዛዙ ፡ ክፍል ፡ አነጋገር ፡ እንደሚከተለው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። )

ላሁኑ ፡ ክርክር ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ በ. . . .ቀን ፡ . . . .ዓ.ም. ወይም ፡ ወደዚያው ፡ ገደማ ፡ የተጻፈውን ፡ በከሣሹ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ (ወይም ፡ አቤቱታ ፡ ) እና ፡ በዚሁ ፡ ክርክር ፡ ጊዜ ፡ በተሰማው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ የተመለከተውን ፡ ዕዳ ፡ መረጋገጫ ፡ ሰነድ ፡ (ወይም ፡ ሒሣብ ፡ መክፈያ ፡ ሰነድ ፡) ከእጃቸው ፡ እንዳያወጡት ፡ ወይም ፡ ከማንኛቸውም ፡ እጅ ፡ እንዳይወጣ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ እንዲከፈል ፡ እንዳይፈርሙበት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንዳያደርጉት ፡ ወይም ፡ የመዋዋያ ፡ ንግግር ፡ እንዳያደርጉበት ፡ . . .እና ፡ . . . .ለተባሉት ፡ ተከሣሾች ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ እስኪሰማ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወደፊት ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ ማገጃ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ታዟል ።

(ስለ ፡ ቅጅ ፡ መብት ፡ ለተነሱ ፡ ክርክሮች ፡ )

ይህ ፡ ክስ ፡ እስኪወሰን ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ . . . .የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ወይም ፡ ከውስጡ ፡ ማናቸውንም ፡ ክፍል ፡ ቢሆን ፡ እንዳያትሙ ፡ አሣትመው ፡ እንዳያወጡ ፡ ወይም ፡ እንዳይሸጡ ፡ ለተከሣሹ ፡ ለአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕረግ ፡ ስም ፡ )). . . .ለአገልጋዮቹ ፡ ለወኪሎቹ ፡ ወይም ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ማገጃ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ታዟል ።

(የሚታገደው ፡ ከመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ )

ተከሣሹ ፡ እሳትሞ ፡ አውጥቶታል ፡ ተብሎ ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ (ወይም ፡ አቤቱታና ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ )የተመለከተውን ፡ . . . . ከተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ . . . . የሚለውን ፡ (ከገጽ ፡ . . . መጀመሪያ ፡ እስከ ፡ ገጽ ፡ . . . . መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ) ክፍል ፤ ይህ ፡ ክስ ፡ እስኪወሰን ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ ተከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማኅበር ፡ ስም ፡ ) . . . አገልጋዮቹ ፡ (ወኪሎቹ ፡ ወይም ፡ ሠራተኞቹ ፡) እንዳያትሙ ፡ አሳትመው ፡ እንዳያወጡ ፤ እንዳይሸጡ ፡ ወይም ፡ ለምንም ፡ ጉዳይ ፡ እንዳያውሉት ፡ ማገጃ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ታዟል ።

(ስለ ፡ ፈልሳሚነት ፡ መብት ፡ ለተነሱ ፡ ክርክሮች ፡ )

ይህ ፡ ክስ ፡ እስኪ ፡ ወሰን ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪ ፡ ታዘዝ ፡ ድረስ ፡ በከሳሾቹ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ (ወይም ፡ አቤቱታና ፡ እሱንም ፡ በመሳሰለው ፡. . ..ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ በተሰጠው ፡ ቃልና ፡ እሱን ፡ በመሳሰለው ፡ ) በተመለከተው ፡ የከሳሾቹ ፡ ወይም ፡ ከከሣሾቹ ፡ የማገኛቸውም ፡ ሥራ ፡ በሆነው ፡ ዓይነት ፡ አፈለሳስም ፡ ባለቀዳዳ ፡ ጡቦችን ፡ (ሌላም ፡ ሥራ ፡ እንደሆን ፡ ዓይነቱ ፡ በመግለፅ ፡) በከሣሾቹ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ (ወይም ፡ በ. . . .) እንደተመለከተው ፡ ለፈልሳሚነት ፡ መብት ፡ ከተወሰነው ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የቀራቸው ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ሠርተው ፡ እንዳይሸጡና ፡ እነዚያኑ ፡ የፍልሰማ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ ማናቸውንም ፡ እንዳይገለብጡ ፡ ቅጅ ፡ እንዳያደርጉ ፡ ወይም ፡ አስመስለው ፡ እንዳይሠሩ ፤ ምንም ፡ ጭማሪ፥ ወይም ፡ ቅናሽ ፡ እንዳያደርጉ ፡ ማገጃ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ታዟል ።

(ስለ ፡ ንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ለተነሱ ፡ ክርክሮች ።)

በከሣሹ ፡ በአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕርግ ፡ ስም ፡) ... የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ (ወይም ፡ አቤቱታ ፡) ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያለውን ፡ ምልክት ፡ በጠርሙስ ፡ ላይ ፡ በመለጠፍ ፡ ከሣሹ ፡ የኔ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ካለት ፡ ምልክት ፡ ውስጥ ፡ ማናቸውንም ፡ ቅርፅ ፡ ወይም ፡ ቅብ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ቅርፁም ፡ ሆነ ፡ ቅቡ ፡ ከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕርግ ፡ ስም ፡) . . . የሸጠውን ፡ ቅርፅ ፡ ወይም ፡ ቅብ ፡ በቀለሙም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ አስመስሎ ፡ በመሥራት ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ እስኪወሰን ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ ተከሣሹ ፡ አቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕርግ ፡ ስም ፡) ... አገልጋዮቹ ፡ ወኪሎቹ ፡ ወይም ፡ ሠራተኞቹ ፡ እንዳይሸጡ ፤ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ ገበያ ፡ እንዳያወጡ ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፡ እንዳያከማቹ ፡ ማገጃ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ታዟል ።

(ሽሪክ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በሥራው ፡ ውስጥ ፡ በምንም ፡ አኳኋን ፡ ጣልቃ ፡ እንዳይገባ ፡ የሚተላለፍ ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ።)

ይህ ፡ ክስ ፡ እስኪወሰን ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወደፊት ፡ እስኪታዘዝ ፡ ድረስ ፡ በአቶ ፡ ... እና ፡ አቶ ፡ ... የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ ተከሣሹ ፡ አቶ ፡ ወይም ፡ በማዕርግ ፡ ስም ፡) ... ወኪሎቹና ፡ አገልጋዮቹ ፡ ማናቸውንም ፡ ውል ፡ እንዳይዋዋሉ ፤ ማናቸውንም ፡ የገንዘብ ፡ መዋዋያ ፡ ሰነድ ፤ ኖት ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ መያዣ ፡ እንዳይቀበሉ ፤ እንዳያዘጋጁ ፤ እንዳይፈርሙ ፡ ወይም ፡ የመዋዋያ ፡ ንግግር ፡ እንዳያደርጉና ፡ ማናቸውንም ፡ የዕዳ ፡ ግዴታ ፡ እንዳይዋዋሉ ፤ ማናቸውንም ፡ ዕቃ ፡ እንዳይገዙና ፡ እንዳይሸጡ ፡ እንዲሁም ፡ በአቶ ፡ (ወይም ፡ በማዕርግ ፡ ስም ፡) ... እና ፡ የሽር

ክና ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ የታልም ፡ ሆነ ፡ የጽሑፍ ፡ ተስፋ ፤ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ግዴታ ፡ እንዳያደርጉ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ እንዳያስደርጉ ፤ ወይም ፡ ይኸው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ማናቸውንም ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ባለዕዳ ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ውል ፤ ተስፋ ፤ ወይም ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ ባለግዴታ ፡ የሚሆንበትን ፡ እንዳያደርጉ ፡ ወይም ፡ እንዳያስደርጉ ፡ ማገጃ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ታዟል ።

## ቅጥር ፡ ፱ ፡

## ስለ ፡ ተረካቢ ፡ መሾም ። (አንቀጽ ፡ ፫፻፹፮ ።)

ለ..........................................................................................

እላይ ፡ በተመለከተው ፡ ክስ ፡ ለ... ለተፈረደለት ፡ ፍርድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ እንዲሆን ፡ ... እንዲያዝ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ትእዛዝ ፡ ስለተላለፈ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቂ ፡ አድርጐ ፡ የሚቀበለው ፡ መያዣ ፡ በማስያዝ ፡ በ፲፱... ዓ.ም. በወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፹፮ ፡ መሠረት ፡ የዚሁ ፡ ንብረት ፡ ተረካቢ ፡ ሆነው ፡ በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ ከተመለከተው ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ጋር ፡ ተሾመዋል ።

በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ረገድ ፡ ስለ ፡ ገቢያዎና ፡ ወጪዎ ፡ ተገቢውንና ፡ ትክክለኛውን ፡ ሂሣብ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. እንዲያቀርቡ ፡ ያሻል ።

በዚሁ ፡ ሹመትዎ ፡ መሠረት ፡ ንብረቱን ፡ ሲረከቡ ፡ ... በመቶ ፡ ይከፈልዎታል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

.....ዳኛ ።

## ቅጥር ፡ ፲ ፡

## ንብረት ፡ ተረካቢው ፡ የሚሰጠው ፡ የዕዳ ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነድ ። (አንቀጽ ፡ ፫፻፹፫ ።)

ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ... ወይም ፡ ለጊዜው ፡ በሥራው ፡ የእሱ ፡ ተተኪ ፡ ለሆነው ፡ ለሚከፈለው ፡ ... ብር ፡ እኛ ፡ ... እና ፡ ... ባንድነትና ፡ በነጠላ ፡ ግዴታ ፡ መግባታችንን ፡ እናረጋግጣለን ። በዚሁም ፡ መሠረት ፡ ይህንኑ ፡ ለመክፈል ፡ ራሳችንን ፡ እያንዳንዳችን ፤ ባንድነት ፡ የሁላችንንና ፡ የያንዳንዳችንን ፡ ወራሾች ፡ ጉዳይ ፡ ፈጻሚዎችና ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ባንድነትና ፡ በነጠላ ፡ ግዴታ ፡ አግብተናል ።

በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. .... በ... ላይ ፡ ... በማለት ፡ (የክሱ ፡ ዓይነት ፡ ይገለጽ ፡) በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ስላቀረበ ፡ እንዲሁም ፡ የ...ን. የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይና ፡ ትርፍ ፡ እንዲቀበል ፡ በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ... ተብሎ ፡ የተጠራውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ በእጁ ፡ እንዲያገባ ፡ ይኸው ፡ ... እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ስለተሾመ ።

ከማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በኪራይና ፡ በትርፍ ፡ ለሚቀበለው ፡ ለማናቸውም ፡ ገንዘብና ፡ በተንቀሳቃሹ ፡ ንብረት ፡ ረገድም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሂሣብ ፡ ያቀረበና ፡ ከዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ ላይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያዘውን ፡ ከወጪ ፡ ቀሪ ፡ ሂሣብ ፡ በየጊዜው ፡ የከፈለ ፡ እንደሆነ ፡ እላይ ፡ ስሙ ፡ የተጠቀሰው ፡ የንብረት ፡ ኃላፊ ፡ ከግዴታ ፡ ነፃ ፡ ሊሆን ፡ አለዚያ ፡ ግን ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ ገደብ ፡ ተደርጓል ። ... ባሉበት ፡ እላይ ፡ ስሙ ፡ የተጠቀሰው ፡ የንብረት ፡ ኃላፊ ፡ ፈርሞ ፡ ያስረከበው ፡ ሰነድ ።

ማ ስ ታ ወ ሻ ፤ የገንዘብ ፡ መያዣ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደሆነ ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ የመያዣው ፡ ግዴታ ፡ እንዲገለጽ ፡ ያስፈልጋል ።

## ሰንጠረዥ ፡ ፮ ።

### ቍጥር ፡ ፩ ።

### የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ። (አንቀጽ ፡ ፫፻፳፫)

… በቍጥር ፡ … … ዓ.ም. ለቀረበው ፡ ክስ ፡ በ… ቀን ፡ ፲፱… ዓ.ም. በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ … ይግባኝ ፡ እንዲታይለት ፡ እያመለከተ ፡ ይግባኝ ፡ ያቀረበበትንም ፡ ፍርድ ፡ የሚቃወምበትን ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይገልፃል ።

### ቍጥር ፡ ፪ ፡

### የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲተላለፍ ፡ የሚሰጥ ፡ ተያዥ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻)

ለ………………………………………………………………

ለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ማገጃ ፡ ተያዥ ፡ የሆነው ፡ … ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ግዴታ ፡ ፈርሟል ። … የተባለው ፡ ከሣሽ ፡ በቍጥር ፡ … ፲፱… ዓ.ም. …. የተባለውን ፡ ተከሣሽ ፡ በዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለከሰሰና ፡ በ… ፲፱… ለከሣሹ ፡ ስለተፈረደ ፡ ተከሣሹም ፡ የ… ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ብሎ ፡ ይግባኙ ፡ ገና ፡ ስላልተወሰነ ።

የተፈረደለት ፡ ከሣሽ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ አመልክቶ ፡ ሳለ ፡ ተከሣሹ ፡ ግን ፡ የፍርዱ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲታገድለት ፡ ማመልከቻ ፡ አቅርቦ ፡ መያዣ ፡ እንዲያስይዝ ፡ ተጠይቋል ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ እኔ ፡ … ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረቴን ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ በማስያዝ ፡ ለ… ብር ፡ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ ተያዥ ፡ መሆኔን ፡ ይህን ፡ ፍርድ ፡ የይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያጸናው ፡ ወይም ፡ የለወጠው ፡ እንደሆነ ፡ ይኸው ፡ ተከሣሽ ፡ የይግባኙን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በትክክል ፡ እንዲፈጸም ፡ በውሳኔው ፡ መሠረት ፡ የሚከፈለውን ፡ ሁሉ ፡ እንዲከፍል ፡ ይህን ፡ ሳያደርግ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በዚህ ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ከተያዘው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ እንዲከፈል ፡ ከዚሁ ፡ ንብረት ፡ ሺያጭ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ የተወሰነውን ፡ ሒሳብ ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ቀሪውን ፡ እኔና ፡ ሕጋዊ ፡ ወኪሎቼ ፡ ራሳችን ፡ ልንከፍል ፡ ባለዕዳ ፡ መሆኔን ፡ አረጋግጣለሁ ።

ይህንኑ ፡ የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ በ… ቀን ፡ ፲፱… ዓ.ም. ፈርሜአለሁ ።

ሰንጠረዥ ፡
(ፊርማ)

ምስክሮች ፡ ፩ኛ.
፪ኛ

### ቍጥር ፡ ፫ ።

### ጉዳዩ ፡ በይግባኝ ፡ ሳለ ፡ የሚሰጥ ፡ መያዣ ። (አንቀጽ ፡ ፬፻)

ለ………………………………………………………………

ለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ማገጃ ፡ ተያዥ ፡ የሆነው ፡ …. ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ የግዴታ ፡ ሰነድ ፡ ፈርሟል ። … የተባለው ፡ ከሣሽ ፡ በቍጥር ፡ … ፲፱…. ዓ.ም. ….. የተባለውን ፡ ተከሣሽ ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ከሰሰና ፡ በ… ቀን ፡ ፲፱… ዓ.ም. ለከሣሹ ፡ ስለ ፡ ተፈረደለት ፡ ተከሣሹ ፡ የ… ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ብሎ ፡ ይግባኙ ፡ ገና ፡ ስላልተወሰነ ።

የተፈረደለት ፡ ከሣሽ ፡ ፍርዱ ፡ እንዲፈጸምለት ፡ አመልክቶ ፡ መያዣ ፡ እንዲያስይዝ ፡ ተጠይቋል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ እኔ ፡ ... ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረቴን ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ በማስያዝ ፡ ለ... ብር ፡ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ ተያዥ ፡ መሆኔን ፡ ይህንም ፡ ፍርድ ፡ የይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የገለበጠው ፡ ወይም ፡ የለወጠው ፡ እንደሆነ ፡ በፍርዱ ፡ መሠረት ፡ ተወስዶ ፡ የነበረውን ፡ ማናቸውንም ፡ ንብረት ፡ ከሣሹ ፡ እንዲመልስና ፡ የይግባኙን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሣኔ ፡ በትክክል ፡ እንዲፈጸም ፡ በይግባኙም ፡ ውሣኔ ፡ መሠረት ፡ የሚከፈለውን ፡ ሁሉ ፡ እንዲከፍል ፡ ይህን ፡ ሳያደርግ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በዚሁ ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ከተያዘው ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈል ፤ ከዚሁ ፡ ንብረት ፡ ሺያጭ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ የተወሰነውን ፡ ሂሣብ ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ እኔና ፡ ሕጋዊ ፡ ወኪሎቼ ፡ ራሳችን ፡ ልንከፍል ፡ ባለዕዳ ፡ መሆኔን ፡ አረጋግጣለሁ ።

ይህንኑ ፡ የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ፈርሜአለሁ ።

ፊርማ ፡...

ምስክሮች ፡ ፩ኛ.
፪ኛ.

<u>ቍጥር ፡ ፱ ፡</u>

<u>ለይግባኝ ፡ ወጪ ፡ የሚሰጥ ፡ መያዣ ። (አንቀጽ ፡ ፮፻፫)</u>

ለ.............................................................................................

ለይግባኝ ፡ ወጪ ፡ ተያዥ ፡ የሆነው ፡ ... ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ የግዴታ ፡ ሰነድ ፡ ፈርሟል ። ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በቍጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. ክስ ፡ ቀርቦ ፡ ስለ ፡ ተፈረደው ፡ ፍርድ ፡ በመልስ ፡ ሰጪው ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ስላቀረበ ፡ መያዣ ፡ እንዲያስይዝ ፡ ተጠይቋል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ እኔ ፡ ... ፤ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ንብረቴን ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ በማስያዝ ፡ ለይግባኙ ፡ ወጪ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ ተያዥ ፡ ሆኛለሁ ።

ይህን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ክሱ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ አላዛውርም ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ የሚገባውን ፡ ሳይፈጽም ፡ ቢቀር ፡ ስለ ፡ ይግባኙ ፡ ወጪ ፡ ክፍያ ፡ የሚተላለፍብኝን ፡ ማናቸውንም ፡ ትእዛዝ ፡ እፈጽማለሁ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚከፈለው ፡ ማናቸውም ፡ ገንዘብ ፡ በዚሁ ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ከተያዘው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ይከፈላል ። ከዚሁ ፡ ንብረት ፡ ሺያጭ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ የተወሰነውን ፡ ሂሣብ ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ እኔና ፡ ሕጋዊ ፡ ወኪሎቼ ፡ ራሣችን ፡ ልንከፍል ፡ ባለዕዳ ፡ መሆኔን ፡ አረጋግጣለሁ ።

ይህንኑ ፡ የተያዥነት ፡ ግዴታ ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. ፈርሜአለሁ ።

ሰ ን ጠ ረ ዥ ፡

ፊርማ ፡...

ምስክሮች ፡ ፩ኛ.
፪ኛ

## ቅጥር ፡ ፭ ፡

### ይግባኝ ፡ መቅረቡን ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያውቀው ፡ ለማድረግ ።
### (አንቀጽ ፡ ፩፻፭)

ለ.................................................................

እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ... የሆኑት ፡ ... በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በፈረዳችሁት ፡ ፍርድ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ያቀረቡ ፡ መሆናቸውን ፡ እናስታውቃለን ። ለክሱ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ወረቀቶች ፡ ሁሉ ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ እንድትልኩ ፡ ትጠየቃላችሁ ።

በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም.

....ዳኛ ።

## ቅጥር ፡ ፮ ፡

### ይግባኙ ፡ እንዲሰማ ፡ የተወሰነውን ፡ ቀን ፡ ለማስታወቅ ፡ ለመልስ ፡ ሰጪ ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ። (አንቀጽ ፡ ፩፻፮)

በ.... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም.

የ... ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ ... ላይ ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ።

ለ.............................................................

በዚህ ፡ ክስ ፡ የ... በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ... ይግባኝ ፡ ማቅረቡንና ፡ ይግባኙ ፡ እዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መመዝገቡን ፡ እንዲሁም ፡ ይግባኙ ፡ የሚሰማው ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. እንዲሆን ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መወሰኑን ፡ እናስታውቃለን ።

ራስዎ ፡ ሳይቀርቡ ፡ ቢቀሩ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅዎ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ይግባኝ ፡ እንዲነጋገርልዎ ፡ በሕግ ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ ሳይቀርብ ፡ ቢቀር ፡ በሌሉበት ፡ ተሰምቶ ፡ ይወሰናል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

....ዳኛ ።

ማ ስ ታ ወ ሻ ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲታገድ ፡ ታዞ ፡ እንደሆነ ፡ ነገሩ ፡ በዚሁ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲገለፅ ፡ ያስፈልጋል ።

## ቅጥር ፡ ፯ ፡

### ለክሱ ፡ ተከራካሪ ፡ ለነበረና ፡ በይግባኙ ፡ ግን ፡ ተከራካሪ ፡ ላይሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመልስ ፡ ሰጪነት ፡ አባሪ ፡ እንዲሆን ፡ ላደረገው ፡ ወገን ፡ የሚላክ ፡ ማስታወቂያ ። (አንቀጽ ፡ ፩፻፲፱)

ለ..........................................................

በቍጥር ፡ ... ፲፱... ዓ.ም. ለ... ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበው ፡ ክስ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ስለ ፡ ነበራችሁና ፡ በዚያ ፡ ክስ ፡ ስለተፈረደበት ፡ ፍርድ ፡ ... ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አቅርቦ ፡ የይግባኙ ፡ ውጤት ፡ የሚያገባችሁ ፡ ሆኖ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለታየው ፤

በዚሁ ፡ ይግባኝ ፡ መልስ ፡ ሰጪዎች ። እንድትሆኑ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያዘዛችሁ ፡ መሆኑንና ፡ ይግባኙ ፡ የሚሰማበትንም ፡ ቀን ፡ ለ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. በ... ሰዓት ፡ ያስተላለፈው ፡ መሆኑን ፡ እናስታውቃለን ።

በዚያው ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ በናንተ ፡ በኩል ፡ ሰው ፡ ሳይቀርብ ፡ ቢቀር ፡ ይግባኙ ፡ በሌላችሁበት ፡ ተሰምቶ ፡ ይወሰናል ።

በኔ ፡ ፊርማና ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅተም ፡ በ... ቀን ፡ ፲፱... ዓ.ም. የተላለፈ ።

....ዳኛ ።